
በአዲስ ሥርዓት የተሰናዳ ።

ያማርኛ ሰዋስው ።



ከብላታ መርሐዊ ጎዘን ወልደ ቂርቆስ ፡
ተጻፈ ።

የመጀመሪያው ፈቂቅ በ፲፱፻፲፱ ዓ ም ተጻፈ ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፺፰ ዓ ም ።

በክርስቲያን ማተሚያ ቤት ታተመ ። 4192

ያለባለቤቱ ፈቃድ ሙሉ ፣ ማተም ፣ ወይም ፣ መቅዳት ፣ ከልክሏል ፣ ነው ።
ALL RIGHTS RESERVED

መጀመሪያ ፣ ጊዜ ፣ በ፲፱፻፹፭ ፣ ዓ ፣ ም ፣ በብርሃንና ፣ ሰላም ፣ ማተሚያ ፣ ቤት ፣ ታተመ ።
ሁለተኛ ፣ ጊዜ ፣ በ፲፱፻፹፯ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ሶንደን ፣ ላይ ፣ ታተመ ።
ሶስተኛ ፣ ጊዜ ፣ በ፲፱፻፹፰ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ሶንደን ፣ ላይ ፣ ታተመ ።
አራተኛ ፣ ጊዜ ፣ በ፲፱፻፺፫ ፣ ዓ ፣ ም ፣ በአርቲስቲክ ፣ ማተሚያ ፣ ቤት ፣ ታተመ ።

መ ቅ ድ ም ።

ይህን ፣ ሰዋስው ፣ ለመጻፍ ፣ ያሰብሁበት ፣ ምክንያት ፣ የሚከተለው ፣ ነው ። በ፲፱፻፲፯ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ሚያዝያ ፣ ፲፱ ፣ ቀን ፣ የተፈሬ ፣ መኰንን ፣ ተማሪ ፣ ቤት ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ ላይ ፣ መጀመሪያ ፣ ሲከፈት ፣ እኔ ፣ በግዕዝና ፣ በአማርኛ ፣ አስተማሪ ፣ ነበርሁ ።

በተማሪ ፣ ቤቱ ፣ ደንብ ፣ የተወሰነውም ፣ የትምህርት ፣ ዓይነት ፣ እንግሊዝኛ ፤ ፈረንሳዊኛ ፤ ግዕዝና ፣ አማርኛ ፣ ደግሞ ፣ ሥዕል ፤ ጅምናስቲክ ፤ ሌላም ፣ ተግባረ ፣ እድ ፣ (እና ጤንትና ፣ ሽግኔት ፣ . . .) ነበር ። ስእንግሊዝኛውና ፣ ለፈረንሳዊኛው ፣ ትምህርት ፣ አስፈላጊ ፣ የሆነው ፣ መጽሐፍ ፣ ሁሉ ፣ በደረጃ ፣ በደረጃው ፣ ተሰናድቶ ፣ ቀረበ ። ለሥዕልና ፣ ለሌላውም ፣ ተግባረ ፣ እድ ፣ እንደዚሁ ፣ የሚያሻው ፣ መሣሪያ ፣ ተዘጋጅቶ ፣ ነበር ። ስለ ፣ ግዕዝና ፣ ስለ ፣ አማርኛ ፣ ትምህርት ፣ ግን ፣ የተሰበሰበት ፣ መጻሕፍት ፣ አብዛኞቹ ፣ በጣም ፣ ታላላቅ ፣ የሆኑ ፣ የንባብና ፣ የትርጓሜ ፣ መጻሕፍት ፣ ነበሩ ። የቀሩትም ፤ ወንጌላውያን ፣ መምህራን ፣ ያሰተሙአቸው ፣ አንዳንድ ፣ የግዕዝ ፣ ወይም ፣ የአማርኛ ፣ መጻሕፍት ፣ ነበሩ ።

እንደ ፣ ተማሪ ፣ ቤቱ ፣ ደንብ ፣ ግዕዙንና ፣ አማርኛውን ፣ በተወሰነው ፣ ሰዓት ፣ ማስ ተማር ፣ ጀመርሁ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ የማስተምርባቸው ፣ መጻሕፍት ፣ እንደ ፣ ሌላው ፣ ትምህርት ፣ በረድፍ ፣ በረድፉ ፣ ሆነው ፣ አልተሠሩምና ፣ ትምህርቱ ፣ ለልጆች ፣ ከበድ ፣ ይሆን ባቸው ፣ ነበር ።

የትምህርቱ ፣ ሥራ ፣ በትጋት ፣ ይከሄድ ፣ ጀመር ። ተማሪዎቹም ፣ ለእንግሊዝኛውና ፣ ለፈረንሳዊኛው ፣ ትምህርት ፣ ከሌላው ፣ ሁሉ ፣ ይልቅ ፣ ይጣጣሩለት ፣ ነበር ። የተማሪ ፣ ቤቱ ፣ ሹም ፣ ክቡር ፣ ሐኪም ፣ ወርቅነህ ፣ (አሁን ፣ አዘዥ ፣ ወርቅነህ ፣) «ልጆቻችን ፣ በአገራችን ፣ ትምህርት ፣ በግዕዝና ፣ በአማርኛ ፣ አስቀድሞ ፣ እንዲሠጥ ፣ ያስፈልጋል ፣» እያሉ ፣ በየጊዜው ፣ ያስገነዝቡኝ ፣ ነበር ። እኔም ፣ ትምህርቱን ፣ በቀላሉ ፣ ለማስጠናት ፣ ስል ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ስልት ፣ እያሰናዳውና ፣ በጥቁር ፣ ሰሌዳ ፣ ላይ ፣ እየጻፍሁ ፣ አስተምር ፣ ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ፣ እንደ ፣ አዲሱ ፣ ዘመን ፣ ትምህርት ፤ ደረጃ ፣ በደረጃ ፣ ሆኖ ፣ የተሠራ ፣ የአማርኛ ፣ መጽሐፍ ፣ ስላልነበረ ፣ ተማሪዎቹ ፣ ወደ ፣ ትምህርቱ ፣ የማያዘነብሉ ፣ ሆኑ ። እንዲያውም ፣ እንደመሰልቸት ፣ አሉትና ፣ በአማርኛው ፣ ሰዓት ፣ ሌላውን ፣ ትምህርታቸውን ፣ ለመቀጸል ፣ ይከጅሉ ፣ ነበር ።

ይህን ፣ ሁሉ ፣ ከተመለከትሁ ፣ በኋላ ፣ አማርኛን ፣ ከማስተማር ፣ አስቀድሞ ፣ ማስ ተማሪያውን ፣ ማሰናዳት ፣ አስፈላጊ ፣ እንደሆነ ፣ ተረዳሁ ። አሠራሩም ፣ በአዲሱ ፣ ዘመን ፣

ትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ እንደሚሻል ፡ ተመለከትሁ ። ለጊዜው ፡ ትምህርት ፡ ሕፃናት ፡ የምትባል ፡ ትንሽ ፡ የማንበቢያ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፌ ፡ አሳተምሁ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የአማርኛን ፡ ሰዋስው ፡ ለመጻፍ ፡ አሰብሁ ። ስለዚህም ፡ የአዲሱን ፡ ዘመን ፡ የትምህርት ፡ አካሄድ ፡ ለማወቅ ፡ ስል ፡ በትርፍ ፡ ጊዜያቴ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ለመማር ፡ አጣጣር ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ከአስተማሪዎችም ፡ ከተማሪዎችም ፡ መልክም ፡ እርዳታን ፡ አግኝቼ ፡ ነበር ።

፩ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቁይቼ ፡ የአማርኛውን ፡ ሰዋስው ፡ ለመጻፍ ፡ ጀመርሁ ፡ በእጻ ጽፉም ፡ የቋንቋው ፡ ኃይል ፡ እስከፈቀደልኝ ፡ ድረስ ፡ የአዲሱን ፡ ዘመን ፡ ትምህርት ፡ አክ ሂድ ፡ ለመከተል ፡ ተጣጣርሁ ። ጻፉ ፡ ግን ፡ ቋንቋ ፡ ለራሱ ፡ ነፃነት ፡ አለው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የአከፋፈልንና ፡ የአካሄድን ፡ ምሳሌ ፡ ከሌላ ፡ ብንከተል ፤ አማርኛ ፡ ለራሱ ፡ ሌላ ፡ ውሳኔ ፤ ድንጋጌ ፤ ብያኔ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሆነ ። ስለዚህም ፡ የቋንቋውን ፡ ባሕርይ ፡ በመመርመር ፡ አማርኛውን ፡ ከግዕዙ ፡ ጋር ፡ በማስማማት ፡ ተጽፎ ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ አለቀ ። ወዲያው ፡ በጥቂት ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እየተጻፈ ፡ ተማሪዎች ፡ ይማሩበት ፡ ጀመር ። አካሄዱ ፡ ከአዲሱ ፡ ዘመን ፡ የሰዋስው ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ ስለተመሳሰለ ፡ በተማሪ ዎችም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ሆነ ። ያ ፡ ሁሉ ፡ መሰልቸት ፡ ቀረና ፡ ተማሪዎቹ ፡ እንሰን ፡ ጨምርልን ፡ እያሉ ፡ ፋታ ፡ የማይሰጡኝ ፡ ሆነ ። በየቀኑ ፡ የምሰጣቸውን ፡ የሰዋስው ፡ ትም ህርት ፡ ተማሪዎቹ ፡ በማጥኛ ፡ ደብተራቸው ፡ ላይ ፡ እየጻፉ ፡ እንደመጽሐፍ ፡ አድርገው ፡ ይጠቀሱት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሰዋስዉ ፡ ከየሣ ፡ በሚበልጡ ፡ ተማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጅምሩን ፡ ሰዋስው ፡ ለክቡር ፡ አዛዥ ፡ ወርቅነህ ፡ አሳየኋቸው ። ቁጥሎም ፡ በጠሩ ፡ ቋንቋ ፡ የሚነገረው ፡ የመጀመሪያው ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እማ ርኛ ፡ ቢተረጐም ፡ ኖሮ ፡ ትምህርትን ፡ ለማፋጠን ፡ ብረዳ ፡ ነበር ፡ ብዬ ፡ ምኞቴን ፡ ገለጥሁ ላቸው ። እሳቸውም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ሲያስቡበት ፡ ቁይተው ፡ ኖሮ ፡ ከሣ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ያስተረጐሙዋቸውን ፡ አንድ ፡ የቁዋር ፡ መጽሐፍና ፡ አንድ ፡ የዓለም ፡ ጅዮግራፊ ፡ አሳዩኝ ። እኔም ፡ ጅዮግራፊውን ፡ ተመልክቼ ፡ በቶሎ ፡ ታትሞ ፡ ማስተማሪያ ፡ እንዲሆን ፡ ወተወት ኋቸው ። ጻፉ ፡ ግን ፡ በትልቁ ፡ ጠርነት ፡ ምክንያት ፡ ጅዮግራፊው ፡ ተለመጠ ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡ ግና ፡ ለማረም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጅዮግራፊውን ፡ አዛዥ ፡ ወርቅነህ ፡ ሲያርሙ ፡ እኔም ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ መለየት ፡ በሥራው ፡ እረዳቸው ፡ ነበርና ፡ ጅዮግራፊ ውን ፡ ለማጥናት ፡ የተመቸ ፡ ጊዜ ፡ ሆነልኝ ። የማረሙ ፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ጅዮ ግራፊው ፡ ታትሞ ፡ በ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወጣ ።

እኔም ፡ የጀመርሁትን ፡ ሰዋስው ፡ ወዲያው ፡ ለማሳተም ፡ ምኞት ፡ ነበረኝ ፤ ጻፉ ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ ባይፈቅድ ፡ ቁየ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጻፍሁት ፡ ሰዋስው ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ሲኖር ፡ ጠላት ፡ በወረረን ፡ ጊዜ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተዘረፈብኝ ። በዚህ ፡ እያዘንሁ ፡ ስኖር ፡ አቦሴ ፡ ጻፈራ ፡ የሚባል ፡ ቀድሞ ፡ በተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ይማር ፡ የነበረ ፡ ልጅ ፡ በዚ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጽርት ፡ የነበረውን ፡ አንድ ፡ ግልባጭ ፡ አገኘልኝና ፡ በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰጠኝ ። በዚህም ፡ አቶ ፡ አቦሴን ፡ አመሰግነዋለሁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቀድሞውን ፡ መሠ ረት ፡ አድርጌ ፡ እንደገና ፡ እያረምሁ ፡ ጻፍሁት ።

ይህን ፡ ሰዋስዌን ፡ ስለ ፡ «ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ » መታሰቢያ ፡ ጽፈዋ ለሁ ። ሥራውን ፡ ወደፍጻሜ ፡ ለማድረስና ፡ ለማሳተም ፡ የረዱኝን ፡ የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታን ፡ አመሰግናቸዋለሁ ። ዳግም ፡ በሥራ ላገዙኝ ፡ ወዳጆቼ ፡ ሁሉ ፡ ምስጋናን ፡ አቀርባለሁ ።

ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ።

መግቢያ ።

ይህን ፡ ሰዋስው ፡ ስሚመለከቱ ፡ ሰዎችና ፡ ለአስተማሪዎች ፡ ግልጥ ፡ እንድ ትሆን ፡ ይህችን ፡ መግቢያ ፡ አጽፋለሁ ።

የሰዋስው ፡ አከፋፈል ።

ሰዋስው ፡ በሄ ፡ ታላላቅ ፡ ክፍሎች ፡ ተከፍሎ ፡ ያመኦህል ። መጀመሪያው ፡ «የን ግግር ፡ ክፍል ፤ » ይኖው ፡ «አገባብ ፡ » ይባላል ።

መጀመሪያው ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ።

«የንግግር ፡ ክፍል ፡ » የተባለው ፡ መጀመሪያው ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ከር ፡ ላይ ፡ ተከ ፍሎ ፡ የቃላትን ፡ ንብረት ፡ ኢያዩራይ ፡ ይመድባል ።

ስምንቱ ፡ ክፍሎች ፡ «ስም ፤ — ተውላጠ ፡ ስም ፤ — ቅጽል ፡ ግሥ ፤ — ተውሳክ ፡ ግሥ ፤ — መስተዋድድ ፤ — መስተያምር ፤ — ቃለ ፡ አጋኖ ፤ » ተብለው ፡ በአዲስ ፡ ሠዓሊ ፡ ተመድበዋል ። ከነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ በፊኖው ፡ እንኳ ፡ የማይገኝ ፡ ቃል ፡ እንዳይኖር ፡ ዘሥርዓት ፡ ተደንግጎ አል ። «ግሥ ፤ ቅጽል ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፤ » የተባሉት ፡ በግዕዝ ፡ ሰዋስው ፡ ያለውን ፡ ስግጭ ውን ፡ እንዲያዙ ፡ ንብተዋል ። «ንባር ፤ ዘር ፤ » ይባሉ ፡ የነበሩት ፡ አሁን ፡ «ስም ፡ » ተብለው ፡ ተሰይመዋል ። የቀሩት ፡ አራቱ ፡ ክፍሎች ፡ ግን ፡ በአዲስ ፡ ስያሜ ፡ የተጻፉ ፡ ናቸው ።

«ተውላጠ ፡ ስም ፡ » የተባለው ፡ በግዕዝ ፡ ሰዋስው ፡ «አጸሩ ፡ ገዘገዘር ፤ » ተብሎ ፡ በአርብ ፡ ቅምርና ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ በደቂቅ ፡ እርባታ ፡ በሉላም ፡ ክፍል ፡ የሚገኘውና ፡ እርሱን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ። በግዕዙ ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ። አሁን ፡ ግን ፡ ቃላት ፡ በየወገናቸው ፡ እንዲጠቀለሉ ፡ ስለተፈለገ ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ያክፍል ፡ ሆኖአል ። — «ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ » የተባለው ፡ በግዕዝ ፡ ሰዋስው ፡ አብዛኛው ፡ በንኡስ ፡ አገባብና ፡ በተረፈ ፡ ግሥ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ። «መስተዋድድ ፡ » የተባለው ፡ በግዕዙ ፡ ሰዋስው ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ከተባለው ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ ነው ። «መስተያምር ፡ » የተባለውም ፡ በግዕዙ ፡ ሰዋስው ፡ ዐቢይ ፡ አገባብን ፡ ይመስላል ።

በግዕዙ ፡ ሰዋስው ፡ የተለመዳት ፡ ክፍሎች ፡ (ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡) በዚያው ፡ በቀድሞው ፡ ስማቸው ፡ ጸንተው ፡ ዓ፡ማርኛ ፡ ሰዋስዋችን ፡ እንዲገቡ ፡ ታስቦበት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከአዲሱ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ አ ዘዛኛው ፡ የማይገ ጣጠም ፡ ሆነና ፡ ተትቷል ። ስለምን ፡ ማለት ፤ በአገባብ ፡ ው ስጥ ፡ ከሁን ፡ ና ነግግር ፡ ክፍ ሎች ፡ የምንላቸው ፡ ዘንቅ ፡ ሆነው ፡ በአንድነት ፡ ተነግረሚ ፡ አ በ ሁን ፡ በየመደብ ቸው ፡ መለየት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ።

«አገባብ ፡ » የተባለው ፡ ፪ኛው ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ታላቅ ፡ በወረፍተ ፡ ነገር ፡ አለ ተገቱ ፡ በተነገሩ ፡ ጊዜ ፡ የቃላት ፡ አሰካክ ፡ የሚደራጅበት ፡ ነው ። በመሆ ፡ ሙሪ

ያው ፡ ክፍል ፡ ከተነገሩት ፡ ከፎቱ ፡ ክፍሎች ፡ እየተጠቀሰ ፡ ትርጓሜያቸውና ፡ ሥርዓታ
ቸው ፤ በወረፍተ ፡ ነገርም ፡ እንዴት ፡ እንደሚሰኩ ፡ ይነገርበታል ። አገባቡ ፡ በዚህ ፡ በአ
ሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ በሙሉ ፡ ሆኖ ፡ አልተፈጸመም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ወደፊት ፡ አገባቡ ፡
በሰፊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲወጣ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

ስለማጥበቅና ፡ ስለማላላት ።

ከቃላት ፡ ውስጥ ፡ ጽሕፈቱ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሰለ ፡ በመጥበቅና ፡ በመላላት ፡ ድምፅ ፡
የሚለይ ፡ ነገር ፡ አለ ።

ምሳሌ ፤ አስተማሪው ፡ ተማር ፡ አለኝ ፤ (አላላ ፡)

እኔ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አለኝ ፤ (አጥብቅ ፡)

እነሆ ፡ በመጀመሪያው ፡ ምሳሌ ፡ የተጻፈው ፡ «አለኝ ፡» ሳልቶ ፡ ይነበብና ፡ የመና
ገርን ፡ ምግባር ፡ ያመለክታል ። በዳኛው ፡ ምሳሌ ፡ የተጻፈው ፡ «አለኝ ፡» ጠብቆ ፡ ይነበ
ብና ፡ የመኖርን ፡ ወይም ፡ የማግኘትን ፡ ምግባር ፡ ያመለክታል ። ይሁን ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡
በጣም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለመወሰን ፡ አስበን ፡ በፊደሉ ፡ ራስጌ ፡ የሚጥበቂያ ፡ ምል
ክት ፡ (ይዘት ፡) አድርገን ፡ ነበር ። ጸሩ ፡ ግን ፡ የፊደሉ ፡ ቅርጽ ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ በማተሚያ ፡
ቤት ፡ ስለሌለ ፤ አዲስ ፡ ለማስቀረጽም ፡ ጊዜው ፡ ስላልፈቀደ ፡ ቀርቷል ። ስለዚህም ፡ አስ
ተማሪዎች ፤ የሚጠብቁውንና ፡ የሚላላውን ፡ ቃል ፡ ለይቶ ፡ ለማስረዳት ፡ ማስተዋልና ፡
መመርመር ፡ አለባቸው ።

ስለቃላት ፡ ውሳኔ ።

የአ ፡ ፊደል ፤ የተከተለውን ፡ ቃል ፡ አናግር ፡ ራሱ ፡ ተውጦ ፡ እንደሚጠፋ ፡ በሰ
ዋስው ፡ ውስጥ ፡ በየስፍራው ፡ ተነግሮአል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሥረ ፡ ቀለሙ ፡ እየጠፋ ፡
የቃላት ፡ ውሳኔ ፡ ከመፋለስ ፡ ይደርሳል ፤ ስለ ፡ አ ፡ ፊደል ፡ በየስፍራው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሳ
ኔን ፡ ማድረግ ፡ ባላስቸገረም ፡ ነበር ። ጸሩ ፡ ግን ፡ የውሳኔ ፡ ብዛት ፡ ለተማሪ ፡ ብርቱ ፡ ሸክም ፡
ይሆንበታል ።

የተለመደውን ፡ ንግግር ፡ በዚያው ፡ በልማዱ ፡ ብቻ ፡ ለመወሰን ፤ ወይም ፡ አሻ
ሽሎ ፡ ለመወሰን ፡ ከሊቃውንት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳብ ፡ ተሰምቶአል ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡
ከሊቅ ፡ የሚገኝ ፡ አሳብ ፡ በለማስረጃና ፡ ባለምክንያት ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉም ፡ በየክፍሉ ፡ የተ
መሰገነ ፡ ነው ። ጸሩ ፡ ግን ፡ ብዙዎቹን ፡ አሳቦች ፡ መርምሮ ፡ ጉብኤ ፡ ሊቃውንት ፡ በብያኔ ፡
ሊወስነው ፡ የሚገባ ፡ ነው ።

የደራሲው ፡ ምኞት ፤ ቃላት ፡ ሥረ ፡ ነገራቸውን ፡ ሳያፋልሱ ፡ እንዲጸፉ ፡ ነው ።
ይኸውም ፡ «ያንብን ፡ መጽሐፍ ፡ ወስጃለሁ ፡» በማለት ፡ ፈንታ ፡ «የአንብን ፡ መጽሐፍ ፡
ወስጄአለሁ ፡» እንዲባል ፡ ማለት ፡ ነው ። ጸሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሚጸናው ፡ ጉባኤ ፡
ሊቃውንት ፡ የሚስማማበት ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ስለሆነ ፤ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ በሁለቱ ፡ ዓይነት ፡
ቢጻፍ ፡ ከጸያፍነት ፡ ሊቈጥረው ፡ የሚችል ፡ የለም ።

የፊደላት ፡ ተራ ።

ይህ ፡ ሰዋስው ፡ የተጻፈው ፡ ተለምዶ ፡ በቈየው ፡ « ሀ ለ ሐ መ » በሚለው ፡
የፊደል ፡ ተራ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ « አ በ ገ ደ » በሚል ፡ ተራ ፡ እንዲነገር ፡ አሳብቸ
ውን ፡ ያቀረቡ ፡ ሊቃውንት ፡ አሉ ። ይኸውም ፡ « አ በ ገ ደ » የፊደል ፡ ጥንታዊ ፡
መደቡ ፡ ስለሆነ ፡ የተወደደና ፡ የተመሰገነ ፡ አሳብ ፡ ነው ። ስለ ፡ ፊደላት ፡ ሥርዓት ፡ ከደራ
ሲው ፡ የተጀመረ ፡ ጽሕፈት ፡ ነበረ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ በአሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጨ
መር ፡ ስላልደረሰ ፡ ቈይቶአል ።

ዜሰ ፡ ፊደላት ፡ ሥርዓት ፡ ሲቁ ፡ አስታ ፡ ኪላን ፡ ወልድ ፡ ከፍሌ ፡ የጻፉትን ፡ መጽሐፍ ፡ መመልከት ፡ አስ
ፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ለአስተማሪዎች ፡ እናሰገንዝባለን ።

ሰዋስውን ፡ ለመጻፍ ፡ የተመረጠው ፡ ንግግር ።

ይህ ፡ ሰዋስው ፡ የተጻፈው ፤ ከመምህራንና ፡ ከሊቃውንት ፡ እንደበት ፡ ከሚሰማው ፡
ንግግር ፡ በአብዛኛው ፡ ስፍራ ፡ የተለመደውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ። በልዩ ፡
ውሳኔ ፡ ከልሆነ ፡ በቀር ፡ ያልተማሩ ፡ ባላገሮች ፡ የሚናገሩበትን ፡ ቋንቋ ፡ መደበኛ ፡ አላደ
ረግነውም ። እነሆ ፡ በያገሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቃል ፡ ይሰማል ።

ያንድ ፡ አገር ፡ ባላገሮች ፡ "ገብረ ፡ መድከን ፡ ሚሃኤል" እያሉ ፡ ሲናገሩ ፡ የዚያው ፡
አገር ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑት ፡ ሊቃውንቱ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ ሚካኤል ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡
እንደ ፡ ባላገሮቹ ፡ አይናገሩም ። በሌላው ፡ ሀገር ፡ ደግሞ ፡ ባላገሮቹ ፡ "ጥጭትወረጨት ፡"
እያሉ ፡ ሲናገሩ ፤ የዚያው ፡ ሀገር ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑት ፡ ምሁራኑ ፡ "ጥቂት ፡ ወረቀት ፡"
ቢሉ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ባላገሮቹ ፡ አይናገሩም ። በየሌላውም ፡ ወረዳ ፡ ያልተማሩ ፡ ጨዎች ፡
የሚናገሩበት ፡ አንዳንድ ፡ የልማድ ፡ ቋንቋ ፡ መናሩ ፡ የተረገጠ ፡ ነው ። አሁን ፡ የያገሩን ፡
ጸያፍ ፡ ለመልቀም ፡ አስፈላጊ ፡ ስላልሆነ ፤ ትተነዋል ። ስለዚህም ፡ ለዚህ ፡ ሰዋስው ፡ የተ
መረጠው ፡ ቋንቋ ፡ (በልዩ ፡ ውሳኔ ፡ ከተመደበው ፡ በቀር ፡) በሊቃውንት ፡ አንደበት ፡
የተለመደው ፡ ንግግር ፡ ነው ።

ፊደላትን ፡ ስለማሻሻል ።

ፊደል ፡ የቋንቋ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ። መሣሪያ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲሻሻል ፡ እንዲሰል ፡
እንዲሰነገል ፤ ፊደልም ፡ እንደዚሁ ፡ ተሻሽሎ ፡ ሊታደስ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ። የአማር
ኛን ፡ ፊደል ፡ ለማሻሻል ፡ ከብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳቦች ፡ ቀርበዋል ። የሁሉም ፡
አሳብ ፡ በአናጋሪ ፡ ፊደል ፡ (በዋየል) ይነገር ፡ በማለት ፡ የተባበረ ፡ ሆኖአል ።

(ሀ) መደቡ ፡ ግዕዝ ፡ ወይም ፡ ሳድስ ፡ ሆኖ ፡ በአ ፡ ፊደል ፡ አናጋሪነት ፡ እንዲነ
በብ ፡ አሳብ ፡ ያቀረቡ ፡ አሉ ። ደግሞ ፡ በአ ፡ ፊደልና ፡ በተመደቡ ፡ በሌሎች ፡ ፊደላት ፡
አናጋሪነት ፡ እንዲነበብ ፡ የወሰኑ ፡ አሉ ። የሁሉም ፡ አሳብ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ። ይኸውም ፡
ሲሆን ፡ የፊደላቱ ፡ ቅርጽ ፡ «ሀ ፡ ለ ፡ ሐ ፡ መ ፡» ወይም ፡ አ ፡ በ ፡ ገ ፡ ደ ፡ በሚለው ፡ ቅርጽ ፡
እንዲጸና ፡ ወስነዋል ።

(ለ) በአናጋሪ ፣ ፊደል ፣ እንዲነበብ ፣ አስፈላጊ ፣ ከሆነ ፣ ፊደሉም ፣ በአዲስ ፣ ሥር ዓት ፣ መጻፉ ፣ ከልቀረ ፣ ስሥራ ፣ እንዲቀና ፣ የሳቲኑን ፣ ፊደል ፣ እንቀበለው ፣ ብለው ፣ የሚ ሞኙ ፣ አሉ ።

ስለ አጎዝ ።

አውሮፓውያን ፣ ከወረቦች ፣ ወርሰው ፣ በተሻሻለ ፣ ቅርጽ ፣ ያሰናዱት ፣ የአጎዝ ፣ ፊደል ፣ ለሒሳብ ፣ የሚመች ፣ ስለሆነ ፣ በአገራችን ፣ የተለመደ ፣ ሆኗል ። ስለዚህም ፣ ይህን ፣ አጎዝ ፣ ተጨማሪ ፣ ፊደል ፣ አድርገን ፣ በዘህ ፣ ሰዋስው ፣ ውስጥ ፣ አስገብተናል ። አጎዙም ፣ ይህ ፣ ነው ። « 1.2.3.4.5.6.7.8.9.0 » የሰዋስው ፣ ተራ ፣ ቁጥር ፣ በዘህ ፣ የአጎዝ ፣ ፊደል ፣ ተጽፎአል ።

መልመጃ ።

በየክፍሉ ፣ ወይም ፣ በየምዕራፉ ፣ መጨረሻ ፣ ለትምህርት ፣ ማዕለመጃ ፣ የሚሆኑ ፣ ቃላት ፣ ተጽፈዋል ። ''መልመጃ'' ያልነው ፣ በግዕዙ ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ ''ቅኔዛ'' ወይም ፣ ''ከለዛ'' የሚባለውን ፣ የመሰል ፣ ነው ። በየመልመጃው ፣ ውስጥ ፣ ለማዕጠኛ ፣ የሚሆኑ ፣ ምንባቦች ፣ ተጨምረውበታል ። ከምንባቦቹም ፣ በአንዳንዶቹ ፣ ላይ ፣ አቶ ፣ እርስያ ፣ ሥላሴ ፣ ወረታ ፣ ከሰበሰቡት ፣ የመሰፍንት ፣ ታሪክ ፣ ቢጭሩ ፣ እየተጠቀሰ ፣ ገብቶበታል ።

አስተማሪው ፣ በየመልመጃው ፣ የሚገኙትን ፣ ጥያቄዎችና ፣ ምሳሌዎች ፣ መሠረት ፣ አድርጎ ፣ ሌላም ፣ ማስረጃ ፣ እያቀረበ ፣ እንዲያስተምር ፣ ሊሆን ፣ ይገባዋል ።

ምጎጻረ ፣ ቃል ፣ (የቃል ፣ ማሳጠሪያ) ።

በዚህ ፣ መጽሐፍ ፣ በምጎጻረ ፣ ቃል ፣ (በከፊል) ፣ ተጽፈው ፣ የሚገኙት ፣ ከዘህ ፣ ቀጥሎ ፣ የተመለከቱት ፣ ናቸው ።

መዋ.	= መስተዋድድ ፣	ተ.ግ.	= ተውላጠ ፣ ግሥ ፣
መፃ.	= መስተዛምር ፣	አድ.	= አስረጅ ፣
ቁ.	= ቁጥር ፣	እ.ግ.	= እንደ ፣ ግለት ፣
ቃ.አ.	= ቃለ ፣ አጋኖ ፣	እን.	= እንስት ፣
ተ.ስ.	= ተውላጠ ፣ ስም ፣	ዐ.ነ.	= ዐረፍተ ፣ ነገር ፣
ተባ.	= ተባት ፣	ገ.ግ.	= ገቢር ፣ ግሥ ፣
ተገ.ግ.	= ተገብሮ ፣ ግሥ ፣		

ደራሲው ፣

ብላታ ፣ መርስዔ ፣ ኀዘን ፣ ወልደ ፣ ቂርቆስ ።

ተራ ቁጥር	አርእስተ ፣ ነገር ፣ (ማውጫ ።)	ገጽ ፣
—	መቅድም ፣	፫
—	መግቢያ ፣	፯
—	ምጎጻረ ፣ ቃል ፣ (የቃል ፣ ማሳጠሪያ ፣)	፲
—	አርእስተ ፣ ነገር ፣	፲፭
	መጀመሪያ ፣ ታላቅ ፣ ክፍል ፣	
—	ምዕራፍ ፣ ፩ ፣ የንግግር ፣ ክፍሎች ።	፲፯
1	ጠቅላላ ፣ መግለጫ ።	»
—	፩ኛ ፣ መልመጃ ። (የዕንቊራሪቶች ፣ ምሳሌ ።) . . .	፳
—	ምዕራፍ ፣ ፪ ፣ ስሞች ።	፳፩
10	ክፍል ፣ ፩ ፣ የስም ፣ ዓይነቶች ፣	»
11	የተጸውዖ ፣ ስም ።	፳፪
17	የወል ፣ ስም ።	፳፭
20	የጥቅል ፣ ስም ።	፳፰
21	የቁሰቍስ ፣ ስም ።	»
23	የነገር ፣ ስም ።	፳፱
—	፪ኛ ፣ መልመጃ ። (ምንባብ ፣ — የሸዋ ፣ በላበቶች ።) . .	፴፫
25	ክፍል ፣ ፪ ፣ የተፈጥሮ ፣ ጸታ ።	፴፭
—	፫ኛ ፣ መልመጃ ። (ምንባብ ፣ — የሸዋ ፣ መሳፍንት ።)	፴፱
28	ክፍል ፣ ፫ ፣ ቁጥር ፣ (አንድና ፣ ብዙ ።)	፵፪
—	፬ኛ ፣ መልመጃ ፣ (ምንባብ ፣ — ነጋሚ ፣ ከርስቶስ ።)	፵፮
36	ክፍል ፣ ፬ ፣ ሙያ ።	፵፯
	፭ኛ ፣ መልመጃ ። (ምንባብ ፣ ስብስትያኖስ ።)	፶
45	ክፍል ፣ ፭ ፣ የስሞች ፣ ዝርገር ፣ አፈታት ።	፶፭
—	ምዕራፍ ፣ ፫ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ።	፶፫
47	መግለጫ ።	»
49	ክፍል ፣ ፩ ፣ የተውላጠ ፣ ስም ፣ ዓይነቶች ።	»
50	(ሀ) ምድብ ፣ ተውላጠ ፣ ስም።	»
53	ደርብ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፣	፶፱
56	መዘክር ፣ ተውላጠ ፣ ስም ።	፷፫
59	(ለ) አመልካች ፣ ተውላጠ ፣ ስም ።	፷፮
66	አጸፋ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ።	፸፭
75	(ሐ) መጠይቅ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ።	፸፱
—	፮ኛ ፣ መልመጃ ፣ (ምንባብ ፣ — መርድ ፣ አዝማች ፣ አብቤ ።)	፸፬
80	ክፍል ፣ ፪ ፣ የተውላጠ ፣ ስም ፣ ዝርዝር ፣ አፈታት ፣ . .	፸፰

ተራ ፡ ቁጥር	አርእስተ ፡ ነገር ፡ (ማውጫ ።)	ገጽ
—	ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ቅጽል ፤	፶፯
81	መግለጫ ፤	»
85	ክፍል ፡ ፩ ፡ የቅጽል ፡ አመሠራረት ፡	፶፯
97	ክፍል ፡ ፪ ፡ የቅጽል ፡ ዓይነቶች ።	፷፫
98	(፩ኛ) የዓይነትና ፡ የግብር ፡ ቅጽል ።	፷፬
—	የወገን ፡ ቅጽል ።	»
100	የግብር ፡ ቅጽል ።	፷፭
102	የዓይነት ፡ ቅጽል ።	፷፯
103	(፪ኛ) የአጎገባና ፡ የመጠን ፡ ቅጽል ።	»
104	የተወሰነ ፡ አጎገዝ ።	፷፯
108	ያልተወሰነ ፡ አጎገዝ ።	፸፮
110	(፫ኛ) አመልካች ፡ ቅጽል ።	»
111	የተወሰነ ፡ አመልካች ።	፸፱
112	ያልተወሰነ ፡ አመልካች ።	»
113	ጠቃሽ ፡ አመልካች ።	፹
114	አዛማጅ ፡ ቅጽል ።	»
115	ክፍል ፡ ፫ ፡ የማነጻጸር ፡ ደንብ ።	፹፩
—	፯ኛ ፡ መልመጃ ። (ምንባብ ፡ —መ.አ.አምኃየስና ፡ አስፋ ፡ ወሰን ።)	፹፪
—	ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ ግሥ ።	፹፭
119	መግለጫ ።	»
122	ክፍል ፡ ፩ ፡ የግሥ ፡ ጠባይና ፡ ዓይነት ።	፹፰
123	ገቢር ፡ ግሥ ።	»
125	ተገብሮ ፡ ግሥ ።	»
126	ወላዋይ ፡ ግሥ ።	፹፯
129	ተሻጋሪ ፡ ግሥ ።	»
131	የማይሻገር ፡ ግሥ ።	፹፯
132	ነባር ፡ ግሥ ።	»
»	፰ኛ ፡ መልመጃ ። (ምንባብ ፤ —መ.አ. ወሰን ፡ ሰገድ ።)	፹፯
138	ክፍል ፡ ፪ ፤ አዕማድ ።	፹፱
—	መግለጫ ።	»
142	የአዕማድ ፡ ዓይነት ።	፺
148	የአዕማድ ፡ ጠባይ ።	፺፮
151	የአዕማድ ፡ ባዕድ ፡ መነሻ ።	፺፱
—	፱ኛ ፡ መልመጃ ። (ምንባብ ፤ —ንጉሥ ፡ ማሀለ ፡ ሥላሴ ።)	፺፫

ተራ ፡ ቁጥር	አርእስተ ፡ ነገር ፡ (ማውጫ ።)	ገጽ
133	ክፍል ፡ ፫ ፡ የግሥ ፡ ረዳት ።	፺፬
—	፲ኛ ፡ መልመጃ ። (ምንባብ ፡ —ኃይለ ፡ መለኮት ።) . . .	፺፪
172	ክፍል ፡ ፬ ፡ የአርባታ ፡ መሪዎች ።	፺፫
173	የየዋህ ፡ አርባታ ፡ መሪዎች ።	»
176	የገርገር ፡ አርባታ ፡ መሪዎች ።	፺፱
187	መስተዋድዳውያን ፡ የአርባታ ፡ መሪዎች ።	፻፭
—	፲፩ኛ ፡ መልመጃ ። (ምንባብ ፡ —መሰናንት ፡ በጎንደር ።) .	፻፱
188	ክፍል ፡ ፭ ፡ የግሥ ፡ ስልት ፡ ጊዜያት ።	፻፱
»	መግለጫ ።	»
191	(ሀ) ወዪይ ፡ አንቀጽ ።	፻፲
192	(ለ) ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ።	»
193	(ሐ) አዋዋይ ፡ አንቀጽ ።	፻፫
196	(መ) ንኡስ ፡ አንቀጽ ።	»
—	፲፪ኛ ፡ መልመጃ ። (ምንባብ ፡ —አጼ ፡ ቴዎድሮስ ።) . .	፻፭
201	ክፍል ፡ ፮ ፡ የግሥ ፡ አረባብ ።	፻፯
»	የመሆን ፡ ግሥ ፡ አርባታ ።	»
203	የመኖር ፡ (የአለኝ ፡ ማለት ፡) ግሥ ፡ አርባታ ።	፻፲
205	ክፍል ፡ ፯ ፡ የግሥ ፡ ሙሉ ፡ አርባታ ።	፻፲፫
209	የግሥ ፡ መረለግ ፡ የዋህ ፡ አርባታ ።	፻፲፱
210	የግሥ ፡ መፈለግ ፡ ዝርዝር ፡ አርባታ ።	፻፳፩
213	ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆኑ ፡ ግሦች ።	፻፳፫
218	የግሦች ፡ አስትግቡእ ።	፻፳፱
219	የማያቋርጥ ፡ ግሥ ።	፻፴፩
220	ሥሉጥ ፡ ግሥ ።	፻፴፯
221	ሰያፍ ፡ ግሥ ።	»
222	የማለት ፡ ግሥ ።	»
226	የማለት ፡ ግሥ ፡ የዋህ ፡ አርባታ ፡ በአምንታና ፡ በአሉታ ።	፻፴፫
—	፲፫ኛ ፡ መልመጃ ።	፻፴፱
—	ምዕራፍ ፡ ፯ ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡	፻፴፫
227	መግለጫ ።	»
228	የተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ክፍሎች ፤	፻፴፬
229	(ሀ) የዋህ ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡	»
230	(ለ) መጠይቅ ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡	፻፴፭
231	(ሐ) ከበባ ፡ የሚገኝ ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡	፻፴፮

ተራ ቁጥር	አርእስተ ነገር (ማውጫ ።)	ገጽ
232	የማወዳደር ፡ ደረጃ ፤	፻፴፯
233	የተውሳከ ግሥ ፡ አመዳደብ ፤	»
—	፲፩ኛ ፡ መልመጃ ።	፻፴፰
—	ምዕራፍ ፡ ፯ ፡ መስተዋድድ ፤	፻፴፱
238	መግለጫ ፤	»
239	የመስተዋድድ ፡ አመዳደብ ፤	፻፵
250	የመስተዋድድ ፡ ተሳቢዎች ፤	፻፵፫
—	፲፭ኛ ፡ መልመጃ ፤	፻፵፬
—	ምዕራፍ ፡ ፰ ፡ መስተፃምር ።	፻፵፭
251	መግለጫ ፤	»
253	ወደረኛ ፡ መስተፃምር ፤	»
259	ጥገኛ ፡ መስተፃምር ፤	፻፵፰
—	፲፮ኛ ፡ መልመጃ ።	፻፶፩
—	ምዕራፍ ፡ ፱ ፡ ቃለ አጋኖ ፤	፻፶፪
262	መግለጫ ።	»
263	የቃለ አጋኖ ፡ ዓይነቶች ፤	»
267	መጠይቃን ፡ ወይም ፡ ቃላተ ጥያቄ ፤	፻፶፬
268	(1.) ፊደላውያን ፡ መጠይቃን ፤	፻፶፭
271	(2.) ድምፃውያን ፡ መጠይቃን ፤	፻፶፮
—	፲፯ኛ ፡ መልመጃ ።	፻፶፯
	ሁለተኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ አገባብ ።	
	ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፤	፻፶፰
272	መግለጫ ፤	»
274	ባለቤትና ፡ አንቀጽ ፤	፻፶፱
275	ሐረግ ፤	፻፷
277	የወረፍተ ፡ ነገር ፡ አመዳደብ ፡	፻፷፩
»	ነጠላ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡	»
286	ነጠላ ፡ ወረፍተ ፡ ነገርን ፡ መተንተን ፡	፻፷፭
289	የመተንተን ፡ ሰሌዳ ፡	፻፷፯
290	ድርብ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡	፻፷፯
291	ድርብርብ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡	»
—	፲፰ኛ ፡ መልመጃ ፡ (ክፍለ ፡ አሀጉር ፡)	፻፸፫
—	ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ የቃላት ፡ አገባብ ፡	፻፸፱
293	መግለጫ ፡	»

ተራ ቁጥር	አርእስተ ነገር (ማውጫ ።)	ገጽ
294	በለቤትና ፡ እንቀጽ ፡	፻፸፱
299	የባለቤት ፡ ዘርፍ ፡ ወይም ፡ ተቀጣዩ ፡	፻፹፩
302	የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ፡	፻፹፪
304	ተውላጠ ፡ ስም ፡	»
307	ቅጽል ፡	፻፹፬
311	ተውሳከ ፡ ግሥ ፡	፻፹፰
313	ቅርብና ፡ ሩቅ ፡	፻፹፱
—	፲፱ኛ ፡ መልመጃ ፡	፻፺፯
315	ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ የቃላት ፡ መወራረስ ፡	»
316	ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡ የቃላት ፡ ዝርዝር ፡ አፈታት ፡	፻፹፱
»	መግለጫ ፡ (የአፈታት ፡ አርእስቶች ፡)	»
326	የአፈታት ፡ ምሳሌ ፡	፻፹፱
327	የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ፡ ከባለቤት ፡ ሲቀድም ፡	፻፺፩
—	፳ኛ ፡ መልመጃ ፡	፻፺፮
—	ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡	፻፺፰
328	ክፍል ፡ ፩ ፡ ባዕድ ፡ ሙነሸና ፡ ባዕድ ፡ መድረሻ ፡	»
331	ክፍል ፡ ፪ ፡ ከግዕዝ ፡ የተወረሱ ፡ ቃላት ፡	፻፺፱
334	ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ቋንቋ ፡ የተወረሱ ፡ ቃላት ፡	፼፪
335	ክፍል ፡ ፫ ፡ ነጥበችና ፡ ምልክቶች ፡	፼፭
336	ክፍል ፡ ፬ ፡ የአማርኛ ፡ መዝሙር ፡	፼፰
338	የዜማ ፡ ስልት ፤	፼፱
339	የአማርኛ ፡ ዘፈን ፤	»
340	የአማርኛ ፡ መዝሙር ፤	፼፲
341	የዜማ ፡ ምልክት ፤	፼፲፩
342	የግጥም ፡ ዓይነቶች ፡	፼፲፪
343	ሰምና ፡ ወርቅ ፡	፼፲፩
344	የአማርኛ ፡ ቅኔ ፡	፼፲፱
345	ምሳሌ ፡ (ተረት ፤)	፼፳፩
346	ስለ ፡ ጽሕፈት ፡	፼፳፪

የአማርኛ ሰዋስው ፤

መጀመሪያ ፣ ታላቅ ፣ ክፍል ።

ምዕራፍ ፣ ፩ ፣ የንግግር ፣ ክፍሎች ።

—1—

ጠቅላላ ፣ መግለጫ ።

ሰው ፣ አሳቡን ፣ በንግግር ፣ የሚገልጽባቸው ፣ ቃላት ፣ በየወገን ፣ በየወገናቸው ፣ ሆነው ፣ ሲመደቡ ፣ በስምንት ፣ ታላላቅ ፣ ክፍሎች ፣ ይከፈላሉ ።

እነርሱም ፣ የሚከተሉት ፣ ናቸው ።

፩ኛ ፣ ስም ፤
፪ኛ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፤
፫ኛ ፣ ቅጽል ፤
፬ኛ ፣ ግሥ ፤
፭ኛ ፣ ተውሳከ ፣ ግሥ ፤
፮ኛ ፣ መስተዋድድ ፤
፯ኛ ፣ መስተዋምር ፤
፰ኛ ፣ ቃለ ፣ አጋኖ ፤

—2—

ስም ። ማናቸውም ፣ ነገር ፣ በተለይ ፣ ሆኖ ፣ የሚጠራበትና ፣ ለአንዱ ፣ ነገር ፣ ወይም ፣ ለአንዱ ፣ ዓይነት ፣ የተሰጠው ፣ ስያሜ ፣ ስም ፣ ይባላል ።

ምሳሌ ፣ አብርሃም ፣ አዲስ ፣ አበባ ፤ ፈረስ ፤ መጽሐፍ ፤ ሕልም ።

እነሆ ፣ አሁን ፣ በተሰጠው ፣ ማስረጃ ፤ ‹አብርሃም› የሰው ፣ ስም ፣ ነው ፤ ‹አዲስ ፣ አበባ› የከተማ ፣ ወይም ፣ የቦታ ፣ ስም ፣ ነው ። ‹ፈረስ› የአንድ ፣ ዓይነት ፣ እንስሳ ፣ ስም ፣ ነው ። ‹መጽሐፍ› የዕቃ ፣ ስም ፣ ነው ። ‹ሕልም› ረቂቅ ፣ የሆነ ፣ የነገር ፣ ስም ፣ ነው ።

ስለዚህ ፣ መጠረያ ፣ የሆነ ፣ ማናቸውም ፣ ቃል ፣ ስም ፣ ይባላል ። (ቊ ፣ 11-14 እይ ።)

—3—

ተውላጠ ፣ ስም ፤ በስም ፣ ፈንታ ፣ ተተክቶ ፣ የሚገባ ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፣ ይባላል ።

ምሳሌ ፣ እኔ ፣ አንተ ፤ እርሱ ፣ እርስዋ ፤

አስረጅ ፣ እኔ ፣ አናቴን ፣ እወዳለሁ ፤ እርስዋም ፣ ትወደኛለች ።

እነሆ ፣ ‹እኔ ፣ እርስዋ ፣› የሚለው ፣ ቃል ፣ በስም ፣ ፈንታ ፣ ተተክቶ ፣ እንደገባ ፣ አስተውል ።

ስለዚህም ፡ በስም ፡ ፈንታ ፡ ተተክቶ ፡ የሚገባ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ይባላል ። ትርጓሜው ፡ የስም ፡ ምትክ ፤ ወይም ፡ የስም ፡ ልዋጭ ፡ ማለት ፡ ነው ። በብዙ ፡ ቁጥር ፡ ሲሆን ፡ ተውላጣት ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ ይባላሉ ።

—4—

ቅጽል ። ዓይነትንና ፡ ግብርን ፡ መጠንንም ፡ ለመግለጽ ፡ በስም ፤ ወይም ፡ በተውላጠ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ የሚጨመር ፡ ቃል ፡ «ቅጽል ።» ይባላል ። ስሙ ፡ እንደሚያመለክት ፡ ቅጽል ፡ ማለት ፡ ቅጥያ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምሳሌ ። ጥቁር ፡ ፈረስ ፤ ብርቱ ፡ ፈረስ ፤ አጭር ፡ ፈረስ ።

እነሆ ፡ ቅጽል ፡ የተባሉት ፡ «ጥቁር ፡ ብርቱ ፡ አጭር ፡ ናቸው ። ፈረስ ፡ የአንድ ፡ እንስሳ ፡ ስም ፡ ነው ። «ጥቁር ።» ፈረስ ፡ ሲል ፡ ዓይነቱን ፡ «ብርቱ ፡ ፈረስ ።» ሲል ፡ ግብሩን ፡ አጭር ፡ «ፈረስ ።» ሲል ፡ መጠኑን ፡ የቅጽሉ ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ። ስለዚህም ፡ በስምና ፡ በተውላጠ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ እየተቀጠለ ፡ ዓይነቱን ፤ ግብሩን ፤ መጠኑን ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ «ቅጽል ።» ይባላል ። (ቁ. 97—102 እይ ።)

—5—

ግሥ ። የማድረግንና ፡ የመሆንን ፡ ስሜት ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ጠቅላላ ፡ ስሙ ፡ ግሥ ፡ ይባላል ። ግሥ ፡ የቃላት ፡ ማሰሪያና ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቃላት ፡ ያለ ፡ ግሥ ፡ እንደሚሰሙ ፡ ሆነው ፡ ለመሳከት ፡ አይችሉም ።

ምሳሌ ። ወደደ ፤ አሰበ ፤ ሄደ ፡ ተቀመጠ ፤ ፈለገ ።

አጅ . ያዕቆብ ፡ ይማራል ።

እነሆ ፡ የግሥ ፡ ቃል ፡ የተባለው ፡ ይማራል ፡ ነው ። «ያዕቆብ» ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ ቢቀር ፡ ናሮ ፤ ያዕቆብ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ምንን ፡ እንዳደረገ ፡ ለማወቅ ፡ ባልተቻለም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የግሡ ፡ ቃል ፡ «ይማራል ።» የተጨመረበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያዕቆብ ፡ ምን ፡ እንዳደረገ ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ። የነገሩም ፡ ፍሬ ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ ይገለጻል ።

ስለዚህም ፡ ንግግሮችን ፡ የሚሰበስቧቸውና ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ቃል ፡ ግሥ ፡ ይባላል ።

—6—

ተውላከ ፡ ግሥ ። ከግሥ ፡ በፊት ፡ እየገባ ፡ የአንቀጽን ፡ ጠባይ ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ «ተውላከ ፡ ግሥ ።» ይባላል ። ትርጓሜው ፡ በግሥ ፡ ላይ ፡ የሚጨመር ፡ ወይም ፡ የሚደረብ ፡

ማለት ፡ ነው ። በብዙ ፡ ቁጥር ፡ ሲሆን ፡ ተውላከ-ግሥ ፡ ያሰኛል ። ወይም ፡ ተውላከ ፡ ግሦች ፡ ይባላሉ ።

አጅ . ያዕቆብ ፡ ትምህርትን ፡ በጣም ፡ ይወዳል ። ወደትምህርት ፡ ቤትም ፡ ሁልጊዜ ፡ ይሄዳል ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተሰጠው ፡ ማስረጃ ፡ ተውላከ ፡ ግሥ ፡ «በጣም ፡ ሁልጊዜ» ፡ ናቸው ። በቀላሉ ፡ ለመናገር ፡ ብንፈልግ ፡ ናሮ ፤ «ያዕቆብ» ትምህርትን ፡ ይወዳል ፤ ወደትምህርት ፡ ቤትም ፡ ይሄዳል ፤ » ማለት ፡ በበቃ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የአንቀጾችን ፡ ምግባር ፡ ለመግለጽ ፡ ሁለት ፡ ተውላከ ፡ ግሥ ፡ ተጨመሩ ።

ስለዚህም ፡ በአንቀጽ ፡ ላይ ፡ እየተጨመረ ፡ የአንቀጹን ፡ ምግባርና ፡ ጠባይ ፡ እያጐላ ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ተውላከ ፡ ግሥ ፡ ይባላል ።

— 7 —

መስተዋድድ ። በስምና ፡ በተውላጠ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ በመነሻ ፡ ብቻ ፤ ወይም ፡ በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ እየተጫነ ፡ የንግግርን ፡ ዝምድና ፡ የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ «መስተዋድድ» ይባላል ። ትርጓሜውም ፡ የሚያስማማ ፡ ወይም ፡ አስማሚ ፡ ማለት ፡ ነው ። ብዙ ፡ ቁጥር ፡ ሲሆን ፡ መስተዋድዳን ፡ ያሰኛል ። ወይም ፡ መስተዋድዶች ፡ ይባላሉ ።

አጅ . ያዕቆብ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሄደ ።

እነሆ «ከ ፡ ጋር ፡ ወደ» መስተዋድዳን ፡ ናቸው ። « ከ ፡ ጋር » የተባለው ፡ መስተዋድድ ፡ ልጆቹ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ከመከከል ፡ አድርጎ ፡ በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ ላይ ፡ ተጭኖ ፡ ያዕቆብ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ እንደሄደ ፡ እንጂ ፡ ብቻውን ፡ እንዳልሄደ ፡ እየገለጸ ፤ የበታውን ፡ ንብረት ፡ ያመለክታል ። « ወደ » የተባለውም ፡ መስተዋድድ ፡ ግብፅ ፡ በሚለው ፡ ስም ፡ ላይ ፡ በመነሻ ፡ ብቻ ፡ ተጭኖ ፡ ያዕቆብ ፡ የሄደበትን ፡ ስፍራ ፡ ያመለክታል ።

ስለዚህም ፡ በስምና ፡ በተውላጠ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ መስለው ፡ በሚገኙ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ እየተጫነ ፡ ገብቶ ፡ የንግግርን ፡ ዝምድና ፡ የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ « መስተዋድድ » ይባላል ።

— 8 —

መስተፃምር ። በማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ እየተጫነ ፡ የአንቀጹን ፡ ማሰሪያነት ፡ የሚያስቀርና ፡ ስምን ፡ የሚመስሉ ፡ ነገሮችን ፡ የሚያጫፍር ፡ ቃል ፡ «መስተፃምር» ይባላል ። ትርጓሜው ፡ የሚያያይዝ ፤ ወይም ፡ አያያዥ ፡ ማለት ፡ ነው ። በብዙ ፡ ቁጥር ፡ ሲሆን ፡ መስተፃምራን ፡ ያሰኛል ፤ ወይም ፡ መስተፃምሮች ፡ ይባላሉ ።

አጅ. ያዕቆብና ፡ ዮሐንስ ፡ ትምህርትን ፡ ስለወደዱ ፤ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እየ ፎጡ ፡ ይሄዳሉ ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ ባለቦነው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ምስት ፡ መስተፃምራን ፡ አሉ ። እነርሱም « ና ፡ ስለ ፤ እየ » ናቸው ። « ና » ያዕቆብ ፡ ዮሐንስ ፡ በሚለው ፡ ስም ፡ መከከል ፡ ግብቶ ፡ ሁለቱን ፡ ስሞች ፡ አያይዟል ። « ስለ » ወደጹ ፡ በሚለው ፡ ግሥ ፡ ላይ ፡ ተጭኖ ፤ የአንቀጹንም ፡ ማሰሪያነት ፡ አስወግዶ ፡ ምክንያት ፡ ነጋሪ ፡ ሆኖአል ። « እየ » ሮጡ ፡ በሚለው ፡ ግሥ ፡ ላይ ተጭኖ ፡ የአንቀጹንም ፡ ማሰሪያነት ፡ አስወግዶ ፡ ግብርን ፡ አመልክች ፡ ሆኖአል ።

ስለዚህም ፡ በማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ እየተጫነ ፤ የአንቀጹን ፡ ማሰሪያነት ፡ የሚ ያስቀርና ፡ ስሞችን ፡ የሚያጫፍር ፡ ቃል ፡ ሁሉ « መስተፃምር » ይባላል ።

— 9 —

ቃለ ፡ አጋኖ ፤ በአሰብ ፡ የሚሰማ ፡ እንጻች ፡ ነገር ፡ በማጋነን ፡ ድምፅ ፡ የሚገለጽ በት ፤ ክሌሎችም ፡ ቃላት ፡ ጋር ፡ ገምድናን ፡ ሰያደርግ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ የሚፀና ፡ ቃል ፡ » ቃለ ፡ አጋኖ » ይባላል ።

ምሳሌ ፡ ሆይ ፤ አዬ ፤ ጉድ ፡ እህህ ፤ እኮ ።

አጅ. አምላኬ ፡ ሆይ ፤ እባክህ ፡ ማረኝ ፤ እህህ ፤ ከቶ ፡ ምን ፡ ይሸለኝ ፡ ይሆን ? ።

ስለዚህም ፡ ነገርን ፤ በማጋነን ፡ ድምፅ ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ይባላል ።

፩ኛ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) የንግግር ፡ ክፍሎች ፡ ስንት ፡ ናቸው ? ፤ ስማቸውን ፡ ቁጠር ። ስም ፡ ማለት ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነው ? ፤ ተውላጣ ፡ ስምስ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ፤ ፯ ፡ ስሞች ፡ ፬ ፡ ተውላጣት ፡ ስም ፡ ፯ ፡ ግሶች ፡ ጻፍ ። ከቀሩትም ፡ ክፍሎች ፡ ከያንጻንጻቸው ፡ ሦስት ፡ ቃላት ፡ ጻፍ ።

(ለ) ተሙላከ ፡ ግሥ ፡ ትርጓሜው ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ? ፤ መስተዋድድስ ፤ መስተ ፃምርስ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ። ?

(ሐ) ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጸፉት ፡ ቃላት ፡ እየአንጻንጻቸው ፡ በየትኛው ፡ የንግግር ፡ ክፍል ፡ እንደሆኑ ፡ እየለየህ ፡ አመልክት ።

ያዕቆብና ፡ ሙብሸት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በኩራ ፡ አጠገብ ፡ ሽር ፡ ሽር ፡ ሲሉ ፡ በወንው ፡ ውስጥ ፡ እንቁራሪቶችን ፡ አዩ ። ሙብሸት ፡ ጨዋታን ፡ ይወድ ፡ ነበርና ፤ እንግዲህ ፡ በእን ቁራሪቶቹ ፡ እንጨዋትባቸው ፡ አለ ። ወዲያውም ፡ ድንጋይ ፡ አንሥቶ ፡ ወረወረባቸው ።

ትዕግሥተኛው ፡ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ በእንቁራሪቶቹ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አላደረገም ። ቅልጠልብ ፡ ባልንጀራውንም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መከረው ።

« እንቁራሪቶች ፡ በዚህ ፡ በቀዝቃዛና ፡ በጉድጓዳ ፡ ስፍራ ፡ ሲኖሩ ፡ ሥራቸውን ፡ አያስታጉሉም ። ሁልጊዜ ፡ እየተንጫጩ ፡ በመዝሙራቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምናሉ ። ንግግራቸውን ፡ ብናውቅ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ወሬ ፡ በሰማን ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ''ከዜታችን ፡ መጥቶ ፡ በትርአችን ፡ የሚያውከንን ፡ አግድልን ፡'' ይሉ ፡ ይሆናል ። እንግዲህ ፡ በጨዋ ታቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነግረው ፡ እንዳያስቀሥቱን ፡ ደንጊያ ፡ ልንወረውርባቸውና ፡ ልናስቸግራቸው ፡ አይገባንም ፡ » አለው ።

ሙብሸትም ፡ « ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ የእንቁራሪቶች ፡ ንብረት ፡ ምኞት ፡ የበቂ በት ፡ አይመስለኝም ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ እኛ ፡ ብናወክባቸው ፡ ጨዋታቸው ፡ ይበዛል ፡ » አለ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ ደንጊያ ፡ መወርወርን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ቤታ ቸው ፡ ተመለሱ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ስሞች ።

ክፍል ፡ ፩ ፡ የስም ፡ ዓይነቶች ።

—10—

ሰው ፤ ወይም ፡ ሴላ ፡ ነገር ፡ የሚጠራበት ፡ ቃል ፡ ስም ፡ ይባላል ። ስም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጸፉት ፡ በ፪ ፡ ዓይነቶች ፡ ይመደባል ።

(ሀ) ፩ ፤ የተጸውዖ ፡ ስም ፤
፪ ፤ የወል ፡ ስም ፤
፫ ፤ የጥቅል ፡ ስም ፤
፬ ፤ የቁሳቁስ ፡ ስም ፤

(ለ) ፭ ፤ የነገር ፡ ስም ፤

ከነዚህም ፡ የፊተኞቹ ፡ አራቱ ፡ ክፍሎች ፡ በግዘፍ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ የሚ ጠራባቸው ፡ ስሞች ፡ ናቸው ። የመጨረሻው ፡ « የነገር ፡ ስም » የተባለው ፡ ግን ፡ በዓይን ፡ የማይታይ ፤ ወይም ፡ በእጅ ፡ የማይዳሰስ ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፤ ወይም ፡ ግብር ፡ የሚጠራ በት ፡ ስም ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ « ስም » ብለን ፡ የሰየምነው ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በግዕዝ ፡ ትምህርት ፡ ነጣር ፤ ዘር ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

—11—

የተጸውዖ ፡ ስም ።

የተጸውዖ ፡ ስም ፡ የተባለው ፤ ሰው ፤ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ በተለይ ፡ የሚጠራበ ትና ፡ ተለይቶ ፡ የማታወቅባት ፡ ስመ ፡ ነው ። እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በየንይ ነቱ ፡ ጽፈን ፡ እናሳያለን ።

የሰው ፡ ስም ፤ — ሰሎሞን ፤ ምኒልክ ፡ መኩንን ፤ የሺእመቤት ፤
የአገር ፡ ስም ፤ — አፍሪካ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ሽዋ ፡ ጅሩ ፤
የከተማ ፡ ስም ፤ — አዲስ ፡ አበባ ፤ ጎንደር ፤ ሎንዶን ፤ ፓሪስ ፤
የተራራ ፡ ስም ፤ — መቅደላ ፤ ራስ ፡ ዳሽን ፤ ጅበላ ፤ ክሊማንጃሮ ፤
የወንዝ ፡ ስም ፡ ፤ — ዐባይ ፤ ተከዜ ፤ ሐዋሽ ፤ ቀበና ፤
የባሕሮችና ፡ የኩሬዎች ፡ ስም ፤ — ኤርትራ ፤ ጣና ፤ ዙዋይ ፡ ሐረማያ ።

—12—

የተጸውዖ ፡ ስም ፡ በወል ፡ ስምና ፡ በወገን ፡ ቅጽል ፡ ደንብ ፡ ከልሆነ ፡ በቀር ፡ ብዛት ፡ የለውም ።

ምሳሌ ፡ ሰሎሞን ፡ ምኒልክ ፡ ያለውን ፡ ሰሎሞኖች ፡ ምኒልኮች ፡ ብሎ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ለማብዛት ፡ አይቻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ በየወል ፡ ስም ፡ ደንብ ፡ ሆኖ ፡ «ባኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ምኒልኮች ፡ ሁለት ፡ ናቸው ፡ ቢል ። ወይም ፡ በወገን ፡ ቅጽል ፡ ደንብ ፡ ሰሎሞ ናዊ ፡ ምኒልካዊ ፡ ያለውን ፡ ሰሎሞናውያን ፡ ምኒልክውያን ፡ ብሎ ፡ ቢያበዛ ፡ አያስከለክልም ።

—13—

በተጸውዖ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ እየተደረቡ ፡ የሚገቡ ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ የሚሆኑ ፡ ድርብ ፡ ስሞች ፡ አሉ ። እነርሱም ፡ የማዕርግ ፡ ስምና ፡ የአክብሮት ፡ ስም ፡ ናቸው ።

(ሀ) የማዕርግ ፡ ስም ፡ ከሴት ፡ መንግሥት ፤ ወይም ፡ ከሴት ፡ ክህነት ፡ በሹመት ፡ የሚገኝ ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ አጼ ፡ እቴጌ ፡ እጨጌ ፡ ጳጳስ ፤ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ራስ ፡ ደጃዝማች ፡ ፊታ ውራሪ ፡ መልአክ ፡ ፀሓይ ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ ይሀን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

(ለ) የአክብሮት ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ በሹመት ፡ ሳይሆን ፡ በፈቃድና ፡ በልማድ ፡ የሚደረግ ፡ ስያሜ ፡ ነው ። ለእርሱም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልት ፡ አለው ።

የአክብሮት ፡ ስም ።

ትባዕት ፡ ጸታ ፤ አቶ ፤ ጌታ ፤ የኔታ ፤ አያ ፤ ወይም ፡ አይዋ ፤
እንስት ፡ ጸታ ፤ ወይዘሮ ፤ እመየቴ ፤ ኔኒሆይ ፤ እንኩዬ ፤

የተዘምዶ ፡ ስም ።

ትባዕት ፡ ጸታ ፤ አባባ ፤ ጋሼ ፤ አጐቴ ።

እንስት ፡ ጸታ ፤ እማማ ፤ እተዬ ፡ አክስቴ ።

—14—

ድርብ ፡ ስሞች ፤ በተጸውዖ ፡ ስሞች ፡ ላይ ፡ ተደርበው ፡ ሲገቡ ፡ ክፍላቸው ፡ ከተ ጸውዖ ፡ ስም ፡ ነው ። ተንኖለው ፡ ሲነገሩ ፡ ግን ፡ ከፍላቸው ፡ ከወል ፡ ስም ፡ ይሆናል ። የሚከተለውን ፡ ተመልከት ።

የማዕርግ ፡ ስም ፡ «አጼ ፡ » ምኒልክ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ነበሩ ። (የተጸውዖ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ «አጼ» ይበላል ። (የወል ።)

የአክብሮት ፡ ስም ።

አቶ ፡ » ብርሃኑ ፡ ባለቤቱን ፡ «ወይዘሮ ፡ » ተዋበችን ፡ ያከብራል ። (የተጸውዖ ፡)

አቶ ፡ » የሚባል ፡ ወንድ ፡ ነው ። « ወይዘሮ ፡ » የምትባል ፡ ሴት ፡ ናት ፡ (የወል ፡)

—15—

በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ ከስም ፡ ከፍል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከተውላጠ ፡ ስምና ፡ ከቅጽል ፡ ከግሥና ፡ ከሌሎችም ፡ የንግግር ፡ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ እየተቀላቀለ ፡ ወይም ፡ ሳይቀላቀል ፡ ይገኛል ።

ከተውላጠ ፡ ስም ፡ «የኔ ፡ ነህ ፤ አንተን ፡ ይሰጠኝ ፡ እሱ ፡ እንዳለ ፡ » . . .

ከቅጽል ፡ «ሳሩይ ፤ ሥዩም ፡ መኩንን ፡ ዐቢይ ፡ . . . . . .

ከግሥ ፡ «ከበደ ፡ ዘለቀ ፡ አየለ ፡ ድፋብኛው ፡ ይጨነቁ ፡ ይጋርዱ ፡ ተዋበች ፡ ፈለቀች ፡ እየለች ፡ . . . .

ከመስተዋድድ ፡ «እንደ ፡ ልኩ ፡ በጋሻው ፡ በፈቃዱ ፡ በፍርዱ ፡ » . . . . .

ከቃለ ፡ አጋኖ ፡ አብዩ ፡ ሆይ ፡ አትሞችሆኖ ፡ . . . .

—16—

በዕልተ ፡ ዋምቀት ፡ ቀሳውስት ፡ የሚሰይሙት ፡ የክርስትና ፡ ስም ፡ ዓይነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ሀ) የቅዱሰን ፡ ስም ፡ በቁሙ ፡ መጠሪያ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ፤ አብርሃም ፡ ኤጥሮስ ፡ ሚክኤል ፤ አስቴር ፡ ማራ ፡ እንደማለት ፡ ነው ።

ለ) ወልደ ፣ ወለተ ፣ ገብረ ፣ ዓመተ ፣ ተክለ ፣ ኃይለ ፣ . . . . እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ቃላት ፡ የቅዱሳንን ፡ ስም ፡ ዘርፍ ፡ እያደረጉ ፡ ተገጣጥመው ፡ መጠሪያ ፡ ይሆናሉ ።

ምሳሌ ፤ ወልደ ፡ ማርያም ፤ ወለተ ፡ ሚካኤል ፤ ገብረ ፡ ሥላሴ ፤ ዓመተ ፡ ጻድቅ ፤ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፤ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ እንደማለት ፡ ነው ።

ሐ) ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ የምስጢር ፡ ቃላትን ፡ በመመርመር ፡ የተሰየሙ ፡ ብዙ ፡ ዓይነቶች ፡ ስሞች ፡ ይገኛሉ ።

ምሳሌ ፤ ሥምረተ ፡ አብ ፤ ስርጉተ ፡ ማርያም ፤ ሰዋስወ ፡ ድንግል ፤ አርአያ ፡ ሥላሴ ፤ እርአያ ፡ ዮሐንስ ፤ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለዚህም ፡ በዕለተ ፡ ጥምቀት ፡ የሚሰየሙት ፡ የክርስትና ፡ ስሞች ፡ ብዙ ፡ ዓይነቶች ፡ ናቸው ።

—17—

የወል ፡ ስም ፡

የወል ፡ ስም ፡ የተባለው ፡ ዓይነቱ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፤ በጠቅላላ ፡ የሚጠራበት ፡ ስም ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ ሰው ፤ አገር ፤ ተራራ ፤ ባሕር ፤ ወንዝ ፡ መጽሐፍ ፤ መሬት ፤ ዝግባ ፡ ጎመን ፤ ስንዴ ፡ ስንደዶ ፤ በግ ፤ አንበሳ ፤ እንደማለት ፤

እነሆ ፤ ከላይ ፡ እንደ ፡ተጻፈው ፡ ቃል ፡ «ሰው ፡» በተባለ ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላላ ፡ የሁሉ ፡ ስም ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ፡ እንጂ ፡ «ሰሎሞን ፡ ምኒልክ ፡» እንደማለት ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ የሚሰጥ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ አይደለም ።

አገር ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ ከዓለም ፡ ክፍል ፡ የሆኑ ፡ ቦታዎች ፡ የሚጠሩበት ፡ ስም ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ፡ እንጂ ፡ «ኢትዮጵያ ፤ ግብጽ ፤ ሽዋ ፡» እንደማለት ፡ ላንድ ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ የተሰጠ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ አይደለም ።

አንበሳ ፡ በተባለም ፡ ጊዜ ፡ ከአራዊት ፡ ክፍል ፡ የሆኑ ፡ በያገሩ ፡ ያለው ፡ አንበሳ ፡ ሁሉ ፡ የሚጠራበት ፡ ጠቅላላ ፡ ስም ፡ እንጂ ፤ በተለይ ፡ ሆኖ ፡ ለምናየው ፡ ለአንድ ፡ አንበሳ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ ስም ፡ አይደለም ። እንግዲህ ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ምሳሌ ፡ መመርመር ፡ ነው ።

— 18 —

ወል ፡ ማለት ፡ የጋራ ፡ « የጋር ፡» ማለት ፡ ስለሆነ ፤ የወል ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ የጋርዮሽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ማስረጃ ፡ ዳኛ ፡ የሁሉ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ «ዳኛ ፡ የወል ፡ ምሰሶ ፡ የመኻል ፡» ተብሎ ፡ ይተረታል ።

— 19 —

የወል ፡ ስም ፡ በነጠላና ፡ በብዙ ፡ ቁጥር ፡ ሊነገር ፡ ይቻላል ።

ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ሰው ፡	ሰዎች ፡	ከተማ ፡	ከተሞች ፡
አገር ፡	አገሮች ፡	አንበሳ ፡	አንበሶች ፡
ወንዝ ፡	ወንዞች ፡	በግ ፡	በጎች ፡

የተጸውዖ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ የወል ፡ ስም ፡ ይሆናል ። ይህንንም ፡ በ ፡ ተ ፡ ቁ ፡ 12 ተመልከት ።

— 20 —

የጥቅል ፡ ስም ።

የጥቅል ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ብዙው ፡ የወል ፡ ስም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ተጠቅሎ ፡ የሚጠራበት ፡ የማኅበር ፡ ወይም ፡ የነገድ ፡ ስም ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ ፍጥረት ፤ ሠራዊት ፤ መንጋ ፤ እንጨት ፤ እህል ፡ እንደማለት ።

እነሆ ፤ የፍጥረት ፡ ዓይነቱና ፡ ክፍሉ ፡ ብዙ ፡ እንደሆነ ፡ እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ለመናገር ፡ ብንፈልግ ፡ ፍጥረት ፡ በማለት ፡ ሰብስበን ፡ በዘጎብረት ፡ እንናገራለን ።

የእንስሳትም ፡ ዓይነታቸውና ፡ ስማቸው ፡ ብዙ ፡ እንደሆነ ፡ እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድነት ፡ ተቀላቅለው ፡ በተሰማሩ ፡ ጊዜ ፡ በግ ፤ ፈረስ ፤ በሬ ፡ ብሎ ፡ በመጥራት ፡ ፈንታ ፡ መንጋ ፡ ብለን ፡ በማኅበር ፡ ስማቸው ፡ እንናገራለን ።

በግ ፡ ወይም ፡ በሬ ፡ መባል ፡ በየሰፍራው ፡ ያለ ፡ በግና ፡ በሬ ፡ ሁሉ ፡ የሚጠራበት ፡ የወል ፡ ስም ፡ ነው ። መንጋ ፡ የሚባለው ፡ ስም ፡ ግን ፡ ለበግ ፤ መይም ፡ ለበሬ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንስሳት ፡ ሁሉ ፡ በዘጎብረት ፡ የሚጠሩበት ፡ ስም ፡ እንደሆነ ፡ አስተውል ።

— 21 —

የቁሳቁስ ፡ ስም ።

የቁሳቁስ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ለሰው ፡ አገልግሎት ፡ የሚገባ ፡ የቤት ፡ ዕቃ ፡ ነው ። ከማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ የተሠራ ፡ ዕቃ ፤ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ጉዳይ ፡ የሚገባ ፡ ከሆነ ፡ ቁሳቁስ ፡ ይባላል ።

ምሳሌ ፤ ልብስ ፤ አልጋ ፤ ወንበር ፤ ጫማ ፤ እንደማለት ፡ ነው ።

— 22 —

የቄሳቊስ ፡ ስምና ፡ የወል ፡ ስም ፡ ይወራረሳሉ ። ልዩነታቸውም ፡ የሚታወቀው ፡ በእነጋገር ፡ አገባብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በተረፈ ፡ ልዩነት ፡ የለባቸውም ።

ምሳሌ ፡ ዓሣ ፡ ጨው ፡ ብረት ፡ ሥጋ ፡ ስንዴ ፡

(ሀ) የወል ፡ ስም ።	(ለ) የቄሳቊስ ፡ ስም ።
«ዓሣ» በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል ።	«ዓሣን» መብላት ፡ በብልሃት ፡ ነው ።
«ጨው» ከባሕር ፡ ይነጠራል ።	«ጨው» ወጥን ፡ ያጣፍጣል ።
ከሥጋ ፡ የተወለደ ፡ «ሥጋ» ነው ።	«ሥጋን» የሚበላ ፡ ይጠነክራል ።
አገሬ ፡ «ስንዴን» ያበቅላል ።	«የስንዴ» ዳቦ ፡ ይጣፍጣል ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳሳየነው ፡ በ«ሀ» ክፍል ፡ የተጻፉት ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ ለቤት ፡ ጉዳይ ፡ የሚገቡ ፡ መሆናቸውን ፡ ንግግሩ ፡ እያመለከትም ፡ «ዓሣ ፡ ጨው ፡ ሥጋ ፡ ስንዴ ፡» የተባሉት ፡ የወል ፡ ስሞች ፡ ናቸው ። በ«ለ» ክፍል ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ጥቅም ፡ እንደገቡ ፡ ንግግሩ ፡ ያመለክታልና ፡ የቄሳቊስ ፡ ስሞች ፡ ይባላሉ ።

ስለዚህም ፡ የወልና ፡ የቄሳቊስ ፡ ስም ፡ ልዩነት ፡ በአነጋገሩ ፡ ምሥጢር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

— 23 —

የነገር ፡ ስም ።

በዓይን ፡ የማይታይ ፡ በእጅ ፡ የማይዳሰስ ፡ ባሕርይንና ፡ ሥራን ፡ የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ የነገር ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የግብር ፡ ስም ፡ ይባላል ።

ምሳሌ ፡ ንጽሕና ፡ ጤና ፡ ኃጢአት ፡ ኖድቅ ፡ ወዳጅነት ፡ ጠላትነት ፡ አሳብ ፡ ድምፅ ፡ ብርሃን ፡ ጨለማ ፡ . . . . ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ።

— 24 —

የነገር ፡ ስሞች ፡ በብዙ ፡ የሚገኙት ፡ ከግሥ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግሣውያን ፡ ስሞች ፡ ይባላሉ ። በቅኔ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፡ አርእስት ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ የግብር ፡ ስሞች ፡ ናቸው ።

ምሳሌ ፡ መፈለግ ፡ አፈላለግ ፡ ፍለጋ ፡ ፍላጎት ፡ መልበስ ፡ አለባበስ ፡ ልብስ ፡ መል በሻ ፡ እንደማለት ፡ ነው ።

ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ በቅጽል ፡ ላይ ፡ «ነት» የሚል ፡ ትርፍ ፡ ፊደልን ፡ እየጨመሩ ፡ የመሆንን ፡ ስሜት ፡ የሚገልጹ ፡ የግብር ፡ ስሞች ፡ አሉ ።

ምሳሌ ፡	ቅጽል ፡	የግብር ፡ ስም ።
	ክፉ ፡	ክፉነት ።
	ጨካኝ ፡	ጨካኝነት ።
	በደለኛ ፡	በደለኛነት ።

ሄኖ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) የስም ፡ ዓይነቶች ፡ ስንት ፡ ናቸው ። ? — ስማቸውስ ፡ ማን ፡ ማን ፡ ይባላል ። ? — የተጻውዖ ፡ ስም ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ። ? — የወል ፡ ትርጓሜ ፡ ምን ድር ፡ ነው ። ? — የቀቅል ፡ ስም ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድር ፡ ነው ። ? — የቄሳቊስ ፡ ስም ፡ የተባለውስ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ። ? — የነገር ፡ ስም ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ዓይነት ፡ ነው ። ?

ኗ ፡ የተጻውዖ ፡ ስሞች ፡ — ፪ ፡ የወል ፡ ስሞች ፡ ጻፍ ። ከቀሩትም ፡ የስም ፡ ዓይነቶች ፡ ከያንዳንዳቸው ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ቃላትን ፡ ጻፍ ።

(ለ) ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፈው ፡ ምንባብ ፡ ስሞችን ፡ በየዓይነታቸው ፡ እየለየህ ፡ አመልክት ። (ምንባብ ፡ የግዕዝ ፡ ቃል ፡ ነው ። ትርጓሜው ፡ ማንበቢያ ፡ ወይም ፡ ማስነ በቢያ ፡ ማለት ፡ ነው ።)

ምንባብ ።

ከግራኝ ፡ ሽብር ፡ በኋላ ፡ ሸዋ ፡ በብዙ ፡ ባላባት ፡ የተከፈለ ፡ አገር ፡ ነበር ። በላ ባቶቹም ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነበሩ ። በየአገሩ ፡ የነበሩት ፡ ባላባቶች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ተመልክተዋል ።

በአንመኪያ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ዘሚካኤል ። — በአፍራታ ፡ ወልዴ ፡ ገብር ኤል ። — በግድም ፡ ለታ ። — በመንዝ ፡ ከይሚ ፡ እስከ ፡ ጭማ ፡ ግማ ፡ ከርይ ፡ እስከ ፡ አንኛትላ ፡ ባላምባራስ ፡ ላሉ ። — በግቪ ፡ አውሳብዮስ ። — በዶባ ፡ ጌታቸው ። — በም ሔይ ፡ አዛዥ ፡ መኸዲ ። — በመርሐቤቴ ፡ ወልዱ ። — በሞረት ፡ ጥዱ ። — በተጉለት ፡ ይገበሞል ። — በወግዳ ፡ ሕርያቆስ ። — በሞልጋ ፡ ቀይ ፡ አብዱ ፡ ጥቁር ፡ አብዱ ። —በጠራ ፡ ሌቄ ፡ ሠረቄ ፡ ይባሉ ፡ ነበር ።

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በየራሳቸው ፡ በየወገናቸው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በአንድ ፡ አስ ጋዝ ፡ ተጠቅልለው ፡ አይገዙም ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከጎን ፡ ለሚመጣ ፡ ባለጋራ ፡ መል ያየት ፡ አልነበረም ።

ክፍል ፪ ፥ የተፈጥሮ ጾታ ።

— 25 —

የሕይወት ፥ ነፍስ ፥ ያለው ፥ ፍጥረት ፥ ሁሉ ፤ ሰውም ፥ እንስሳም ፥ ቢሆን ፥ በባሕርዩ ፥ የወንድነት ፤ ወይም ፥ የሴትነት ፥ መለዮ ፥ ይገኝበታል ። የሕይወት ፥ ነፍስ ፥ የሌለባቸው ፥ ፍጥረታት ፥ ግን ፥ የወንድነትና ፥ የሴትነት ፥ መለዮ ፥ የለባቸውም ። እነዚህም ፥ ሁሉ ፥ በሰዋስው ፥ ጀንብ ፥ የተወሰነ ፥ ስም ፥ አላቸው ።

(ሀ) በተፈጥሮ ፥ ባሕርዩ ፥ ወንድ ፥ የሆነ ፥ ሁሉ ፥ «ጾታው ፥ ተባዕት ፥ » ነው ፥ ይባላል ። የወንድ ፥ ወገን ፥ ማለት ፥ ነው ።

(ለ) በተፈጥሮ ፥ ባሕርዩ ፥ ሴት ፥ የሆነ ፥ ሁሉ ፥ ጾታው ፥ «እንስት ፥ » ነው ፥ ይባላል ። የሴት ፥ ወገን ፥ ማለት ፥ ነው ።

(ሐ) የሕይወት ፥ ነፍስ ፥ የሌለው ፥ ፍጥረት ፥ ግን ፥ የወንድነት ፤ ወይም ፥ የሴትነት ፥ ባሕርይ ፥ የለውምና ፥ «ግዑዝ ፥ » ጾታ ፥ ይባላል ። ነፃ ፥ የሆነ ፤ ወይም ፥ ከሁለቱ ፥ የተለየ ፥ ወገን ፥ ማለት ፥ ነው ።

በግዕዝ ፥ ተባዕት ፤ እንስት ፤ የሚለው ፥ ቃል ፥ ወደ ፥ ቅጽልነት ፥ ሲለወጥ ፥ ተባዕታይ ፤ እንስታይ ፤ ያሰኛል ፤ ተባዕታይ ፥ እንስታይ ፥ ማለት ፥ ከግዕዝ ፥ ቃል ፥ የተመሠረተ ፥ ነው ። በአማርኛም ፥ ለከብቶች ፥ ብቻ ፥ ተባዕት ፤ እንስት ፥ ተብሎ ፥ ይነገራል ። በአማርኛ ፥ ወንዴ ፤ ሴቴ ፥ የሚባል ፥ ቃል ፥ በእንጨቶች ፥ ላይ ፥ ሲነገር ፥ ይኖራል ። ከዚህም ፥ የተነሣ ፥ ከሊቃውንት ፥ ወገን ፥ ወንዴ ፥ ጾታ ፤ ሴቴ ፥ ጾታ[1] ፤ ያሰኛል ፥ ብለው ፥ የበየኑ ፥ አሉ ። ደራሲውም ፥ ይህን ፥ አሳብ ፥ በሙሉ ፥ ይቀበለዋል ።

(መ) የሕይወት ፥ ነፍስ ፥ ያለው ፥ የፍጥረት ፥ ስም ፥ ወንድ ፤ ወይም ፥ ሴት ፤ መሆኑን ፥ የማይለይ ፥ የሆነ ፥ እንደሆነ ፥ ጾታው ፥ «የወል ፥ » ነው ፥ ይባላል ። ይኸውም ፥ ልጅ ፤ አያት ፤ አስተማሪ ፥ እንደማለት ፥ ያለ ፥ ነው ። ወል ፥ ማለት ፥ ምን ፥ እንደሆነ ፥ ቁ. 18 ፥ ተመልከት ።

— 26 —

ተባዕት ፤ ወይም ፥ እንስት ፥ ያልሆነ ፥ ስም ፥ ሁሉ ፤ በወንድ ፤ ወይም ፥ በሴት ፤ አንቀጽ ፥ ቢጠራ ፥ እያስከለክልም ። ይሁን ፥ እንጂ ፥ እንደልማድ ፥ ሆኖ ፤ በወንድ ፥ ስም ፥ የሚጠራ ፥ ነገር ፥ አለ ።

ምሳሌ ፤ ነፋስ ፤ ነፈሰ ፤ ዝናም ፥ ዘነመ ፤ ወንዙ ፥ ደረቀ ፥ ውኃው ፥ ደፈረሰ ፤ ጎሕ ፥ ቀደደ ፤ መከር ፥ ደረሰ ፤ ገደል ፥ ተናደ ፥ ይበላል ።

እንደዚሁም ፥ ደግሞ ፥ በሴት ፥ ስም ፥ የሚጠራ ፥ ነገር ፥ አለ ።

ምሳሌ ፤ ዉሬቃ ፥ ወጣች ፤ የአጥቢያ ፥ ኮከብ ፥ ታየች ፤ ኢትዮጵያ ፥ እጅጅን ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ታደርሳለች ፥ ይባላል ።

— 27 —

ስሞች ፤ በተባዕትና ፥ በእንስት ፥ ጾታ ፥ ሲገቡ ፥ አዩ ፥ አዩ ፥ ጠባይ ፥ አላቸው ።

ጠባያቸውም ፥ (ሀ) ቃል ፥ ለሞጭ ፤ (ለ) ቅጽል ፥ ፈላጊ ፥ ተብሎ ፥ በሁለት ፥ አከፋፍሎ ፥ ይመደባል ።

ቃል ፥ ለዋጭ ፥ የሚባለው ፥ ለወንድ ፥ ስም ፥ በተነገረው ፥ ቃል ፥ አንጻር ፤ ስለ ፥ ሴት ፥ ስም ፥ የሚነገረው ፥ ቃል ፥ ግብሩ ፥ አንድ ፥ ሁኖ ፥ ሳለ ፤ በፍጹም ፥ ልዩ ፥ ሲሆን ፤ ነው ።

ምሳሌ ፤ ወንዱን ፥ አባት ፥ ብሎ ፤ በአንጻሩ ፥ ሴቲቱን ፥ እናት ፥ ይላል ። ይህም ፥ በፍጹም ፥ የተለየ ፥ ቃል ፥ እንደሆነ ፥ አስተውል ። በዚህ ፥ ዓይነት ፥ የሆኑ ፥ ቃላት ፥ ብዙዎች ፥ አይደሉም ።

ቅጽል ፥ ፈላጊ ፥ የሚባለው ፥ ወንድና ፥ ሴትን ፥ የማያስለይ ፥ ቃል ፥ ነው ። ጾታው ፥ የወል ፥ ነው ።

ምሳሌ ፤ ልጅ ፤ አያት ፤ አስተማሪ ፥ ሲባል ፥ ወንድ ፤ ወይም ፥ ሴት ፥ መሆኑን ፥ ለይቶ ፥ አያስታውቅም ። ሴቶችም ፥ ወንዶችም ፥ ሊጠሩበት ፥ ይቻላል ፤ ማለት ፥ ነው ። ነገር ፥ ግን ፥ ለይቶ ፥ ለመናገር ፥ ያስብን ፥ እንደሆነ ፤ «ወንድ ፥ ወይም ፥ ሴት» ፥ የሚል ፥ ቃል ፥ እየጨመርን ፤ ወንድ ፥ ልጅ ፤ ሴት ፥ ልጅ ፤ ወንድ ፥ አያት ፤ ሴት ፥ አያት ፤ ወንድ ፥ አስተማሪ ፤ ሴት ፥ አስተማሪ ፤ እያልን ፥ እንናገራለን ።

አዮ ፤ ማናቸውም ፥ ሰው ፥ ሲሞት ፥ ወንድ ፥ ልጅ ፥ ባይኖረው ፥ ርስቱ ፥ ለሴት ፥ ልጁ ፥ ይሰፍ ። (ዘኍል ፥ ፳፯ ፥ ፰ ።)

ስለዚህም ፥ ወንድንና ፥ ሴትን ፥ የማያስለዩ ፥ ቃላት ፤ ቅጽል ፥ ፈላጊዎች ፥ ይባላሉ ። በአማርኛ ፥ ቋንቋ ፥ በዚህ ፥ ደንብ ፥ የሚገቡ ፥ ቃላት ፥ ብዙዎች ፥ ናቸው ።

እነዚህንም ፥ ሁሉ ፥ ከዚህ ፥ በታች ፥ ጽፈን ፥ እናመለክታለን ።

(ሀ) ቃል ፥ ለዋጭ ።

ተባ.ጾታ.	እን.ጾታ.	ተባ.ጾታ.	እን.ጾታ.	ተባ.ጾታ.	እን.ጾታ.
አሴ ፥	አቡጌ ፥	ወንድም ፥	እኅት ፥	ጕረምሳ ፥	ኰረዳ ፥
አቶ ፥	መያዣሮ ፥	አጎት ፥	አክስት ፥	ሰፌ ፥	ገረድ ፥
ጌታ ፥	እመቤት ፥	ወንድ ፥	ሴት ፥	በሬ ፥	ላም ፥
አባት ፥	እናት ፥	ባል ፥	ሚስት ፥	ወይፈን ፥	ጊደር ፥

ለ) ቅጽል ፥ ፊላጊዎች ፤

ስም ፥	ተባ.ጾታ	እን.ጾታ.	ስም ፥	ተባ.ጾታ.	እን.ጾታ.
ልጅ ፥	ወንድ ፥ ልጅ ፥	ሴት ፥ ልጅ ፥	ንብር ፥	ወንድ ፥ ንብር ፥	ሴት ፥ ንብር ፥
ምግቢት ፥	ወንድ ፥ ምግቢት ፥	ሴት ፥ ምግቢት ፥	አንበሳ ፥	ወንድ ፥ አንበሳ ፥	ሴት ፥ አንበሳ ፥
አስተማሪ ፥	ወንድ ፥ አስተማሪ ፥	ሴት ፥ አስተማሪ ፥	ወፍ ፥	ወንድ ፥ ወፍ	ሴት ፥ ወፍ ፥
አገልጋይ ፥	ወንድ ፥ አገልጋይ ፥	ሴት ፥ አገልጋይ	አጋዘን ፥	ወንድ ፥ አጋዘን ፥	ሴት ፥ አጋዘን ፥
እፊት ፥	ወንድ ፥ እፊት ፥	ሴቱ ፥ እፊት ፥	አህያ ፥	ወንድ ማመጽ	ሴት ፥ አህያ ፥

የኖ ፥ መልመጃ ።

ሀ) የተፈጥሮ ፥ ጸታዎች ፥ ስንት ፥ ናቸው ? ። ስማቸው ፥ ማን ፥ ማን ፥ ይባላል ? ፤ ከተባዕት ፥ ጸታ ፥ ሯ ፤ ከእንስት ፥ ጸታ ፥ ሯ ፤ ከወል ፥ ጸታ ፥ ሯ ፥ ቃላት ፥ ጻፍ ።

ለ) ከዚህ ፥ በታች ፥ የተጻፈውን ፥ ቃል ፥ በየጸታው ፥ ለይተህ ፥ ተናገር ።

ላም ፤	በሬ ፤	አባት ፥	ወይፈን ፤	ጨረቃ ፤
ሕዝብ ፥	ተዋላ ፥	አስተማሪ ፥	ዘሆን ፥	ጨለማ ፥
ምድር ፥	ቸርነት ፥	አያት ፥	ደመና ፥	ጳውሎስ ፥
ርግብ ፥	ኃይል ፥	ሌጎት	ድብ ፥	ጴጥሮስ ፥
ሰማይ ፥	ንብር ፥	አክስት ፥	ጌታ ፥	ፀሐይ ፥
ቀን ፥	እናት ፥	ወንድም ፥	ጊደር ፥	ፈረስ ፥

ሐ) ከዚህ ፥ በታች ፥ ከተጻፈው ፥ ምንባብ ፥ ስሞችን ፥ በየጸታቸው ፥ እየለየህ ፥ ተናገር ።

ምንባብ ።

በግራኝ ፥ ሽብር ፥ ጊዜ ፥ ከአጼ ፥ ልብነ ፥ ድንግል ፥ ልጆች ፥ አንደኛው ፥ አቤቶ ፥ ያዕቆብ ፥ በሸዋ ፥ ቀርቶ ፥ ነበር ። እርሱም ፥ ገራም ፥ ፋሲልንና ፥ ሥግው ፥ ቃልን ፥ ይወልዳል ። ገራም ፥ ፋሲል ፤ የሱስንዮስ ፥ አባት ፥ ነው ። ገራም ፥ ፋሲል ፥ ሱስንዮስን ፥ የመለጀው ፥ ከመ ግሳው ፥ በላበት ፥ ከሕርያቆስ ፥ ልጅ ፥ ከወይዘሮ ፥ ሐመልማል ፥ ነው ።

ሥግው ፥ ቃል ፤ የሸዋ ፥ መሰፍንት ፥ አባት ፥ ነው ። የምስፍናው ፥ ግዛት ፥ የተጀመረውና ፥ እየጐላም ፥ የሚነገረው ፥ ከነጋሢ ፥ ክርስቶስ ፥ ወዲህ ፥ ነው ።

እነሆ ፥ ከሥግው ፥ ቃል ፥ ጀምሮ ፥ ያሉትን ፥ የሸዋ ፥ መሰፍንት ፥ እንደ ፥ ትውልዳቸው ፥ ተራ ፥ ጽፈናቸዋል ።

ሥግው ፥ ቃል ፤ ወረደ ፥ ቃልን ፥ ይወልዳል ። — ወረደ ፥ ቃል ፤ ልብሰ ፥ ቃልን ፥ ይወልዳል ። ልብሰ ፥ ቃል ፥ *ከወይዘሮ ፥ ሰንበልት ፤ ነጋሢን ፥ ይወልዳል ። — ነጋሢ ፤ ስብስቴን ፥ ይወልዳል ። — ስብስቴ ፤ መርድ ፥ አዝማች ፥ አብዬን ፥ ይወልዳል ። መርድ ፥ አዝማች ፥ አብዬ ፥ ((ስመ ፥ ጥምቀቱ ፥ ወረደ ፥ ቃል ፥) መርድ ፥ አዝማች ፥ እምኃየስን ፥ ይወልዳል ። — መርድ ፥ አዝማች ፥ እምኃየስ ፥ ከወይዘሮ ፥ ዕፁብና ፥ መርድ ፥ አዝማች ፥ አስፋወሰንን ፥ ይወልዳል ። — መርድ ፥ አዝማች ፥ አስፋወሰን ፥ (ስመ ፥ ጥምቀቱ ፥ ቴዎድሮስ ፥ መርድ ፥ አዝማች ፥ ወሰን ፥ ሰገድን ፥ ይወልዳል ። — መርድ ፥ አዝማች ፥ ወሰን ፥ ሰገድ ፥ (ስመ ፥ ጥምቀቱ ፥ ወልደ ፥ ጊዮርጊስ ፥) ከወይዘሮ ፥ ዘነበ ፥ ወርቅ ፥ ንጉሥ ፥ ግሀለ ፥ ሥላሴን ፥ ይወልዳል ። — ንጉሥ ፥ ግሀለ ፥ ሥላሴ ፥ ኃይለ ፥ መለኮትን ፥ ይወልዳል ። — ኃይለ ፥ መለኮት ፥ ከወይዘሮ ፥ እጅግአየሁ ፥ አጼ ፥ ምኒልክን ፥ ይወልዳል ።

የአፂ ፥ ምኒልክን ፥ አልጋ ፥ የያዙ ፥ በፊት ፥ የሴት ፥ ልጃቸው ፥ የወይዘሮ ፥ ሽዋረገድ ፥ ልጅ ፥ አቤቶ ፥ ኢያሱ ፥ ናቸው ። በኋላም ፥ ሌቲቱ ፥ ልጃቸው ፥ ንግሥት ፥ ዘውዲቱ ፥ ምኒልክ ፥ ናቸው ።

የተወዳጅ ፥ ንጉሣችን ፥ የአጼ ፥ ኃይለ ፥ ሥላሴ ፥ ትውልድ ፥ ከንጉሥ ፥ ግሀለ ፥ ሥላሴ ፥ ላይ ፥ ሲደርስ ፥ በአንደኛው ፥ ዘርፍ ፥ ይወርዳል ።

ንጉሥ ፥ ግሀለ ፥ ሥላሴ ፥ ወይዘሮ ፥ ተናኘ ፥ ወርቅንና ፥ ሴሎችንም ፥ ይወልዳሉ ። —

ወይዘሮ ፥ ተናኘ ፥ ወርቅ ፥ የዶባውን ፥ በላባት ፥ ደጃዝማች ፥ ወልደ ፥ ሚካኤልን ፥ አግብተው ፥ ልዑል ፥ ራስ ፥ መኮንንን ፥ ይወልዳሉ ። — ልዑል ፥ ራስ ፥ መኮንንም ፥ ከወይዘሮ ፥ የሺ ፥ አመቤት ፥ ንጉሠ ፥ ነገሥት ፥ ቀዳማዊ ፥ አጼ ፥ ኃይለ ፥ ሥላሴን ፥ ወለዱ ።

«አቤቱ ፥ ግዛትህን ፥ ለንጉሡ ፥ ስጠው ፤ ጽድቅህንም ፥ ለንጉሡ ፥ ልጅ ። »

*ልብስ ፥ ቃል ፥ የሚለውን ፥ በሞሪሽ ፥ አውጥቶ ፥ ወረደ ፥ ቃል ፥ ሰንበልትን ፥ ወለደ ፤ ሰንበልት ፥ ነጋሢን ፥ ወለደች ፥ የሚል ፥ ታፊክ ፥ ይገኛል ።

ክፍል ፫ ፡ ቁጥር ።

— 28 —

አንድ ፡ ነገር ፡ በነጠላው ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ የአንድ ፡ ቁጥር ፤ ወይም ፡ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ይባላል ። በነጠላ ፡ የተነገረውም ፡ ያ ፡ ቃል ፡ በብዙነት ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ ይባላል ። ስለዚህም ፡ በሰዋስው ፡ ደንብ ፡ «ነጠላ ፡ » ማለት ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ የተነገረ ፡ «ብዙ ፡ » ማለት ፡ በብዙነት ፡ የተነገረ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቁጥር ፡ በተባለው ፡ ክፍል ፡ የምናገኘው ፡ ጥቅም ፡ አንዱን ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ተሰውጦ ፡ ማየት ፡ ነው ።

— 29 —

ከስሞች ፡ ከፍል ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ ብዛትን ፡ አይፈልግም ፤ ውልጊዜ ፡ በነጠላ ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ። ነገር ፡ ግን ፡ መደቡን ፡ ለቅቆ ፡ ከወል ፡ ስም ፡ መደብ ፡ የገባ ፡ እንደሆነ ፡ በብዙ ፡ መጠራት ፡ አለበት ።

ምሳሌ ፡ በግብጽ ፡ ፲፯ ፡ ፈርዖኖች ፡ ነግሠዋል ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ምሳሌ ፡ የተጸፈው ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ የነበረው ፡ ፈርዖን ፡ ወደ ፡ ወል ፡ ስም ፡ ተለውጦ ፡ እንደበዛ ፡ አስተውል ።

የወል ፡ የቄሳሮስ ፤ የነገር ፡ ስሞች ፡ በነጠላም ፡ በብዙም ፡ ይነገራሉ ።

ምሳሌ ፡ ፈረስ ፤ ፈረሶች ፤ ቤት ፤ ቤቶች ፤ ብልሃት ፡ ብልሃቶች ፤ እንደግለት ፡ ነው ።

— 30 —

የጥቅል ፡ ስሞች ፡ በነጠላ ፤ ወይም ፡ በብዙ ፡ ይነገራሉ ።

ምሳሌ ፤ መንጋ ፤ መንጎች ፤ ግጎበር ፤ ግጎበሮች ፤ መራዊት ፤ መራዊቶች ፤ እንደግለት ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የጥቅል ፡ ስሞች ፡ ውስጠ ፡ ብዛት ፡ ያላቸው ፡ ስለሆኑ ፤ ቃላቸው ፡ ወደ ፡ ብዙነት ፡ ሳይለወጥ (በአንድ) ወይም ፡ በብዙ ፡ ቃል ፡ ቢነገሩ ፡ አያስነውሩም ። ይህም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። መንጋ ፡ ግጎበር ፡ የጥቅል ፡ ስም ፡ ነው ። መንጋው ፤ ወይም ፡ ግጎበሩ ፡ ተሰበሰበ ፡ ቢል ፤ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ መንጋው ፤ ወይም ፡ ግጎበሩ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ቢል ፤ መንጎቹ ፡ ግጎበሮቹ ፡ ከላለ ፡ ተብሎ ፡ አያስነቅፍም ፡ ማለት ፡ ነው ።

—31—

ለብዙ ፡ ቁጥር ፡ መደቡ ፡ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ ቁጥር ፡ ውል ጊዜ ፡ ከነጠላው ፡ ቁጥር ፡ ይመሠረታል ። ስሞችን ፡ ብዙ ፡ ለማድረግ ፡ ስንፈልግ ፡ በነጠላው ፡ ስም ፡ ላይ ፡ የማብዣ ፡ ቅጥያ ፡ ዎች ፡ ወይም ፡ ች ፡ እያልን ፡ እንጨምራለን ። የአጨማመሩም ፡ ደንብ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

(ሀ) መድረሻው ፡ ራብዕ ፡ ሳድስ ፤ የሆነ ፡ ቃል ፡ የመጨረሻ ፡ ፊደሉን ፡ ሳብዕ ፡ አድርጎ ፡ ች ፡ ይጨመርበትና ፡ ብዙ ፡ ይሆናል ። ምሳሌ ፡ ጌታ ፡ ጌቶች ፡ ሰው ፡ ሰዎች ፤ እንደማለት ፡ ነው ።

(ለ) መድረሻው ፡ ሳብዕ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ የመጨረሻ ፡ ፊደሉ ፡ ሳይሰውጥ ፡ ች ፡ ይጨመርበትና ፡ ብዙ ፡ ይሆናል ። ምሳሌ ፡ በቅሎ ፤ በቅሎች ፤ መሰንቆ ፤ መሰንቆች ፤ እንደማለት ፡ ነው ።

(ሐ) መድረሻው ፡ ከፅብ ፡ ሣልስ ፡ ኃምስ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ መጨረሻ ፡ ፊደሉ ፡ ሳይሰወጥ ፡ ዎች ፤ ይጨመርበትና ፡ ብዙ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ፡ ክፉ ፡ ክፉዎች ፡ ፈታውራሪ ፡ ፈታውራሪዎች ፤ ገበሬ ፡ ገበሬዎች ፡ እንደ ማለት ፡ ነው ።

ከሊቃውንት ፡ ወገን ፡ ሩሐ ፡ በሚባል ፡ ክፍል ፡ ያሉየነውን ፡ ውሳኔ ፡ የማይፈቅዱ ፡ አሉ ። እንዳሳብፉውም ፡ ክፉ ፡ ክሮች ፤ ፈታውራሪ ፡ ፈታውራሮች ፡ ገበሬ ፡ ገበሮች ፡ ያሰኛል ፡ ብለው ፡ ያውጃሉ ። አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ማናቸውም ፡ ስም ፡ ብዙ ፡ ሲሆን ፡ የመጨረሻ ፡ ፊደሉ ፡ ሳይሰወጥ ፡ ዎች ፡ ሊጨመርበት ፡ ያስፈልጋል ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ ውሳኔን ፡ ያበጃሉ ። ይኸውም ፡ ክፉ ፡ ክፉዎች ፡ ፈረ ፡ ፈረዎች ፤ ጌታ ፡ ጌታዎች ፡ ገበሬ ፡ ገበሬዎች ፡ በቅሎ ፡ በቅሎዎች ፡ እንደግለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ውሳኔ ፡ በእንድ ፡ ዓይነት ፡ ደንብ ፡ የተደነገገ ፡ ስለሆነ ፡ ሰሕሲና ፡ የሚስማማ ፡ ነው ።

(መ) የብዛት ፡ ደንብ ፡ በተውላጠ ፡ ስምና ፡ በግሥ ፡ በኩል ፡ ሲሆን ፡ የላይኛውን ፡ ውሳኔ ፡ «ች ፡ ዎች ፡» የተባለውን ፡ አይከተልም ። ሰነርሱ ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ አላቸው ።

ተውላጠ ፡ ስም ፡ በብዙ ፡ ሲነገር ፡ እኔ ፤ የሚለው ፡ እኛ ፤ አንተ ፡ የሚለው ፡ እነ አንተ ፡ ይሆናል ። በግሥ ፡ በኩልም ፡ የብዛትን ፡ ምልክት ፡ የሚሰጥ ፡ የእርባታ ፡ መሪ ፡ የሚባለው ፡ ገርገር ፡ ነውና ፡ ከስፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እንናገረዋለን ። ቁ ፡ ያሬዛ ፡ ያሬቪ ፡ እይ ።

—32—

ስሞች ፡ ብዙ ፡ የሚሆኑበት ፡ ውሳኔ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ተጽፎ ፡ ይታያል ።

(ሀ) ደንበኛው ፡ የአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ «ች» ወይም ፡ «ዎች ፡» እየተጨመረበት ፡ ብዙ ፡ ይሆናል ። የሚከተለውን ፡ ተመልከት ።

ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ብዙ ፡	ብዙዎች ፡	አግራ ፡	አግሮች ፡	ቤት ፡	ቤቶች ፡
ክፉ ፡	ክፉዎች ፡	ወይራ ፡	ወይሮች ፡	ስም ፡	ስሞች ፡
ኩሩ ፡	ኩሩዎች ፡	ጋሳ ፡	ጋሎች ፡	ልጅ ፡	ልጆች ፡
ቀጣፊ ፡	ቀጣፊዎች ፡	ጌታ ፡	ጌቶች ፡	ፈረስ ፡	ፈረሶች ፡
ለውጥ፡አዝራር፡ለውጥ፡አዝራሮች፡		ገበራ ፡	ገበሬዎች ፡	በቅሎ ፡	በቅሎች ፡
ፈሪ ፡	ፈሪዎች ፡	አንክሴ ፡	አንክሴዎች ፡	መሰንቆ ፡	መሰንቆች ፡
ፈታውራ ፡ ፈታውራዎች ፡		በሬ ፡	በሬዎች ፡	ማነቆ ፡	ማነቆች ፡

(ለ) አማርኛ ፡ የወረሳቸው ፡ አንዳንድ ፡ የግዕዝ ፡ ቃላት ፡ እንደ ፡ ግዕዙ ፡ ደንብ ፡ ይበዛሉ ።

ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ሊቅ ፡	ሊቃውንት ፡	ነፍስ ፡	ነፍሳት ፡	ነቢይ ፡	ነቢያት ፡
መልአክ ፡	መላእክት ፡	ንጉሥ ፡	ነገሥት ፡	ጻድቅ ፡	ጻድቃን ፡
መኰንን ፡	መኳንንት ፡	መጽሐፍ ፡	መጻሕፍት ፡	ቃል ፡	ቃላት ፡
መምህር ፡	መምህራን ፡	ሐዋርያ ፡	ሐዋርያት ፡	ልውል ፡	ልውሎን ፡

(ሐ) ፍጹም ፡ ግዕዝ ፡ ሳይሆን ፡ ከግዕዝ ፡ ጋር ፡ ዝምድና ፡ ያለው ፡ የአማርኛ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ግዕዝም ፡ እንደ ፡ አማርኛም ፡ ሊበዛ ፡ ይችላል ።

ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ቁስ ፡	ቁሶች ፤ ወይም ፡ ቁሳውስት ፡
መነኵሴ ፡	መነኰሴዎች ፤ ወይም ፡ መነኰሳት ፡
ገዳም ፡	ገዳሞች ፤ ወይም ፡ ገዳማት ፡
ደብር ፡	ደብሮች ፤ ወይም ፡ አድባራት ፡

ሙ) አንዳንድ ፡ ቃል ፡ መደቡ ፡ ግዕዝ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ብዛቱ ፡ በአማርኛ ፡ ደንብ ፡ ይሆናል ።

ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
እግር ፡	እግሮች ፡	መሠረት ፡	መሠረቶች ፡	ልቁጠ ፡	ልብቶች ፡
ጎደን ፡	ጎዶኖች ፡	ጠረኢ ፡	ጠረዒዎች ፡	አጎት ፡	አጎቶች ፡
ፈረስ ፡	ፈረሶች ፡	ላሕር ፡	ባሕሮች ፡	ጾም ፡	ጾሞች ፡
አንበሳ ፡	አንበሶች ፡	ቤተ፡መንግሥት፡	ቤተ፡መንግሥቶች፡	ባሕርይ ፡	ላሕርዮች ፡
ፅንሥ ፡	ፅንሶች ፡	መዘንቶ ፡	መዛንቶች ፡	ዜት ፡	ዜቶች ፡

—33—

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቁ ፡ 32 «ለ» ያመለክትነውን ፡ ውሳኔ ፡ አንዳንድ ፡ ሊቃውንት ፡ አይፈቅዳትም ። እንደ ፡ አሰባቸውም ፤ ሰሞች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ብዙነት ፡ በተለወጡ ፡ ጊዜ ፡ ከግዕዝ ፡ ሳይደባለቁ ፡ በአማርኛው ፡ ደንብ ፡ ብቻ ፡ እንዲበዙ ፡ ያፈልጋሉ ። ይኸ ውም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ምሳሌ ።

ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ሊቅ ፡	ሊቆች ፡	ነፍስ ፡	ነፍሶች ፡	ነቢይ ፡	ነቢዮች ፡
መልአክ ፡	መልአኽቶች ፡	ንጉሥ ፡	ንጉሦች ፡	ጻድቅ ፡	ጻዲ ቆች ፡
መኰንን ፡	መኰንኖች ፡	መጽሐፍ ፡	መጽሐፎች ፡	ቃል ፡	ቃሎች ፡
መምህር ፡	መምህሮች ፡	ሐዋርያ ፡	ሐዋርያዎች ፡	ልውል ፡	ልዉሎች ፡

ይህ ፡ አሰባቸው ፡ አንድ ፡ ውሳኔን ፡ ብቻ ፡ የሚደግዝ ፡ ስለመሆኑ ፡ ለተማረው ፡ ድክምን ፡ የሚያቀል ፡ ሊሆን ፡ በቻለ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የአማርኛ ፡ ቋንቋችን ፡ በግዕዝ ፡ የተጌጠና ፤ ከግዕዝ ፡ ጋር ፡ የተሰባቀለ ፡ ስለሆነ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የግዕዙን ፡ ደንብ ፡ መከተሉ ፡ የማይቀር ፡ ነው ።

—34—

ከግዕዝ ፡ የተወረሱ ፡ የብዙ ፡ ቃላት ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ በጸያፍ ፡ አበዛዝ ፡ ይነገራሉ ።

ምሳሌ ፤ ጻድቃን ፡ የሚለውን ፡ ጻድቃኖች ፤ መላእክት ፡ የሚለውን ፡ መላእክቶች ፤ ከሀናት ፡ የሚለውን ፡ ከሀናቶች ፡ ቀሳውስት ፡ የሚለውን ፡ ቀሰውስቶች ፤ ኪሩብ ፡ የሚለውን ፡ ኪሩቤሎች ፤ . . . . እንደማለት ፡ ነው ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የብዛት ፡ ደንብ ፡ ልማዳዊ ፡ ጸያፍ ፡ እንለዋለን ።

— 35 —

ማናቸውንም ፣ ነገር ፣ በየወገኑ ፣ ጠቅልሎ ፣ ለመናገር ፣ ባስፈለገ ፣ ጊዜ ፣ በአንዱ ፣ ስም ፣ ላይ ፣ « እነ » እየተጨመረ ፣ የብዙ ፣ ይሆናል ።

ምሳሌ ፣ (ሀ) እነ ፣ በቀለ ፣ ወደ ፣ ተማሪ ፣ ቤት ፣ መጡ ።

(ለ) እነ ፣ እርሱ ፣ (እነርሱ ፣) ሰዋስውን ፣ ይማራሉ ።

(ሐ) የትምህርት ፣ ጠላቶች ፣ እነ ፣ ስንፍና ፣ እነ ፣ ሀኬት ፣ ናቸው ።

ስለዚህ ፣ « እነ » የተባለው ፣ ቃል ፣ ወንን ፣ አብዝ፤ ወይም ፣ እንዳንኛ ፣ አብዝ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። እነ ፣ ከአ ፣ ፊደል ፣ በቀር ፣ ሌሎቹ ፣ ፊደሳት ፣ ሲከተሉት ፣ በነጥብ ፣ ቢከፈል ፣ ጸያፍ ፣ እያሰኝም ፤ የአ ፣ ፊደል ፣ ሲከተለው ፣ ግን ፣ በነጥብ ፣ አይከፈልም ። ምክንያቱም ፣ የአ ፣ ፊደል ፣ ድምፁን ፣ ለተከታዩ ፣ ዋሎ ፣ እርሱ ፣ ራሱ ፣ መጥፋት ፣ ልማዱ ፣ ስለሆነና ፣ በዚያ ፣ ፈንታ ፣ የሚተካ ፣ ስለሆነ ፣ ነው ።

፩ኛ ፣ መልመጃ ።

(ሀ) በሰዋስው ፣ ዴንብ ፣ ስሞችን ፣ የምናበዛበት ፣ ክፍል ፣ ስሙ ፣ ማን ፣ ይባላል? ። ፪ ነጠላ ፣ ስም ፣ ፫ የብዙ ፣ ስም ፣ ጸፍ ።

(ለ) ከዚህ ፣ በታች ፣ በነጠላነት ፣ የተጻፉትን ፣ ቃላት ፣ ወደ ፣ ብዙነት ፤ በብዙነት ፣ የተጻፉትንም ፣ ወደ ፣ ነጠላነት ፣ አዙራቸው ።

ሀብት ፣	መሳፍንት ፣	ቂስ ፣	አገሮች ፣	ዳኅት ፣
ሃይማኖት ፣	መላእክት ፣	በላባት ፣	ከሩብ ፣	ገደል ፣
ሊቃውንት ፣	መዝሙር ፣	ቤተ ፣ መንግሥት ፣	ወንዝ ፣	ጥበብ ፣
ልብ ፣	ሥራ ፣	ተስፋ ፣	ዓይን ፣	ጫሮች ፣
ሕግ ፣	ርስት ፣	ችንክሮች ፣	ዛፍ ፣	ጽጋግ ፣
መንግሥታት ፣	ርግብ ፣	ጎዘን ፣	የትምህርት ፣ ቤቶች ፣	ፍየል ፣

(ሐ) ከዚህ ፣ በታች ፣ ከተጻፈው ፣ ምንባብ ፣ ስሞችን ፣ እየለየህ ፣ አመልክት ። በነጠላ ፣ ቁጥር ፣ የተጻፈውን ፣ ወደብዙነት ፣ ለውጠው ።

ምንባብ ።

ኒጋሚ ፣ ክርስቶስ ፣ የሚባል ፣ አንድ ፣ የሸዋ ፣ መስፍን ፣ ነበረ ። አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ ዘርፉ ፣ ቀርቶ ፣ ኒጋሚ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። እርሱ ፣ በ፲፯፻፫ኛ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ዓይኔ ፣ የምነባል ፣ ከተማውን ፣ መሠረተ ። በከተማውም ፣ አንድ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ በአግዝአትን ፣ ማርያም ፣ ሠራ ።

ከዚህም ፣ በኋላ ፣ ኒጋሚ ፣ በምሥራቅና ፣ በደቡብ ፣ ያለውን ፣ አገር ፣ እያቀና ፣ ምድርን ፣ በገመድ ፣ እየለካ ፣ ለሕዝቡ ፣ ያካፍል ፣ ጀመረ ። መፈትን ፣ በግብር ፣ እያደረገ ፣ ኀበር ፣ ግንደበል ፣ ቂስ ፣ አወዳሽ ፣ እያለ ፣ መትከል ፣ የጀመረ ፣ ኒጋሚ ፣ ክርስቶስ ፣ ነው ፣ ይባላል ።

በግራኝ ፣ ምክንያት ፣ ዋናው ፣ ቤተ ፣ መንግሥት ፣ ከሸዋ ፣ አልሮ ፣ ወደ ፣ ጎንደር ፣ ተዛውሮ ፣ ነበር ። በዚያን ፣ ጊዜም ፣ የሸዋ ፣ መሳፍንት ፣ ክዋናው ፣ ቤተ ፣ መንግሥት ፣ ጋር ፣ የነበራቸውን ፣ ግንኙነት ፣ ይብዛ ፣ ይነስ ፣ እንጂ ፣ አልተውትም ፣ ነበር ። ስለዚህም ፣ ኒጋሚ ፣ ክርስቶስ ፣ በአድያም ፣ ሰገድ ፣ ኢያሱ ፣ ጊዜ ፣ ወደ ፣ ጎንደር ፣ ተጠርቶ ፣ ሄዶ ፣ ሳለ ፣ በ፲፯፻፶፬ ፣ ዓ ፣ ም ፣ በዚያው ፣ ሞተና ፣ ፊት ፣ አበ ፣ በሚባል ፣ ደብር ፣ ተቀበረ ። አልጋውንም ፣ ልጁ ፣ ስብስቴ ፣ መረሰ ።

ክፍል ፣ ፪ ፣ ሙያ ።

— 36 —

ስሞች ፣ ወይም ፣ ስሞችን ፣ መስለው ፣ የሚገኙ ፣ ቃላት ፣ በሀረፍተ ፣ ነገር ፣ ውስጥ ፣ ተገጣጥመው ፣ በተነገሩ ፣ ጊዜ ፣ የቃሉን ፣ ንብረት ፣ የምናውቅበት ፣ ክፍል ፣ ሙያ ፣ ይባላል ። ይኸውም ፣ ስም ፣ (ሙያ) በቅኔ ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ የታወቀና ፣ የተለመደ ፣ ነው ።

— 37 —

የስሞች ፣ ሙያ ፣ እንደሚከተለው ፣ በቮ ፣ ተመድበአል ።

(ሀ) በለቤት ።

(ለ) ተሳቢ ። {ተጠቃሽ ፣ ተሳቢ ። / የመስተዋድድ ፣ ተሳቢ ።

(ሐ) ዘርፍ ።

ባለቤት ፣ የሚባለው ፣ አንቀጹ ፣ የሚነገርለት ፣ ስም ፣ ነው ። ተሳቢ ፣ የሚባለውም ፣ ስለ ፣ አንቀጹ ፣ የሚነገረው ፣ ነገር ፣ ነው ። ዘርፍ ፣ የሚባለውም ፣ በባለቤት ፣ ወይም ፣ በተሳቢ ፣ ላይ ፣ ተጨምሮ ፣ የሚገባ ፣ ቃል ፣ ነው ።

የተሳቢ ፣ ዓይነቱ ፣ ሁለት ፣ ነው ። አንቀጹ ፣ ገቢር ፣ ሲሆን ፣ ለአንቀጹ ፣ ቀጥተኛ ፣ ተገዥ ፣ የሆነው ፣ ቃል ፣ ተጠቃሽ ፣ ወይም ፣ ርቱዕ ፣ ተሳቢ ፣ ይባላል ። ከመስተዋድድ ፣ ቃላት ፣ አንዳንዶቹን ፣ እያስከተለ ፣ በገቢር ፣ ወይም ፣ በተገብሮ ፣ አንቀጽ ፣ የሚገዘው ፣ ቃል ፣ የመስተዋድድ ፣ ተሳቢ ፣ ይባላል ።

— 38 —

ባለቤትን ፣ ለማወቅ ፣ ብንፈልግ ፣ የተነገረውን ፣ የግሥ ፣ አንቀጽ ፣ ይዘን ፣ ማን ? ወይም ፣ ምን ? ብለን ፣ በመጠየቅ ፣ ባለቤቱን ፣ እናገኘዋለን ።

ምሳሌ ፡ ያዕቆብ ፡ ደከመ ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ በተጻፈው ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡ የአንቀጹ ፡ ባለቤት ፡ ያዕቆብ ፡ ነው ። «ደከመ» ብሎ ፡ ነገሩን ፡ ያቆመ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ? ወይም ፡ ምን ? ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ አለ ብን ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አገሌ ፡ ወይም ፡ ያዕቆብ ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ እንችላለን ።

ስለዚህም ፡ አንቀጹ ፡ የተነገረለትን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ነገር ፡ የሚያስታውቀን ፡ ቃል ፡ ባለቤት ፡ ይባላል ። እንደ ፡ ግብሩስ ፡ ቢሆን ፡ ስም ፡ ጠሪ ፡ ወይም ፡ ተነቢ ፡ ሊባል ፡ በተ ገባው ፡ ሠር ። ነገር ፡ ግን ፡ «ባለቤት ፡» የተባለው ፡ ቃል ፡ በቅጄ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ተለ ምዶ ፡ የኖረ ፡ ስለሆነ ፡ በዚሁ ፡ አጽንተነዋል ።

—39—

ስሞች ፡ በባለቤትነት ፡ የሚከተለውን ፡ ሙያ ፡ ይይዛሉ ።

የአንቀጽ ፡ ባለቤት ፡ { ሰሎሞን ፡ ነገሠ ፡ (አንቀጹ ፡ ተጉበሮ ፡ ነው) ; ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሠራ ፡ (አንቀጹ ፡ ገቢር ፡ ነው) }

ሰሚ ፡ ባለቤት ፡ { አዝዕርትን ፡ ሃይ ፡ ስምህ ፡ ይቀደስ ። ; ዮሐንስ ፡ ትምህርትን ፡ አጥና ፡ } አንቀጹ ፡ የዘፀ ፡ መደብ ፡ ሊሆን ፡ ያስፈልጋል)

—40—

ተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡ የተባለውን ፡ ለማወቅ ፡ ብንፈልግ ፡ የተነገረውን ፡ የግሥ ፡ አንቀጽ ፡ ይዘን ፡ ማንን ? ወይም ፡ ምንን ? ብለን ፡ ስንጠይቅ ፡ ተሰቢውን ፡ ለማግኘት ፡ እንችላለን ። እንደዚህም ፡ የሚደረገው ፡ አንቀጹ ፡ ለዚ ፡ ወይም ፡ ገቢር ፡ የሆነ ፡ እንደ ሆነ ፡ ነው ።

ምሳሌ ፡ ያዕቆብ ፡ ዮሴፍን ፡ መረቀው ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ በተጻፈው ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡ የአንቀጹ ፡ ተሰቢ ፡ ዮሴፍ ፡ ነው ። ያዕቆብ ፡ መረቀ ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ ነገሩን ፡ ቢያቆም ፡ ምንን ? ወይም ፡ ማንን ? ብለን ፡ መጠ የቅ ፡ ያስፈልገናል ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እገሌን ፡ ወይም ፡ ዮሴፍን ፡ የሚል ፡ እንድ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ እንችላለን ።

ስለዚህም ፡ እንቀጹ ፡ የተነገረበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚያስታውቀን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡ ይባላል ። ተጠቃሽ ፡ የተባለውም ፡ ቃል ፡ በቅጄ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተ ለመደ ፡ ነው ።

—41—

ተጠቃሽ ፡ ተሰቢን ፡ ለማድረግ ፡ በስሞች ፡ ላይ ፡ የምንጨምረው ፡ ቃል ፡ «ን» ነው ።

ስሞች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ በተጠቃሽ ፡ ሙያ ፡ ይውሳሉ ።

ምሳሌ ፡ ውብሸት ፡ አንበሳን ፡ ገደለ ። (ተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡)
ከበደ ፡ የዱር ፡ አንበሳን ፡ ገደለ ። (ባለዘርፍ ፡ ተሰቢ ፡)
ገርማነህ ፡ አሮጊ ፡ አንበሳን ፡ ገደለ ። (ባለቅጽል ፡ ተሰቢ ፡)
በላይነህ ፡ መዝሙሩን ፡ ዘመረ ። (ዘመጻዊ ፡ ተሰቢ ፡)

—42—

የመስተዋድድ ፡ ተሰቢ ፡ የተባለውን ፡ ለማወቅ ፡ ብንፈልግ ፡ የተነገረውን ፡ አን ቀጽ ፡ ይዘን ፡ ለማን ? ብሎን ? ወዴት ? ከየት ? እስከየት ? ከማን ፡ ጋር ? ብለን ፡ ስንጠ ይቅ ፡ ምክንያቱን ፡ ለማግኘት ፡ እንችላለን ።

እነዚህንም ፡ ሁሉ ፡ የሚያሟሉና ፡ የሚያስማሙ ፡ የመስተዋድድ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ።

ምሳሌ ። ያዕቆብ ፡ በረከቱን ፡ ለዮሴፍ ፡ ሰጠ ፡ (ለ) ተቀበይ ።
ጥሩነህ ፡ ተዋበችን ፡ በአስጌጋ ፡ ገረፋት (በ) ግድረጊያ ።
ጌታነህ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። (ወደ ፡) መገስገሻ ።
ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ ፲፬ ፡ ትውልድ ፡ ነው ። ከ እስከ ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ።

ያዕቆብ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ተሰደደ ። (ከ ጋር ፡) ተጫፋሪ ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተሰጠው ፡ ምሳሌ ፡ «ተቀበዩ ፡ ዮሴፍ ፡ ማድረጊያው ፡ አለ ንጋ ፡ መገስገሻው ፡ ቤት ፡ መነሻው ፡ አብርሃም ፡ መድረሻው ፡ ዳዊት ፡ ተጫፋሪው ፡ ልጆች ፡» የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ።

—43—

ዘርፍ ፡ የሚባለው ፡ በባለቤት ፡ ወይም ፡ በተሰቢ ፡ ላይ ፡ እየተደረበ ፡ በመስተዋ ድድ ፡ ተዛምዶ ፡ በለገንዘብን ፡ የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ ነው ። ዘርፍ ፡ አያያዥ ፡ « የ »ነው ።

በተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡ ላይ ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡ የራሱን ፡ አያያዥ ፡ የ ን ፡ ውጦ ፡ የተሰ ቢዎቹን ፡ መስተዋድድ ፡ ተሸክሞ ፡ ይንዘል ።

ምሳሌ ፡ የሰአል ፡ ቤት ፡ ፈረሰ ፡ (የባለቤት ፡ ዘርፍ ።

ዳዊት ፡ የሰአልን ፡ መንግሥት ፡ ወሰደ ። (የተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡ ዘርፍ ።)
ሴዴቅያስ ፡ ለፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ገዘረ ። (የተቀበይ ፡ ተሰቢ ፡ ዘርፍ ።)
ኤልያስ ፡ በአሰት ፡ ስረገሳ ፡ ወረገ ። (የማድረጊያ ፡ ተሰቢ ፡ ዘርፍ)
ዋሳውን ፡ ወደ ፡ ጌታውን ፡ ቤት ፡ ሄደ ። (የመገስገሻ ፡ ተሰቢ ፡ ዘርፍ ።)
ያዕቆብ ፡ ከፈርዖን ፡ አገር ፡ ደረሰ ። (የመድረሻ ፡ ተሰቢ ፡ ዘርፍ)
ያዕቆብ ፡ ከግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ኖረ ። (የተጫፋሪ ፡ ተሰቢ ፡ ዘርፍ ።)

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተሰጠው ፡ ምሳሌ ፡ የሳአል ፡ ቤት ፡ ፈረሰ ፡ የሳአልን ፡ መን

ግሥት ፡ መሰደ ፡ ባለጊዜ ፡ ዘርፍ ፡ አያያዝ ፡ ምልክት ፡ « የ » አልጠፋም ። በሌሎቹ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ « የ » ተውጦ ፡ ጠፍቶ ፡ የመስተዋድዱ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ እንደቆመ ፡ አስተውል ። በጭራም ፡ «ለየፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ገበረ ። በየአሳት ፡ ሰረገላ ፡ ወረገ ፤ ወደ ፡ የጌታውን ፡ ቤት ፡ ሄደ ። ከየፈርዖን ፡ አገር ፡ ደረሰ ። ከየግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ኖረ ። » አይባልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

—44—

ከግዕዝ ፡ የተወረሱ ፡ ባለዘርፍ ፡ የሆኑ ፡ ቃላት ፡ በአማርኛ ፡ ይገኛሉ ።

ምሳሌ ። ቤተ ፡ መንግሥት ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ቤተ ፡ ክህነት ፤ ሥጋ ፡ በዓል ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደግለት ፡ ነው ። እነዚህም ፡ እንደገና ፡ ዘርፍ ፡ ሆነው ፡ በሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡ የአማርኛውን ፡ ደንብ ፡ ይከተላሉ ። ይኸውም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጕልላት ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሹም ፡ እንደግለት ፡ ነው ።

፩ሺ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) ስሞች ፡ በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የሚመደቡባቸው ፡ ሙያዎች ፡ ስንት ፡ ናቸው ? ። ተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ? ። የመስተዋድድ ፡ ተሰቢ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ? ። በሰቤት ፡ ዘርፍ ፡ የተባሉት ፡ ቃላቸ ፡ ዓይነታቸው ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡ ነው ? ።

(ለ) ከባለቤትና ፡ ከዘርፍ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ቃላት ፡ ጸኖ ፡ ይተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡ ፲ ፡ ቃላት ፡ ጸኖ ። ከመስተዋድድ ፡ ተሰቢ ፡ ፲፩ ፡ ቃላት ፡ ጸኖ ።

(ሐ) ከዚህ ፡ ቦታች ፡ ከተጻፈው ፡ ምንባብ ፡ ላይ ፡ የስሞችን ፡ ሙያ ፡ እየለየህ ፡ ተናገር ።

ምንባብ ።

በሸዋ ፡ ስብስትያኖስ ፡ የሚባል ፡ መስፍን ፡ ነበር ። የቁልምጫ ፡ ስሙ ፡ ስብሲቴ ፡ ይባላል ። በ፲፯፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አባቱ ፡ ንጋሢ ፡ ኮርስቶስ ፡ ትንሬር ፡ ላይ ፡ ቢሞት ፡ አልጋውን ፡ ወረሰና ፡ ወጉንና ፡ ባላገሩን ፡ ሰብስቦ ፡ ስለ ፡ አባቱ ፡ ሞት ፡ ከአስለቀሰ ፡ በኋላ ፡ «እንግዲህ ፡ ስሜ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ነውና ፤ መርድ ፡ አዝማች ፡ ብለህ ፡ ሞራኝ ፡ አልዚያ ፡ እቀጣሃለሁ ። » ብሎ ፡ ለሕዝቡ ፡ አስታወቀ ። ስምን ፡ መልአክ ፡ ያወጣዋል ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ ስብስትያኖስ ፤ ጋሥጮን ፡ ወግቶ ፡ ካይፋት ፡ አስወጥቶአቸዋል ። መላ ፡ ግዛቱ ፡ ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ነው ። ቆይቶም ፡ ልጁ ፡ አብዬ ፡ ሸፈተበትና ፡ ጅላ ፡ ሚዳ ፡ በሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ በ፲፯፻፶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ተዋግቶአል ። በዚህም ፡ በውጊያው ፡ ላይ ፡ ስብስቴ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ አብዬ ፡ አልጋውን ፡ ወረሰ ።

ክፍል ፡ ፩ ፡ የስሞች ፡ ዝርዝር ፡ አፈታት ።

—45—

በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቃል ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡ ተለይቶ ፡ ሙያው ፡ እየተነገረ ፡ በተፍታታ ፡ ጊዜ ፡ ተዘርዝሮ ፡ ተፈታ ፡ ይባላል ። አሁንም ፡ የስሞችን ፡ ዝርዝር ፡ አፈታት ፡ ስናመለክት ፡ ዓይነታቸውንና ፡ ቁጥራቸውን ፡ ጸታቸውንና ፡ ሙያቸውን ፡ ለይቶ ፡ መናገር ፡ ያስፈልገናል ።

— 46 —

ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፈው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ስሞች ፡ በያንዳንዳቸው ፡ የሚዘረዘሩባቸውን ፡ አርእስቶች ፡ ያመለክታል ።

ዓይነት ፡	ጸታ ፡	ቁጥር ፡	ሙያ ፡
የተጸውዖ ፡ ስም ፡	ተባዕት ፡	ነጠላ ፡	ባለቤት ፡
የወል ፡ ስም ፡	እንስት ፡	ብዙ ፡	ተሰቢ ፡
የጥቅል ፡ ስም ፡	ግዑዝ ፡		ዘርፍ ፡
የቂላቊስ ፡ ስም ፡	የወል ፡		
የነገር ፡ ስም ፡			

ምሳሌ ፤ (ሀ) ልጆች ፡ ትምህርትን ፡ ይወዳሉ ።

«ልጆች» የወል ፡ ስም ፤ የወል ፡ ጸታ ፤ የብዙ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ባለቤት ፤ ባለቤት ፡ ነቱ ፡ ለአንቀጽ ፡ ይወዳሉ ፡ ነው ።

«ትምህርት» የነገር ፡ ስም ፤ ግዑዝ ፡ ጸታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ተሰቢ ፤ ተሰቢ ፡ ነቱ ፡ የአንቀጽ ፡ ይወዳሉ ፡ ነው ።

ን ፡ የገቢር ፤ ወይም ፡ የርቱዕ ፡ ተሰቢ ፡ ምልክት ።

ይወዳሉ ፡ ገቢር ፡ አንቀጽ ፡

(ለ) የጥሩነህ ፡ መጽሐፍ ፡ በወረቀት ፡ ተሸፍኖአል ።

«የ» መስተዋድድ ፡ ዘርፍ ፡ አያያዝ ፤ ጥሩነህ ፡ የሚባለውን ፡ ዘርፍ ፡ አያይዘአል ።

«ጥሩነህ ፡» የተጸውዖ ፡ ስም ፤ ተባዕት ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ዘርፍ ፡ በመስተዋድድ ፡ የ ፡ ተያይዘ ፡ ለመጽሐፍ ፡ ዘርፍ ፡ ሆኖአል ።

«መጽሐፍ ፡» የቁሳቊስ ፡ ስም ፤ ግዑዝ ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ባለቤት ፤ ባለቤትነቱ ፤ ለአንቀጽ ፡ ተሸፍኖአል ፡ ነው ።

«በ ፡» መስተዋድድ ፡ ሙያው ፡ ማድረጊያ ፡ መረቀት ፡ በሚለው ፡ ተሳቢ ፡ ላይ ፡ ገዥ ፡ ሆኖአል ።

«መረቀት ፡» የቁሳቊስ ፡ ስም ፤ ግዑዝ ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ተሳቢ ፤ በመስተዋድድ ፡ «በ ፡» ተገዝቶ ፡ የማድረጊያ ፡ ተሳቢ ፡ ሆኖአል ።

«ተሸፍኖአል ፡» ተገብሮ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

(ሐ) ተዋበች ፤ መጽሐፍዋን ፡ ይዛ ፡ ከጓደኞችዋ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄደች ።

«ተዋበች ፡» የተጸውዖ ፡ ስም ፡ እንስት ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ባለቤት ፤ ባለቤትነትዋ ፡ ለአንቀጽ ፡ ሄደች ፡ ነው ።

«መጽሐፍዋን ፡» የቁሳቊስ ፡ ስም ፤ ግዑዝ ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ተሳቢ ፤ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡ (ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡) «ይዛ ፡» ስፀአታል ።

«ይዛ ፡» ተውሳከ ፡ ግሥ ፡ (ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡)

«ከጓደኞችዋ ፡ ጋር ፡» የነገር ፡ ስም ፤ የወል ፡ ጾታ ፤ የብዙ ፡ ቁጥር ፤ ሙያ ፡ ተሳቢ ፤ በመስተዋድድ ፡ «ከ ፡ ጋር ፡» ተገዝቶ ፡ የአንቀጽ ፡ ሄደች ፡ ተሳቢ ፡ ሆኖአል ።

«ወደ ፡» መስተዋድድ ፡ ሙያው ፡ መገስገሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በሚለው ፡ ተሳቢ ፡ ላይ ፡ ገዥ ፡ ሆኖአል ።

«ትምህርት ፡ ቤት ፡» የቁሳቊስ ፡ ስም ፤ ግዑዝ ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ሙያ ፡ ተሳቢ ፤ በመስተዋድድ ፡ «ወደ ፡» ተገዝቶ ፡ የአንቀጽ ፡ «ሄደች ፡» ተሳቢ ፤ ሆኖአል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ።

—47—

መግለጫ ።

ተውላጠ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ በስም ፡ ፈንታ ፡ እየተተከ ፡ የሚገባ ፡ ቃል ፡ ነው ።

የተነገረውን ፡ ስም ፡ እንዳይደጋገም ፡ ለማድረግ ፡ ብንፈልግ ፡ በእርሱ ፡ ስፍራ ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ እንተከለን ። ይህም ፡ ተተክቶ ፡ የሚገባው ፡ ቃል ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ይላላል ። ትርጓሜው ፡ የስም ፡ ልዋጭ ፤ ወይም ፡ የስም ፡ ምትክ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምሳሌ ። «ገቦማንሽ ፡ የዝማንሽን ፡ መጽሐፍ ፡ ትወዳለች ። በመጽሐፉም ፡ የገቦማንሽን ፡ ትምህርት ፡ ታጠናለች ።» በማለት ፡ ፈንታ ፡ «ገቦማንሽ ፡ መጽሐፍዋን ፡ ትወዳለች ፤ በእርሱም ፡ ትምህርትዋን ፡ ታጠናለች ።» ብለን ፡ እንናገራለን ።

እነሆ ፡ «ዋ ፡ እርሱ ፡ ች ፡» በስሞቹ ፡ በገቦማንሽና ፡ በመጽሐፍ ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ተተኩ ፡ አስተውል ።

—48—

ተውላጠ ፡ ስም ፡ በስም ፡ ስፍራ ፡ የሚገባ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የስም ፡ እከል ፤ መሰል ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ጸታውና ፡ ቊጥሩ ፡ ምትክ ፡ የሆነበትን ፡ ስም ፡ እንዲመስል ፡ ያስፈልጋል ።

ክፍል ፡ ፩ ።

የተውላጠ ፡ ስም ፡ ዓይነቶች ።

—49—

ተውላጠ ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጻፉት ፡ በ፫ ፡ ታላላቅ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፈላል ።

ሀ) ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ምሳሌ ። እኔ ፡ አንተ ፡ እርሱ ፤ .....

ለ) አመልክች ፡ ተውላጠ ፡ ስም ። ምሳሌ ። ይህ ፤ ያ ፡ ው ፤ .....

ሐ) መጠይቅ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ። ምሳሌ ። ማን ፡ ምን ፤ የቱ ፤ .....

ከነዚህም ፡ ሌላ ፤ ድርብ ፤ መሸርን ፤ አጸፋ ፡ አገናዛቢ ፤ ..... የሚባሉ ፡ ንኡሳን ፡ ክፍሎች ፡ አሉ ። ሁሉም ፡ በየቦታቸው ፡ ይነገራሉ ።

—50—

(ሀ) ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ።

ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ከሰስት ፡ ላይ ፡ ተመድበው ፡ በሚነገሩት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ እየተተከ ፡ የሚገባው ፡ ቃል ፡ ነው ።

ራሱ ፡ ተናጋሪ ፡ ሲሆን ፤ በጅሮ ፡ መደብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ «እኔ ፤ እኛ ፤» የሚለው ፡ ነው ።

በአጠገብ ፡ ሆኖ ፡ የሚነጋገሩት ፡ ሲሆን ፡ በሩቅ ፡ መደብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ አንተ ፤ አንቺ ፤ እርስዎ ፤ እነአንተ ፡ የሚለው ፡ ነው ።

በሩቅ ፡ ሆኖ ፡ የሚነገርለት ፤ ወይም ፡ የሚነገርበት ፡ ግን ፡ በቅርብ ፡ መደብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ እርሱ ፤ እርስዋ ፤ እነርሱ ፡ እርሳቸው ፤ እነእርሳቸው ፡ የሚለው ፡ ነው ።

—51—

ምድቦች ፡ የተባሉት ፡ ዋነኞቹ ፡ የስም ፡ ምትኮች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በገበርዝር ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ። ከፊለ ፡ ቃል ፤ ተብ ፡ ማለት ፡ ተበሰት ፡ እን ፡ ማለት ፡ እንስት ፡ ማለት ፡ ነው ።

መደብ ፡	ጾታ	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	የአዝብሮት ፡ ቃል ።	
				ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ቅኖ ፡	ተብ.እን.	እኔ ፡	እኛ ፡	እርስዎ ፡	እነአንተ ፡
ያኖ ፡	ተብ.	አንተ ፡	እነአንተ ፡	እርስዎ ፡	እነአንተ ፡
	እን.	አንቺ ፡	እነአንተ ፡		
ርኖ ፡	ተብ.	እርሱ ፡	እነእርሱ ፡	እርሳቸው ፡	እነእርሳቸው ፡
	እን.	እርስዋ ፡	እነእርሱ ፡	እርሳቸው ፡	እነእርሳቸው ፡

—52—

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቁ ፡ 51 ፡ እንደሚታየው ፡ አንተ ፡ ብሎ ፡ እነአንተ ፡ እርሱ ፡ ብሎ ፡ እነእርሱ ፡ ተብሎ ፡ እንደተጻፈ ፡ አስተውል ።

የ«አ ፡» ፊደል ፡ ሌላውን ፡ አናግር ፡ ራሱ ፡ ተውጦ ፡ የሚቀር ፡ ስለሆነ ፡ በተለመደው ፡ ንግግር ፡ እነርሱ ፡ እነርሳቸው ፡ ተብሎ ፡ ይጻፋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የ ፡ አ ፡ ድምፅ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በንግግር ፡ ሊገለጽ ፡ የማያስፈልግ ፡ ቢሆን ፡ በጽሕፈት ፡ ጊዜ ፡ ሥርወ ፡ ፊደሉ ፡ እንዳይጠፋ ፡ ለማድረግ ፡ ደራሲው ፡ ያስገበታል ።

የአ ፤ ፊደላት ፡ የሚቀሩበት ፤ ወይም ፡ የማይቀሩበት ፡ ውሳኔ ፡ በየደጁ ፡ ይገኛል ።

—53—

ድርብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ።

ነገርን ፡ አስረግጦ ፡ ለመናገር ፡ ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አጽንዖተ ፡ ነገር ፡ በምድቦች ፡ ተውለጣተ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ እየተደረቡ ፡ የሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ አሉ ። እነእርሱም ፡ «ራስ ፤ ብገዛ ፡ እጅ ፤ ቅል ፤ » ናቸው ። በሰዋስው ፡ ደንብ ፡ ድርብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ።

ድርቦች ፡ ተውላጣተ ፡ ስም ፡ በዋነኞቹ ፡ ተውላጣተ ፡ ስም ፡ ደንብ ፡ እየተዘረዘሩ ፡ ይገባሉ ።

ምሳሌ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ አንተ ፡ ራስህ ፤ እኔ ፡ በገዛ ፡ እጄ ፡ አንተ ፡ በገዛ ፡ እጅህ ። እኔ ፡ ለቅሌ ፤ አንተ ፡ ለቅልህ ፡ . . . እንደማለት ፡ ነው ።

—54—

«ቅሉ ፡» ሳይዘረዝር ፡ አንተ ፡ ቅሉ ፤ እርሱ ፡ ቅሉ ፡ እያለ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ክፍሉ ፡ ከመስተፃምር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከተውሳጠ ፡ ስም ፡ አይደለም ። የትርጓሜውም ፡ ስሜት ፡ ራስን ፡ ሳይለቅ ፡ እንኳ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምሳሌ ፡ «እኔ ፡ ቅሉ» ወይም ፡ «እኔ ፡ ራሴ ፡ እንኳ» ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ።

ከሊቃውንት ፡ ወገን ፡ «እኔ ፡ ቅሌ ፡ አንተ ፡ ቅልህ ፡ እርሱ ፡ ቅሉ ፤ እርስዋ ፡ ቅልዋ ፤ እኛ ፡ ቅላችን ፡ እነአንተ ፡ ቅላችሁ» እነርሱ ፡ ቅላቸው ፡ እያለ ፡ በቮቱ ፡ መደቦች ፡ ይዘረዘራል ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ደራሲው ፡ የሚያጸናው ፡ የላይኛውን ፡ ውሳኔ ፡ ነው ።

—55—

ነገሩን ፡ በጣም ፡ ለማጠንከር ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ «እኔ ፡ ራሴ ፡ በገዛ ፡ እጄ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ በገዛ ፡ እጅህ ፡» እያለ ፡ እየተደራረበ ፡ ይገባል ። እንደዚህም ፡ ሲሆን ፡ እጽፍ ፡ ድርብ ፡ ተውሳጠ ፡ ስም ፡ ይባላል ።

—56—

መዘክር ፡ ተውላጠ ፡ ስም ።

የተዘነጋ ፡ ወይም ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ነገርን ፡ ለማስታወስ ፡ በስም ፡ ፈንታ ፡ እያስገባን ፡ የምንነጋገርበት ፡ ቃል ፡ መዘክር ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ይባላል ። ትርጓሜው ፡ አስታዋሽ ፡ የስም ፡ ምትክ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

ዓይነት ፡	ጾታ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
የሰው ፡ ስም ፡ መዘክር ፡	ተብ.	እገሌ ፡	እነእገሌ ፡
	እን.	እገሊት ፡	እነእገሊት ፡
	ተብ.እን.	እንተን ፡	እነእንተን ፡
የነገር፡መዘክር፡	ግዑዝ.	እንትን ፡	እንትኖች ፡

ምሳሌ ፡ «ያስቆጠ ፡ መጥቱ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አስበ ፡ ሰለ ፡ ስሙ ፡ ስጊዜው ፡ የተዘነጋው ፡ እንደሆነ ፡ «እገሌ ፡» መጥቶ ፡ ነበር ፤ ወይም ፡ «እንተን ፡» መጥቶ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡

ስሙን ፥ እያሰላሰለ ፥ ይናገራል ። «እንተን ፥ » በማለት ፥ ፈንታ ፥ አንዳንድ ፥ ጊዜ ፥ «እን ተና ፥ » ብሎ ፥ በማጋነን ፥ ይናገረዋል ።

እንደዚሁም ፥ ደግሞ ፥ «መጽሐፉን ፥ ስጠኝ ፥ » ለማለት ፥ እስበ ፥ ሳለ ፥ ስሙ ፥ ከአፉ ፥ የጠፋበት ፥ እንደሆነ ፥ «እንትኑን ፥ » ስጠኝ ፥ ይላል ። የሚናገረው ፥ ስለ ፥ ቦታ ፥ ሲሆን ፥ ግን ፥ «እንትና ፥ » ይላል ፥ ይኸውም ፥ ወደ ፥ እንክዐር ፥ እሄዳለሁ ፥ በማለት ፥ ፈንታ ፥ ወደ ፥ «እንትና ፥ » እሄዳለሁ ፥ ይላል ፥ ማለት ፥ ነው ።

— 57 —

«እገሌ ፥ የሚለው ፥ ቃል ፥ በምድብ ፥ ተውላጠ ስም ፥ እየተመራ ፥ ስሙ ፥ ላልታወቀ ፥ ሰው ፥ ሁሉ ፥ መዘክር ፥ ሆኖ ፥ ስለሚገባ ፤ «እኔ ፥ እገሌ ፥ ነኝ ፥ አንተ ፥ እገሌ ፥ ነህ ፥ አርሱ ፥ እገሌ ፥ ነው ። . . . እያለ ፥ በመሆን ፥ አንቀጽ ፥ ብቻ ፥ ቦርቱም ፥ መደበኞች ፥ ሊረዳ ፥ ይቻላል ።

በሌሎቹ ፥ አንቀጾች ፥ ግን ፤ ስሚ ፥ ባለቤት ፥ ሲሆን ፥ በዚኛው ፥ መደብ ፥ በትእ ዛዝ ፥ አንቀጽ ፥ ይነገራል ።

ምሳሌ ፥ «እገሌ ፤ ወይም ፥ እንተን ፥ ትምህርትን ፥ አጥና » ይላል ። በዚህም ፥ ጊዜ ፥ ቃለ ፥ አጋሞ ፥ «ሆይ ፥ » ሙስጠ ፥ ታዋቂ ፥ ሆኖ ፥ ተሠውሮ ፥ ቀርቶአል ።

ሰሚ ፥ ባለቤት ፥ ያልሆነ ፥ እንደሆነ ፥ ግን ፥ በዚኛው ፥ መደብ ፥ በማንኛውም ፥ አን ቀጽ ፥ ይነገራል ። ይኸውም ፥ «እገሌ ፥ መጣ ፤ እንተን ፥ መጥቶ ፥ ነበር ፥ ወይም ፥ ይምጣ » እንደማለት ፥ ነው ።

« እንተን ፥ እነእንተን ፥ » በማለት ፥ ፈንታ ፤ « እንቶኔ ፥ እነእንቶኔ ፥ » ተብሎ ፥ የሚነገርበት ፥ አገር ፥ አለ ። « እነ » አጎናኝ ፥ አብዝር ፥ ነው ። (ተ. ቁ. 35 ፥ አይ ፥)

— 58 —

ምድብ ፥ ተውላጠ ፥ ስም ፥ እንደሌላው ፥ ስም ፥ ሁሉ ፥ ተጠቃሽ ፥ ተሳቢ ፥ ዘርፍ ፥ የመስተዋድድ ፥ ተገዥ ፥ ይሆናል ።

ተጠቃሽ ፥ ተሳቢ ፥ ሲሆን ፥ እኔን ፥ እንተን ፥ እንቺን ፥ . . . ይላል ።

ዘርፍ ፥ ሲሆን ፥ የእኔ ፥ የአንተ ፥ የአንቺ ፥ . . . ይላል ።

የመስተዋድድ ፥ ተገዥ ፥ ሲሆን ፤ ለእኔ ፥ ለአንተ ፥ ለአንቺ ፤ . . . ይላል ።

ሌሎቹም ፥ መስተዋድዳን ፤ በ ፤ ወደ ፥ ስለ ፥ ከ—ጋር ፤ . . . . እንደዚሁ ፥ ይገባሉ ።

— 59 —

(ለ) አመልከች ፥ ተውላጠ ፥ ስም ።

አመልከች ፥ ተውላጠ ፥ ስም ፥ የሚባለው ፥ በፈት ፥ ወይም ፥ በኋላ ፤ ለሚነገረው ፥ ስም ፥ አጸፋ ፥ የሚሆን ፥ ቃል ፥ ነው ። በስተፊት ፥ ወይም ፥ በስተኋላው ፥ የሚገኘውም ፥ ስም ፥ አጸፋ ፥ ተቀባይ ፥ ይባላል ።

— 60 —

አመልከች ፥ ተውላጠ ፥ ስም ፥ አንዳንድ ፥ ጊዜ ፥ አጸፋዊ ፥ ተውላጠ ስም ፥ ተብሎ ፥ ይጠራል ። አጸፋ ፥ በብዙ ፥ ቃል ፥ ይተረጐማል ። በዚህ ፥ ክፍል ፥ ግን ፥ ድጋሚ ፥ ማለት ፥ ነው ።

— 61 —

በአመልከች ፥ ተውላጠ ፥ ስም ፥ ክፍል ፥ ከ፫ንገሩት ፥ ቃላት ፥ ዋነኞቹ ፥ እነዚህ ፥ የሚከተሉት ፥ ናቸው ።

ጾታ ፥	ነጠላ ፥		ብዙ ፥	
	የቅርብ ፥	የሩቅ ፥	የቅርብ ፥	የሩቅ ፥
ተባ.	ይህ ፥ (ይኸ)	ያ ፥	እነዚህ ፥ ወይም ፥ እኒህ ፥ (እነይህ ፥)	እነዚያ ፥ ወይም ፥ እኒያ ፥ (እኒያ ፥)
እን.	ይህች ፥	ያች ፥	እሊህ ፥	እሊያ ፥
የወል ፥	ኛው ፥	ኛው ፥	ኞች ፥	ኞች ፥

ከዚህ ፥ በላይ ፥ የተጻፉት ፥ ቃላት ፥ አመልከች ፥ ቅጽል ፥ ወይም ፥ አመልከች ፥ ተው ላጠ ፥ ስም ፥ ለመሆን ፥ ይችላሉ ። (ቁ 110—113 ፥ አይ) ። ልዩነታቸውም ፥ የሚታወቀው ፥ በአገባባቸው ፥ ነው ።

ስምን ፥ ተክትለው ፥ በገቡ ፥ ጊዜ ፥ ክፍላቸው ፥ ከአመልከች ፥ ቅጽል ፥ ነው ። ስምን ፥ ሳይከተሉ ፥ በቂ ፥ ሆነው ፥ በተነገሩ ፥ ጊዜ ፥ ግን ፥ ክፍላቸው ፥ ከአመልከች ፥ ተውላጠ ስም ፥ ይሆናል ።

ምሳሌ ። « ይህ » መጽሐፍ ፥ የወ፡በሸት ፥ ነው ። (አመልክች ፥ ቅጽል ።) የው፡በሸት ፥ መጽሐፍ ፥ « ይህ » ነው ። (አመልክች ፥ ተውላጠ ፥ ስም ።

— 62 —

« ይህ ፥ ያ » ከመስተዋድዳን ፥ ጋር ፥ ሆነው ፥ በተገዙ ፥ ጊዜ ፥ የግዕዙ ፥ ቃል ፥ « ዘ » ጥንታዊ ፥ ስፍራውን ፥ ሲፈልግ ፥ ይታያል ።

ምሳሌ ። እንደዚህ ፥ ስዚህ ፥ በዚህ ፥ ስለዚህ ፥ እንደዚያ ፥ ስዚያ ፥ በዚያ ፥ ስለዚያ ፥ ከላይ ፥ በቁ. 61 ፥ የተጻፈው ፥ « ይህ ፥ ያ » የሚለውም ፥ ቃል ፥ ወደ፡በኩነት ፥ ሲለወጥ ፥ እንዚህ ፤ እነዚያ ፤ እንዳሰኝ ፥ አስተውል ።

አማርኛ ፥ ከግዕዝ ፥ የተወለደ ፥ ስለሆነ ፥ የግዕዙን ፥ ቃል ፥ አንዳንድ ፥ ጊዜ ፥ ጣልቃ ፥ አስገብቶት ፥ ይገኛል ።

— 63 —

« ይህ ፤ ያ ፥ እነዚህ ፤ እነዚያ ፥ . . . » ዘተባሉት ፥ አመልክች ፥ ተውላጣተ ፥ ስም ፥ ላይ ፥ በንጠላ ፥ « ኛው » እየተጨመረባቸው ፥ ይነገራሉ ። በብዙ ፥ ሲሆን ፥ ግን ፥

«ዋች » ያሰኛሉ ፤ ወይም ፡ ያለምንም ፡ ተጨማሪ ፤ አጸፋ ፡ ይሆናሉ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የማ ረጋገጥን ፡ ምግባር ፡ ያመለክታሉ ።

ምሳሌ ። (ሀ) « ያኖው » መጽሐፍ ፡ የውብሸት ፡ ነው ። (አመልካች ፡ ቅጽል ፡)

የውብሸት ፡ መጽሐፍ ፡ « ያኖው » ፡ ነው ፡ (አመልካች ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡)

(ለ) አጋዘኖችና ፡ ላሞች ፡ ሁሉም ፡ እንስሳ ፡ ናቸው ።

«እነዚያ » ፡ ወይም « እነዚያኞች ፡ » (=አጋዘኖች) ፡ የዱር ፡ እንስሳ ፡ ይባላሉ ።

እነዚህ ፡ ወይም ፡ እነዚህኞች ፡ (=ላሞች ፡) የቤት ፡ እንስሳ ፡ ይባላሉ ።

— 64 —

ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ተጫፍረው ፡ በተነኩ ፡ ጊዜ ፡ የሩቁ ፡ አጸፋ ፡ ለፊተኛው ፤ የቅ ርቡ ፡ አጸፋ ፡ ለኋለኛው ፤ ስም ፡ አመልካች ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ። እኔ ፡ ዜግንና ፡ ቅኔን ፡ ተምሬአለሁ ። ይኸኛውን ፡ (=ቅኔ ፡) ከጎጃም ፡ ያኛውን ፡ (=ዜማ ፡) ከቤገምድር ፡ ተማርሁት ።

— 65 —

መድረሻውን ፡ ሳድስ ፡ ከሚያደርግ ፡ ቃል ፡ በቀር ፡ የቀሩት ፡ ቃላት ፡ አንድ ፡ ዓይ ነት ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ በተነጻጸሩ ፡ ጊዜ ፡ « ው » የሚል ፡ ቃል ፤ ለዘያ ፡ ለተነገረው ፡ ስም ፡ ተተክቶ ፡ አጸፋ ፡ ይሆናል ። መድረሻውን ፡ ሳድስ ፡ የሚያደርገውም ፡ ቃል ፡ ሳድሱ ፡ ወደ ፡ ከፅብነት ፡ ይለወጣል ፤ ወይም ፡ ሳድሱ ፡ ሳይለወጥ ፡ አጸፋ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ። (ሀ) የቄላ ፡ አየር ፡ ከደጋው (=አየር ፡) ይልቅ ፡ ይቀዘቅዛል ።

(ለ) የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ዐሐይ ፡ (=ብርሃን) አይደለም ።

የፀሐዩ ፡ (=ብርሃን ፡) ይሞቃል ፤ የጨረቃው (=ብርሃን ፡) አይሞቅም ።

— 66—

አጸፋ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ።

በግሶች ፡ ላይ ፡ አየተጫኑ ፡ የአርዕያ ፡ መሪ ፡ የሚሆኑት ፡ ቃላት ፡ በግብራቸው፡ ግሣውያን ፡ አጸፎች ፡ ይባላሉ ። ክፍላቸውም ፡ ከአመልካች ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ቃላት ፡ የባለቤት ፡ ዝርዝር ፡ የተሰቢ ፡ አጸፋ ፡ ተብለው ፡ ይመደባሉ ። እንደ ፡ ግብራቸውስ ፡ ድርብ ፡ ባለቤት ፤ ድርብ ፡ ተሰቢ ፡ መባል ፡ በተገባቸው ፡ ነበር ።

ግሣውያን ፡ አጸፎች ፡ በጠቅላላ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጸፉት ፡ ናቸው ።

መደብ ፡	ጾታ ፡	የባለቤት ፡ ዝርዝር ፡		የተሰቢ ፡ አጸፋ ፡	
		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፤	ተባ. እን.	ሁ ፤ ኝ ፤	ን ፤	ኝ ፤	ን ፤
፪ኛ ፤	ተባ.	ህ ፤	(አ) ችሁ ፤	ህ ፤	(አ) ችሁ ፤
	እን.	ሽ ፤	(አ) ችሁ ፤	ሽ ፤	(አ) ችሁ ፤
	ተባ.እን.ኤ	(ካፅብ ፡)	(አ) ችሁ ፤	ም ፤	(አ) ችሁ ፤
፫ኛ ፤	ተባ.	ግፅዝ ፡ ወይም ፤ ራብዕ ፡	(ካፅብ)	ው ፤	(አ) ቸው ፤
	እን.	(አ) ት ፤	(ካፅብ)	(አ) ት ፤	(አ) ቸው ፤

ይህ ፡ (*) ምልክት ፡ በተደረገበት ፡ መስመር ፡ ላይ ፡ የተጸፉት ፡ ቃላት ፡ በአክብ ሮት ፡ መንገድ ፡ ለወንድ ፡ ወይም ፡ ለሴት ፤ የሚነገሩ ፡ ናቸው ።

በቅንፍ ፡ ተከበው ፡ የሚታዩት ፡ የ ፡ «አ» ፊደላት ፡ በሥርወ ፡ ነገሩ ፡ አያሉ ፡ በንግ ግር ፡ ልማድ ፡ ተውጠው ፡ የሚቀሩት ፡ ናቸው ። ግፅዝ ፤ ካፅብ ፡ ራብዕ ፡ ተብሉ ፡ ምልክት ፡ የተደረገባቸውም ፡ ስፍራዎች ፡ የየግሡን ፡ መድረሻ ፡ ከመለወጥ ፡ በቀር ፡ እንደሌሎች ፡ ልዩ ፡ ፊደል ፡ የሌላቸው ፡ ቃላት ፡ ናቸው ።

— 67 —

ግሣውያን ፡ አጸፎች ፡ የግሥ ፡ አርዕያ ፡ መሪ ፡ በሚሆኑበት ፡ በዘሃው ፡ ጊዜ ፡ የአ ጸፋነት ፡ ግብራቸውን ፡ ይፈጽማሉ ። የባለቤት ፡ ዝርዝር ፡ ወይም ፡ የተሰቢ ፡ አጸፋ ፡ የሚ ሆኑበትን ፡ ግብር ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በያንዳንዱ ፡ እየዘረዘርን ፡ እንገልጻለን ።

— 68 —

የባለቤት ፡ ዝርዝር ። ፊልግ ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ እያረባን ፡ እናሳያለን ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፤	ተባ.እን.	ሁ ፡=እኔ ፡ (ፈለግሁ ፡)	ን ፡=እኛ ፡ (ፈለግን ፡)
፪ኛ ፤	ተባ.	ህ ፡=አንተ ፡ (ፈለግህ ፡)	አችሁ=አነጋገሮ ፡ (ፈለጋችሁ ፡)
	እን.	ሽ ፡=አንቺ ፡ (ፈለግሽ ፡)	» » »
፫ኛ ፤	ተባ.	(ግፅዝ ፡ ይነገራል ፤)	(ካፅብ ፡ ይነገራል ።)
	እን.	ች ፡=እርስዋ ፡ (ፈለገች ፤)	» »

— 69 —

የባለቤት ፡ ዝርዝር ፡ የተባሉት ፡ ተውላጣተ ፡ ስም ፡ ‹‹የመሆን ፤›› ግሥ ፡ ላይ ፡ ሲረቡ ፡ ጥቂት ፡ አመል ፡ ይለውጣሉ ፤ እነእርሱም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

መደብ ፡	ጾታ ፡	ነጠላ ፡	የብዙ ፡
፩ኛ ፤	ተባ. እን.	ኘ ፡=እኔ ፡(ነኘ ፡)	ን ፡=እኛ ፡(ነን ፤)
፪ ፤	ተባ.	ሀ ፡=አንተ ፡(ነህ ፤)	አችሁ=እነአንተ ፡(ናችሁ፡)
	እን.	ሽ ፡=አንቺ ፡(ነሽ ፤)	» » » »
	ተባ.እን.	ዎ ፡=አርስዎ ፡(ነዎ ፤)	» » » »
፫ ፤	ተባ.	ው ፡=እርሱ ፡(ነው ፤)	(አ)ቸው ፡=እነእርሱ ፡(ናቸው ፤)
	እን.	(አ)ት=እርስዋ ፡(ናት ፤)	» » » »

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያመለከትነው ፡ የመሆን ፡ አንቀጽ ፡ ‹ነ› ፡› ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በእርሱም ፡ ላይ ፡ የአርባታ ፡ መሪዎች ፡ እንደተጨመሩበት ፡ አስተውል ።

— 70 —

የ ተ ሳ ቢ ፡ አ ጸ ፋ ።

የተሳቢ ፡ አጸፋ ፡ ነገሩ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ሁለት ፡ ዓይነቶች ፡ አሉት ። እነእር ሱም ፡ በየግብራቸው ፡ (ሀ) የተጠቃሽ ፡ ተሳቢ ፡ አጸፋ ፡ (ለ) የኮቀባይ ፡ ተሳቢ ፡ አጸፋ ፡ ይባላሉ ።

(ሀ) የተጠቃሽ ፡ ተሳቢ ፡ አጸፋ ። ‹‹ለገኘ›› በሚል ፡ አንቀጽ ፡ እያረባን ፡ እናሳያለን ።

መደብ ፡	ጾታ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡	ተባ.እን.	ኘ ፡=እኔን ፡(ለገኘኝ ፡)	ን ፡=እኛን ፡(ለገኘን ፡)
፪ኛ ፡	ተባ.	ሀ ፡=አንተን ፡(ለገህ ፡)	አችሁ ፡=እናንተን ፡(ለገኘችሁ ፡)
	እን.	ሽ ፡=አንቺን ፡(ለገኘሽ ፡)	» » »
	ተባ.እን	ዎ ፡=እርስዎን ፡(ለገኙዎ ፡)	» » »
፫ኛ ፡	ተባ	(ው፡=እርሱን ፡(ለገኘው ፡)	ኣቸው ፡=እነእርሱን ፡(ለገኟቸው፡)
	እን	(ት ፡=እርሱን ፡(ለገኘችው ፡)	» » »
		(አ)ት=እርስዋን ፡(ለገኟት ፡)	» » »

(ለ) የኮቀባይ ፡ ተሳቢ ፡ አጸፋ ። ‹‹ሰጠ›› በሚል ፡ አንቀጽ ፡ እያረባን ፡ እናሳያለን ።

መደብ ፡	ጾታ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡	ተባ.እን.	ኘ ፡=ለእኔ ፡(ሰጠኝ ፡)	ን ፡=ለእኛ ፡ (ሰጠን ፡)
፪ኛ ፡	ተባ.	ሀ ፡=ለአንተ ፡(ሰጠህ ፡)	(አ) ችሁ=ለእነአንተ (ሰጣችሁ)
	እን.	ሽ ፡=ለአንቺ ፡(ሰጠሽ ፡)	» » »
	ተባ.እን.	ዎ ፡=ለእርስዎ ፡(ሰጠዎ ፡)	» » »
፫ኛ ፡	ተባ.	ው ፡=ለእርሱ ፡(ሰጠው ፡)	አ)ቸው=ለእነእርሱ(ሰጣቸው
	እን.	ት ፡=ለእርሱ ፡(ሰጠችት ፡)	» » »
		(አ)ት=ለእርስዋ ፡(ሰጣት ፡)	» » »

በዚህ ፡ ሕግ ፡ የሚረቡ ፡ ግሦች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። እነእርሱም ፡ የመስ ጠትን ፡ ግብር ፡ የሚያሳዩት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ ዝርዝሩን ፡ በግሥ ፡ ክፍል ፡ ተመ ልከት ፡ (ቁ. 172 እይ ።)

— 71 —

ማስገንዘቢያ ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሮ ፡ ተ. ቁ. የተጻፉት ፡ የተጠቃሽና ፡ የተቀ ባይ ፡ አጸፎች ፡ የረቡት ፡ ከፎቱ ፡ የአርባታ ፡ መደቦች ፡ በአንደኛው ፤ ‹ እርሱ ፡ › በሚ ለው ፡ መደብ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ አስተውል ። የቀሩትም ፡ ፯ቱ ፡ መደቦች ፡ እንደ ፡ ሕጋ ችው ፡ በዚው ፡ ዓይነት ፡ ይረባሉ ።

— 72 —

በቁ. 70 ፡ የተጻፉት ፡ አጸፎች ፡ ከመስተዋድዳን ፡ ክፍል ፡ ‹ ለ ፤ በ› ፡ እየተጨመ ሩላቸው ፡ ይዘረዘራሉ ። ከእነእርሱም ፡ አብዛኞቹ ፡ ትራስ ፡ የሚሆናቸውን ፡ የአ ፡ ፊደ ላት ፡ እየቀጠሩ ፡ ድምፃቸውን ፡ እየመረሉ ፡ ይነገራሉ ።

በ፩ኛ ፡ መደብ ፡ ‹ ልኝ ፡ ብኝ ፤ ልን ፤ ብን ፤ › ይላል ።
በ፪ኛ ፡ መደብ ፤ ልህ ፤ ልሽ ፤ ልዎ ፤ ብህ ፤ ብሽ ፤ ብዎ ፤ በሞው ፤ ይላል ።
በ፫ኛ ፡ መደብ ፡ ለት ፤ ላት ፤ በት ፤ ባት ፤ ላቸው ፡ ፤ በችው ፤ ይላል ።
ል ፡ የበን ፡ ፤ ‹ በ ፡ የክፉ ፡ መፍታ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ። ፈለገልኝ ፡ =ስለእኔ ፡ ወይም ፡ ለእኔ ፡ ብሎ ፡ ፈለገ ።

ፈለገብኝ ፡ =በእኔ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ እኔን ፡ ለመጉዳት ፡ ብሎ ፡ ፈለገ ።
የቀረውንም ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ አካሄድ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

— 73 —

አገናዛቢ ፣ አጸፋ ። ።

በስሞች ፣ ላይ ፣ እየተጨመሩ ፣ ባለንብረትን ፣ የሚጠቅሱ ፣ ተውላጣተ ፣ ስም ፣ አገ ናዛቢ ፣ አጸፋ ፣ ይባላሉ ። ዋቂቶች ፣ ብቻ ፣ ሲለወጡ ፣ የቀሩት ፣ በሮ ፣ ተ. ቁ. የተጸፉት ፣ ናቸው ። እነእርሱንም ፣ በሚከተለው ፣ እናሳያለን ።

መደብ ፣ ጾታ ፣		ነጠላ ፣	ብዙ ፣
፩ኛ ፣	ተባ.እን.	ዩ=የእኔ ፣(ጌታዩ=የእኔ ፣ጌታ ፣)	አ) ችን፣የእኛ-(ጌታችን=የእኛ ፣ጌታ
፪ኛ ፣	ተባ.	ሀ=የአንተ ፣(ጌታህ=የአንተ ፣ጌታ)	አ) ችሁ=የእነአንተ=ጌታችሁ
	እን.	ሽ=የአንቺ፣(ጌታሽ=የአንቺ፣ጌታ ፣	=የእነአንተ ፣ ጌታ ፣)
	ተባ.እን.	ዎ=የእርስዎ(ጌታዎ-የእርስዎ፣ጌታ	» » »
፫ኛ ፣	ተባ.	ው=የእርሱ(ጌታው=የእርሱ፣ጌታ	» » »
	እን.	ዋ=የእርስዋ(ጌታዋ፣የእርስዋ ጌታ	አ) ዋው=የእነርሱ ፣ ጌታዋው ፣
			=የእነርሱ ፣ ጌታ ፣)
			» » »

— 74 —

በግዕዝ ፣ ቋንቋ ፣ « የ » የነበረው ፣ ቃል ፣ በአማርኛ ፣ « ዩ » ተብሎ ፣ ተለውጠ አል ። ይኸውም ፣ ቃል ፣ መድረሻው ፣ ሳድስ ፣ በሆነ ፣ ስም ፣ ላይ ፣ ሲገባ ፣ ራሱ ፣ ተውጦ ፣ ሳድሱን ፣ ኃምስ ፣ ያደርገዋል ።

ምሳሌ ። « ቤትዩ ፣ ፈረስዩ ፣ » በማለት ፣ ፊንታ ፣ ቤቴ ፣ ፈረሴ ፣ ይላል ።

እንደዚሁም ፣ ደግሞ ፣ በእ ፣ ፊደል ፣ የሚነሡት ፣ አገናዛቢዎች ፣ ድምፃቸውን ፣ ለተከታዮቻቸው ፣ እያወረሱ ፣ ተውጠው ፣ ይቀራሉ ።

ምሳሌ ። « ጌታአችን ፣ ፈረስአችን ፣ በማለት ፣ ፊንታ ፣ « ጌታችን ፣ ፈረሳችን ፣ ይላል ።

—75—

(ሐ) መጠይቅ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፣

መጠይቅ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፣ የሚባለው ፣ አንዳች ፣ ነገር ፣ የሚጠየቅበት ፣ ቀለ ነው ። « መጠይቅ ፣ » ከግስዝ ፣ የመጣ ፣ ቃል ፣ ነው ። ትርጓሜው ፣ የሚያረጋግጥ ፣ ጠያቂ ፣ እረጋጋጭ ፣ ግለት ፣ ነው ።

— 76 —

መጠይቃን ፣ ተውላጣተ ፣ ስም ፣ እነዚህ ፣ ናቸው ።

« ማን ? ምን ? የቱ ? »

« ማን ፣ » ለሰው ፣ « ምን ፣ » ለነገር ፤ « የቱ ፣ » ለሰውም ፣ ለነገርም ፣ ጥያቄ ፣ መጠ የቂያ ፣ ይሆናል ። ሁሉንም ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ እንዘረዝራቸዋለን ።

ዓይነት ፣	የሰው ፣ መጠየቅ ፣		የነገር ፣ መጠየቅ ፣	
	ነጠላ ፣	ብዙ ፣	ነጠላ ፣	ብዙ ፣
ባለቤት ፣	ማን ?	እነማን ?	ምን ?	ምኖች ?
ተሰቢ ፣	ማንን ፣ ማን ?	እነማንን ፣ እነማን ?	ምንን ፣ ምን ?	ምኖችን ?
አገናዛቢ ፣	የማን ?	የእነማን ?	የምን ?	የምኖች ?
አማራጭ ፣	የቱ ?	የትኞች ?	የቱ ?	የትኞች ?

ከነዚህ ፣ ከተጸፉት ፣ ዋቂቶቹን ፣ በምሳሌ ፣ እንገልጻለን ።

ከሰማይ ፣ ማን ፣ መረደ ? ፣ . . . . . (የግሥ ፣ ባለቤት)

ምን ፣ ትሳለህ ፣ . . . . . (የግሥ ፣ « አለ ፣ » ተሰቢ ፣)

ነቢይ ፣ ስለማን ፣ ይናገራል ? . . . . . (የመስተዋድድ ፣ ተገዥ)

ያ ፣ የማን ፣ መጽሐፍ ፣ ነው ? . . . . (አገናዛቢ ፣)

ከእነዚህ ፣ ልጆች ፣ የቱ ፣ ይበልጣል ? . . . (አማራጭ ፣)

— 77 —

« ምን ፣ » የመሆን ፣ አንቀጽ ፣ ሲጨመርበት ፣ ፊደሉን ፣ ቀንሶ ፣ በጠበቀ ፣ ድምፅ ፣ ይነገራል ። ምነው ? (=ምን ፣ ነው ?)

ምሳሌ ፣ « ምንድን ፣ » ወይም ፣ « ምንድር ፣ » (=ምን ፣ ነገር ፣) በስም ፣ ላይ ፣ ተጭኖ ፣ ስለገባ ፣ በአመል ፣ መደቅጽል ፣ ይሰባል ።

— 78 —

« ማን ? የቱ ? » እንደ ፣ አመልካች ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፣ « ኛው » ፣ እየተጨመረ ብኖው ፣ ማንኛው ? የትኛው ? ተብለው ፣ ይነገራሉ ፤ በዚህም ፣ ጊዜ ፣ ግብራቸው ፣ አማ ራጭነት ፣ ነው ።

— 79 —

« ምን » በማድነት ፣ አኳኋን ፣ ሲነገር ፣ የአንክሮ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፣ ይባላል ። ምሳሌ ፤ ምን ፣ ሰነፍ ፣ ልጅ ፣ ነው ! ምነዋ ፣ ልጂ !

፭ኛ ፡ መልመጃ ።

1. ተውላጠ ፡ ስም ፡ በስንት ፡ ክፍሎች ፡ ይከፈላል ?

   ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነው ?

   (ሀ) የመጀመሪያውንና ፡ የሁለተኛውን ፡ መደብ ፡ የስም ፡ ምትክች ፡ ንገረኝ ።

   (ለ) የሰስተኛውን ፡ መደብ ፡ የስም ፡ ምትክች ፡ ጻፍ ።

2. ድርብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ ተናገር ፤

   ከድርብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ፱ ፡ ቃላት ፡ ጻፍ ፤

3. መዘክር ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ ንገረኝ ።

   ቃሉንም ፡ በያንዳንዱ ፡ ለይተህ ፡ አስታውቀኝ ፤

4. ከአመልካች ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ክፍል ፡ ፲፪ ፡ ቃላትን ፡ ተናገር ፤

   (ሀ) ‹ይህ ፡ ያ ፡› የተባሉትን ፡ በምሳሌ ፡ አድርገህ ፡ አስታውቅ ።

   (ለ) ግሣውያን ፡ አቤርች ፡ የተባሉትን ፡ ቁጠራቸው ።

   (ሐ) የባለቤት ፡ ዝርዝር ፡ ከተባሉት ፡ ላይ ፡ የግሥ ፡ ቃላትን ፡ እየጨመርህ ፡ አርባ ።

   (መ) የተጠቃሽ ፡ ተሳቢ ፡ አጸፎች ፡ በተባሉት ፡ ላይ ፡ ፫ ፡ የግሥ ፡ ቃላትን ፡ እየጨመርህ ፡ አርባ ። የተቀባይ ፡ ተሳቢ ፡ አጸፎች ፡ የተባሉትንም ፡ በ፱ ፡ ግሦች ፡ አርባቸው ።

5. አገናዛቢ ፡ አጸፋ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ ግለጽ ።

   በ፭ ፡ ስሞች ፡ ላይ ፡ እየዘረዘርህ ፡ ምሳሌ ፡ ስጠኝ ።

6. መጠየቅ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ የተባሉትን ፡ ቁጠራቸው ። ‹ምን ፡ ማን ፡ የቱ ፡›

   እንዴት ፡ እንደሚገቡ ፤ ፫ ፡ ምሳሌ ፡ ጻፍልኝ ።

7. ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፈው ፡ ምንባብ ፡ በተውላጠ ፡ ስም ፡ ደንብ ፡ የሆኑትን ፡ ቃላት ፡ እየለየህ ፡ አስታውቅ ።

ም ን ባ ብ ።

የስብስቴን ፡ አልጋ ፡ የወረሰ ፡ ልጁ ፡ መርድ ፡ አጭጮች ፡ አብዩ ፡ ነው ። እርሱ ፡ ደጋ ፡ ደጋውን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርስት ፡ እያደረገ ፡ ቄሳ ፡ ቄሳውንቷ ፡ ለበላንርና ፡ ለወታደር ፡ እየሰጠ ፡ አገሩን ፡ ያቀናው ፡ ጀመር ።

በዘመኑ ፡ የነበሩት ፡ የጎንደሩ ፡ ንጉሥ ፡ የአጼ ፡ በካፋ ፡ ልጅ ፡ ጳጳሚ ፡ ኢያሱ ፡ ነበሩ ። እናታሞው ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ የቋራ ፡ ባላባት ፡ ልጅ ፡ ስለሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡

ቋረኛ ፡ ኢያሱ ፡ ይበሳሉ ። እርሳቸውም ፡ መኳንንቶቻቸውን ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑልንና ፡ ራስ ፡ መዳጀን ፡ የጦር ፡ አዝማቾች ፡ አድርገው ፡ ወር ፡ ላኩበት ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዩ ፡ ዓይኔ ፡ የምትባለውን ፡ የንጋሣጌ ፡ ከተማ ፡ ምሽግ ፡ አደርጎ ፡ ቄያቸውና ፡ ሁሉቱን ፡ የጦር ፡ አበጋዞች ፡ ገጠማቸው ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ተማረከ ። ራስ ፡ ወዳጀ ፡ ግን ፡ በጭንቅ ፡ አመለጠ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የጎንደር ፡ ጭፍራ ፡ ተማረከና ፡ አገሩን ፡ አጥለቀለቀው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የጎንደርን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተማረ ፡ ይባላል ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዩ ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚገባ ፡ ምርኮ ፡ ሞቹን ፡ እየጠያየቀ ፡ ሥርዓቱን ፡ ደንቡን ፡ ይጎበዝብ ፡ ጀመር ። መርድ ፡ አዝማች ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደገዛ ፡ ሞተና ፡ በሐር ፡ አምባ ፡ ቀዳስ ፡ ሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበረ ። ልጁ ፡ አምኃየስ ፡ አልጋውን ፡ ወረሰ ።

ክፍል ፡ ፪ ፡ የተውላጠ ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ አፈታት ።

—80—

ተውላጠ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ስም ፡ ተዘርዝሮ ፡ ይፈታል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዓይነቱን ፡ መደቡን ፡ ጾታውን ፡ ቁጥሩን ፡ ሙያውን ፡ ለይቶ ፡ መናገር ፡ ያስፈልጋል ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፈው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ የሚዘረዘርበት ፡ አርአስተ ፡ ያመለክታል ።

ዓይነት ፡	መደብ ፡	ጾታ ፡	ቁጥር ፡	ሙያ ፡
ምድብ ፡ አመልካች ፡ መጠይቅ ፡	፩ኛ ፡ ፪ኛ ፡ ፫ኛ ፡	ተባዕት ፡ እንስት ፡ የወል ፡ ግዑዝ ፡	ነጠላ ፡ ብዙ ፡	ባለቤት ፡ ተሳቢ ፡ ዘርፍ ፡ አገናዛቢ ፡ አጸፋ ፡

ምሳሌ ፡ እኔ ፡ አናቴን ፡ አመዳለሁ ፤ እርስዋም ፡ ትወደኛለች ።

«እኔ» ምድብ ፡ ተ.ስ. ፩ኛ ፡ መደብ ፡ የወል ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ሙያው ፡ ባለ ቤት ፡ ባለቤትነቱ ፡ ለአንቀጽ ፡ አመዳለሁ ።

«አናቴን» ፡ (አናት ፡ ዬ ፡) የወል ፡ ስም ፡ እንስት ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ሙያው ፡ ተሳቢ ፡ ተሳቢነቱ ፡ የአንቀጽ ፡ አመዳለሁ ።

(፩) አመልካች ፣ ተ.ስ. ይኛ ፣ መደብ ፣ የወል ፣ ጾታ ፤ ነጠላ ፣ ቁጥር ፣ ሙያው ፣ አገናዛቢ ፣ እናት ፣ ከሚለው ፣ ቃል ፣ ጋር ፣ ተስማምቶ ፣ ሳድሱን ፣ ኃምስ ፣ አድርጎ ፣ ውስጠ ፣ ቀሪ ፣ ሆኖ ፣ በለገንዘቡን ፣ ያመለክታል ። እናትዬ ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ እናቴ ፣ ብለ ል ። «ን» ፣ አመልካች ፣ ቅጽል ፣ ነው ።

« እወዳለሁ ፣ » (=እወድ ፣ አለ ፣ ሁ ፣) ግሥ ፤ ገቢር ። አንቀጽ ።

« ሁ » አመልካች ፣ ተ.ስ. ይኛ ፣ መደብ ፣ የወል ፣ ጾታ ፤ ነጠላ ፣ ቁጥር ፣ ሙያው ፣ አጸፋ ፣ አጸፋነቱ ፣ ለባለቤቱ ፣ ለእኔ ፣ ነው ።

« እርስዋም ፣ » (=እርስዋ ፣ ም ፣) ምድብ ፣ ተ.ስ.ይኛ ፣ መደብ ፣ አንስት ፣ ጾታ ፤ ነጠላ ፣ ቁጥር ፣ ሙያው ፣ ባለቤት ፣ ባለቤትነቱ ፣ ለአንቀጽ ፣ ትወደኛለች ፣ ነው ።

« ትወደኛለች ፣ » (=ትወደ ፣ ኝ ፣ አለች ፣) ግሥ ፣ ገቢር ፣ አንቀጽ ፣

"ኝ ፣ ,(=እኔን ፣) አመልካች ፣ ተ.ስ. ይኛ ፣ መደብ ፣ የወል ፣ ጾታ ፣ ነጠላ ፣ ቁጥር ፣ ሙያ ው ፣ ተሳቢ ፣ ተሳቢነቱ ፣ የአንቀጽ ፣ ትወድ ፣ አለች ፣ ነው ። የወደኋሳውን ፣ ፊደል ፣ ግዕዝ፣ አድርጎ ፣ የወደፊቱን ፣ ፊደል ፣ አን ፣ ው.ጠ ፣ ራሱ ፣ ኛ ፣ (ትወደኛለች ፣) ተብሎ ፣ በራሰ ፣ ተነግሮአል ።

ምዕራፍ ፣ ፪ ፣ ቅጽል ።

—81—

መግለጫ ፣ በስሞች ፣ ወይም ፣ በነገሮች ፣ ላይ ፣ እየተጨመረ ፣ ትርጓሜያቸውን ፣ የሚገልጽ ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ቅጽል ፣ ይባላል ። በሀረፍተ ፣ ነገር ፣ ውስጥ ፣ እንዳች ፣ ነገር ፣ በተ ነገረ ፣ ጊዜ ፣ ምን ፣ ዓይነት ? ስንት ? የቱ ? ወይም ፣ የትኛው ? የሚል ፣ ጥያቄ ፣ ይገቸመን ፣ ይሆናል ። ይህን ፣ የጥያቄውን ፣ ቃል ፣ ለመምለትም ፣ ሌላ ፣ ቃል ፣ እንድንጨምርበት ፣ ግድ ፣ ይሆንብናል ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እየጨመርን ፣ የነገሩን ፣ ትርጓሜ ፣ የምንገልጽበት ፣ ቃል ፣ ቅጽል ፣ የሚባለው ፣ ነው ።

ምሳሌ ፣ መኰንን ፣ ፈረስ ፣ አለው ።

ጥ. ስንት ? ም. አንድ ፣ ፈረስ ፤
ጥ. ምን ፣ ዓይነት ? ም. ጥቁር ፣ ፈረስ ።
ጥ. የትኛው ፣ ነው ? ም. ይኸኛው ፣ ፈረስ ፣ ነው ።

እነሆ ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ የተነገሩት ፣ «አንድ» «ይህ ፣ » ቁቁር ፣ » ቅጽሎች ፣ ናቸው ። ስለ ፣ ፈረሱ ፣ አኳኋን ፣ ለተጠየቀውም ፣ ጥያቄ ፣ የሚያስፈልገውን ፣ ትርጓሜ ፣ እየገለጸ ፣ እንዳስረዱ ፣ አስተውል ።

— 82 —

ቅጽል ፣ በስም ፣ ላይ ፣ ተጨምሮ ፣ በተነገረ ፣ ጊዜ ፣ ተከታይ ፣ ወይም ፣ ዘርፍ ፣ አስ ተኔ ፣ ይባላል ። ይኸውም ፣ ጥቁር ፣ ፈረስ ፤ ነጭ ፣ ልብስ ፤ እንደማለት ፣ ነው ። ስምን ፣ ሳይ ከተል ፣ ለብቻው ፣ በተነገረ ፣ ጊዜ ፣ ግን ፣ በቂ ፣ ይባላል ። በቂ ፣ መባሉም ፣ ለሚነገረው ፣ የግሥ ፣ ቃል ፣ ባለቤት ፣ ወይም ፣ ተሳቢ ፣ ሆኖ ፣ ሊገባ ፣ የሚችል ፣ ስለሆነ ፣ ነው ። ይኸውም ፣ «ፈረሱ ፣ ጥቁር ፣ ነው ፤ ክፉን ፣ በክፉ ፣ አትቃወሙት ፣ » እንደማለት ፣ ነው ።

— 83 —

ቅጽል ፤ ውስጠ ፣ የ ፣ ግልጽ ፣ የ ፣ የሚባል ፣ አመል ፣ አለው ። ውስጠ ፣ የ ፣ የሚባ ለው ፣ ግሣውያን ፣ መስተዋምራን ፣ «የ ፣ የም ፣ የሚ ፣ የግ ፣ » በንባብ ፣ ሳይጨመሩበት ፣ በምሥጢር ፣ ብቻ ፣ የሚገኙበት ፣ ቃል ፣ ነው ። ግልጽ ፣ የ ፣ የሚባለው ፣ ግን ፣ «የ ፣ የም ፣ የሚ ፣ የግ ፣ » በወቢይ ፣ አንቀጽ ፣ ላይ ፣ እየገቡ ፣ የሚገኙበት ፣ ቃል ፣ ነው ።

ምሳሌ ፤

ተከታይ ፣ ቅጽል ፤	ጥቁር ፣ ፈረስ ፣ አለኝ ፤	(ውስጠ ፣ የ)
	የጠቆረ ፣ ፈረስ ፣ አለኝ ፤	(ግልጽ ፣ የ)
በቂ ፣ ቅጽል ፤	ፈረሱ ፣ ጥቁር ፣ ነው ፤	(ውስጠ ፣ የ)
	ፈረሱ ፣ የጠቆረ ፣ ነው ፤	(ግልጽ ፣ የ)

— 84 —

«የ ፣ » ዘርፍ ፣ አያያዥ ፣ ሆኖ ፣ የሚገባበት ፣ ስም ፣ ወይም ፣ ነገር ፣ አንጻንድ ፣ ጊዜ ፣ ቅጽል ፣ ይሆናል ። በንባብ ፣ ዘርፍ ፣ እየመሰለ ፣ በምሥጢር ፣ ግብርን ፣ ያመለክታል ። ይህን ፣ የመሰለ ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ዘርፍ ፣ አስተኔ ፣ ቅጽል ፣ ተብሎ ፣ ተሰይሞአል ።

ምሳሌ ፣ «የገ'ማነህ ፣ ቤት ፣ » ትልቅ ፣ ነው ፣ (ዘርፍ ፤)

«የግንብ ፣ ቤት ፣ » ብዙ ፣ ዘመን ፣ ይኖራል ። (ዘርፍ ፣ አስተኔ ፣ ቅፍል ፣)

እነሆ ፣ «የሆግነህ ፣ ቤት ፣ » የሚለው ፣ ቃል ፣ የቤቱ ፣ ጌታ ፣ ገ'ማነህ ፣ መሆኑን ፣ ስለሚያመለክት ፣ ዘርፍ ፣ ነው ። « የግንብ ፣ ቤት ፣ » የሚለው ፣ ግን ፣ ቤቱ ፣ የተገነበ ፣ መሆ ኑን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የቤቱ ፣ ጌታ ፣ ግንብ ፣ መሆኑን ፣ አያስረዳንም ። ስለዚህም ፣ ይህን ፣ የመሰለው ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ዘርፍ ፣ አስተኔ ፣ ቅጽል ፣ ተብሎአል ።

ክፍል ፣ ፩ ።

— 85 —

የቅጽል ፣ አመሠራረት ።

ቅጽል ፣ ከስሞች ፣ ላይ ፣ ሊመሠረት ፣ ይችላል ። እንደ ፣ ግዕዝ ፣ ደንብ ፣ ዊ ፣ በስ ሞች ፣ ላይ ፣ በተጨመረ ፣ ጊዜ ፣ የወንን ፣ ወይም ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፣ ይሆናል ፤ ተባ ጾታ

በነጠላ ፣ ቁጥር ፣ ዊ ፣ በብዙ ፣ ቁጥር ፣ ውያን ፣ እን ፡ ጸታ ፡ በነጠላ ፣ ቁጥር ፣ ዊት ፣ በብዙ ፣ ቁጥር ፣ ውያት ፣ ያሰኛል ፤ ይኸውም ፣ እንደሚከተለው ፣ ነው ።

ስም ፣	ተባ ፡ ጸታ ፡		እን ፡ ጸታ ፡	
	ነጠላ ፣	ብዙ ፣	ነጠላ ፣	ብዙ ፣
ያዕቆብ ፣	ያዕቆባዊ ፣	ያዕቆባውያን ፣	ያዕቆባዊት ፣	ያዕቆባውያት ፣
እስራኤል ፣	እስራኤላዊ ፣	እስራኤላውያን ፣	እስራኤላዊት ፣	እስራኤላውያት ፣
ኢትዮጵያ ፣	ኢትዮጵያዊ ፣	ኢትዮጵያውያን ፣	ኢትዮጵያዊት ፣	ኢትዮጵያውያት ፣
እንግሊዝ ፣	እንግሊዛዊ ፣	እንግሊዛውያን ፣	እንግሊዛዊት ፣	እንግሊዛውያት ፣
እንስሳ ፣	እንስሳዊ ፣	እንስሳውያን ፣	እንስሳዊት ፣	እንስሳውያት ፣
መጽሐፍ ፣	መጽሐፋዊ ፣	መጽሐፋውያን ፣	መጽሐፋዊት ፣	መጽሐፋውያት ፣
ብርሃን ፣	ብርሃናዊ ፣	ብርሃናውያን ፣	ብርሃናዊት ፣	ብርሃናውያት ፣

ከዚህ ፣ በላይ ፣ የተጻፈው ፣ የቅጽል ፣ ደንብ ፣ በተጻውሮ ፣ ስም ፣ ላይ ፣ ሲገባ ፣ የወገን ፣ ቅጽል ፣ ይሆናል ። በሌሎቹ ፣ ስሞች ፣ ላይ ፣ ሲገባ ፣ ግን ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፣ ነው ።

— 86 —

የወገን ፣ ቅጽል ፣ በአማርኛ ፣ ደንብ ፣ ሲነገር ፣ እንደሚከተለው ፣ ይሆናል ።

(ሀ) መድረሻው ፣ ከሰብ ፣ ወይም ፣ ሰብዕ ፣ የሆነ ፣ የበታ ፣ ስም ፣ ዬ ፣ እየተጨመረ በት ፣ የወገን ፣ ስም ፣ ይሆናል ።

(ለ) መድረሻው ፣ ግልስ ፣ ወይም ፣ ራብዕ ፣ ወይም ፣ ሳድስ ፣ የሆነ ፣ የበታ ፣ ስም ፣ የመድረሻ ፣ ፊደሉን ፣ ወደ ፣ ኃምስነት ፣ ለውጠ ፣ የወገን ፣ ቅጽል ፣ ይሆናል ።

(ሐ) መድረሻው ፣ ኃምስ ፣ የሆነ ፣ የበታ ፣ ስም ፣ ግን ፣ ምንም ፣ ሳይለወጥ ፣ ያው ፣ ራሱ ፣ የወገን ፣ ቅጽል ፣ ይሆናል ። ይህንንም ፣ ሁሉ ፣ በሚከተለው ፣ እናመለክታለን ።

	የበታ ፣ ስም ።	ወገን ፣ ቅጽል ።	
ከሰብ ፣	የኛ ፣	የኛዬ ፣	(=የየኛ ፣ ሰው ፣)
	ጅሩ ፣	ጅሩዬ ፣	(=የጅሩ ፣ ሰው ፣)
	ወሎ ፣	ወሎዬ ፣	(=የወሎ ፣ ሰው ፣)
ሳብዕ ፣	ሲዳሞ ፣	ሲዳሞዬ ፣	(=የሲዳሞ ፣ ሰው ፣)
ግልስ ፣	አሩሲ ፣	አሩሲ ፣	(=የአሩሲ ፣ ሰው ፣)
ራብዕ ፣	ላስታ ፣	ላስቲ ፣	(=ላስታ ፣ ሰው ፣)
	ሸዋ ፣	ሸዋ ፣	(=የሸዋ ፣ ሰው ፣)
	ቆጣ ፣	ቆጪ ፣	(=የቆጣ ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ ዚማ ፣)
	ቡልጋ ፣	ቡልጊ ፣	(=የቡልጋ ፣ ሰው ፣)
	ወግዳ ፣	ወግዲ ፣	(=የወግዳ ፣ ሰው ፣)

ኃምስ ፣	መራቤቴ ፣	መራቤቲ ፣	(=የመራቤቴ ፣ ሰው ፣)
	ሰላሌ ፣	ሰላሌ ፣	(=የሰላሌ ፣ ሰው ፣)
	አጋሜ ፣	አጋሚ ፣	(=የአጋሚ ፣ ሰው ፣)
	ግሺ ፣	ግሺ ፣	(=የግሺ ፣ ሰው ፣)
ሳድስ ፣	ሆላንድ ፣	ሆላንዲ ፣	(=የሆላንድ ፣ ሰው ፣)
	ሞሪት ፣	ሞሪቲ ፣	(=የሞሪት ፣ ሰው ፣)
	ተጉለት ፣	ተጉለቲ ፣	« የተጉለት ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ ዜግ ፣ »
	ጎንደር ፣	ጎንደሬ ፣	(=የጎንደር ፣ ሰው ፣)
	ጎጃም ፣	ጎጃሜ ፣	(=የጎጃም ፣ ሰው ፣)

— 87 —

ከዚህ ፣ በላይ ፣ በአማርኛ ፣ ደንብ ፣ የተጻፈው ፣ የወገን ፣ ቅጽል ፣ በብዛት ፣ ጊዜ ፣ እንደ ፣ ስም ፣ ደንብ ፣ ይበዛል ። ይህም ፣ ጎንደሬ ፣ ጎንደሮች ፣ እንደማለት ፣ ነው ። አመል ከች ፣ ቅጽል ፣ ሳይጨመርበት ፣ በተነገረ ፣ ጊዜም ፣ ሁሉንም ፣ ጸታ ፣ ያስተባብራል ። ይኸውም ፣ እገሌ ፣ ጎንደሬ ፣ ነው ፣ እገሊት ፣ ጎንደሬ ፣ ናት ፣ ያሰኛል ፣ ማለት ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ አመልከች ፣ ቅጽል ፣ የተጨመረበት ፣ እንደሆነ ፣ ጎንደሬው ፣ ጎንደሬይቱ ፣ እያለ ፣ ተባዕትና ፣ እንስት ፣ ጸታውን ፣ ይለያል ።

—88—

የበታን ፣ ስም ፣ ወገን ፣ ቅጽል ፣ ለማድረግ ፣ በተፈለገ ፣ ጊዜ ፣ ስሙ ፣ የአማርኛውን ፣ ወይም ፣ የግዕዙን ፣ ደንብ ፣ የማይከተል ፣ ልሆን ፣ በዘርፍ ፣ እያያዝ ፣ ይገለጻል ።

ምሳሌ ፤ —ከፈ ፣ ወይም ፣ ከፋዊ ፣ ብሎ ፣ በመናገር ፣ ፈንታ ፣ የከፋ ፣ ሰው ፣ ሊባል ፣ ይቻላል ፣ ማለት ፣ ነው ። እንዲህም ፣ ሆኖ ፣ ሲገባ ፣ ዘርፍ ፣ እስተኔ ፣ ወገን ፣ ቅጽል ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ።

— 89 —

የወታ ፣ ስም ፣ (አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ የጥቅል ፣ ስም ፣) ኛ ፣ የሚል ፣ ቃል ፣ በተጨመረበት ፣ ጊዜ ፣ ድንቁን ፣ ወይም ፣ የሀገርን ፣ ልማድና ፣ ባህል ፣ ያመለክታል ። መድረሻው ፣ ከሰብ ፤ ግልስ ፤ ኃምስ ፤ ሳድስ ፤ ሳብዕ ፣ የሆነ ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ፊደሉ ፣ ሳይለወጥ ፣ ኛ ፣ ይጨመርበታል ። መድረሻው ፣ ራብዕ ፣ የሆነ ፣ ቃል ፣ ግን ፣ የመጨረሻ ፣ ፊደሉ ፣ ሳድስ ፣ ሆኖ ፣ ኛ ፣ ይጨመርበታል ።

ምሳሌ ፤

ከዕብ ፡	የኛ ፡	የኛኛ ፡	(=የየኛ ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ ባህል ፡ ሀገር ፡)
	ድሩ ፡	ድሩኛ ፡	(=የድሩ ፡ » » »)
ግእስ ፡	አሩሲ ፡	አሩሲኛ ፡	(=የአሩሲ ፡ » » »)
ራብዕ ፡	አማራ ፡	አማርኛ ፡	(=የአማራ ፡ ነገድ ፡ ቋንቋ ፡)
	ወለጋ ፡	ወለጋኛ ፡	(=የወለጋ ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ በህል ፡ ሀገር ፡)
	ጋላ ፡	ጋልኛ ፡	(=የጋላ ፡ ነገድ ፡ ቋንቋ ፡)
	ከምባታ ፡	ከምባትኛ ፡	(=የከምባታ ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)
ኃምስ ፡	ሱማሌ ፡	ሱማልኛ ፡	(=የሱማሌ ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)
	አደሬ ፡	አደርኛ ፡	(=የአደሬ ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)
ሳድስ ፡	አገው ፡	አገውኛ ፡	(=የአገው ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)
	እንግሊዝ	እንግሊዝኛ ፡	(=የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)
	ወረብ ፡	ወረብኛ ፡	(=የወረብ ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)
	ጎንደር ፡	ጎንደርኛ ፡	(=የጎንደር ፡ ባህል ፡ ወይም ፡ ንግግር ፡
ሳብዕ ፡	ሲዳሞ ፡	ሲዳሞኛ ፡	(=የሲዳሞ ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)
	ወላሞ ፡	ወላሞኛ ፡	(=የወላሞ ፡ ሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡)

— 90 —

ቅጽል ፡ ከወል ፡ ስምና ፡ ከቁሳቊስ ፡ ስም ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ። ቅጥያ ፡ የሚሆኑ ትም ፡ ሬደላት ፡ ኛ ፤ ም ፤ ማ ፤ ናቸው ። እነእርሱም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ እየገቡ ፡ በሕ ርይን ፡ ወይም ፡ ግብርን ፡ ወይም ፡ ወገንነትን ፡ ያመለክታሉ ።

ምሳሌ ፤ ስም ፡ ቅጽል ፡

ተራራ ፡	ተራራማ ፡ ወይም ፡ ተራራም ፡	(=ተራራ ፡ የበዛበት ፡ አገር ፡)
ድንጋይ ፡	ድንጋያማ ፡ ወይም ፡ ድንጋያም ፡	(=ድንጋይ ፡ የበዛበት ፡ ስፍራ ፡)
ቄላ ፡	ቄለኛ ፡	(=በቄላ ፡ የሚኖር ፡)
ደጋ ፡	ደገኛ ፡	(=በደጋ ፡ የሚኖር ፡)
ከተማ ፡	ከተመኛ ፡	(=የከተማ ፡ ባህል ፡)
ፈረስ ፡	ፈረሰኛ ፡	(=ፈረስን ፡ መጋለብ ፡ የሚያውቅ ፡)
ጦር ፡	ጠረኛ ፡	(=የጦርን ፡ ሥራ ፡ የሚያውቅ ፡)
ወንጀል ፡	ወንጀለኛ ፡	(=ወንጀልን ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡)

— 91

በመል ፡ ስም ፡ ክፍል ፡ የሚነገሩ ፡ የአካላት ፡ ስሞችና ፡ ሌሎች ፡ እንዳንድ ፡ ነገ ሮች ፡ ጌ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ እየተጨመረባቸው ፡ በተነገሩ ፡ ጊዜ ፡ አጠገብነትን ፡ እየገለጹ ፡ አመልካች ፡ ቅጽል ፡ ይሆናሉ ።

ምሳሌ ፡ ስም ፡ ቅጽል ፡

ራስ ፡ ራስጌ ፡ (=በራስ ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ በራስ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡)
እጅ ፡ እጅጌ ፡ (=በእጅ ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡)
አንገት ፡ አንገትጌ ፡ (=በአንገት ፡ በኩል ፡ የሚገኝ ፡)
ወገብ ፡ ወገብጌ ፡ (=በወገብ ፡ በኩል ፡ ያለ ፡)
ጸር ፡ ጸርጌ ፡ (=በጸር ፡ በሰል ፡ የሆነ ፡)

እነዚህ ፡ ቃላት ፡ በምሥጢር ፡ የበታች ፡ ቅጽሎች ፡ ስለሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ተናግረናቸዋል ። ሌላው ፡ ስፍራቸውም ፡ በተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

— 92 —

ቅጽል ፡ ከነገር ፡ ስም ፡ ላይ ፡ ይመሠረታል ። አብዛኛው ፡ የነገር ፡ ስም ፡ መሠረቱ ፡ ከግሥ ፡ ቃል ፡ ስለሆነ ፡ ከነገር ፡ ስም ፡ ላይ ፡ የሚገኘውም ፡ ቅጽል ፡ ጥሩ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ግማሹ ፡ ቅጽል ፡ ተከታይ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሲገባ ፡ ይችላል ። ተከታይ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ማለት ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ተ. ቁ. 82 ፡ ተመልከት ።

ከአርእስት ፡ ላይ ፡ ሲመሠረት ፡ — መግደል ፡ ብሎ ፡ መግደያ ፤ መግረፍ ፡ ብሎ ፡ መግረፍያ ፤ ማንበብ ፡ ብሎ ፡ ማንበቢያ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡ በታን ፡ ወይም ፡ ዕቃን ፡ የሚ ያመለክት ፡ ነው ።

ከጥሬ ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ ሲመሠረት ፡— ክፉት ፡ ብሎ ፡ ክፋተኛ ፤ ወይም ፡ ክፉትም ፡ ነገር ፡ ብሎ ፡ ነገረኛ ፡ ቁመት ፡ ብሎ ፤ ቁመታም ፡ ብርሃን ፡ ብሎ ፡ ብርሃናዊ ፡ ይላል ። ይኸ ውም ፡ በሕርይንና ፡ ግብርን ፡ የሚየመለክት ፡ ነው ።

— 93 —

ቅጽል ፡ ከግሥ ፡ ክፍል ፡ ይገኛል ፤ ውስጠ ፡ የ ፤ ድጋፍ ፡ ፈላጊ ፤ ሳድስ ፡ ቅጽል ፡ መስተምራዊ ፡ ቅጽል ፡ ተብሎ ፡ ይከፈላል ። ውስጠ ፡ የ ፤ እና ፡ ድጋፍ ፡ ፈላጊ ፡ ቅጽል ፡ የወንድንና ፡ የሴትን ፡ ጾታ ፡ ለይተው ፡ አያስታውቁም ፤ የቀሩት ፡ ግን ፡ እየለዩ ፡ ያስታ ውሱ ።

(ሀ) ውስጠ ፡ የ ፡ የሚባለው ፡ ቅጽል ፤ አስተግሪ ፤ ፈላጊ ፤ ጸሐፊ ፤ አሞግቂ ፤ ገላይ ፤ ነጋቢ ፤ ጥቁር ፡ ቀይ ፡ . . . ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ። ግሥ ፡ በአዕማድ ፡ መን

ገድ ፣ ውስጥ ፣ የ ፤ ቅጽሎችን ፣ ያስገኛል ። ይኸውም ፣ »ፈላጊ ፣ አስፈላጊ ፣ አፈላላጊ ፤ አፋላጊ ፤ ተፈላጊ ፤ ተፈላላጊ ፤ ተፋላጊ ፤ «እንደማለት ፣ ነው ።

(ለ) ድጋፍ ፣ ፈላጊ ፣ የሚባለው ፣ ቅጽል ፣ ገብ ፤ ወለድ ፤ አደር ፤ አበድ ፤ . . . ይህን ፣ የመሰለ ፣ ሁሉ ፣ ነው ።

ምሳሌ ፤ «ውሃ-ገብ ፣ መሬት ፣ አለኝ ።

ልብ-ወለድ ፣ ታሪክ ፣ ጽፈአለሁ ።

ተግፊው ፣ ጠም-አደር ፣ ነው ።

አውቆ-አበድ ፣ መነሸሌ ፣ ያታልላል ፣ »እንደማለት ፣ ነው ።

እነሆ ፣ ውሃ ፤ ልብ ፤ ጦም ፤ ፀውቆ ፤ የተባሉት ፣ ቃላት ፣ ከወደኋላው ፣ ተጨምረው ፣ ለቅጽሉ ፣ ድጋፍ ፣ እንደሆኑት ፣ አስተውል ። ይህን ፣ የመሰለውም ፣ ቃል ፣ በንኡስ ፣ ጭረት ፣ ተጋግሞ ፣ እንዲጻፍ ፣ ሙሴን ፣ ተደርጎል ። ንኡስ ፣ ጭረት ፣ የተባለውም ፣ (-) ነው ።

(ሐ) ሳድስ ፣ ቅጽል ፣ የሚባለው ፣ አማርኛ ፣ ከግዕዝ ፣ የወረሰውና ፣ በአካሄድም ፣ የግዕዙን ፣ ደንብ ፣ የሚከተለው ፣ ቃል ፣ ነው ።

ምሳሌ ፤

ተባ.	ነጠላ ፣	ከቡር ፣	ልዑል ፣	ቅዱስ ፣	ብፁዕ ፣	ሕያው ፣
	ብዙ ፣	ከቡራን ፣	ልዑላን ፣	ቅዱሳን ፣	ብፁዓን ፣	ሕያዋን ፣
አን.	ነጠላ ፣	ክብርት ፣	ልዕልት ፣	ቅድስት ፣	ብፅዕት ፣	ሕያውት ፣
	ብዙ ፣	ክቡራት ፣	ልዑላት ፣	ቅዱሳት ፣	ብፁዓት ፣	ሕያዋት ፣

(መ) መስተየምራዊ ፣ ቅጽል ፣ የሚባለው ፣ በወጪይ ፣ አንቀጽ ፣ ላይ ፣ በጎላፊ ፣ የ ፣ በአሁንና ፣ በትንቢት ፣ የም ፤ የሚ ፤ የማ ፤ እየተጨመሩበት ፣ የሚነገረው ፣ ቃል ፣ ነው ። አንላንድ ፣ ጊዜም ፣ በግብሩ ፣ ግጨጸ ፣ የ ፤ ታዉሎ ፣ ይጠራል ። ይኸውም ፣ እንደሚከተለው ፣ ነው ፦

በጎላፊ ፣ ሲገባ ፣ የ ፤ የመጣ ፤ የሄደ ፤ የለበሰ ፣ . . . ይላል ።

በአሁንና ፣ በትንቢት ፣ ሲገባ ፣ የም ፤ የምመጣ ፣ የምሄድ ፤ የምለብስ ፤ ይላል ።
የሚ ፤ የሚመጣ ፤ የሚሄድ ፤ የሚለብስ ፤ ይላል ።
የማ ፣ የማይመጣ ፤ የማይሄድ ፤ የማይለብስ ፣ ይላል ።

ከንባር ፣ ስምና ፣ ከግሥ ፣ ክፍል ፣ የሚመሠረቱ ፣ ቅጽሎች ፣ ተከታይ ፣ ወይም ፣ በቂ ፣ ሆነው ፣ ይቀጸላሉ ። ተከታይ ፣ በቂ ፣ ማለት ፣ ምን ፣ እንደሆነ ፣ ካሁን ፣ በፊት ፣ በ82 ተ. ቁ. አመልክተናል ።

—95—

ቅጽል ፣ ከተውሰከ ፣ ግሥ ፣ ላይ ፣ በተዘዋዋሪ ፣ መንገድ ፣ ይመሠረታል ። አዘዋወሩም ፣ እንደሚከተለው ፣ ነው ። በመጀመሪያ ፣ ተውሰከ ፣ ግሡ ፣ የንባር ፣ ስም ፣ መደመሆን ፣ ይለወጥና ፣ በዚያ ፣ ላይ ፣ ቅጽሉ ፣ ይመደባል ። ይኸውም ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፣ ነው ።

ምሳሌ ፤	ተውሰከ ፣ ግሥ ፣	የንባር ፣ ስም ፣	ቅጽል ፤
	ጸጥ ፣	ጸጥታ ፣	ጸጥተኛ ፣
	ዝም ፣	ዝምታ ፣	ዝምተኛ ፣
	ዝግ ፣	ዝግታ ፣	ዝግተኛ ፣
	ከፍ ፣	ከፍታ ፣	ከፍተኛ ፣
	ዝቅ ፣	ዝቅታ ፣	ዝቅተኛ ፣
	አል ፣	አሉታ ፣	አሉተኛ ፣

—96—

ቅጽል ፣ ከመስተዋድድ ፣ ከፍል ፣ ይመሠረታል ። ይኸውም ፣ በታን ፣ ወይም ፣ ጊዜን ፣ የሚያመለክት ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፣ ነው ።

ምሳሌ ፤	መስተዋድድ ፣	ቅጽል ፤
	ላይ ፣	ላይኛ ፣
	ታች ፣	ታችኛ ፣
	ፊት ፣	ፊተኛ ፣
	ኋላ ፣	ኋለኛ ፣
	መከከል ፣	መካከለኛ ፣

ከፍል ፣ ፪ ፣ የቅጽል ፣ ዓይነቶች ፣

—97—

ቅጽል ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ ፴ተጸፉት ፣ በቮ ፣ ታላላቅ ፣ ክፍሎች ፣ ይከፈላል ። እነርሱም ፣ ደግሞ ፣ በንኡሳን ፣ ከፍሎች ፣ ተከፍለው ፣ ይመደባሉ ።

፩ኛ ፣ የዓይነትና ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፤

(ሀ) የመገን ፣ ቅጽል ፤ ኢትዮጵያዊ ፤ ጎንደሬ ፤ አማርኛ ፣ . . .
(ለ) የግብር ፣ ቅጽል ፤ መልከም ፤ ደግ ፣ ዮር ፤ . . .
(ሐ) የዓይነት ፣ ቅጽል ፤ ቀይ ፤ ጥቁር ፤ ረጅም ፤ አጭር . . .

ቅጽሉን ፣ ለማግኘት ፣ ምን ፣ ዓይነት ? ወይም ፣ እንዴት ፣ ያለ ? ተብሎ ፣ ይጠየቃል ።

ዩኛ ፣ የአጎዝና ፣ የመጠን ፣ ቅጽል ።

(ሀ) የተወሰነ ፣ አጎዝ ፤ አንድ ፤ ሁለት ፤ ሶስት ፣ አንደኛ ፤ ሁለተኛ . . .
(ለ) ያልተወሰነ ፣ አጎዝ ፤ አያሌ ፣ ጥቂት ፣ ሁሉ ፣ . . .

ቅጽሉን ፣ ለማግኘት ፣ ስንት ? ወይም ፣ ምን ፣ ያህል ? ተብሎ ፣ ይጠየቃል ።

ዩኛ ፣ አመልካች ፣ ቅጽል ።

(ሀ) የተወሰነ ፣ አመልካች ፤ ይህ ፤ ያ ፤ ይህች ፣ . . .
(ለ) ያልተወሰነ ፣ አመልካች ፣ ው ፤ ዋ ፤ ዩቱ ፣ . . .
(ሐ) ጠቃሽ ፤ አመልካች ፤ ን ፣
(መ) አዛማጅ ፤ ቅጽል ፤ የ ፤ የም ፤ . . .

ቅጽሉን ፣ ለማግኘት ፣ የትኛው ? ወይም ፣ ማንኛው ? ተብሎ ፣ ይጠየቃል ።

በአመልካች ፣ ቅጽል ፣ ክፍል ፣ ከተነገሩት ፣ ቃላት ፣ አብዛኞቹ ፣ በተውላጠ ፣ ስም ፣ ክፍል ፣ የተነገሩት ፣ ናቸው ፣ (ቁ 59—65 ፣ እይ ፣) ስለዚህም ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ አመልካች ፣ ቅጽል ፣ በመባል ፣ ፈንታ ፣ የተውላጠ ፣ ስም ፣ ቅጽል ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ።

—98—

ዩኛ ፣ የዓይነትና ፣ የግብር ፣ ቅጽል ።

(ሀ) የወገን ፣ ቅጽል ።

የወገን ፣ ቅጽል ፣ የሚባለው ፣ በተጸውዖ ፣ ስም ፣ ላይ ፣ ዊ ፣ የሚል ፣ ቢዕድ ፣ መድረሻ ፣ እየተጨመረበት ፣ ወይም ፣ መድረሻውን ፣ ኃምስ ፣ እያደረገ ፣ ወገንነትን ፣ የሚገልጽ ፣ ቃል ፣ ነው ። ይኸውም ፣ ኢትዮጵያዊ ፤ ያዕቆባዊ ፤ ጎንደሬ ፣ ሸዋ ፣ እንደማለት ፣ ነው ። (ቁ. 85—86)

ኛ ፣ የሚል ፣ ቢዕድ ፣ መድረሻ ፣ በተጸውዖ ፣ ስም ፣ ላይ ፣ በተጨመረ ፣ ጊዜ ፣ ቋን ቋን ፣ ወይም ፣ ያገርን ፣ ባህል ፣ ያመለክታል ። ይኸውም ፣ አማርኛ ፤ ጋልኛ ፤ ጎንደርኛ ፣ እንደማለት ፣ ነው ። በአንዳንድ ፣ የወል ፣ ስሞች ፣ ላይ ፣ ሲጨመር ፣ ግን ፣ ስፍራን ፣ አመልካች ፣ ይሆናል ። ይኸውም ፣ ቂለኛ ፣ ደገኛ ፣ . . . እንደማለት ፣ ነው ።

— 99 —

በዘርፍ ፣ ደንብ ፣ እየገቡ ፣ ወገንን ፣ ወይም ፣ መኖሪያን ፣ የሚገልጹ ፣ የወል ፣ ስሞች ፣ ዘርፍ ፣ አስተኔ ፣ ቅጽል ፣ ተብለው ፣ በወገን ፣ ቅጽል ፣ ክፍል ፣ ይጠራሉ ።

ምሳሌ ፣ የወርቅ ፣ ሰዓት ፣ (ከወርቅ ፣ ወገን ፣ የተወራ ፣)
የአንከበር ፣ ሰው ፣ (በአንከበር ፣ የሚኖር ።)
የወንዝ ፣ ዓሣ ፣ (ከወንዝ ፣ የተገኘ ።)

— 100 —

(ለ) የግብር ፣ ቅጽል ።

የግብር ፣ ቅጽል ፣ የሚባለው ፣ የተነገረው ፣ ነገር ፣ በምን ፣ አኳኋን ፣ እንዳለ ፣ የሚያመለክት ፣ ቃል ፣ ነው ። ስለዚህም ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ የባሕርይ ፣ ቅጽል ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ።

የግብር ፣ ቅጽል ፣ በ፫ ፣ አከፋፈሎች ፣ ይመደባል ።

(ሀ) ፣ ደንበኛው ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፣ ከግሥ ፣ ክፍል ፣ ይገኛል ፤ ይኸውም ፣ ደግ ፣ ክፉ ፣ መልከም ፣ መጥፎ ፣ ክሩ ፣ . . . የሚለው ፣ ነው ።

(ለ) ፣ ከተጸውዖ ፣ ስም ፣ በቀር ፣ በሌላው ፣ ስም ፣ ላይ ፣ ኛ ፤ ም ፤ ግ ፤ ጌ ፤ የሚል ፣ ቢዕድ ፣ መድረሻ ፣ እየተጨመረበት ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፣ ይሆናል ።

(ቁ. 90 —91 እይ ።)

ኛ ፤ (=የሆነ ፣ ወይም ፣ ያለበት ፣) ብልሃተኛ ፣ አመለኛ ፣ ወፈኛ ፣ . . .
ም ፤ (=የሆነ ፣ ወይም ፣ ያለበት ፣) ውሽታም ፣ ቅዠታም ፣ ድንጋያም ፤ . . .
ግ ፤ (=ያለበት ፣ ወይም ፣ የሞላበት) ድንጋያማ ፣ ተራራማ ፣ ውሀማ ፣ . . . .
ጌ ፤ የሚጨመርበት ፣ ቃል ፣ በቅጽልም ፣ በተውላከ ፣ ግሥም ፣ ክፍል ፣ ይነገራል ። ይኸውም ፣ እሮጌ ፣ ራስጌ ፣ ጻርጌ ፣ . . . እንደማለት ፣ ነው ። ትርጓሜው ፣ አጠገብነትን ፣ የሚገልጽ ፣ ነው ።

(ሐ) አንዳንድ ፣ የግብር ፣ ቅጽል ፣ ድጋፍ ፣ ቃል ፣ እየተደረገለት ፣ ይነገራል ። ይኸውም ፣ ልብወለድ ፤ ሥራፈት ፤ ዐውቆ-አበድ ፣ . . . . . እንደማለት ፣ ነው ። (ቁ. 93 (ለ) እይ ።)

—101—

መልእክትን ፣ የሚያመለክቱ ፣ ቃላት ፤ በግብር ፣ ቅጽል ፣ ክፍል ፣ ሆነው ፣ ይነገራሉ ። እነሱም ፣ በጽሒፍ ፣ ቃል ፣ የሚነገሩት ፣ ቅጽሎችና ፣ ብጤ ፣ አስተኔ ፣ . . . ናቸው ።

(ሀ) በጽሒፍ ፣ ቃል ፣ ምክንያት ፣ አብዛኞቹ ፣ የዓይነትና ፣ የግብር ፣ ቅጽሎች ፣ ናቸው ። እነርሱም ፣ መድረሻቸውን ፣ ሰድስ ፣ እድርገው ፣ በ፱ ፣ ወይም ፣ በ፫ ፣ ፊደላት ፣ ይገኛሉ ።

ምሳሌ ፡> ቂል ፣ ሞኝ ፤ ቀይ ፤ ነጭ ፤ ጅል ፣ ቅጠል ፤ የሚለውን ፣ ቃል ፤ ቂላቂል ፤ ሞኖሞኝ ፤ ቀያቀይ ፣ ነጫንጭ ፣ ጅላጅል ፤ ቅጠላቅጠል ፣ እንደማለት ፣ ሁሉ ፣ ነው ።

(ለ) ብጤ ፤ በወል ፣ ስምና ፣ በነገር ፣ ስም ፣ ላይ ፣ እየተጨመረ ፣ ይገባል ። ትርጓሜውም ፣ መሰል ፣ ወይም ፣ መሳይ ፣ ማለት ፣ ነው ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ጥቂትነትን ፣ ስለሚያመለክት ፣ የመጠን ፣ ቅጽል ፣ ይሆናል ።

ምሳሌ ፤ አስተማሪው ፡ ወርቅ ፡ ብጤ ፡ ሰዓት ፡ አለው ።
አስተማሪው ፡ ሰነፍ ፡ ብጤ ፡ ነው ።
የውብሸት ፡ ፈረስ ፡ ጥቁር ፡ ብጤ ፡ ነው ።
ውብሸት ፡ የኔ ፡ ብጤ ፡ ተማሪ ፡ ነው ።
በሳጥኔ ፡ ውስጥ ፡ ልብስ ፡ ብጤ ፡ አለኝ ።
በስንዴው ፡ ውስጥ ፡ እንክርዳድ ፡ ብጤ ፡ አለበት ።

} የግብር ፡ ቅጽል ፡
} የመጠን ፡ ቅጽል

(ሐ) አስተኔ ፡ በማንኛውም ፡ ስም ፡ ላይ ፡ እየተጨመረ ፡ ይገባል ። ትርጓሜው ፡ የሚመስል ፡ ወይም ፡ ያለበት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ ብሀ ፡ አስተኔ ፡ መሬት ፡ አታክልትን ፡ ያፋፋል ።
ፈረሱ ፡ ቀይ ፡ አስተኔ ፡ ነው ።

— 102 —

(ሐ) የዓይነት ፡ ቅጽል ።

የዓይነት ፡ ቅጽል ፡ የሚባለው ፡ የተነገረው ፡ ነገር ፡ የሚታወቅበትን ፡ ምልክት ። የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ ጥቁር ፡ ቀይ ፤ ነጭ ፡ ረጅም ፡ አጭር ፤ ትልቅ ፤ ትንሽ ፡ . . . ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

አስተውል ፤ ትልቅ ፡ ትንሽ ፤ ረጅም ፡ አጭር ፡ . . . የዓይነት ፡ ቅጽሎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የመጠን ፡ አይባሉም ። የዓይነትን ፡ ቅጽል ፡ ለማግኘት ፡ ጥያቄው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ? ወይም ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡ ? የሚል ፡ ነው ። የመጠንን ፡ ቅጽል ፡ ለማግኘት ፡ ግን ፡ ጥያቄው ፡ ስንት ፡ ? ወይም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ? የሚል ፡ ነውና ፡ ልዩነቱን ፡ በዚህ ፡ ልትረዳው ፡ ትችላለህ ።

— 103 —

ፀኛ ፡ የአጎዝና ፡ የመጠን ፡ ቅጽል ፡

የአጎዝ ፡ ቅጽል ፡ የሚባለው ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ በተራ ፡ ወይም ፡ በመድበል ፡ ሆኖ ፡ ቁጥሩና ፡ ልኩ ፡ የሚታወቅበት ፡ ቃል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ « አንድ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ . . . » እንደማለት ፡ ነው ።

መጠን ፡ ማለትም ፡ ብዙ ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ በመድበል ፡ የሚያስታውቅ ፡ ስለሆነ ፡ ወደ ፡ አጎዝ ፡ ደርበን ፡ መድበነዋል ። ይኸውም ፡ « ሁሉ ፡ አያሌ ፤ ነጠላ ፤ እጥፍ ፡ . . . » እንደማለት ፡ ነው ።

የአጎዝ ፡ ቅጽል ፡ (ሀ) የተወሰነ ፡ (ለ) ያልተወሰነ ፡ ተብሎ ፡ በሁለት ፡ መደበኞች ፡ ይመደባል ።

— 104 —

(ሀ) የተወሰነ ፡ አጎዝ ።

የተወሰነ ፡ አጎዝ ፡ የሚባለው ፡ እርግጠኛውን ፡ ቁጥር ፡ የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ በአጎዝና ፡ በዝርዝር ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ መደበኛ ፡ ቁጥር ፡ ይባላል ።

፩ ፡ አንድ
፪ ፡ ሁለት
፫ ፡ ሶስት
፬ ፡ አራት
፭ ፡ አምስት
፮ ፡ ስድስት
፯ ፡ ሰባት
፰ ፡ ስምንት
፱ ፡ ዘጠኝ
፲ ፡ ዐሥር
፲፩ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ
፳ ፡ ሀያ
፴ ፡ ሠላሳ
፵ ፡ አርባ
፶ ፡ አምሳ
፷ ፡ ስሳ
፸ ፡ ሰባ
፹ ፡ ሰማንያ
፺ ፡ ዘጠና
፻ ፡ መቶ
፼ ሚሊዮን . . . . . .

— 105 —

መደበኛ ፡ ቁጥር ፡ የብዙ ፡ ሆኖ ፡ ሰለ ፡ በልማድ ፡ የነጠላ ፡ ስም ፡ ቅጽል ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ፤ ሸሬ ፡ ፈረስ ፡ ገዛሁ ፤ (=ሸሬ ፡ ፈረሶችን ፡ ገዛሁ ፤)
ፎ ፡ ቤት ፡ አለኝ ፤ (=ፎ ፡ ቤቶች ፡ አሉኝ ፤)
ሶ ፡ ልጅ ፡ ወልጃለሁ ፤ (=ሶ ፡ ልጆችን ፡ ወልጃለሁ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በነገር ፡ ስምና ፡ በቁልቁሉ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ ለነጠላ ፡ ስም ፡ ቢቀጸል ፡ ጸያፍ ፡ አይሆንም ።

ምሳሌ ፤ አምስቱን ፡ እንጀራና ፡ ሁለቱን ፡ ዓሣ ፡ አንሥቶ ፡ ያዘ ።
ሁለት ፡ ልብስ ፡ ያለው ፡ አንዱን ፡ ለሌላው ፡ ይስጥ ፤
እስራኤል ፡ በግብጽ ፡ ፬፻፴ ፡ ዓመት ፡ ኖሩ ።
ከአዲስ ፡ አበባ ፡ እስከ ፡ አክሱም ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ያስጉዛል ።

— 106 —

በመደበኛው ፡ ቁጥር ፡ ላይ ፡ «ኛ ፤ ያ ፤» የሚል ፡ ባዕድ ፡ መድረሻ ፡ ሲጨመርበት ፡ ሕገኛ ፡ ቁጥር ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ አንደኛ ፤ ሁለተኛ ፤ ሰስተኛ ፤ . . . . . ወይም ፡ አንድያ ፤ ሁለትያ ፤ ሰስትያ ፤ . . . እንደማለት ፡ ነው ። አንደኛ ፤ ሁለተኛ ፤ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መጀመሪያ ፡ ዳግመኛ ፤ ተብሎ ፡ ይቆጠራል ። ሕገኛን ፡ ቁጥር ፡ በዝርዝር ፡ ሳይሆን ፡ በአ

ጎዝ ፡ ፈደል ፡ ለመጻፍ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ኖ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ይጨመርበታል ። ይኸውም ፡ ፅኖ ፡ ፂኖ ፡ ይሳል ፡ እንጂ ፡ ፅደኖ ፡ ፂተኖ ፡ አይባልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቀጻማዊ ፡ ዳግማዊ ፡ ሣልሳዊ ፡ .... የሚለው ፡ የግዕዙ ፡ ሕገኛ ፡ ቁጥር ፡ ስለ ፡ ነገ ሥታት ፡ ስም ፡ ተረ ፡ በአማርኛ ፡ የተለመደ ፡ ነው ።

—107—

በመደበኛው ፡ ቁጥር ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጨምሮ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ የግብዛት ፡ ምግባር ፡ ይገለጥበታል ።

ምሳሌ ፤ አንድ ፡ እጅ ፤ ሁለት ፡ እጅ ፤ ሶስት ፡ እጅ ፤ ..... ይላል ፤ ትርጓሜ ውም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የመቀነስን ፡ ምግባር ፡ የሚያመለክቱ ፡ ሲሶ ፡ እርቦ ፡ እምሽ ፡ ዐሥሬት ፡ ..... ተብለው ፡ የሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ አሉ ። ትርጓሜያቸውም ፡ ከ፫ ፡ ፩ ፡ ከ፬ ፡ ፩ ፡ ከ፭ ፡ ፩ ፡ ከ፲ ፡ ፩ ፡ ማለት ፡ ነው ።

—108—

(ሰ) ያልተወሰነ ፡ አጎዝ ።

ያልተወሰነ ፡ አጎዝ ፡ የሚባለው ፡ በመድበል ፡ (ወይም ፡ በጅምላ ፡) ሆኖ ፡ የሚነገረው ፡ ቁጥር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ብዙ ፡ ጥቂት ፡ አያሌ ፡ ምንም ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ መላው ፡ ሞኒስ ፡ አጥፍ ፡ ነጠላ ፡ » ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ የተነገረውን ፡ ነገር ፡ መብዛቱንና ፡ ማነሱን ፡ ያስ ታውቃሉ ፡ እንጂ ፡ በተለይ ፡ እርግጠኛ ፡ ቍጥሩን ፡ ስለማይገልጡ ፡ የመጠን ፡ አጎዝ ፡ ይባላሉ ።

—109—

ፀተወሰነ ፡ አጎዝ ፡ ላይ ፡ ያህል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በተጨመረበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተ ወሰነ ፡ አጎዝ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ፤ የሰዋስው ፡ ደቀ ፡ መዘሙርት ፡ ፯ ፡ ናቸው ፤ (የተወሰነ ፡ አጎዝ) ።
የሰዋስው ፡ ደቀ ፡ መዘሙርት ፡ ፯ ፡ ያህል ፡ ናቸው ፤ (ያልተወሰነ ፡ አጎዝ) ።

—110

ቮኛ ፡ አመልካች ፡ ቅጽል ።

አመልካች ፡ ቅጽል ፡ እንደ ፡ አጎዝ ፡ ሁሉ ፡ «የተወሰነ ፡ ያልተወሰነ ፡» ተብሎ ፡ ሙሉለት ፡ ክፍሎች ፡ ይመደባል ።

ማናቸውም ፡ ነገር ፡ በተለይ ፡ ተረጋግጦ ፡ «ይህ ፡ ሰው ፡ ያ ፡ ቤት» ፡ ተብሎ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ የቅጽሉ ፡ ቃል ፡ የተወሰነ ፡ አመልካች ፡ ይባላል ።

በእርግጥ ፡ የታወቀ ፡ ሳይሆን ፡ «ሰውየው ፡ ቤቱ» ፡ ተብሎ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ያልተወሰነ ፡ አመልካች ፡ ቅጽል ፡ ይባላል ።

—111—

(ሀ) የተወሰነ ፡ አመልካች ።

የተወሰኑ ፡ አመልካቾች ፡ የሚባሉት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተጻፉት ፡ ሩቅንና ፡ ቅርብን ፡ የሚያስታውቁ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ።

ምሳሌ ፤ (ሀ)	የቅርብ ፡ ቅጽል ፤	የሩቅ ፡ ቅጽል ፤	
ተባ.	ይህ ፡	ያ ፡	ነጠላ ፡
እን.	ይህች ፡	ያች ፡	
ተባ.እን.	እነዚህ ፡ እኒህ ፡	እነዚያ ፡ እኒያ ፡	ብዙ ፡
እን.	እሊህ ፡	እሊያ ፡	

የመስተዋድድ ፡ ቃል ፡ ሲጨመርባቸው ፡ ዘ ፡ የሚል ፡ ፈደል ፡ ይገኝባቸዋል ።

ምሳሌ ፤ (ለ)	የቅርብ ፡ ቅጽል ፤	የሩቅ ፡ ቅጽል ፤	
ተባ.	እንደዚህ ፡	እንደዚያ ፡	ነጠላ ፡
እን.	እንደዚች ፡ (እንደዚህች) ፡	እንደዚያች ፡	
ተባ.እን.	እንደነዚህ ፡	እንደነዚያ ፡	ብዙ ፡

—112—

(ለ) ያልተወሰነ ፡ አመልካች ።

ያልተወሰነ ፡ አመልካች ፡ የሚባሉት ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። እነእርሱም ፡ የቅር ቡን ፡ ወይም ፡ የሩቁን ፡ ሊያመለክቱ ፡ ይችላሉ ።

ተባ. « ው ፡ ዮ ፡ ዮው ፡ ከዕብ ፤ ፈደል ፡ አንድ ፤ ማናቸው ፤ ማንኛው ፡ ሌላ ፡
እን. ዋ ፤ ጁቱ ፡ ዮ ፡ ዮዋ ፤ ማንኛዋ ፡ ማናቸዉቱ ፡ . . . . . .

ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ቃል ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ አገባቡም ፡ እንደሚከተ ለው ፡ ነው ።

ምሳሌ፤ ው ፡ « አንበሳው ፡ አገሣ ፡ »
ዮ ፤ ወይም ፡ ዮው ፡ « ጌትዮው ፡ ተቈጣ ፡ »
ከሰብ ፡ ፊደል ፤ «ወንዙ ፡ ደፈረሰ ፡ »
አንድ ፤ « አንድ ፡ ይፈርድ ፡ አንድ ፡ ይቀድ ፡ »
ማናቸውም ፡ « ቀኑ ፡ ሲደርስ ፡ ማናቸውም ፡ ይፈጸማል ።
ማንኛውም ፡ ወይም ፡ ማንም ፤ « ማንም ፡ ሊፈርድብኝ ፡ አይችልም ፡ »
ሴላ ፡ « በሴላ ፡ ቀን ፡ እመጣለሁ ፡ »
ዋ ፤ ዎቱ ፤ « ከተማዋ ፡ ወይም ፡ ከተማዎቱ ፡ ተደረጀች ። »
ዮ ፡ ዮዋ ፡ «ሴትዮዋ ፡ የልብሱን ፡ ዘርፍ ፡ የዳሰሰው ፡ እንደሆነ ፡ እድናለሁ ፡ ብላ ፡ አሰበች ፡ »

ማናቸው ፡ ማናቸዎቱ ፡ ማንኛው ፡ ማንኛዎቱ ፡ ከሆቱ ፡ ቃላት ፡ ማናቸዎቱ ፡ (ማንኛዋ ፡) ትበልጣለች ?

— 113 —

(ሐ) ጠቃሽ ፡ አመልካች ።

ጠቃሽ ፡ አመልካች ፡ የሚባለው ፡ « ን » ነው ፤ ትርጓሜው ፡ ያ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለገቢር ፡ እንቀጽ ፡ ተገዥ ፡ የሚሆነውን ፡ ተሰቢ ፡ ያመለክታል ።

ምሳሌ፤ ልጆች ፡ ጨዋታን ፡ ይወዳሉ ።
እነሆ ፡ ን ፡ ተሰቢውን ፡ ጠቅሶ ፡ እንጻመለከተ ፡ አስተውል ።

— 114 —

(መ) አዛማጅ ፡ ቅጽል ።

አዛማጅ ፡ ቅጽል ፡ የሚባለው ፡ መስተዋምሩ ፡ የ ፡ እየሳበው ፡ ግሥ ፡ ከስም ፡ ጋር ፡ የሚዛመድበት ፡ ቃል ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ አንጻንድ ፡ ጊዜ ፡ መስተዋምራዊ ፡ ቅጽል ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። (ቁ. 93 (መ) እይ)

በጎላፊ ፡ አንቀጽ ፡ የ ፡ በአሁንና ፡ በትንቢት ፡ የም ፡ በስተ ፡ መነሻ ፡ ይወድቁበ ቃል ። በአ ፡ ፊደል ፡ የሚነሣ ፡ ግሥ ፡ ሲሆን ፡ መስተየምሩ ፡ ራብዕ ፡ ይሆናል ፤ ይ ፡ በለበ ትም ፡ ስፍራ ፡ ግልስ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ፤ ጎላፊ ፡ ያመነ ፡ የተጠመቀ ፡ ይዳን ።

ያውንና ፡ ትንቢት ፡ { የምታደርገውን ፡ ፈጥነህ ፡ አድርግ ።
{ የሚሞት ፡ ሽማግሌ ፡ አይርገምህ ።
{ የማስተምርህን ፡ ስማኝ ።

ክፍል ፡ ፫ ፡ የማነጻጸር ፡ ደንብ ።

— 115 —

አንድ ፡ ነገር ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ በተነጻጸረ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛውን ፡ አብልጠ ፡ ወይም ፡ አሳንሶ ፡ ለመናገር ፡ ስንፈልግ ፡ የመስተዋድድ ፡ ክፍል ፡ የሆነውን ፡ «ከ—ይልቅ ፡ » እና ፡ ከተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ክፍል ፡ የሆኑትን ፡ «እጅግ ፡ በጣም ፡ » በየቅጽሉ ፡ ላይ ፡ እየጨመርን ፡ ለማበላለጥ ፡ እንችላለን ። ቅጽሉ ፡ በደረጃ ፡ ቃል ፡ ሲነገር ፡ አማራጭ ፡ ይበላል ። ማነጻጸር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ! ማበላለጥ ፡ ያሰኛል ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። ደራሲው ፡ ግን ፡ አሳቡን ፡ በዚሁ ፡ ያጸናዋል ።

— 116 —

«ከ—ይልቅ ፡ » ተነጻጻሪውን ፡ ቃል ፡ በመከከል ፡ አድርጎ ፡ ይገባል ። ከማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ቅጽልና ፡ ስም ፡ ጋር ፡ እየተዛመደ ፡ አበላላጭ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ፤ ውብሸትና ፡ ጌታሁን ፡ ይማራሉ ።
ከውብሸት ፡ ይልቅ ፡ ጌታሁን ፡ ትጉህ ፡ ነው ።
ውብሸት ፡ ከትምህርት ፡ ይልቅ ፡ ጨዋታን ፡ ይወዳል ።

«ከ» ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ሲገበና ፡ ሲያነጻጽር ፡ አብላጭ ፡ መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ አማራጭ ፡ ይበላል ። (ቁ. 118 ፡ እይ ።)

— 117 —

«እጅግ ፡ በጣም ፡ » የተባሉት ፡ ቃላት ፡ ለየራሳቸው ፡ ተለይተው ፡ ሲገቡ ፡ አብላጮች ፡ ይሆናሉ ። «እጅግ ፡ » ለሚለው ፡ የመጠን ፡ ቅጽሎች ፤ «በጣም ፡ » ለሚለው ፡ የዓይነትና ፡ የግብር ፡ ቅጽሎች ፡ ይስማሙታል ።

«እጅግ ፡ በጣም ፡ » ተብሎ ፡ በአንድነት ፡ ሲገባ ፡ አበላላጭ ፡ ሆኖ ፡ በይ ፡ ደረጃ ፡ ይነገራል ።

የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ተነጻጻሪ ፤ ሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡ አብላጭ ፤ ሰስተኛውም ፡ አበላላጭ ፡ ይባላል ። ሁሉንም ፡ በሚከተለው ፡ ሰሌዳ ፡ ተመልከት ።

ተነጻጻሪ ፡	አብላጭ ፡ ደረጃ ።	አበላላጭ ፡ ደረጃ ።
ብዙ ፡	እጅግ ፡ ብዙ ፡	እጅግ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡
ጥቂት ፡	እጅግ ፡ ጥቂት ፡	እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡
ረጅም ፡	እጅግ ፡ ረጅም ፡	እጅግ ፡ በጣም ፡ ረጅም ፡
ጥቁር ፡	በጣም ፡ ጥቁር ፡	እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥቁር ፡
ክፉ ፡	በጣም ፡ ክፉ ፡	እጅግ ፡ በጣም ፡ ክፉ ፡
ብልሃተኛ ፡	በጣም ፡ ብልሃተኛ ፡	እጅግ ፡ በጣም ፡ ብልሃተኛ ፡
ድንጋያማ ፡	በጣም ፡ ድንጋያማ ፡	እጅግ ፡ በጣም ፡ ድንጋያማ ፡

— 118 —

የቅጽል ፡ ታል ፡ ተደጋግሞ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ አማራጭ ፡ ይባላል ።

ምሳሌ ፡ ትጉህ ፡ ትጉሁ ፡ ተግሪ ፡ ጠንክር ፡ ይማራል ። ሰነፍ ፡ ሰነፉ ፡ ይማማል ።

የወይን ፡ ፍሬ ፡ ጥቁር ፡ ጥቁሩ ፡ ይጣፍጣል ። ቀይ ፡ ቀዩ ፡ ይከመድዳል ።

‹ከ› ብቻውን ፡ ንጠቶ ፡ አማራጭ ፡ ሲሆን ፡ እንደሚከተለው ፡ ሆኖ ፡ ይገባል ።

ከመሞት ፡ መሰንበት ፡ ይሻላል ።

ከመልክም ፡ ሽቱ ፡ መልክም ፡ ስም ፡ ይሻላል ።

፯ኛ ፡ መልመጃ ።

(ሀ)—ቅጽል ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡ ታል ፡ ነው ?

ቅጽልን ፡ ለማግኘት ፡ እንዲት ፡ ተብሎ ፡ ይጠየቃል ?

ቅጽል ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ ይባላል ?

በስም ፡ ላይ ፡ ተጨምሮ ፡ ሲነገርስ ፡ ግን ፡ ይባላል ?

በቂ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?

(ለ)—ቅጽል ፡ ከምን ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ይመሠረታል ?

ከስም ፡ ላይ ፡ እንዲት ፡ እንደሚገኝ ፡ አስረዳኝ ።

ከግሥ ፡ ከፍልም ፡ እንዲት ፡ እንደሚመሠረት ፡ አስረዳኝ ።

(ሐ)—የቅጽል ፡ ዓይነቶች ፡ ስንት ፡ ናቸው ?

የግይነትና ፡ የጉብር ፡ ቅጽል ፡ የሚባለው ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡ ነው ?

የአጎዝና ፡ የመጠን ፡ ቅጽል ፤ አመልካች ፡ ቅጽል ፡ የሚባለውስ ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡ ነው ? ከያይነቱ ፡ ጅ ፡ ጅ ፡ ታላት ፡ ጸፍ ።

(መ)—የግበላለጥ ፡ ደረጃ ፡ እንዲት ፡ እንደሆን ፡ ዓይነቱን ፡ እየለየህ ፡ ንግረኝ ?

ከያይነትም ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ታላት ፡ ማስረጃ ፡ ድረፀ ፡ አስረዳኝ ።

(ሠ)—ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፉት ፡ ምንባቦች ፡ ቅጽሎችን ፡ እየለየህ ፡ በየስማቸው ፡ አስታውቅ ።

በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ የሆኑትን ፡ ቅጽሎች ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ እያዛወርህና ፡ ከታላቁ ፡ ጋር ፡ እያስማማህ ፡ እንጠብ ።

ምንባቦች ።

፩ኛ ፡

ሙርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡ የሙርድ ፡ አዝማች ፡ አብጹ ፡ ልጅ ፡ ነው ። በምስፍናም ፡ ከነጋሢ ፡ ጀምሮ ፡ ፱ኛ ፡ ቁጥር ፡ ይሆናል ።

እርሱ ፡ ከአፀቅ ፡ የበለጠ ፡ ጀግና ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ከአፀቅ ፡ ከተማ ፡ ከሐር ፡ አምባ ፡ ሁነ ሥቶ ፡ ሄደና ፡ አንከበር ፡ የሚባለውን ፡ ከተማ ፡ ቁረቁረ ። ከ፲፯፻፹፫ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሸዋን ፡ በምስፍና ፡ ፴፪ ፡ ዓመት ፡ ገዛ ።

በዘመኑ ፡ አያሌ ፡ መሰኑ ፡ የሚባል ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ ጋራ ፡ ተግርከ ፡ ሰ በረው ፡ ሸፈተበት ። ነገር ፡ ግን ፡ ባላገር ፡ ተሰብስቦ ፡ ያዘና ፡ ሰጠው ። እምኃየስ ፡ በጣ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ያገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሞር ፡ አሥኃየስ ፡ ይሉው ፡ ነበር ። ፴፪ ፡ ዓመት ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ ሸምግሎ ፡ ሞተና ፡ አንከበር ፡ ላይ ፡ በመራው ፡ በቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ተቀበረ ። ምስፍናውንም ፡ ልጁ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አሰፋ ፡ ወሰን ፡ ወረሰ ።

፪ኛ ፡

መርድ ፡ አዝማች ፡ አሰፋ ፡ ወሰን ፡ የአባቱን ፡ የአምኃየስን ፡ አልጋ ፡ ወርሶ ፡ ከ፲፯ ፻፸፭ ፡ እስከ፲፰፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ፴፪ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ሸዋን ፡ በምስፍና ፡ ገዛ ። እርሱ ፡ በጣም ፡ የተግረ ፡ ቅኔ ፡ አዋቂም ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተነሥተው ፡ የነበሩት ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ ባላባቶች ፡ ሁሉም ፡ ቅኔ ፡ አዋቂዎች ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ስግኖውንም ፡ ከዚህ ፡ ተዋለን ፡ እናነግሮልን ።

በነገደር ፡ አጼ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤ በትግሬ ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጉብርአል ፡ በነጃም ፡ ራስ ፡ ጎበሉ ፤ በላስታ ፡ ደጃዝማች ፡ በቀተ ፤ በጀዋ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አሰፋ ፡ ወሰን ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በቅኔ ፡ እውቀት ፡ የተመሰገኑ ፡ ነበሩ ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አሰፋ ፡ ወሰን ፡ በአፀቁ ፡ አልጋ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ሰበት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ በአንከበር ፡ ሆኖ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሰይል ፡ በእውቀትና ፡ በፈሊጥ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ አቅንቷል ። በኋላም ፡ የነገደሩ ፡ አጼ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከላይ ፡ የተጠሩትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባላባቶች ፡ አስከትተው ፡ ወደ ፡ ጀዋ ፡ ዘመቱበት ። ጻሩ ፡ ግን ፡ ገና ፡ ወሎ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ታከቱና ፡ ዝቅዋቅዋ ፡ አሉ ። የመሯንም ፡ ጋላ ፡ አልፈው ፡ ጀዋ ፡ ላይ ፡ ከመርድ ፡ አዝማች ፡ አሰፋ ፡ ወሰን ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ እንደማይለክላቸው ፡ ተረዱትና ፡ ወየለፍራቸው ፡ ተመለሱ ። ወዲያው ፡ ታላቅ ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ ጀፍቶ ፡ ቄያቸውና ፡ ሁሉንም ፡ ዛትንትን ፡ አደረጋቸው ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አሰፋ ፡ ወሰን ፡ ብዙ ፡ አጣያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተክሏል ። ብዙ ፡ ገዳማትም ፡ አቅንቷል ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በ፲፰፻፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጎዳር ፡ ጌር ፡ ቀን ፡ ሞተና ፡ ወሬራው ፡ በአንከበር ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበረ ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ። ግሥ ።

———///———

—119—

መግለጫ

አንዳች ፡ ነገርን ፡ ለመናገር ፡ ወይም ፡ ለመጻፍ ፡ የፈለግን ፡ እንደሆነ ፡ አድራጊው ፡ ምንን ፡ እንዳደረገ ፤ ወይም ፡ ምንን ፡ እንደተደረገ ፣ ልንናገር ፡ ግድ ፡ ይሆንብናል ። ስለ ዚህም ፡ ግሥን ፡ የንግግር ፡ መፈጸሚያ ፡ አድርገን ፡ እንጠራዋለን ። የግሥ ፡ ቃል ፡ በተጨ መረ ፡ ጊዜ ፡ የንግግሩ ፡ አሳብ ፡ ሙሉ ፡ ይሆንና ፡ አንድ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

—120—

የንግግር ፡ መፈጸሚያና ፡ ማሠሪያ ፡ አድርገን ፡ የምንጠራው ፡ ቃል ፡ « ግሥ » ወይም ፡ አንቀጽ ፡ ይባላል ። ግሥ ፡ ጠቅላላ ፡ ስሙ ፤ አንቀጽ ፡ የውስጥ ፡ ስሙ ፡ ነው ።

አንቀጽ ፡ መባሉ ፤ በር ፡ መወሰኛ ፡ መክልከያ ፤ እንደሆነ ፤ ቃላትም ፡ በርሱ ፡ ይወ ሰኑበታልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ከግዕዝ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ትርጓሜውም ፡ በር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ግሥ ፡ መባሉ ፡ ባለ ፡ ብዙ ፡ ጓዝ ፤ ባለ ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ግሥ ፡ የብዛትን ፡ ነገር ፡ የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ ስለሆነ ፡ « ሰማይ ፡ ከነግሡ ፤ ምድር ፡ ከነልብሱ » ፡ ተብሎ ፡ ይተረታል ። ከሊቃውንት ፡ ወገን ፡ « ጌሠ» ያለውን ፡ የግዕዙን ፡ ቃል ፡ ይዘው ፡ ግሥ ፡ ማለት ፡ ገስጋሽ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚተረጉሙ ፡ አሉ ። አንዳንዶች ፡ ደግ ሞ ፡ « ግስንግስ » ፡ ያለውን ፡ አማርኛ ፡ ይዘው ፡ ጓዘ ፡ ብዙ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይተረጉ ሉ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ምሥጢሩ ፤ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

—121—

የንግግርን ፡ አሳብ ፡ በግልጽ ፡ ለማሰማትና ፡ አንድ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ስንፈልግ ፡ አጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ፭ ባለቤትና ፡ ፭ ግሥ ፡ ሊኖሩን ፡ ያስፈልጋል ።

አጅ. ውሻ ፡ ጮኸ ፡ ዝናም ፡ ዘነመ ፤ አባት ፡ ልጁን ፡ ቀጣ ፤

እነሆ ፣ በዚህ ፡ በተሰጠው ፡ ማስረጃ ፡ « ውሻ ፤ ዝናዎ አባት» የተባሉት ፡ ስሞች ፡ ብቻቸውን ፡ ተነግረው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ምንን ፡ እንዳደረጉ ፤ ወይም ፡ ምንን ፡ እንደተደ ረጉ ፡ ለማወቅ ፡ በልተቻለም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የግሥ ፡ ቃል ፡ « ጮኸ ፤ ዘነመ ፤ ቀጣ ፤ » ሲጨመርባቸው ፡ ድርጊታቸው ፡ ወይም ፡ ሁኔታቸው ፡ ተገልጾ ፡ ይታወቃል ።

ክፍል ፡ ፭ ፡ የግሥ ፡ ጠባይና ፡ ዓይነት ።

—122—

(፩) የግሥ ፡ ጠባዮች ።

ግሥ ፡ ፫ ፡ ጠባዮች ፡ አሉት ። እነርሱም ፡ ገቢር ፤ ተገብሮ ፤ መለዋወጥ ፡ ናቸው ።

—123—

ገቢር ፡ ግሥ ።

ገቢር ፡ ግሥ ፡ የሚባለው ፡ ለአንቀጹ ፡ ርቱዕ ፡ ተሰቢ ፡ (ወይም ፡ ቀጥታ ፡ ተሳቢ ፡) የሚያሰ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፤ የሚታወቀው ፡ በቃሉ ፡ መድረሻ ፡ ላይ ፡ ን ፡ የሚል ፡ የገቢር ፡ ምልክት ፡ ሲጨመርበት ፡ ነው ። (በ124 ፡ ቁ. (ሀ ፡ ለ ፡) ተመል ከት ።) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የአንቀጹ ፡ ጠባይ ፡ ገቢር ፡ ነው ፡ ይባላል ። ን ፡ የገቢር ፡ ምልክት ፡ ሲሆን ፡ በቅጽል ፡ ክፍል ፡ ጠቃሽ ፡ አመልካች ፡ ተብሎ ፡ እንደተመደበና ፡ ትርጓሜው ፡ ያ ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በ113 ቁ. አሳይተናል ።

—124—

ተሳቢው ፡ በለዘርፍ ፡ ወይም ፡ ባለቅጽል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የገቢሩ ፡ ምልክት ፡ ን ፡ በዘርፍ ፡ ወይም ፡ በቅጽሉ ፡ ላይ ፡ ይውላል ። (አጅ. ሐ ፡ ተመልከት ።) እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ዘርፉ ፡ ወይም ፡ ቅጽሉ ፡ ለራሱ ፡ ባለዘርፍ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የገቢሩ ፡ ምልክት ፡ ን ፡ በዘ ርፉም ፡ በተሰቢውም ፡ ላይ ፡ ይውላል ። (አጅ . መ ፡ ተመልከት ።)

አጅ . (ሀ) ዳዊት ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ ።
(ለ) ዮሐንስ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ።
(ሐ) ያዕቆብ ፡ ጀሠቱን ፡ ነገድ ፡ ወለደ ።
(መ) አብርሃም ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ንጉሥ ፡ መልከጺዴቅን ፡ አገኘው ።

—125—

ተገብሮ ፡ ግሥ ።

ተገብሮ ፡ ግሥ ፡ የሚባለው ፡ ለአንቀጹ ፡ ርቱዕ ፡ ተሰቢ ፡ የማያሻው ፡ የሆነ ፡ እን ደሆነ ፡ ነው ። ተገብሮ ፡ ግሥ ፡ ያለምንም ፡ ተሰቢ ፡ ይነገራል ። (አስረጅ ፡ ሀ ፡ ተመልከት ።) ጻሩ ፡ ግን ፡ ኢርቱዕ ፡ ተሳቢን ፡ (ቀጥታ ፡ ያልሆነ ፡ ተሳቢን ፡) ለማግኘት ፡ ይችላል ። (አስረጅ ፡ ለ. ሐ ፡ ተመልከት ።) ይኸውም ፡ ኢርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ በመስተዋድድ ፡ የሚገዛ ፡ ቃል ፡ ነው ።

አስረጅ ፤ (ሀ) ያዕቆብ ፡ አረጀ ።
(ለ) ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረደ ።
(ሐ) ሰሎሞን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

—126—

ወላዋይ ፣ ግሥ ።

ወላዋይ ፣ ግሥ ፣ የሚባለው ፣ አንቀጹ ፣ በገቢርም ፣ በተገብሮም ፣ ልማዱ ፣ (ለመ ሥራ ፣) የሚችል ፣ የሆነ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ።

አጅ. ውብሸት ፣ ወደ ፣ አገሩ ፣ ሄደ ። ወይም ፣ አገሩን ፣ ሄደ ፣

ውብሸት ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ገባ ፤ ወይም ፣ ቤቱን ፣ ገባ ፣ ይላል ።

ዳሩ ፣ ግን ፣ ይህ ፣ ሙሳኔ ፣ የሚጣስበት ፣ ምክንያት ፣ ስላለ ፣ የሚከተለውን ፣ ተ. ቁ. 127 ፣ እይ ።

—127—

ወላዋይ ፣ ግሥ ፣ የተባለውን ፣ ሙሳኔ ፣ ከሊቃውንት ፣ ወገን ፣ የማይቀበሉ ፣ አሉ ። ምክንያቱም ፣ ይህ ፣ ነው ። «ውብሸት ፣ አገሩን ፣ ሄደ ፣» ባለ ፣ ጊዜ ፣ ን ፣ ከፍሉ ፣ ከመስተ ዋድድ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ከተጠቃሽ ፣ አመልካች ፣ አይደለም ። ትርጓሜውም ፣ ወደ ፣ ማለት ፣ ይሆናል ፣ ብለው ፣ ይመስናሉ ። ደራሲውም ፣ ይህን ፣ ሙሳኔ ፣ ያመስግነዋል ።

—128—

(፪) የግሥ ፣ ዓይነቶች ።

ግሥ ፣ በ፫ ፣ ታላላቅ ፣ ዓይነቶች ፣ ተመድበ ፣ ይነገራል ። እነርሱም ፣ ተሻጋሪ ፣ ግሥ ፣ የማይሻገር ፣ ግሥ ፣ ነባር ፣ ግሥ ፣ ይባላሉ ።

እነዚህም ፣ ፫ ፣ ዓይነቶች ፣ በቅኔ ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ ገቢር ፣ ተገብሮ ፣ በተባለው ፣ ከፍል ፣ ተጠቅሰዋል ፣ ይነገሩ ፣ ነበር ። ባሁኑ ፣ ሙሳኔ ፣ ግን ፣ የተለየ ፣ ነገር ፣ አሰ ። ልዩነቱ ንም ፣ በሚከተለው ፣ መመልከት ፣ ነው ።

—129—

ተሻጋሪ ፣ ግሥ ።

የአንቀጹ ፣ ግብር ፣ በአድራጊው ፣ ላይ ፣ ብቻ ፣ ተወሰኖ ፣ ሳይቀር ፣ ወደ ፣ ተደራ ጊው ፣ ያለፈ ፣ እንደሆነ ፣ ግሡ ፣ ተሻጋሪ ፣ ይባላል ። ጠባዩ ፣ ገቢርነት ፣ ነው ።

አጅ ፣ አባት ፣ ልጁን ፣ አስተማረ ።

ጻዊት ፣ ጎልያድን ፣ ገደለ ።

—130—

ተሻጋሪ ፣ ግሥ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ድርብ ፣ ተሰቢን ፣ ይዘ ፣ ይገኛል ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ የገቢሩ ፣ ምልክት ፣ ን ፣ በመጀመሪያው ፣ ተሰቢ ፣ ላይ ፣ ወቻ ፣ ይሆንና ፣ ከዚያው ፣ ላይ ፣ ይቀራል ። ምሥጢሩ ፣ ሲመረመር ፣ ግን ፣ የመስተዋድድ ፣ ቃል ፣ ውስጠ ፣ ቀሪ ፣ ሆኖ ፣ የጉደለ ፣ ነው ።

አስረጅ ፣ አስተማሪ ፣ ልጁን ፣ ሰዋስው ፣ አስተማረ ፣ (=ለልጁ ፣ ሰዋስውን ፣ አስተማረ ።)

ኢየሱስ ፣ ውኃን ፣ ጠጅ ፣ አደረገ ። (—ውኃን ፣ ጠጅ ፣ እንዲሆን ፣ አደረገ ።)

— 131 —

የማይሻገር ፣ ግሥ ።

የአንቀጹ ፣ ግብር ፣ ወደሌላ ፣ ሳያልፍ ፣ በአድራጊው ፣ ላይ ፣ ብቻ ፣ ተወስኖ ፣ የሚ ቀር ፣ ሲሆን ፣ ግሡ ፣ የማይሻገር ፣ ይባላል ።

ገቢርነት ፣ ወይም ፣ ተገብሮነት ፣ ይስማማዋል ።

አጅ. ውብሸት ፣ ልብሱን ፣ ለበሰ ። ሰሎሞን ፣ መንግሥትን ፣ ወረሰ ። } ገቢር ፣

ያዕቆብ ፣ አርጅቶ ፣ ሞተ ። ውብሸት ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ሄደ ። } ተገብሮ ፣

— 132 —

ነባር ፣ ግሥ ።

እንደ ፣ ግሥ ፣ ደንብ ፣ ሙሉ ፣ እርባታ ፣ የሌላቸው ፣ ግሦች ፣ በግብራቸው ፣ ነባር ፣ ግሥ ፣ ተብለው ፣ ይጠራሉ ። ነባር ፣ ማለት ፣ ወዲያ ፣ ወዲህ ፣ የማይል ፣ ተቀማጭ ፣ ማለት ፣ ነው ። እነዚህም ፣ ግሦች ፣ እንደሌሎቹ ፣ ሁሉ ፣ በአፅማድ ፣ ተዘርዝረው ፣ ስለማይረቡ ፣ ነባር ፣ ተብለዋል ። እንደነዚህ ፣ ያሉት ፣ ግሦች ፣ ብዙ ፣ አይደሉም ። ዋነኞቹም ፣ (ሀ) የመ ሆን ፣ ግሥ ፣ (ለ) የመኖር ፣ ግሥ ፣ ናቸው ።

— 133 —

የመሆን ፣ ግሥ ፣ ነው ፣ ነበረ ፣ . . . የሚል ፣ ቃልን ፣ እየወለደ ፣ ይረባል ፣

የመኖርም ፣ ግሥ ፣ አለ ፣ ኖረ ፣ . . . ፣ የሚል ፣ ቃልን ፣ እየወለደ ፣ ይረባል ።

አለ ፣ የሚለው ፣ ቃል ፣ ላልቶ ፣ ሲነበብ ፣ የመኖርን ፣ ምግባር ፣ ያመለክታል ። ይኸውም ፣ » እግዚአብሔር ፣ ብርሃን ፣ ይሁን ፣ አለ ፣ » እንደማለት ፣ ነው ። ጠብቆ ፣ ሲን በብ ፣ ግን ፣ የመኖርን ፣ ምግባር ፣ ይገልጻል ። » በዘህ ፣ ተራራ ፣ ለአብ ፣ የሚሰግዱበት ፣ ጊዜ ፣ አለ ፣ » እንደማለት ፣ ነው ።—

—134 —

ከዘህ ፣ በላይ ፣ የተነገሩት ፣ የመሆንና ፣ የመኖር ፣ ግሦች ፣ በአንቀጽነታቸው ፣ ራሳቸውን ፣ ችለው ፣ በገቡ ፣ ጊዜ ፣ እንደ ፣ ግሥ ፣ ደንብ ፣ በየቱም ፣ መደበኛ ፣ ሊረቡ ፣ ይችላሉ ። ይኸውም ፣ ነበርሁ ፣ ነበርህ ፣ ነበረች ፣ ነበረ ፣ አለሁ ፣ አለህ ፣ አለች ፣ አለ ፣ . . . እንደማለት ፣ ነው ። ደግሞ ፣ ረዳት ፣ ሆነው ፣ በብዙ ፣ አንቀጽ ፣ ላይ ፣ እየተጸረፉ ፣ በገቡ ፣ ጊዜ ፣ እንደሚከተለው ፣ ይሆናሉ ። (ቁ. 135 136 እይ ።)

— 135 —

የመሆን ፣ ግሥ ፣ « ነበረ ፣ « መድረሻውን ፣ ሳድስ ፣ አድርን ፣ ነበር ፣ » ተብሎ ፣ በቮቱም ፣ መደቦች ፣ ይገባል ። ይኸውም ፣ መጥቼ ፣ ነበር ፤ መጥተህ ፣ ነበርን ፤ መጥታ ፣ ነበር ፤ መጥቶ ፣ ነበር ፤ . . . እንደማለት ፣ ነው ።

— 136 —

የመኖር ፣ ግሥ ፣ « አለ » በነጠላ ፣ ቁጥር ፣ በፅኛ ፣ መደብና ፣ በሮኛ ፣ መደብ ፣ በእንስት ፣ ጾታ ፣ (መጥቼአለሁ ። መጥታለች ፣ ብሎ ፣) ከሚለወጥ ፣ በቀር ፤ በሴሎቹ ፣ ላይ ፣ መድረሻውን ፣ ሳድስ ፣ አድርን ፣ አል ፣ ተብሎ ፣ ይገባል ። ይኸውም ፣ መጥተህ ፣ አል ፤ መጥ ተሽ ፣ አል ፤ መጥቶ ፣ አል ፤ መጥተን ፣ አል ፤ መጥቼ ፣ አለሁ ፤ መጥተው ፣ አል ፤ ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ።

—137 —

አ የተወጋውን ፣ ፈደል ፣ እናግሮ ፣ ድምፁን ፣ አውርሶ ፣ መታጣት ፣ ልማዱ ፣ ነው ። ስለዚህም ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ በ136 ቁ . ያመለከትናቸው ፣ ቃላት ፣ « መጥቻለሁ ፤ ፣ መጥተሃል ፤ መጥተሻል ፣ መጥቷል ፤ መጥታለች ፣ መጥተናል ፤ መጥታችኋል ፤ መጥተዋል ፤ » ተብለው ፣ ይጸፋሉ ።

፭ኛ ፣ መልመጃ ።

(ሀ)—ግሥ ፣ ስንት ፣ ጠባዮች ፣ አሉት ? ግሥ ፣ ማለት ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው ?
በዚር ፣ ግሥ ፣ የሚነገር ፣ ፭ ዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ጻፍ ።
በተገብሮ ፣ ግሥ ፣ የሚነገር ፣ ፭ ዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ጻፍ ።
የግይሽገር ፣ ግሥ ፣ እንዲት ፣ ያለ ፣ ዓይነት ፣ ነው ። ?
ከግይሽገር ፣ ግሥ ፣ ፭ ፣ ቃላትን ፣ ተናገር ።
ከተሻጋሪ ፣ ግሥ ፣ ፯ ፣ ቃላትን ፣ ተናገር ።
ወላዋይ ፣ ግሥ ፣ እንዲት ፣ እንደሆን ፣ በምሳሌ ፣ አስረዳ ።
ነባር ፣ ግሥ ፣ የተባሉትን ፣ ቃላት ፣ ቆጥረህ ፣ አስታውቅ ።

(ለ)—ከዚህ ፣ በታች ፣ ከተጻፈው ፣ ምንባብ ፣ ግሦችን ፣ በየጠባያቸውና ፣ በየዓይነ ታቸው ፣ እየለየህ ፣ አስታውቅ ።

ምንባብ ።

መርድ ፣ አዝማች ፣ ወሰን ፣ ሰገድ ፣ በአባቱ ፣ በመርድ ፣ አዝማች ፣ አስፋ ፣ ወሰን ፣ ዘመን ፣ አበጋዝ ፣ ሆኖ ፣ በውሳጤነት ፣ ይገዛ ፣ ነበር ። አበቱ ፣ ሲሞቱ ፣ አልጋውን ፣ ያዘ ። ሰውየውም ፣ ኃይለኛና ፣ ስመ ፣ ጥር ፣ ጀግና ፣ ነበር ፣ ይባላል ። በጋሸው ፣ ብዙ ፣ አገሮችን ፣

አቅንታል ። ከተማውን ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ሰፍራ ፣ አይቶ ፣ ቁንዲ ፣ ላይ ፣ አደረገው ። ያጤ ፣ ዘርፀ ፣ ያዕቆብ ፣ ከተማ ፣ የነበረውን ፣ ይብረ ፣ ብርሃንን ፣ እንደገና ፣ የመሠረተ ፣ እርሱ ፣ ነው ። ይብረ ፣ ሲባሃስንና ፣ ሌሎችንም ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ ለመሥራት ፣ አስጀምሮ ፣ ነበር ።

መርድ ፣ አዝማች ፣ ወሰን ፣ ሰገድ ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ሕዝቡን ፣ ሰበሰበና ፣ ስሜን ፣ ራስ ፣ ብለህ ፣ ጥራኝ ፣ አለዚያ ፣ እቀጣሃለሁ ፣ ብሎ ፣ አስገደደው ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ራስ ፣ ወሰን ፣ ሰገድ ፣ እየተባለ ፣ ይጠራ ፣ ጀመር ። እያደረም ፣ ኃይል ፣ ተሰማውና ፣ ወደ ፣ ጎንደር ፣ ለመዝ መት ፣ አሰበ ፣ በዚያ ፣ ዘመን ፣ ወደንበረው ፣ ወደ ፣ ራስ ፣ ጉግሣ ፣ እነሆ ፣ መምጣቱ ፣ ነውና ፣ ድልድል ፣ ሰፍራ ፣ ይዘህ ፣ ጠብቀኝ ፣ ብሎ ፣ ላከበት ፣ ይባላል ። ነገር ፣ ግን ፣ መኳንንቶቹ ፣ ወደ ፣ ጎንደር ፣ መዝመትን ፣ አልወደዱምና ፣ በአንድ ፣ ጠንቋይ ፣ ምክር ፣ ብርቱውን ፣ አሳ ብን ፣ አደከመት ። ሲዝልም ፣ አይተው ፣ ሰኔ ፣ ፭ ፣ ቀን ፣ (ሰም) ፲፰፻፩ ፣ ዓ ፣ ም ፣ በፎ ፣ በባሪ ያው ፣ እጅ ፣ አስገደሉትና ፣ ባቀናው ፣ ከተማ ፣ በቁንዲ ፣ ተቀበረ ። ራስ ፣ ወሰን ፣ ሰገድ ፣ የግዛቱ ፣ ዘመን ፣ ፬ ፣ ዓመት ፣ ተመንፈቅ ፣ ያህል ፣ ነው ። —ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ልጁ ፣ ግሀለ ፣ ሥላሴ ፣ በዙፋኑ ፣ ተተክ ።

ክፍል ፣ ፪ ፣ አዕማድ ።

— 138 —

መግለጫ ፣

አዕማድ ፣ የሚባሉት ፣ ለግሥ ፣ አርባታ ፣ መነሻ ፣ መቋቋሚያ ፣ የሚሆኑት ፣ ግሦች ፣ ናቸው ። በነጠላ ፣ ቁጥር ፣ ዐምድ ፣ ይባላል ። በብዙ ፣ ቁጥር ፣ ግን ፣ አዕማድ ፣ ወይም ፣ ዐምዶች ፣ ያሰኛል ፣ የዐምድ ፣ ትርጓሜው ፣ ምሰሶ ፣ ማለት ፣ ነው ። ምሰሶ ፣ ቤትን ፣ አጽንቶ ፣ እንዲያቆመው ፣ በነዚህም ፣ ግሦች ፣ አንቀጾች ፣ ይቋቋሙ-በትዋልና ፣ በዚህ ፣ ምሳሌ ፣ ተሰይሟል ።

— 139 —

የአዕማድ ፣ ደንበኛ ፣ ቁጥራቸው ፣ ፭ ፣ ነው ። እነርሱም ፣ አድራጊ ፣ አስደራጊ ፣ አደራራጊ ፣ ተደራጊ ፤ ተደራራጊ ፣ ተብለው ፣ ይጠራሉ ። ከነዚህም ፣ አደራራጊና ፣ ተደራ ራጊ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ድርብ ፣ ዐምድ ፣ ይዘው ፣ ይገኛሉ ። እንዲህም ፣ ሲሆን ፣ አዳራጊ ፣ ተዳራጊ ፣ የሚባሉ ፣ ዘመዳም ፣ የሆኑ ፣ ሌሎች ፣ ፪ ፣ አዕማድ ፣ ይጨመሩበትውና ፣ የአዕማድ ፣ ቁጥር ፣ እስከ ፣ ፯ ፣ ይደርሳል ።

— 140 —

ማናቸውም ፣ ግሥ ፣ የአዕማድን ፣ ደንብ ፣ በሙሉ ፣ ወይም ፣ በከፊል ፣ መፈጸም ፣ አለበት ።

— 141 —

አዕማድ ፡ በርኖ ፡ መደብ ፡ በሚነገረው ፤ ተባዕታይ ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ በሆነው ፡ ፀላፊ ፡ የግሥ ፡ ቃል ፡ ይነገራሉ ። ይኸም ፡ ገደለ ፤ አስገደለ ፤ አገዳደለ ፤ አጋደለ ፤ ተገደለ ፤ ተገዳደለ ፤ ተጋደለ ፡ እንደማለት ፡ ነው ። የግሦች ሥር ፡ ከንሡስ ፡ አንቀጽ ፡ እንደሆነ ፡ መደረት ፡ እንናገረዋለን ። እንደ ፡ ሕጉ ፡ ፪ሆን ፡ አዕማድም ፡ በንሡስ ፡ አንቀጽ ፡ ሊነገሩ ፡ በተገባ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ መገደል ፤ ማስገደል ፤ ማገዳደል ፡ ማጋደል ፤ መገደል ፡ መገዳደል ፤ መጋደል ፡ እንደማለት ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በግዕዙ ፡ ትምህርት ፡ በጎሳሬ ፡ የግሥ ፡ ቃል ፡ እየተነገሩ ፡ ስለተለመዱ ፡ አሁንም ፡ በዚያው ፡ ልማድ ፡ ተጽፈዋል ።

— 142 —

የአዕማድ ፡ ዓይነት ።

አዕማድ ፡ ጽኑዓን ፡ ድኩማን ፡ ተብለው ፡ በ፪ ፡ ዓይነት ፡ ይመደባሉ ። ጽኑዓን ፡ የሚባሉት ፡ ከፎ ፡ እስከ ፡ ኗ ፡ መደብ ፡ ለመድረስ ፡ የሚችሉት ፡ ናቸው ። ድኩማን ፡ የሚባሉትም ፡ ከፎ ፡ መደብ ፡ በታች ፡ የሚቀሩት ፡ ናቸው ።

— 143 —

ከጽኑዓን ፡ ወገዶች ፡ ገደለ ፤ ፈለገ ፤ ማለ ፤ ገባ ፤ ከድኩማን ፡ ወገዶች ፡ ዘነመ ፤ ተኛ ፤ በተባሉት ፡ ግሦች ፡ የአመዳደበቸውን ፡ ምሳሌ ፡ እናሳያለን ።

የግሡ ፡ ሥር ፡	አድራጊ ፡	አስደራጊ ፡	አደራራጊ ፡	አዳራጊ ፡	ተደራጊ ፡	ተደራራጊ ፡	ተዳራጊ ፡
ሙገደል ፡	ገደለ ፡	አስገደለ ፡	አገዳደለ ፡	አጋደለ ፡	ተገደለ ፡	ተገዳደለ ፡	ተጋደለ ፡
መፈለግ ፡	ፈለገ ፡	አስፈለገ ፡	አፈላለገ ፡	አፍለገ ፡	ተፈለገ ፡	ተፈላለገ ፡	ተፋለገ ፡
መማል ፡	አማለ ፡	አስማለ ፡	አማማለ ፡	— —	ማለ ፡	ተማማለ ፡	— —
መተው ፡	ተወ ፡	አስተወ ፡	— —	— —	ተተወ ፡	— —	— —
መዝነም ፡	አዝነመ ፡	አስዘነመ ፡	— —	— —	ዘነመ ፡	— —	— —
መተኛት ፡	— —	አስተኛ ፡	— —	— —	ተኛ ፡	— —	— —

— 144 —

አዕማድ ፡ መነሻቸውን ፡ በግዕዝ ፡ በራብዕ ፡ በኃምስ ፡ በሳብዕ ፡ ፊደል ፡ ያደርጋሉ ። ይኸውም ፡ ገደለ ፡ ማለ ፡ ሄደ ፡ ቆመ ፡ እንደማለት ፡ ነው ። መድረሻቸውንም ፡ በግዕዝና ፡ በራብዕ ፡ ፊደል ፡ ያደርጋሉ ። ይኸውም ፡ ፈለገ ፡ ገባ ፡ እንደማለት ፡ ነው ።

— 145 —

አዕማድ ፡ ከ፪ ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ በሆኑ ፡ ፊደላት ፡ ይነገራሉ ። ይኸውም ፡ አየ ፤ ፈለገ ፤ ተረጐመ ፤ አፈገፈገ ፤ አጮረመረመ ፤ እንደማለት ፡ ነው ።

—146—

ከአዕማድ ፡ ወገን ፡ በ፩ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ የሚነገር ፡ የለም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሸ ፡ የሚል ፡ አድራጊ ፡ ፀምድ ፡ በ፩ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ ሊነገር ፡ ይገኛልና ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ነው ።

—147—

ሸ ፡ ስለሚለው ፡ ግሥ ፡ ነገር ፡ አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ና ፡ የመጣህ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ እንደሆነ ፡ ሸ ፡ የፈለግህ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። እኛ ፡ ግን ፡ ከ ፡ ና ፡ ጋራ ፡ አናነጻጽረውም ። ሸ ፡ ለፈለግህ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ድኩም ፡ ፀምድ ፡ ነው ፡ እንላለን ። ምክንያቱም ፡ ና ፡ በርቱ ፡ መደቦች ፡ ሊዘረዘር ፡ አይችልም ። ሸ ፡ ግን ፡ ሸው ፡ ሸህ ፡ ሻሽ ፡ ሸች ፡ ሽ ፡ እያለ ፡ በርቱ ፡ መደቦች ፡ እየገባ ፡ በርቱም ፡ ጊዜያቶች ፡ ሊረባ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ።

የቃልን ፡ ሞክሼነት ፡ ለመለየት ፡ እሸ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ ብለው ፡ የሚበይኑ ፡ መምህራን ፡ አሉ ። ምክንያቱም ፡ እሸ ፡ ሲል ፡ ግሥ ፡ ሽ ፡ ሲል ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ የሚከተሉትን ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባሉ ።

(ሀ) መጻሕፍትን ፡ እሸ ፡ መርምር ። (ግሥ ፡)

(ለ) የሰናፍጭ ፡ ምግብ ፡ ሆድን ፡ ሽ ፡ ያደርጋል ። (ተውሳክ ፡ ግሥ ፡)

ይህንን ፡ ብያኔ ፡ ደራሲው ፡ አይቃወመውም ።

—148—

የአዕማድ ፡ ጠባይ ።

የአዕማድ ፡ ጠባያቸው ፡ ገቢር ፡ ወይም ፡ ተገብሮ ፡ ነው ። የገቢር ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ፀምዶች ፡ አድራጊ ፡ አስደራጊ ፡ አደራራጊ ፡ አዳራጊ ፡ ናቸው ። የተገብሮ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸውም ፡ ተደራጊ ፡ ተደራራጊ ፡ ተዳራጊ ፡ ናቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ የሚጣስበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። እርሱንም ፡ በአገባብ ፡ ክፍል ፡ ይመለከታል ።

—149—

ከአዕማድ ፡ ውስጥ ፡ አድራጊ ፡ ወይም ፡ ተደራጊ ፡ ፀምድ ፡ አርእስት ፡ አሰማድ ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ርእሰ ፡ ፀምድ ፡ ያሰኛል ። ትርጓሜው ፡ የአዕማድ ፡ ራስ ፡ ወይም ፡ ሥር ፡ ማለት ፡ ነው ።

—150—

አድራጊና ፡ ተደራጊ ፡ ዐምዶች ፡ የአዕማድ ፡ ራሶች ፡ መበላቸው ፡ ማናቸውም ፡ ግሥ ፡ በባዕድ ፡ መነሽ ፡ ረዳትነት ፡ ከነሱ ፡ ስለሚመሠረት ፡ ነው ። አድራጊና ፡ ተደራጊ ፡ ዐምዶች ፡ ግን ፡ በዕድ ፡ መነሽን ፡ አይሹም ።

አድራጊ ፡ ዐምድ ፡ መሠረት ፡ ሲሆን ፡ ተደራጊውን ፡ ከዚያው ፡ ከርሱ ፡ ያስገኛል ። ይኸም ፡ ገደለ ፡ ብሎ ፤ ተገደለ ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ተደራጊ ፡ ዐምድም ፡ መሠረት ፡ ሲሆን ፡ አድራጊውን ፡ ከርሱ ፡ ያስገኛል ። ይኸም ፡ መጣ ፡ ብሎ ፤ አመጣ ፡ እንደ ማለት ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

—151—

በዕድ ፡ መነሽ ፡

አርእስተ ፡ አዕማድ ፡ ከሚሆኑት ፡ ግሦች ፡ በቀር ፡ ለአዕማድ ፡ ሁሉ ፡ በዕድ ፡ መነሽ ፡ አላቸው ። እነአርሱም ፡ አ ፡ አስ ፡ አስተ ፡ ተ ፡ ናቸው ። በ ፡ አ ፡ ፊደል ፡ የሚነሣ ፡ ግሥ ፡ ሲገዋግቸውም ፡ ራብዕ ፡ ይሆናሉ ። ይኸውም ፡ አሰ ፡ አስታ ፡ ታ ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። አስተ ፡ የሚለው ፡ በዕድ ፡ መነሽ ፡ በዋቂቶች ፡ ግሦች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል ።

አ	የአድራጊ ፡	በዕድ ፡	መነሽ ፡	ይሆናል ፡	አድ.	መጣ ፡ ብሎ ፡ አመጣ ፡ ይላል ።
	የአደራራጊ	»	»	»	»	ፈለገ ፡ ብሎ ፡ አፈላለገ ፡ ይላል ።
	የአዳራጊ ፡	»	»	»	»	ፈለገ ፡ ብሎ ፡ አፋለገ ፡ ይላል ።
አስ	የአስደራጊ ፡	»	»	»	»	ፈለገ ፡ ብሎ ፡ አስፈለገ ፡ ይላል ።
አስተ	የአደራራጊ ፡	»	»	»	»	አወቀ ፡ ብሎ ፡ አስተዋወቀ ፡ ይላል ።
ተ	የተደራጊ ፡	»	»	»	»	ፈለገ ፡ ብሎ ፡ ተፈለገ ፡ ይላል ።
	የተደራራጊ ፡	»	»	»	»	ፈለገ ፡ ብሎ ፡ ተፈላለገ ፡ ይላል ።
	የተዳራጊ ፡	»	»	»	»	ፈለገ ፡ ብሎ ፡ ተፋለገ ፡ ይላል ።

—152—

ጥንት ፡ ቀለማቸው ፡ በ ፡ አ ፡ በ ፡ ተ ፡ የሚጀመር ፡ የአዕማድ ፡ ሥሮች ፡ (=አድራጊ ፡ ተደራጊ) ፡ በተነገሩ ፡ ጊዜ ፡ አ ፡ ተ ፡ በዕድ ፡ መነሽ ፡ እንዳይበሉ ፡ እወቅ ። አ ፡ ወይም ፡ ተ ፡ ጥንተ ፡ ቀለም ፡ የሚሆኑዋቸው ፡ የአዕማድ ፡ ሥሮች ፡ (አርእስተ ፡ አዕማድ) ፡ በጣም ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ ጥቂቶችን ፡ እንጽፋለን ።

አ	አየ ፤ አወቀ ፤ አሰበ ፤ አበበ ፤ አመለጠ ፤ አፈጠጠ ፤	(አድራጊ ፡ ርእሰ ፡ ዐምድ ፡) (ተደራጊ ፡ ርእሰ ፡ ዐምድ ፡)
ተ	ተረጐመ ፤ ተለመ ፤ ተወ ፤ ተኰሰ ፤ ተነሣ ፤ ተረፈ ፤	(አድራጊ ፡ ርእሰ ፡ ዐምድ ፡) (ተደራጊ ፡ ርእሰ ፡ ዐምድ ፡)

አ ፡ ተ ፡ ጥንተ ፡ ቀለም ፡ የሚሆኑአቸውን ፡ ግሦች ፡ በልዩ ፡ ምልክት ፡ ለመወሰን ፡ አይቻልም ። የሚሸለውም ፡ ምክር ፡ ቃላቱን ፡ በተለይ ፡ ማጥናት ፡ ወይም ፡ በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ መመልከት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ግእ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) የግሥ ፡ አዕማድ ፡ ስንት ፡ ናቸው ? ። ፈለገ ፤ አገኘ ፤ ተቀመጠ ፤ ረገመ ፤ መረቀ ፡ » በተባሉት ፡ ግሦች ፡ አዕማድን ፡ እየዘረዘርህ ፡ ተናገር ።
ርእሰ ፡ አዕማድ ፡ የተባሉት ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
ርእሰ ፡ ዐምድ ፡ ከሆነው ፡ ከአድራጊ ፡ መደብ ፡ ኟ ግሦችን ፡ ለምሳሌ ፡ አምጣ ።
ርእሰ ፡ ዐምድ ፡ ከሆነው ፡ ከተደራጊ ፡ መደብ ፡ ኟ ግሦችን ፡ ለምሳሌ ፡ አምጣ ።

(ለ) ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፈው ፡ ምንባብ ፤ አዕማድን ፡ በየመደባቸው ፡ እየለየህ ፡ ተናገር ። በምንባቡ ፡ የሚገኘውን ፡ ግሥ ፡ በአዕማድ ፡ ደንብ ፡ እየዘረዘርህ ፡ ተናገር ።

ምንባብ ።

የራስ ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ ልጆች ፡ አቤቶ ፡ በሁሩና ፡ ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ ነበሩ ። ምላቁ ፡ አቤቶ ፡ በሁሩ ፡ አበጋዝነት ፡ ተሹሞ ፡ በመርሐቤቴ ፡ ቂላ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ራስ ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቀንዲ ፡ እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ቢነግሥ ፡ የጅሩ ፡ ጋላ ፡ መንገድ ፡ አሳጥቶ ፡ አስቀረው ። ስለዚህም ፡ ታናሹ ፡ ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ ከሰላ ፡ ድንጋይ ፡ ተጠርቶ ፡ መጣና ፡ በአብቴ ፡ በራስ ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ ወዲያው ፡ ንጉሠ ፡ ሸዋ ፡ ተብለው ፡ ይጠሩ ፡ ጀመር ። ሽማግሌዎቻችን ፡ እንኳ ፡ ሲጫወቱ ፡ «በታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ በማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ እንዲህ ፡ ተደረገ ፡» እያሉ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ይተርኩ ። «ራስ ፡ ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ሸዋ ፡» የሚልም ፡ ደብዳቤ ፡ ተገኝቷል ። ደግሞ ፡ «ዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘራስ ፡ ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ሸዋ ፤ ዝ ፡ ከበሮ ፡ ዘራስ ፡ ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ሸዋ ። » የሚል ፡ በየአድባራቱ ፡ በየስፍራው ፡ ይገኛል ።

ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ በአንከበር ፡ ላይ ፡ የቀዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሳንጸው ፡ አንጎለላንና ፡ ደብረ ፡ ብርሃንን ፡ ከተማ ፡ አድርገው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በዘመናቸው ፡ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ ጀግኖች ፡ እነ ፡ አቶ ፡ መተከ ፤ እነ ፡ ቋንቁሬ ፡ ባቡ ፡ እንደነበሩ ፡ ይተረክል ። ማሀሉ ፡ ሥላሴ ፡ በሕዝባቸው ፡ ዘንድ ፡ የተወደዱ ፡ ነበሩ ። ፴፱ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደገዙ ፡ ታመሙና ፡ አልጋቸውን ፡ ለትንሹ ፡ ልጃቸው ፡ ሰኅይለ ፡ መለኮት ፡ አውርሰው ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ላይ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፪ ፡ ፲፰፻፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐረፉ ። ኋ.ሥ ፡ ልጃቸው ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ አንከበር ፡ ወስደው ፡ በቀዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀበሩዋቸው ።

ክፍል ፫ ፣ የግሥ ፣ ረዳት ።

—153—

የግሥ ፣ ረዳት ፣ የሚባሉት ፣ በቦዝ ፣ አንቀጽ ፣ ላይ ፣ እየተጫኑ ፣ ከዋናው ፣ ግሥ ፣ ጋር ፣ ተቀላቅለው ፣ ማሰሪያ ፣ አንቀጽ ፣ የሚሆኑት ፣ ቃላት ፣ ናቸው ። እነርሱም ፣ በጠቅላላ ፣ የመሆንና ፣ የመኖር ፣ ግሥ ፣ ተብለው ፣ ይጠራሉ ። ማናቸውም ፣ ግሥ ፣ በአድራጊና ፣ በተደራጊ ፣ ወይም ፣ በገዢርና ፣ በተገብር ፣ የተመደበ ፣ ነው ፣ ብለናል ። ስለዚህም ፣ የመሆንና ፣ የመኖር ፣ ግሥ ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ የመደረግና ፣ የማድረግ ፣ ግሥ ፣ ቢባል ፣ በቀና ፣ ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ምሥጢሩን ፣ በመመልከት ፣ መሆን ፣ መኖር ፣ ተብሎ ፣ ተሰይሟል ።

—154—

የመሆን ፣ ግሥ ፣ በእርባታ ፣ ጊዜ ፣ «ነው ፣ ነበር ፣ ሆነ ፣ አለ ፣ (ላልቶ) ፣ ሂመረ ፣ ቂየ ፣ አገኘ ፣ » የሚባሉትን ፣ ቃላት ፣ በየስልቱ ፣ ይዘ ፣ ይገኛል ።) በግዕዝ ፣ ከዊን ፣ ከዊኖ ፣ ይላል ፣) ማናቸውም ፣ ተደራጊ ፣ ግሥ ፣ በምሥጢር ፣ የመሆን ፣ ግሥ ፣ ወገን ፣ ነው ።

—155—

የመኖር ፣ ግሥ ፣ በእርባታ ፣ ጊዜ ፣ «አለ ፣ (ጠብቆ ፣) ነበረ ፣ » የሚባሉትን ፣ ቃላት ፣ ይዘ ፣ ይገኛል ።

መኖር ፣ የሚባለው ፣ ቃል ፣ በሁለት ፣ ትርጓሜ ፣ ይፈታል ። አለኝታን ፣ ወይም ፣ አለኝ ፣ ማለትን ፣ የሚገልጽ ፣ ሲሆን ፣ ነባር ፣ ግሥ ፣ ነው ፣ በግዕዙ ፣ ቦ ፣ ነው ። ሲዘረዘርም ፣ ብየ ፣ ብክ ፣ ብኪ ፣ ቦቱ ፣ . . . ይላል ። ቦ ፣ መኖር ፣ ሲሆን ፣ «እምኀበ ፣ ቦ ፣ ኀበ ፣ አልቦ ፣ » ይላል ። የዚህም ፣ ትርጓሜው ፣ ከመኖር ፣ ወደ ፣ አለመኖር ፣ ወይም ፣ ከመገኘት ፣ ወደ ፣ አለመገኘት ፣ ማለት ፣ ነው ።

መኖር ፣ የሚባለው ፣ ቃል ፣ የኑሮን ፣ ወይም ፣ የሕይወትን ፣ ምግባር ፣ የሚገልጽ ፣ ሲሆን ፣ ራሱን ፣ የቻለ ፣ ተደራጊ ፣ ግሥ ፣ ይሆናል ። በግዕዝ ፣ ሐዩ ፣ ሐይዎት ፣ ወይም ፣ ሀልዎ ፣ ህላዎት ፣ የሚለው ፣ ነው ። ሀልዎ ፣ ሀልዎት ፣ ከነባሩ ፣ ግሥ ፣ ጋራ ፣ የሚስማማ ዘይ ፣ ጊዜያት ፣ አለና ፣ በጥንቃቄ ፣ መመልከት ፣ ያስፈልጋል ።

—156—

በመሆንና ፣ በመኖር ፣ ግሥ ፣ ላይ ፣ እየተጨመሩ ፣ የሚነገሩ ፣ ቃላት ፣ ረዳቶቹን ፣ ችላው ፣ በተነገሩ ፣ ጊዜ ፣ ግሦች ፣ ተብለው ፣ ይጠራሉ ። እንደሌላውም ፣ ግሥ ፣ ሊረቡ ፣ ይችላሉ ። በጎላፊ ፣ ቦዝ ፣ ወይም ፣ በትንቢት ፣ ቦዝ ፣ ላይ ፣ እየተጨመሩ ፣ በገቡ ፣ ጊዜ ፣ ግን ፣ ረዳቶች ፣ ይባላሉ ። ጎላፊ ፣ ቦዝና ፣ ትንቢት ፣ ቦዝ ፣ ምን ፣ እንደሆነ ፣ ወደፊት ፣ በስፋ ፣ ራው ፣ ይነገራል ፣ (ቁ. 181—185 እይ ።)

—157—

ነው ።

ነው ፣ ለመሆን ፣ ግሥ ፣ የአሁን ፣ ጊዜያት ፣ ነው ። ሥረ ፣ ነገሩ ፣ ነ ፣ ነው ። የእርባታ ፣ መሪዎች ፣ «ኝ ፣ ህ ፣ ሽ ፣ ም ፣ ች ፣ ው ፣ ን ፣ አችሁ ፣ አቸው ፣ » እየተጨመሩበት ፣ በር ቱም ፣ መደቦች ፣ በአሁን ፣ ጊዜያት ፣ ይረባል ። እነሆ ፣ በአምንታና ፣ በአሉታ ፣ እንዲት ፣ እንደሚረባ ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ እናመልክታለን ።

መደብ ፣ ጾታ ፣		አምንታ ፣		አሉታ ፣	
		ነጠላ ፣	ብዙ ፣	ነጠላ ፣	ብዙ ፣
ሰኛ ፣	የወል ፣	ነኝ ፣	ነን ፣	አይደለሁም ፣	አይደለንም ፣
፪ኛ ፣	ተባ.	ነህ ፣	ናችሁ ፣	አይደለህም ፣	አይደላችሁም ፣
	እን.	ነሽ ፣	»	አይደለሽም ፣	»
፫ኛ ፣	ተባ.	ነው ፣	ናቸው ፣	አይደለም ፣	አይደሉም ፣
	እን.	ነች ፣ (ናት ፣)	»	አይደለችም ፣	»

—158—

ነበረ ።

ነበረ ፣ ለመሆን ፣ ወይም ፣ ለመኖር ፣ ግሥ ፣ ረዳት ፣ ይሆናል ።

በመሆን ፣ ግሥ ፣ ክፍል ፣ ረዳት ፣ ሆኖ ፣ ሲነገር ፣ መድረሻውን ፣ ሰይስ ፣ አድርጎ ፣ «ነበር ። » ተብሎ ፣ ይገባል ፣ በጎላፊ ፣ ወይም ፣ በትንቢት ፣ ቦዝ ፣ ላይ ፣ እየተጫነ ፣ ይረባል ። በጎላፊ ፣ ቦዝ ፣ ላይ ፣ ሲገባ ፣ የሩቅ ፣ ጎላፊ ፣ በትንቢት ፣ ቦዝ ፣ ላይ ፣ ሲገባ ፣ አዋዋይ ፣ አንቀጽ ፣ ይሆናል ።

በጎላፊ ፣ ቦዝ ፣ አንቀጽ ፣ ሲገባ ፣ እንደሚከተው ፣ ይሆናል ።

መደብ ፣ ጾታ ፣		አምንታ ፣		አሉታ ፣	
		ነጠላ ፣	ብዙ ፣	ነጠላ ፣	ብዙ ፣
ሰኛ ፣	የወል.	መጥዩ ፣ ነበር ፣	መጥተን ፣ ነበር ፣	አልመጣውም ፣ ነበር ፣	አልመጣንም ፣ ነበር ፣
፪ኛ ፣	ተባ.	መጥተህ ፣ ነበር ፣	መጥታችሁ ፣ ነበር ፣	አልመጣህም ፣ ነበር ፣	አልመጣችሁም ፣ ነበር ፣
	እን.	መጥተሽ ፣ ነበር ፣	» »	አልመጣሽም ፣ ነበር ፣	» »
፫ኛ ፣	ተባ.	መጥቶ ፣ ነበር ፣	መጥተው ፣ ነበር ፣	አልመጣም ፣ ነበር ፣	አልመጡም ፣ ነበር ፣
	እን.	መጥታ ፣ ነበር ፣	» »	አልመጣችም ፣ ነበር ፣	» »

የተለመደውን ፣ ንግግር ፣ በመከተል ፣ መጥቼ ፣ ነበር ፣ ያለውን ፣ በአሉታ ፣ አልመጣሁም ፣ ነበር ፣ ብለን ፣ ጽፈናል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ በሳሜም ፣ አማርኛ ፣ ከላይ ፣ የተጻፉት ፣ አሉታዎች ፣ «አልመጥቼም ፣ ነበር ፣ አልመጥሀም ፣ ነበር ፣ ..... » ተብለው ፣ ሲነገሩ ፣ ይሰማሉ ። ይኸውም ፣ ቃል ፣ መጥቼ ፣ ነበር ፣ ከሚለው ፣ ከሥረ ፣ ነገሩ ፣ ጋር ፣ የተስማማ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ መልክም ፣ ውሳኔ ፣ መሆኑ ፣ እያጠረጠርም ። የመጣሁ ፣ አሉታ ፣ አልመጣሁም ፣ ሊሆን ፣ የተገባ ፣ ነው ። የመጥቼ ፣ ነበር ፣ አሉታም ፣ አልመጥቼም ፣ ነበር ፣ ቢል ፣ ትክክለኛ ፣ ሥንሥር ፣ ነው ።

—159—

በትንቢት ፣ ቦዝ ፣ ላይ ፣ ሲገባ ፣ እንደሚከተለው ፣ ይሆናል ።

መደብ ፣ ጾታ ፣		አምንታ ፣		አሉታ ፣	
		ነጠላ ፣	ብዙ ፣	ነጠላ ፣	ብዙ ፣
፩ኛ ፣	የወል ፣	እመጣ ፣ ነበር ፣	እንመጣ ፣ ነበር ፣	አልመጣም ፣ ነበር ፣	እንመጣም ፣ ነበር ፣
፪ኛ ፣	ተባ ፣	ትመጣ ፣ ነበር ፣	ትመጡ ፣ ነበር ፣	አትመጣም ፣ ነበር ፣	አትመጡም ፣ ነበር ፣
	እን ፣	ትመጪ ፣ ነበር ፣	» »	አትመጪም ፣ ነበር ፣	» »
፫ኛ ፣	ተባ ፣	ይመጣ ፣ ነበር ፣	ይመጡ ፣ ነበር ፣	አይመጣም ፣ ነበር ፣	አይመጡም ፣ ነበር ፣
	እን ፣	ትመጣ ፣ ነበር ፣	» »	አትመጣም ፣ ነበር ፣	» »

—160—

ነበረ ፣ በረዳትነት ፣ ሲገባ ፣ የግሥ ፣ አመሉን ፣ ሳይተው ፣ ይረባል ፣ የሚሉ ፣ አሉ ። ይኸውም ፣ «መጥቼ ፣ ነበርሁ ፤ መጥተህ ፣ ነበርህ ፤ መጥተሽ ፣ ነበርሽ ፤ ..... አልመጣሁም ፣ ነበርሁ ፤ አልመጣህም ፣ ነበርህ ፤ አልመጣሽም ፣ ነበርሽ ፤ .....» ያሰኛል ፣ ማለት ፣ ነው ። ይህ ፣ ንግግር ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ የተለመደ ፣ ቢሆን ፣ ደራሲው ፣ የላይኛውን ፣ ውሳኔ ፣ (ቁ. 159 ፤) በመምረጥ ፣ ያጸናዋል ።

—161—

ነበረ ፤ በመኖር ፣ ግሥ ፣ ክፍል ፣ ሲነገር ፣ የእርባታ ፣ መሪዎች ፣ «ኝ ፣ ሀ ፤ ሽ ፣ ሙ ፣ ት ፣ ን ፣ አችሁ ፣ አቸሙ ፤» እየተጨመሩበት ፣ በጎላፊ ፣ ጊዜያት ፣ በቮቱም ፣ መደቦች ፣ ይረባል። እነሆ ፣ በአምንታና ፣ በአሉታ ፣ እንዲት ፣ እንደሚረባ ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ እናመለክታለን ።

መደብ ፣ ጾታ ፣		አምንታ ፣		አሉታ ፣	
		ነጠላ ፣	ብዙ ፣	ነጠላ ፣	ብዙ ፣
፩ኛ ፣	የወል ፣	ነበረኝ ፣	ነበረን ፣	አልነበረኝም ፣	አልነበረንም ፣
፪ኛ ፣	ተባ ፣	ነበረህ ፣	ነበራችሁ ፣	አልነበረህም ፣	አልነበራችሁም ፣
	እን ፣	ነበረሽ ፣	»	አልነበረሽም ፣	»
፫ኛ ፣	ተባ ፣	ነበረው ፣	ነበራቸው ፣	አልነበረውም ፣	አልነበራቸውም ፣
	እን ፣	ነበራት ፣	»	አልነበራትም ፣	»

— 162 —

ሆነ ።

ሆነ ፣ መሠረቱ ፣ ከመሆን ፣ ግሥ ፣ ነው ። ራሱን ፣ ችሎ ፣ እንደ ፣ ግሥ ፣ ደንብ ፣ በየዋህም ፣ በዝርዝርም ፣ እርባታ ፣ ይረባል ። በረዳትነት ፣ መልክ ፣ ሲገባ ፣ በትንቢት ፣ አንቀጽ ፣ ላይ ፣ እየተመጨረ ፣ በቁም ፣ ቀሪ ፣ ሆኖ ፣ ይረባል ።

ይኸውም ፤ ይመጣል ፣ ሆነ ፤ ትመጣለች ፣ ሆነ ፤ ትመጣለህ ፣ ሆነ ፤ ይመጣሉ ፣ ሆነ ፤ ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ ሆነ ፣ ምክንያትን ፣ ሰጭ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ዋና ፣ ረዳት ፣ አይደለም ። ምክንያትም ፣ እነሆ ፣ ወይም ፣ ስለ ፣ በሚል ፣ አገባብ ፣ የሚተካ ፣ ስለሆነ ፣ ነው ። ማሰሪያው ፣ የኖያቄ ፣ ወይም ፣ የእንከር ፣ አንቀጽ ፣ ነው ።

አስረጅ ፡—ውብሸት ፣ ይማማላል ፣ ሆነ ፤ ምን ፣ ማድረግ ፣ ይሻላል ?

(=እነሆ ፣ ውብሸት ፣ ማገጠ ፣ ምን ፣ ማድረግ ፣ ይሻላል ?)

(=ውብሸት ፣ ስለማገጠ ፣ (ወይም ፣ የሚማማጥ ፣ ስለሆነ ፣) ምን ፣ ማድረግ ፣ ይሻላል ?)

—163 —

ይሆናል ።

ይሆናል ፣ በትንቢት ፣ አንቀጽነት ፣ በሁለት ፣ ወገን ፣ ያገለግላል ፤ ለደንበኛው ፣ ግሥ ፣ ለመሆን ፣ ትንቢት ፣ አንቀጽ ፣ ነው ።

ለነባሩ ፣ ግሥ ፣ ለመሆንም ፣ ትንቢት ፣ አንቀጽ ፣ ነው ። በነርሱም ፣ መካከል ፣ ልዩ ነቱ ፣ ሊታወቅ ፣ አይቻልም ።

የግሥ ፣ ረዳት ፣ ሲሆን ፣ በጎላፊና ፣ በትንቢት ፣ ቦዝ ፣ ላይ ፣ እየተጫነ ፣ ይገባል ። ይኸውም ፣ መጥቶ ፣ ይሆናል ፣ ይመጣ ፣ ይሆናል ፣ እንደማለት ፣ ነው ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አጠራጣሪ ፣ አንቀጽ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ።

— 164 —

አለ ፣ (በማጥበቅ ፣ ድምፅ ።)

አለ ፣ በማጥበቅ ፣ ድምፅ ፣ ሲነገር ፣ ፩ኛ ፣ በመሆን ፣ ግሥ ፣ ፪ኛ ፣ በመኖር ፣ ግሥ ፣ ክፍል ፣ ይገባል ።

(፩ኛ) በመሆን ፣ ግሥ ፣ ክፍል ፣ ሲነገር ፣ እንደሚከተለው ፣ ይሆናል ።

(ሀ) የእርባታ ፣ መሪዎች ፣ ሁ ፣ ህ ፣ ሽ ፣ ች ፣ ን ፣ አችሁ ፣ አቸው ። እየተጨመሩበት ፣ በቮቱም ፣ መደቦች ፣ ይረባል ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ ስመሆን ፣ ግሥ ፣ የቅርብ ፣ ጊዜያት ፣ ይሆናል ። በአምንታና ፣ በአሉታ ፣ እንደሚከተለው ፣ ይረባል ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		አምንታ ፡		አሉታ ፡	
		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡	የወል ፡	አለሁ ፡	አለን ፡	የለሁም ፡	የለንም ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	አለህ ፡	አላችሁ ፡	የለህም ፡	የላችሁም ፡
	አን.	አለሽ ፡	»	የለሽም ፡	»
፫ኛ ፡	ተባ.	አለ ፡	አሉ ፡	የለም ፡	የሉም ፡
	አን.	አለች ፡	»	የለችም ፡	»

— 165 —

(ለ) የግሥ ፡ ረዳት ፡ ሲሆን ፡ በጎላፊና ፡ በትንቢት ፡ በዝ ፡ ላይ ፡ ተጫኖ ፡ እየገባ ፡ በሰስቱም ፡ መደቦች ፡ ይረባል ። በጎላፊ ፡ ቦዝ ፡ ሲገባ ፡ ግሡን ፡ የቅርብ ፡ ጎላፊ ፡ ያደርገዋል ። በትንቢት ፡ ቦዝ ፡ ሲገባ ፡ ግሡን ፡ የአሁን ፡ ጊዜያት ፡ ወይም ፡ ትንቢት ፡ ያደርገዋል ። መድረሻውን ፡ ላድስ ፡ አድርጎ ፡ «አል ፡» ተብሎ ፡ በአንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ይነገራል ። ይኸን ንም ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		የቅርብ ፡ ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡		የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡	
		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡	የወል ፡	መጥፎአለሁ=መጥቻለሁ ፡	መጥተንአለንመጥተናል	እመጣለሁ=እመጣለሁ ፡	እንመጣለን ፡ =እንመጣለን ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	መጥተህ አለህ=መጥተሃል ፡	መጥታችሁ ፡ አላችሁ ፡	ትመጣለህ=ትመጣለህ ፡	ትመጡአላችሁ
	አን.	መጥተሽአለሽ=መጥተሻል ፡	=መጥታችኋል ፡ » »	ትመጪአለሽ=ትመጫለሽ ፡	ትመጣላችሁ ፡ »
፫ኛ ፡	ተባ.	መጥቶአል ፡ =መጥቷል ፡	መጥተውአል=መጥተዋል	ይመጣል=ይመጣል ፡	ይመጡአሉ ፡ =ይመጣሉ ፡
	አን.	መጥታ ፡ አለች=መጥታለች ፡	» »	ትመጣአለች=ትመጣለች ፡	

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ አርባታ ፡ በአምንታ ፡ መደብ ፡ ነው ። በአሉታም ፡ ሲረባ ፡ «አልመጣሁም ፡ አልመጣም ፡ . . . » ያሰኛል ። «አልመጥቼም ፡ አልመጥተሀም ፡» የሚለው ፡ የጎጃሞች ፡ አማርኛ ፡ ስሥረ ፡ ነገሩ ፡ የተመቸና ፡ የተስማማ ፡ ነው ። አስተውል ፡ የአ ፡ ፊደል ፡ አናጋሪ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ መጥቶአል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መጥቷል ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ።

— 166 —

(፪ኛ ፡) በመኖር ፡ ግሥ ፡ (ወይም ፡ በአለኝታ ፡ ግሥ ፡) ሲነገር ፡ እንደሚከተለው ፡ ይሆናል ። የአርባታ ፡ መሪዎች ፡ «ኝ ፡ ህ ፡ ሽ ፡ ው ፡ ት ፡ ን ፡ አችሁ ፡» አሞው ፡ እየተጫኑ በት ፡ በቮቱም ፡ መደቦች ፡ ይረባል ።

እነሆ ፡ በአምንታና ፡ በአሉታ ፡ እንዲት ፡ እንደሚረባ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ጽፈን ፡ እናመለክታለን ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		አምንታ ፡		አሉታ ፡	
		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡	የወል	አለኝ ፡	አለን ፡	የለኝም ፡	የለንም ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	አለህ ፡	አላችሁ (=አለአችሁ ፡)	የለህም ፡	የላችሁም ፡
	አን.	አለሽ ፡	» »	የለሽም ፡	»
፫ኛ ፡	ተባ.	አለው ፡	አላቸው (=አለአቸው ፡)	የለውም ፡	የላቸውም ፡
	አን.	አላት ፡	» »	የለችም ፡	»

— 167 —

አለ ፡ (በግላላት ፡ ድምፅ ፡)

አለ ፡ በመሳላት ፡ ድምፅ ፡ ሲነገር ፡ በሁለት ፡ ዓይነቶች ፡ ይተረጐማል ። ሁለቱም ፡ ዓይነቶች ፡ በምስጠር ፡ እንጂ ፡ በጽሕፈት ፡ አይለያዩም ።

የመናገርን ፡ ምግባር ፡ ሲገልጽ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ አድራጊ ፡ ዐምድ ፡ ይሆናል ። ትርጓሜው ፡ ተናገረ ፡ ማለት ፡ ነው ። በጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ እንደሌላው ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ የራሱን ፡ በዝ ፡ ይዘ ፡ ይረባል ።

(ሀ) ፡ በአሁን ፡ ጊዜያት ፡ በአምንታና ፡ በአሉታ ፡ እንዲት ፡ እንደሚረባ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እናመለክታለን ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		አምንታ ፡		አሉታ ፡	
		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡	የወል ፡	አልሁ ፡	አልን ፡	አላልሁም ፡	አላልንም ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	አልህ ፡	አልአችሁ (አላችሁ)	አላልህም ፡	አላላችሁም ፡
	አን.	አልሽ ፡	» »	አላልሽም ፡	»
፫ኛ ፡	ተባ.	አለ ፡	አሉ ፡	አላለም ፡	አላሉም ፡
	አን.	አለች ፡	»	አላለችም ፡	»

(ለ) በጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ እንደሚከተለው ፡ በአምንታና ፡ በአሉታ ፡ ይረባል ።

መደብ ፡ ጾታ ፡	አምንታ ፡		አሉታ ፡	
	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ያ/ኖ ፡ የወል ፡	ብዬ፡አለሁ፡(ብያለሁ)	ብለን ፡ አል ፡ (ብለናል)	አላልሁም ፡	አላልንም ፡
ዪኖ ፡ ተባ.	ብለህ፡አል ፡ (ብለሃል)	ብላችሁአል(ብላችኋል)	አላልህም ፡	አላላችሁም
እን.	ብለሽ፡አል፡(ብለሻል)	» »	አላልሽም ፡	»
ቦኖ ፡ ተባ.	ብሎ ፡ አል ፡ (ብሏል)	ብለው፡ አል ፡(ብለዋል)	አላለም ፡	አላሉም ፡
እን.	ብላአለች ፡ (ብላለች)	» »	አላለችም ፡	»

በጎጇሞች ፡ አማርኛ ፡ በአሉታው ፡ ጊዜ ፡ አልብሉም ፡ አልብዬም ፡ አልብለውም ፡ አልብለሀም ፡ . . . ተብሎ ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ ሥረ ፡ ነገሩን ፡ የተከተለና ፡ የተስማማ ፡ ስለሆነ ፡ ጸያፍ ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

— 168 —

አለ ፡ የመሆንን ፡ ምግበር ፡ የሚገልጽ ፡ ሲሆን ፡ ረዳት ፡ ግሥ ፡ ይበላል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከግብር ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ለዚሁ ፡ የተመደቡትን ፡ ቃላት ፡ ይዘ ፡ ይገባል ። ለም ሳሌ ፡ « ዝም ፡ « ቁጭ ፡ ዳብ ፡ ዝቅ ፡ » እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ብዙ ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ አሉ ፤ እነሱም ፡ ብቻቸውን ፡ ሲነገሩ ፡ ምንም ፡ ስሚት ፡ የላቸውም ። ከሌሎችም ፡ ግሦች ፡ ጋር ፡ ዝምድና ፡ የላቸውም ። ግሥ ፡ አለ ፡ በተዉሔመረበቸው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ስሚታቸውን ፡ አያ ጉሉ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ይሆናሉ ።

አስረጅ ፡ « ዝም ፡ አለ ፡ ዝም ፡ ብሏል ፤ ዝም ፡ ብሎ ፡ ነበር ፤ ዝም ፡ ይላል ፡ ዝም ፡ ማለት ፤ ዝም ፡ ብሎ ፡ ፡ » እንደማለት ፡ ነው ። እንደ ፡ ግሥ ፡ ደንብ ፡ በሙሉ ፡ ሊረቡ ፡ ይች ላሉ ።

— 169 —

ጀመረ ።

ጀመረ ፡ በግሥነቱ ፡ ሲነገር ፡ አድራጊ ፡ ዐምድ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ «ጀመርሁ ፡ ጀመርህ ፡ ጀመርሽ ፡ ጀመረ ። » እያለ ፡ እንደሌላው ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ በየዋህም ፡ በዝርዝርም ፡ እርባታ ፡ ይረባል ።

በረዳትነት ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡ መድረሻውን ፡ ሳድስ ፡ አድርጎ ፡ « ጀመር ። » ተብሎ ፡ ይነገራል ። በትንቢት ፡ በገ ፡ ላይ ፡ እየተጫነ ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ « አመጣ ፡ ጀመር ፡ ትመጣ ፡ ጀመር ፤ ትመጪ ፡ ጀመር ፤ ይመጣ ፡ ጀመር ፤ » እንደማለት ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክፍሉ ፡ ከመሆን ፡ ግሥ ፡ ነው ። ይመጣ ፡ ጀመር ፤ ወይም ፡ ይመጣል ፡ ሆነ ፡ ቢል ፡ ምሥጢሩ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ነው ።

አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ የግሥ ፡ ደንቡን ፡ ሳይለቅ ፡ ረዳት ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ይመስናሉ ። ይኸውም ፡ አመጣ ፡ ጀመርሁ ፡ ትመጣ ፡ ጀመርህ ፡ ትመጪ ፡ ጀመርሽ ፡ ይመጡ ፡ ጀመሩ ፡ . . . » ይላል ፡ እንደማለት ፡ ነው ።

— 170 —

ቂየ ።

ቂየ ፡ በግሥነቱ ፡ ሲነገር ፡ ተደራጊ ፡ ዐምድ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ «ቂየሁ ፡ ቂየህ ፡ ቂየሽ ፡ ቂየ ፡ . . . » እያለ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ በየዋህም ፡ በዝርዝር ርም ፡ እርባታ ፡ ይረባል ።

በረዳትነት ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡ በጎላፊው ፡ ቦዝ ፡ ሳይ ፡ እየተጫነ ፡ ይገበና ፡ እንደ ፡ ግሥነቱ ፡ ደንብ ፡ ይረባል ። ይኸውም ፡ «መጥቶ ፡ ቂየ ፡ ሄዳ ፡ ቂየች ፡ » እንደማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምሥጢሩ ፡ ከመሆን ፡ ግሥ ፡ ይዘመዳል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ቋንቋ ፡ የሚነገረው ፡ በጥቂቶች ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

— 171 —

አገኘ ።

አገኘ ፡ በግሥነቱ ፡ ሲነገር ፡ አድራጊ ፡ ዐምድ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አገኘሁ ፡ አገኘህ ፤ አገኘሽ ፡ አገኘ ፤ «አያለ ፡ እንደሌላው ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ በየዋህም ፡ በዝርዝርም ፡ እርባታ ፡ ይረባል ። በረዳትነት ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡ በጎላፊ ፡ ቦዝ ፡ ላይ ፡ እየተጫነ ፡ አንደ ፡ ግሥነቱ ፡ ደንብ ፡ ይረባል ። በምሥጢር ፡ የመሆንን ፡ ምግበር ፡ ያመለክታል ።

አስረጅ ፡ ብርሃኑ ፡ መጽሐፉን ፡ ለማምጣት ፡ ቢሄድ ፡ ጠፍቶ ፡ አገኘው ፡ (=አጣው ።)

ፈለቀ ፡ ወንድሙን ፡ ለማየት ፡ ቢመጣ ፡ ሄዶ ፡ አገኘው ፡ (=አጣው ፡ ወይም ፡ ሳያገኘው ፡ ቀረ ።)

ፈለቀ ፡ ወንድሙን ፡ ለማየት ፡ ቢመጣ ፡ ሄዶ ፡ ቂየው ፡

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተሰጡት ፡ ማስረጃዎች ፡ የማግኘትንና ፡ የመቂየትን ፡ ምግበር ፡ የሚገልጹ ፡ አይደሉም ። ብርሃኑ ፡ መጽሐፉን ፡ ለማምጣት ፡ ቢሄድ ፡ ጠፍቶ ፡ አገኘው ፡ » ባለ ፡ ጊዜ ፡ ማጣቱን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከጠፋበት ፡ በኋላ ፡ ማግኘቱን ፡ አያስ ረዳም ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ « ፈለቀ ፡ ወንድሙን ፡ ለማየት ፡ ቢመጣ ፡ ሄዶ ፡ አገኘው ፡ ወይም ፡ ሄዶ ፡ ቂየው ፡ በለ ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኘው ፡ መቅረቱን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ማግኘቱን ፡ ወይም ፡ መቂየቱን ፡ አያመለክትምና ፡ «አገኘ ፡ ቂየ ፡ » የግሥ ፡ ረዳት ፡ መበላ ቸው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

፲፫ ፣ መልመጃ ።

ሀ—የግሥ ፣ ረዳት ፣ የሚባሉት ፣ እነማን ፣ ናቸው ?

የመኖር ፣ ግሥ ፣ እንዴት ፣ እንደሆነ ፣ አስረዳኝ ።
የመሆን ፣ ግሥ ፣ ምን ፣ ዓይነት ፣ እንደሆነ ፣ ንገረኝ ።
የግሥ ፣ ረዳቶች ፣ እንዴት ፣ እንደሚረቡ ፣ ምሳሌን ፣ ስጠኝ ።
«አለ ፣» የሚለው ፣ ቃል ፣ በመጥበቅና ፣ በመላላት ፣ ድምፅ ፣ ሲነገር ፣ ልዩነቱን፣ በምሳሌ ፣ እያደረግህ ፣ ንገረኝ ።
ለምሳሌ ፣ ያቀረብሃቸውን ፣ የግሥ ፣ ረዳቶች ፣ ሁሉ ፣ ወደ ፣ አሉታ ፣ አዙራቸው። አምንታና ፣ አሉታ ፣ እንዴት ፣ እንደሆነ ፣ በምሳሌ ፣ ተናገር ።

ለ—ከዚህ ፣ በታች ፣ ከተጻፈው ፣ ምንባብ ፣ የግሥ ፣ ረዳቶችን ፣ እየለየህ ፣ አመል ክት ። በአምንታ ፣ የተጻፈውን ፣ ወደ ፣ አሉታ ፣ ለውጠው ። በአሉታ ፣ የተጻፈውንም ፣ ወደ ፣ አምንታ ፣ እየለወጥህ ፣ አሳይ ።

ምንባብ ።

ግሀስ ፣ ሥላሴ ፣ ከሞቱ ፣ በኋላ ፣ ልጃቸው ፣ ኃይለ ፣ መለኮት ፣ ወዲያው ፣ አልጋ ውን ፣ ወርሰው ፣ በሰላም ፣ ይገዙ ፣ ጀመር ። ወዲያውም ፣ በሕዝብ ፣ አፍ ፣ አጨ ፣ ኃይሉ ፣ መባል ፣ ተለመደ ። ኃይለ ፣ መለኮት ፣ ለኦሪሳ ፣ ነበርስቶስ ፣ ጅኖ ፣ ትውልድ ፣ ይሆናሉ ።

በነገሡ ፣ በፀኖው ፣ ዘመን ፣ ወደ ፣ አሩሲ ፣ ዘምተው ፣ ኖሮ ፣ ብርቱ ፣ ጦርነት ፣ አግ ኝተዋው ፣ ነበር ፣ ይባላል ። ወዲያውም ፣ በዚያው ፣ ዘመን ፣ ቋረኛው ፣ ደጃች ፣ ከሣ ፣ አባ ፣ ታጠቅ ፣ ጎሻም ፣ ላይ ፣ ትንሽ ፣ ራስ ፣ ዓሊን ፣ ድል ፣ አድርገዋቸው ፣ ነበርና ፣ ሸሽተው ፣ ወደ ፣ ሽዋ ፣ ሲመጡ ፣ ደራ ፣ ላይ ፣ ቀቂዲበ ፣ የተባለ ፣ ባላባት ፣ እግኝቶ ፣ አሰራቸው ።

ኃይለ ፣ መለኮትም ፣ ይህን ፣ ሰሙና ፣ ገሥግሠው ፣ ሄደው ፣ ቀቂዲበን ፣ አሥ ረው ፣ ራስ ፣ ዓሊን ፣ ይዘው ፣ ተመልሰዋል ።

ኃይለ ፣ መለኮት ፣ ልበ ፣ ሰፊ ፣ ጀግና ፣ ባለአእምሮ ፣ ነበሩ ፣ ይባላል ። ስለዚህም፣ አባታቸው ፣ ግሀለ ፣ ሥላሴ ፣ ታላቁ ፣ ልጅ ፣ አቶ ፣ ሰይፉ ፣ እያሉ ፣ አልጋውን ፣ ለኃይለ፣ መለኮት ፣ ሰጥተው ፣ ሞቱ ።

እንደዚህ ፣ አድርገው ፣ ለአገራቸው ፣ እየተከላከሉ ፣ ሲኖሩ ፣ በነገሡ ፣ በ፲፫ኛው፣ ዓመት ፣ አጼ ፣ ቴዎድሮስ ፣ ሽዋን ፣ ሊወጉ ፣ መጡ ። ኃይለ ፣ መለኮትም ፣ ደብረ ፣ በግዕ ፣ በሚ ባል ፣ ስፍራ ፣ ላይ ፣ በድንገት ፣ ታመው ፣ ጎጃር ፣ ኗ ፣ ቀን ፣ ፲፰፻፺፫ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ሞቱ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ የሸዋ ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ የኃይለ ፣ መለኮትን ፣ ልጅ ፣ ምኒልክን ፣ ይዘ ፣ ሸሸ ። አጼ ፣ ቴዎድ ሮስ ፣ ግን ፣ የኃይለ ፣ መለኮትን ፣ መቃብር ፣ ደብረ ፣ በግዕን ፣ አይተው ፣ ወደ ፣ አንኮበር ፣ ተመ ለሱ ። ጎላም ፣ የሸዋ ፣ ሕዝብ ፣ መከረና ፣ የባላባቱን ፣ ልጅ ፣ አጼ ፣ ምኒልክን ፣ ይዘ ፣ ለአጼ ፣ ቴዎ ድሮስ ፣ ገበሳቸው ። አጼ ፣ ቴዎድሮስም ፣ ምኒልክን ፣ ይዘው ፣ ወደ ፣ ቤገምድር ፣ ተመለሱ ።

ክፍል ፣ ፪ ፣ የእርባታ ፣ መሪዎች ።

— 172 —

የእርባታ ፣ መሪዎች ፣ የሚባሉት ፣ በየዋህ ፣ እርባታና ፣ በዝርዝር ፣ እርባታ ፣ ጊዜ ፣ በመድረሻ ፣ ወይም ፣ በመነሻ ፣ ላይ ፣ እየተጨመሩ ፣ ግሥ ፣ የሚረባቸው ፣ ቃላት ፣ ናቸው ።

የእርባታ ፣ መሪዎች ፣ በየዋህ ፣ እርባታ ፣ ጊዜ ፣ (ሀ) ፬መድረሻ ፣ ላይ ፣ የሚገቡት ፣ « ው ፣ ህ ፣ ሽ ፣ ግዕዝ ፣ ወይም ፣ ራብዕ ፣ ፊደል ፣ ት ፣ ን ፣ አችሁ ፣ አኖው ፣ » ናቸው ። (ለ) በመነሻ ፣ ላይ ፣ የሚገቡት ፣ «እ ፣ ት ፣ የ ፣ እን ፣ » ናቸው ። የላይኞቹ ፣ በኅላፊ ፣ አንቀጽ ፣ ይገባሉ ። የታችኞቹ ፣ በትንቢት ፣ አንቀጽ ፣ ላይ ፣ ይገባሉ ።

„ሀ„ የተባለው ፣ የእርባታ ፣ መረ ፣ በዝርዝር ፣ እርባታ ፣ ጊዜ ፣ ወደግዕዝነት ፣ ሲለ ወጥ ፣ ሽ ፣ ይሆናል ። ይሽውም ፣ ፊለግህ ፣ ብሎ ፣ ፊለግሽኝ ፣ ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ። ህ ፣ የግ ዕዝነት ፣ ድምፁ ፣ ስለጠፋ ፣ ሽ ፣ የሚል ፣ ፊደል ፣ በቅርቡ ፣ ዘመን ፣ ተፈጥሮለታል ። አንዳ ንድ ፣ ጊዜም ፣ ዐረቢውን ፣ ጐን ፣ ይወርሳል ። ይሽውም ፣ ፈለግኋችሁ ፣ ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ።

— 173 —

የየዋህ ፣ እርባታ ፣ መሪዎች ።

የየዋህ ፣ እርባታ ፣ መሪዎች ፣ ባለቤትን ፣ ስለሚያመለክቱ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ የባ ለቤት ፣ ዝርዝር ፣ ይሰላሉ ፣ (ቁ. 68 ፣ እይ ።) በመሆን ፣ ግሥ ፣ ላይ ፣ ሲሆን ፣ መሪዎቹ ፣ ዋቄት ፣ ይለወጣሉ ። ይሽውም ፣ «ኝ ፣ ህ ፣ ሽ ፣ ው ፣ ት ፣ ን ፣ አችሁ ፣ አኖው ፣ » ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ። (ቁ. 157 ፣ እይ ።)

የዋህ ፣ ማለት ፣ ቀላል ፣ ወይም ፣ ገር ፣ ማለት ፣ ነው ። በዚህ ፣ መደብ ፣ የሚነገረው ፣ እርባታ ፣ ቀላል ፣ ስለሆነ ፣ የዋህ ፣ ተብሎአል ። የዋህ ፣ እርባታ ፣ በ፷፱ ፣ ተውላጣት ፣ ስም ፣ መደብ ፣ ይገባል ። እርሱም ፣ ለዝርዝር ፣ እርባታ ፣ መሠረት ፣ ይሆናል ። (ቁ. 177—እይ ።)

—174 —

የየዋህ ፣ እርባታ ፣ መሪዎች ፣ በመድረሻ ፣ ላይ ፣ እየተጨመሩ ፣ ሲገቡ ፣ አረባባቸው ፣ እንደሚከተለው ፣ ነው ። ይሽንኑም ፣ «መፈለግ ፣» በሚለው ፣ ግሥ ፣ እያረቡን ፣ በአምንታም ፣ በአሉታም ፣ እናሳያለን ።

መደብ ፣ ጾታ ፣	ምንታ ፣		አሉታ ፣	
	ኅላፊ ፣	ተከታይ ፣	ነበሰላ ፣	ተከታይ ፣
፩ኛ ፣ ነጠላ ፣	ፈለግ—ሁ ፣	ፈለግ—ኝ ፣	አል—ፈለግ—ሁም ፣	አል—ፈለግ—ንም ፣
፪ኛ ፣ ተባ.	ፈለግ—ህ	ፈለግ—አችሁ	አል—ፈለግ—ህም ፣	አል-ፈለግ-አችሁም
እን.	ፈለግ—ሽ	» »	አል ፈለግ—ሽም ፣	»
፫ኛ ፣ ተባ.	ፈለገ ፣	ፈለጉ ፣	አል—ፈለገ—ም ፣	አል—ፈለጉ—ም ፣
እን.	ፈለገ—ች	»	አል—ፈለገ—ችም ፣	»

በዚህ ፡ መንጠረጊያ ፡ ውስጥ ፡ « ፈለግ-አችሁ ፡ አልፈለግ-አችሁም ፡ » የተባለው ፡ ቃል ፡ የአ ፡ ፊደል ፡ ተውጦ ፡ « ፈለጋችሁ ፡ አልፈለጋችሁም ፡ ተብሎ ፡ ይጻፋል ።

— 175 —

የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ በመነሻ ፡ ላይ ፡ እየተጨመሩ ፡ ሲገቡ ፡ አረባባቸው ፡ እንደ ሚከተለው ፡ ነው ። ይኸንኑም ፡ « መፈለግ ፡ በሚለው ፡ ግሥ ፡ በአምንታም ፡ በአሉታም ፡ እያረባን ፡ እናሳያለን ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		አምንታ ፡		አሉታ ፡	
		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ	ብዙ ፡
፩ኛ ፡ የወል ፡		እ-ፈልጋለሁ ፡	እ-ንፈልጋለን	አል-ፈልግም ፡	አን-ፈልግም ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	ት-ፈልጋለህ ፡	ት-ፈልጋላችሁ ፡	አት-ፈልግም ፡	አት-ፈልግም ፡
	እን.	ት-ፈልጊአለሽ ፡	»	አት-ፈልጊም ፡	»
፫ኛ ፡	ተባ.	ይ-ፈልጋል ፡	ይ-ፈልጋሉ ፡	አይ-ፈልግም ፡	አይ-ፈልጉም ፡
	እን.	ት-ፈልጋለች ፡	»	አት-ፈልግም ፡	»

እነሆ ፡ በሥረ ፡ ነጥሩ ፡ እፈልግለሁ ፡ ያሰኝ ፡ የነበረው ፡ « አ » ተውጦ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ተብሏል ። የቀረውንም ፡ በዚሁ ፡ አካሄድ ፡ ተመልከት ።

— 176 —

የዝርዝር ፡ እርባታ ፡ መሪዎች ፡

የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ በዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ጊዜ ፡ በመድረሻ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይገኛሉ ። እነርሱም ፡ « ኝ ፡ ህ ፡ ሽ ፡ ው ፡ ት ፡ አት ፡ አችሁ ፡ አሞ ፡ ። » ናቸው ። ዝርዝር ፡ እርባታ ፡ በየዋህ ፡ እርባታ ፡ ላይ ፡ ተመድቦ ፡ እየተዘረዘረ ፡ ይረባል ።

የዝርዝር ፡ እርባታ ፡ መሪዎች ፡ (ሀ) የተሰቢነትን ፡ ምግባር ፡ በሚያመለክቱበት ፡ ጊዜ ፡ የተጠቃሽ ፡ ተሰቢ ፡ አጸፋ ፡ ይባላሉ ። ትርጓሜው ፡ « እኔን ፡ አንተን ፡ አርሱን ፡ . . . » ማለት ፡ ነው ። ቁ. 70 አይ ።)

(ለ) የተቀባይነትን ፡ ምግባር ፡ በሚያመለክቱበት ፡ ጊዜ ፡ የተቀባይ ፡ አጸፋ ፡ ይባላሉ ። ትርጓሜአቸው ፡ ለእኔ ፡ ለአንተ ፡ ማለት ፡ ነው ። . . .(ቁ. 70 አይ)

— 177 —

የተሰቢነትን ፡ ምግባር ፡ የሚያመለክተውን ፡ ዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ « መፈለግ » በሚለው ፡ ግሥ ፡ እናሳያለን ። በየዋህ ፡ እርባታ ፡ ላይ ፡ እንዲት ፡ እንደሚመ ረትም ፡ እናመለክታለን ። ዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ቁጥሩ ፡ እስከ ፡ ሃያ ፡ ይደርሳል ።

— 178 —

የዋህ ፡ እርባታ ፡	ዝርዝር ፡ እርባታ ።								
	ነጠላ ፡ ቁጥር ፡						የብዙ ፡ ቁጥር ፡		
	፩ኛ ፡ መደብ ፡	፪ኛ ፡ መደብ ፡		፫ኛ ፡ መደብ ፡			፩ኛ ፡ መደብ ፡	፪ኛ ፡ መደብ ፡	፫ኛ ፡ መደብ ፡
	የወል ፡ ኝ ፡	ተባ. ህ.	እን. ሽ.	ተባ. ው ት	እን. አት		የወል ፡ ን	የወል ፡ አችሁ	የወል ፡ አቸው ፡
ፈለግሁ ፡	—	ፈለግሁህ ፡	ፈለግሁሽ ፡	ፈለጉኝ ፡	ፈለጊት ፡		—	ፈለግኋችሁ	ፈለግኋቸው ፡
ፈለግህ ፡	ፈለግከኝ ፡	—	—	ፈለገኝ ው ፡	ፈለገች ት ፡		ፈለገን ፡	—	ፈለገችው ፡
ፈለግሽ ፡	ፈለገችኝ ፡	—	—	ፈለገው ፡	ፈለገች ት ፡		ፈለገች ኙ ፡	—	ፈለገቻቸው ፡
ፈለገ ፡	ፈለገኝ ፡	ፈለገ ህ ፡	ፈለገ ሽ ፡	ፈለገ ው ፡	ፈለጋ ት ፡		ፈለገ ኙ ፡	ፈለጋችሁ	ፈለጋቸው ፡
ፈለገች ፡	ፈለገችኝ ፡	ፈለገችህ ፡	ፈለገች ሽ ፡	ፈለገች ው ፡	ፈለገች ት ፡		ፈለገችን ፡	ፈለገችሁ ፡	ፈለገቻቸው ፡
ፈለግን ፡	—	ፈለገንህ ፡	ፈለግን ሽ ፡	ፈለገን ው ፡	ፈለገች ት ፡		—	ፈለገናችሁ ፡	ፈለገናቸው ፡
ፈለጋችሁ ፡	ፈለጋችሁኝ ፡	—	—	ፈለጋችሁት ፡	ፈለጋችኋት ፡		ፈለጋችሁን ፡	—	ፈለጋችኋቸው ፡
ፈለጉ ፡	ፈለጉኝ ፡	ፈለጉህ ፡	ፈለጉሽ ፡	ፈለጉት ፡	ፈለጓት ፡		ፈለጉን ፡	ፈለገችሁ ፡	ፈለጓቸው ፡

የዋህ ፡ እርባታ ፡	ዝርዝር ፡ እርባታ ።								
	ነጠላ ፡ ቁጥር ፡						የብዙ ፡ ቁጥር ፡		
	፩ኛ መደብ ፡	፪ኛ ፡ መደብ ፡		፫ኛ ፡ መደብ ፡			፩ኛ ፡ መደብ ፡	፪ኛ መደብ ፡	፫ኛ ፡ መደብ ፡
	የወል ፡ ኝ ፡	ተባ. ህ.	እን. ሽ	ተባ. ት ው	እን. አት		የወል ፡ ን	የወል አችሁ	የወል ፡ አቸው ፡
አደልሁ ፡	—	አደልሁህ ፡	አደልሁሽ ፡	አደልውት ፡	አደልኋት ፡		—	አደልኋችሁ	አደልኋቸው ፡
አደልህ ፡	አደልከኝ ፡	—	—	አደልኸው ፡	አደለሃት ፡		አደልን ፡	—	አደልሃቸው ፡
አደልሽ ፡	አደልሽኝ ፡	—	—	አደልሽው ፡	አደልሻት ፡		አደልችሁ ፡	—	አደልሻቸው ፡
አደለ ፡	አደለኝ ፡	አደለህ ፡	አደለ ሽ ፡	አደለው ፡	አደላት ፡		አደለን ፡	አደላችሁ ፡	አደላ ቸው ፡
አደለች ፡	አደለችኝ ፡	አደለች ህ ፡	አደለችሽ ፡	አደለችው ፡	አደለቻት ፡		አደለችን ፡	አደለቻችሁ ፡	አደለቻቸው ፡
አደልን ፡	—	አደልንህ ፡	አደልንሽ ፡	አደልነው ፡	አደልናት ፡		—	አደልናችሁ ፡	አደልናቸው ፡
አደላችሁ ፡	አደላችሁኝ ፡	—	—	አደላችሁት ፡	አደላችኋት ፡		አደላችሁን ፡	—	አደላችኋቸው ፡
አደሉ ፡	አደሉኝ ፡	አደሉህ ፡	አደሉሽ ፡	አደሉት ፡	አደሏት ፡		አደሉን ፡	አደሏችሁ	አደሏቸው ፡

— 179 —

በንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ክፍል ፡ የእርባታ ፡ መሪዎች ።

የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ በንኡስ ፡ አንቀጽም ፡ ክፍል ፡ ገብተው ፡ ይገኛሉ ። መድረሻው ፡ ግዕዝ ፡ የሆነ ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ ዓይነቱ ፡ አንድ ፡ ነው ። እርሱንም ፡ «ፈለገ» ፡ በሚለው ፡ አድራጊ ፡ ዐምድ ፡ እናሳያለን ። መድረሻው ፡ ራብዕ ፡ የሆነ ፡ ግሥ ፡ ግን ፡ በመድረሻው ፡ ላይ ፡ ተ ፡ የሚል ፡ ባዕድ ፡ ፊደል ፡ ይጨመርበታል ። ይህንንም ፡ «ገበ» ፡ በሚል ፡ ተደራጊ ፡ ዐምድ ፡ እየአረበን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እናሳያለን ። (ቁ. 180 እይ ።)

— 180 —

ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ክፍሉ ፡ ከግብር ፡ ስም ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተጻፈው በስም ፡ ደንብ ፡ ይዘረዘራል ። መዘርዘሪያውም ፡ የዋሀ ፡ እርባታ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡ የወል ፡		መፈለጌ ፡	መፈለጋችን ፡	መግባቴ ፡	መግባታችን ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	መፈለግህ ፡	መፈለጋችሁ ፡	መግባትህ ፡	መግባታችሁ ፡
	እን.	መፈለግሽ ፡	»	መግባትሽ ፡	»
፫ኛ ፡	ተባ.	መፈለጉ ፡	መፈለጋቸው ፡	መግባቱ ፡	መግባታቸው ፡
	እን.	መፈለግዋ ፡ (ታ)	»	መግባትዋ (ታ)	»

— 181 —

ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ በጎላፊውም ፡ በትንቢቱም ፡ እንደ ፡ ግሥ ፡ ደንብ ፡ በየዋሀም ፡ በዝርዝርም ፡ እርባታ ፡ ይነገራል ። በየዋሀ ፡ እርባታ ፡ ሲረባ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተጻፈው ፡ ነው ። (ቁ. 182 እይ ፩)

— 182 —

ጎላፊ ፡ ቦዝ ፡ በየዋሀ ፡ እርባታ ፡ ሲረባ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡ የወል ፡		ፈልጌ ፡	ፈልገን ፡	ገብቼ ፡	ገብተን ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	ፈልገህ ፡	ፈልጋችሁ ፡	ገብተህ ፡	ገብታችሁ ፡
	እን.	ፈልገሽ ፡	»	ገብተሽ ፡	»
፫ኛ ፡	ተባ.	ፈልጎ ፡	ፈልገው ፡	ገብቶ ፡	ገብተው ፡
	እን.	ፈልጋ ።	»	ገብታ ፡	»

— 183 —

ጎላፊ ፡ ቦዝ ፡ በዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ሲረባ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ይህንንም ፡ መፈለግ ፡ በሚለው ፡ ግሥ ፡ እናሳያለን ።

የዋሀ ፡ እርባታ ፡	ዝርዝር ፡ እርባታ ።							
	ነጠላ ፡ ቁጥር ።						የብዙ ፡ ቁጥር ፡		
	፩ኛ ፡ መ ፡ የወል ፡ ኝ	፪ኛ ፡ መደብ ፡ ተባ. ህ	እን. ሽ	፫ኛ ፡ መደብ ፡ ተባ. ው ት	እን. አት	፩ኛ ፡ መ ፡ የወል ፡ ን	፪ኛ ፡ መ ፡ የወል ፡ አችሁ ፡	፫ኛ ፡ መደብ ፡ የወል ፡ አቸው ፡
ፈልጌ ፡	—	ፈልጌህ ፡	ፈልጊ ፡	ፈልጌው ፡	ፈልጊአት ፡	—	ፈልጊአችሁ	ፈልጊአቸው ፡
ፈልገህ ፡	ፈልገኸኝ ፡	—	—	ፈልገኸው ፡	ፈልገሃት ፡	ፈልገናን ፡	—	ፈልገሃቸው ፡
ፈልገሽ ፡	ፈልገሽኝ ፡	—	—	ፈልገሽው ፡	ፈልገሸት ፡	ፈልገሽን ፡	—	ፈልገሻቸው ፡
ፈልጎ ፡	ፈልጎኝ ፡	ፈልጎህ ፡	ፈልጎሽ ፡	ፈልጎው ፡	ፈልጎት ፡	ፈልጎን ፡	ፈልጎችሁ ፡	ፈልጎአቸው ፡
ፈልጋ ፡	ፈልጋኝ ፡	ፈልጋህ ፡	ፈልጋሽ ፡	ፈልጋው ፡	ፈልጋት ፡	ፈልጋን ፡	ፈልጋችሁ ፡	ፈልጋቸው ፡
ፈልገን ፡	—	ፈልገንህ ፡	ፈልገንሽ ፡	ፈልገነው ፡	ፈልገናት ፡	—	ፈልገናችሁ	ፈልገዋቸው ፡
ፈልጋችሁ ፡	ፈልጋችሁኝ ፡	—	—	ፈልጋችሁት	ፈልጋችኋት	ፈልጋችሁን ፡	—	ፈልጋችኋቸው ፡
ፈልገው ፡	ፈልገውኝ ፡	ፈልገውህ ፡	ፈልገውሽ ፡	ፈልገው ፡	ፈልገዋት ፡	ፈልገውን ፡	ፈልገዋችሁ	ፈልገዋቸው ፡

የጎላፊ ፡ ቦዝ ፡ ዝርዝር ፡ እርባታ ፡ በወቢይ ፡ አንቀጽነት ፡ ገብቶ ፡ ማሰሪያ ፡ ሲሆን ፡ ፈልጌህ ፡ አለሁ ፡ ፈልጌህ ፡ ነበር ፡ ፈልጌህ ፡ ይሆናል ፡ እያለ ፡ ረዳትን ፡ እየያዘ ፡ ይነገራል ።

—184—

ትንቢት ፡ ቦዝ ፡ በየዋሀ ፡ እርባታ ፡ ሲረባ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

መደብ ፡ ጾታ ፡		ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ኛ ፡ የወል		እፈልግ ፡	እንፈልግ ፡	እገባ ፡	እንገባ ፡
፪ኛ ፡	ተባ.	ትፈልግ ፡	ትፈልጉ ፡	ትገባ ፡	ትገቡ ፡
	እን.	ትፈልጊ ፡	»	ትገቢ ፡	»
፫ኛ ፡	ተባ.	ይፈልግ ፡	ይፈልጉ ፡	ይገባ ፡	ይገቡ ፡
	እን.	ትፈልግ ፡	»	ትገባ ፡	»

የትንቢት ፡ ቦዝ ፡ የዋሀ ፡ እርባታ ፡ በወቢይ ፡ አንቀጽነት ፡ ገብቶ ፡ ማሰሪያ ፡ ሲሆን ፡ እፈልግ ፡ ነበር ፡ እፈልጋለሁ ፡ እፈልግ ፡ ይሆናል ፡ እያለ ፡ ረዳትን ፡ እየጨመረ ፡ ይነገራል ።

—185—

ትንቢት ፡ ቦዝ ፡ በዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ሲረባ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ይህን ኑም ፡ መፈለግ ፡ በሚለው ፡ ግሥ ፡ ዘርዝረን ፡ እናሳያለን ።

የዋህ ፡ እርባታ፡	ዝርዝር ፡ እርባታ ፡							
	ነጠላ ፡ ቁጥር ፡					የብዙ ፡ ቁጥር ።		
	፩ኛ፡ መ የወል ኝ	፪ኛ፡ መደብ ፡ ተባ. ህ. እን. ሽ		፫ኛ፡ መደብ ፡ ተፃ. ው. ት. እን. አት		፩ኛ፡ መ የወል ን	፪ኛ መደብ የወል አችው	፫ኛ መደብ የወል፡አቸው
እፈልግ፡	—	እፈልግህ፡	እፈልግሽ፡	እፈልገው፡	እፈልጋት፡	—	እፈልጋችሁ፡	እፈልጋቸው፡
ትፈልግ፡	ትፈልጎኝ፡	—	—	ትፈልገው፡	ትፈልጋት፡	ትፈልጉን፡	—	ትፈልጋቸው፡
ትፈልጊ፡	ትፈልጊኝ፡	—	—	ትፈልጊው፡	ትፈልጊአት፡	ትፈልጊን፡	—	ትፈልጊአቸው
ይፈልግ፡	ይፈልገኝ፡	ይፈልግህ፡	ይፈልግሽ፡	ይፈልገው፡	ይፈልጋት፡	ይፈልጉን፡	ይፈልጋችሁ፡	ይፈልጋቸው፡
ትፈልግ፡	ትፈልገኝ፡	ትፈልግህ፡	ትፈልጊሽ፡	ትፈልገው፡	ትፈልጋት፡	ትፈልጉን፡	ትፈልጋችሁ፡	ትፈልጋቸው፡
እንፈልግ፡	—	እንፈልግህ፡	እንፈልግሽ፡	እንፈልገው፡	እንፈልጋት፡	—	እንፈልጋችሁ	እንፈልጋቸው
ትፈልጉ፡	ትፈልጉኝ፡	—	—	ትፈልጉት፡	ትፈልጓት፡	ትፈልጉን፡	—	ትፈልጓቸው፡
ይፈልጉ፡	ይፈልጉኝ፡	ይፈልጉህ፡	ይፈልጉሽ፡	ይፈልጉት፡	ይፈልጓት፡	ይፈልጉን፡	ይፈልጓችሁ፡	ይፈልጓቸው፡

የትንቢት ፡ በዝ ፡ እርባታ ፡ በዐቢይ ፡ አንቀጽነት ፡ ገብቶ ፡ ማሰሪያ ፡ ሲሆን ፡ እፈልግ ፡ ነበር ፤ እፈልግህ ፡ አለው ፡ እፈልግህ ፡ ይሆናል ፡ . . . እያለ ፡ ረዳትን ፡ እየያዘ ፡ ይነገራል ። በአዋዋይ ፡ አንቀጽም ፡ ሲገባ ፡ እፈልግህ ፡ ዘንድ ፡ እንድፈልግህ ፡ ልፈልግህ ፡ . . . . እያለ ፡ ይዘረዘራል ።

— 186 —

ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ በየዋህ ፡ እርባታ ፡ ጊዜ ፡ መነሻውን ፡ በ፮ኛ ፡ መደብ ፡ « ል ፡ እን ፡ » በሮ ፡ መደብ ፡ « ይ ፡ ት » ፡ እያደረገ ፡ ያለ ፡ በዕድ ፡ መድረሻ ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ «ልፈልግ ፡ እንፈልግ ፤ ይፈልግ ፡ ይፈልጉ ፡ ትፈልግ ፡ » እንደማለት ፡ ነው ። በ፪ኛ ፡ መደብ ፡ መነሻ ፡ ወይም ፡ መድረሻ ፡ ሳይኖረው ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ «ፈልግ ፤ ፈልጊ ፡ ፈልጉ ፡ » እንደማለት ፡ ነው ።

ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ይረባል ። የእርባታ ፡ መሪዎቹም ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ የተናገርናቸው ፡ « ኝ ፤ ህ ፤ ሽ ፤ ው ፡ ት ፡ አት ፡ ን ፤ አችሁ ፤ አቸው ፡ » ናቸው ። (ቁ. 176 እይ ።) አዘራዘሩም ፡ ልፈልግህ ፡ ልፈልግሽ ፡ . . . . . እያለ ፡ ስለሆነ ፡ አከሄዱ ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ እንደተነገረው ፡ አኳኋን ፡ ነው ። (ቁ. 183 እይ) ።

— 187 —

መስተዋድዳውያን ፡ የእርባታ ፡ መሪዎች ።

ከመስተዋድድ ፡ ክፍል ፡ የሆኑት ፡ « ለ ፡ በ ፡ » በዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ደንብ ፡ እየገቡ ፡ ሲረቡ ፡ ለ ፡ የበላ ፡ በ ፡ የክፉ ፡ መፍቻ ፡ ይሆናሉ ። ከሁን ፡ በፊት ፡ በየስፍራው ፡ በጻፍናቸው ፡ ዝርዝር ፡ እርባታዎች ፡ በሁሉም ፡ ሊገቡ ፡ ይችላሉ ። (ቁ. 177—186 እይ ።)

ለ ፡ ዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ሆኖ ፡ ሲገባ ፡ ታሉ ፡ «ልኝ ፡ ልህ ፤ ልሽ ፤ ለት ፡ ላት ፤ ልን ፤ ላችሁ ፤ ላቸው» ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፡ ፈለግሁልህ ፡ ፈለግህልኝ ፡ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

በ ፡ ዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ሆኖ ፡ ሲገባ ፡ ታሉ ፡ «ብኝ ፤ ብህ ፤ ብሽ ፤ በት ፤ ባት ፤ ብን ፤ ባችሁ ፡ ባቸው » ይሆናል ፡ ይኸውም ፡ ፈለግሁብህ ፡ ፈለግህብኝ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፩ኛ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ የሚባሉት ፡ እንዲት ፡ ያሉ ፡ ታላት ፡ ናቸው ?
የዋህ ፡ እርባታ ፡ በስንት ፡ መደብ ፡ ይረባል ?
የየዋህ ፡ እርባታ ፡ መሪዎች ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
ዝርዝር ፡ እርባታ ፡ በስንት ፡ መደብ ፡ ይረባል ?
የዝርዝር ፡ እርባታ ፡ መሪዎች ፡ እነማን ፡ ናቸው ?

(ለ) በዝርዝር ፡ እርባታ ፡ ጊዜ ፡ የተሰበ,ነትን ፡ ምግባር ፡ የሚያመለክቱት ፡ የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ ስንት ፡ ናቸው ?
እነሱስ ፡ እነማን ፡ ናቸው ? የተቀበይነትን ፡ ምግባር ፡ የሚያመለክቱት ፡ የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ ስንት ፡ ናቸው ? እነሱስ ፡ እነማን ፡ ናቸው ? መስተዋድዳን ፡ የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
በ ፡ እንዴት ፡ ሆኖ ፡ ይገባል ? ለ ፡ የምን ፡ መፍቻ ፡ (መተርጉሚያ) ይሆናል ።

(ሐ) የየዋህና ፡ የዝርዝር ፡ እርባታ ፡ መሪዎች ፡ በኃላፈ ፡ በትንቢት ፡ በትእዛዝ ፡ በዐዝ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚገቡና ፡ እንደሚዘረዘሩ ፡ «ወደደ ፡ አስተማረ» በሚባሉት ፡ ግሶች ፡ አስረዳኝ ።
የዋሁን ፡ እርባታ ፡ በሮቱም ፡ መደቦች ፡ እያረባህ ፡ አስከ ፡ ፰ ፡ ቁጥር ፡ አድርሰው ።
ዝርዝሩንም ፡ እርባታ ፡ በሮቱ ፡ መደቦች ፡ እያረባህ ፡ አስከ ፡ ፺፩ ፡ ቁጥር ፡ አድርሰው ።

(መ) ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፈው ፡ ምንባብ ፡ የእርባታ ፡ መሪዎች ፡ የሆኑትን ፡ እየለየህ ፡ አስታውቅ ። የዋሁን ፡ እርባታና ፡ ዝርዝሩን ፡ እርባታ ፡ እየለየህ ፡ ጻፍ ፤ በአምንታ ፡ የተጻፈውን ፡ አንቀጽ ፡ ወደ ፡ አሉታ ፡ ለውጠው ።

ምንባብ ።

የጎንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ክደከመ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ያስነሣቸው ፡ ሰዎች ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ሠልጥነው ፡ መሰፍንት ፡ እየተባሉ ፡ ነገሥታቱን ፡ በፈቃዳቸው ፡ እያነገሡና ፡ እየሻሩ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ። ከፈጸሜ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በኋላ ፡

ታላቁ ፣ ራስ ፣ ዓለና ፣ ተከታዮቻቸው ፣ ፲፩ ፣ ዓመት ያህል ፣ ገዝተዋል ። ከዚያም ፣ በኋላ ፣ የታላቁ ፣ ዓሊ ፣ የአጎት ፣ ልጅ ፣ ራስ ፣ ጉግሣ ፣ አልጋውን ፣ ወረሰ ። እርሱም ፣ ከ፲፯፻፲፪ እስከ ፲፰፻፲፫ ፣ ዓ ፡ ም ፣ ፳፮ ፣ ዘመን ፣ በመስፍንነት ፣ የገዛ ፣ ነው ። የራስ ፣ ጉግሣ ፣ ልጆች ፣ ራስ ፣ ይማምና ፣ ራስ ፣ ማርዬ ፣ ራስ ፣ ዶሪ . . . ናቸው ።

ራስ ፣ ጉግሣ ፣ ሲሞት ፣ ልጁ ፣ ራስ ፣ ይማም ፣ ወርሶ ፣ ፱ ፣ ዓመት ፣ ያህል ፣ ገዝቶአል ። ከዚያም ፣ በኋላ ፣ ወንድሙ ፣ ራስ ፣ ማርዬ ፣ የራስ ፣ ይማምን ፣ አልጋ ፣ ወርሶ ፣ ፫ ፣ ዓመት ፣ ገዝቷል ። በእርሱም ፣ ላይ ፣ የስሜኑ ፣ ደጃች ፣ ውቤ ፣ እንደወትሮው ፣ ተነሥቶ ፣ ሸፈተና ፣ እንጨት ፣ ካብ ፣ በሚባል ፣ አገር ፣ ላይ ፣ ጦርነት ፣ ገጠመው ። ደጃች ፣ ውቤ ፣ ድል ፣ ሆነና ፣ ተያዘ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ደጃች ፣ ውቤ ፣ ወትሮ ፣ ድል ፣ መሆን ፣ ብቻ ፣ ሲሆንበት ፣ ጊዜ ፣ ተመረረና ፣ ለራስ ፣ ማርዬ ፣ ሱሌ ፣ ሆኖ ፣ ተቀመጠ ።

በዚያ ፣ ዘመን ፣ ደጃች ፣ ሰብአ ፣ ጋዲስ ፣ የሚባል ፣ የአጋሜ ፣ ገዥ ፣ ኃይል ፣ እግኝቶ ፣ በጋሎችም ፣ ላይ ፣ በርትቶ ፣ አልገዛም ፣ ብሎ ፣ ነበር ። ስለዚህም ፣ ራስ ፣ ማርዬ ፣ ሰብአ ፣ ጋዲስን ፣ ለመውጋት ፣ ዘመተ ። ሰብአ ፣ ጋዲስ ፣ እዋጋለሁ ፣ አንጂ ፣ አልሸሽም ፣ ብሎ ፣ በደብረ ፣ ዐባይ ፣ በኩል ፣ ተከዜ ፣ ወይም ፣ ማይ ፣ እስላም ፣ በሚባል ፣ ስፍራ ፣ ላይ ፣ ገጠመውና ፣ ተዋጉ ። ራስ ፣ ማርዬ ፣ ድል ፣ አድርጎ ፣ ሰብአ ፣ ጋዲስ ፣ ተማርከ ፣ ሳለ ፣ ደጃች ፣ ሐጎስ ፣ የሚባል ፣ የሰብአ ፣ ጋዲስ ፣ ልጅ ፣ አዘንግቶ ፣ ግዳይ ፣ የሚጥል ፣ ወታደር ፣ መስሎ ፣ እየፎከረ ፣ ከራስ ፣ ማርዬ ፣ ዘንድ ፣ ቀረበና ፣ አረር ፣ በተለጕመ ፣ ነፍጥ ፣ ራስ ፣ ማርዬን ፣ ግምባሩን ፣ ፈጥርቆ ፣ ጣለው ። የራስ ፣ ማርዬ ፣ አሽከሮች ፣ ደጃች ፣ ሐጎስን ፣ ወዲያው ፣ ተቀራምተው ፣ ገደሉት ። በነጋታውም ፣ ደጃች ፣ ሰብአ ፣ ጋዲስ ፣ ተደበደበ ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ የራስ ፣ ማርዬ ፣ ወንድም ፣ ራስ ፣ ዶሪ ፣ በአልጋው ፣ ተቀመጠ ። ራስ ፣ ዶሪ ፣ አጼ ፣ ሰሎሞንን ፣ በሳንደር ፣ አንግሦ ፣ ሰስት ፣ ወር ፣ ያህል ፣ እንደገዛ ፣ ወዲያው ፣ ሞተ ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ከራስ ፣ ጉግሣ ፣ ወንድም ፣ ከደጃች ፣ አሉላ ፣ የተወለደው ፣ ትኩ ፣ የሚባል ፣ ሰው ፣ ትንሹ ፣ ራስ ፣ ዓሊ ፣ ተብሎ ፣ አልጋውን ፣ ያዘ ። እርሱም ፣ በጎንደር ፣ የአጼ ፣ ተክለ ፣ ጊዮርጊስን ፣ ልጅ ፣ አጼ ፣ ዮሐንስን ፣ አንግሦ ፣ አናቱን ፣ ከአጼ ፣ ዮሐንስ ፣ ጋር ፣ አጋብቶ ፣ እቴጌ ፣ መነን ፣ አሰኝቶ ፣ ይገዛ ፣ ጀመር ። አውንም ፣ በዚህ ፣ ዘመን ፣ የትግሬውና ፣ የስሜኑ ፣ ገዥ ፣ ደጃች ፣ ውቤ ፣ ሸፍቶ ፣ ተነሣና ፣ ወደ ፣ ራስ ፣ ዓሊ ፣ ዘመተ ። እኒህም ፣ ሁለቱ ፣ መሰናክት ፣ ደብረ ፣ ታቦር ፣ ላይ ፣ ገጥመው ፣ ተዋጉ ። ነገር ፣ ግን ፣ በእ ፣ ወነን ፣ ደጃች ፣ ውቤ ፣ ድል ፣ ሆኖ ፣ ተያዘ ። በእ ፣ ወነንም ፣ ራስ ፣ ዓሊ ፣ ድል ፣ የሆነ ፣ መሰለውና ፣ ሸሽቶ ፣ ወደ ፣ ዋድላ ፣ ተፈተለከ ። ሆኖም ፣ ራስ ፣ ዓሊ ፣ አንሰራርቶ ፣ ወደ ፣ አልጋው ፣ እስኪመለስ ፣ ድረስ ፣ ዓሊ ጋዝ ፣ ብሩ ፣ የተባለ ፣ ስመ ፣ ጥር ፣ ጀግና ፣ ደጃች ፣ ውቤ ንና ፣ አልጋን ፣ ጨብጦ ፣ ቈየና ፣ ለራስ ፣ ዓሊ ፣ አስረከበ ።

የትግሬውና ፣ የስሜኑ ፣ ገዥ ፣ ደጃች ፣ ውቤ ፣ በየጊዜው ፣ ይሸፍት ፣ የነበረበት ፣ ምክንያት ፣ ጋሎች ፣ የማይገብቸውን ፣ አልጋ ፣ ይዘው ፣ በመኖራቸው ፣ ተቈርቁሮ ፣ ነው ። ስለዚህም ፣ ለስብከት ፣ እንዲመቸኝ ፣ ብሎ ፣ ጳጳሱን ፣ አቡነ ፣ ሰላማን ፣ ይዞ ፣ ተነሥቶ ፣ ነበር ። በዚህ ፣ ቀን ፣ ጳጳሱ ፣ አቡነ ፣ ሰላማ ፣ በዓለ ጋዝ ፣ እጅ ፣ ተያዘው ፣ ነበር ። እንዲህ ፣ አድርጎ ፣ አልጋን ፣ መፈለግ ፣ ለገዦች ፣ ልማዳቸው ፣ ነው ።

ራስ ፣ ዓሊ ፣ ከተመለሰ ፣ በኋላ ፣ ዓሊ ጋዝ ፣ ብሩ ፣ ያቂየውን ፣ አሥረኛ ፣ ደጃች ፣ ውቤን ፣ ፈትቶ ፣ ለቀቀው ። የስሜንም ፣ ብላገር ፣ ሁሉ ፣ የደጃች ፣ ውቤን ፣ ወንድም ፣ ደጃች ፣ መርሶን ፣ ይዘ ፣ ሸፍቶ ፣ ነበርና ፣ ደጃች ፣ ውቤን ፣ ወደ ፣ አልጋው ፣ አሳስደርስም ፣ ብሎ ፣ እንገራጠጠ ። ነገር ፣ ግን ፣ ዓሊ ጋዝ ፣ ብሩ ፣ እንደገና ፣ ጦር ፣ አስከትቶ ፣ ሄደና ፣ ደጃቹ ፣ መርሶን ፣ ወግቶ ፣ ድል ፣ ነሥቶ ፣ ደጃች ፣ ውቤን ፣ ከሸመቱ ፣ መለሰው ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ በጎጃም ፣ ደጃች ፣ ብሩ ፣ ጎሹ ፣ አልገዛም ፣ ብሎ ፣ ዐመፀና ፣ ራስ ፣ ዓሊ ፣ ወደ ፣ ጎጃም ፣ ዘምቶ ፣ ሳለ ፣ አባ ፣ ታጠቅ ፣ ደጃች ፣ ከማ ፣ (ኋላ ፣ አጼ ፣ ቴዎድሮስ ፣ የተባሉት) ፣ በራስ ፣ ዓሊ ፣ ላይ ፣ ሸፍቶ ፣ ራስ ፣ ዓሊን ፣ ለመውጋት ፣ ወደ ፣ ጎጃም ፣ ገሠገሠ ። ራስ ፣ ዓሊም ፣ ድል ፣ ሆኖ ፣ ወደ ፣ ሸዋ ፣ ሸሸቶ ፣ አመለጠ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ የመሳፍንት ፣ ዘመን ፣ ተፈጸመ ፣ ይባላል ።

ክፍል ፩ ፣ የግሥ ፣ ስልት ። ጊዜያት ።

— 188 —

መግለጫ ፣

ግሥ ፣ አራት ፣ ስልቶች ፣ አሉት ፣ እነርሱም ፣

(ሀ) ዐቢይ ፣ አንቀጽ ፣
(ለ) ትእዛዝ ፣ አንቀጽ ፣
(ሐ) አሻሻይ ፣ አንቀጽ ፣
(መ) ንኡስ ፣ አንቀጽ ፣

ተብለው ፣ ይጠራሉ ። በግዕዝ ፣ ሰዋስው ፣ ማሰሪያ ፣ ለመሆን ፣ የሚችል ፣ ግሥ ፣ ሁሉ ፣ በጠቅላላው ፣ ዐቢይ ፣ አንቀጽ ፣ ይባላል ። ከዚህም ፣ የተነሣ ፣ ትእዛዝ ፣ አንቀጽ ፣ በዐቢይ ፣ አንቀጽ ፣ ክፍል ፣ ሆኖ ፣ ይነገራል ። አውን ፣ ግን ፣ ትእዛዝ ፣ አንቀጽ ፣ ሰብሥው ፣ ሆኖ ፣ ተመድቦአል ፣ ምክንያቱንም ፣ በአገባብ ፣ መመልከት ፣ ነው ። አሻሻይ ፣ አንቀጽ ፣ የተባለውም ፣ በግዕዙ ፣ ሰዋስው ፣ ዘንድ ፣ አንቀጽ ፣ ተብሎ ፣ የሚነገረው ፣ ነው ።

— 189 —

ግሦች ፣ የሚረቡባቸው ፣ ጊዜያቶች ፣ ሶስት ፣ ናቸው ።

ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፤ ያለፈውን ፡ ነገር ፡ የሚያመለክት ፡ ወደደ ፤ ፈለገ ፤ . . . እ ፡ ግ ፡ የአ
ሁን ፡ ጊዜያት ፡ አሁን ፡ የተደረገውን ፡ የሚያመለክት ። ይወድዳል ፡ ይፈልጋል ፤ . . . እ·ግ ፤

ትንቢታዊ ፡ ጊዜያት ፡ ወደፊት ፡ የሚሆነውን ፡ የሚያመለክት ። ይወድዳል ፡
ይፈልጋል ፤ . . . እ.ግ.

እነዚህ ፡ ደግሞ ፡ የዋዚ ፡ የቅርብ ፡ የሩቅ ፤ . . . የሚያሰኝ ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ አላቸው ።
የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፤ «በመሆንና ፡ በአለኝ ፡ ማለት ፡» ግሥ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡
በሌሎቹ ፡ ግሦች ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፤ ከላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ቃል ፡
ይነገራል ።

—190—

ጾታ ፡ —መደብ— ፡ ቍጥር ።

ግሥ ፡ እንደ ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ ተባዕትና ፡ አንስት ፡ ጾታ ፡ የነጠላና ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡
አለው ። ደግሞም ፡ እንደ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ፫ ፡ መደቦች ፡ አሉት ። እነርሱም ፡ ያኛ ፡ ያኛ ፡
፫ ፡ ይባላሉ ።

ምሳሌ ፤ ፈለግሁ ፤ ፈለግህ ፡ ፈለግሽ ፤ ፈለገ ፤ ፈለገች ፡ ፈለግን ፡ ፈለጋችሁ ፤ ፈለጉ ፤
ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

—191—

(ሀ) ዐቢይ ፡ አንቀጽ ።

ዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ለቃላት ፡ ማሰሪያና ፡ መፈጸሚያ ፡ የሚሆን ፡ ቃል ፡ ነው ። እነሆ ፡
በቮቱ ፡ ጊዜያቶች ፡ እንዲት ፡ እንደሚገባ ፡ መፈለግ ፡ በሚል ፡ ግሥ ፡ በገቢርና ፡ በተገብሮ ፡
በቮተኛ ፡ መደብ ፤ ተባ ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ እያረባን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እናሳያለን ።

ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፤	ገቢር ፡ ግሥ ፤	ተገብሮ ፡ ግሥ ፡
የዋህ ፡ ጎላፊ ፡	ፈለገ ፡	ተፈለገ ፡
የቅርብ ፡ ጎላፊ ፡	ፈልጎአል ፡	ተፈልጎአል ፡
የሩቅ ፡ ጎላፊ ፡	ፈልጎ ፡ ነበር ፡	ተፈልጎ ፡ ነበር ፡
የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።		
የዋህ ፡	ይፈልግአል ፡	ይፈለጋል ፡
የቅርብ ፡	ሊፈልግ ፡ ነው ፡	ሊፈለግ ፡ ነው ፤

የቅርብ ፡ ትንቢት ፡ በተመሰነ ፡ አከሄድ ፡ ከልሆነ ፡ በቀር ፡ መደበኛነት ፡ የለውም ።

—192—

ለ) ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ።

የማዘዝ ፡ ምግባር ፡ የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ይባላል ።
እርሱም ፡ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ለቃላት ፡ ማሰሪያ ፡ ይሆናል ።

የአሁን ፡ ጊዜያት ፡ ይፈልግ ፡ ይፈለግ
ትንቢታዊ ፡ ጊዜያት ፡ እንዲፈልግ ፡ ይሁን ፡ እንዲፈለግ ፡ ይሁን ፡
ዋኛው ፡ ትእዛዝ ፡ በአሁን ፡ ጊዜያት ፡ በዩኛው ፡ መደብ ፡ የሚነገረው ፡ ነው ፤ ይ'ኸውም ፡
«ፈልግ ፤ ተፈለግ ፡» የሚል ፡ ነው ።

—193—

(ሐ) አዋዋይ ፡ አንቀጽ ።

አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ የተባለው ፡ ውሳኔን ፤ ምክንያትን ፡ ምጥትን ፡ ጸጸትን ፡
የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ነው ። በግዕዙ ፡ ሰዋስው ፡ «ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ ወይም ፡ ሣልሳይ ፡»
ተብሎ ፡ ይጠራል ። አሁን ፡ ግን ፡ በአዲስ ፡ ውሳኔ ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ ብለን ፡ ሰይ
መነዋል ።

—194—

አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ «ምክንያታዊ ፡ ተምኔታዊ ፤» ተብሎ ፡ በሁለት ፡ አካሄድ ፡
ይከፈላል ።

«ምክንያታዊ ፡» የተባለው ፡ ምክንያትን ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፡ ማሰሪያ ፡ ለመሆን ፡
አይችልም ፤ » ዘንድ ፤ ሊ ፤ እንደ ፤ ቢ ፡ ኖሮ ፤ የሚያሰኙ ፡ ቃላት ፡ በትንቢታዊ ፡ ቦዝ ፡
ከ ፤ (የ—እንደሆነ ፡) በጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ ላይ ፡ እየተጨመሩ ፡ ሲገቡ ፡ ምክንያት ፡ ገላጮች ፡
ይሆናሉ ። ይኸውም ፡» ይፈልግ ዘንድ ፤ እንዲፈልግ ፡ ሊፈልግ ፡ ቢፈልግ ፡ ኖሮ ፡ ከፈ
ለገ ፤ የፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ እያለ ፡ ይረባል ፤ ማለት ፡ ነው ።

— 195 —

«ተምኔታዊ ፡ » የተባለውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። (ሀ) በጎላፊ ፡ አንቀጽ ፡
ላይ ፡ በ ፡ የሚል ፡ ፊደል ፡ በስተ ፡ መነሻ ፡ ሲጨመርበት ፡ ማሰሪያ ፡ ይሆናል ። አዋዋይ፡
መስተፃምር ፡ ቢ ፡ ቢ ፡ —ኖሮ ፡) ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ፡ ሆኖ ፡ 'ይከተለዋል ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ የጸጸትን ፡ ወይም ፡ የምጥትን ፡ ምግባር ፡ ያመለክታል ። ይኸውም ፡ በፈለገ ፡ ነበር ፤
በገባ ፡ ነበር ፤ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። (ለ) በትንቢት ፡ ቦዝ ፡ ላይ ፡ «ነበር ፡» የሚል ፡ የግሥ ፡
ረዳት ፡ እየተጨመረበት ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ ይፈልግ ፡ ነበር ፤ ይገባ ፡ ነበር ፤ ይላል ፡
ማለት ፡ ነው ።

— 196 —

(መ) ንኡስ ፡ አንቀጽ ።

በንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ክፍል ፡ የሚነገሩት ፡ «አርእስት ፤ ቦዝ ፤ አንቀጽ ፤ ግሣዊ ፡
ቅጽል ፤ ዘር ፡ ናቸው ።

አርእስት ፡ የተባለው ፡ መነሻው ፡ ሁልጊዜ ፡ «መ» በሚል ፡ ፊደል ፡ የሚጀመር ፡
የነገር ፡ ስም ፡ ነው ። ግሥ ፡ ከአርሱ ፡ ስለሚመሠረት ፡ አርእስት ፡ ተብሎአል ።
ምሳሌ ። መፈለግ ፤ መግባት ፤ መሆን ፡ መኖር ፤

— 197 —

አርእስት ፡ በግብሩ ፡ የነገር ፡ ስም ፡ ነው ፡ ብለናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ ስለሌለው ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ልዩ ፡ ጠባይ ፡ አለው ።

ምሳሌ፡ . .መግበት ፡ መፈለግ ፡ . .የሚሰው ፡ ቃል፡ . .መግበቶች ፡ መፈሰጎች ፡ ተብሎ ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ቁጥር ፡ አይለወጥም ። በምሥጢር ፡ አርእስትን ፡ የሚመስል ፡ ሳቢ ዘር ፡ የሚባል ፡ ቃል ፡ አለ ። እርሱም ፡ አፈላለግ ፤ አገባብ ፡ እንደማለት ፡ ያለ ፡ ነው ። ሳቢ ዘር ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ቁጥር ፡ ሲለወጥ ፡ ይችላል ፡ ይኸውም ፡ አፈላለጎች ፡ አገባቦች ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

— 198 —

ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ በጎላፊና ፡ በትንቢት ፡ ጊዜያት ፡ ይነገራል ።

ምሳሌ ። ፈልጎ ፤ ገብቶ ፤ . . . (ጎላፊ ፡ ቦዝ)

ይፈልግ ፤ ይገባ ፡ . . . (ትንቢታዊ ፡ ቦዝ ፡)

ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ ከላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ ብቻውን ፡ ሲነገር ፡ አንዳች ፡ የንግግር ፡ ስሜት ፡ አይገለጽበትም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከግሥ ፡ ረዳቶች ፡ ጋር ፡ ሲነገር ፡ ጎላፊውም ፡ ትንቢቱም ፡ ማስሪያ ፡ አንቀጽ ፡ (ወቢይ ፡ አንቀጽ ፡)ይሆናል ። (ቁ. 153 አይ ።) ጎላፊ ፡ ቦዝ ፡ ያለ ፡ ግሥ ፡ ረዳት ፡ ከሌሎች ፡ ግሦች ፡ ጋር ፡ ሲነገር ፡ የጊዜው ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ይሆናል ። ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ በሚከተለው ፡ ምሳሌ ፡ እናስረዳለን ።

ምሳሌ ፤ (ሀ) ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ሲሆን ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ፈልጎአል ፤ ፈልጎ ፡ ነበር ፤ ገብቶአል ፤ ገብቶ ፡ ነበር ።
ይፈልግአል ፤ ይፈልግ ፤ ነበር ፡ ይገባል ፤ ይገባ ፡ ነበር ።

(ለ)ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ሲሆን ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ተማሬ ፡ መጽሐፉን ፡ ፈልጎ ፡ አገኘ ።
ተማሪውን ፡ ከቤት ፡ ገብቶ ፡ አየሁት ።

— 199 —

«ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ »በየዋህ ፡ ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ «የ» በአሁንና ፡ በትንቢት ፡ ጊዜያት፡ «የም ፡ የሚ ፡ » የሚል ፡ መስተዛምራዊ ፡ አገባብ ፡ እየተጨመረበት ፡ የሚነገር ፡ ቃል ፡ ነው ። በግስገ ፡ ሰዋስው ፡ ግልስ ፡ ቅጽል ፡ ሳድስ ፡ ቅጽል ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ምሳሌ ፡ የፈስገ ፡ የገባ ፡ የሆነ ፡ የነበረ ፡ . . . . .(ጎላፊ ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡)

የሚፈልግ ፡ የሚገባ ፡ የምሆን ፡ የምኖር ፡ . . . . . (ትንቢታዊ ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡

200 —

«ዘር ፡» የሚባለው ፡ ከግሥ ፡ ከሩል ፡ የሚገኘው ፡ ወይም ፡ ግሥን ፡ የሚያስገኘው ፡ የግብር ፡ ስም ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ ፍለጋ ፡ ፍላጎት ፡ ሁኔታ ፡ አለኘታ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

፲፪ኛ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) የግሥ ፡ ስልቶች ፡ ስንት ፡ ናቸው ?

ወቢይ ፡ አንቀጽ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ነው ?
ዋነኛው ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ነው ?
አዋዋይ ፡ አንቀጽና ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ቃሳት ፡ ናቸው ?
ለነዚህ ፡ ለተጻፉት ፡ ጥያቄዎች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ምሳሌ ፡ አምጣ ።

(ለ) አርእስት ፡ የተባለውን ፡ በምሳሌ ፡ ንገረኝ ።

ጎላፊ ፡ ቦዝና ፡ ትንቢታዊ ፡ ቦዝ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡« መረቀ ፤ ረገመ ፤ ገደለ ፡» በሚል ፡ ግሥ ፡ አስረዳኝ ። በወቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ክፍል ፡ «ጎላፊ ፤ የአሁንና ፡ ትንቢት ፤» የተባሉትን ፡ ጊዜያቶች ፡ በነዚሁ ፡ ግሦች ፡ እያረባህ ፡ አስረዳኝ ። ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ዘር ፡ የሚባለውን ፡ በምሳሌ ፡ አስረዳኝ ።

(ሐ) ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፈው ፡ ምንባብ ፡ ፩ቱን ፡ የነገር ፡ ስልቶችና ፡ ቦቱን ፡ ጊዜያቶች ፡ እየለየህ ፡ በየወገኑ ፡ አመልክት ።

ም ን ባ ብ ፡

ከመሰፍንት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ አልጋውን ፡ የያዙ ፡ አጼ ፡ ቴምድሮስ ፡ ናቸው ። አጼ ፡ ቴምድሮስ ፡ የቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ ካሣ ፡ ይባል ፡ ነበር ። የትንሽ ፡ ራስ ፡ ዓሊን ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችን ፡ አግብተው ፡ ከራስ ፡ ዓሊ ፡ በታች ፡ በተራ ፡ ወታደርነት ፡ ሲኖሩ ፡ በኑሮአቸው ፡ ተመረሩና ፡ ሸፈቱ ።

አማታቸው ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ዘምተው ፡ ሳሉ ፡ ከራስ ፡ ዓሊ ፡ እናት ፡ ከእቴጌ ፡ መነን ፡ ጋር ፡ ተዋጉ ። እቴጌ ፡ መነንን ፡ ድል ፡ አደረጉዋቸውና ፡ ወዲያው ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ ወሰሉበት ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ገሠገሡ ። ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ ድል ፡ ሆኑና ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ገቡ ።

ቋረኛው ፡ ከሣ ፡ አብ ፡ ታጠቅ ፡ በያገሩ ፡ እየተዋጉ ፡ አገር ፡ ሲያሳምኑ ፡ ፱ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቈዩ ። በ[illegible] ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ የሸዋን ፡ ባለአልጋ ፡ ምኒልክን ፡ (በኋላ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ የተባሉትን ፡) አግኝተው ፡ ይዘው ፡ ተመለሱ ። አጼ ፡ ምኒልክ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አብ ፡ ታጠቅ ፡ ከሣ ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ሄደው ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ወግተው ፡ ስሜን ፡ ላይ ፡ በጸደቡ ፡ በአውን ፡ ሰላማ ፡ እጅ ፡ ተቀብተው ፡ አጼ ፡ ቴምድሮስ ፡ ተብለው ፡ ነገሡ ።

የአጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የመጀመሪያ ፡ አሳባቸው ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ አሰማምተው ፡ ሽፍታንና ፡ ወንበዴን ፡ አጥፍተው ፡ ለመግዛት ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በኋላ ፡ ግን ፡ በሕዝብ ፡ ጠባይ ፡ ተመረሩና ፡ የፈተኖው ፡ አሳባቸው ፡ እየጐደለ ፡ ሄደ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሊታውንትና ፡ ሕዝቡ ፡ አሊረው ፡ ከባዕድ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አጣሉአቸው ። መኳንንቱና ፡ ባላገሩም ፡ በያለበት ፡ ከዳቸው ። በመጨረሻም ፡ ሰር ፡ ሮቤርት ፡ ናፒዬር ፡ የሚባል ፡ የእንግሊዝ ፡ የመር ፡ አበጋዝ ፡ የሀንድ ፡ መታደሮችን ፡ ይዘ ፡ መጥቶ ፡ ከበባቸው ። እርሳቸውም ፡ ብዙ ሞውን ፡ እንደቀሩ ፡ አይተው ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ገቡ ። በዚያም ፡ የተጋላቸውን ፡ ያህል ፡ ከተከላከሉ ፡ በኋላ ፡ ጠሩ ፡ ገፍቶ ፡ ቢደርስባቸው ፡ አልማረክም ፡ ብለው ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ሕይወታቸውን ፡ አሳልፈው ፡ ሞቱ ። ስለ ፡ አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታሪክ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መጽሐፍ ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል ።

ከአጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ የላስታው ፡ ባላባት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አጼ ፡ ተብለው ፡ አልጋውን ፡ ያዙ ። እርሳቸውም ፡ ቀድሞ ፡ ከአጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በታች ፡ በተገዥነት ፡ ሰሱ ፡ ወሎ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ጀግንነታቸውን ፡ ስላሳዩ ፡ ተመስግነው ፡ ታፍረው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። አጼ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተወላጅነታቸው ፡ ነገደ ፡ ዛጔ ፡ ከሚባለው ፡ ከአገው ፡ ላስታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ አይደለም ። ስለዚህም ፡ ጎጃሞች ፡ በየጊዜው ፡ እንገዛም ፡ እያሉ ፡ ስለአወኩአቸው ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ዘምተው ፡ ነበር ። በዚያም ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ደጃች ፡ ተድላን ፡ ይዘው ፡ አገሩን ፡ ለራስ ፡ አዳል ፡ ሰጥተው ፡ ተመለሱ ። ፫ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደገዙ ፡ በትግሬ ፡ አባ ፡ በዝብዝ ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ ተነሡባቸውና ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ሄመቱ ፡ በውጊያውም ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ተያዙና ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ታስረው ፡ ሞቱ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ « አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተብለው ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ገዙ ። ከርሳቸውም ፡ ቀጥሎ ፡ የሸዋው ፡ ንጉሥ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተብለው ፡ ፳፪ ፡ ዓመት ፡ ገዙ ። የእነዚህ ፡ የሁለቱ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ በሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

ክፍል ፮ ፡ የግሥ ፡ አረባብ ።

— 201 —

የመሆን ፡ ግሥ ፡

የመሆን ፡ ግሥ ፡ እርባታ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። እርባታውም ፡ በሁለት ፡ አከሄድ ፡ ይመደባል ። ፩ኛው ፡ ሁኔታን ፡ ያመለክታል ። ፪ተኛውም ፡ በስፍራው ፡ ላይ ፡ መገኘትን ፡ ወይም ፡ መኖርን ፡ ያመለክታል ።

(ሀ) ወቢያ ፡ አንቀጽ ።

1 . የአሁን ፡ ጊዜያት ፡

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ ፡	እኔ ፡ ነኝ ፡	፩ ፡ እኛ ፡ ነን ፡	፩ ፡ እኔ ፡ አለሁ ፡	፩ ፡ እኛ ፡ አለን ፡
፪—	አንተ ፡ ነህ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፡	፪ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ	፪— አንተ ፡ አለህ ፡ አንቺ ፡ አለሽ ፡	፪ ፡ እናንተ ፡ አላችሁ ፡
፫—	እርሱ ፡ ነው ፡ እርስዋ ፡ ነች (ናት)	፫ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው	፫— እርሱ ፡ አለ ፡ እርስዋ ፡ አለች ፡	፫ ፡ እነርሱ ፡ አሉ ፡

ማስገንዘቢያ ፡

የአማርኛ ፡ ግሥ ፡ እኔ ፡ አንተ ፡ . . . የሚለው ፡ ተውላጠ ፡ ግሥ ፡ ሳይጨመርበትም ፡ ሊረባ ፡ ይችላል ።

2 . ጎላፊ ፡ ጊዜያት

፩— ነበርሁ ፡	፩—ነበርን ፡	፩— ነበርሁ ፡	፩—ነበርን ፡
፪— ነበርህ ፡ ነበርሽ ፡	፪—ነበራችሁ ፡	፪— ነበርህ ፡ ነበርሽ ፡	፪—ነበራችሁ ፡
፫— ነበረ ፡ ነበረች ፡	፫—ነበሩ ፡	፫— ነበረ ፡ ነበረች ፡	፫—ነበሩ ፡

3 . ትንቢታዊ ፡ ጊዜያት ።

፩— እሆናለሁ ፡	፩—እንሆናለን ፡	፩— እኖራለሁ ፡	፩—እንኖራለን ፡
፪— ትሆናለህ ፡ ትሆኛለሽ ፡	፪—ትሆናላችሁ ፡	፪— ትኖራለህ ፡ ትኖሪአለሽ ፡	፪—ትኖራላችሁ ፡
፫— ትሆናለህ ፡ ትሆናለች ፡	፫—ይሆናሉ ፡	፫— ይኖራል ፡ ትኖራለች ፡	፫—ይኖራሉ ፡

(ለ) ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡

፩— ልሁን ፡	፩—እንሁን ፡	፩— ልኑር ፡	፩—እንኑር ፡
፪— ሁን ፡ ሁኚ ፡	፪—ሁኑ ፡	፪— ኑር ፡ ኑሪ ፡	፪—ኑሩ ፡
፫— ይሁን ፡ ትሁን ፡	፫—ይሁኑ ፡	፫— ይኑር ፡ ትኑር ፡	፫—ይኑሩ ፡

(ሐ) አዋዋይ ፡ አንቀጽ ።

፩— ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ።

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ።

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩—	ብሆን ፡ ናሮ ፡	፩—ብንሆን ፡ ናሮ ፡	፩— ኖሬ ፡ ቢሆን ፡	፩—ኖረን ፡ ቢሆን ፡
፪—	ብትሆን ፡ ናሮ ፡ ብትሆኚ ፡ ናሮ ፡	፪—ብትሆኑ ፡ ናሮ ፡	፪ ኖረህ ፡ ቢሆን ፡ ኖረሽ ፡ ቢሆን ፡	፪—ኖራችሁ ፡ ቢሆን ፡
፫—	ቢሆን ፡ ናሮ ፡ ብትሆን ፡ ናሮ ፡	፫—ቢሆኑ ፡ ናሮ ፡	፫— ኖሮ ፡ ቢሆን ፡ ኖራ ፡ ቢሆን ፡	፫—ኖረው ፡ ቢሆን ፡

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

፩—	ብሆን ፡	፩—ብንሆን ፡	፩— ብኖር ፡	፩—ብንኖር ፡
፪—	ብትሆን ፡ ብትሆኚ ፡	፪—ብትሆኑ ፡	፪— ብትኖር ፡ ብትኖሪ ፡	፪—ብትኖሩ ፡
፫—	ቢሆን ፡ ብትሆን ፡	፫—ቢሆኑ ፡	፫— ቢኖር ፡ ብትኖር ፡	፫—ቢኖሩ ፡
፩—	እሆን ፡ ዘንድ ፡	፩—እንሆን ፡ ዘንድ ፡	፩— እኖር ፡ ዘንድ ፡	፩—እንኖር ፡ ዘንድ ፡
፪—	ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ትሆኚ ፡ ዘንድ ፡	፪—ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡	፪— ትኖር ፡ ዘንድ ፡ ትኖሪ ፡ ዘንድ ፡	፪—ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡
፫—	ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡	፫—ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡	፫— ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡	፫—ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡

ማስገንዘቢያ ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ፡ «እንድ ፡ ል ፡» የሚል ፡ ቃል ፡ እየተጨመረበት ፡ ይረባል ። ይኸውም ፡ እንደሆን ፡ ልሆን ፡ እንድኖር ፡ ልኖር ፡ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪ ፡ ተምኔታዊ ፡ አዋዋይ ።

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ።

፩—	በሆንሁ ፡ ነበር ፡	፩—ብሆንን ፡ ነበር ፡	፩— በኖርሁ ፡ ነበር ፡	፩—በኖርን ፡ ነበር ፡
፪—	በሆንህ ፡ ነበር ፡ በሆንሽ ፡ ነበር ፡	፪— በሆናችሁ ፡ ነበር ፡	፪— በኖርህ ፡ ነበር ፡ በኖርሽ ፡ ነበር ፡	፪—በኖራችሁ ፡ ነበር
፫—	በሆነ ፡ ነበር ፡ በሆነች ፡ ነበር ፡	፫ በሆኑ ፡ ነበር ፡	፫— በኖረ ፡ ነበር ፡ በኖረች ፡ ነበር ፡	፫—በኖሩ ፡ ነበር ፡

ማስገንዘቢያ ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ እርባታ ፡ «ነበር» የሚለው ፡ የግሥ ፡ ረዳት ፡ ሳይጨመርበትም ፡ ብቻውን ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ «በሆንሁ ፡ በኖርሁ ፡ ያሰኛል ፡ ማለት ፡ ነው ።

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ ፡	እሆን ፡ ነበር ፡	፩ ፡ እንሆን ፡ ነበር ፡	፩ ፡ እኖር ፡ ነበር ፡	፩—እንኖር ፡ ነበር
፪ ፡	ትሆን ፡ ነበር ፡ ትሆኚ ፡ ነበር ፡	፪ ፡ ትሆኑ ፡ ነበር ፡	፪ ፡ ትኖር ፡ ነበር ፡ ትኖሪ ፡ ነበር ፡	፪—ትኖሩ ፡ ነበር ፡
፫ ፡	ይሆን ፡ ነበር ፡ ትሆን ፡ ነበር ፡	፫ ፡ ይሆኑ ፡ ነበር ፡	፫ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ ትኖር ፡ ነበር ፡	፫—ይኖሩ ፡ ነበር ፡

(መ) ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ።

አርእስት ።

መሆን ፡ መኖር ፡

ዐዝ ፡ አንቀጽ ፡

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡

ሆኖ ፡ ኖሮ ፡

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡

፩— እሆን —	፩—እንሆን —	፩ — እኖር —	፩ — እንኖር —
፪— ትሆን — ትሆኚ —	፪ — ትሆኑ —	፪ — ትኖር — ትኖሪ —	፪ — ትኖሩ —
፫— ይሆን — ትሆን —	፫ — ይሆኑ —	፫ — ይኖር — ትኖር —	፫ — ይኖሩ —

ግሣዊ ፡ ቅጽል ።

ጎላፊ ፡ ጊዜያት ። — የነበርሁ ፡ የነበርህ ፡ እያለ . . . ይረባል ።
የአሁን ፡ ጊዜያት ። — የሆንሁ ፡ የሆንህ ፡ እያለ . . . ይረባል ።
ትንቢታዊ ፡ ጊዜያት ። — የምሆን ፡ የምትሆን ፡ የምኖር ፡ የምትኖር . . እያለ ፡ ይረባል ።

ዘር ።

ውኔታ ፡ አካኋን ፡ መሆን ። ‖ ኑሮ ፡ አኗኗር ፡ መኖር ።

የመሆን ፡ ግሥ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነው ። ክፍሉም ፡ ከተደራጊ ፡ ዐምድ ፡ ስለሆነ ፡ ከላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ በየዋህ ፡ እርባታ ፡ ብቻ ፡ ይረባል ፡ እንጂ ፡ ግርዝር ፡ እርባታ ፡ የለውም ።

«ሆነ ፡ ነበረ ፡» የሚባሉት ፡ ግሦች ፡ በነባሩ ፡ ግሥ ፡ «በመሆን ፡» ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ ገብተው ፡ እንደተነገሩ ፡ አስተውል ። ነገር ፡ ግን ፡ በግሥነት ፡ ደንበኞው ፡ ተለይተው ፡ ሲነገሩ ፡ ልዩነት ፡ እንዳላቸው ፡ ማወቅ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ። በአገባብ ፡ ተመልከት ።

— 203 —

የመኖር ፡ (ወይም ፡ የአለኝ ፡ ማለት፡) ግሥ ።

የመኖር ፡ ግሥ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። የመኖር ፡ ግሥ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ትር ጓሜ ፡ አለው ። እንደኖው ፡ በቢታው ፡ ላይ ፡ የመኖርን ፡ ወይም ፡ የመገኘትን ፡ ምግባር፡ የሚያመለክተው ፡ ነው ። የእርሱም ፡ መደቡ ፡ ከመሆን ፡ ግሥ ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ፡ በቁ ፡ 202 ፡ አረባበን ፡ አሳይተናል ። አሁን ፡ ግን ፡ በልዩ ፡ መደብ ፡ የምንጽፈው ፡ ‹የመ ኖር ፡ ግሥ ፡ › የማግኘት ፡ ወይም ፡ የአለኝ ፡ ማለት ፡ ምግባር ፡ የሚገለጽበት ፡ ነውና ፡ ልዩነ ቱን ፡ በየስልቱ ፡ መመርመር ፡ ነው ።

(ሀ) ዐቢይ ፡ አንቀጽ ።

1. የአሁን ፡ ጊዜያት ።

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ —	አለኝ ፡	፩ — አለን ፡
፪ —	አለህ ፡ / አለሽ	፪ — አላችሁ ፡
፫ —	አለው ፡ / አላት ፡	፫ — አላቸው ፡

2 ፡ ግላፊ ፡ ጊዜያት ።

፩ —	ነበረኝ ፡	፩ — ነበረን ።
፪ —	ነበረህ ፡ / ነበረሽ ፡	፪ — ነበራችሁ ።
፫ —	ነበረው ፡ / ነበራት ፡	፫ — ነበራቸው ።

3. ትንቢታዊ ፡ ጊዜየት ።

፩ —	ይኖረኛል ፡	፩ — ይኖረናል ፡
፪ —	ይኖርሃል ፡ / ይኖርሻል ፡	፪ — ይኖራችኋል ፡
፫ —	ይኖረዋል ፡ / ይኖራታል ፡	፫ — ይኖራቸዋል ፡

(ለ) ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ።

፩ —	ይኑረኝ ፡	፩ — ይኑረን ፡
፪ —	ይኑርህ ። / ይኑርሽ ፡	፪ — ይኑራችሁ ፡
፫ —	ይኑረው ፡ / ይኑራት ፡	፫ — ይኑራቸው ፡

ማስገንዘቢያ ። እንዲኖረኝ ፡ ይሁን ፡ እንዳኖርህ ፡ ይሁን ፡ እያለም ፡ ይረባል ።

(ሐ) አዋዋይ ፡ አንቀጽ ።

፩— ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ።

1. ግላፊ ፡ ጊዜያት ፡

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩ ፡	ኖሮኝ ፡ ቢሆን ፡	፩ ፡ ኖሮን ፡ ቢሆን ፡
፪ ፡	ኖሮህ ፡ ቢሆን ፡ / ኖሮሽ ፡ ቢሆን ፡	፪ ፡ ኖራችሁ ፡ ቢሆን ፡
፫ ፡	ኖሮት ፡ ቢሆን ፡ / ኖሮአት ፡ ቢሆን ፡	፫ ፡ ኖሮአቸው ፡ ቢሆን ፡

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

፩ ፡	ቢኖረኝ ፡	፩ ፡ ቢኖረን ፡
፪ ፡	ቢኖርህ ፡ / ቢኖርሽ ፡	፪ ፡ ቢኖራችሁ ፡
፫ ፡	ቢኖረው ፡ / ቢኖራት ፡	፫ ፡ ቢኖራቸው ፡
፩ ፡	ይኖረኝ ፡ ዘንድ ፡	፩ ፡ ይኖረን ፡ ዘንድ ፡
፪	ይኖርህ ፡ ዘንድ ፡ / ይኖርሽ ፡ ዘንድ ፡	፪ ፡ ይኖራችሁ ፡ ዘንድ ፡
፫ ፡	ይኖረው ፡ ዘንድ ፡ / ይኖራት ፡ ዘንድ ፡	፫ ፡ ይኖራቸው ፡ ዘንድ ፡

ማስገንዘቢያ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ፡ ‹እንድ ፡ ል› የሚል ፡ ቃል ፡ እየተጨመረበት ፡ ይረባል ። ይኸውም ፡ እንዲኖረኝ ፡ ሊኖረኝ ፡ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪— ተምኔታዊ ፡ አዋዋይ ።

1. ግላፊ ፡ ጊዜያት ፡

ጸጸትና ፡ ምኞት ፡	፩ ፡	በኖረኝ ፡ ነበር ፡	፩ ፡ በኖረን ፡ ነበር ፡
	፪ ፡	በኖረህ ፡ ነበር ፡ / በኖረሽ ፡ ነበር ፡	፪ ፡ በኖራችሁ ፡ ነበር ፡
	፫ ፡	በኖረው ፡ ነበር ፡ / በኖራት ፡ ነበር ፡	፫ ፡ በኖራቸው ፡ ነበር ፡

2. የአሁንና ፣ የትንቢት ፣ ጊዜያት ።

		ነጠላ ፣	ብዙ ፣
ጸጸትና ፣ ምኞት ፣	፩ ፤	ይኖረኝ ፣ ነበር ፣	፩ ፤ ይኖረን ፣ ነበር ፣
	፪ ፣	ይኖርህ ፣ ነበር ። / ይኖርሽ ፣ ነበር ፣	፪ ፤ ይኖራችሁ ፣ ነበር ፣
	፫ ፤	ይኖረው ፣ ነበር ፣ / ይኖራት ፣ ነበር ፣	፫ ፤ ይኖራቸው ፣ ነበር ፣

(መ) ንኡስ ፣ "አንቀጽ"

አርእስት ።

መኖር ፣ ወይም ፣ አለኝ ፣ ማለት ፣

በዝ ፣ አንቀጽ ፣

1. ጎላፊ ፣ ጊዜያት ፣

ነበር ፤ ኖሮ ።

2. የአሁንና ፣ የትንቢት ፣ ጊዜያት ፣

፩ — ይኖረኝ—	፩—ይኖረን—
፪— ይኖርህ— / ይኖርሽ—	፪—ይኖራችሁ—
፫— ይኖረው— / ይኖራት—	፫—ይኖራቸው—

ግማዊ ፣ ቅጽል ።

ጎላፊ ፣ ጊዜያት ፡—የነበረኝ ፤ የነበረህ ፣ . . . እያለ ፣ ይረባል ።
የአሁን ፣ ጊዜያት ፡—የአለኝ ፤ የአለህ ፣ . . . እያለ ፣ ይረባል ።
ትንቢታዊ ፣ ጊዜያት ፡—የሚኖረኝ ፣ የሚኖርህ ፣ . . . እያለ ፣ ይረባል ።

ዘርና ፣ ላቢዘር ።

አለኝታ ፣ ወይም ፣ አለኝ ፣ ማለት ። መኖር ፤ ንብረት ።

— 204 —

የመኖር ፣ ግሥ ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ እንደተጻፈው ፣ በየዋህ ፣ እርባታ ፣ ብቻ ፣ ይረባል ፣ እንጂ ፣ ዝርዝር ፣ እርባታ ፣ የለውም ። በንባብ ፣ ተዋብሮን ፣ ሊመስል ፣ በምሥጢር ፣ ገቢር ፣ ነው ። « መያዝ ፣ ማግኘት ፣ » የሚሰሉት ፣ ግሦች ፣ ይዘመዱታል ። እንደ ፣ ልማድ ፣ ሆኖ ፣ ገቢርን ፣ ሳይስብም ፣ ይነገራል ፣ እንጂ ፣ መሳብ ፣ ይገባው ፣ ነበር ። በግዕዙም ፣ ሰዋስው ፣ « በ ፣ አልበ ፣ » የሚለው ፣ የመኖር ፣ ግሥ ፣ በዱሮ ፣ ጊዜ ፣ ገቢርን ፣ ይስብ ፣ ነበር ፣ ይባላል ። ይኸውም ፣ « ሐመር ፣ ሐዳስ ፣ ዘአልብኪ ፣ ነውረ ፣ » በማለቱ ፣ ይታያል ።

ክፍል ፣ ፯ ፣ የግሥ ፣ ሙሉ ፣ እርባታ ።

— 205 —

ግሦችን ፣ በየወገናቸው ፣ ለማርባት ፣ እንዲመች ፣ የሚከተሉት ፣ ግሦች ፣ አለቆች ፣ ተባለው ፣ ይጠራሉ ።

1) መፈለግ ፣ —መድረሻው ፣ ግእዝ ፣ ለሆነ ፣ ግሥ ፣ (ለ ፣ ከሚሆን ፣ በቀር ።)
2) መክፈል ፣ —መድረሻው ፣ "ለ" የሚል ፣ ግዕዝ ፣ ፊደል ፣ ለሆነ ፣ ግሥ ።
3) መግበት ፣ —መድረሻው ፣ ራብዕ ፣ ለሆነ ፣ ለማናቸውም ፣ ግሥ ።
4) መከተል ፣ —በመነሻው ፣ ተ ፣ የሚል ፣ ፊደል ፣ ለሚገኝበት ፣ ግሥ ።
5) ማወቅ ፣ —መነሻው ፣ አ ፣ ዐ ፣ ለሆነ ፣ ግሥ ።
6) መውደድ ፣ —በዶጊም ፣ ለሚነገር ፣ ግሥ ።

—206—

በዶጊም ፣ የሚነገር ፣ ግሥ ፣ በእርባታ ፣ ጊዜ ፣ በአንዳንድ ፣ ስፍራ ፣ ላይ ፣ ፅኖው ፣ ቀለም ፣ ጠብቆ ፣ ፄኖው ፣ ተውጦ ፣ ይነገራል ። ይኸውም ፣ ወደደ ፣ ብሎ ፣ ይወዳል ፣ ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ በጽሕፈት ፣ ላይ ፣ የማጥበቂያ ፣ ምልክት ፣ ኀና ፣ ስላልተጸነጎገ ፣ ፊደሉ ፣ ሳይጐድል ፣ እንዲጻፍ ፣ ወስነናል ።

ምሳሌ ፤ የመውደድ ፣ ግሥ ፣ ትንቢቱን ፣ ይወዳል ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ ይወድዳል ፣ ማለት ፤ የመፍሰስ ፣ ግሥ ፤ ትንቢቱን ፣ ይፈሳል ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ ይፈስላል ፣ ማለት ፣ የተሻለ ፣ ይሆናል ።

—207—

መድረሻው ፣ "ለ" የሆነ ፣ ግሥ ፣ በእርባታ ፣ ውስጥ ፣ በአንዳንድ ፣ ስፍራ ፣ ላይ ፣ የ ፣ የሚል ፣ ባዕድ ፣ መነሻን ፣ ሲያበጅ ፣ ይገኛል ፣ ይኸውም ፣ ነድያለሁ ፤ ትነድያለሽ ፤ ነድዬ ፣ " ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ።

መድረሻው ፣ ራብዕ ፣ የሆነ ፣ ግሥ ፣ በንኡስ ፣ አንቀጽ ፣ የ"ተ" ፊደል ፣ ይጨመርበታል ። ይኸውም ፣ መግበት ፣ መብላት ፣ ገብቶ ፣ በልቶ ፣ « ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ።

በመነሻ ፣ ተ ፣ የሚገኝበት ፣ ግሥ ፣ በአንዳንድ ፣ ስፍራ ፣ ላይ ፣ "ተ" ይዋጣል ። ይኸውም ፣ ይከተላል ፣ ይቀመጣል ፣ ይላል ፣ እንጂ ፣ ይትከተላል ፣ ይትቀመጣል ፣ አይልም ፣ ማለት ነው ። ይህ ፣ ውሳኔ ፣ ለመላው ፣ አይደለም ። "ተኖ ፣ ተለመ ፣ ተረጉመ" የሚባሉት ፣ ግሦች ፣ ይተኖል ፣ ይተለማል ፣ ይተረጉማል ፣ ሲያሰኙ ፣ ይገኛሉ ።

—208—

የግሥ ፣ እርባታ ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ በአንዳንዶቹ ፣ ላይ ፣ ጥቂት ፣ ጥቂት ፣ ልዩነት ፣ ቢኖረው ፣ መደቡ ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፣ ነው ።

እነሆ ፣ « መፈለግ ፣ የሚለውን ፣ ግሥ ፣ በሙሉ ፣ እርባታ ፣ በየዋህም ፣ በዝርዝርም ፣ እያረባን ፣ እንገልጻለን ። የዋህ ፣ እርባታ ፣ የምንለው ፣ እኔ ፣ አንተ ፣ . . . በሚያሰኘው ፣ የእርባታ ፣ መሪ ፣ እየተመራ ፣ በቀላሉ ፣ የሚረባው ፣ ነው ። ይኸውም ፣ እፈልጋለሁ ፣ ትፈልጋለህ ፣ . . . . . የሚለው ፣ ነው ። (ቁ. 209 ፣ አይ ፣) ዝርዝር ፣ እርባታ ፣ የሚባለውም ፣ እኔን ፣ አንተን ፣ . . የሚያሰኝ ፣ የተሰቢ ፣ አጸፋ ፣ በሚጨመርበት ፣ የእርባታ ፣ መሪ ፣ እየተመራ ፣ በሰፈው ፣ የሚገባ ፣ ረዘረመ ፣ ነው ። ይኸውም ፣ « እፈልገኛለሁ ፣ ይፈልገኛል ፣ . . . የሚለው ፣ ነው ። (ቁ. 210 ፣ አይ ።)

— 209 —

የግሥ ፡ መፈለግ ፡ የዋሀ ፡ እርባታ ፡

(ሀ) ዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡

1. ኅላፊ ፡ ጊዜያት ፡

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
የዋሀ ፡ ኅላፊ ።	፩— ፈለግሁ ፡	፩—ፈለግን ፡
	፪— ፈለግህ ፡ ፈለግሽ ፡	፪ —ፈለጋችሁ ፡
	፫— ፈለገ ፡ ፈለገች ፡	፫—ፈለጉ ፡
የቅርብ ፡ ኅላፊ ።	፩— ፈልጌአለሁ ፡	፩—ፈልገንአል ፡
	፪— ፈልገህአል ፡ ፈልገሽአል ፡	፪—ፈልጋችሁአል ፡
	፫— ፈልጎአል ፡ ፈልጋአለች ፡	፫—ፈልገውአል ፡

ማስገንዘቢያ ። አ ፡ ተውጠ ፡ ፈልገሃል ፡ ፈልገሻል ፡ . . . እየተባለም ፡ ይነገራል ።

የሩቅ ፡ ኅላፊ ።	፩— ፈልጌ ፡ ነበር ፡	፩—ፈልገን ፡ ነበር ፡
	፪— ፈልገህ ፡ ነበር ፡ ፈልገሽ ፡ ነበር ፡	፪—ፈልጋችሁ ፡ ነበር ፡
	፫— ፈልጎ ፡ ነበር ፡ ፈልጋ ፡ ነበር ፡	፫—ፈልገው ፡ ነበር ፡

2 የአውንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡

የቅርብ ።	፩— ልፈልግ ፡ ነው ፡	፩—ልንፈልግ ፡ ነው ፡
	፪— ልትፈልግ ፡ ነው ፡ ልትፈልጊ ፡ ነው ፡	፪—ልትፈጉ ፡ ነው ፡
	፫— ሊፈልግ ፡ ነው ፡ ልትፈልግ ፡ ነው ፡	፫—ሊፈልጉ ፡ ነው ፡
የዋሀ ።	፩— እፈልግለሁ ፡	፩—እንፈልግለን ፡
	፪— ትፈልግለህ ፡ ትፈልጊለሽ ፡	፪—ትፈልጋላችሁ ፡
	፫— ይፈልግለት ፡ ትፈልግለት ፡	፫—ይፈልጉ ፡

ማስገንዘቢያ ። (ሀ) አ ፡ ተውጠ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ትፈልጋለህ ፡ . . . እየተባለ ፡ ይነገራል ፡
(ለ) የጥርጥር ፡ ምግባር ፡ በሚነገርበት ፡ ጊዜያት ፡ እፈልግ ፡ ይሆናል ፡
ትፈልግ ፡ ይሆናል ፡ ትፈልጊ ፡ ይሆናል ፡ እያለ ፡ ይረባል ።

(ለ) ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ።

1. የአሁን ፡ ጊዜያት ፡

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡
	፩— ልፈልግ ፡	፩—እንፈልግ ፡
	፪— ፈልግ ፡ ፈልጊ ፡	፪—ፈልጉ ፡
	፫— ይፈልግ ፡ ትፈልግ ፡	፫—ይፈልጉ ፡

2. ትንቢታዊ ፡ ጊዜያት ።

	፩— እንድፈልግ ፡ ይሁን ፡	፩—እንድንፈልግ ፡ ይሁን ፡
	፪— እንድትፈልግ ፡ ይሁን እንድትፈልጊ ፡ ይሁን	፪—እንድትፈልጉ ፡ ይሁን ፡
	፫— እንዲፈልግ ፡ ይሁን ፡ እንድትፈልግ ፡ ይሁን	፫—እንዲፈልጉ ፡ ይሁን ፡

(ሐ) አዋዋይ ፡ አንቀጽ ።

፩ ፡ ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ።

1. ኅላፊ ፡ ጊዜያት ፡

የዋሀ ፡ ኅላፊ	፩— ብፈልግ ፡ ኖሮ ፡	፩—ብንፈልግ ፡ ኖሮ ፡
	፪— ብትፈልግ ፡ ኖሮ ፡ ብትፈልጊ ፡ ኖሮ ፡	፪—ብትፈልጉ ፡ ኖሮ ፡
	፫— ቢፈልግ ፡ ኖሮ ፡ ብትፈልግ ፡ ኖሮ ፡	፫—ቢፈልጉ ፡ ኖሮ ፡

ማስገንዘቢያ ፡ «ኖሮ» ፡ የሚለው ፡ ረዳቱ ፡ ግሥ ፡ ቀርቶ ፡ ብቻውንም ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ «ብፈልግ ፡ ብትፈልግ ፡ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።
በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ክፍሉ ፡ ከትንቢታዊ ፡ ጊዜያት ፡ ይሆናል ።

የሩቅ ፡ ኅላፊ	፩—ፈልጌ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡	፩—ፈልገን ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡
	፪— ፈልገህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፈልገሽ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ	፪—ፈልጋችሁ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡
	፫— ፈልጎ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ፈልጋ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ	፫—ፈልገው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡

(ሐ) አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ (ለጣቂ ፡)

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

		ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ውለተኛ ፡	፩ —	እፈልግ ፡ ዘንድ ፡	፩ — እንፈልግ ፡ ዘንድ ፡
	፪ —	ትፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ትፈልጊ ፡ ዘንድ ፡	፪ — ትፈልጉ ፡ ዘንድ ፡
	፫ —	ይፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ትፈልግ ፡ ዘንድ ፡	፫ — ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡
ምክንያተኛ ፡	፩ —	እንዲፈልግ ፡	፩ — እንድንፈልግ ፡
	፪ —	እንድትፈልግ ፡ እንድትፈልጊ ፡	፪ — እንድትፈልጉ ፡
	፫ —	እንዲፈልግ ፡ እንድትፈልግ ፡	፫ — እንዲፈልጉ ፡

ማስገንዘቢያ ፡ «እንደ ፡ »በማለት ፡ ፈንታ ፡ «ለ»የሚል ፡ ቃል ፡ እየተጨመረ ፡ እንደዚያው ፡ ይረባል ። ይኸውም ፡ «ልፈልግ ፡ ልትፈልግ ፡ ልትፈልጊ ፡ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪ ፡ — ኮምኣታዊ ፡ አዋዋይ ፡

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ።

ጸጸት ፡	፩ —	በፈለግሁ ፡ ነበር ፡	፩— በፈለግን ፡ ነበር ፡
ወይም ፡ ምኞት ፡	፪ —	በፈለግህ ፡ ነበር ፡ በፈለግሽ ፡ ነበር ፡	፪ — በፈለጋችሁ ፡ ነበር ፡
	፫ —	በፈለገ ፡ ነበር ፡ በፈለገች ፡ ነበር ፡	፫ — በፈለጉ ፡ ነበር ፡

2. ፡ የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

ጸጸት ፡	፩ —	እፈልግ ፡ ነበር ፡	፩ — እንፈልግ ፡ ነበር ፡
ወይም ፡ ምኞት ፡	፪ —	ትፈልግ ፡ ነበር ፡ ትፈልጊ ፡ ነበር ፡	፪ — ትፈልጉ ፡ ነበር ፡
	፫ —	ይፈልግ ፡ ነበር ፡ ትፈልግ ፡ ነበር ፡	፫ — ይፈልጉ ፡ ነበር ፡

ማስገንዘቢያ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ «ነበር» ፡ የሚለውም ፡ ሳያጨመርበት ፡ «በፈለግሁ ፡ በፈለግህ ፡ . . . እያለ ፡ ይረባል ። ይኸውም ፡ በጎላፊ ፡ ወይም ፡ በትንቢት ፡ ጊዜያት ፡ እየገባ ፡ ጸጸትንና ፡ ምኞትን ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

(መ) ንኡስ ፡ አንቀጽ ።

አርእስት ።

መፈለግ ።

በዝ ፡ አንቀጽ ።

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት

		ነጠላ ፡	ብዙ ፡
	፩ —	ፈልጌ —	፩ — ፈልገን —
	፪ —	ፈልገህ — ፈልገሽ —	፪ — ፈልጋችሁ —
	፫ —	ፈለገ — ፈለጋ —	፫ — ፈልገው ፡

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

	፩ —	እፈልግ —	፩— እንፈልግ —
	፪ —	ትፈልግ — ትፈልጊ —	፪ — ትፈልጉ —
	፫ —	ይፈልግ — ትፈልግ —	፫ — ይፈልጉ —

ግሣዊ ፡ ቅጽል ።

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ።

	፩ —	የፈለግሁ ፡	፩ — የፈለግን ፡
	፪ —	የፈለግህ ፡ የፈለግሽ ፡	፪ — የፈለጋችሁ ፡
	፫ —	የፈለገ ፡ የፈለገች ፡	፫ — የፈለጉ ፡

ማስገንዘቢያ ። የሩቅ ፡ ጎላፊ ፡ ሲሆን ፡ «ፈልጌ ፡ የነበር ፡ ፈልገህ ፡ የነበር ፡ እያለ ፡ ይረባል ፡

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

	፩ —	የምፈልግ	፩ የምንፈልግ ፡
	፪ —	የምትፈልግ ፡ የምትፈልጊ ፡	፪ — የምትፈልጉ ፡
	፫ —	የሚፈልግ ፡ የምትፈልግ ፡	፫ — የሚፈልጉ ፡

(መ) ንአ·ስ ፡ አንቀጽ ። (ለጣቂ ፡)

ው·ስጠ ፡ የ ፡

ነጠላ ፡	ብዙ ፡
መፈለጊያ ፡	መፈለጊያዎች ፡

ዘርና ፡ ሰበ.ዘር ፡

ፍ·ለጋ ፡	ፍ·ለጋዎች ፡
ፍ·ላጎት ፡	ፍ·ላጎቶች ፡
አፈላለግ ፡	አፈላለጎች ፡

የግሥ ፡ መፈለግ ፡ ዝርዝር ፡ እርባታ ።

የአማርኛ ፡ ሰዋስው ፡ ዝርዝር ፡ እርባታው ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቁ. 209 ፡ በየቀሀ ፡ እርባታ ፡ የጸናናቸው ፡ ቃላት ፡ እንደገና ፡ ዝርዝር ፡ አጸፋ ፡ እየ ተዉ·መረባቸው ፡ ይረዳሉ ። ይህንኑም ፡ በወረፍተ ፡ ነገር ፡ እየሞላን ፡ ለማስረዳት ፡ ስንል ፡ ተውላጠ ፡ ስሞችን ፡ ባለቤትና ፡ ተሳቢ ፡ እያደረግን ፡ ጽፈናል ፡ ። ፡ ቁ .211 ፡ እይ ።

የ ፡ አ ፡ ፊደል ፡ ድምፁን ፡ ለተከታዩ ፡ አውርሶ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ እንደሚታጣ ፡ በየስፍራው ፡ ተናግረናል ። ስለዚህም ፡ በሚከተለው ፡ እርባታ ፡ በእንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ «አ» እየተዋጠ ፡ መጻፉን ፡ አስተውል ። ይኸውም ፡ «እፈልጋቸውአለሁ» ሊባል ፡ የሚገባው ፡ ቃል ፡ እፈልጋቸዋለሁ ። እየተባለ ፡ ተጽፎአል ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አ ፡ ሳይዋጥ ፡ ቢጻፍም ፡ ሥረ ፡ ነገሩ ፡ እንዲሁ ፡ ነውና ፡ ጸያፍ ፡ አያሰኝም ።

የ ፡ ሀ ፡ ፊደል ፡ የግዕዝነት ፡ ድምፁ ፡ በልግድ ፡ ጠፍቶ ፡ እንደቀረ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ተናግረናል ። (ተ ፡ ቁ ፡ 172 እይ ።) ስለዚህም ፡ የእርባታ ፡ መሪው ፡ ሀ ፡ ግዕዝ ፡ አናጋሪ ፡ ድምፅ ፡ ብተከተለው ፡ ጊዜ ፡ ኸ ፡ ወደመሆን ፡ ይለወጣል ። ይኸውም ፡ «ፈለግህ ፡ » የ°ፈ ለው ፡ ቃል ፡ ሲዘረዘር ፡ «ፈለግኸኝ ፡ ፈለግኸው ፡ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

— 211 —

ግ ር ፃ ር ፡ እ ር ባ ታ ው ።

ባለቤት ፡ ተ.ስ.	ተሳቢ ፡ ተ.ስ.	ዐ ቢ ይ ፡ አ ን ቀ ጽ ። ጎ ላ ፊ ፡ ጊ ዜ ያ ት ፡ የቀሀ ፡ ጎላፊ ፡	የቅርብ ፡ ጎላፊ ፡	የሩቅ ፡ ጎላፊ ፡	የአውንና ፡ የትጉዚት ፡ ጊዜያት ፡	ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ የአሁን ፡ ጊዜያት ፡
እኔ ፡	እኔን ፡	—	—	—	—	—
	አንተን ፡	ፈለግሁህ ፡	ፈልጌህ ፡	ፈልጌህ ፡ ነበር ፡	እፈልግሃለሁ ፡	ልፈልግህ ፡
	አንቺን ፡	ፈለግሁሽ ፡	ፈልጌሽ ፡	ፈልጌሽ ፡ ነበር ፡	እፈልግሻለሁ ፡	ልፈልግሽ ፡
	እርሱን ፡	ፈለግሁት ፡	ፈልጌው ፡	ፈልጌው ፡ ነበር ፡	እፈልገዋለሁ ፡	ልፈልገው ፡
	እርሶን ፡	ፈለግኋት ፡	ፈልጌአለሁ ፡	ፈልጌአት ፡ ነበር ፡	እፈልጋታለሁ ፡	ልፈልጋት ፡
	እኛን ፡	—	—	—	—	—
	እናንተን ፡	ፈለግኋችሁ ፡	ፈልጌአችኋለሁ ፡	ፈልጌአችሁ ፡ ነበር ፡	እፈልጋችኋለሁ ፡	ልፈልጋችሁ ፡
	እነርሱን ፡	ፈለግኋቸው ፡	ፈልጌአቸዋለሁ ፡	ፈልጌአቸው ፡ ነበር ፡	እፈልጋቸዋለሁ ፡	ልፈልጋቸው ፡
አንተ ፡	እኔን ፡	ፈለግኸኝ ፡	ፈልገኸኛል ፡	ፈልገኸኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልገኛለህ ፡	ፈልገኝ ፡
	አንተን ፡	—	—	—	—	—
	አንቺን ፡	—	—	—	—	—
	እርሱን ፡	ፈልገኸው ፡	ፈልገኸዋል ፡	ፈልገኸው ፡ ነበር ፡	ትፈልገዋለህ ፡	ፈልገው ፡
	እርሶን ፡	ፈለግኸት ፡	ፈልገሃታል ፡	ፈልገሃት ፡ ነበር ፡	ትፈልጋታለህ ፡	ፈልጋት ፡
	እኛን ፡	ፈለግኸን ፡	ፈልገኸናል ፡	ፈልገኸን ፡ ነበር ፡	ትፈልገናለህ ፡	ፈልገን ፡
	እናንተን ፡	—	—	—	—	—
	እነርሱን ፡	ፈለግሃቸው ፡	ፈልጋቸዋል ፡	ፈልጋቸው ፡ ነበር ፡	ትፈልጋቸዋለህ ፡	ፈልጋቸው ፡
አንቺ ፡	እኔን ፡	ፈለግሽኝ ፡	ፈልገሽኛል ፡	ፈልገሽኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልጊኛለሽ ፡	ፈልጊኝ ፡
	አንተን ፡	—	—	—	—	—
	አንቺን ፡	—	—	—	—	—
	እርሱን ፡	ፈለግሽው ፡	ፈልገሽዋል	ፈልገሽው ፡ ነበር ፡	ትፈልጊዋለሽ ፡	ፈልጊው ፡
	እርሶን ፡	ፈለግሽት ፡	ፈልገሻታል ፡	ፈልገሻት ፡ ነበር ፡	ትፈልጊአታለሽ ፡	ፈልጊአት ፡
	እኛን ፡	ፈለግሽን ፡	ፈልገሽናል ፡	ፈልገሽን ፡ ነበር ፡	ትፈልጊናለሽ ፡	ፈልጊን ፡
	እናንተን ፡	—	—	—	—	—
	እነርሱን ፡	ፈለግሻቸው ፡	ፈልገዋቸዋል ፡	ፈልገሻቸው ፡ ነበር ፡	ትፈልጊአቸዋለሽ ፡	ፈልጊአቸው ፡
እርሱ ፡	እኔን ፡	ፈለገኝ ፡	ፈልጎኛል ፡	ፈልጎኝ ፡ ነበር ፡	ይፈልገኛል ፡	ይፈልገኝ ፡
	አንተን ፡	ፈለገህ ፡	ፈልጎሃል ፡	ፈልጎህ ፡ ነበር ፡	ይፈልግሃል ፡	ይፈልግህ ፡
	አንቺን ፡	ፈለገሽ ፡	ፈልጎሻል ፡	ፈልጎሽ ፡ ነበር ፡	ይፈልግሻል ፡	ይፈልግሽ ፡
	እርሱን ፡	ፈለገው ፡	ፈልጎታል ፡	ፈልጎት ፡ ነበር ፡	ይፈልገዋል ፡	ይፈልገው ፡
	እርሶን ፡	ፈለጋት ፡	ፈልጋታል ፡	ፈልጋት ፡ ነበር ፡	ይፈልጋታል ፡	ይፈልጋት ፡
	እኛን ፡	ፈለገን ፡	ፈልጎናል ፡	ፈልጎን ፡ ነበር ፡	ይፈልገናል ፡	ይፈልገን ፡
	እናንተን ፡	ፈለጋችሁ ፡	ፈልጎችኋል ፡	ፈልጎችሁ ፡ ነበር ፡	ይፈልጋችኋል ፡	ይፈልጋችሁ ፡
	እነርሱን ፡	ፈለጋቸው ፡	ፈልጎቸዋል ፡	ፈልጎቸው ፡ ነበር ፡	ይፈልጋቸዋል ፡	ይፈልጋቸው ፡

ባለቤት፡ ተ. ቁ.	ቁ ሳቢ ፡ ተ . ቁ.	ፀዲይ ፡ አንቀጽ ፡ (ስማቂ ፡)				
		ጎ ሳ ፌ ፡ ጊ ዜ ያ ት ፡			የአውንና፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡	ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡
		የዋህ ፡ ጎላፊ ፡	የቅርብ ፡ ጎላፊ ፡	የሩቅ ፡ ጎላፊ ፡		የአውንኚዜያት ፡
እርዳዋ፡	እኔን ፡	ፈለገኞኝ ፡	ፈልጋዎልኞ ፡	ፈልጋኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልገኛለኞ ፡	ትፈልጊኝ ፡
	አንተን ፡	ፈለገችህ ፡	ፈልጋማለች ፡	ፈልጋህ ፡ ነበር ፡	ትፈልጊሃለች ፡	ትፈልግህ ፡
	አንቺን ፡	ፈለገችሽ ፡	ፈልጋሽለች ፡	ፈልጋሽ ፡ ነበር ፡	ትፈልጊሻለች ፡	ትፈልግሽ ፡
	እርሱን ፡	ፈለገችው ፡	ፈልጋዋለች ፡	ፈልጋው ፡ ነበር ፡	ትፈልጊዋለች ፡	ትፈልገው ፡
	እርስዋን ፡	ፈለገቻት ፡	ፈልጋታለች ፡	ፈልጋት ፡ ነበር ፡	ትፈልጋታለች ፡	ትፈልጋት ፡
	እኛን ፡	ፈለገችን ፡	ፈልጋናለች ፡	ፈልጋን ፡ ነበር ፡	ትፈልጋናለች ፡	ትፈልገን ፡
	እናንተን ፡	ፈለገቻችሁ ፡	ፈልጋችሁአለች ፡	ፈልጋችሁ ፡ ነበር ፡	ትፈልጋችሁአለች ፡	ትፈልጋችሁ ፡
	እነርሱን ፡	ፈለገቻቸው ፡	ፈልጋቸዋለች ፡	ፈልጋቸው ፡ ነበር ፡	ትፈልጋቸዋለች ፡	ትፈልጋቸው ፡
እኛ ፡	እኔን ፡	—	—	—	—	—
	አንተን ፡	ፈለግህ ፡	ፈልገንሃል ፡	ፈልገህ ፡ ነበር ፡	እንፈልግሃለን ፡	እንፈልግ ፡
	አንቺን ፡	ፈለግሽ ፡	ፈልገንሻል ፡	ፈልገሽ ፡ ነበር ፡	እንፈልግሻለን ፡	እንፈልጊ ፡
	እርሱን ፡	ፈለግነው ፡	ፈልገነዋል ፡	ፈልገነው ፡ ነበር ፡	እንፈልገዋለን ፡	እንፈልገው ፡
	እርስዋን ፡	ፈለግናት ፡	ፈልገናታል ፡	ፈልገናት ፡ ነበር ፡	እንፈልጋታለን ፡	እንፈልጋት ፡
	እኛን ፡	—	—	—	—	—
	እናንተን ፡	ፈለግናችሁ ፡	ፈልገናችሁአል ፡	ፈልገናችሁ ፡ ነበር ፡	እንፈልጋችሁአለን	እንይልጋችሁ ፡
	እነርሱን ፡	ፈለግናቸው ፡	ፈልገናቸዋል ፡	ፈልገናቸው ፡ ነበር ፡	እንፈል ነዋቸዋለን ፡	እንፈልጋቸው ፡
እናንተ፡	እኔን ፡	ፈለጋችሁኝ ፡	ፈልጋችሁኛል ፡	ፈልጋችሁኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልጉኛላችሁ ፡	ፈልጉኝ ፡
	አንተን ፡	—	—	—	—	—
	አንቺን ፡	—	—	—	—	—
	እርሱን ፡	ፈለጋችሁት ፡	ፈልጋችውታል ፡	ፈልጋችሁት ፡ ነበር ፡	ትፈልጉታላችሁ ፡	ፈልጉት ፡
	እርስዋን ፡	ፈለጋችሁአት ፡	ፈልጋችኋታል ፡	ፈልጋችኋት ፡ ነበር ፡	ትፈልጉታላችሁ ፡	ፈልጉት ፡
	እኛን ፡	ፈለጋችሁን ፡	ፈልጋችሁናል ፡	ፈልጋችሁን ፡ ነበር ፡	ትፈልጉናላችሁ ፡	ፈልጉን ፡
	እናንተን ፡	—	—	—	—	—
	እነርሱን ፡	ፈለጋችሁአቸው ፡	ፈልጋችኋቸዋል ፡	ፈልጋችኋቸውነበር ፡	ትፈልጓቸዋላችሁ ፡	ፈልጓቸው ፡
እነርሱ፡	እኔን ፡	ፈለጉኝ ፡	ፈልገውኛል ፡	ፈልገውኝ ፡ ነበር ፡	ይፈልጉኛል ፡	ይፈልጉኝ ፡
	አንተን ፡	ፈለጉህ ፡	ፈልገውሃል ፡	ፈልገውህ ፡ ነበር ፡	ይፈልጉሃል ፡	ይፈልጉህ ፡
	አንቺን ፡	ፈለጉሽ ፡	ፈልገውሻል ፡	ፈልገውሽ ፡ ነበር ፡	ይፈልጉሻል ፡	ይፈልጉሽ ፡
	እርሱን ፡	ፈለጉት ፡	ፈልገውታል ፡	ፈልገውት ፡ ነበር ፡	ይፈልጉታል ፡	ይፈልጉት ፡
	እርስዋን ፡	ፈለጓት ፡	ፈልገዋታል ፡	ፈልገዋት ፡ ነበር ፡	ይፈልጓታል ፡	ይፈልጓት ፡
	እኛን ፡	ፈለጉን ፡	ፈልገውናል ፡	ፈልገውን ፡ ነበር ፡	ይፈልጉናል ፡	ይፈልጉን ፡
	እናንተን ፡	ፈለግችው ፡	ፈልገዋችኋል ፡	ፈልገዋችው ፡ ነበር ፡	ይፈልጓችኋል ፡	ይፈልጓችው ፡
	እነርሱን ፡	ፈለጓቸው ፡	ፈልገዋቸዋል ፡	ፈልገዋቸው ፡ ነበር ፡	ይፈልጓቸዋል ፡	ይፈልጓቸው ፡

ባለቤት፡ ተ. ቁ.	ተሳቢ ፡ ተ. ቁ.	(ሐ) አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡				
		ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡			ተምኔታዊ ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡	
		ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡	የአውንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡		ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡	የአውንና ፡ የትን ቢት ፡ ጊዜያት ፡
እኔ ፡	እኔን ፡	—	—	—	—	—
	አንተን ፡	ብፈለግህ ፡ ኖሮ ፡	እፈልግህ ፡ ዘንድ ፡	እንድፈልግህ ፡	በፈለግሁህ ፡ ነበር ፡	እፈልግህ ፡ ነበር ፡
	አንቺን ፡	ብፈለግሽ ፡ ኖሮ ፡	እፈልግሽ ፡ ዘንድ ፡	እንድፈልግሽ ፡	በፈለግሁሽ ፡ ነበር ፡	እፈልግሽ ፡ ነበር ፡
	እርሱን ፡	ብፈለገው ፡ ኖሮ ፡	እፈልገው ፡ ዘንድ ፡	እንድፈልገው ፡	በፈለግሁት ፡ ነበር ፡	እፈልገው ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	ብፈለጋት ፡ ኖሮ ፡	እፈልጋት ፡ ዘንድ ፡	እንድፈልጋት ፡	በፈለግኋት ፡ ነበር ፡	እፈልጋት ፡ ነበር ፡
	እኛን ፡	—	—	—	—	—
	እናንተን ፡	ብፈለጋችሁ ፡ ኖሮ ፡	እፈልጋችሁ ፡ ዘንድ ፡	እንድፈልጋችሁ ፡	በፈለግኋችሁ ፡ ነበር ፡	እፈልጋችሁ ፡ ነበር ፡
	እነርሱን ፡	ብፈለጋቸው ፡ ኖሮ ፡	እፈልጋቸው ፡ ዘንድ ፡	እንድፈልጋቸው ፡	በፈለግኋቸው ፡ ነበር ፡	እፈልጋቸው ፡ ነበር ፡
እኛ ፡	እኔን ፡	ብትፈልገኝ ፡ ኖሮ ፡	ትፈልገኝ ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልገኝ ፡	ፈፈለግህኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልገኝ ፡ ነበር ፡
	አንተን ፡	—	—	—	—	—
	አንቺን ፡	—	—	—	—	—
	እርሱን ፡	ብትፈልገው ፡ ኖሮ ፡	ትፈልገው ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልገው ፡	ፈፈለግኸው ፡ ነበር ፡	ትፈልገው ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	ብትፈልጋት ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጋት ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጋት ፡	ፈፈለግኻት ፡ ነበር ፡	ትፈልጋት ፡ ነበር ፡
	እኛን ፡	ብትፈልገን ፡ ኖሮ ፡	ትፈልገን ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልገን ፡	ፈፈለግኸን ፡ ነበር ፡	ትፈልገን ፡ ነበር ፡
	እናንተን ፡	—	—	—	—	—
	እነርሱን ፡	ብትፈልጋቸው ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጋቸው ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጋቸው ፡	ፈፈለግኻቸው ፡ ነበር ፡	ትፈልጋቸው ፡ ነበር ፡
እናንተ፡	እኔን ፡	ብትፈልጊኝ ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጊኝ ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጊኝ ፡	በፈለግሽኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልጊኝ ፡ ነበር ፡
	አንተን ፡	—	—	—	—	—
	አንቺን ፡	—	—	—	—	—
	እርሱን ፡	ብትፈልጊው ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጊው ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጊው ፡	በፈለግሽው ፡ ነበር ፡	ትፈልጊው ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	ብትፈልጊአት ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጊአት ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጊአት ፡ እንድትፈልጊን ፡	በፈለግሽት ፡ ነበር ፡	ትፈልጊአት ፡ ነበር ፡
	እኛን ፡	ብትፈልጊን ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጊን ፡ ዘንድ ፡		በፈለግሽን ፡ ነበር ፡	ትፈልጊን ፡ ነበር ፡
	እናንተን ፡	—	—	—	—	—
	እነርሱን ፡	ብትፈልጊአቸው ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጊአቸው ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጊ አቸው ፡	በፈለግሽቸው ፡ ነበር ፡	ትፈልጊአቸው ፡ ነበር ፡
እርሱ፡	እኔን ፡	በፈለገኝ ፡ ኖሮ ፡	ይፈልገኝ ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልገኝ ፡	በፈለገኝ ፡ ነበር ፡	ይፈልገኝ ፡ ነበር ፡
	አንተን ፡	በፈለገህ ፡ ኖሮ ፡	ይፈልገህ ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልገህ ፡	በፈለገህ ፡ ነበር ፡	ይፈልገህ ፡ ነበር ፡
	አንቺን ፡	በፈለገሽ ፡ ኖሮ ፡	ይፈልገሽ ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልገሽ ፡	በፈለገሽ ፡ ነበር ፡	ይፈልገሽ ፡ ነበር ፡
	እርሱን ፡	በፈለገው ፡ ኖሮ ፡	ይፈልገው ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልገው ፡	በፈለገው ፡ ነበር ፡	ይፈልገው ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	በፈለጋት ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጋት ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጋት ፡	ሥፈለጋት ፡ ነበር ፡	ይፈልጋት ፡ ነበር ፡
	እኛን ፡	በፈለገን ፡ ኖሮ ፡	ይፈልገን ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልገን ፡	በፈለገኝ ፡ ነበር ፡	ይፈልገን ፡ ነበር ፡
	እናንተን ፡	በፈለጋችው ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጋችው ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጋችው ፡	በፈለጋችው ፡ ነበር ፡	ይፈልጋችው ፡ ነበር ፡
	እነርሱን ፡	በፈለጋቸው ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጋቸው ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጋቸው ፡	በፈለጋቸው ፡ ነበር ፡	ይፈልጋቸው ፡ ነበር ፡

ባለቤት፡ ተ. ፱.	ተሳቢ፡ ተ. ሰ.	አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰጣቂ ፡)				
		ምክንያታዊ ፡			ተምኔታዊ ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡	
		ኀላፊ ፡ ጊዜያት ፡	የአውንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡		ኀላፊ ፡ ጊዜያት ፡	የአውንና ፡ የትንቢት ፡
እርስዮ፡	እኔን ፡	ብትፈልገኝ ፡ ኖሮ ፡	ትፈልገኝ ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልገኝ ፡	በፈለገችኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልገኝ ፡ ነበር ፡
	አንተን ፡	ብትፈልግህ ፡ ኖሮ ፡	ትፈልግህ ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልግህ ፡	በፈለገችህ ፡ ነበር ፡	ትፈልግህ ፡ ነበር ፡
	አንቺን ፡	ብትፈልግሽ ፡ ኖሮ ፡	ትፈልግሽ ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልግሽ ፡	በፈለገችሽ ፡ ነበር ፡	ትፈልግሽ ፡ ነበር ፡
	እርሱን ፡	ቢትፈልገው ፡ ኖሮ ፡	ትፈልገው ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልገው ፡	በፈለገችው ፡ ነበር ፡	ትፈልጌው ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	ብትፈልጋት ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጋት ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጋት ፡	በፈለገቻት ፡ ነበር ፡	ትፈልጋት ፡ ነበር ፡
	እኛን ፡	ብትፈልገን ፡ ኖሮ ፡	ትፈልገን ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልገን ፡	በፈለገችን ፡ ነበር ፡	ትፈልገን ፡ ነበር ፡
	እናንተን ፡	ብትፈልጋችሁ ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጋችሁ ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጋችሁ ፡	በፈለገቻችሁ ፡ ነበር ፡	ትፈልጋችሁ ፡ ነበር ፡
	እነርሱን ፡	ቢትፈልጋቸው ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጋቸው ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጋቸው ፡	በፈለገቻቸው ፡ ነበር ፡	ትፈልጋቸው ፡ ነበር ፡
እኛ ፡	እኔን ፡	—	—	—	—	—
	አንተን ፡	ብንፈልግህ ፡ ኖሮ ፡	እንፈልግህ ፡ ዘንድ ፡	እንድንፈልግህ ፡	በፈለግንህ ፡ ነበር ፡	እንፈልግህ ፡ ነበር ፡
	አንቺን ፡	ብንፈልግሽ ፡ ኖሮ ፡	እንፈልግሽ ፡ ዘንድ ፡	እንድንፈልግሽ ፡	በፈለግንሽ ፡ ነበር ፡	እንፈልግሽ ፡ ነበር ፡
	እርሱን ፡	ብንፈልገው ፡ ኖሮ ፡	እንፈልገው ፡ ዘንድ ፡	እንድንፈልገው ፡	በፈለግነው ፡ ነበር ፡	እን ፈልጋት ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	ብንፈልጋት ፡ ኖሮ ፡	እንፈልጋት ፡ ዘንድ ፡	እንድንፈልጋት ፡	በፈለግናት ፡ ነበር ፡	—
	እኛን ፡	—	—	—	—	እንፈልጋችሁ ፡ ነበር ፡
	እናንተን ፡	ብንፈልጋችሁ ፡ ኖሮ ፡	እንፈልጋችሁ ፡ ዘንድ ፡	እንድንፈልጋችሁ ፡	በፈላግናችሁ ፡ ነበር ፡	እንፈልጋችሁ ፡ ነበር ፡
	እነርሱን ፡	ብንፈልጋቸው ፡ ኖሮ ፡	እንፈልጋቸው ፡ ዘንድ ፡	እንድንፈልጋቸው ፡	በፈለግናቸው ፡ ነበር ፡	
እናንተ ፡	እኔን ፡	ቢትፈልጉኝ ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጉኝ ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጉኝ ፡	በፈለጋችሁኝ ፡ ነበር ፡	ትፈልጉኝ ፡ ነበር ፡
	አንተን ፡	—	—	—	—	—
	አንቺን ፡	—	—	—	—	—
	እርሱን ፡	ብትፈልጉት ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጉት ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጉት ፡	በፈለጋችሁት ፡ ነበር ፡	ትፈልጉት ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	ብትፈልጓት ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጓት ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጓት ፡	በፈለጋችኋት ፡ ነበር ፡	ትፈልጓት ፡ ነበር ፡
	እኛን ፡	ብትፈልጉን ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጉን ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጉን ፡	በፈለጋችሁን ፡ ነበር ፡	ትፈልጉን ፡ ነበር ፡
	እናንተን ፡	—	—	—	—	—
	እነርሱን ፡	ብትፈልጓቸው ፡ ኖሮ ፡	ትፈልጓቸው ፡ ዘንድ ፡	እንድትፈልጓቸው ፡	በፈለጋችኋቸው ፡ ነበር ፡	ትፈልጓቸው ፡ ነበር ፡
እነርሱ ፡	እኔን ፡	ቢፈልጉኝ ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጉኝ ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጉኝ ፡	በፈለጉኝ ፡ ነበር ፡	ይፈልጉኝ ፡ ነበር ፡
	አንተን ፡	ቢፈልጉህ ፡ ኖሮ ፡	ያፈልጉህ ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጉህ ፡	በፈለጉህ ፡ ነበር ፡	ይፈልጉህ ፡ ነበር ፡
	አንቺን ፡	ቢፈልጉሽ ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጉሽ ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጉሽ ፡	በፈለጉሽ ፡ ነበር ፡	ይፈልጉሽ ፡ ነበር ፡
	እርሱን ፡	ቢፈልጉት ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጉት ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጉት ፡	በፈለጉት ፡ ነበር ፡	ይፈልጉት ፡ ነበር ፡
	እርስዋን ፡	ቢፈልጓት ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጓት ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጓት ፡	በፈለጓት ፡ ነበር ፡	ይፈልጓት ፡ ነበር ፡
	እኛን ፡	ቢፈልጉን ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጉን ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጉን ፡	በፈለጉን ፡ ነበር ፡	ይፈልጉን ፡ ነበር ፡
	እናንተን ፡	ቢፈልጓችሁ ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጓችሁ ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጓችሁ ፡	በፈለጓችሁ ፡ ነበር ፡	ይፈልጓችሁ ፡ ነበር ፡
	እነርሱን ፡	ቢፈልጓቸው ፡ ኖሮ ፡	ይፈልጓቸው ፡ ዘንድ ፡	እንዲፈልጓቸው ፡	በፈለጓቸው ፡ ነበር ፡	ይፈልጓቸው ፡ ነበር ፡

ማስገንዘቢያ ፡ ምክንያታዊ ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ በጎላፊው ፡ ጊዜያት ፡ «ኖር ፡ » የሚለው ፡ ረዳቱ ፡ ግሥ ፡ ሰያጨመርበትም ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ ብፈልግህ ፡ ብፈል ግሽ ፡ . . . እያለ ፡ ይረባል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ «እንደ ፡ » በሚለውም ፡ ፈንታ ፡ « ለ » ተተ ክቶ ፡ እንደዚያው ፡ ይረባል ። ይኸውም ፡ ልፈልግህ ፡ ልፈልግሽ ፡ ይሳል ፡ ማለት ፡ ነው ።

(መ) ንኡስ ፡ አንቀጽ ።

ከንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ክፍል ፡ በዝ ፡ አንቀጽ ፡ እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ ዝርዝር ፡ እር ባታ ፡ አለው ፡ (ቁ ፡ 181—185 እይ ፡) ግሣዊ ፡ ቅጽልም ፡ እንደዚሁ ፡ በዝርዝር ፡ እር ባታ ፡ ይረባል ።

አርእስት ፡ ግን ፡ የነገር ፡ ስም ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በአገናዛቢ ፡ አጸፋ ፡ ብቻ ፡ ይዘረዘራል ። ይኸውም ፡ መፈለጌ ፡ መፈለግህ ፡ መፈለግሽ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ቁ. 179— 180 ፡ እይ)

— 212 —

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በየዋሀና ፡ በዝርዝር ፡ እርባታ ፡ የተጻፈው ፡ ግሥ ፡ «መፈለግ ፡ » ሕገኛ ፡ ይባላል ። እንደ ፡ እርሱ ፡ ሆነው ፡ ወይም ፡ ከዋቂት ፡ ጥቂት ፡ ልዩነት ፡ በቀር ፡ እር ሱን ፡ መስለው ፡ የሚረቡ ፡ ግሦችም ፡ ሕገኞች ፡ ይባላሉ ። በእርሱ ፡ አከሄድ ፡ ለመርዳት ፡ የማይችሉ ፡ ግሦች ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ወጦች ፡ ይባላሉ ።

— 213 —

ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆኑ ፡ ግሦች ፡ በአራት ፡ አከሄድ ፡ ይለያሉ ።

(ሀ) በአዕማድ ፡ ላይ ፡ ቃላቸውን ፡ ይለውጣሉ ።

(ለ) በንኡስ ፡ አንቀጻቸው ፡ ላይ ፡ በዕድ ፡ ፊደልን ፡ ያመጣሉ ።

(ሐ) በወገ ፡ አንቀጻቸው ፡ ላይ ፡ ፊደላቸውን ፡ ይለውጣሉ ፡ ወይም ፡ ያጕድሳሉ ።

(መ) በእርባታ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ቃልን ፡ ይወልዳሉ ።

— 214 —

በአዕማድ ፡ ላይ ፡ ቃላቸውን ፡ የሚለውጡ ፡ ግሦች ፡ ብዙዎች ፡ አይደሉም ። ከእ ኦሉም ፡ ላይ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

ምሳሌ ፡ « አለ ፡ » ሳልቶ ፡ ሲነገር ፡ ተመሆንን ፡ ምግበር ፡ እየገለጸ ፡ በተደራጊነት ፡ ወምድ ፡ የግሥ ፡ ረዳት ፡ ይሆናል ። የእርሱ ፡ አስደራጊ ፡ « አሰኘ ፡ » ይላል ። እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ « ሆነ ፡ » ተደራጊ ፡ ወምድ ፡ ነው ። የእርሱ ፡ አድራጊ ፡ ዓአደረገ ፡ » የሚሰው ፡ ግሥ ፡ ስለሆነ ፡ አዲስ ፡ ቃል ፡ መገኘቱን ፡ አስተውል ።

አድ ፡ ዝም ፡ አለ ፡ ዝም ፡ አሰኘ ፡ ድል ፡ ሆነ ፡ ድል ፡ አደረገ ፡ እያለ ፡ ይረባል ።

— 215 —

በንኡስ ፡ አንቀጻቸው ፡ ላይ ፡ በዕድ ፡ ፈደልን ፡ የሚያመጡ ፡ ግሦች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። በአዕማድ ፡ ደንቡ ፡ መድረሻው ፡ ራብዕ ፡ የሆነ ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ በንኡስ ፡ አንቀጹ ፡ የ-ተ ፡ ፈደል ፡ ይገኝበታል ። መድረሻው ፡ ግዕዝ ፡ የሆነ ፡ አንዳንድ ፡ ግሦም ፡ እንደዚሁ ፡ ሲሆን ፡ ይገኛል ።

እጅ ፡ «ገበ ፤ በላ ፤ ቀረ ፤ ቄየ ፤ » የሚለው ፡ የግሥ ፡ ዐምድ ፡ በአርእስት ፡ «መግ ብት ፡ መብላት ፡ መቅረት ፡ መቄየት ፤ » በጎላፈ ፡ በዙ ፡ «ንብቶ ፤ በልቶ ፤ ቀርቶ ፤ ቄይቶ ፤ » ይላል ። እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ መነሻው ፡ ተ ፡ ያሆነ ፡ አንዳንድ ፡ የግሥ ፡ ዐምድ ፤ በአርእ ስቱና ፡ በትንቢታዊ ፡ ቦዙ ፡ ላይ ፡ ተ ፡ ይጠፋ-በታል ። ይኸውም «ተከተለ ፤ ተቀመጠ ፡ » የሚለው ፡ ግሥ ፡ «መከተል ፤ መቀመጥ ፤ ወይም ፡ እከተል ፤ እቀመጥ ፤ » ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ በሰጠነው ፡ አስረጅ ፡ «መትከተል ፡ መትቀመጥ ፤ እትከተል ፡ እትቀመጥ ፡» አልተባለምና ፡ ተ ፡ እንደጠፋ ፡ አስተውል ።

— 216 —

በዐገ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ፊደላቸውን ፡ የሚለውጡ ፡ ወይም ፡ የሚያጕድሉ ፡ ግሦች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

እጅ ፡ የሚለት ፡ ግሥ ፡ ጎላፊ ፡ በዙን ፡ ብሎ ፡ ይላል ።
የመተው ፡ ግሥ ፡ ጎላፊ ፡ በዝን ፡ ትቶ ፡ ይላል ።

— 217 —

በአርባታ ፡ ላይ ፡ አዳስ ፡ ቃልን ፡ የሚወልድ ፡ የመምጣት ፡ ግሥ ፡ ነው ። ይኸ ውም ፡ በትእዛዝ ፡ አንቀጹ ፡ በዛኛው ፡ መደብ ፡ ና ፡ ነዪ ፡ ኑ ፡ ሲል ፡ ይገኛል ፡ ማለት ፡ ነው ።

— 218 —

የግሦች ፡ አስተግቡእ ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ የተሰበሰቡት ፡ ግሦች ፡ በአርእስት ፡ ይገባቸው ፡ ተጽፈዋል ። «አስተግቡአ ፡ » ከግዕዝ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ነው ። ትርጓሜው ፡ ስብሰብ ፡ ወይም ፡ የተሰበ ሰበ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህ (*) ምልክት ፡ የሚገኝባቸው ፡ ግሦች ፡ በአድራጊ ፡ ወይም ፡ በተደራጊ ፡ ዐምድ ፡ ሊነገሩ ፡ የሚችሉት ፡ ናቸው ።
ምሳሌ ፡ « መፈለግ ፤ » የሚለው ፡ ቃል ፡ ቦኖው ፡ ፈደል ፡ ለ ፡ ጠብቆ ፡ ሲነገር ፡ የአድ

ራጊው ፡ የፈለት ፡ ዐምድ ፡ ይሆናል ። ዜኖው ፡ ፈደል ፡ ፈ ፡ ጠብቆ ፡ ሲነገር ፡ የተደራጊው ፡ የተፈለገ ፡ ዐምድ ፡ ይሆናል ።

*መለመን ፡	መልቀም ፡	*መላክ ፡	መልፋት ፡	መሄድ ፡	ማለት ፡
*መመለስ ፡	መምሰል ፡	መሣል ፡	መምታት ፡	መሆን ፡	ማመን ፡
*መረጠጥ ፡	መርጠብ ፡	መራቅ ፡	መርታት ፡	መቆም ፡	ማረስ ፡
*መሰግሰግ ፡	መስረቅ ፡	*መሳም ፡	መስማት ፡	*መሾም ፡	ማሰብ ፡
*መሸመት ፡	መቀበር ፡	መሻክር ፡	መቀጣት ፡	መዘር ፡	ማሸት ፡
*መቀደስ ፡	መቅመስ ፡	*መቃም ፡	መትጋት ፡	*መፎክር ፡	ማቀፍ ፡
*መበተን ፡	መብረድ ፡	*መባረክ ፡	መብሳት ፡	መተለም ፡	ማበድ ፡
*መነቅነቅ ፡	መንገር ፡	*መናቅ ፡	መንቃት ፡	*መተርጉም ፡	ማነቅ ፡
*መከመር ፡	መክበድ ፡	*መካድ ፡	መላለት ፡	*መተኩስ ፡	ማከት ፡
*መወርወር ፡	መውደድ ፡	*መዋጥ ፡	መሬራት ፡	*መተው ፡	ማወቅ ፡
*መዘመር ፡	መዝፈን ፡	*መፃት ፡	*መሳሳት ፡	መኩተል ፡	ማዘን ፡
*መደመር ፡	መድከም ፡	*መዳመጥ ፡	*መታታት ፡	መሰማራት ፡	ማደር ፡
*መገደፍ ፡	መግደል ፡	*መጋት ፡	*መናኘት ፡	መቀመጥ ፡	ማገም ፡
*መጠርጠር ፡	መጥረግ ፡	*መጣፈጥ ፡	መቁየት ፡	መቀየም ፡	ማጠብ ፡
*መጨመር ፡	መጭመቅ ፡	*መጫር ፡	መጫጫት ፡	መቀማጠል ፡	ማጨድ ፡
*መፈለግ ፡	መፍረስ ፡	*መፋቅ ፡	መፋፋት ፡	መገረም ፡	ማፈር ፡

— 219 —

የማያቋርጥ ፡ ግሥ ።

በአድራጊ ፡ ዐምድ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በተደራጊ ፡ ዐምድ ፡ ክፍል ፡ የሚነገር ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ማቋረጥን ፡ ምግባር ፡ እየገለጸ ፡ በፅኑም ፡ የግሥ ፡ ስልቶች ፡ እየገባ ፡ በሙሉ ፡ እርባታ ፡ ይረባል ። በተሰቢው ፡ ላይ ፡ የከፈል ፡ አገባብ ፡ ከ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜም ፡ የመምረጥንና ፡ የማሸሽልን ፡ ጠባይ ፡ ያመለክታል ። (ሀ) ከመድረሻው ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ ፈደል ፡ በደጊም ፡ ያናግራል ፡ (ምሳሌውን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ (ሀ) በሚለው ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ተመልከት) ። (ለ) ግሡ ፡ በተውሳክ ፡ ግሥ ፡ የሚመራ ፡ ሲሆን ፡ ተውሳክ ፡ ግሡ ፡ በደጊሙ ፡ ቃል ፡ ይነገራል ። (ምሳሌውን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ (ለ) በሚለው ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ተመልከት ፡)

(ሀ)
- አስተማሪ ፡ ተማሪውን ፡ ያስተማራል ።
- ተማሪው ፡ ትምህርቱን ፡ ይማማራል ፡
- ብልሀ ፡ ልጅ ፡ የአስተማሪውን ፡ እርአያ ፡ ይከታተላል ።
- አስተማሪ ፡ ከተማሪዎች ፡ መከከል ፡ ያጠና ፡ ያጠናውን ፡ ይመራርጣል ።

(ለ) ውብሸት፡ ባልንጀራውን ፡ ሲያይ ፡ ሰቅ ፡ ሰቅ ፡ ይላል ።
እናት ፡ ልጅዋን ፡ ሰም ፡ ሰም ፡ ታደርጋለች ።
ትምህርትን ፡ ለማጥናት ፡ ቸል ፡ ቸል ፡ አትበል ።
ልጆች ፡ በመስክ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ቁጭ ፡ ይላሉ ።

— 220 —

ሥሉጥ ፡ ግሥ ።

ሥሉጥ ፡ ግሥ ፡ የሚባለው ፡ ከግንኛውም ፡ ግሥ ፡ አየተስማማ ፡ የሚገባና ፡ የሚነገር ፡ ቃል ፡ ነው ።

አጅ. መምሰል ፤ መፍቀድ ፤ መጀመር ፤ መፈለግ ፤ መሸት ፤ መቻል ፤ መግበት ፡ . . . ናቸው ። ከሁን ፡ በፊት ፡ የግሥ ፡ ረዳቶች ፡ የተባሉትም ፡ በግብራቸው ፡ ሥሉጣን ፡ ናቸው ።

— 221 —

ሰያፍ ፡ ግሥ ።

ሰያፍ ፡ ግሥ ፡ የሚባለው ፡ እንደ ፡ ግሥ ፡ ደንብ ፡ በመደብና ፡ በጾታ ፡ በቁጥር ፡ ሳይወሰን ፡ ማሰሪያ ፡ የሚሆንና ፡ አሰያይ ፡ የሚናገሩበት ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ሰያፍ ፡ ማለት ፡ ቀጥ ፡ በቀጥ ፡ ያልሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሰያፍ ፡ ግስ ፡ የሚባለው ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ እርሱ ፡ የሚነገርበትን ፡ ትንቢታዊ ፡ አንቀጽ ፡ ወርሶ ፡ ይገኛል ። ከመድረሻው ፡ በፊት ፡ የሚገኘውንም ፡ ፈጠውን ፡ ፊደል ፡ ቢ ፡ ተ ፡ ይ ፡ . . . እያሰኝ ፤ ወይም ፡ ራቡን ፡ ሳድስ ፡ አድርጎ ፡ ዋ ፡ የሚል ፡ ፊደልን ፡ እየወሰደ ፡ ይነገራል ። ይሽውም ፡ ይሏል ፡ «ይወጂል ፤ ይታጠቢል ፤ ይመለከታል ፤ ወይም ፡ ይል ዋል ፤ ይወድዋል ፤ ይታጠብዋል ፤ ይመለከትዋል ፡ » ያሰኛል ፡ ማለት ፡ ነው ። በምሥጢርም ፡ ከመሆን ፡ ግሥ ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ።

ምሳሌ ፡ 1. ይወጂል ፡ ከልብ ፡ ይታጠቢል ፡ ከክንድ ።
2. እውቀትን ፡ ለማስፋት ፡ መጻሕፍትን ፡ ይመለከቷል ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለምሳሌ ፡ የተሰጠው ፡ ቃል ፡ በመሆን ፡ ግሥ ፡ ቢለወጥ ፡ እንደሚ ከተለው ፡ ይሆናል ።

1. ሲወድዱ ፡ ከልብ ፡ ነው ፡ ሲታጠቡም ፡ ከክንድ ነው ።
2. እውቀትን ፡ ለማስፋት ፡ መጻሕፍትን ፡ መመልከት ፡ ነው ።

በሮኛ ፡ መደብ ፡ የሚነገረውም ፡ አንቀጽ ፡ ሰያፍ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

— 222 —

የ ማለት ፡ ግሥ ።

ግሥ ፡ አለ ፡ ላልቶ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ የመናገርን ፡ ምግባር ፡ እንደሚገልጽ ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ አስታውቀናል ፡ (ቁ. 167 እይ ።)

የማለት ፡ ግሥ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ተለይቶ ፡ በቃላት ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ንይል ፡ አለው ። በግዕዙ ፡ ሰዋስው ፤ ይቤ ፡ የሚባለው ፡ ግሥ ፡ ነው ።

— 223 —

ወቢይ ፡ አንቀጽ ፡ የቃላት ፡ ማሰሪያና ፡ መፈጸሚያ ፡ ስለሆነ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ሊገዛ ፡ አይችልም ። የማለት ፡ ግሥ ፡ ግን ፡ ወቢይ ፡ አንቀጽን ፡ እንደ ፡ ተሳቢ ፡ አድርጎ ፡ ሲገዛው ፡ ይገኛል ። ይህንንም ፡ በሚከተለው ፡ ተመልከት ።

ምሳሌ ፤ « ሆነ ፡ — መጣ ፡ — መሸ ፡ — ገባ ፡ — ፈለገ ፡ —» እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በወ ቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ከፍል ፡ ያሉ ፡ ማሰሪያዎች ፡ ናቸው ። ከነርሱ ፡ ሁለቱ ፡ ወይም ፡ ሰስቱ ፡ ቃላት ፡ በወረፍተ ፡ ነገር ፡ ተገጣጥመው ፡ ቢነገሩ ፡ ሁሉም ፡ የየራሳቸውን ፡ ምግባር ፡ ይገልጻሉ ፡ እንጂ ፡ አንደኛው ፡ አንቀጽ ፡ ሌላውን ፡ ተገዢ ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ።

አጅ ፡ «አስተማሪ ፡ ጊዜው ፡ መሸ ፡ መጣ ፡» ተብሎ ፡ ቢነገር ፡ መጣ ፡ የሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ለወረፍተ ፡ ነገሩ ፡ አንጻች ፡ ስሜቱን ፡ አያተርፍለትም ። ጸሩ ፡ ግን ፡ «አስተማሪ ፡ ጊዜው ፡ መሸ ፡ አለ ፡» የተባለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግሥ ፡ አለ ፡ «መሸ ፡» የሚለውን ፡ አን ቀጽ ፡ ተሳቢ ፡ አድርጎ ፡ ወረፍተ ፡ ነገሩን ፡ የተሟላ ፡ ያደርገዋል ። ትርጓሜውም ፡ «አስ ተማሪ ፡ ጊዜው ፡ እንደመሸ ፡ (ወይም ፡ መሸ ፡ ማለትን ፡) ተናገረ ፡» ማለት ፡ ነው ።

— 224 —

የማለት ፡ ግሥ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በምግባሩ ፡ የጥቅስ ፡ ወይም ፡ የትች ፡ ግሥ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። በአዕማድም ፡ ደንብ ፡ ግሥ ፡ አለ ፡ አድራጊ ፡ መደብ ፡ ነው ። ተደራጊ ውም ፡ ተባለ ፡ ያሰኛል ።

— 225 —

የማለት ፡ ግሥ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ በየዋህና ፡ በዝርዝር ፡ አርባታ ፡ በሙሉ ፡ ይረባል ። የአርባታውንም ፡ አኳኋን ፡ ለማሰየት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በየዋህ ፡ አር ባታ ፡ ብቻ ፡ በአምንታና ፡ በአሉታ ፡ እያረባን ፡ እንገልጻለን ፡ (ቁ. 226 ፡ እይ ።)

የማለት ፡ ግሥ ፡ መነሻ ፡ ፊደሉ ፡ አ ፡ ስለሆነ ፡ መነሻው ፡ እየታጣ ፡ የሚነገርበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ደግሞ ፡ መድረሻው ፡ ለ ፡ ስለሆነ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የ ፡ ወደመሆን ፡ ይለወጣል ።

— 226 —

የግስት ግሥ የዋሀ እርባታ ከዚህ ቀጥሎ የተጸፈው ነው ።

(ሀ) ዐቢይ አንቀጽ ።

የአምንታ እርባታ ።	የዋሀ ጎላፊ ።	የአሉታ እርባታ ።

ጎላፊ ጊዜያት ፡

	ነጠላ ፡	ብዙ ፡		ነጠላ ፡	ብዙ ፡
፩	አልሁ ፡	አልን ፡	፩	አላልሁም ፡	አላልንም ፡
፪	አልህ ፡ አልሽ ፡	አላችሁ ፡	፪	አላልህም ፡ አላልሽም ፡	አላላችሁም ፡
፫	አለ ፡ አለች ፡	አሉ ፡	፫	አላለም ፡ አላለችም ፡	አላሉም ፡

የቅርብ ጎላፊ ።

፩	ብያለሁ ፡	ብለናል ፡	፩	አልብዬም ፡	አልብለንም ፡
፪	ብለሃል ፡ ብለሻል ፡	ብላችኋል ፡	፪	አልብለህም ፡ አልብለሽም ፡	አልብላችሁም ፡
፫	ብሏል ፡ ብላለች ፡	ብለዋል ፡	፫	አልብሎም ፡ አልብላም ፡	አልብለውም ፡

የሩቅ ጎላፊ ።

፩	ብዬ ፡ ነበር ፡	ብለን ፡ ነበር ፡	፩	አልብዬም ፡ ነበር ፡	አልብለንም ፡ ነበር ፡
፪	ብለህ ፡ ነበር ፡ ብልሽ ፡ ነበር ፡	ብላችሁ ፡ ነበር ፡	፪	አልብለህም ፡ ነበር ፡ አልብልሽም ፡ ነበር ፡	አልብላችሁም ፡ ነበር ፡
፫	ብሎ ፡ ነበር ፡ ብላ ፡ ነበር ፡	ብለው ፡ ነበር ፡	፫	አልብሎም ፡ ነበር ፡ አልብላም ፡ ነበር ፡	አልብለውም ፡ ነበር ፡

ማስገንዘቢያ ፡ ከዚህ በላይ በቅርብና በሩቅ ጎላፊ በአሉታ የተጸፈውን የማይቀበሉ አሉ ፤ እንደ አሳባቸውም በየዋሁ ጎላፊ የተጸፈውን አሉታ ይመስናሉ ።

ዐቢይ አንቀጽ (ለጣቂ)

የአምንታ እርባታ ፡		የአሉታ እርባታ ፡	
ነጠላ ፡	ብዙ ፡	ነጠላ ፡	ብዙ ፡

2. የአሁንና የትንቢት ጊዜያት ።

፩	እላለሁ ፡	እንላለን ፡	፩	አልልም ፡	አንልም ፡
፪	ትላለህ ፡ ትያለሽ ፡	ትላላችሁ ፡	፪	አትልም ፡ አትዪም ፡	አትሉም ፡
፫	ይላል ፡ ትላለች ፡	ይላሉ ፡	፫	አይልም ፡ አትልም ፡	አይሉም ፡

(ለ) ትእዛዝ አንቀጽ ።

፩	ልበል ፡	እንበል ፡	፩	አልበል ፡	አንበል ፡
፪	በል ፡ በዪ ፡	በሉ ፡	፪	አትበል ፡ አትበዪ ፡	አትበሉ ፡
፫	ይበል ፡ ትበል ፡	ይበሉ ፡	፫	አይበል ፡ አትበል ፡	አይበሉ ፡

(ሐ) አዋዋይ አንቀጽ ፡

ሀ—ምክንያታዊ አዋዋይ ፡

1. ጎላፊ ጊዜያት ።

፩	ብል ፡ ኖሮ ፡	ብንል ፡ ኖሮ ፡	፩	ባልል ፡ ኖሮ ፡	ባንል ፡ ኖሮ ፡
፪	ብትል ፡ ኖሮ ፡ ብትዪ ፡ ኖሮ ፡	ብትሉ ፡ ኖሮ ፡	፪	ባትል ፡ ኖሮ ፡ ባትዪ ፡ ኖሮ ፡	ባትሉ ፡ ኖሮ ፡
፫	ቢል ፡ ኖሮ ፡ ብትል ፡ ኖሮ ፡	ቢሉ ፡ ኖሮ ፡	፫	ባይል ፡ ኖሮ ፡ ባትል ፡ ኖሮ ፡	ባይሉ ፡ ኖሮ ፡

ማስገንዘቢያ 1 ኖሮ የሚለው ረዳቱ ግሥ ቀርቶ ብቻውንም ይነገራል ። ይኸውም ብል ብትል ባልል ባትል ...ይላል ማለት ነው ።

እንደዚሁም ደግሞ የሩቅ ጎላፊ ለማድረግ ብዬ ብሆን ኖር ፤ ብለህ ቢሆን ኖር ፤ አልል ቢሆን ኖር ፤ አትል ቢሆን ኖር ፤ ...እያለ በጎላፊ በገሃ አንቀጽ ላይ ቢሆን ኖር የሚል ቃል እየተጨመረበት ይረባል ።

አዋዋይ፡ አንቀጽ፡ (ሰጣቂ ።)

የአምንታ ፡ እርባታ ፡		የአሉታ ፡ እርባታ ፡	
ነጠላ፡	ብዙ፡	ነጠላ፡	ብዙ፡

2. የአሁንና ፡

የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡

፩ —	እA ፡ ዘንድ፡	እንA ፡ ዘንድ፡			
፪ —	ትA ፡ ዘንድ፡ ትዪ ፡ ዘንድ፡	ትሉ ፡ ዘንድ ፡			
፫ —	ይA ፡ ዘንድ፡ ትA ፡ ዘንድ፡	ይሉ ፡ ዘንድ ፡			
፩ —	እንድA ፡	እንድንA ፡	፩ —	እንዳልA ፡	እንዳንA ፡
፪ —	እንድትA ፡ እንድትዪ ፡	እንድትሉ ፡	፪ —	እንዳትA ፡ እንዳትዪ ፡	እንዳትሉ ፡
፫ —	እንዲA ፡ እንድትA ፡	እንዲሉ ፡	፫ —	እንዳይA ፡ እንዳትA ፡	እንዳይሉ ፡

ማስተንበቢያ ፡ እንደ ፡ በሚለው ፡ ፈንታ ፡ ለ ፡ የሚል ፡ ተጨምሮ ፡ እንደዚያው ፡ ይረባል. ይኸውም ፡ ልA ፤ ልትA ፤ ላልA ፤ ላትA ፤ ...ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪. ተምኔታዊ ፡ አዋዋይ ።

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ።

፩ —	ባልሁ ፡ ነበር ፡	ባልን ፡ ነበር ፡	፩ —	ባላልሁም ፡ ነበር ፡	ባላልንም ፡ ነበር
፪ —	ባልህ ፡ ነበር ፡ ባልሽ ፡ ነበር ፡	ባላችሁ ፡ ነበር ፡	፪	ባላልህም ፡ ነበር ፡ ባላልሽም ፡ ነበር ፡	ባላላችሁም ፡ ነበር ፡
፫ —	ባለ ፡ ነበር ፡ ባለች ፡ ነበር ፡	ባሉ ፡ ነበር ፡	፫ —	ባላለም ፡ ነበር ፡ ባላለችም ፡ ነበር ፡	ባላሉም ፡ ነበር ፡

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

፩ —	አል ፡ ነበር ፡	እንል ፡ ነበር ፡	፩ —	አልልም ፡ ነበር ፡	አንልም ፡ ነበር
፪ —	ትA ፡ ነበር ፡ ትዪ ፡ ነበር ፡	ትሉ ፡ ነበር ፡	፪ —	አትልም ፡ ነበር ፡ አትዪም ፡ ነበር ፡	አትሉም ፡ ነበር ፡
፫ —	ይA ፡ ነበር ፡ ትA ፡ ነበር ፡	ይሉ ፡ ነበር ፡	፫ —	አይልም ፡ ነበር ፡ አትልም ፡ ነበር ፡	አይሉም ፡ ነበር ፡

(መ) ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡

አ ር እ ስ ት ።

የአምንታ ፡ እርባታ ፡		የአሉታ ፡ እርባታ ፡	
ማለት ፡		አለማለት ፡	

በዝ፡ አንቀጽ ።

ነጠላ፡	ብዙ፡	ነጠላ፡	ብዙ፡

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ።

፩ —	ብዬ ፡ —	ብለን —	፩ —	አልብዬ —	አልብለን —
፪ —	ብለህ — ብልሽ —	ብላችሁ—	፪ —	አልብለህ — አልብልሽ —	አልብላችሁ—
፫ —	ብሎ — ብላ	ብለው —	፫ —	አልብሎ — አልብላ —	አልብለው

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

፩ —	እA —	እንA —	፩ —	አልA —	አንA —
፪ —	ትA — ትዪ —	ትሉ —	፪ —	አትA — አትዪ —	አትሉ —
፫ —	ይA — ትA —	ይሉ —	፫ —	አይA — አትA —	አይሉ —

ግሣዊ ፡ ቅጽል ።

1. ጎላፊ ፡ ጊዜያት ።

፩ —	ያልሁ ፡	ያልን ፡	፩ —	ያላልሁ ፡	ያላልን ፡
፪ —	ያልህ ፡ ያልሽ ፡	ያላችሁ ፡	፪ —	ያላልህ ፡ ያላልሽ ፡	ያላላችሁ ፡
፫ —	ያለ ፡ ያለች ፡	ያሉ ፡	፫ —	ያላለ ፡ ያላለች ፡	ያላሉ ፡

2. የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ።

፩ —	የምA ፡	የምንA ፡	፩ —	የማልA ፡	የማንA ፡
፪ —	የምትA ፡ የምትዪ ፡	የምትሉ ፡	፪ —	የማትA ፡ የማትዪ ፡	የማትሉ ፡
፫ —	የሚA ፡ የምትA ፡	የሚሉ ፡	፫ —	የማይA ፡ የማትA ፡	የማይሉ ፡

3. ውስጠየ ።

አምንታ፣	አሉታ ፡
አልሁ ፡ ባይ ፡ መባያ ፡	አሉተኛ ፡

4. ዘርና ፡ ሳቢ.ዘር ።

ግለት ፡ ባህል ፡ አባበል ፡	አሰማለት ፡ አሉታ ፡

ፐሮኖ ፡ መልመጃ ።

1—አራቱን ፡ የግሥ ፡ ስልቶች ፡ በጥቁር ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ እንደሚከተለው ፡ አድርገህ ፡ ጻፍ ።

ወቢይ ፡ አንቀጽ ፡	ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡	አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡	ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡

2—የግሥ ፡ ክፍል ፡ የሆኑትን ፡ ቃላት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፉት ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ እየመረጥህ ፡ ተናገር ። ክፍላቸውም ፡ ከየትኛው ፡ የግሥ ፡ ስልት ፡ እንደሆነ ፡ እያመለከትህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ በየስልቱ ፡ እግርጌ ፡ ጻፋቸው ።

የትምህርት ፡ ሰዓት ፡ ደረሰ ፡ አስተማሪ ፡ መጽሐፉን ፡ ያዘ ። ተማሪ ፡ ይማር ፡ ጀመር ። መጽሐፉ ፡ ትልቅ ፡ ነበር ። ትምህርት ፡ መልክም ፡ ነው ። ሥራ ፡ ያስከብራል ። ሰንፍና ፡ ያስንቃል ። እገርህን ፡ ውደድ ። ንጉሥህን ፡ አክብር ። ጠላትህን ፡ ውደድ ፡ አድርግ ። አብርሃም ፡ ቢመጣ ፡ ናሮ ፡ ይማር ፡ ነበር ፡ እኔ ፡ ቀርቼ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በተመታሁ ፡ ነበር ። መሐንዲስ ፡ እንድሆን ፡ እመኛለሁ ። ጅዖሜትሪን ፡ እማር ፡ ዘንድ ፡ አስባለሁ ። አጥቶ ፡ ማግኘት ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። አግኝቶ ፡ ማጣት ፡ ግን ፡ ያሳዝናል ። መሸት ፡ ከለ ፡ ሁሉ ፡ ይገኛል ። በጎ ፡ አድራጊ ፡ ዋጋውን ፡ ያገኛል ። ክፉ ፡ ለክፉ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ከአንጋገር ፡ ይፈረዳል ፡ ከአያያዝ ፡ ይቀየዳ ።

3—ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፈውን ፡ እያነበብህ ፡ አንቀጾችን ፡ በየጊዜያቸው ፡ እየለየህ ፡ ተናገር ። ይኸውም—''ነሳፊ ፡ የአውን—የትንቢት ፡ '' ጊዜያት ፡ እያሉ ፡ ግስጽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ክፍላቸውም ፡ ከየትኛው ፡ ስልት ፡ እንደሆነ ፡ ተናገር ።

ይግለጡ ፡ ቤትን ፡ ሠራ ። ልጆች ፡ በመስክ ፡ ላይ ፡ ይጫወታሉ ። ከብቶቹ ፡ በሚዳው ፡ ተሰማርተዋል ። ጊዜው ፡ ሊመሽ ፡ ነው ። እኔ ፡ በግለጻ ፡ እነግለጡ ። ወደ ፡ ቤት ፡ እንግባ ። አንተ ፡ መጽሐፍህን ፡ አንሣ ። እርሱ ፡ እንዲከተለን ፡ ይሁን ። ትምህርት ፡ ተጀምሮ ፡ ይሆናል ።

ገበሬ ፡ እርሻውን ፡ ያለሰልሳል ። ክረምት ፡ ሊመጣ ፡ ነው ። ክረምት ፡ ገባ ። መከር ፡ ደረሰ ። እህሉ ፡ ይታጨዳል ። የሰው ፡ ክፋቱ ፡ ከአንደበቱ ፡ ነው ። ኃጢአት ፡ ባይኖር ፡ ሞት ፡ በልነበረም ። ከመሞት ፡ መሰንበት ፡ ይሻላል ። አንድ ፡ ይወልድ ፡ አንድ ፡ ይፈርድ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ። ተውሳክ ፡ ግሥ ።

227

መግለጫ ።

ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ የሚባለው ፡ ከግሥ ፡ በፊት ፡ እየገባ ፡ የአንቀጽን ፡ ጠባይ ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ተብሏል ። ትርጓሜው ፡ የግሥ ፡ ጭማሪ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የግሥን ፡ ጠባይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከሌሎችም ፡ የንግግር ፡ ክፍሎች ፡ የአንዳንዶችን ፡ ጠባይ ፡ እየገለጸ ፡ ሲገባ ፡ ይገኛል ። ይህንኑም ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

(ሀ) በግሥ ፡ ላይ ፡ ሲገባ ፡ —
ፈለቀ ፡ በትጋት ፡ (ወይም ፡ ተግቶ ፡) ይማራል ።
ፈለቀ ፡ ክፉኛ ፡ ታሟል ።

(ለ) በቅጽል ፡ ላይ ፡ ሲገባ ፡ —
የገጾማህ ፡ ልብስ ፡ ፈጽሞ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።
እርሱ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ነው ።

(ሐ) በተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ላይ ፡ ሲገባ ። —
አስተማሪው ፡ ሁልጊዜ ፡ ተግቶ ፡ ያስተምራል ።
እንግዲህ ፡ በጣም ፡ እንተዋወቅ ።

(መ) ከመስተዋድድ ፣ ጋር ፣ ሲገባ ።
እርሱ ፣ በቀጥታ ፣ ወደ ፣ እኔ ፣ መጣ ።
የወባይ ፣ ወንዝ ፣ ልክ ፣ በሐምሌ ፣ ወር ፣ ይሞላል ።
(ሠ) በመስተዋምር ፣ ላይ ፣ ሲገባ ።
እውነተኛ ፣ ደስታ ፣ ጤንነት ፣ ሲገኝ ፣ ብቻ ፣ ነው ።

228

የተውሳክ ፣ ግሥ ፣ ክፍሎች ።

ተውሳክ ፣ ግሥ ፣ በ፫ ፣ ታላላቅ ፣ ክፍሎች ፣ ይመደባል ።

(ሀ) የዋሀ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።
(ለ) መጠይቅ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።
(ሐ) ከበባ ፣ የሚገኝ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

እነዚህ ፣ ደግሞ ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ንኡሳን ፣ ክፍሎች ፣ ይከፈላሉ ። በተውሳክ ፣ ግሥ ፣ ክፍል ፣ የሚነገሩት ፣ ቃላት ፣ አንዳንዶቹ ፣ በመስተዋድድና ፣ በመስተዋምር ፣ ክፍል ፣ ይገኛሉ ። ልዩነታቸውም ፣ የሚታወቅ ፣ የአገበባቸውን ፣ ስልት ፣ በግዕቅ ፣ ነውና ፣ በየዐንቀው ፣ ጠንቅቆ ፣ መመልከት ፣ ነው ።

— 229 —

(ሀ) የዋሀ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

የዋሀ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ፣ « የጊዜ ፣ —የቦታ ፣ —የግብር ፣ —የቁጥር ፣ —የመጠን ፣ —የምክንያት ፣ —የአምንታና ፣ የአሉታ ፣ » ተብሎ ፣ ይመደባል ። የዋሀ ፣ ግስት ፣ ገር ፣ ወይም ፣ ቀላል ፣ ግስት ፣ ነው ፣ ብለን ፣ ከሁን ፣ በፊት ፣ ተናግረናል ። (ቁ.173 እይ ።) በዚህ ፣ ክፍል ፣ የሚነገሩትም ፣ የተውሳክ ፣ ግሥ ፣ ታላቅ ፣ በቀላል ፣ የሚታወቁ ፣ ወይም ፣ በግልጽ ፣ የሚታዩ ፣ ስለሆኑ ፣ በዚሁ ፣ ስያሜ ፣ ተሰይመዋል ። ከነእርሱም ፣ ዋና ፣ ዋኖቹን ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ ለምሳሌ ፣ በየክፍሉ ፣ ጽፈናል ።

1. የጊዜ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

« ዱሮ ፣ —ዋንት ፣ —ቀድሞ ፣ —አስቀድሞ ፣ —አሁን ፣ —በቅርቡ ፣ —በፍጥነት ፣ —እንግዲህ ፣ —ሁልጊዜ ፣ —ሁልቀን ፣ —ዕለት ፣ ዕለት ፣ —በየዕለቱ ፣ —ትናንት ፣ —ዛሬ ፣ ነገ ፣ —በነጋው ፣ —በማግሥቱ ፣ —በፊት ፣ —በኋላ ፣ —ወዲያው ፣ —ዕለቱን ፣ —ቶሎ ፣ »

2. የቦታ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

« እዚህ ፣ —እዚያ ፣ —እዚያንች ፤ —ወዲህ ፣ —ወዲያ ፣ —ወዲያንች ፤ —በላይ ፣ —በታች ፣ —በራስጌ ፣ —በግርጌ ፣ —በውስጥ ፣ —በውጭ ፣ —ወዲያው ፣ —በስቲያው ፣ —

3. የግብር ፣ ወይም ፣ የዓይነትና ፣ የአኳኋን ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

« እንዲህ ፣ —እንዲያው ፣ —ድንገት ፣ —ፈጽሞ ፣ —ክቶ ፣ —በቀጥታ ፣ —ክፉኛ ፣ —በዝግታ ፣ —በጸጥታ ፣ —እርስ ፣ በርስ ፣ —ቀስ ፣ በቀስ ፣ —ላይ ፣ በላይ ፣ —ፊት ፣ ለፊት ፣ —እንደ ፣ —ይመስል ። »

4. የቁጥር ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

« መጀመሪያ ፣ —ዳግመኛ ፣ —እንደገና ፣ —አንደዱ ፣ —ሁለተዱ ፣ —አንድ ፣ በአንድ ፣ —እያንዳንድ ፣ —በሁለት ፣ በሁለት ፣ —በተሰይ ፣ —ስብቻ ፣ —በዘጎብረት ፣ »

5. የመጠንና ፣ የማበላለጥ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

« እጅግ ፣ —በጣም ፣ —በብዙ ፣ —በጥቂት ፣ —በመጠን ፣ —ፈጽሞ ፣ —በጭራሽ ፣ —አንዳች ፣ —አብዛኛው ፣ —እምብዛም ፣ —እኩል ፣ በኩል ፣ —መሳ ፣ ለመሳ ፣ —ግማሽ ፣ በግማሽ ፣ —ጥቂት ፣ በጥቂት ፣ —በየጥቂቱ ፣ »

6. የምክንያት ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

« ስለዚህ ፣ —እንደዚህ ፣ —እንደ ፣ —መጠን ፣ »

7 የአምንታና ፣ የአሉታ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

አምን ፣ —እሺ ፣ —በዩ ፣ —እውነት ፣ —እርግጥ ፣
እንኳን ፣ —እንቢ ፣ —አሌ ፤ —አንጃ ፣

230

(ለ) መጠይቅ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ።

መጠይቅ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ፣ የተባለው ፣ በተውሳክ ፣ ግሥ ፣ ክፍል ፣ ጥያቄን ፣ ለማቅረቢያ ፣ የሚጠቅም ፣ ቃል ፣ ነው ። ይህም ፣ እንደላይኖው ፣ በየክፍሉ ፣ ተዘርግቦ ይነገራል ።

1. —የጊዜ ፣ ተ. ግ. ። « መቼ — ምንጊዜ ፣ — ምንዩ ፣ — ለምንጊዜው ፣ — ተመቸው ። »...
2. —የቦታ ፣ ተ. ግ. ። « ወዴት ፣ — የት ፣ » . . .
3. —የግብር ፣ ተ. ግ. ። « እንዴት ፤ — እንደምን ። » . . .
4. —የቁጥር ፣ ተ. ግ ። « ስንት ፣ ጊዜ ፤ — ስንትዱ ። » . . .
5. —የመጠን ፣ ተ. ግ. ። « ምን ፣ ያህል ፣ — የቱን ፣ ያህል ። » . . .
6. —የምክንያት ፣ ተ. ግ. ። « ስለምን — ለምን — በምን — ። » . . .
7. —የአምንታና ፣ የአሉታ ፣ ተ. ግ. ። በውኑ ፤ እስቲ ። . .

በመጠይቅ ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ፣ ክፍል ፣ ከሚነገሩት ፣ ቃላት [illegible] በቃለ ፣ አጋኖና ፣ በሌላም ፣ ክፍል ፣ ይገኛሉ ። ልዩነታቸውም ፣ የ ጊታው [illegible] ፣ ነገሩ ፣ አኳኋን ፣ ነው ።

— 231 —

(ሐ) ከበዝ ፡ የሚገኝ ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ።

ከግሥ ፡ ክፍል ፡ የሚገኝ ፡ በዝ ፡ አንቀጽ ፡ በተውሳከ ፡ ግሥነት ፡ ይገባል ። ዳግ መኖም ፡ ከመስተፃምር ፡ ክፍል ፡ የሚሆኑ ፡ ና—እየ—› በግሥ ፡ ላይ ፡ እየተጫኑ ፡ ሲገቡ ፡ የበዝን ፡ ምግባር ፡ ይዘው ፡ በተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ደንብ ፡ ይነገራሉ ። እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ በሚከ ተለው ፡ እናሳያለን ።

እርሱ ፡ ፈርቶ ፡ ሸሸ ።
እርሱ ፡ ፈራና ፡ ሸሸ ፤ (ፈርቶ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ፈራ ።)
እርሱ ፡ እየፎጠ ፡ ሄደ ፡ (ፎጠ ።)

— 232 —

የግወጻጸር ፡ ወይም ፡ የማጻጸር ፡ ደረጃ ።

ከተውሳከ ፡ ግሥ ፡ አንጻንጾቹ ፡ ቃላት ፡ እንደ ፡ ቅጽል ፡ ደንብ ፡ የግወጻጸር ደረጃ ፡ አላቸው ። ይኸውም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ተግቶ ፡ ይማራል ፤ .. .. (ተነጻጻሪ ፡ ደረጃ ፤)
በጣም ፡ ተግቶ ፡ ይማራል ፤ .. .. (አብላጭ ፡ ደረጃ ፤)
እጅግ ፡ በጣም ፡ ተግቶ ፡ ይማራል ። .. (አበላላጭ ፡ ደረጃ ።)

— 233 —

የተውሳከ ፡ ግሥ ፡ አመጻጸብ ።

ተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ባዕድ ፡ መነሻ ፡ ሠያሜ ፡ ወይም ፡ ባሪድ ፡ ጨመረበት ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ይመደባል ። ይህንኑም ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

ባዕድ ፡ መነሻ ፡	ተውሳከ ፡ ግሥ ፡
ለ—	ለጊዜው ፤ ለይስሙላ ፤ ላመሉ ፤ ለላመት ፡ . . .
በ—	በፍጥነት ፤ በድንገት ፤ በግዴታ ፡ በዝግታ ፡ በራስጌ ፡ በብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ . . .
በየ—	በየስፍራው ፡ ፤ በየጊዜው ፤ በየቀኑ ፡ . . .
በስተ—	በስተ ፡ ላይ ፡ በስተ ፡ ራስጌ ፤ በስቲያው ፡
እንደ—	እንዲያው ፡ እንደገና ፤ እንደተግላ ፤ እንደጊዜው ፤ . . .
ባዕድ ፡ መድረሻ ፡	
—ና ፡	ተማረና ፡ ይማርና ፤ . . .
—ኛ ፡	ክቡኛ ፡ ሰው ፡ ሰውኛ ፤ . . .
—ው ፡	ወዲያው ፡ ለጊዜው ፡ . . .
—ን ፡	ዕለቱን ፤ ያንጊዜውን ፤ ግታውን ፡ . . .
—ኑ ፡	ያኔውኑ ፤ ግታውኑ ፤ ሌሊቱኑ ፡ . . .

— 234 —

ተደጋግመው ፡ ወይም ፡ ተጫፍረው ፡ የሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ በወረፍተ ፡ ነገር ፡ ተገ ጣጥመው ፡ በተነገሩ ፡ ጊዜ ፡ የተውሳከ ፡ ግሥን ፡ መደብ ፡ ይይዛሉ ።

ምሳሌ ። ልጅ ፡ «ዋቂት ፡ በጥቂት ፡» ያድጋል ።

ባሕርዩ ፡ «በቀን ፡ በቀኑ ፡» ይለዋወጣል ፡
ሽማግሌ ፡ «ቀስ ፡ በቀስ ፡» ይጫዋታል ።
ኃጥአ ፡ ሰው ፡ ከፋትን ፡ «በላይ ፡ በላይ ፡» ይጨምራል ፡
ተማሪዎች ፡ «ፈትና ፡ ኋላ ፡» ይሄዳሉ ፡
«የግታ ፡ ግታ ፡» ድሉ ፡ የኛ ፡ ነው ።
ጥጋበኛ ፡ «ላይና ፡ ታች ፡» ይረግጣል ፡
ሥራ ፡ ፈት ፡ «ወዲያና ፡ ወዲህ ፡» ይዘራል ።
ያገሬ ፡ ሜዳ ፡ «ቢሄዱት ፡ ቢሄዱት ፡» አያልቅም ።
የሰአል ፡ ቤት ፡ «እያነሰ ፡ እያነሰ ፡» ሄደ ፡
«ውሎ ፡ ውሎ ፡» ከቤት ፡ «ናሮ ፡ ናሮ ፡» ከመሬት ፡ ነው ።

235 —

ከግሥ ፡ ክፍል ፡ የማይገኙ ፡ መይም ፡ የሚገኙ ፡ ቃለ ፡ አጋኖች ፡ ከመሆን ፡ ግሥ ፡ ጋር ፡ እየተዋሐዱ ፡ ሲገቡ ፡ የተውሳከ ፡ ግሥነትን ፡ ምግባር ፡ ይይዛሉ ።

(ሀ) ከግሥ ፡ ክፍል ፡ የማይገኙ ፡ የተባሉት ፡ ለምሳሌ ፡ «ለጥ ፡ — ብቅ ፡ — ቀጥ ፡ ተግ ፡ — ቸል ፡ ከፍ ፡ — ዝግ ፡ — ዱብ ፡ — ጸጥ ፡ — ፈቀቅ ፡» .... ናቸው ። የመሆን ፡ ግሥ ፡ አፅማድ ፡ « አለ ፡ አደረገ ፡ አሰኘ ፡» —በሁሉም ፡ ወይም ፡ በያንዳንዱ ፡ እየተጨመሩላቸው ፡ ግሥን ፡ አክለው ፡ መስለው ፡ ይወጣሉ ።

እጅ ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡	ግሥ ፡ «አለ ፡»	ግሥ ፡ «አደረገ ፡»	ግሥ ፡ «አሰኘ ፡»
ለጥ ፡	ለጥ ፡ አለ ፡	ለጥ ፡ አደረገ ፡	—
ብቅ ፡	ብቅ ፡ አለ ፡	ብቅ ፡ አደረገ ፡	ብቅ ፡ አሰኘ ፡
ከፍ ፡	ከፍ ፡ አለ ፡	ከፍ ፡ አደረገ ፡	ከፍ ፡ አሰኘ ፡
ዝግ ፡	ዝግ ፡ አለ ፡	ዝግ ፡ አደረገ ፡	ዝግ ፡ አሰኘ ፡

(ለ) ከግሥ ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ የተባሉት ፡ ለምሳሌ ፡ — ላላ ፡ ሞቅ ፡ —ራቅ ፡— ሉብ ፡ ሳቅ ፡ — ቀመስ ፡ — ብትን ፡ — ትርፍርፍ ፡ — ትኝት ፡ — ትውት ፡ ነቅነቅ ፡ ንቅንቅ ፡ — ጨበጥ ፡ — ጭብጥ ፡» እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ እንደላይኛው ፡ መሆን ፡ ግሥ ፡ ጋር ፡ እየተዋሐዱ ፡ ይገባሉ ።

አጅ. ግሥ፣	ቃለ አጋኖ፣	ግሥ «አለ»	ግሥ «አደረገ»	ግሥ «አሰኘ»
መላላት፣	ላላ፣	ላላ፣ አለ፣	ላላ፣ አደረገ፣	—
መሞቅ፣	ሞቅ፣	ሞቅ፣ አለ፣	ሞቅ፣ አደረገ፣	—
መራቅ፣	ራቅ፣	ራቅ፣ አለ፣	ራቅ፣ አደረገ፣	—
መሳም፣	ሳም፣	—	ሳም፣ አደረጉ፣	—
መሳብ፣	ሳብ፣	ሳብ፣ አለ፣	ሳብ፣ አደረገ፣	—
መተው፣	ትውት፣	—	ትውት፣ አደረገ፣	ትውት፣ አሰኘ፣
መሸት፣	ትኝት፣	ትኝት፣ አለ፣	—	—

— 236 —

ከዚህ፣ በላይ፣ ቁ. በ235፣ (ለ) የተነገሩት፣ ቃላት፣ የማብለጥና፣ የማሳነስ፣ ደረጃ፣ ይታይባቸዋል። ይኸውም፣ እንደሚከተለው፣ ነው። አሳናሹ፣ ደረጃ፣ በአርእስት፣ ላይ፣ መስተዋድድ፣ እንደ፣ እየተጨመረበት፣ ይገባል።

አጅ. ግሥ፣	አብላጭ፣	አሳናሽ፣
መላላት፣	ላላ፣ አለ፣	እንደ፣ መላላት፣ አለ፣
መሰቅ፣	ሰቅ፣ አለ፣	እንደ፣ መሰቅ፣ አለ፣
መሳብ፣	ሳብ፣ አደረገ፣	እንደ፣ መሳብ፣ አደረገ፣
መተው፣	ትውት፣ አደረገ፣	እንደ፣ መተው፣ አለ፣

የቀረውንም፣ በዚሁ፣ አካሄድ፣ ይመለከታል።

— 237 —

ና፣ በል። እነዚህ፣ ቃላት፣ ለግስ፣ መምጣትና፣ ለግሥ፣ ግለት፣ ትእዛዝ፣ እንቀጾች፣ ናቸው። ዳሩ፣ ግን፣ አንዳንድ፣ ጊዜ፣ የግሥነት፣ ጠባያቸውን፣ እየተዉ፣ በቃለ፣ አጋኖ፣ ወይም፣ በተውሳክ፣ ግሥ፣ ደንብ፣ ሲገቡ፣ ይገኛሉ። በዚያን፣ ጊዜም፣ በትእዛዝ፣ ስልት፣ የበታን፣ ወይም፣ የጊዜን፣ አኳኋን፣ ይገልጻሉ።

ምሳሌ፣—ና፣ ሂድ፣ (=ከዚህ፣ ወግድ፣)
ና፣ ግባ፣ (=እሺ፣ ግቡ፣)
በል፣ሂድ፣(=አሁኑን፣ ሂድ፣)
በል፣ ግባ፣(=እሺ፣ ግባ፣)

፲፪ኛ ፣ መልመጃ።

ከዚህ፣ በታች፣ ከተጻፉት፣ ወረፍተ፣ ነገሮች፣ ውስጥ፣ ተውሳክ፣ ግሦችን፣ እየለየህ፣ አመልክት።

ሁልጊዜ፣ እውነትን፣ ተናገር።— ሐሰትን፣ ፈጽሞ፣ አትናገር።— ዮሐንስ፣ ከቶ፣ ታሟል።— ዛሬ፣ ከሆስፒታል፣ ገባ።— በልጋ፣ ሳይ፣ ትኝት፣ ብሏል።— ሕሙሙን፣ ከቶ፣ አላወቀውም።— ሽማግሌ፣ በዝግታ፣ ይራመዳል።— ወጣት፣ ዱብ፣ ዱብ፣ ይላል።— ተግሣጽ፣ ለጊዜው፣ ያሳዝናል።— የኋላ፣ ኋላ፣ ደስ፣ ያሰኛል።— ሥልጡን፣ ልጅ፣ እሺ፣ በጀ፣ ይላል።—ባለጌ፣ እንቢ፣ ማለትን፣ ያዘወትራል።— ግብዝ፣ ሰው፣ ለይስሙላ፣ ይናገራል።— ቃሉንም፣ በቀን፣ በቀኑ፣ ይለዋውጥአል።— መጽሐፍህን፣ እስቲ፣ ስጠኝ፣?— እንኳን፣ አልሰጥህም።— እባክህ፣ እንደዱ፣ ስጠኝ ?እኔ፣ በመጽሐፌ፣ እያነበብሁ፣ አመሰላሁ።— እርሱ፣ መጽሐፉን፣ ገለጠና፣ አነበበ።— መጽሐፉን፣ ይግለጥና፣ያነብብ።— ትምህርቱን፣ ቀስ፣ በቀስ፣ ያጠናል።— ልጆች፣ እንዳንድ፣ እያሉ፣ ተሰበሰቡ።— እርስ፣ በርሶቹው፣ ይጫወታሉ።— ወደቤታቸው፣ ያንጊዜውን፣ ተመለሱ።— ነገ፣ እግር፣ መንገዴን፣ አይሃለሁ።— በሽተኛውን፣ በስቲያው፣ እንጮ በኛለን፤— እንግዲህ፣ በየቤታችን፣ እንግባ፣— በል፣ ዳኅና፣ እደር።

ምዕራፍ ፣ ፮ ፣ መስተዋድድ ፣

— 238 —

መግለጫ፣—

መስተዋድድ፣ በስም፣ ወይም፣ ስምን፣ መስለው፣ በሚገኙ፣ ቃላት፣ ላይ፣ እየተጫነ፣ ገብቶ፣ በወረፍተ፣ ነገር፣ ውስጥ፣ የንግግርን፣ ዝምድና፣ የሚያሳይ፣ ቃል፣ ነው። የመስተዋድድ፣ ትርጓሜ፣ አስማሚ፣ ወይም፣ አዋዋጅ፣ እንደ፣ ማለቅ፣ ነው።

ምሳሌ፣— እርሱ፣ በዱላ፣ መታኝ።
እርሱ፣ በወንበር፣ ላይ፣ ተቀመጠ።
እርሱ፣ ከልጁ፣ ጋር፣ ይጫወታል።

እነሆ፣ በዚህ፣ በተሰጠው፣ ምሳሌ፣ መስተዋድዶቹ፣ በ፣ በ፣— ላይ፣ ከ—ጋር፣ ናቸው። የፈተኖው፣ በመነሻ፣ ብቻ፣ የኋለኞቹ፣ በመነሻም፣ በመድረሻም፣ ገብተው፣ ተሰቢዎቹን፣ ከእንቀጾቹ፣ ጋር፣ አስማምተዋቸዋል። መስተዋድዶቹ፣ ሳይጨመሩ፣ ሲቀር፣ ዱላ፣ መታኝ፣— እርሱ፣ ወንበር፣ ተቀምጧል፣— እርሱ፣ ልጁ፣ ይጫወታል። ተብሎ፣ ቢነገር፣ ኖሮ፣ ትክክለኛ፣ ንግግር፣ ሊሆን፣ ባልቻለም፣ ነበር። ስለዚህም፣ መስተዋድድ፣ የንግግርን፣ ዝምድና፣ የሚያሳይ፣ ቃል፣ ነው። መስተዋድድ፣ የሚያርፍበትም፣ ስም፣ የመስተዋድድ፣ ተሰቢ፣ ወይም፣ ተገዢ፣ ይባላል።

— 239 —

የመስተዋድድ ፡ አመጻደብ ፡

መስተዋድዶች ፡ በየሙያቸው ፡ ሲነገሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይመደባሉ ።

(ሀ) ፡ መነሻ ። — ከ . . .

አጅ ፡ ከጎንደር ፡ መጣ ።

(ለ) ፡ መገስገሻ ። — ወደ ፡ እ ፡ . . .

አጅ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እሄዳለሁ ። እቤቱ ፡ እሄዳለሁ ።

(ሐ) ፡ መድረሻ ። እስከ ፡ ድረስ ። (ወይም ፡ እስከ ፡ . . . ድረስ ፡) . . .

አጅ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ (ወይም ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡) አታገግለው ?

(መ) ፡ ማድረጊያ ። — በ ፡ . . .

አጅ ፡ በዱላ ፡ መታኝ ።

(ሠ) ፡ አጫፋሪ ። — ከ— ጋር ፡

አጅ ፡ እርሱ ፡ ከልጁ ፡ ጋር ፡ ይጫወታል ።

(ረ) ፡ ማንጸሪያ ። — እንደ ፡ . . .

አጅ ፡ አገሪቱ ፡ መልካም ፡ ናት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ አይደለችም ።

ማስገንዘቢያ ። — ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉት ፡ ምዳቤዎች ፡ በቅኔ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተለመዱ ፡ በለሆኑ ፡ የዋንኩን ፡ ለማሳየት ፡ ስንል ፡ ጽፈናቸዋል ። ከነዚህም ፡ በቀር ፡ «ለ ፡ አቀባይ ፡ — የ ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥ» ፡ . . . የሚባሉ ፡ አሉ ።

በአዲሱ ፡ አካሄድ ፡ ግን ፡ «የበታ ፡ — የጊዜ ፡ — የምክንያት ፡ . . . » እየተባሉ ፡ ይመደባሉ ። (በአገባብ ፡ ተመልከት ።)

— 240 —

የመስተዋድድ ፡ ቃላት ፡ አብዛኞቹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉት ናቸው ።

በስተ ፡ መነሻ ፡ የሚገቡት ፡ — ለ ፡ — በ ፡ — ተ ፡ — ከ ፡ — ወደ ፡ — እ ፡ — እስከ ፡ — እንደ ፡ — ስለ ፡ — በስተ ፡ — ያለ ፡ — . . . ናቸው ።

ምሳሌ ፡ — መጽሐፉን ፡ ለ ፡ በቀለ ፡ ሰጠው ።

ከጎንደር ፡ (ወይም ፡ ተጎንደር ፡) መጣ ።

ወደ ፡ ቤቱ ፡ (ወይም ፡ እቤቱ ፡) ገባ ።

እኔ ፡ እስከ ፡ ጎጃም ፡ እሄዳለሁ ።

እናንተም ፡ እንደእኔ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁኑ ።

እርሱ ፡ ስለ ፡ አብ ፡ ይናገራል ።

በሐይ ፡ በስተ ፡ ምሥራቅ ፡ ትወጣለች ።

ያለ ፡ አባቱ ፡ የሚያስብልኝ ፡ የለም ።

— 241 —

ተሰቢሙን ፡ ወይም ፡ ተገርሙን ፡ ቃል ፡ በመከከል ፡ አድርገው ፡ በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ የሚገቡ ፡ መስተዋድዶች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። በስተ ፡ መነሻ ፡ ከሚገኙት ፡ ዋነኞቹ ፡ በ ፡ ከ ፡ ወደ ፡ ናቸው ። ይህንኑም ፡ ለምሳሌ ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

የበታ ፡ መስተዋድዶች ፡ (※ ይህ ፡ ምልክት ፡ ያለባቸው ፡ ቃላት ፡ እንደቡ ፡ የበታ ፡ እንደቡ ፡ የጊዜ ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ።)

በ . . ላይ ፡ ※	ከ . . ላይ ፡ ※	ከ . . በላይ ፡ ※	ከ . . በስተ ፡ ላይ ፡	ወደ . . ላይ ፡
በ . . ሥር ፡	ከ . . ሥር ፡	ከ . . በታች ፡ ※	ከ . . በስተ ፡ ታች ፡	ወደ . . ውስጥ ፡
በ . . ውስጥ ፡ ※	ከ . . ውስጥ ፡ ※	ከ . . በውጭ ፡	ከ . . በስተ ፡ ውስጥ ፡	ወደ . . አጠገብ ፡
በ . . ውጭ ፡	ከ . . ውጭ ፡	ከ . . በአፍአ ፡	ከ . . በስተ ፡ ውጭ ፡	ወደ . . ዘንድ ፡
በ . . አጠገብ ፡	ከ . . አጠገብ ፡	ከ . . በፊት ፡ ※	ከ . . በስተ ፡ ፊት ፡	ወደ . . ጋ ፡
በ . . ዘንድ ፡	ከ . . ዘንድ ፡	ከ . . አስቀድሞ	ከ . . በስተ ፡ ኋላ ፡	ወደ . . ዳር ፡
በ . . ጋ ፡	ከ . . ጋ ፡	ከ . . በኋላ ፡ ※	ከ . . በስተ ፡ ዳር ፡	ወደ . . ማዶ ፡
በ . . ፊት ፡	ከ . . ፊት ፡	ከ . . በኩል ፡ ※	ከ . . በስተ ፡ ማዶ ፡	(ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡)
በ . . ኋላ ፡	ከ . . ኋላ ፡	ከ . . ሳን ፡	ከ . . ጀምሮ ፡	
በ . . አቅራቢያ	ከ . . አቅራቢያ	ከ . . ባሻገር ፡	ከ . . ቀጥሎ ፡	
በ . . መከከል	ከ . . መከከል ፡	ከ . . ማዶ ፡	ከ . . ለጥቆ ፡	

የምክንያትና ፡ የአኳኋን ፡ መስተዋድዶች ።

ስለ ፡ . . ነገር ፡	ከ . . በቀር ፡	ከ . . ጋር ፡
በ . . . ነገር ፡	ከ . . በስተቀር ፡	ከ . . ሌላ ፡

— 242 —

ከዚህ ፡ በላይ ፡ (ቁ.241) የተነገሩት ፡ መስተዋድዶች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ መነሻ ፡ ሆው ፡ አየቀረ ፡ በዘልማድ ፡ መድረሻቸው ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ።

አጅ ፡ — እርሱ ፡ አገሩ ፡ ላይ ፡ ተሾሞአል ፡ (=በአገሩ ፡ ላይ ፡)

እርሱ ፡ አባቱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጠ ፡ (=ከአባቱ ፡ ዘንድ ፡)

ዛሬ ፡ ችሎት ፡ ላይ ፡ አየሁት ፡ (=በችሎት ፡ ላይ ፡)

— 243 —

ከ . . . ጋር ፡ — የተባለው ፡ ቃል ፡ በግዕዙ ፡ ሰዋስው ፡ ምስለ ፡ የሚባለው ፡ ነው ። ወደ ፡ አማርኛም ፡ ሲገለበጥ ፡ ጋራ ፡ ይባላል ።

አጅ ፡ —ኢትትዋነይ ፡ ምስለ ፡ ደቂቅ ፡ =ከልጆች ፡ ጋራ ፡ አትጫወት ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ጋራ ፡ የሚለው ፡ ጋር ፡ እንዳባል ፡ መስነናል ። ምክንያቱም ፡ ጋራ ፡ እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በተራራነት ፡ ስለሚነገር ፡ የቃሉን ፡ ሞክሸነት ፡ ለመለየት ፡ ሲባል ፡ ነው ።

— 244 —

ከወደ ፤ አቅጣጫን ፣ የሚያመለክት ፣ ድርብ ፣ የበታ ፣ መስተዋድድ ፣ ነው ። ትርጓሜው ፣ በኩል ፣ ወይም ፣ ዘንድ ፣ ማለት ፣ ነው ።

አጅ ፣ —ከወደ ፣ ጎንደር ፣ መጣ ። =ከጎንደር ፣ በኩል ፣ መጣ ።

ሌሎችም ፣ መስተዋድዶች ፣ እንደዚሁ ፣ ተደራርበው ፣ ሲገቡ ፣ ይገኛሉ ።

— 245 —

ጋ ፣ አጠገብነትን ፣ የሚያመለክት ፣ የበታ ፣ መስተዋድድ ፣ ነው ።
ትርጓሜው ፣ አጠገብ ፣ ወይም ፣ ዘንድ ፣ ማለት ፣ ነው ።

አጅ ፣ እርሱ ፣ እዛፉ ፣ ጋ ፣ (=እዛፉ ፣ አጠገብ ፣ ወይም ፣ ዘንድ ፣) ተቀምጧል ።

ጋ ፣ የተባለውን ፣ ቃል ፣ በንግግር ፣ የሚያዘወትሩ ፣ የሸዋ ፣ ባላገሮች ፣ ናቸው ። ምሁራኑም ፣ እንደ ፣ ጸያፍ ፣ ያዩበቸዋል ። ጸሩ ፣ ግን ፣ ጋ ፣ ጸያፍ ፣ ሊባል ፣ አይቻልም ። ፈራስጌ ፣ እግርጌ ፣ አንገትጌ ፣ ተብሎ ፣ በተነገረ ፣ ጊዜ ፣ ጌ ፣ አጠገብነትን ፣ የሚያመለክት ፣ እንደሆነ ፣ አውንም ፣ «እዛፉ ፣ ጋ ፣ » ወይም ፣ «ከዛፉ ፣ ጋ ፣ » በለ ፣ ጊዜ ፣ አጠገብነትን ፣ የሚያመለክት ፣ ነው ።

— 246 —

ስሞች ፣ ወይም ፣ ስሞችን ፣ መስለው ፣ የሚገኙ ፣ ነገሮች ፣ የ ፣ በሚባል ፣ ቃል ፣ ተገጣጥመው ፣ ይነገራሉ ። የ ፣ የሚወድቅበትም ፣ ቃል ፣ ዘርፍ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። (ቁ. 43 ፣ አይ ።)

አጅ ፣ —የሰማይ ፣ ከከብ ፣ ያበራል ።
የምድር ፣ ባቡር ፣ ፈጣን ፣ ነው ።
የአንግሊዝ ፣ አገር ፣ ደሴት ፣ ነው ።

— 247 —

ዘርፍ ፣ አያያዝ ፣ የ ሌሎች ፣ መስተዋድዶች ፣ በተደረበቡበት ፣ ጊዜ ፣ ተውጦ ፣ ይቀራል ።

አጅ ፣ ለሰማይ ፣ ከከብ ፣ ሰገደ ።
በምድር ፣ ባቡር ፣ ተሳፈረ ።
ወደ ፣ እንግሊዝ ፣ አገር ፣ ሄደ ።

ሌሎችም ፣ በመጨረሻ ፣ የሚገቡ ፣ መስተዋድዶች ፣ እንደዚሁ ፣ እየተደረቡ ፣ በገቡ ፣ ቁጥር ፣ የ ን ፣ ውጠው ፣ ያስቀሩታል ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ የ ፣ ውስጠ ፣ ታዋቂ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። (ቁ. 43 አይ ።)

— 248 —

« ለ ፤ ላ ፤ ል ፤ በ ፤ ባ ፤ ብ ፤ » በአጸፎች ፣ ተውላጣተ ፣ ስም ፣ ላይ ፣ እየተጨመሩ ፣ በግሥ ፣ መድረሻ ፣ ላይ ፣ ይገባሉ ። (ቁ. 72 ፣ አይ ።)

ለ ፣ የበን ፣ በ ፣ የክፉ ፣ መፍቻ ፣ ይሆናሉ ። ሁሉም ፣ የምክንያት ፣ መስተዋድዶች ፣ ናቸው ።

አጅ 1 መጣለት ፣ መጣላት ፣ መጣልኝ ፣ . . . .
መጣበት ፣ መጣባት ፣ መጣብን ፣ . . . .

— 249 —

መስተዋድድና ፣ ተውሳከ ፣ ግሥ ። ያው ፣ አንዱ ፣ ቃል ፣ እንጂ ፣ መስተዋድድ ፣ ወይም ፣ እንደ ፣ ተውሳከ ፣ ግሥ ፣ ሆኖ ፣ ሲገባ ፣ ይገኛል ።

አጅ ፣ እርሱ ፣ ከአብርሃም ፣ በፊት ፣ ይሄድ ፣ ነበር ፣ (መስተዋድድ)
እርሱን ፣ በፊት ፣ (=ዱሮ ፣) አላወቀውም ፣ ነበር ፣ (ተውሳከ ፣ ግሥ)

— 250 —

የመስተዋድድ ፣ ተሰቢዎች ።

መስተዋድድ ፣ ከስምና ፣ ከተውላጠ ፣ ስም ፣ ሌላ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ሌሎችንም ፣ የንግግር ፣ ክፍሎች ፣ ሲስብ ፣ ወይም ፣ ሲገዛ ፣ ይገኛል ። በዚህ ፣ አኳኋን ፣ የሚነገሩትም ፣ ቃላት ፣ ስም ፣ መሰሎች ፣ ተብለው ፣ ይጠራሉ ። ይህንኑም ፣ በሚከተለው ፣ እናሳያለን ።

ቅጽል ።

ክፉን ፣ በክፉ ፣ አትቃወሙት ።
ላለፈ ፣ ክረምት ፣ ቤት ፣ አይሠራም ።

ተውሳከ ፣ ግሥ ።

ለሁልጊዜ ፣ አትለየኝ ።
ለወደፊት ፣ እንተዋወቅ ።

ግሥ ።

በጠንብሁ ፣ (=ጠንብሁ ፣ በማለት ፣) ጠብ ፣ የለም ።
በይመስላል ፣ (=ይመስላል ፣ በማለት) አይፈረድም ።
ሰው ፣ ሁሉ ፣ ለመስማት ፣ የፈጠነ ፣ ለመናገር ፣ የዘገየ ፣ ይሁን ።

፲፩ኛ ፣ መልመጃ ።

(ሀ) ከዚህ ፣ በታች ፣ ከተጻፉት ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሮች ፣ ውስጥ ፣ መስተዋድዶችን ፣ እየለየህ ፣ አመልክት ።

በወንበር ፣ ላይ ፣ ተቀመጠ ። —መጽሐፉን ፣ ለልጁ ፣ ሰጠ ። —በጹላ ፣ መታኝ ። በዛፍ ፣ ሥር ፣ ዐረፈ ። —ትምህርቴን ፣ በጀመር ፣ ውስጥ ፣ እጨርሳለሁ ። —ትምህርት ፣ በሰነርች ፣ ዘንድ ፣ የተጠላ ፣ ነው ። —በዕውር ፣ ፊት ፣ ዕንቅፋትን ፣ አታድርግ ። —ልጅ ፣ በአባቱ ፣ አጠገብ ፣ ይቀመጣል ። —እወንዙጋ ፣ አይቼዋለሁ ። —ቤቴ ፣ በገበያ ፣ አቅራቢያ ፣ ነው ። —በሕዝብ ፣ መካከል ፣ ተናገረ ። —ከመሬት ፣ ላይ ፣ ወደቀ ። —ከእናቱ ፣ ዘንድ ፣ መጣ ። —ከሰው ፣ በታች ፣ ሆነ ። —ከራስ ፣ በላይ ፣ ነፋስ ፣ ነው ። —እግዚአብሔርን ፣ የማያምኑ ፣ ከሃይማኖት ፣ በእፍኣ ፣ ያሉ ፣ ናቸው ። —ከአብርሃም ፣ ፊት ፣ ቆሞ ፣ እየሁት ። —ከእ ፣ ወር ፣ በኋላ ፣ እመለሳለሁ ። —ከቤቱ ፣ ጎን ፣ ዛፍ ፣ አለ ። —ከሕዝብ ፣ መካከል ፣ ተመረጠ ። —ከወንዝ ፣ ባሻገር ፣ (ወይም ፣ ማዶ ፣) መጣ ። —ወንድሜን ፣ ከሸለቆው ፣ በስተላይ ፣ አየሁት ። —ገበየሁ ፣ ከቤቱ ፣ በስተ ፣ ውስጥ ፣ ነበረ ። —እኔ ፣ ከአጀቡ ፣ በስተ ፊት ፣ እሄድ ፣ ነበር ። —ከእንድ ፣ ዓመት ፣ ጀምሮ ፣ እንተዋወቃለን ። —ከውጪ ፣ ቀጥሎ ፣ ገቦማነህ ፣ ቆሟል ። —ከጅሩ ፣ ለጥቆ ፣ ላምዋሽ ፣ ይገኛል ። —ወደ ፣ ዛፍ ፣ ላይ ፣ ሲወጣ ፣ አየሁት ። —ወደ ፣ እናቱ ፣ ዘንድ ፣ እሄዳለሁ ። —ስለ ፣ ፈለቀ ፣ ነገር ፣ የማውቀውን ፣ ልንገርህ ። —እርሱ ፣ በትምህርት ፣ ነገር ፣ ትጉህ ፣ ነው ። ከገቦማነህ ፣ በቀር ፣ የሚበልጠው ፣ የለም ። —ከኃጢአት ፣ በስተቀር ፣ ሁሉን ፣ ፈጸመ ። —ከተማሪው ፣ ጋር ፣ መጣ ። —ከዮሐንስ ፣ ሌላ ፣ ዘመድ ፣ የለውም ።

(ለ) ከዚህ ፣ በታች ፣ በተጻፉት ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሮች ፣ ውስጥ ፣ የሚገኘውን ፣ ባዶ ፣ ባዶውን ፣ ስፍራ ፣ በተስማሚው ፣ መስተዋድድ ፣ እየሞላህ ፣ ተናገር ።

መኩንን ። —ሎንዶን ፣ መጣ ። ፈረሱ ። —ሜዳ ፣ ይሮጣል ። ፈረሱን ፣ —አለንጋ ፣ መታው ። እጁን ፣ —ጠረጴዛ ። —አኖረ ። እኔ ፣ —አባቴ ። —እሄዳለሁ ። ማታ ። —ቤቴ ፣ እመለሳለሁ ። አስተማሪው ። —ኢትዮጵያ ። —ይተርክል ። እርሱ ። —ተማሪዎቹ ፣ ሽልማትን ፣ ይሰጣል ። ልጅ ። —አባቱ ። —ይኖራል ። ዕውር ። —መሬው ። —አይሄድም ። ለትጉህ ፣ ልጅ ። —ፊት ። —ዳረጎት ፣ ይጨመርለታል ።

፲፪ኛ ፣ ምዕራፍ ፣ ፫ ፣ መስተዋምር ።

— 251 —

መግለጫ ።

መስተዋምር ፣ የሚባለው ፣ ቃላትንና ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሮችን ፣ ለማያያዝ ፣ ወይም ፣ ለማጣመር ፣ የሚጠቅም ፣ ቃል ፣ ነው ። መስተዋምር ፣ በአንቀጽ ፣ ላይ ፣ እያረፈ ፣ የአንቀጹን ፣ ግሰሪያነት ፣ ያስቀረዋል ።

ምሳሌ ፦
(ሀ)
- እርሱ ፣ ይጫወታል ፤ እርስዋም ፣ ትዘፍናለች ።
- ነገ ፣ ወደ ፣ ተማሪ ፣ ቤት ፣ እሄዳለሁ ፤ ወይም ፣ ከቤቱ ፣ እውላለሁ ።
- አባቱ ፣ ይቀጣኛል ፤ ይሁን ፣ እንጂ ፣ በጣም ፣ ያዝንልኛል ።

(ለ)
- የመጣህ ፣ እንደሆን ፣ አብረን ፣ እንሄዳለን ።
- ቢፈልግ ፣ ይስጠኝ ፣ ባይፈልግ ፣ ይተወው ።
- መጨረሻውን ፣ ሳላይ ፣ አልቀየምም ።

እነሆ ፤ «ም ፣ ወይም ፣ ይሁን ፣ እንጂ ፤ የ—እንደሆን ፣ ቢ ፣ ባ ፣ ሳ ፣» የተባሉት ፣ ቃላት ፣ መስተዋምሮች ፣ ናቸው ። በመጀመሪያው ፣ ክፍል ፣ (ሀ) በሚለው ፣ ላይ ፣ እንደተመለከተው ፣ በየራሳቸው ፣ ሊነገሩ ፣ የሚችሉትን ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሮች ፣ መስተዋምሮቹ ፣ እንዲያያዙ ፣ አድርገዋቸዋል ። (ለ) በሚለው ፣ ክፍል ፣ እንደተመለከተው ፣ መስተዋምሮቹ ፣ በየአንቀጻቸ ፣ ላይ ፣ ተጭነው ፣ ግሰሪያነትን ፣ እያስቀሩ ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሩን ፣ እያይዘውታል ።

ስለዚህም ፣ መስተዋምር ፣ ቃላትንና ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሮችን ፣ ለማጣመር ፣ የሚጠቅምና ፣ የአንቀጹን ፣ ግሰሪያነት ፣ የሚያስቀር ፣ ቃል ፣ ነው ፣ ብለን ፣ እንወስናለን ።

— 252 —

መስተዋምር ፣ በሁለት ፣ ክፍሎች ፣ ይከፈላል ። እነርሱም ፣ የሚከተሉት ፣ ናቸው ።

(ሀ) ወደረኛ ፣ መስተዋምር ።

(ለ) ጥገኛ ፣ መስተዋምር ።

እነዚህ ፣ ደግሞ ፣ እንደገና ፣ በንኡስ ፣ ክፍሎች ፣ እየተከፋፈሉ ፣ ይነገራሉ ።

— 253 —

(ሀ) ፣ ወደረኛ ፣ መስተዋምር ።

ወደረኛ ፣ ማለት ፣ ተተካካይ ፣ ወይም ፣ ተመሳሳይ ፣ ማለት ፣ ነው ። በዚህ ፣ ክፍል ፣ የሚነገረው ፣ ቃል ፣ ያለ ፣ መስተዋምር ፣ ቢነገር ፣ ኖሮ ፣ መደበኛውን ፣ ቃል ፣ በማዕርግ ፣ የሚተካከለው ፣ ስለሆነ ፣ ወደረኛ ፣ ተብሎአል ። እነሆ ፣ ከላይ ፣ ቁ. 251 (ሀ) ለምሳሌ ፣ የተጻፉት ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሮች ፣ ያለ ፣ መስተዋምር ፣ ሲነገሩ ፣ እንደሚከተለው ፣ ይሆናሉ ።

ምሳሌ ። እርሱ ፡ ይጫወታል ። እርስዋ ፡ ትዘፍናለች ።
ነገ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እሄዳለሁ ። ከሴቱ ፡ እውላለሁ ።
አበቱ ፡ ይቀጣኛል ። በጣም ፡ ያዝንልኛል ።

እነሆ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ የዐረፍተ ፡ ነገርነትን ፡ ምጣር ፡ እንይያዙ ፡ አስተውል ።

— 254 —

ወደረኛ ፡ መስተፃምር ፡ በአረት ፡ አከሄድ ፡ ይመደባል ።
(1) አጫፋሪ ፡ ወይም ፡ አዳጋሚ ።
(2) አማራጭ ፡ ወይም ፡ አወላዋይ ፡
(3) አፍራሽ ፡ ወይም ፡ ተቃራኒ ፡
(4) ምክንያታዊ ።
እነዚህንም ፡ በያንዳንዳቸው ፡ እየዘረዘርን ፡ እንጽፋለን ።

— 255 —

(1) አጫፋሪ ፡ ወይም ፡ አዳጋሚ ።

አጫፋሪ ፡ የተበለው ፡ አንዱንና ፡ ሌላውን ፡ ቃል ፡ የሚያጋጥም ፡ ነው ። ይኸ ውም ፡ በግስዙ ፡ ሰዋስው ፡ ዋዊ ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

አዳጋሚ ፡ የሚባለውም ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሩ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በመስተፃምር ፡ ሲያገም ፡ ነው ። ሁሉንም ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

አጅ ። ''ና'' ። — አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ የአክሱም ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ።
ማሰንንዘቢያ ። ከመምህራን ፡ ወገን ፡ እና ፡ ተብሎ ፡ እንዲጻፍ ፡ የሚመስኑ ፡ አሉ ።
ይኸውም ፡ —አብርሃ ፡ እና ፡ አጽብሐ ፡ ተብሎ ፡ እንዲጻፍ ፡ ማለት ፡ ነው ።
''ም'' ። እርሱ ፡ ይወደኛል ፡ ያከብረኛልም ።

ጌታውንና ፡ ተፈራ ፡ ውብሸትም ፡ ይጫወታሉ ።

ነቢያት ፡ ስለክርስቶስ ፡ ትንቢትን ፡ ተናገሩ ፡ ሐዋርያትም ፡ አስተማሩ ።
''ም''—ም ። — እርሱም ፡ እኔም ፡ በአንድነት ፡ እንጣር ፡ ነበር ።

እርሱ ፡ ቂስም ፡ ደብተራም ፡ ነው ።
''ደግሞ'' ። — እርሱ ፡ ብልህ ፡ ነው ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፤
''እንደ ፤ — ሁሉ'' ፡ ገብሬ ፡ እንደ ፡ ዠማነህ ፡ ሁሉ ፡ የተማረ ፡ ነው ።
''በቢያውም ፡ ላይ'' ፡ — እኔና ፡ ፈለቀ ፡ ጓደኞች ፡ ነን ፤ በዚያውም ፡ ላይ ፡ እንዘመጻለን ።
''ከዚያውም ፡ ዘንድ'' ። ኢትዮጵያዊ ፡ ነኝ ፤ ከዚያውም ፡ ዘንድ ፡ ጎንደሬ ፡ ነኝ ።
''ሳ ። ስ'' ። — ከበደ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ይሄዳል ፤ አንተስ ፡ (አንተስ ፡) ወዴት ፡ ትሄዳለህ ?
ማሰንንዘቢያ ፡ በዚህ ፡ ንግግር ፤ ጥያቄው ፡ ''ወዴት'' ፡ መሆኑንና ፤ ''ስ ፡ ሳ'' ፡ እንዳልሆኑ ፡ አስተውል ። ትርጓሜያቸውም ፡ « ደግሞ ፡ » እንደማለት ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

— 256 —

(2) አማራጭ ፡ ወይም ፡ አወላዋይ ።

በአንድ ፡ ነገርና ፡ በአንዳች ፡ ነገር ፡ መካከል ፡ የግግረጥ ፡ ወይም ፡ የግወላወል ፡ አኳኋን ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ መስተየምሩ ፡ አማራጭ ፡ ወይም ፡ አወላዋይ ፡ ይባላል ።

አጅ ። —''ወይም'' ፡ — ዛሬ ፡ ወይም ፡ ነገ ፡ እመጣለሁ ። (አወላዋይ ፡)
እርሳሱን ፡ ወይም ፡ ቀለሙን ፡ ስጠኝ ፡ (አማራጭ ፡)
''ወይም ፡ — ወይም'' ፡ — ወይም ፡ ዛሬ ፡ ወይም ፡ ነገ ፡ እመጣለሁ ።
ወይም ፡ እርሳሱን ፡ ወይም ፡ ቀለሙን ፡ ስጠኝ ።
''ወይ ፡ —ወይ'' ። — ወይ ፡ ዛሬ ፡ ወይ ፡ ነገ ፡ እመጣለሁ ።
''ወይ ፡ — ወይ ፤ —ወይ'' ፡ — እርሱ ፡ ወይ ፡ አልተማረ ፤ ወይ ፡ አላረሰ ፡ ወይ ፡ አልነገደ ፡ በምን ፡ ትኖር ፡ ሲኖር ፡ ነው ? ።
''ወይም ፡— ወይንም'' ። — ትጉህ ፡ ተማሪ ፡ ዜማ ፡ ወይም ፡ ቅኔ ፡ ወይንም ፡ ትርጓሜ ፡ ይማራል ።
''አለዚያም ፡ — አለበለዚያም'' ። — ትምህርታችንን ፡ እናጥና ፤ አለዚያም ፡ (አለበለዚያም) ፡ እንጫወት ።
''ሆነ'' ። በሞት ፡ ሆነ ፡ በሕይወት ፡ የሰው ፡ ክብሩ ፡ አገሩ ፡ ነው ።
''ይሁን'' ። ወንድሜ ፡ ዛሬ ፡ ይሁን ፡ ነገ ፡ በባቡር ፡ ይመጣል ።
''ቢሆን'' ፡ ሕይወት ፡ ቢሆን ፡ ሞት ፡ ቢሆን ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ የሚያስተወኝ ፡ የለም ።

— 257 —

(3) አፍራሽ ፡ ወይም ፡ ተቃራኒ ።

አፍራሽ ፡ የሚባለው ፤ የነገሩን ፡ አኳኋን ፡ በአፍራሽነት ፡ ወይም ፡ በተቃራኒነት ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ነው ።

አጅ ፡

''ነገር ፡ ግን'' ፡ — እኔና ፡ አብርሃም ፡ በውልደት ፡ እኩዮች ፡ ነን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አብርሃም ፡ በቁመት ፡ ይበልጠኛል ።
''ግን'' ። እኔ ፡ አጭር ፡ ነኝ ፡ አብርሃም ፡ ግን ፡ (ወይም ፡ ግን ፡ አብርሃም) ፡ ረጅም ፡ ነው ።
''ጻሩ ፡ ግን'' ። — ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ አንብቤ ፡ ነበር ፤ ጻሩ ፡ ግን ፡ አላስታውሰውም ።
''ስ'' ። —እውነትን ፡ መናገር ፡ ያስከብራል ፤ ሐሰትስ ፡ ያዋርዳል ።
እርሱ ፡ ይመጣ ፡ አይመስለኝም ፤ ከመጣስ ፡ (= ከመጣ ፡ ግን ፡ ወይም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከመጣ ፡) እቀበለዋለሁ ።
''ይሁን ፡ እንጂ ። ይሁንና ። የሆነ ፡ ሆኖ ። ቢሆንም ... ። ሥራህን ፡ መልከም ፡ ትሠራለህ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ (ወይም ፡ ይሁንና ፡ .....) በሥራህ ፡ አትመክ ።

''ግና ፣ ቢሆን'' ፣ —እርሱ ፣ በደለኝ ፣ ይለኛል ፤ ግና ፣ ቢሆን ፣ አልበደልሁትም ።
''እንኚ'' ። ወደ ፣ መከራ ፣ አታግባን ፤ ከክፋ ፣ አድነን ፣ እንኚ ።
እድናለሁ ፣ እንኚ ፣ አልሞትም ።
''ብቻ'' ። ''ብቻ'' ። —አይዘህ ፣ ገንዘብህን ፣ እከፍልሃለሁ ፤ ብቻ ፣ ታገሠኝ ።
''ሆኖም ፣ ብሎም'' ። —ዘለቀ ፣ ብስጩ ፣ ነው ፤ ሆኖም ፣ (ወይም ፣ ብሎም ፣)ሆደ ፣ ገር ፣ ነው ።

—258—

(4) ምክንያታዊ ፣

(ሀ) ምክንያትን ፣ ሰጪ ።
''ና'' ። —ለሰሙ ፣ ትዕግሥት ፣ ይገባዋል ፤ ክብር ፣ የሚገኝ ፣ በትዕግሥት ፣ ነውና ፤
''ከዚህ ፣ የተነሣ'' ። —ታደሰና ፣ ዘለቀ ፣ ጓደኞች ፣ ናቸው ። ከዚህም ፣ የተነሣ ፣ ይፋቀራሉ ።
(ለ) ምክንያትን ፣ ተርጓሚ ፣ (ወይም ፣ ምኞትና ፣ ጸጸት ፣)
''እንዲህ ፣ ከሆነ'' ፣ ሕግን ፣ ያልጠበቀ ፣ ይፈረድበታል ። እንዲህ ፣ ከሆነ ፣ ሕግን ፣ እንጠብቅ ።
''እንግዲያ'' ። ጊዜው ፣ መሽቶአል ፤ እንግዲያ ፣ በየቤታችን ፣ እንግባ ።
''ታዲያ'' ። እኔ ፣ ማደሪያ ፣ የለኝም ። ታዲያ ፣ ከምን ፣ ታድራለህ ? ፣
ማስገንዘቢያ ፣ እነዚህ ፣ ቃላት ፣ ስ ፣ የሚለው ፣ አፍራሹ ፣ መስተፃምር ፣ እየ ፣ እየተጨመረላቸውና ፣ አያጋነናቸው ፣ ይነገራሉ ። ይኸውም ፣ «እንዲህስ ፣ ከሆነ ፣ እንግዲያስ » ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ።
''እገኪያ'' ፣ እርሱ ፣ ብዙ ፣ መጽሐፍ ፣ አለው ። እንኪያ ፣ ለምን ፣ አይማርም ?
''እንግዲያማ'' ፣ አሁን ፣ ገንዘብ ፣ የለኝም ፤ እንግዲያማ ፣ እሰጥህ ፣ ነበር ።

—259—

(ለ) ጥገኛ ፣ መስተፃምር ፣

ጥገኛ ፣ ማለት ፣ ራሱን ፣ ያልቻለ ፣ ወይም ፣ ከሌላው ፣ በታች ፣ ሆኖ ፣ የሚያድር ፣ ማለት ፣ ነው ። በዚህ ፣ ክፍል ፣ የሚነገረው ፣ የሰዋስው ፣ ቃል ፣ ከመደበኛው ፣ ዐረፍተ ፣ ነገር ፣ እየተጠጋ ፣ የሚነገር ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ጥገኛ ፣ ተብሏል ።

ምሳሌ	ጥገኛ	መደበኛ ፣
	ዓለም ፣ እንደ ፣ ተፈጠረ ፣	በሃይማኖት ፣ እናውቃለን ፣
	አስተማሪውን ፣ ስለ ፣ ፈራ ፣	ጠንክሮ ፣ ይማራል ።
	ገንዘቤን ፣ ቢሰጠኝ ፣	እቀበላለሁ ።
	ብወድቅም ፣ እንኳ ፣	እነሣለሁ ።

ጥገኛ ፣ መስተፃምር ፣ ሁልጊዜ ፣ በአንቀጽ ፣ ላይ ፣ እየተጫነ ፣ መግባት ፣ አለበት ። ከሁን ፣ በፊት ፣ በቅጽልና ፣ በአዋዋይ ፣ አንቀጽ ፣ ክፍል ፣ ተነግረው ፣ ከነበሩትም ፣ ቃላት ፣ አንዳንዶቹ ፣ በየጠቢያቸው ፣ ከዚህ ፣ ይገኛሉ ።

—260—

በጥገኛ ፣ መስተፃምር ፣ ክፍል ፣ ከሚነገሩት ፣ ቃላት ፣ ዋነኞቹ ፣ «እንደ ፣ ስለ ፣ ሲ ፣ በ ፣ ከ ፣ የ» ናቸው ። በአፈዴል ፣ የሚነሣ ፣ ቀለም ፣ በ-ኮ-ኮ-ላቸው ፣ ቁጥር ፣ መድረሻቸው ፣ ወደ ፣ ራ-ብዕንት ፣ ይልወጣል ።

አንጻር ፣ ወይም ፣ ማንጸሪያ ።

እንደ ፣	ፈቃድህ ፣ በሰማይ ፣ እንደሆነ ፣ እንዲሁም ፣ በምድር ፣ ይሁን ።
	ዓለም ፣ እንደተፈጠረ ፣ በሃይማኖት ፣ እናውቃለን ።
እንዲ ፣	እንደ ፣ ሰማን ፣ ሁሉ ፣ እንዲሁ ፣ አየን ፣
	አባት ፣ ለልጁ ፣ እንዳራራ ፣ እግዚአብሔርም ፣ ለወዳጆቹ ፣ እንዲሁ ፣ ይራራላቸዋል ።
	ክርስቶስ ፣ በምስጋና ፣ እንዲመጣ ፣ እናምናለን ።
እንዳ ፣	በዚህ ፣ ነገር ፣ እንዳልገባህበት ፣ በእውነት ፣ እናገራለሁ ።
	ነገሩ ፣ ሳይገለጽ ፣ እንደማይቀር ፣ አምናለሁ ።

ምክንያትን ፣ አመልካች ።

ስለ ፣	አስተማሪውን ፣ ስለፈራ ፣ ተገቶ ፣ ይማራል ።
	አስተማሪውን ፣ ስለሚፈራ ፣ ቶሎ ፣ ቶሎ ፣ ያጠናል ።
ና ፣	ትምህርትን ፣ ፈልጓልና ፣ ከተማሪ ፣ ቤት ፣ አይለይም ።
	ትምህርትን ፣ ይፈልጋልና ፣ ያጠናል ።
ከ—ዘንድ ፣	ትምህርትን ፣ ከወደደ ፣ ዘንድ ፣ ማጥናት ፣ ይገባዋል ።

ሁኔታን ፣ አመልክች ።

እየ ፣ እያ ፣	በየስፍራው ፣ እየቆመ ፣ ይሄዳል ።
	እየጮኸ ፣ ይናገራል ። እያነበበ ፣ ያጠናል ።
ሲ ፣ ስ ፣	ሲማር ፣ ዋለ ።
	ስትማር ፣ ዋለች ።

ውለታን ፣ አመልክች ።

የ—እንደሆነ ።	መጽሐፌን ፣ የሰጠኝ ፣ እንደሆን ፣	እርሳሱን ፣ እመልስለታለሁ ።
	መጽሐፌን ፣ የሚሰጠኝ ፣ እንደሆን ፣	
ከ	መጽሐፌን ፣ ከሰጠኝ ፣	
የሚ ፣ ከ	መጽሐፌን ፣ የሚሰጠኝ ፣ ከሆነ ፣	
ቢ	መጽሐፌን ፣ ቢሰጠኝ ፣	
የሚ ፣ ቢ	መጽሐፌን ፣ የሚሰጠኝ ፣ ቢሆን ፣	
ቢ—ኖሮ	እዚህ ፣ ቢመጣ ፣ ኖሮ ፣	እንጂወት ፣ ነበር ።
ቢ—ኖሮ	እዚህ ፣ ብትመጪ ፣ ኖሮ ፣	

ድርደራን ፡ ለጭ ፡ ወይም ፡ አመላካቾች ።

ብ ፡	ነገ ፡ ብትመጣ ፡ እጠብቅሃለሁ ።
እንደሆን ፡	ትመጣ ፡ እንደሆን ፡ ልጠብቅህ ።
	ያልመጣህ ፡ እንደሆን ፡ አዝናለሁ ።
ብ—ም	ብመጣም ፡ ብቀርም ፡ አስታውቅህአለሁ ።
ቢ—ም	ቢመጣም ፡ ቢቀርም ፡ አጠብቀዋለሁ ።
ቢ—ስ	ቢመጣስ ፡ (=የመጣ ፡ እንደሆነ ፡) አቀበለዋለሁ ።
	ወንድሜ ፡ ነገ ፡ ይመጣ ፡ አይመጣ ፡ አላውቅም ።
	ይብዛም ፡ ይነስ ፡ ግብፐ ፡ አደርጋለሁ ።
ሆነ ፡	ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ለኔ ፡ እኩል ፡ ነው ።
ሆነ—ሆነ	ያም ፡ ሆነ ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ለእኔ ፡ እኩል ፡ ነው ።

አጋናኝ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡	አበቴ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢመታኝ ፡ ይወድደኛል ።
እንኳ ፡	አበቴ ፡ ቢመታኝም ፡ እንኳ ፡ ያዝንልኛል ።
ምንም ፡	ምንም ፡ ብደኽይ ፡ ታማኝ ፡ ነኝ ።
እኮ	ብወድቅም ፡ እኮ ፡ እነሣለሁ ።
ብያ	ብወድቅም ፡ ብያ ፡ እነሣለሁ ።

ጊዜን ፡ አመልካች ።

እንደ ፡	ደወሱ ፡ እንደ ፡ ተደወለ ፡ ደረስሁ ።
ሲ ፡	ደወል ፡ ሲደወል ፡ አልነበርሁም ።
ሰ ፡	ባሱር ፡ ሲመጣ ፡ እሳፈራለሁ ።
ስ ፡	ባሱር ፡ ሳይመጣ ፡ እንሰነባበት ።
እስኪ—ድረስ ፡	ስመለስ ፡ እጠይቅሃለሁ ።
እስኪ ፡ እስቲ ፡ እስከ ፡ እስተ ፡ እስቲ ፡ እስት ፡	ሜልክል ፡ እስከ ፡ ሞተች ፡ ድረስ ፡ አልወለደችም ።
	ተማሪ፡ቤት፡እስኪከፈት፡(ወይም፡ እስቲከፈት)፡እጠናለሁ።
	ትምህርቴን፡እስክጨርስ፡(እስትጨርስ፡)እማራለሁ ።
ከ ፡	ይህ ፡ ቤት ፡ ከተሠራ ፡ ቆይታል ።
ሳለ ፡	አባት ፡ ሳለ ፡ እጊጥ ፡ ፀሐይ ፡ ሳለች ፡ ሩጥ ።
በ—ጊዜ ፡	በተማርሁ ፡ ጊዜ ፡(=በምማርበት ፡ ጊዜ ፡)አልጫወትም ።
ከ—በኋላ ፡	ከተማርሁ ፡ በኋላ ፡ እጫወታለሁ ።
ከ—ጀምሮ ፡	ከተወለደሁ ፡ ጀምሮ ፡ (ወይም ፡ አንሥቶ ፡) እዚሁ ፡ ነኝ ።
ከ	ጅብ ፡ ከሄደ ፡(=ከሄደ ፡ በኋላ ፡)ውሻ ፡ ጮኸ ።

አመዛዛኝ ።

ከ	ከተማረ ፡ የተመራመረ ፡ ይብልጣል ፡ (ይልቅ ፡)
ከ.	ጅብ ፡ ከበላህ ፡(=ከሚበላህ ፡ ይልቅ ፡)ገድለኸው ፡ ተቀደስ ።
ከ	እኔ ፡ ከሞት ፡ ጠላቴ ፡ ይሙት ።
ከ—ይልቅ ፡	ከአስፈሙ ፡ ይልቅ ፡ የሚመጣው ፡ ይበልጣል ።
እንደ—መጠን ፡	እንደ ፡ አሰብሁት ፡ መጠን ፡ ሳይሆንልኝ ፡ ቀረ ።
በ—መጠን ፡	በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ እረዳሃለሁ ።
እንደ—ያህል ፡	ያልተማረ ፡ ሰው ፡ እንደሞተ ፡ ያህል ፡ ነው ።
ከ—ቁጥር ፡	በሰው ፡ ላይ ፡ የዛተ ፡ ከአደረገው ፡ ቁጥር ፡ ነው ።

— 261 —

ግልጸ ፡ «የ» ፡ ቅጽል ።

በወቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ እየተጨመሩ ፡ አንቀጹን ፡ ወደ ፡ ቅጽልነት ፡ የሚለውጡት ፡ ''የ ፡ የም'' ፡ መደበኞው ፡ ከመስተፃምር ፡ ነው ። እንደ ፡ ጊዜ ፡ ግብራቸውም ፡ እንደዱ ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ በሌላም ፡ ጊዜ ፡ መስተፃምራዊ ፡ ቅጽል ፡ ተብለው ፡ ነበር ፡ ቁ.93 ፡ (መ) ፡ 199 ፡ እይ ።) አሁን ፡ ደግሞ ፡ በደንብና ፡ ስፍራቸው ፡ ከዚህ ፡ ይንገራሉ ። የአ ፡ ፊደል ፡ ሲከተሳቸው ፡ ወደራብዕነት ፡ እየተለወጠ ፡ ''ያ ፡ የሚ'' ፡ ይሆናሉ ። ይ ፡ የሚል ፡ ፊደል ፡ ሲከተለው ፡ ''የሚ'' ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ። «የ» — የገደለ ፡ የፈለገ ፡ —
«ያ» — ያወቀ ፡ ያደረ ፡ (=የወቀ ፡ የአደረ ።)
«የም» — የምትገድል ፡ የምትፈልግ ።
«የሚ» — የሚፈልግ ፡ የሚገድል ። (=የምይፈልግ ፡ የምይገድል ።)
«የማ» — የማይፈልግ ፡ የማይገድል ።(=የምአይፈልግ ፡ የምአይገድል ።

ጥሬና ፡ መልመጃ ።

(ሀ) ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተጻፉት ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ መስተፃምሮቹን ፡ እየለየህ ፡ አመልክት ።

እኔና ፡ እርሱ ፡ እንድፋለን ፤ እርስዋም ፡ ታነብለች ። እኔም ፡ እርሱም ፡ እርስዋም ፡ እንማራለን።—አስተማሪው ፡ ይወድደኛል ፤ ያዝንልኛልም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከትምህርት ፡ ስቀር ፡ ይገሥጸኛል ።—ጨዋታን ፡ እወዳለሁ ፤ ቢሆንም ፡ ትምህርቴን ፡ አጠናለሁ ።—በፈተና ፡ ማን ፡ እንደሚበልጥ ፡ አላውቅም ፡ ወይ ፡ እኔ ፡ ወይ ፡ እርሱ ፡ እንሸለማለን ።—ያም ፡ ሆነ ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ወደፈት ፡ ይታያል ።—ጓደኛ ፡ ኪበልጥ ፡ ተግቶ ፡ መማር ፡ ይሻላል ።

(ለ) ወደ ረኛ ፡ የተባለውንና ፡ ጥገኛ ፡ የተባለውን ፡ መስተፃምር ፡ በምሳሌ ፡ አመ ልክት ።—ገረ ፡ የመስተፃምር ፡ ቃላት ፡ ጸሎ ፡ እነርሱንም ፡ በወረዳቱ ፡ ነገር ፡ እየሞላህ ፡ ተናገር ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ።

— 262 —

መግለጫ ።

ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ከሌሎች ፡ የንግግር ፡ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ ግንኙነትን ፡ አያደርግም ፤ በአሳብ ፡ የሚሰማ ፡ አንዳች ፡ ነገርን ፡ በማጋነን ፡ ድምፅ ፡ እየገለጸ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ጸንቶ ፡ ይነገራል ።

ስለዚህም ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፤ አንዳች ፡ ነገር ፡ በማጋነን ፡ ድምፅ ፡ የሚገለጽበት ፡ ቃል ፡ ነው ።

— 263 —

የቃለ ፡ አጋኖ ፡ ዓይነቶች ።

የአማርኛ ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ አብዛኛውም ፡ የፈደል ፡ ምልክት ፡ ሳይኖረው ፡ በድምፅ ፡ ብቻ ፡ ስለሚሰማ ፡ ዓይነቱን ፡ ለመወሰን ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆናል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዋነኞቹን ፡ ክፍሎች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ጽፈን ፡ እንመድባለን ።

አክብሮት ፡ —« ሆይ ! አቤቱ ! »
መገረምና ፡ መደነቅ ።—«ሆሆይ ፡ ! ጉድ ! ወዮ ! ወይጉድ ! እረጉድ ! ፡ እረግኝ !— ጉድ ፡ ነው ! ግሩም ፡ ነው ! »
ድንጋጤ ። ! — «ውይ ! ወይኔ ፡ ወይዛሬ ! »
ደስታ ። «— አሰይ ! አልል ! አሰይ ! አሰይ ! አልል ! አልል ! አልልል....
ትክዜ ፡ ወይም ፡ ጎዘን ። —«አዬ ! አዬጉድ ! አህህ ! »
ጩኸትና ፡ ልቅሶ ። —አሌ !...አዬዬ ! ውይ ፡ ውይ ! »
ዕረፍት ። «እፎይ ! —ተመስገን ! »
ሰላምታ ። —«ጤና ፡ ይስጥልኝ ! »
መሳቅ ። —ሀ ሀ ሀ ፡ ሀ ሀ ሀ ! »
ትዝታ ።—«እኽ ! እሀ ! እረግ ! »
ዛቻ ።—«ቆይ ! ቆይ ፡ ብቻ ! ግደየለም ! »
ማገላመስ ።—«ጉሽ ! ውሽን ! አበጀህ ! ያሳድግህ ! »
ማረጋገጥ ። —«እንዲታ ! አክ ! »

ጥቆማ ። — እነሆ ! ይኸው ! ይኸውና ! ያውና ! »
ማስፈራራት ። —« ዋ ! ጉድ ፡ ፈላ ! መጣልሃ ! ይኸውልሃ ! »
አጠራጣሪ ። — « እንጃ ! ይሆናላ ። »
ንቀት ፡ ወይም ፡ ብስጭት ። —« ኤዲያ ! (=ወዲያ ፡) ኤጭ ! አይ ! አይወዲያ »
ጥሪ ። — አሎ ! አረበል ! አረገሌ ! (=አገሌ ፡ ሆይ) »
የጥሪ ፡ መልስ ። — አቤት ! አሜት ! (=እመቤት ፡) »
ከነዚህም ፡ የሚበዙ ፡ ሌሎች ፡ ቃሎች ፡ ይገኛሉ ።

— 264 —

ቃለ ፡ አጋኖዎች ፡ እንደ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ የንግግርን ፡ ስሜት ፡ እየሞሉ ፡ ሲያ ስረዱ ፡ ይችላሉ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ — (ሀ) አንዳንዶቹ ፡ «አ» የሚለውን ፡ መስተዋድድ ፡ ትራስ ፡ እያደረጉ ፤ ወይም ፡ ሳያደርጉ ፡ እንደ ፡ ግሥ ፡ ደንብ ፡ በቮቱ ፡ መደበኛ ፡ ሲዘረዘሩ ፡ ይገኛሉ ። (ለ) አንዳንዶቹም ፡ ራሳቸው ፡ ሳይዘረገፉ ፡ ሌላውን ፡ ተዘርዛሪ ፡ ቃል ፡ እያስከ ተሉ ፤ ወይም ፡ እየተከተሉ ፡ ሲገቡ ፡ ይገኛሉ ። (ሐ) የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ የዝርዝርን ፡ ምግ ባር ፡ ሰይሙ ፡ በአማካይ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ይነገራሉ ።

ምሳሌ ። (ሀ) ወዮ=! ወዮልኝ ! ወዮልሀ ! ወዮላቸው ! . . .
እንጃ ! ። = እንጃልሀ ! እንጃለት ! እንጃላቸው ! . . .
አይዘህ ። = አይዞሽ ! አይዘአችሁ ! . . .
ያውልህ ! — ያውልሽ ! ያውላችሁ ! . . .
ይኸውልህ ! — ይኸውልሽ ! ይኸውላችሁ ! . . .
(ለ) እንኳን ፡ ደኅና ፡ ገባህ ! እንኳን ፡ ደኅና ፡ ገባችሁ ! . . .
ደኅና ፡ ሁን ! ደኅና ፡ ዋሉ ! . . .
(ሐ) ሃይማኖት ፡ ያውርድ ፡ ሹመት ፡ ያዳብር ፡ . . .
ጉድ ፡ እኮ ፡ ነው ! ይገርማል ፡ እኮ ! . . .

— 265 —

ሌሎቹ ፡ የንግግር ፡ ክፍሎች ፡ በወረዳቱ ፡ ነገር ፡ እየተሳኩ ፡ ተንግረው ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አኳኋን ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ሲሆኑ ፡ ይገኛሉ ። ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ቃለ ፡ ጥያቄ ፡ እንዲከተላቸው ፡ ይፈልጋሉ ። እነሆ ! ሁሉንም ፡ በሚከተለው ፡ ምሳሌ ፡ እናሰያለን ።
ስም ። እናንት ፡ ሰነፎች ፡ የገላትያ ፡ ሰዎች ! ለጽድቅ ፡ እንዳትታዘዙ ፡ ማን ፡ አታለላችሁ ?
ዐጂ ! ምነዋ ? ።
ተውላጠ ፡ ስም ። ድሀው ፡ ሽማግሌ ፡ ከመንገድ ፡ ሳይ ፡ ወድቋል ፤ እኔን ! ወዲት ፡ ልው ሰደው ፡ ይሆን ?
የዘመኑ ፡ ሰው ፡ ሲያቀርቡት ፡ ይርቃል ፤ ሲያፈቅሩት ፡ ይጠላል ፤ ወይ ፡ እንተ ! ከቶ ! ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሸላል ?

ግሥ ። ''ወዪ ፡ አንቀጽ'' ። አንዱን ፡ ሳንይዘው ፡ ከረምኩ ፡ መጣልሃ ! እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይበጀናል ?

ተመስገን ፡ ጌታዬ ፤ አንተ ፡ ታውቃለሃ !

«ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ » ራስን ፡ ማመስገን ፡ የሚገባ ፡ ከሆነ ፡ ራሳችንን ፡ ማመስገን ፡ እንጀምራ !

አሁን ፡ ምን ፡ በደልሁህ ? ፡ — እግዚአብሔር ፡ ይይልሃ !

''በዝ ፡ አንቀጽ'' ። ጉድ ፡ ፈልቶ ! አንተን ፡ ማን ፡ ጠየቀህ ?

መስተዋምር ። አንተም ፡ የመጣኸው ፡ ልትማር ፡ ነው ? — እንዲታ !

ማስገንዘቢያ ። ወዪ ፡ አንቀጽና ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ መድረሻውን ፡ ወደ ፡ ራሳዕኑት ፡ ለውጦ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ወይም ፡ ጥያቄ ፡ ይሆናል ። ልዩነቱ ፡ የሚታወቀውም ፡ እንደ ፡ አነጋገሩ ፡ አጣዓብ ፡ ነው ። አንቀጹ ፡ ቀንቱን ፡ በራሱዕ ፡ የሚጨርስ ፡ ሲሆን ፡ ጥያቄነቱ ፡ ወይም ፡ ቃለ ፡ አጋኖነቱ ፡ የሚታወቀው ፡ በድምዕ ፡ ወይም ፡ በምልክቶች ፡ (!?) ብቻ ፡ ነው ።

— 266 —

ከድምዕ ፡ የተነሣ ፡ ተመሥርተው ፡ የሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ ክፍላቸው ፡ ከቃለ ፡ አጋኖ ፡ ነው ።

አጅ ፡ — ኧው ፡ ፡ — ግው ፡ ፡ — ድው ፡ ፡ — ኳ ፡ ፡ — ኳኳ ፡ ፡ — እገጭ ፡ ፡ — እምቦጭ ፡ ፡ — እርጭ ፡ ፡ — ጓ ፡ ፡ — ጓጓ ፡ ፡ — እሂሀን ፡ የመሰሉ ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ። እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ የመሆን ፡ ግሥን ፡ ተከትለው ፡ ሲገቡ ፡ እንደ ፡ ግሥ ፡ ሁሉ ፡ ይሆናሉ ።

ምሳሌ ፡ — ኧው ፡ አለ ፡ ፡ — ግው ፡ አለ ፡ ፡ — እምቦጭ ፡ አለ ፡ ፡ — . . . እ. ግ. ነው ።

ስለዚህም ፡ በድምዕ ፡ የሚታወቁ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ብቻቸውን ፡ ሲነገሩ ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ይባላሉ ። ከመሆን ፡ ግሥ ፡ ጋር ፡ ሲነገሩ ፡ ግን ፡ በግብራቸው ፡ ተውሰክ ፡ ግሥ ፡ ወይም ፡ የግሥ ፡ ረዳት ፡ ይባላሉ ። (ቁ. 168 ፤ 234. እይ ፡)

— 267 —

መጠይቃን ፡ ወይም ፡ ቃላተ ፡ ጥያቄ ።

መጠይቃን ፡ የተባሉት ፡ የጥያቄ ፡ ቃላት ፡ አብዛኞቹ ፡ በየዐታው ፡ እንደ ፡ ጊዜ ፡ ግብራቸው ፡ ተነግረዋል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጠቅላላ ፡ መደባቸው ፡ ከዚህ ፡ ስለሆነ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በየስልታቸው ፡ እንጽፋቸዋለን ።

መጠይቃን ፡ የተባሉት ፡ የጥያቄ ፡ ቃላት ፡ (1) ፊደላውያን ፡ (1) ድምፃውያን ፤ ተብለው ፡ በ፪ ፡ ክፍል ፡ ይመደባሉ ። ከአውሮፓውያን ፡ የወረስነው ፡ የጥያቄ ፡ ምልክት ፡ (?) ለሁሉም ፡ ይደረግላቸዋል ።

— 268 —

(1) ፊደላውያን ፡ መጠይቃን ፡

ፊደላውያን ፡ የተባሉት ፡ የጥያቄ ፡ ቃላት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተጻፈው ፡ ይከፈላሉ ።

(ሀ) በዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ የሚውሉ ፡ መጠይቃን ። ''ን ፡ ወይ ,, ፡

(1) የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ማን ፡ ያስተውላል ?

ጎዘን ፡ ነውን ? — መከራ ፡ ነውን ? ፡ መሰደድ ፡ ነውን ?

ወይም ፡ ጎዘን ፡ ነወይ ?—መከራ ፡ ነወይ ? — መሰደድ ፡ ነወይ ?

(2) ፈልጎ ፡ ነበርን ?— ፈልጎ ፡ ኖሯልን ?— ይፈልጋልን ? = ይፈልግን ?

ወይም ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ፡ ወይ ? — ፈልጎ ፡ ኖሮአል ፡ ወይ ፡ = ይፈልጋል ፡ ወይ ? ይፈልግ ፡ ወይ ?

ማስገንዘቢያ ።

(ሀ) «ን ፡ ወይ ፡ » በስም ፡ ላይ ፡ ሲገቡ ፡ የመሆንን ፡ ግሥ ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ አድርገው ፡ ይነገራሉ ። ቢሆንም ፡ ጥያቄነታቸው ፡ የሚታወቀው ፡ በድምዕ ፡ ምልክት ፡ ስለሆነ ፡ አዲሱ ፡ ምልክት ፡ (?) ሊኖርላቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

አጅ — ልመኖሪያህ ፡ የትኛውን ፡ ትመርጣለህ ? — አንከባርን ፡ ጎንደርን ፡ (= አንከባርን ፡ ነወይ ፡ ወይስ ፡ ጎንደርን ፡ ነወይ ፡)

(ለ) ከመሆሀራን ፡ ወገን ፡ «ን ፡ ወይ ፡ » በሚገቡባቸው ፡ ቃላት ፡ አዲሱ ፡ ምልክት ፡ ?) ሊደረግባቸው ፡ አያስፈልግም ፡ እነርሱ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ የሚመስኑ ፡ አሉ ። ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ን ፡ በተጠቃሽነት ፡ ''ወይ,, ፡ በመስተጻምርነት ፡ ከሌላ ፡ ጉዳይ ፡ የሚገቡበት ፡ ጊዜያት ፡ ስለሚገኙ ፡ በሞክሼ ፡ እንዳ ያሰቡቱ ፡ ምልክቱ ፡ (?) ምንጊዜም ፡ እንዲደረግ ፡ መስነኖል ።

— 269 —

በአዋዋይ ፡ አንቀጽና ፡ በንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ የሚውሉ ፡ መጠይቃን ። ''ስ ፡ ሳ' ፡ ቢመጣስ ፡ ? ቢመጣሳ ?

መጥቶ ፡ እንደሆነስ ? መጥቶ ፡ እንደሆነሳ ?

ቢመጣ ፡ ኖሮስ ፡ ? ቢመጣ ፡ ኖሮሳ ?

እነዚህንም ፡ በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ስንገልጻቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ይሆናሉ ።

አጅ ፡ ትምህርት ፡ ሳናጠና ፡ አስተማሪው ፡ ቢመጣስ ? (ቢመጣሳ ?) ።

ወደጫዋታ ፡ እንሂድ ፡ አስተማሪው ፡ መጥቶ ፡ እንደሆነስ ? (መጥቶ ፡ እንደሆነሳ ?) ትናንት ፡ አላጠናንም ፡ ነበር ፡ አስተማሪው ፡ ቢጠይቀን ፡ ኖሮስ ? (ቢጠይቀን ፡ ኖሮሳ ?)

ማስገንዘቢያ ።

(ሀ) ፡ ,,ስ ፡ ሳ ፡ ,,ጥያቄ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ የግጋነንም ፡ ጠባይ ፡ ይገኝባቸዋል ፤ ይኸውም ፡ የሚታወቀው ፡ በአነጋገሩ ፡ ድምዕ ፡ ነው ።

(ለ) አንቀጽን ፡ ሳይከተሉ ፡ በስም ፡ ላይ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ የአዳጋሚነት ፡ ግብራ ፡ ቸውን ፡ ሳይተዉ ፡ ጥያቄዎች ፡ ይሆናሉ ። አንተጸም ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።

ምሳሌ ፡ አብርሃም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟል ፡ ነው ።

ይስሐቅስ ? — ያዕቆብስ ? ።

ወይም ፡ ይስሐቅሳ ?— ያዕቆብሳ ? ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ አንጋገር ፡ «ስ ፡ ሳ ፡ » የተባሉት ፡ ቃላት ፤ ሲነገር ፡ የሚገባውን ፡ አንቀጽ ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ አድርገው ፡ አስቀርተው ፡ እነርሱ ፡ ተተክተዋል ። ቢገለጽ ፡ ኖሮ ፡ ይስሐቅስ ፡ ያዕቆብስ ፡ ወይም ፡ ይስሐቅሳ ፡ ያዕቆብሳ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟል ፡ አይደሉምን ? ። የሚል ፡ ቃል ፡ ይጨመርበት ፡ ነበር ። እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ ቢነገር ፡ ኖሮ ፡ «ስ ፡ ሳ » ፡ አዳጋሚ ፡ ይባላሉ ፡ እንጂ ፡ ጥያቄ ፡ ባልተባሉም ፡ ነበር ። (ቁ.255 እይ ።)

— 270 —

በተውላጠ ፡ ስም ፡ በቅጽል ፡ በተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ላይ ፡ የሚውሉ ፡ መጠይቃን ።

እነርሱም ፡ ማን ፡ ምን ? የቱ ? ስንት ? እንዴት ? ወዴት ? ለምን ? ስለምን ?... እኒህን ፡ የመሰሉ ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ቃላት ፡ በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ተሳክተው ፡ ወይም ፡ በየራሳቸው ፡ ፀንተው ፡ ቢነገሩ ፡ ጥያቄ ፡ ይሆናሉ ። (ቁ. 76 ፡ 229 ፡ እይ ።)

— 271 —

(2) ፡ ድምፃውያን ፡ መጠይቃን ።

ድምፃውያን ፡ የተባሉት ፡ የጥያቄ ፡ ቃላት ፡ ስለጥያቄው ፡ የፈደል ፡ ምልክት ፡ የሌላቸውና ፡ በድምፅ ፡ ብቻ ፡ የሚታወቁ ፡ ናቸው ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ምሳሌውን ፡ በጥያቄና ፡ በመልስ ፡ እናሳያለን ።

ጥ —	አገርህ ፡ የት ፡ ነው ። —	ም —	አንከበር ፡
»	መቼ ፡ መጣህ ። —	»	ትናንት ፡
»	ዝናም ፡ ዘነመ ።	»	አምን ፡ ዘንሚል፡
»	አባትህ ፡ ይመጣሉ ። —	»	እንኳን ፡ አይመጡም ፡

እነሆ ፡ በዚህ ፡ በሰጠነው ፡ ምሳሌ ፡ የፈተኞቹ ፡ ሁለቱ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች «የት፡ መቼ ፡ » የሚል ፡ የጥያቄ ፡ ቃል ፡ ስላለባቸው ፡ ጥያቄነታቸውን ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ያስረ ዳሉ ። — የታችኞቹ ፡ ጀቱ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ግን ፡ በድምፅ ፡ ብቻ ፡ (በዜማ ፡ በተ

ነገሩ ፡ ጊዜ ፡) ይታወቃሉ ፡ እንጂ ፡ በተረፈ ፡ ምንም ፡ ምልክት ፡ የለባቸውም ። ነገሩን ፡ ለመለየት ፡ ብንፈልግ ፡ እንደሚከተለው ፡ ማድረግ ፡ አለብን ።

ዝናም ፡ ዘነመ ? ።	አባትህ ፡ ይመጣሉ?
ወይም ፡ ዝናም ፡ ዘነመ ፡ ወይ ?	አባትህ ፡ ይመጣሉ ፡ ወይ ፡
ወይም ፡ ዝናም ፡ ዘነመን ?	አባትህ ፡ ይመጣሉን ፡

ስለዚህም ፡ የጥያቄው ፡ ምልክት ፡ (?) በማንኛውም ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ እን ዲያረግ ፡ መስነናል ።

ፕሬኛ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) ከዚህ ፡ በታች ፡ በጥያቄና ፡ በመልስ ፡ ከተጻፉት ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ቃለ ፡ አጋ ኖቹን ፡ እየለየህ ፡ አመልክት ።

ታደሰ ! — አቤት ! — ዛሬ ፡ ገና ፡ ነው ፡ እኮ ! — እረ ! እውነትህን ፡ ነው ?— ዛሬ ፡ ብዙ ፡ ጨዋታ ፡ አለን ። ገና ፡ ጫወታ ፡ ታውቃለህ ? —እንዴታ ! — እነሆ ! ልጆች ይጫወታሉ ። — አሰይ ፡ እኔም ፡ ልጫወት ፡ ። — አዬጉድ ! ዱላዬን ፡ እረስቼዋለሁ ። — ኡዲያ ! የት ፡ ረሳኸው ? — እዚህ ፡ ይውን ፡ እዚያ ፡ አላውቀውም ፡ ። — ይገርማል ፡ እኮ ! እንዴት ፡ አታውቀውም ? — እስቲ ፡ ሳስታውሰው ? — እኝ ! ከቤቱ ፡ ጓሮ ፡ ነው ። — እንግዲህ ፡ እንጫወት ። — ውብሸት ፡ ኳሷን ፡ አንጭሳት ። — ሆሆይ ! እግሬን ፡ ሊሰነክሰኝ፡ ነበር ። — እፎይ ፡ እናቴ ! ደከመኝ ።— ሀ ሀ ሀ ! መድከምህ ፡ ነወይ ? —ለካ ፡ ሊደክመኝ ፡ ይወቃ ። እንግዲህ ፡ በየቤታችን ፡ እንግባ ። — ጤና ፡ ይስዋልኝ ! — ደኅና ፡ እደር ።

(ለ) በቃለ ፡ አጋኖ ፡ ደንብ ፡ የሚገቡ ፡ ፲፪ ፡ ቃላትን ፡ ጻፍ ፤ — እነርሱንም ፡ በም ሳሌ ፡ እያደረግህ ፡ አመልክት ። — የጥያቄ ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ አስረዳኝ ። — ፈደላውያን ፡ መጠይቃን ፡ የተባሉትን ፡ ጻፍ ። — ድምፃውያን ፡ መጠይቃን ፡ የተባሉት ንም ፡ በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ እየሞላህ ፡ አምስት ፡ ምሳሌ ፡ አምጣ ።

ሁለተኛ ፣ ታላቅ ፣ ክፍል ።

አ ገ ባ ብ ።

ምዕራፍ ፣ I ። ወረፍተ ፣ ነገር ።

— 272 —

መግለጫ ።

ወረፍተ ፣ ነገር ፣ ማለት ፣ የነገር ፣ ማሳረፊያ ፣ ወይም ፣ ማቆሚያ ፣ ወይም ፣ መግቻ ፣ ግለት ፣ ነው ። ቃላት ፣ በየብቻቸው ፣ ሲነገሩ ፣ የየራሳቸውን ፣ እንጂ ፣ የንግግሩን ፣ ስሜት ፣ ሊገልጹ ፣ አይችሉም ። በዘንብረት ፣ ተቀነባብረው ፣ ሲነገሩ ፣ ግን ፣ ንግግሩን ፣ ፍጹግዊ ፣ ያደርጉታል ።

ስለዚህም ፣ የንግግርን ፣ ስሜት ፣ ፍጹም ፣ የሚያደርገው ፣ «የቃላት ፣ መተባበር ፣ በሰዋስው ፣ ደንብ ፣ ወረፍተ ፣ ነገር ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ።

አጅ ፣ — ፀሐይ ፣ — ወጣ ።
ከበደ ፣ — ወደ ፣ — ቤቱ ፣ — ሄደ ።
በከተማ ፣ — የሚኖር ፣ — ሰው ፣ — እንደ — ባላገር ፣ አይደለም ።

እነሆ ፣ እነዚህ ፣ ቃላት ፣ በየብቻቸው ፣ ቢነገሩ ፣ ኖሮ ፣ የንግግሩ ፣ አሰብ ፣ ፍጹም ፣ ባልሆነም ፣ ነበር ፣ ነገር ፣ ግን ፣ በዘንብረት ፣ ስለተነገሩ ፣ ንግግሩ ፣ ፍጹምነትን ፣ አግኝቷል ።

— 273 —

ወረፍተ ፣ ነገርን ፣ በፀ ፣ አከሄድ ፣ ልንለየው ፣ ወይም ፣ በፀ ፣ ዓይነት ፣ ልንመድበው ፣ እንችላለን ። ይኸውም ፣ እንደሚከተለው ፣ ነው ።

(ሀ) ማናቸውም ፣ ንግግር ፣ በአምንታ ፣ ሆነ ፣ በአሉታ ፣ ቢነገር ፣ ንግግሩ ፣ በጥያቄና ፣ በትእዛዝ ፣ ወይም ፣ በማጋነን ፣ ድምፅ ፣ የማይነገር ፣ ከሆነ ፣ ሐተታዊ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። እንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ ንባባዊ ፣ እንለዋለን ። ትርጓሜው ፣ ነገርን ፣ አመልካች ፣ ወይም ፣ ተራኪ ፣ እ.ግ.ነው ። አብዛኛው ፣ ንግግር ፣ ከሌሎቹ ፣ ይልቅ ፣ በዚህኛው ፣ ክፍል ፣ ሲነገር ፣ ይገኛል ።

አጅ ፣ — ከበደ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ሄደ ፣ ነገ ፣ ትምህርትን ፣ እንማራለን ፣ } አምንታ ፣
ከበደ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ አልሄደም ፣ የትምህርት ፣ ሰዓት ፣ አልደረሰም ፣ } አሉታ ፣

(ለ) የግዘዝ ፣ ወይም ፣ የመከልከል ፣ አኳኋን ፣ የሚነገርበት ፣ ሲሆን ፣ ትእዛዛዊ ፣ ወ.ነ. ፣ ይባላል ። የምኞትና ፣ የፍላጎት ፣ የልመናና ፣ የምልጃ ፣ አኳኋን ፣ የሚነገርበት ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ወደዚሁ ፣ ክፍል ፣ ተጠቅልሎ ፣ ይነገራል ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ ሁሉም ፣ በትእዛዝ ፣ አንቀጽ ፣ እንዲነገሩ ፣ መሆን ፣ አለባቸው ።

አጅ — ከበደ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ይሂድ ፤
አበትህንና ፣ እናትህን ፣ አክብር ፤
ግንዘብ ፣ አበድረኝ ፤
አቤቱ ፣ ተነሥ ፤ ጠላቶችህም ፣ ይበተኑ ። } አምንታ ፣

ሊሠራ ፣ የማይወድ ፣ አይብላ ፤
ከበደ ፣ ወደቤቱ ፣ አይሂድ ፤
ወደ ፣ ፈተና ፣ አታግባን ፤
እንደ ፣ ግብዞች ፣ አትሁን ። } አሉታ ፣

(ሐ) የጥያቄ ፣ አኳኋን ፣ የሚነገርበት ፣ ሲሆን ፣ ጥያቄያዊ ፣ ወ. ነ ፣ ይባላል ።

አጅ — ከበደ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ሄደወይ ? } አምንታ ፣
ሥራውን ፣ ጨርሰአል ፣ ወይ ?
ከበደ ፣ ወደቤቱ ፣ አልሄደምን ? } አሉታ ፣
የሞተ ፣ ዳግመኛ ፣ አይነግምን ?

(መ) በአሳብ ፣ የሚታወቅ ፣ የአንክሮ ፣ አኳኋን ፣ ሲነገርበት ፣ አጋናኝ ፣ ወ.ነ. ፣ ይባላል ።

አጅ — እንዴት ፣ ያለህ ፣ ሰነፍ ፣ ኖረሃል ?
አንዱን ፣ ሳንይዘው ፣ ጊዜው ፣ አለፈብ ?

እነዚህም ፣ አራቱ ፣ ዓይነቶች ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ እንደ ፣ ንግግሩ ፣ አኳኋን ፣ እርስ ፣ በራሳቸው ፣ ሲመራረሱም ፣ ይኸኛሉ ።

— 274 —

ባለቤትና ፣ አንቀጽ ።

ወረፍተ ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ በሁለት ፣ ነገሮች ፣ የተቋቋመ ፣ መሆኑን ፣ ማወቅ ፣ አለብን ። እነርሱም ፣ ባለቤትና ፣ አንቀጽ ፣ ናቸው ።

እነሆ ፣ « ከበደ ፣ ወደቤቱ ፣ ሄደ » ብለን ፣ ስንናገር ፣ በወረፍተ ፣ ነገር ፣ የተቀነባበረና ፣ ሙሉ ፣ ስሜት ፣ ያለው ፣ አንድ ፣ ንግግር ፣ መናገራችን ፣ ነው ። ይህንኑም ፣ ወረፍተ ፣ ነገር ፣ ከሁለት ፣ ሳይ ፣ ብንመድበው ፣

(ሀ) ..ከበደ ፣ የተባለው ፣ ስለ ፣ እርሱ ፣ የሚነገርለት ፣ ነው ። እርሱም ፣ ባለቤት ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ።

(ለ) .. ወደቤቱ ፣ ሄደ ፣ የሚለውም ፣ ቃል ፣ ስለ ፣ ከበደ ፣ የተነገረው ፣ ነው ። እርሱም ፣ አንቀጽ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ።

ስለዚህም ፣ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ከሚገለጸው ንግግር ፥ ኗኖው ፥ ወገን ፣ በለቤት ፤ ዘኖው ፣ ወገን ፣ አንቀጽ ፣ ተብሎ ፥ ይመደባል ። ምንም ፣ እንኳ ፣ ተሰብቢ ፣ በዝቶ ፣ ዐረፍተ ፣ ነገሩ ፣ ቢረዝም ፣ ጠቅላላ ፣ ምዳቤው ፣ ከነዚህ ፣ ከውስቱ፣ አይወጣም።

— 275 —

ሐረግ ።

በዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ውስጥ ፣ ሐረግ ፣ የሚባል ፣ አነስተኛ ፣ ክፍል ፣ አናበጀለን ። ለእርሱም ፣ ደግሞ ፣ ዐቢይ ፤ ንኡስ ፣ የሚል ፣ ደረጃ ፣ ይደረግለታል ።

« ዐረፍተ ፣ ነገር » የንግግርን ፣ አሳብ ፣ በሙሉ ፣ መግለጫ ፣ ነው ።

« ዐቢይ ፣ ሐረግ ፣ » የአንቀጽ ፣ ቃል ፣ የሚገኝበት ፣ የዐረፍተ ፣ ነገሩ ፣ ትንሽ ፣ ክፍል ፣ ነው ።

« ንኡስ ፣ ሐረግ ፣ » የአንቀጽ ፣ ቃል ፣ ሳይኖረው ፣ ትንሽ ፣ ንግግር ፣ ያለበት ፣ የዐቢይ ፣ ሐረግ ፣ ትንሽ ፣ ክፍል ፣ ነው ።

ሐረግ ፣ የተባለው ፣ ስም ፣ በቅኔ ፣ ተማሪ ፣ ቤት ፣ ከቤት ፣ መምቻ ፣ በፊት ፣ የሚገኝና ፣ የስንኝ ፣ መከፈያ ፣ መደልደያ ፣ ሆኖ ፣ በመኖር ፣ የታወቀ ፣ ቃል ፣ ነው ።

ሐረግ ፣ እርስ ፣ በርሱ ፣ ተሳሰቢ ፣ እንደሆነ ፣ ንግግርም ፣ በዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ውስጥ ፣ እርስ ፣ በርሱ ፣ ይሳሳባልና ፣ በዚያው ፣ ተምሳሌት ፣ ሐረግ ፣ ብለን ፣ ሰይመነዋል ።

— 276 —

ሐረግ ፣ ብለን ፣ የሰየምነው ፣ የዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ክፍል ፣ የአንቀጽ ፣ ቃል ፣ የማይገኝበት ፣ ሲሆን ፣ ንኡስ ፣ ሐረግ ፣ ይባላል ፤ የአንቀጽ ፣ ቃል ፣ የሚገኝበት ፣ ሲሆን ፣ ግን ፣ ዐቢይ ፣ ሐረግ ፣ ይባላል ፣ ብለናል ። ስለዚህም ፣ ሁሉም ፣ ማሰሪያ ፣ አንቀጽ ፣ የሌላቸውና ፣ ንግግሩን ፣ ፍጹም ፣ የማያደርጉ ፣ ናቸው ።

ዐቢይ ፣ ሐረግ ፣	አጅ ፣ ንኡስ ፣ ሐረግ ፣
በአሸዋ ፣ ላይ ፣	
ከብዙ ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣	
በክፉ ፣ ዘመን ፣	
በአሸዋ ፣ ላይ ፣ የተሠራ ፣	
ከብዙ ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ የመጣ	
በክፉ ፣ ዘመን ፣ የተገኘ ፣	

እነዚህ ፣ ንኡስ ፣ ሐረግና ፣ ዐቢይ ፣ ሐረግ ፣ እንዴት ፣ እንደሆኑ ፣ ምሳሌውን ፣ በቀላሉ ፣ አሳይተናል ። ንኡስ ፣ ሐረግም ፣ ወደ ፣ ዐቢይ ፣ ሐረግነት ፣ እንደተጠቀለለ ፣ አስተውል ። ዐቢይ ፣ ሐረግም ፣ እንዲሁ ፣ ወደ ፣ ዐረፍተ ፣ ነገርነት ፣ ይጠቀለላል ። ይኸውም ፣ በአሸዋ ፣ ላይ ፣ የተሠራ ፣ ቤት ፣ ቆሎ ፣ ይፈርሳል ፤ እ.ግ. ነው ። አሁን ፣ የንግግሩ ፣ ስሜት፣ እንደ ፣ ተሟላ ፣ አስተውል ።

— 277 —

የዐረፍተ ፣ ነገር ፣ አመዳደብ ።

ነጠላ ፣ ዐረፍተ ፣ ነገር ።

አንድ ፣ ባለቤትና ፣ አንድ ፣ አንቀጽ ፣ ብቻ ፣ የሚነገሩበት ፣ ዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ነጠላ ፣ ይባላል ። ምክንያቱም ፣ በአንድ ፣ ባለቤትና ፣ በአንድ ፣ አንቀጽ ፣ ብቻ ፣ የንግግሩን ፣ አሳብ ፣ በሙሉ ፣ የሚያስረዳ ፣ ስለሆነ ፣ ነው ። በባለቤት ፣ ላይ ፣ የሚጨመር ፣ ዘርፍ ፣ ወይም ፣ ቅጽል ፤ እንደዚሁ ፥ ደግሞ ፣ የአንቀጽ ፣ ተገዥ ፣ የሆነ ፣ ተሰቢ ፣ ወይም የመስተዋድድ ፣ ተገዥና ፣ ተውሳክ ፣ ግሥ ፣ ተጨምሮ ፣ ቢነገር ፣ በነዚሁ ፣ ክፍሎች ፣ ተጠቅልሎ ፣ ይነገራል ።

አጅ ፦— ፀሐይ ፣ ወጣ ። — ዝናም ፣ ዘነመ ።
ከበደ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ሄደ ። — ብርሃኔ ፣ ነገ ፣ ይመጣል ።
አባት ፣ ልጁን ፣ ይወድዳል ። — ላም ፣ ወተትን ፣ ትሰጣለች ።
ፈሪ ፣ ሰው ፣ ምክንያትን ፣ ያበዛል ።
የከበደ ፣ ቤት ፣ ችልቅና ፣ ሰፊ ፣ ነው ።

— 278 —

ነጠላ ፣ ዐረፍተ ፣ ነገር ፣ የሚመደብባቸው ፣ ክፍሎች ፣ ዋነኞቹ ፣ አራት ፣ ናቸው ። ቃሉ ፣ በሚፍታታበት ፣ ጊዜያት ፣ ግን ፣ እነርሱ ፣ እንደገና ፣ የውስጥ ፣ ክፍል ፣ ሰ,ያበጁ ፣ ይገኛሉ ።

(ሀ) ፣ ባለቤት ፣
(ለ) ፣ የባለቤት ፣ ዘርፍ ፣ ወይም ፣ ተቀጣይ ።
(ሐ) ፣ አንቀጽ ። (አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ ማሰሪያ ፣ አንቀጽ ፣ ይባላል)።
(መ) ፣ የአንቀጽ ፣ ተሰቢ ፣ ወይም ፣ ተጨማሪ

ከነዚህ ፣ ከአራቱ ፣ ክፍሎች ፣ መጀመሪያውና ፣ ሰስተኛው ፣ ክፍል ፣ (እነርሱም ፣ ባለቤትና ፣ አንቀጽ ፣ ናቸው ፣) የዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ምሰሶች ፣ ይባላሉ ። ምክንያቱም ፣ ዐረፍተ ፣ ነገር ፣ ያለነእርሱ ፣ ሊቆሚም ፣ የማይችል ፣ ስለሆነ ፣ ነው ። ፪ኛውና ፣ ፬ኛው ፣ ክፍሎች ፣ ግን ፣ የእነርሱ ፣ ተጨማሪዎች ፣ ናቸው ።

አንቀጹ ፣ ግዜር ፣ ሲሆን ፣ ተሰቢ ፣ እንዲኖረው ፣ ያስፈልጋል ። ተጉበሮ ፣ ከሆነ፣ ግን ፣ በባለቤትና ፣ በአንቀጽ ፣ ብቻ ፣ ቢነገር ፣ የንግግሩን ፣ አሳብ ፣ አያጐድለውም ። ወይም ፣ የመስተዋድድ ፣ ተገዥ ፣ ይታከልለታል ። ይኸውም ፣ — ‹ፀሐይ ፣ ወጣ ። › ወይም ፣ ‹ፀሐይ ፣ በስተምሥራቅ ፣ ወጣ ። › እንደ ፣ ማለት ፣ ያለ ፣ ነው ።

— 279 —

(ሀ) በለቤት ።

በለቤት ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የሚነገርለት ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ስምን ፡ አክሎ ፡ መስሎ፡ የሚገኝ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ነው ።

አጅ ፡ — ከበደ ፡ መጣ ። (እነሆ ፡ ስለከበደ ፡ መናገራችን ፡ ነው) ።
አንበሳው ፡ አገሣ ። (እነሆ ፡ ስለ ፡ አንበሳው ፡ መናገራችን ፡ ነው) ።
ነጋሪቱ ፡ ይጮሸማል ። (እነሆ ፡ ስለ ፡ ነጋሪቱ ፡ አካኋን ፡ መናገራችን ፡ ነው) ።

—280 —

በለቤት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ የንግግር ፡ ክፍል ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ ከላይ ፡ እንደተባለው ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ስምን ፡ አክሎ ፡ የሚገኝ ፡ ቃል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

አጅ ፡ — ስም ። — ከበደ ፡ መጣ ።

ተውላጠ ፡ ስም ። እርሱ ፡ ይጽፋል ።
አርእስት ። — መቀመጥ ፡ ሰውን ፡ ያሰለቻል ።
ዘር ፡ — ሥራ ፡ ሰውን ፡ ያስከብራል ።
በቂ ፡ ቅጽል ። ቀይ ፡ ይደምቃል ፡ (ውስጠ ፡ የ ፡)
» » የሄደ ፡ አይመለስም ፡ (ግልጽ ፡ የ ፡)

ማስገንዘቢያ ፡ እነሆ ፡ « ቀይ ፡ » « የሄደ ፡ » በለ ፡ ጊዜ ፡ « ሰው ፡ » የሚለው ፡ ቃል ፡ ውስጠ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ ሳይነገር ፡ ቀርቷል ። ትርጓሜውም ፡ ቀይ ፡ ሰው ፡ የሄደ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው። ውስጠ ፡ ቀሪ ፡ ማለት ፡ ነገሩ ፡ በአእምሮ ፡ ታውቆ ፡ በንግግር ፡ ሳይገለጽ ፡ የሚቀርና ፡ በቃ ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ተሰውሮ ፡ ስሜቱን ፡ የሚያስታውቅ ፡ ማለት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ፤ ምሥጢሩ ፡ ያው ፡ ነው ።

— 281 —

(ለ) የበለቤት ፡ ዘርፍ ፡ ወይም ፡ ተቀጣይ ።

የበለቤቱን ፡ አካኋን ፡ ለመግለጽ ፡ የሚጨመረው ፡ ቃል ፡ ዘርፍ ፡ ወይም ፡ ተቀጣይ ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ ቅጽል ፡ ወይም ፡ የቅጽልን ፡ ምግባር ፡ ይዞ ፡ የሚገኝ ፡ ማንኛውም ፡ ቃል ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ በጠቅላላው ፡ ቅጽል ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ ይገባዋል ።

አጅ — 1. ስም ።

የሰአል ፡ መንግሥት ፡ ወደቀ ። (አገናዛቢ ፡ ዘርፍ ፡)
የከበደ ፡ መጽሐፍ ፡ አዲስ ፡ ነው ። »
የገሠገሠ ፡ ጥርስ ፡ በለብዙ ፡ ዋጋ ፡ ነው ። »
የመርቅ ፡ ሰዓት ፡ ይወደዳል ። (ዘርፍ ፡ አስተኔ ፡ ቅጽል ፡)
የግንብ ፡ ቤት ፡ ይጠነክራል ። »

2. ተውላጠ ፡ ስም ።

የእርሱ ፡ ልብስ ፡ ተቀደደ ። (አገናዛቢ ፡ ዘርፍ ፡)
ወንድምህ ፡ (= የአንተ ፡ ወንድም ፡) ይጠራሃል ። (አገናዛቢ ፡ ዝርዝር ፡)

3. ቅጽል ።

አጭር ፡ ፈረስ ፡ ፈጣን ፡ ነው ። (ውስጠ ፡ የ ፡ ቅጽል ፡)
እውነተኛ ፡ ሰው ፡ ይከበራል ።
የአለፈ ፡ ነገር ፡ አይቂጭህ ። (ግልጽ ፡ የ ፡ ቅጽል ፡)
የማሞት ፡ ሽማግሌ ፡ አይርገምህ ። »

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጻፉት ፡ ፀረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ባለቤት ፡ የተባሉት ፡ « መንግሥት ፡ — መጽሐፍ ፡ — ጥርስ ፡ — ሰዓት ፡ — ቤት ፡ ልብስ ፡ ወንድም ፡ — ፈረስ ፡ — ሰው ፡ — ነገር ፡ — ሽማግሌ ፡ » ናቸው ። በስተግርጌ ፡ የጭረት ፡ ምልክት ፡ (መስመር ፡) የተደረገባቸው ፡ ቃላት ፡ በባለቤቶቹ ፡ ላይ ፡ እንደተጨመሩባቸው ፡ አስተውል። እነርሱም ፡ የባለቤት ፡ ዘርፎች ፡ ወይም ፡ ተቀጣዮች ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ።

በአገናዛቢ ፡ ዘርፍና ፡ በአገናዛቢ ፡ ዝርዝር ፡ መከከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ እም ብዛም ፡ ሩቅ ፡ አይደለም ። — አንደ ፡ ዘርፍ ፡ ደንብ ፡ የ ፡ በግልጽ ፡ ሲጨመርበት ፡(የእርሱ ፡ ልብስ ፡)አገናዛቢ ፡ ዘርፍ ፡ ይባላል ። በዝርዝር ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ (ወንድምህ ፡) አገናዛቢ ፡ ዝርዝር ፡ ይባላል ።

— 282 —

(ሐ) አንቀጽ ፡

አንቀጽ ፡ የሚባለው ፡ ስለባለቤት ፡ የሚነገርና ፡ የንግግር ፡ አለብ ፡ የሚፈጸም በት ፡ ቃል ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ማሰሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ የአንቀጽ ፡ ዓይነቶች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

1. ወሲይ ፡ አንቀጽ ፡

ከበደ ፡ መጣ ። (መጥቷል ፡ — መጥቶ ፡ ነበር ።)
ከበደ ፡ ይመጣል ። (ሊመጣ ፡ ነው ፡ — ይመጣ ፡ ይሆናል ።)

2. ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ።

ከበደ ፡ ይምጣ ። (እንዲመጣ ፡ ይሁን ።)

3. ተምኔታዊ ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ።

ብልክበት ፡ ኖሮ ፡ ከበደ ፡ በመጣ ፡ ነበር ፡ (ይመጣ ፡ ነበር ።)

4. የመሆን ፡ አንቀጽ ።

ዮሐንስ ፡ አናጢ ፡ ነው ።

— 283 —

የአንቀጹ ፡ ጠባይ ፡ ገቢርና ፡ ተሻጋሪ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ አንቀጹ ፡ ተሳቢ ፡ እንዲኖረው ፡ በግድ ፡ ያስፈልጋል ። አለዚያ ፡ ግን ፡ የንግግሩ ፡ አሳብ ፡ የተጓደለ ፡ ይሆናል ።

እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ « ዳዊት ፡ ገደለ ፤ » ብለን ፡ ብንናገር ፡ ምንን ? ወይም ፡ ማንን? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይመጣብናል ። ነገር ፡ ግን ፡ « ዳዊት ጎልያድን ፡ ገደለ ፤ » ያልን ፡ እንደሆን ፡ የንግግሩ ፡ አሳብ ፡ የተፈጸመ ፡ ይሆናል ።

ገቢር ፤ ተሻጋሪ ፤ ማለት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ተ. ቁ. ፡ 122 ፤ 128 ፡ እይ ።

— 284 —

(መ) የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ።

ከላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ፡ የሚባለው ፤ የአንቀጹን ፡ ትግበር ፡ ለመግለጽ ፡ የምንጨምረው ፡ ቃል ፡ ነው ። የአንቀጽ ፡ ተጨማሪ ፡ የሚባለውም ፡ በመስተዋድድ ፡ የሚያያዝ ፡ ማንኛውም ፡ ነገርና ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ነው ።

የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ።

ስም ፡ —	ዳዊት ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ ።	(ያለዘርፍ ፡)
	ዳዊት ፡ የሳኦልን ፡ መንግሥት ፡ ወሰደ ፡	(ከዘርፍ ፡ ጋር ፡)
ተውሳጠ ፡ ስም ። —	እኔ ፡ እርሱን ፡ ፈለግሁ ።	(ግልጽ ፡ ተ ፡ ስ፡)
	እኔ ፡ ፈለግሁት ። (ት = እርሱን ፡)	(ዝርዝር ፡ ተ ፡ ስ)
ቅጽል ። —	እግዚአብሔር ፡ እውነተኛን ፡ ይወድዳል ፡	(በቂ ፡)
	እግዚአብሔር ፡ ያመነውን ፡ በረድኤት ፡ ይቀበላል ፡ ።	
እርእሰት ፡	ከመማገጥ ፡ ይልቅ ፡ መሣርን ፡ እመርጣለሁ ።	
ዘር ።	እርሱ ፡ ትምህርትን ፡ ወደደ ።	
ሳቢ ፡ ዘር ፡	እርሱ ፡ እኔጋርን ፡ ያውቃል ።	

— 285 —

የአንቀጽ ፡ ተጨማሪ ።

የአንቀጽን ፡ ትግበር ፡ ለመመለያ ፡ የሚጨመረው ፡ ቃል ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡) ወይም ፡ ተውሳክ ፡ ግሣዊ ፡ መመለያ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ይኸውም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

እጅ ፡ — ተውሳከ ፡ ግሥ ፡ — ዮሐንስ ፡ ክፋኛ ፡ ታማ ።

ተውሳከ ፡ ግሣዊ ፡ ሐረግ ። — ዝማነህና ፡ ውብሸት ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ይሄዳሉ ።

ተውሳክ ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ። — ፈለጥ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲማር ፡ ዋለ ።

መስተዋድዳዊ ፡ ሐረግ ፡ — የዘመደ ፡ ጥል ፡ ቤት ፡ ለቤት ፡ ይቀራል ።

በዝ ፡ ወይም ፡ የበዝ ፡ ሐረግ ። — ዳዊት ፡ ጎልያድን ፡ በድንጋይ ፡ መትቶ ፡ ገደለው ።

እርእስታዊ ፡ ሐረግ ፡ — ለመስማት ፡ የፈጠንህ ፡ ለመናገር ፡ የዘገየህ ፡ ሁን ፡

ስለዚህም ፡ የአንቀጽ ፡ ተግበር ፡ የሚሟላበት ፡ ቃል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከሌላ ። ክፍል ፡ ቢሆን ፡ በግብሩ ፡ ተውሳከ ፡ ግሣዊ ፡ መመለያ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ።

— 286 —

ወረፍተ ፡ ነገርን ፡ መተንተን ።

ነጠላ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡ ሆኖ ፡ ይተነተናል ። ዋናዎቹ ፡ መተንተኛች ፡ ከላይ ፡ የተነገሩት ፡ ፬ቱ ። ክፍሎች ፡ ናቸው ። (ቁ. 278 እይ ፡) አንቀጽ ፡ ለተባለው ፡ ለሰስተኛው ፡ ክፍል ፡ እንደገና ፡ ንኡሳን ፡ ክፍሎች ፡ ተደርገውስታል ። ይህንንም ፡ በሚከተለው ፡ የመተንተን ፡ ሰሌዳ ፡ ይመለከቷል ። (ቁ. 289 እይ ።)

— 287 —

በወረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ቃላት ፡ በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ በግብር ፡ በግብራቸው ፡ ተዘርዝረው ፡ ተገልጸዋል ። ቁ. 289 እይ ።) ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሰያንዳንዱ ፡ የንግግር ፡ ክፍል ፡ አንዳንድ ፡ መንጠረዥ ፡ ለማስመር ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለሆነ ፡ በግብር ፡ ወገናሞች ፡ የሆኑት ፡ ቃላት ፡ እንደሚከተለው ፡ ሥርዓት ፡ እየተጠቀሰሱ ፡ እንዲጸፉ ፡ ይደረጋል ።

(ሀ) የዘርፍ ፡ ዘርፍ ፡ ወይም ፡ የዘርፍ ፡ ቅጽል ፡ ወይም ፡ የቅጽል ፡ ዘርፍ ፡ በእንድነት ፡ ይጸፋል ፤ (ለ) የግሥ ፡ ረዳት ፡ ከአንቀጹ ፡ ሳይለይ ፡ ይጸፋል ። (ሐ) መስተዋድዳዊ ፡ ወይም ፡ መስተፃምራዊ ፡ ሐረግ ፡ ''መመሊያ ፡'' በሚለው ፡ ክፍል ፡ ይጠቀሰሳል ። (መ) በአንቀጽ ፡ ላይ ፡ የሚውል ፡ የተውላጠ ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ስለ ፡ ባለቤት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተሳቢ ፡ ተተክቶ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ከአንቀጹ ፡ ጋር ፡ በቅንፍ ፡ ተከብቦ ፡ ይጸፋል ። (ይኸውም ፡ አውን ፡ በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ እተናተን ፡ ለማመልከቻ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሁልጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ ይደረጋል ፡ ማለት ፡ አይደለም) ፤ በደንበኛ ፡ ስፍራውም ፡ ያለቅንፍ ፡ ተጽሮ ፡ ይነገራል ። (ሠ) በአንድ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ከ፩ ፡ የሚበልጥ ፡ ተሳቢ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪና ፡ መመሊያ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ብዛቱን ፡ ለማሳየት ፡ የአኅዝ ፡ ተራ ፡ በቅንፍ ፡ ይጻፍበታል ።

ድርብ ፡ ወይም ፡ ድርብርብ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ፡ በሚተነተንበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ምጻቤ ፡ በቂ ፡ አይደለም ።

— 288 —

የሚከተሉት ፡ ወረፍተ ፡ ነገሮች ፡ በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ (ተ ፡ ቁ ፡ 289) የመተንተን ፡ ሥርዓት ፡ እንዲታይባቸው ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

1) ብልሀ ፡ አስተማሪ ፡ ወጣት ፡ ልጄን ፡ ሰዋስው ፡ በትጋት ፡ ያስተምራል ።

2) የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ አጣልያኖችን ፡ በአድዋ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ በሕዝብ ፡ እና ፡ ታላቁ ፡ ምኒልክ ፡ ተብሉ ።

3) ለጌታው ፡ ታማኝ ፡ የሆነ ፡ ሎሌ ፡ ከድህም ፡ የሚያርፍበትን ፡ የአገልግሎቱን ፡ ዋጋ ፡ ከጌታው ፡ ዘንድ ፡ ያገኛል ።

4) አዲስዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚያስከብራትን ፡ የነፃነት ፡ ዕድል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትዋ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መሪነት ፡ አገኘች ።

5) የንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ የሚፈጽሙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ በየተራራውና ፡ በየሸለቆው ፡ ሠነው ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተዋግተው ፡ ነፃነታቸውን ፡ ለመድፈር ፡ የመጣውን ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ አደረጉት ።

6) ትናንት ፡ ስፈልግህ ፡ ዋልህ ።

— 289 —

የመተንተን ፡ ሰሌዳ ።

ዐረፍተ፡ ነገር ፡	(ለ) ባለቤት ፡	(ሐ) አንቀጽ ።			(መ) ጉውላ፡ ግሣዊ፡ መሙላሊያ፡ (አግባሪያ፡ አንቀጽ፡)
		(ሀ) ዘርፍ ፡ ወይም ፡ ተቀጣይ ፡	ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡	ድርጊቱ፡ የሚገለጽበት፡ ተብሏ ፡	የቃል ፡ መግለጫ ፡ ተጨማሪ ፡
(1)	አስተማሪ ፡	ግልህ ፡	ያስተምራል ፡	(1) ልጁን ፡ (2) ስዋሀውን ፡	ወጣት ፡	በትጋት ፡
(2)	አዴ፡ምኒልክ፡	የኢትዮጵያ፡ ንጉሠነገሥት፡	ገቡ ፡	ታላቁ ፡ ምኒልክ ፡		(1) ኢጣልያኖችን፡ በአድዋ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ (2) በሸዋ ፡ አፍ ፡
(3)	ሱሴ ፡	ለጌታው ፡ ታማኝ ፡ የሆነ፡	ያገኛል ፡	የአገልግሎ ፡ ት ፡ ዋጋ ፡	ከድክም ፡ የሚያድናቸው፡	ከጌታው ፡ ዘንድ ፡
(4)	ኢትዮጵያ ፡	አዲስዋ ፡	አገኘች ፡	የነፃነት ፡ ዕድል ፡	የሚያስከብራ ፡ ትን ፡	በንጉሥ ፡ ነገሥትዋ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መሪነት፡
(5)	አርበኞች ፡	(1)የንጉሣቸ ፡ ውን ፡ ፈቃድ ፡ የሚፈጽሙ ፡ (2)የኢትዮጵያ ፡	ዖል ፡ አደረጉት ፡	ጠላታቸውን ፡	ነፃነታቸውን ፡ ለመድፈር ፡ የመጣውን ፡	(1) በየተራራውና ፡ በየሸለቆው ፡ ሀገሩ ፡ ተቀምተው ፡ (2) ደ፣ ዓመት ፡ ሙሉ ፡
(6)	ሙ (=አጼ)፡		ቀል (ሠ)	ህ(=ሕንተን)		ትናንት ፡ በተፈልማ(ህ)

— 290 —

ድርብ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ።

በአንድ ፡ ሙሉ ፡ ንግግር ፡ ውስጥ ፡ ከአንድ ፡ የሚበልጥ ፡ የአንቀጽ ፡ ቃል ፡ የሚገኝበትና ፡ ሐረጉ ፡ የረዘመ ፡ ሲሆን ፡ ድርብ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ይባላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የአንቀጹ ፡ ቃል ፡ በመስተያምር ፡ ከማሰሪያነት ፡ የታገደ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

አጅ ፡ — የዕጂይ ፡ ልጅ ፡ ዳዊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ያደረበትና ፡ ኃይል ፡ የተሰጠው ፡ ጀግና ፡ ስለነበረ ፡ ፍልስጥኤማዊዉን ፡ ጎልያድን ፡ በወንጭፍ ፡ ድንጋይ ፡ መትቶ ፡ ገደለው ፤ ራሱንም ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጠው ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ በተሰጠው ፡ ማስረጃ ፡ የነገሩ ፡ ፍሬ ፡ « ዳዊት ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ፡ ራሱንም ፡ ቆረጠ ፡ » የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ። የቀረው ፡ ግን ፡ ተሳቢና ፡ መሙሊያ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ነው ። ድርብ ፡ መባሉም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

— 291 —

ድርብርብ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ።

ተሳቢው ፡ ሲረዝምና ፡ ራሱን ፡ የቻለው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ በአጻጋሚ ፡ መስ ተፃምር ፡ እየተነባበረና ፡ በዋዊ ፡ እየተደጋገመ ፡ ሲነገር ፡ « ድርብርብ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ይባላል ። ይሁንና ፡ የንግግሩ ፡ በለቤት ፡ ያው ፡ የፊተኛው ፡ ሆኖ ፡ በዋዊ ፡ እንዲተሳሰፍ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

አጅ ፡ « የዕጂይ ፡ ልጅ ፡ ዳዊት ፡ በጐልማሳነቱ ፡ የበጎች ፡ ጠባቂ ፡ ሳለ ፡ እስራ ኤል ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍሮች ፡ እንደ ፡ ተከበቡ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠብቃቸ ውን ፡ በጎች ፡ ለሌላ ፡ ጠባቂ ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ሰፈር ፡ ሄደ ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በሳኦል ፡ ፊት ፡ የጀግንነት ፡ ቃሉን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላም ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ ጎል ያድ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጥሩር ፡ ለብሶ ፡ የናስ ፡ ኮር ፡ ደፍቶ ፡ ሰይፍ ፡ ይዞ ፡ ቢቄየው ፡ የእሸናፊውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጋሻ ፡ ከለላ ፡ አድርጎ ፡ በወንጭፍ ፡ ድንጋይ ፡ ከግምባሩ ፡ ላይ ፡ መታው ፤ ሰይፉንም ፡ ከአፎቱ ፡ አውጥቶ ፡ ጥብቅበውን ፡ ቆረጠው ። »

እነሆ ፡ በዚህ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ «ዳዊት ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ሰፈር ፡ ሄደ ፤ ጎልያድን ፡ በድንጋይ ፡ መታው ፤ ጥብቅበውን ፡ ቆረጠው ። » የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ። የቀረው ፡ ግን ፡ ተሳቢና ፡ ተጨማሪ ፡ ነው ።

ስለዚህም ፡ ተሳቢና ፡ የአንቀጽ ፡ ቃል ፡ በዋዊ ፡ ተደጋግሞ ፡ በጅ ፡ ባለቤት ፡ ሲነ ገር ፡ ድርብርብ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

— 292 —

ድርብና ፡ ድርብርብ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ በየሐረጉ ፡ አየተመደበ ፡ የመተንተን ፡ ሰሌዳ ፡ ይደረግለታል ። የአተናተኑም ፡ ሥርዓት ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ነጠላ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ከሰየነው ፡ ምሳሌ ፡ ይልቅ ፡ የተጠነቀቀና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምጸሌ ፡ የተጻፈ ፡ መሆን ፡ አለበት ። የሕፃናትን ፡ አእምሮ ፡ እንጻያሰለች ፡ በማለት ፡ ሰሌዳውን ፡ አውን ፡ በዚህች ፡ በትንሽዋ ፡ መጽሐፋችን ከመጻፍ ፡ ታግሠናል ።

፲፰ኛ ፡ መልመጃ ።

(ሀ) ወረዳተ ፡ ነገር ፣ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ? ፡ — የወረዳተ ፡ ነገር ፡ ስልቱ ፣ ወይም ዓይነቱ ፡ ሰንት ፡ ነው ? ፡ — ከያይነቱ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ምሳሌ ፡ አምጣ ።

(ለ) ወረዳተ ፡ ነገር ፡ የሚሆነው ፡ እንዲት ፡ ያሉ ፡ ቃላት ፡ ሲገኙበት ፡ ነው ? ፡ በለቤት ፡ የሚሆነው ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ነው ? ባለቤት ፡ ለወረዳተ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ይይዝለታል ? ፡ — ለወረዳተ ፡ ነገር ፡ የአንቀጽ ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድን ፡ ነው ?፡

(ሐ) ወረዳተ ፡ ነገር ፡ እንዲት ፡ ሆኖ ፡ በንኡስ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ? ፡ — ሐረግ ፡ ማለት ፡ ትርጓሜው ፡ ምንድን ፡ ነው ? — ንኡስ ፡ ሐረግ ፡ የተባለውን ፡ በምሳሌ ፡ አሳይ። ፲ ፡ ወረዳተ ፡ ነገሮችን ፡ ለምሳሌ ፡ ጻፍ ። እነርሱንም ፡ በወቢይ ፡ ሐረግና ፡ በንኡስ ፡ ሐረግ ፡ ለመከፈል ፡ ይቻል ፡ እንደሆነ ፡ እየለየህ ፡ አመልክት ።

(መ) ከዚህ ፡ በቃች ፡ ከተጻፉት ፡ ወረዳተ ፡ ነገሮች ፡ ባለቤትንና ፡ ዘርፍን ፡ ወይም ፡ ተቀጣይን ፡ እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ አንቀጽንና ፡ ተሳቢን ፡ ተውሳከ ፡ ግሣዊ ፡ መሙሊያ ፡ የተባለውንም ፡ በየግብሩ ፡ እየለየህ ፡ አመልክት ።

የሰው ፡ ልጆች ፡ የሚኖሩበት ፡ ምድር ፡ በጠቅላላው ፡ ዓለም ፡ ተብላ ፡ ትጠራለች ። — ዓለም ፡ በጅ ፡ ታላሰቅ ፡ ክፍሎች ፡ ትከፈላለች ። — ከጅቱ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ አንደኛው ፡ አፍሪከ ፡ ወይም ፡ አፍሪታ ፡ ይባላል ። — በአፍሪከ ፡ ምሥራቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትባል ፡ አገር ፡ ትገኛለች ። — በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ወርጂና ፡ ቁመታ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነበር ። — ኢትዮጵያ ፡ በዱሮ ፡ ዘመን ፡ ባለ ፡ እርባ ፡ አህጉር ፡ ነበረች ። — በአጼ ፡ ክሌብ ፡ ጊዜ ፡ በ፴፯ ፡ አህጉር ፡ ተከፍላ ፡ ነበር ። — ኢትዮጵያ ፡ በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ በ፲፪ ፡ ታላላቅ ፡ አህጉር ፡ ተከፍላለች ። በዱሮ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የባሕር ፡ ጠረፎች ፡ ዋነኞቹ ፡ ምጽዋና ፡ ዘይላ ፡ ናቸው ። በምጽዋ ፡ አጠገብ ፡ ቀድሞ ፡ ድኽኖ ፡ የሚባል ፡ ዋና ፡ ጠረፍ ፡ ነበር ። — የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ አጼ ፡ ክሌብ ፡ ወታደሮቹን ፡ ወደ ፡ የመን ፡ ግዛቹ ፡ ወደ ፡ ናግራን ፡ ከተማ ፡ ሲልክ ፡ የነበረበት ፡ ጠረፍ ፡ ይህ ፡ ድኽኖ ፡ ነው ። አጼ ፡ ክሌብ ፡ መርከቦች ፡ ነበሩት ። በሁኑ ፡ ዘመን ፡ ከ፲፪ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አህጉር ፡ ሐረር ፡ የተባለው ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነው ። በምሥራቃዊ ፡ ደቡቡ ፡ በኩል ፡ ውጋጂን ፡ የተባለ ፡ ሰፊ ፡ አውራጃ ፡ ይገኝበታል ። በውጋጂን ፡ ዕጣንና ፡ ከርቤ ፡ ሙጫ ፡ ከየዛቱ ፡ ሳይ ፡ እየተቀረፈ ፡ ይለቀማል ። — ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ በዘላንነት ፡ የሚኖሩ ፡ የውጋጂን ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። — ከውጋጂን ፡ ስለተወለዱ ፡ ውጋጂኖች ፡ ይባላሉ ። በውጋጂን ፡ ውስጥ ፡ ወልዋል ፡ የሚባል ፡ ሰፍራ ፡ ይገኛል ። — ሀርሰም ፡ ከመቶ ፡ የሚበልጡ ፡ የውሀ ፡ ጕድጓዶች ፡ ይገኙበታል ። እነዚህ ፡ የውሀ ፡ ጕድጓዶች ፡ በዱሮ ፡ ዘመን ፡ የተቈፈሩ ፡ ናቸው ። የጕድጓዶቹ ፡ ጥልቀት ፡ በአንዳንዱ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ፻ ፡ ክንድ ፡ ይረዝማል ። —እነዚህን ፡ ጕድጓዶች ፡ ያስቈፈሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡

እጼ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ በላገርቹ ፡ ውጋጂኖች ፡ ይተርከሉ ። ወልዋል ፡ በጎጻር ፡ ሸንጌ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለተደረገው ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለኢጣሊያ ፡ ግጭት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ስፍራ ፡ ነው ። በውጋጂን ፡ ወንዝ ፡ በዋቢ ፡ ሸበል ፡ ጻር ፡ ለጻር ፡ በእርሻ ፡ የሚኖሩ ፡ ልዩ ፡ ዘሮች ፡ ይገኛሉ ፤ እነርሱም ፡ በአጼ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ የተመሩ ፡ ገባሮችና ፡ ዘላኖች ፡ መሆናቸው ፡ ይተረከላቸዋል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

የቃላት ፡ አገባብ ።

— 293 —

መግለጫ ፡

ቃላት ፡ በንግግር ፡ ተሰካክተው ፡ እንድ ፡ ወረዳተ ፡ ነገርን ፡ ለመሆን ፡ እንዲት ፡ እንደሚችሉ ፡ የምናስታውቅበት ፡ የሰዋስው ፡ ክፍል ፡ አገባብ ፡ ይባላል ።

በአገባብ ፡ ሶስት ፡ ዋኖች ፡ ነገሮች ፡ ይገኙበታል ።

1, ተሰማሚውን ፡ መወሰን ፡
2, ተሳሳቢውን ፡ መወሰን ፡
3, ቅደም ፡ ተከተሉን ፡ መወሰን ፡

ተሰማሚውን ፡ መወሰን ፡ ማለት ፡ አንድና ፡ ብዙን ፡ ሴትና ፡ ወንድን ፡ ሩቅና ፡ ቅርብን ፡ መለየት ፡ ነው ። ተሳሳቢን ፡ መወሰን ፡ ማለት ፡ አንዱ ፡ ቃል ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ የሚሠለጥንበትን ፡ አኳኋን ፡ በየሙያው ፡ ማደራጀት ፡ ነው ። — ቅደም ፡ ተከተልን ፡ መወሰን ፡ ማለት ፡ ቃላት ፡ በወረዳተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙበትን ፡ ስፍራንና ፡ ተራ ፡ መለየት ፡ ነው ።

— 294 —

ባለቤትና ፡ አንቀጽ ።

ባለቤትና ፡ አንቀጽ ፡ በቁጥርም ፡ በጾታም ፡ በመደብም ፡ መመሳሰል ፡ አለበቸው ።

(ሀ) ባለቤቱ ፡ ተባዕታይ ፡ ቢሆን ፡ አንቀጹም ፡ ተባዕታይ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ባለቤቱ ፡ አንስታይ ፡ ቢሆን ፡ አንቀጹም ፡ አንስታይ ፡ መሆን ፡ አለበት ። (ለ) ባለቤት ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ቢነገር ፡ አንቀጽም ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ መነገር ፡ አለበት ። (ሐ) አንቀጹ ፡ በተነገረበት ፡ መደብ ፡ ባለቤቱም ፡ ተሰማሚ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

እጅ ፡—	የታረመ ፡ ንግግር ፡	ያልታረመ ፡ ንግግር ፡
	ገምነህ ፡ መጣ ፡	ገምነህ ፡ መጣች ፡
	ገምነሽ ፡ መጣች ፡	ገምነሽ ፡ መጣ ፡
	ከበደ ፡ መጣ ፡	ከበደ ፡ መጡ ፡(ተ ቁ.306እይ)።
	ከበደና ፡ ገምነህ ፡ መጡ ፡	ከበደና ፡ ገምነህ ፡ መጣ ፡
	እኔ ፡ መጣሁ ፡	እኔ ፡ መጣህ ፡
	አንተ ፡ መጣህ ፡	አንተ ፡ መጣ ፡
	እርሱ ፡ መጣ ፡	እርሱ ፡ መጣሁ ፡

—295—

ባለቤት ፣ ከአንቀጽ ፣ አስቀድሞ ፣ ይገባል ። አንቀጽም ፣ ከባለቤት ፣ በኋላ ፣ ይገ
ባል ። ይህንኑም ፣ በሚከተለው ፣ ምሳሌ ፣ እናሳያለን ።

የታረመ ፣ ንግግር ፤	ያልታረመ ፣ ንግግር ፤
ዝምንህ ፣ መጣ ፣	መጣ ፣ ዝምንህ ፣
ባቡር ፣ መጣ ፣	መጣ ፣ ባቡር ፣
ዳዊት ፣ ጎልያድን ፣ ገደለ ፣	ገደለ ፣ ዳዊት ፣ ጎልያድን ፣

—296—

ባለቤት ፣ በግጥም ፣ ሆኖ ፣ ሲነገር ፣ ከአንቀጽ ፣ በኋላ ፣ ሲገባ ፣ ይገኛል ።

እጅ ፣ እባብ ፣ ሆነ ፣ ውቤ ፣ ሰውነቱን ፣ ትቶ ፣
ሊነክስ ፣ ነው ፣ አሉ ፣ ካቡን ፣ ተጠግቶ ፤

እነሆ ፣ በዚህ ፣ በግጥሙ ፣ ቃል ፣ አንቀጹ ፣ «ሆነ ፣ » ቀድሞአል ፣ ባለቤቱ ፣ ውቤ ፣ ከአንቀጽ ፣ በኋላ ፣ ገብቷል ።

—297—

ባለቤት ፣ የሚገኝ ፣ ከሰምና ፣ ከተውላጠ ፣ ስም ፣ ወይም ፣ እነሱን ፣ መስለው ፣ ከሚነገሩ ፣ ቃላት ፣ ነው ። አንቀጽም ፣ በድቡ ፣ መደቦች ፣ በየዋህ ፣ እርባታ ፣ እየረባ ፣ በተ ነገረ ፣ ጊዜ ፣ በገዛ ፣ ራሱ ፣ ዝርዝር ፣ ባለቤትን ፣ ያመለክታል ። ባለቤት ፣ ቢኖረው ፣ አን ቀጹ ፣ የሚያመለክተው ፣ ቃል ፣ ዝርዝር ፣ ይባላል ። ባለቤት ፣ ባይኖረው ፣ ግን ፣ ያው ፣ ዝርዝሩ ፣ የባለቤት ፣ ምትክ ፣ ይሆናል ።

እጅ ፣ (ሀ) አኔ ፣ ከቤቴ ፣ መጣሁ ፣	እጅ ፣ (ለ) ከቤቴ ፣ መጣሁ ፣
እርስዋ ፣ ወደ ፣ ቤትዋ ፣ ሄደች ፣	ወደቤትዋ ፣ ሄደች ፣
እኛ ፣ ምሳችንን ፣ በላን ።	ምሳችንን ፣ በላን ፣

እነሆ ፣ (ሀ) በተባለው ፣ ማስረጃ ፣ ባለቤቶቹ ፣ «አኔ ፣ እርስዋ ፤ እኛ ፣ » የተባ ሉት ፣ ተውላጠ ፣ ስሞች ፣ ናቸው ፤ በየአንቀጹ ፣ መድረሻ ፣ ላይ ፣ የተጨመሩት ፣ «ሁ» ት ፣ ን ፣ » በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ዝርዝሮች ፣ ናቸው ። (ለ) በሚለው ፣ ማስረጃ ፣ ግን ፣ ተውላጠ ፣ ስሞቹ ፣ «አኔ ፤ እርስዋ ፤ እኛ ፣ » አልተነገሩም ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ ዝርዝሮቹ ፣ «ሁ ፣ ች ፣ ን ፣ » በተውላጠ ፣ ስሞች ፣ ምትክ ፣ ሆነው ፣ የባለቤትነት ፣ ሙያ ፣ ስለያዙ ፣ ባለቤ ቶች ፣ ይባላሉ ።

— 298—

ባለቤትን ፣ ለማወቅ ፣ የሚቻለው ፣ ለተነገረው ፣ አንቀጽ ፣ ማን? ፣ — ወይም ፣ ምን ? ፣ የሚል ፣ ጥያቄን ፣ በማቅረብ ፣ ነው ።

እጅ ፣—«መጣ» ፣ የሚል ፣ አንቀጽ ፣ የተነገረ ፣ እንደሆነ ፣ ማን? ፣ ወይም ፣ ምን? ፣ ተብሎ ፣ ይጠየቃል ። በመልሱም ፣ ባለቤቱ ፣ ይታወቃል ። ይኸውም ፣ ዝምንህ ፣ መጣ ፣ ባቡር ፣ መጣ ፣ ይላል ፣ ማለት ፣ ነው ።

— 299 —

የባለቤት ፣ ዘርፍ ፣ ወይም ፣ ተቀጣይ ።

ዘርፎችና ፣ ተቀጣዮች ፣ ከባለቤት ፣ ይቀድማሉ ። የግዕርግ ፣ ስሞችም ፣ ይህ ንኑ ፣ ደንብ ፣ ይከተላሉ ። ይህንኑም ፣ በሚከተለው ፣ ምሳሌ ፣ እናሳያለን ።

	የታረመ ፣ ንግግር ።	ያልታረመ ፣ ንግግር ።
ዘርፍ ።	የሰማይ ፣ ወፍ ፣ በረረች ፣ የከበደ ፣ ልብስ ፣ ተቀደደ ፣	ወፍ ፣ የሰማይ ፣ በረረች ፣ ልብስ ፣ የከበደ ፣ ተቀደደ ፣
ቅጽል ።	አጭር ፣ ፈረስ ፣ ጠንካራ ፣ ነው ። ትጉህ ፣ ተማሪ ፣ ሰዋስውን ፣ ይማራል ፣	ፈረስ ፣ አጭር ፣ ጠንካራ ፣ ነው ። ተማሪ ፣ ትጉህ ፣ ሰዋስውን ፣ ይማራል ፣
የግዕርግ ፣ ስም ።	አጼ ፣ ዘርዐ ፣ ያዕቆብ ፣ የአልጋ ፣ ወራሹ ፣ አሰፋ ፣ ወሰን ፣ መንገድ ፣ የደጃዝማች ፣ አፈወርቅ ፣ መንገድ ፣ አቶ ፣ አበዬ ፣	ዘርዐ ፣ ያዕቆብ ፣ አጼ ፣ የአሰፋ ፣ ወሰን ፣ አልጋ ፣ ወራሹ ፣ መንገድ የአፈወርቅ ፣ ደጃዝማች ፣ መንገድ ፣ አበዬ ፣ አቶ ።

— 300 —

ዘርፍ ፣ ወይም ፣ ተቀጣይ ፣ የሚሆነው ፣ ቃል ፣ የፈረስ ፣ ስም ፣ ሲሆን ፣ ከባለቤቱ ፣ ቢቀድም ፣ ወይም ፣ ቢከተል ፣ አያስከለክልም ።

እጅ ፣—ጎበና ፣ አባ ፣ ዳጪው ፣ (ወይም ፣ አባ ፣ ዳጪው ፣ ጎበና) ፣ ከአማን ፣ አስከ ፣ አቢጋር ፣ ያለውን ፣ አገር ፣ አቀኑ ፤ እርሳቸውም ፣ በ፲፰፻፱፬ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ሰኔ ፣ ፭፯ ፣ ቀን ፣ ሞተው ፣ ይጠረ ፣ ሊባኖስ ፣ ተቀበሩ ።

— 301 —

ተቀጣይ ፣ ወይም ፣ ዘርፍ ፣ ከአመልካች ፣ ቅጽል ፣ ጋር ፣ ሆኖ ፣ ከባለቤት ፣ በኋላ ፣ በተነገረ ፣ ጊዜ ፣ ተጣማሪ ፣ ባለቤት ፣ ይባላል ። ይኸውም ፣ እንደሚከተለው ፣ ነው ።

ራስ ፣ መኩንን ፣ የጦር ፣ አበጋዙ ፣ በ፲፰፻፱፰ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ጎጃር ፣ ጅጋ ፣ ቀን ፣ እምባላጌ ፣ ላይ ፣ የጠላትን ፣ ጦር ፣ ድል ፣ አደረጉ ።

የጎንደሩ ፣ ንጉሥ ፣ ኢያሱ ፣ አድያም ፣ ሰገድ ፣ በ፲፰፻፲፯ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ጨለያንና ። ጉድሩን ፣ እናርያንም ፣ አስገበሩ ።

አቶ ፣ ዝምንህ ፣ አናጢው ፣ ወደ ፣ ቤታችን ፣ መጣ ።

— 302 —

የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ፡

የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከአንቀጽ ፡ በፊት ፡ ከባለቤት ፡ በኋላ ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ «ዳዊት ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ» ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ተሳቢ ፡ እንደ ፡ ባለ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ዘርፍና ፡ ቅጽል ፡ እያስከተለ ፡ ሊነገር ፡ ይችላል ። አገባቡም ፡ ከሳይ ፡ ስለ ባለቤት ፡ እንደተነገረው ፡ ዓይነት ፡ ነው ። (ቁ. 299 ፡ እይ ፡)

ተሳቢው ፡ በገቢር ፡ አንቀጽ ፡ የሚገዛ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ''ን'' ፡ የሚል ፡ መጥቀሻ ፡ ይጨምርበታል ። ተሳቢውም ፡ ባለ ፡ ዘርፍ ፡ ወይም ፡ ብለቅጽል ፡ ሲሆን ፡ መጥቀሻው ፡ ''ን'' አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በዋናው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በዘርፉ ፡ ወይም ፡ በቅ ጽሉ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ። ዘርፉ ፡ ወይም ፡ ቅጽሉ ፡ ሌላ ፡ ተቀጣይ ፡ ቢኖረው ፡ ግን ፡ መጥቀ ሻው ፡ ''ን'' በሁሉም ፡ ላይ ፡ ሲገባ ፡ ይገኛል ። ሁሉንም ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

አጅ ፡ ዝማነህ ፡ ልብስን ፡ ለበሰ ።
ዝማነህ ፡ ነጭ ፡ ልብስን ፡ ለበሰ ።
ዝማነህ ፡ ነጩን ፡ ልብሱን ፡ ለበሰው ።
ዝማነህ ፡ የከበደን ፡ መጽሐፍ ፡ ወሰደ ።
ፈርዖን ፡ የያዕቆብን ፡ አጅ ፡ ዮሴፍን ፡ አከበረ ።

— 303 —

በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ የሆነ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ በዋዊ ፡ ተጫፍሮ ፡ በተ ነገረ ፡ ጊዜ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጹ ፡ የብዙ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሐ ንስ ፡ መጡ ፡ ቢል ፡ እንጂ ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሐንስ ፡ መጣ ፡ አይልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከግብር ፡ ስሞች ፡ ወገን ፡ አንዳንዶቹ ፡ በዋዊ ፡ ተጫፍረው ፡ ሳለ ፡ በነጠላ ፡ አን ቀጽ ፡ ሲነገሩ ፡ ይገኛሉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በምሥጢር ፡ ተጫፋሪዎች ፡ አይደሉም ። ለም ሳሌ ፡ ''ተድላና ፡ ደስታ ፡ በቤታችን ፡ በዛ'' ፡ ተብሎ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ምሥጢሩ ፡ ተድላ ፡ ከደስታ ፡ ጋር ፡ በቤታችን ፡ በዛ ፡ ማለት ፡ ነው ።

— 304 —

ተውላጠ ፡ ስም ፡

ተውላጠ ፡ ስም ፡ ምትክ ፡ የሚሆንለትን ፡ ስም ፡ በጸታም ፡ በቁጥርም ፡ በመደ ብም ፡ መምሰል ፡ አለበት ።

አጅ ፡—በላይህ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?—እርሱ ፡ ከቤት ፡ ነው ።
መርቅነሽ ፡ ምን ፡ ትሠራለች? ፡—እርስዋ ፡ ትማራለች ።
ልጆች ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ? ፡—እነርሱ ፡ ይጫወታሉ ።

— 305 —

ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ወይም ፡ ከስም ፡ ጋር ፡ በዋዊ ፡ ተጫፍ ረው ፡ በተነገሩ ፡ ጊዜ ፡ አንቀጻቸው ፡ በሚከተለው ፡ ደንብ ፡ ይነገራል ።

(ሀ) ከተጫፋሪቹ ፡ አንዱ ፡ የመጀመሪያው ፡ መደብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አንቀጹ ፡ የመጀመሪያው ፡ መደብ ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ መሆን ፡ አለበት ።

አጅ ፡ እኔና ፡ አንተ ፡ (ወይም ፡ አንተና ፡ እኔ ፡) ጓደኞች ፡ ነን ።
እኔና ፡ እርሱ ፡ እንማራለን ።
እኔና ፡ ከበደ ፡ እንጫወታለን ።

(ለ) ከተጫፋሪቹ ፡ አንዱ ፡ የሌኛው ፡ መደብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ (ነገር ፡ ግን ፡ የመጀመሪያው ፡ መደብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ባይኖር ፡ ነው ፡) አንቀጹ ፡ የዚ ኛው ፡ መደብ ፡ የብዙ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

አጅ ፡ አንተና ፡ እርሱ ፡ (ወይም ፡ እርሱና ፡ አንተ ፡) ነን ፡ እንድትመጡ ።
አንቺና ፡ እርስዋ ፡ ትምህርታችሁን ፡ አጥኑ ።
አንቺም ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ቤታችው ፡ ሂዱ ።
አንተና ፡ ከበደ ፡ ነን ፡ ልብሳችሁን ፡ እንድታጥቡ ፡ ይሁን ።

(ሐ) ተጫፋሪዎቹ ፡ በቮኛው ፡ መደብ ፡ ያሉት ፡ ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ ወይም ፡ ስሞች ፡ ብቻ ፡ የሆኑ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ ያው ፡ የቮኛው ፡ መደብ ፡ አንቀጽ ፡ በብዙ ፡ ይነገራል ።

አጅ—እርሱም ፡ እርስዋም ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።
እርሱና ፡ ከበደ ፡ ጨዋታን ፡ ይወዳሉ ።

— 306 —

የአክብሮት ፡ ቃል ፡ በሚነገበት ፡ ጊዜ ፡ «አንተ ፡ አንቺ ፡» በማለት ፡ ፈንታ ፡ እርስዎ ፡ ይላል ። አንቀጹ ፡ ግን ፡ የሶስተኛው ፡ መደብ ፡ የብዙው ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፡ እርስዎ ፡ መጡ ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

«እርሱ ፡ እርስዋ ፡» በማለት ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ አክብሮት ፡ እርሳቸው ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ። አንቀጹም ፡ እንደራሳቸው ፡ የቮኛው ፡ መደብ ፡ የብዙው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እርሳ ቸው ፡ መጡ ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

«እነርሱ ፡» የሚለው ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ በአክብሮት ፡ ሲሆን ፡ እነእርሳቸው ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ። አንቀጹም ፡ እንደዚያው ፡ እንደራሳቸው ፡ ነው ።

ማስገንዘቢያ ፡ የአክብሮት ፡ ቃል ፡ በሽዋ ፡ አማርኛ ፡ ጥቂት ፡ ተለይቶ ፡ ይገኛል ። ይኸ ውም ፡ በልማድ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጸያፍ ፡ መስሎ ፡ ቢታይ ፡ ሥረ ፡ ነገሩን ፡ የተከተለ ፡ ስለሆነ ፡ አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ጸያፍ ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡ ይቀበሉታል ። «አንተ ፡ አንቺ ፡» የሚለውን ፡ አንቱ ፡ ይላል ። አንቱታ ፡ የሚባለውም ፡ ሥረዩ ፡ ቃል ፡ ከዚሁ ፡ ይገኛል ። አንቀጹም ፡ ያው ፡ የራሱ ፡ መደብ ፡ ይነገርለታል ።

አጅ ፡ አንቱ ፡ ምን ፡ ታደርጋለሁ ። አንቱ ፡ መጽሐፉን ፡ አንሡ ። .....

—307—

ቅጽል ።

ቅጽል ፡ በባለቤት ፡ ወይም ፡ በተሰቢ ፡ ወይም ፡ በዘርፍ ፡ ላይ ፡ እየተጨመረ ፡ ይገ ባል ። በቁጥር ፡ ከሚጨመርበት ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ መመሳሰል ፡ ይገባዋል ። በጾታ ፡ ግን ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ወይም ፡ ግዕዝ ፡ ቀመስና ፡ ግዕዝ ፡ አስተኔ ፡ ቅጽል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባለቤቱን ፡ ለመምሰል ፡ ግዴታ ፡ የለበትም ። ይኸውም ፡ ሴትንና ፡ ወንድን ፡ አይለይም ፡ ማለት ፡ ነው ። ግዕዝ ፡ ቀመስ ፡ የሚባለው ፡ ከግዕዝ ፡ የተመረሰ ፡ ቃል ፡ ነው ። ግዕዝ ፡ አስተኔ ፡ የሚባለው ፡ ግን ፡ ቃሉ ፡ ከግዕዝ ፡ የተገኘ ፡ ሳይሆን ፡ በግዕዙ ፡ ደንብ ፡ የሚነገር ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

አጅ ፡ (ሀ) የዓይነትና ፡ የግብር ፡ ቅጽል ።

ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ተባ.)ቀይ ፡ በፊ	ቀዮች ፡ በፊዎች
አን.)ቀይ ፡ ላም ፡	ቀዮች ላሞች ፡
ተባ.)እውንተኛ ፡ አባት ፡	እውንተኞች ፡ አባቶች ፡
አን.)እውንተኛ ፡ እናት ፡	እውንተኞች ፡ እናቶች ፡
ተባ.)ክፉ ፡ ወንድም ፡	ክፉዎች ፡ ወንድሞች ፡
አን.)ክፉ ፡ እኅት ፡	ክፉዎች ፡ እኅቶች ፡

አጅ ፡ (ለ) ግዕዝ ፡ ጠቀስ ፡ ወይም ፡ (አስተኔ) ፡ ቅጽል

ነጠላ ፡	ብዙ ፡
ርኅሩኅ ፡ አባት ፡	ርኅሩኆች ፡ አባቶች ፡
ርኅርኅት ፡ እናት ፡	ርኅሩኆች ፡ እናቶች ፡
መንፈሳዊ ፡ ወንድም ፡	መንፈሳውያን ፡ ወንድሞች ፡
መንፈሳዊት ፡ እኅት ፡	መንፈሳውያት ፡ እኅቶች ፡
እንግሊዛዊ ፡ ሐኪም ፡	እንግሊዛውያን ፡ ሐኪሞች ፡
እንግሊዛዊት ፡ ሐኪም ፡	እንግሊዛውያት ፡ ሐኪሞች ፡

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ (ሀ) ፡ በተባለው ፡ ማስረጃ ፡ የአማርኛው ፡ ቅጽል ፡ የሴት ንና ፡ የወንድን ፡ ጾታ ፡ ሰይሰይ ፡ ገብቷል ። ይኸውም ፡ ቀይ ፡ በፊ ፡ ቀይ ፡ ላም ፡ ተብ ሏል ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ጾታውን ፡ ለመለየት ፡ ቀዪት ፡ ላም ፡ ያሰኛል፡ ብለው ፡ ይደነግጋሉ ። ቢሆንም ፡ አብዛኛው ፡ ልማድ ፡ ሲያጸድቀው ፡ አይጎናም ። (ለ) በተ ባለው ፡ ማስረጃ ፡ ግዕዝ ፡ ቀመስ ፡ የሆነው ፡ ቅጽል ፡ «መንፈሳዊ ፡ መንፈሳዊት ፡ እያለ ፡ የሴትንና ፡ የወንድን ፡ ጾታ ፡ ለይቶ ፡ አሳያቷል ።

— 308 —

ቅጽል ፡ የማነጻጸር ፡ ወይም ፡ የማወዳደር ፡ ደረጃ ፡ እንዳለው ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ አስታውቀናል ፡ (ተ ፡ ቁ ፡ 117 ፡ አይ ፡) ከእርሱም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ማነጻጸሪያ ፡ አለ ። ይኸ ውም ፡ ክፉ ፡ ብሎ ፡ የክፉ ፡ ክፉ ፡ ደግ ፡ ብሎ ፡ የደግ ፡ ደግ ፤ ፈጣን ፡ ብሎ ፡ የፈጣን ፡ ፈጣን ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

የማረጋገጥና ፡ የማመሳሰልን ፡ ግብር ፡ ለመግለጽ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ቀያይ ፡ ጥቋ ቁር ፡ አጫጭር ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ። ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ቃል ፡ አማራጭ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ አብዝር ፡ እንዳልሆነ ፡ ተመልከት ።

አጅ ፡	ቀይ ፡ በፊ ፡	ቀዮች ፡ በፊዎች ፡	ቀያይ ፡ በፊ ፡	ቀያዮች ፡ በፊዎች ፡
	ደግ ፡ ሰው ፡	ደጎች ፡ ሰዎች ፡	ደጋግ ፡ ሰው ፡	ደጋጎች ፡ ሰዎች ፡
	አጭር ፡ ፈረስ ፡	አጭሮች ፡ ፈረሶች ፡	አጫጭር ፡ ፈረስ ፡	አጫጭሮች ፡ ፈረሶች ፡

«ቀያይ ፡ ደጋግ ፡ አጫጭር ፡» . . . እኒህን ፡ የመሰሉ ፡ ቃላት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በዘልማድ ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ ቢመስሉ ፡ መደባቸው ፡ ከነጠላ ፡ ቁጥር ፡ መሆኑን ፡ እንወስናለን ።

— 309 —

አጎዝ ፡ ቅጽል ፡ ከኔ ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ የብዙ ፡ ቅጽል ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የብዙው ፡ ቁጥር ፡ አጎዝ ፡ ለነጠላ ፡ ስም ፡ ቅጽል ፡ እየሆነ ፡ ተለምዶ ፡ ስለ ፡ ኖረ ፡ ይህ ፡ አዲሱ ፡ ውሳኔ ፡ ሰሚታውን ፡ ሳያሰቅቀው ፡ አይቀርም ። የሚከተለውን ፡ ምሳሌ ፡ ተመልከት ።

በልማድ ፡ የኖረው ፡	አዲሱ ፡ ውሳኔ ፡
ኢየሱስ ፡ በፎ ፡ እንጀራና ፡ በፀ ፡ ዓሣ ፡ ፎ ፡ ሺህ ፡ ሰውን ፡ አጠገበ ።	ኢየሱስ ፡ በፎ ፡ እንጀሮችና ፡ በፀ ፡ ዓሦች ፡ ፎሺህ ፡ ሰዎችን ፡ አጠገበ ።
፪ ፈረስ ፡ በማ ፡ ብር ፡ ገዛሁ ።	፪ ፈረሶችን ፡ በማብሮች ፡ ገዛሁ ።
፪ ልብስ ፡ ያለው ፡ አንዱን ፡ ለሌለው ፡ ይስጥ ።	፪ ልብሶች ፡ ያሉት ፡ አንዱን ፡ ለሌለው ፡ ይስጥ ፡
፪ እግር ፡ እለኝ ፡ ብሎ ፡ ክፋ ፡ ዘፍ ፡ ላይ ፡ የሚወጣ ፡ የለም ።	፪ እግሮች ፡ አሉኝ ፡ ብሎ ፡ ከፀዘሮች ፡ ላይ ፡ የሚወጣ ፡ የለም ።

ማስገንዘቢያ ፡ አዲሱ ፡ ውሳኔ ፡ በመጣቆች ፡ ዘንድ ፡ እስኪለመድ ፡ ድረስ ፡ በልማድ ፡ አን ደኖረው ፡ ሆኖ ፡ ቢጸና ፡ ከጸያፍ ፡ አይቈጠርም ።

— 310 —

ውስጠ ፡ ብዛት ፡ ያላቸው ፡ ቅጽሎች ፡ ቃላቸውን ፡ ሰይለውጡ ፡ ለነጠላ ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ቅጽል ፡ እየሆኑ ፡ ይገባሉ ። ከእነርሱም ፡ ጥቂቶቹን ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

ሁሉ ። — እነሆ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ተከተለው ፡ (ነጠላ ፡ ቁ ፡)
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለትምህርቱ ፡ ይሰሰሉ ፤ (የብዙ ፡ ቁ ፡)

አንዳንድ ። — አንዳንድ ፡ ልጅ ፡ ጨዋታን ፡ ብቻ ፡ ይወድዳል ፡ (ነጠላ ፡ ቁ ፡)
አንዳንድ ፡ ልጆች ፡ ለትምህርት ፡ ይተጋሉ ። (የብዙ ፡ ቁ ፡)

— 311 —

ተውሳክ ፡ ግሥ ።

ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜያት ፡ ከሚገልጸው ፡ ቃል ፡ ሳይርቅ ፡ በአጠገብ ፡ እየሆነ ፡ ይገባል ። ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ የቁጥር ፡ የጾታ ፡ ሥርዓት ፡ የለውም ። ያው ፡ አንዱ ፡ ቃል ፡ ለወንድ ፡ ወይም ፡ ለሴት ፡ ጾታ ፤ በነጠላ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ቁጥር ፡ ለሚነገር ፡ አን ቀጽ ፡ መግለጫ ፡ ይሆናል ።

አጅ ፡ ከበደ ፡ ክፉኛ ፡ ታሚል ፡
ተዋበች ፡ ክፉኛ ፡ ታማለች ፡
ከበደና ፡ ተዋበች ፡ ክፉኛ ፡ ታመዋል ።

— 312 —

መስተዋድድ ።

መስተዋድድ ፡ በስሞች ፡ ወይም ፡ ስሞችን ፡ መስለው ፡ በሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ ላይ ፡ እየተጫነ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ስሞችን ፡ ተሰቢ ፡ ወይም ፡ ተገኝ ፡ ያደርጋቸዋል ። መስተዋድድ ፡ በሚገዛቸው ፡ ቃላት ፡ በመነሻ ፡ ወይም ፡ በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ እየገባ ፡ ይነገራል ።

አጅ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ጎንደር ፡ ሄደ ፡
እርሱ ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

— 313 —

ቅርብና ፡ ሩቅ ።

ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ የሚባሉት ፡ አመልካቾቹ ፡ ቅጽሎች ፡ ''ይህ ፡ ይህች ፤ ያ ፡ ያች ፡'' የሚገለጹባቸው ፡ ቃሎች ፡ ናቸው ። ''ይህ—ይህች ፤'' የቅርብ ፤ ''ያ ፤ ያች ፡'' የሩቅ ፡ ቅጽሎች ፡ (ወይም ፡ አገባቦች ፡) ይባላሉ ። እነዚህ ፡ ቃላት ፤ (ሀ) በባለቤት ፡ ላይ ፡ ሲቀጸሉ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ በባለቤት ፡ ስፍራ ፡ ሲነገሩ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጻቸው ፡ ከርኖው ፡ መደብ ፡ ግሥ ፡ ይገኛል ። (ለ) በተሰቢ ፡ ላይ ፡ ሲቀጸሉ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ በተሰቢነት ፡ ሲነገሩ ፡ ግን ፡ በማንኛውም ፡ የግሥ ፡ መደብ ፡ ያሰስራሉ ። የሚከተለውን ፡ ማስረጃ ፡ ተመልከት ።

አጅ ፡ (ሀ)		አጅ ፡ (ለ)		
ይህ ፡ በፊ ፡ ያ ፡ በፊ ፡	ይዋጋል ፡	ይህን ፡ ወይም ፡ ያን ፡ ይህችን ፡ ወይም ፡ ያችን ፡	መጽሐፍ ፡	ተምሬአለሁ ፡ (ተምረናል ፡) ተምረሃል ፡ ተምረሻል ፡ (ተምራችኋል ፡) ተምርሃል ፡ ተምሬሰች ፡ ተምረዋል ፡
ይህች ፡ ላም ፡ ያች ፡ ላም ፡	አትዋጋም ፡			

እነሆ ፡ (ሀ) በተባለው ፡ ማስረጃ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጹ ፡ የርኖው ፡ መደብ ፡ ግሥ ፡ ብቻ ፡ ሆኖአል ። (ለ) በተባለውም ፡ ማስረጃ ፡ በማንኛውም ፡ የግሥ ፡ መደብ ፡ ሲያሰስር ፡ እንደሚችል ፡ አስረድተናል ።

— 314 —

ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ በአመልካች ፡ ቅጽል ፡ ከፍል ፡ ወይም ፡ አመልካቹ ፡ ቅጽል ፡ በወደቀበት ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይታወቃል ። በተውላጠ ፡ ስምና ፡ በግሥ ፡ መደበኞች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ የለም ። በዘልማድ ፡ ''እንተ ፡ አንቺ'' የሚያሰኘው ፡ ተውላጠ ፡

ስምና ፡ የግሡ ፡ መደብ ፡ የቅርብ፤ እርሱ ፡ እርስዋ ፡ የሚያሰኘው ፡ ተውላጠ ፡ ስምና ፡ የግሡ ፡ መደብ ፡ የሩቅ ፡ ተብሎ ፡ ይነገር ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ የቅርቡም ፡ የሩቁም ፡ ''እርሱ ፡ እርስዋ'' ፡ በሚያሰኘው ፡ በርኖው ፡ መደብ ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ። ለዚሁም ፡ አጭር ፡ ማስረጃ ፡ ''ይህ ፡ ሰው ፡ ሄደ ፤ ያ ፡ ሰው ፡ መጣ'' ፡ ተብሎ ፡ በርኖው ፡ የግሥ ፡ መደብ ፡ ይነገራል ፡ እንጂ ፡ ''ይህ ፡ ሰው ፡ ሄድህ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ መጣህ'' ፡ ተብሎ ፡ በዩኖው ፡ የግሥ ፡ መደብ ፡ አይነገርም ።

ጥያቄ ፡ መልመጃ ፡

(ሀ) ፡ አገባብ ፡ የሚባለው ፡ ምን ፡ የሚደረግበት ፡ ክፍል ፡ ነው ?—በአገባብ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ውሳኔዎች ፡ ይገኙበታል ? ፡—ባለቤትና ፡ አንቀጽ ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ይስማማሉ ?—ባለቤትን ፡ ለማግኘት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ጥያቄን ፡ ታቀርባለህ ?—።

(ለ) ''እኔ ፡ እኛ'' ፡ የሚለው ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ከሌላ ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ በዋዊ ፡ ሲጫ ፈር ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጹ ፡ ከየትኛው ፡ መደብ ፡ ይሆናል ? ፡—''አንተ ፡ አንቺ ፡ እናንተ ፡'' የሚለውስ ፡ ከሌላ ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ ሲጫፈር ፡ አንቀጹ ፡ ከየትኛው ፡ መደብ ፡ ይሆናል ? —ለዚህ ፡ ነገር ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆኑ ፡ ዐሥር ፡ ቃላትን ፡ አምጣ ።—ስለ ፡ ባለቤትና ፡ ስለ ፡ ተሳቢ ፡ ስለ ፡ ዘርፍና ፡ ስለ ፡ ቅጽል ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆኑ ፡ ሯ ፡ ቃላትን ፡ አቅርብህ ፡ ምሳሌ ውን ፡ እያሰናዳህ ፡ ታናገር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

የቃላት ፡ መወራረስ ፡

— 315 —

በአንዱ ፡ ከፍል ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፡ በሌላው ፡ ከፍል ፡ እየገባ ፡ ሲነገር ፡ ይገኛል ። ይህንኑም ፡ ለማስረዳት ፡ ዋቂቶቹን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ ጽፌን ፡ በምሳሌ ፡ እየገለጽን ፡ እናስረዳለን ።

ቃሎች ፡	የንግግር ፡ ከፍሎች ፡	ማስረጃ ፡
ሁሉ ፡	ቅጽል (የመጠን) ፡	ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ተከተለው ፡ (የባለቤት ፡ ቅጽል)
	»(ስለ ፡ ስም ፡ የገቡ)	ሁሉ ፡ የየራሱን ፡ ጉዳይ ፡ ያስባል ። (ብቁ ፡ ባለቤት ፡)
	» »	ሁሉን ፡ መርምሩ ፡ የተሻለውንም ፡ አጽኑ ። (በቂ ፡ ተሰቢ ፡)
	ተ. ስ.	ፈረሰኞችና ፡ እግረኞች ፡ ሲጫወቱ ፡ ውለው ፡ ሁሉም ፡ ሳይ ፡ ሸናኑ ፡ ገቡ ።
ሆነ ፡	ግሥ ፡	ዘንድሮ ፡ የኴነሬ ፡ ጊዜያት ፡ ሆነ ።
	መፃ. (=ወይም ፡)	ሕይወት ፡ ሆነ ፡ ሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ።

ቃሎች ፡	የንግግር ክፍሎች	ማስረጃ ፡
ሌላ ፡	መዋ.(=በቀር ፡)	ከመኰንን ፡ ሌላ ፡ የሚበልጠኝ ፡ የለም ።
	ቅጽል ፡	ዛሬ ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍን ፡ ተቀበልሁ ።
ልክ ፡	ቅጽል ፡	እርሱ ፡ ልክ ፡ ቃልን ፡ ይናገራል ።
	ተ. ግ.	እኔና ፡ እርሱ ፡ ልክ ፡ ደረስን ።
መጀመሪያ ፡	ቅጽል ፡	መጀመሪያው ፡ ማዕርግ ፡ ክቡር ፡ ነው ።
	». (ስለ፡ስም፡የገባ)	የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው ።
	ተ. ግ.	ሽማግሌ ፡ መጀመሪያ ፡ (በመጀመሪያ ፡) ይናገራል ።
ስለ ፡	መዋ.	አስተማሪው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይናገራል ።
	መፃ.	እርሱ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ስለተማረ ፡ ሽልማትን ፡ አገኘ ፡
በቀር ፡	መዋ.	ከበሽተኛ ፡ በቀር ፡ ሁሉም ፡ ይሥራ ።
	መፃ.	ከብቶቹ ፡ ሲጠፉብኝ ፡ በቀር ፡ እኔ ፡ ደኅና ፡ ነኝ ።
ብቻ ፡	ቅጽል ፡	እኔ ፡ ትምህርትን ፡ ብቻ ፡ እወድዳለሁ ።
	ተ. ግ.	ትጉህ ፡ ስለሆንህ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ትበልጠኛለህ ።
	መፃ.	ስዛሬው ፡ ምሬሃለሁ ፡ ብቻ ፡ ለወደፊቱ ፡ ተጠንቀቅ ።
ና ፡	ግሥ ፡(ትእዛዝ ፡)	ወደዚህ ፡ ና ።
	መፃ.(አሟፋፊ ፡)	ከበደ ፡ ና ፡ ዝግንህ ፡ ይጫወታሉ ።
	ተ. ግ.(በገ ፡)	ቤቱን ፡ ከፈተና ፡ (ከፍቶ ፡) ገባ ።
ን ፡	ቅጽል ፡(ጠቃቸ)	ጻዊት ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ ፡ (=ያን ፡ ጎልያድ ፡)
	ተ. ስ.	ወደ ፡ ቤት ፡ ገባን ፡ (=እኛ ፡)
	..	ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወሰደን ፡ (=እኛን ፡)
	..	መጽሐፉን ፡ ስጠን ፡ (=ለእኛ ፡)
	ቃለ ፡ ጥያቄ ፡	ነገ ፡ ትመጣለህን ?
አንዳች ፡	ቅጽል ፡	ልጆቼ ! የምንበላው ፡ አንዳች ፡ እንጀራ ፡ አላችሁን ?
	ተ.ግ.(=ምንም)	በዚህ ፡ ነገር ፡ አንዳች ፡ አላውቅም ፡
አንድ ፡	ቅጽል ፡(የተወሰነ)	አንድ ፡ ፈረስ ፡ አለኝ ፡
	.. (ያልተወሰነ)	አንድ ፡ አምስት ፡ ፈረሶች ፡ አሉኝ ፡ (=ያህል ፡)
እንደ ፡	መዋ.	እንደ ፡ አብርሃም ፡ ቸር ፡ የለም ፡
	መፃ.	ዓለም ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ በሃይማኖት ፡ እናውቃለን ፡
እንጂ ፡	መፃ.	ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ፡ ከክፋ ፡ አድነን ፡ እንጂ ፡
	..	እድናለሁ ፡ እንጂ ፡ አልሞትም ፡
	ቃ. አ. (=አክ)	ትናንት ፡ የመጣው ፡ እርሱ ፡ እንጂ ፡ ነው !
እጅ ፡	ስም ፡	እጅ ፡ ያለው ፡ ሠርቶ ፡ ይብላ ፡
	ተ. ግ.	ጻድቃን ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ከፀሐይ ፡ ኀ ፡ እጅ ፡ ያበራሉ ።

ቃሎች ፡	የንግግር ክፍሎች	ማስረጃ ፡
ከ—	መዋ.	ከጎንደር ፡ መጣ ፡
	ተ. ግ.	የማይሠራ ፡ ከሙት ፡ ይቁጠራል ፡
ከ—ጀምሮ ፡	መዋ.	ከጎንደር ፡ ጀምሮ ፡ ተከትሎኝ ፡ መጣ ፡
	መፃ.	ከመጣሁ ፡ ጀምሮ ፡ አላገኘሁትም ፡
የ ፡	መዋ. (ዘርፍ ፡)	የጻዊት ፡ ቤት ፡ እየሰፋ ፡ ሄደ ፡
	መፃ.	በአሸዋ ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ ቤት ፡ ፈጥኖ ፡ ይፈርሳል ፡
ያህል ፡	ቅጽል.	አምስት ፡ ያህል ፡ መጽሐፍ ፡ ተምሬአለሁ ፡
	..	አንተን ፡ ያህል ፡ ልጅ ፡ ወልጃለሁ ፡
	ተ. ግ.	በልጅረህን ፡ የራስህን ፡ ያህል ፡ ውደደው ፡
ይልቅ ፡	መፃ. (ጥንኛ ፡)	ከጫዋታ ፡ ይልቅ ፡ ትምህርትን ፡ እመርጣለሁ ፡
	.. (ወደረኛ ፡)	ገንዘብ ፡ በማጣትህ ፡ አትዘን ፡ ይልቅ ፡ ጠንክረህ ፡ ሥራ ፡
ወደ ፡	መዋ.	ወደ ፡ አገሩ ፡ ሄደ ፡
	መፃ.	ነፋስ ፡ ወደ ፡ ወደደው ፡ ይነፍሳል ፡
ወዲያ ፡	መዋ.	ከወንዙ ፡ ወዲያ ፡ ዛፍ ፡ አለ ፡
	ተ. ግ.	ከፈቱ ፡ ወዲያ ፡ ሂድ ፡
ጥቂት ፡	ቅጽል ።	ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ አለኝ ፡
	ተ. ግ.	አበክህ ፡ ጥቂት ፡ ታገሠኝ ፡
ፊጽሞ ፡	ግሥ ፡ (በገ ፡)	ጌታችን ፡ በሚኖው ፡ ቀን ፡ ሥራውን ፡ ፈጽሞ ፡ ወረፈ ፡
	ተ. ግ.	አናንተን ፡ ፈጽሞ ፡ አላውቃችሁም ፡

መግለጫ ።

በወረፍተ ፡ ነገር ፡ ተቀነባብረው ፡ የሚገኙ ፡ ቃላት ፡ በየዓይነታቸው ፡ እየተፍታቱ ፡ የሚነገሩባቸው ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ አርእስተ ፡ ነገሮች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በየክፍሉ ፡ ተለይተው ፡ ተጽፈዋል ። በየአንጻሩም ፡ የየነገሩ ፡ ማስረጃ ፡ በምሳሌ ፡ እየተጻፈ ፡ ተገልጸበታል ።

— 317 —

ስም ፣

ማንኛውንም ፣ ነገር ፣ በተለይ ፣ ወይም ፣ በጥቅል ፣ አድርጎ ፣ ለመጥሪያ ፣ የሚስ የመው ፣ ስያሜ ፣ « ስም ፣ » ይበላል ።

ስሞች ፣ ወይም ፣ ስሞችን ፣ የመሰሉ ፣ ነገሮች ፣ በሚከተሉት ፣ አርእስቶች ፣ ይፈታሉ ።

የስም ፣ ዓይነቶች ።

1—የተጸውዖ ፣ ስም ፣ (ይኸውም ፣ አንድ ፣ የታወቀ ፣ ነገር ፣ በልዩ ፣ የሚጠራበት ፣ ነው ።)
አጅ ፣ — ገበየሁ ፣ ጎበና ፣ ሙጋዴን ፣ ግቤ ፣ ጣና ፣ . . .

ድርብ ፣ የተጸውዖ ፣ ስም ። (ይኸውም ፣ የማዕርግ ፣ ወይም ፣ የአክብሮት ፣ ስም ፣ ነው ።)
አጅ ፣ — አጼ ፤ እቴጌ ፤ ደጃዝማች ፤ አቶ ፤ አባባ ፤ አማሞ ፣ . . .

2—የወል ፣ ስም ፣ (ይኸውም ፣ ዓይነቱ ፣ ጅየሆነ ፣ ሁሉ ፣ በዘጎብረት ፣ የሚጠራበት ፣ ነው ።)
አጅ ፣ — አገር ፣ ወንዝ ፤ ተራራ ፣ አንበሳ ፣ ስንዴ ፣ . . .

3—የጥቅል ፣ ስም ፣ (ይኸውም ፣ የማኅበር ፣ ወይም ፣ የነገር ፣ ስም ፣ ነው ።)
አጅ ፣ —ሠራዊት ፣ እንስሳ ፤ እንጨት ፣ አህል ፣ . . .

4—የቂሰቀስ ፣ ስም ፣ (ይኸውም ፣ ለሰው ፣ አገልግሎት ፣ የሚገባ ፣ የቤት ፣ ዕቃ ፣ ነው ።)
አጅ ፣ —ልብስ ፤ አልጋ ፤ መጽሐፍ ፤ ቤት ፤

5—የነገር ፣ ስም ። (ይኸውም ፣ የማይታይ ፣ ወይም ፣ የማይዳሰስ ፣ የነገርና ፣ የግብር ፣ ስም ፣ ነው ።)
አጅ ፣ —ብርሃን ፤ ጨለማ ፤ ክፋት ፤ ደግነት ፤ ሕልም ፤

(ጽታ ፣ ወንን ፣)

1—ተባዕት ፣ (ወንድ ፣) —አባት ፤ ወንድም ፣ በሬ ።
2—እንስት ፣ (ሴት ፣) —እናት ፤ እኅት ፤ ላም ።
3—የወል ። (ወንድ ፣ ወይም ፣ ሴት ፣) — ልጅ ፤ አያት ፤ አስተማሪ ።
4—ግዑዝ ። (ወንድ ፣ ወይም ፣ ሴት ፣ ያልሆነ ፣) — ጠረጴዛ ፤ ቤት ፤ ከክብ ።

ማስገንዘቢያ ። በወል ፣ ጾታ ፣ የሚነገር ፣ ስም ፣ ሁሉ ፣ በአፈታት ፣ ጊዜ ፣ የእን ቀጹን ፣ ጾታ ፣ መውረስ ፣ አለበት ። እነሆ ፣ ለምሳሌ ፣ አስተማሪ ፤ ሴትም ፣ ወን ድም ፣ የሚጠራበት ፣ ቃል ፣ ስለሆነ ፣ የወል ፣ ስም ፣ ተብሏል ፤ በንግግር ፣ ውስጥ ፣ ግን ፣ አስተማሪ ፣ ይናገራል ፣ የተባለ ፣ እንደሆነ ፣ እንቀጹ ፣ ተባዕት ፣ ስለሆነ ፣ ስሙም ፣ ተባዕት ፣ ይባላል ። አስተማሪ ፣ ትናገራለች ፣ የተባለ ፣ እን ደሆነም ፣ እንቀጹ ፣ እንስት ፣ ስለሆነ ፣ ስሙም ፣ እንስት ፣ ይባላል ፣ ማለት ፣ ነው ።

ቁጥር ፣ (አንድነት ፣ ብዙነት ፣)

1 — ነጠላ ። (አንድ ፣ ብቻ ፣ የሆነ ፣)—ቤት ፤ ፈረስ ፤ ጌታ ።

2 — የብዙ ። (ከአንድ ፣ በላይ ፣ የሆነ ፣)—ቤቶች ፤ ፈረሶች ፤ ጌቶች ።

መደብ ፣

1 — ባለቤት ።
ሀ—የአንቀጽ ፣ ባለቤት ። ከበደ ፣ ሄደ ። ገ/ማነህ ፣ መጽሐፉን ፣ ያዘ ።
ለ—ሰሚ ፣ ባለቤት ። —ከበደ ፣ ሂድ ። አባታችን ፣ ሆይ ፣ ስምህ ፣ ይቀደስ ።
ሐ—ተጣማሪ ፣ ባለቤት ። —አለቃ ፣ ምላት ፣ እንከበሬው ፣ ስለጽዳት ፣ ይጠኑቀቁ ፣ ነበር ።

2 — ተሳቢ ።
ሀ—የአንቀጽ ፣ ተሳቢ ። —ዳዊት ፣ ጎልያድን ፣ ገደለ ።
ተጣማሪ ። ዳዊት ፣ ጎልያድን ፣ ፍልስጥኤማዊውን ፣ ገደለ ።
ለ—የመስተዋድድ ፣ ተገዢ ። —እርሱ ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ መጣ ።
ተጣማሪ ። —እርሱ ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ ከቅድስት ፣ ሀገር ፣ መጣ ።
ሐ—ቤተኛ ፣ ተሳቢ ። —በራበኝ ፣ ጊዜ ፣ መብሳትን ፣ እበሳለሁ ።

3 — ዘርፍ ።
ሀ—የባለቤት ፣ ዘርፍ ። የከበደ ፣ ልብስ ፣ ተቀደደ ፣
ተጣማሪ ። —የተማሪው ፣ የከበደ ፣ ልብስ ፣ ተቀደደ ፣
ለ—የተሳቢ ፣ ዘርፍ ። - የከበደን ፣ ልብስ ፣ ቀደደ ፣
ተጣማሪ ። —የተማሪውን ፣ የከበደን ፣ ልብስ ፣ ተደደ ።

— 318 —

ተውላጠ ፣ ስም ።

የስም ፣ ምትክ ፣ ሆኖ ፣ የሚነገር ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ተውላጠ ፣ ስም ፣ ይባላል ። ተው ላጠ ፣ ስም ፣ በሚከተሉት ፣ አርእስቶች ፣ እየተዘረዘረ ፣ ይፈታል ።

የተውላጠ ፣ ስም ፣ ዓይነቶች ።

1—ምድብተ ፣ ስ ።
መደበኛ ፣ ተ.ስ.—እኔ ፣ አንተ ፣ እርሱ ፣ እኛ . . .
ድርብ ፣ ተ.ስ.—እኔ ፣ራሴ ፣ አንተ ፣ ራስህ ፣ እኔ ፣ በገዛ ፣ እጄ . . .
መዘክር ፣ ተ.ስ.—እገሌ ፣ እገሊት ፤ እንትን ፣ እንተን . . .
አጸፋ ፣—ይህ ፤ ያ ፤

2-አልመከች ፣ ተ.ስ
ዝርዝር ፣—ሁ ፤ ህ ፣ ሽ ፤ ው ፣ . . .
አገናዛቢ ፣—ህ ፣ ሽ ፤ ዋ ፣ (—ቤትህ ፣ ቤትሽ ፣ . . .)

3—መጠይቅ ፣ ተ.ስ.—ማን ፣ ምን ፤ የቱ ፤

ጾታ ፣

1—ተባዕት ። (ወንድ ፣) አንተ ፤ እርሱ ፤ እገሌ . . .
2—አንስት ። (ሴት ፣) አንቺ ፣ እርስዋ ፤ እገሊት . . .
3—የወል ። (ወንድ ፣ ወይም ፣ ሴት ፣) እኔ ፣ እኛ ፣ እናንተ ፤ እነእርሱ ፣ እርስዎ ፤ እንተን ፣

ማስገንዘቢያ ፣ የወል ፣ ተ.ስ.—ከሁን ፣ በፊት ፣ በስም ፣ ከፍል ፣ እንደተነገረው ፣ አኳኋን ፣ በአፈታት ፣ ጊዜ ፣ የእንቀጹን ፣ ጾታ ፣ ይወስዳል ።

መደብ ፣	፩ኛ ፣ መደብ ፡—እኔ ፤ እኛ ፣ ፪ኛ ፣ መደብ ፡—አንተ ፤ አንቺ ፤ አናንተ ፤ አርስዎ ፤ እንተን ፡ እንትን ። ፫ኛ ፣ መደብ ፡—እርሱ ፤ እርስዋ ፤ እነርሱ ፤ እንተን ፡ እንትን ፤
ቁጥር ፣	1—ነጠላ ።—እኔ ፤ አንተ ፤ እርሱ ፤ እግሌ ፤ እንተን ፤ እንትን ፤ 2—የብዙ ።—እኛ ፤ አናንተ ፤ እነርሱ ፤ እነእገሌ ፤ እነእንተን ፤ እንትኖች ፤
ጾታ ፣	1—ባለቤት ፡ ሀ—የአንቀጽ ፣ ባለቤት ።—''እርሱ ፡'' ሄደ ። ልብስዋን ፡ ለበሰ ''ች'' ለ—ስሚ ፣ ባለቤት ።—አንተ ፣ ወደቤት ፡ ግባ ። ሐ—ተጣማሪ ፣ ባለቤት ፡—እኔ ፣ ራሴ ፡ አይቼዋለሁ ። 2—ተሰቢ ፡ ሀ—የአንቀጽ ፣ ተገኝ ።—ከበደ ፣ ''እኔን ፡''ጠራኝ ። ከበደ ፣ መታ''ኝ''። ተጣማሪ ፣ ተገኝ ።—እርሱን ፣ ራሱን ፡ አይቼዋለሁ ። ለ—የመስተዋድድ ፣ ተገኝ ።—መጽሐፉን ፡ ለእኔ ፡ ሰጠኝ ። ተጣማሪ ፣ ተገኝ ።—መጽሐፉን ፡ ለእኔ ፡ ለራሴ ፡ ሰጠኝ ። ሐ—ቤተኛ ፣ ተሰቢ ።—ልብስን ፡ ለበሰ ፡ (መልበስን ፡ ለበሰ ፡) 3—ዘርፍ ። ሀ—የባለቤት ፡ ዘርፍ ።—የእርሱ ፡ ቤት ፡ ታነጸ ። ተጣማሪ ፣ የባ ፡ ዘ ።—የእርሱ ፡ የራሱ ፡ ቤት ፡ ታነጸ ። ለ—የተሰቢ ፡ ዘርፍ ።—ከበደ ፡ የእኔን ፡ መጽሐፍ ፡ ወሰደ ። ተጣማሪ ፣ የተ ፡ ዘ ።—ከበደ ፡ የእኔን ፡ የራሴን ፡ መጽሐፍ ፡ ወሰደ ።

ግሥ ።

የንግግር ፡ አሳብ ፡ የሚጠቀለልበት ፤ የማድረግና ፡ የመደረግ ፡ ምግባርም ፡ የሚገለጽበት ፡ ቃል ፡ ግሥ ፡ ይባላል ። ግሥ ፡ በሚከተሉት ፡ አርእስቶች ፡ እየተዘረዘረ ፡ ይፈታል ።

የግሥ ፡ አሰማሙ ፡	1—አድራጊ ።—(ራሱ ፡ የሚያደርግ ፡) —ገደለ ፤ ፈለገ ፡ ተወ ፡ አዘነመ ። 2—አስደራጊ ።—(ሌላውን ፡ የሚያስደርግ ፡) አስገደለ ፡ አስፈለገ ። 3—አደራራጊ ፡ (ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ አንዱንና ፡ ሌላውን ፡ የሚያደራርግ ፡) አጋደለ ፤ አፈላለገ ፤ አማማለ ። 4—አዳራጊ ። (ረዳት ፡ ሆኖ ፡ አንዱን ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ የሚያዳርግ ፡) አጋደለ ፤ አፋለገ ፤ አጋጠመ ። 5—ተደራጊ ።—(ራሱ ፡ የሚደረግ ፡) ተገደለ ፤ ተፈለገ ፤ ግለ ፤ ዘነመ ፤ 6—ተደራራጊ ፡ (እርስ ፡ በርስ ፡ መደራረግ ፡) ተገዳደለ ፤ ተፈላለገ ፤ ተግለለ ፤ 7—ተዳራጊ ። (አንዱና ፡ ሌላው ፡ መደራረግ ፡) ተጋደለ ፤ ተፋለገ ፤

ዓይነት ፡	1—ተሻጋሪ ። (ድርጊቱ ፡ ወደሌላ ፡ የሚያልፍ ፡)—ገደለ ፤ ፈለገ ፤ አስተማረ ፤ 2—የማይሻገር ። (ድርጊቱ ፡ በራሱ ፡ የሚፈጸር ፡)—ሄደ ፤ ለበሰ ፤ ወረሰ ፤ 3—የግሥ ፡ ረዳት ። — አል ፤ ነበር ፤ ጀመር ፡ . . .
ጠባይ ፡	1—ገቢር ። — ፈለገ ፤ አስፈለገ ፤ አፈላለገ ፤ አፋለገ ። 2—ተገብሮ ። — ተፈለገ ፤ ተፈላለገ ፤ ተፋለገ ።
ጾታ ፡	1—ተባዕት ። — (ለወንድ ፡ የሚነገር ፡) ፈለግህ ፤ ፈለገ ፤ 2—እንስት ። — (ለሴት ፡ የሚነገር ፡) ፈለግሽ ፤ ፈለገች ፤ 3—የወል ። —(ለሴትም ፡ ለወንድም ፡ የሚነገር ፡) ፈለግሁ ፡ ፈለግን ፡ ፈለጋችሁ ፡ (ፈለጉ ፡ ''ለአክብሮት ፡'') 4—ሰያፍ ። (ጸታ ፡ ሰይሰይ ፡ የሚነገር ፡) ይፈልጓል ፤ ይመለከቷል ፤ ይሻሉ ።
መደብ ፡	፩ኛ ፡ መደብ ። — ፈለግሁ ፡ — ፈለግን ፤ ፪ኛ ፡ መደብ ። — ፈለግህ ። ፈለግሽ ። ፈለጋችሁ ። (እርስዎ ፡ ፈለጉ ፡) ፫ኛ ፡ መደብ ። — ፈለገ ፤ ፈለገች ፤ ፈለጉ ።
ቁጥር ፡	1—ነጠላ ። — ፈለግሁ ፤ ፈለግህ ፤ ፈለግሽ ፤ ፈለገ ፤ ፈለገች ። 2—የብዙ ። — ፈለግን ፤ ፈለጋችሁ ፤ ፈለጉ ።
ጊዜያት ፡	1—ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ { የዋሀ ፡ ጎላፊ ። —ፈለገ ፤ ተፈለገ ፡ የቅርብ ፡ ጎላፊ ። —ፈልጎአል ። ተፈልጎአል ። የሩቅ ፡ ጎላፊ ። ፈልጎ ፡ ነበር ፤ ተፈልጎ ፡ ነበር ።
	2—የአውን ፡ ጊዜያት ። —ነኝ ፤ ነህ ፤ ነሽ ፤ ነው ። አለሁ ፤ አለህ ፤ . . .
	3—የአውንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡ { የዋሀ ። — ይፈልጋል ። የቅርብ ። — ሊፈልግ ፡ ነው ።
ስልት ፡	1—ወሪይ ፡ አንቀጽ ። —ፈለገ ፤ ፈልጎአል ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ። ይፈልጋል ።
	2—ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ። —ፈልግ ፤ ይፈልግ ። እንዲፈልግ ፡ ይሁን ።
	3—አቁዋይ ፡ { መስተዋምራዊ ። —ቢፈልግ ፡ኖር ፡ፈልጎቢሆን ፡ኖር ። ተምኔታዊ ። —ይፈልግ ፡ ነበር ፤ በፈለገ ፡ ነበር ። ምክንያታዊ ። —(ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ ለብቻው ፡ ተሠርቷል ፡ ቁ. 320 እይ ።)
	4—ንዑስ ፡ አንቀጽ ።—(ለብቻው ፡ ተሠርቷል ፡ ቁ. 321 እይ ።)

— 320 —

ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡

ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ በአዋዋይ ፡ ክፍል ። ''ሙለተኛ ፤ ምክንያተኛ'' ፡ ተብሎ ፡ እንደ ሚነገር ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ አሳይተናል ፡ (ገጽ ፡ ፻፲፯ ፡ እይ) ። አሁንም ፡ ከግሥ ፡ የሚሰይበትን ፡ ሙያ ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ የግሥ ፡ ወገን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በአዕማድ ፡ በዓይነት ፡ በጠባይ ፡ በጸታ ፡ በመደብ ፡ በቁጥር ፡ ከዋናው ፡ ከእናቱ ፡ ግሥ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፤ ቃላትንም ፡ ሲሰጠ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሙያ ፡ የሚከተለውን ፡ ሥርዓት ፡ ይከተላል ።

ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ በምሥጢር ፡ ከአርእስት ፤ ይተባበራል ፤ በጠባይም ፡ ወደ ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ የሚሳብበት ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል ።

ምሳ ፦

1—ሙለተኛ ።

''ዘንድ ፡ ''—ገበሬ ፡ ምግቡን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ (=አገኝ ፡ ብሎ) ይሠራል ።

ልብሴን ፡ አጥብ ፡ ዘንድ ፡ (=አጥብ ፡ ብዬ ፡) ሰሙና ፡ ገዛሁ ።

2—ምክንያተኛ ፡ —

''እንዲ'' ። —ገበሬ ፡ ምግቡን ፡ እንዲያገኝ (=ለማግኘት ፡ ሲል) ይሠራል ።

''እንዳ'' ። —ከንደኞቹ ፡ እንዳላንስ ፡ (=ላለማነስ ፡ ስል ፡) አጠናሁ ።

''እንድ'' ። —አገሬን ፡ እንድሄድ ፡ (=ልሂድ ፡ ብዬ ፡) ተሰናብቻለሁ ።

'' ሊ '' ። —እርሱ ፡ ታሞ ፡ ሊሞት ፡ በሚንቅ ፡ ዳነ ።

'' ላ '' ። —እርሱ ፡ በሚንቅ ፡ ታሞ ፡ ላይሞት ፡ ዳነ ።

'' ል '' ። —ሥራህን ፡ ከጨረስህ ፡ ልትሄድ ፡ (=መሄድን ፡) ትችላለህ ።

— 321 —

ንኡስ ፡ አንቀጽ ።

ከንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ክፍል ፡ ዘር ፡ የሚባለው ፡ በስም ፡ ደንብ ፡ ስለሚነገር ፡ ከዚህ ፡ አናነሣውም ። አሁን ፡ የምንጽፈው ፡ (ሀ) ስለ ፡ «አርእስት ፡ » (ለ) ፡ ስለ ፡ ቦዝ ። (ሐ) ስለ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ። (መ) ስለ ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ነው ።

(ሀ) አርእስት ።

አርእስት ፡ የግሥ ፡ ወገን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በአዕማድ ፤ በዓይነት ፡ በጠባይ ፤ ከዋናው ፡ ከእናቱ ፡ ግሥ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። በግሥ ፡ ደንብ ፡ የሚነገሩት ፡ «ጸታ ፡ መደብ ፤ ቁጥር ፤ ጊዜያት ፤ » በአርእስት ፡ ላይ ፡ አይገኙም ። እንደ ፡ ግሡ ፡ ኃይል ፤ ቃላትን ፡ ይሰጣል ።

አርእስት ፡ የነገር ፡ ስም ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የስም ፡ ሙያዎችን ፡ ይዘ ፡ ይገኛል ። ስም ፡ እንደሚዘረዝርም ፡ ይዘረዘራል ። ይኸውም ፡ መፈለጌ ፡ መፈለግህ ፡ መፈለግሽ ፤ . . . ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ሙያውን ፡ በሚከተለው ፡ ተመልከት ።

ምሳ ፦

1— የአንቀጽ ፡ ባለቤት ። —«ማየት» ፡ ከመስማት ፡ ይበልጣል ።

ዝ.ከ. «መሄድ ፡ » ሁሉን ፡ ያሳያል ።

ዝ.ከ. ከፉን ፡ «መስማት ፡ » ያሳዝናል ።

2—የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ። — እርሱ ፡ ማስተማርን ፡ ይወድዳል ።

ዝ.ከ. የአባቱን ፡ መሞት ፡ ገና ፡ አልሰማም ።

3—የመስተዋድድ ፡ ተገዥ ። ስመስማት ፡ የፈጠንህ ፡ ለመናገር ፡ የዘገየህ ፡ ሁን ።

ዝ.ከ. በመቆም ፡ መሞት ፡ አለ ።

ዝ.ከ. መከራን ፡ በመታገሥ ፡ ክብር ፡ ይገኛል ።

4—የአንቀጽ ፡ መመሪያ ፡— በቡሩ ፡ እንደ ፡ መቆም ፡ አለና ፡ ተጓዘ ።

ቀኑ ፡ እንደ ፡ መምሸት ፡ ብሏል ።

ጠንክሮ ፡ እንደመሥራት ፡ ይግጣል ።

(ለ) ቦዝ ፡ አንቀጽ ።

ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ የግሥ ፡ ወገን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ «በአዕማድ ፤ በዓይነት ፤ በጠባይ ፤ በጸታ ፤ በመደብ ፤ በቁጥር ፤ በጊዜያት ፤ «ከዋናው ፡ ከእናቱ ፡ ግሥ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። አሁን ፡ የምናሳየው ፡ ሙያውን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ምሳ ፦

1—የግሥ ፡ ረዳት ፡ (አል ፡ ነበር ፡ ጀመር ፡ . . . ይጨመሩበታል ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ግሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ይሆናል ።)

ፈልጎአል ፡ ይፈልግአል ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ፡ ይፈልግ ፡ ነበር ።

2—መመሪያ ፡—(በርቱም ፡ መደበኞች ፡ እየረበ ፡ ይገበል ።)

ቤቱን ፡ ከፍቶ ፡ (=ከከፈተ ፡ በኋላ ፡) ገባ ።

ቤቱን ፡ ከፍቼ ፡ (=ከከፈትሁ ፡ በኋላ ፡) ገባሁ ፡ ።

3—ምክንያትን ፡ ሰጭ ፡ (ይኸውም ፡ በቸኮሁ ፡ መደብ ፡ እርሱ ፡ በሚለው ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ።

መርቆ ፡ መብሳት ፡ (=እየሠሩ ፡ መብሳት) ያስመሰማናል ።

እውነትን ፡ ተናግሮ ፡ (=እየተናገሩ ፡) ከመሸበት ፡ ያድራል ።

ለፍቶ ፡ ለፍቶ ፡ መና ፡ መቅረት ፡ ያሳዝናል ።

(ሐ) ግሣዊ ፡ ቅጽል ።

ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ የግሥ ፡ ወገን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ‹በአዕ ግድ › በዓይነት ፡ በጠባይ ፡ በጾታ ፡ በመደብ ፡ በቁጥር ፡ በጊዜያት ፡ ‹ከዋናው ፡ ከእናቱ ፡ ግሥ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ።

ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ በግብሩ ፡ የቅጽል ፡ ወገን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የቅጽልን ፡ ደንብ ፡ ይከተላል ። የመስተየምር ፡ ቃል ፡ ‹የ› ፡ ስለሚጨመርበትም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ መስተየምራዊ ፡ ቅጽል ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ውስጠ ፡ የ ፡ የሚባለው ፡ ቅጽል ፡ የግሥ ፡ ወገን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ተሰቢን ፡ ሲስብ ፡ ይገኛል ። በአፈታት ፡ ግን ፡ የቅጽልን ፡ ደንብ ፡ ብቻ ፡ ይከተላል ። ስለዚህም ፡ ውስጠ ፡ የ ፡ ከዚህ ፡ አልተነገረም ። —አሁን ፡ የምንጽፈው ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ የሚገባበትን ፡ አኳኋን ፡ ለማሰየት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የአገባቡ ፡ አኳኋን ፡	1—ተከታይ ፡ —	የአሰፈ ፡ ከረምት ፡ አይመሰስም ።
	ዝ.ከ.	የተጀመረ ፡ ነገር ፡ መፈጸሙ ፡ አይቀርም ።
	ዝ.ከ.	የሚሞት ፡ ሽማግሌ ፡ አይርገምህ ፡
	2—በቂ—	ውኃን ፡ የተጠማ ፡ (ሰው) ፡ መጥቶ ፡ ይጠጣ ።
	ዝ.ከ.	ብልህ ፡ ሰው ፡ ያለፈውን ፡ (ነገር ፡) አይዘነጋም ፡
	ዝ.ከ.	የሚሄድ ፡ (ሰው ፡) ይሂድ ፡
	3—አረጋጋጭ ፡	(ይኸውም ፡ በመሆን ፡ ግሥ ፡ የሚያሳስር ፡ ሲሆን ፡ ነው ።)
		ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረገው ፡ ከሰማይ ፡ የወረደው ፡ ነው ።

(መ) ሰቢ ፡ ዘር ።

ሰቢ ፡ ዘር ፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ የግሥ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ተሰቢን ፡ ሲስብ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ‹በአዕማድ ፡ በዓይነት ፡ በጠባይ ፡ በጾታ ፡ በመደብ ፡ በጊዜያት› የግሡን ፡ ደንብ ፡ ፈጽሞ ፡ አይከተልም ። በሌላውም ፡ ግብሩ ፡ የስም ፡ ወገን ፡ ነው ። የአንድና ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ አለው ። በሙያም ፡ እንደሚከተለው ፡ ሆኖ ፡ ይነገራል ።

ሙያ ፡	1—ባለቤት ፡—	የሽማግሌ ፡ ‹አክሄድ ፡› በዝግታ ፡ ነው ፡
	2—ተሰቢ ፡—	ብልህ ፡ ሰው ፡ ‹አንጋገርን ፡› ያውቃል ፡
		የነገደር ፡ ደብተራ ፡ ‹ዚቅ ፡ አወራረድን ፡› ያሰምራል ።
	3—ዘርፍ ፡—	ለክህናት ፡ ‹የአቋቋም ፡› ተራ ፡ አሳቸው ።
		የአጻጻፍ ፡ ሥርዓትን ፡ ‹ ሰላሴ ፡ ሳይ ፡ ተማርሁ ። ›
	4—መመ.ሰ.ያ፡—	ለአክሄዱ ፡ ቁም ፡ አለው ።
		ከአነጋገር ፡ ይፈረጻል ፤ ከአያያዝ ፡ ይቀደጻል ።

— 322 —

ቅ ጽ ል ።

በስሞች ፡ ቁይም ፡ ስሞችን ፡ መስለው ፡ በሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ ላይ ፡ እየተጨመረ ፡ የነገሩን ፡ ተግባርና ፡ ዓይነት ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ "ቅጽል" ፡ ይባላል ። ቅጽል ፡ በሚከተሉት ፡ አርእስቶች ፡ እየተዘረዘረ ፡ ይፈታል ።

ዓይነት ፡	1—የዓይነት ፡ ቅጽል ፡	ዓይነት ፡—"ቀይ ፡ ጥቁር ፡ ረጅም ፡ አጭር" ።
		ግብር ፡—"መልከም ፡ ግር ፡ ክፉ ፡ እውነተኛ" ።
		ወገን ፡—"እስራኤላዊ ፡ ተጉለቴ ፡ አማርኛ" ።
	2—የመጠን ፡ ቅጽል ፡	የተወሰነ ፡ አነገገ ፡—"አንድ ፡ ሁለት ፡ ፩ኛ ፡ ፪ኛ" ።
		ያልተወሰነ ፡ አነገገ ፡—"አያሌ ፡ ጥቂት ፡ ሁሉ" ።
		የተወሰነ ፡—"ይህ ፡ ያ ። ያሃች ፡ ይሽኛው ፡ ያኛው" ።
	3—አመልከች ፡ ቅጽል ፡	ያልተወሰነ ፡—"ምንም ፡ ማንኛውም ፡ አንዳች ፡ ሌላ" ።
		ጠቃቢ ፡ "ን" ፡ መጽሐፍን ፡ ያዝ ።
		መስተየምራዊ ፡—የወደቀ ፡ ሰው ፡ ይነሣል ።
ግወዳጅረያ ፡ ደረጃ ፡	1—ተነጻጻሪ ፡—(ቀላል ፡ ቅጽል ፡)—"ብዙ ፡ ጥቂት ፡ ክፉ" ፡	
	2—አብላጭ ፡—አጅግ ፡ ብዙ ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ እጅግ ፡ ክፉ" ።	
		ወይም ፡ "የብዙ ፡ ብዙ ፡ የጥቂት ፡ ጥቂት ፡ የክፉ ፡ ክፉ" ።
	3—አበላላጭ ፡—"አጅግ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥቂት" ።	
		ወይም ፡ "በጣም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ በጣም ፡ የጥቂት ፡ ጥቂት" ።
የአገባቡ ፡ አኳኋን ፡	1—ተከታይ ፡—"እውነተኛ ፡ ሰው ፡ የተከበረ ፡ ነው ። »	
	2—በቂ ፡—"እውነተኛ ፡ ይወደጻል ፡"	
	3—አረጋጋጭ ፡—(በመሆን ፡ ግሥ ፡ የሚያሳስር ፡ ነው ።)	
	"አባቴ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነው ፡" ።	
	"መጽሐፌ ፡ አዲስ ፡ ነው" ።	

— 323 —

ተውሳክ ፡ ግሥ ።

በግሥና ፡ በቅጽል ፡ ላይ ፡ እየተጨመረ ፡ የንግግሩን ፡ ስሜት ፡ እያጐላ ፡ የሚተለጠው ፡ ቃል ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ይባላል ። ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ በሚከተሉት ፡ አርእስቶች ፡ እየተዘረዘረ ፡ ይፈታል ።

ዓይነት ፡	1—የጊዜ ፡ ተ. ግ. ። —(ጊዜን ፡ የሚያመለክት) ፡ እውን ፡ እንግዲህ ፡ ትናንትና ፡ 2—የቦታ ፡ ተ. ግ. ። —(ወዴትነትን ፡ የሚያመለክት ፡) እዘያ ፡ እዘያሃች ፡ በሳይ ፤ በታች ፤ 3—የግብር ፡ ተ. ግ. ። (እንዴትነትን ፡ የሚያመለክት ፤) በቀዋታ ፤ በዝግታ ፤ ክፉኛ ፡ 4—የቁጥር ፡ ተ. ግ. ። —አንዶዬ ፤ ሁለተዬ ፡ ዳግመኛ ፡ በጎብረት ፤ በተለይ ፡ 5—የመጠንና ፡ የማበላለጥ ፡ ተ. ግ. ። —እጅግ ፤ በጣም ፤ በጥቂቱ ፤ አንጻች ። 6—የጥርጥር ፡ ተ. ግ. ። —ምናልባት ፤ እንደተቻለ ፤ ያህል ። 7—የአምንታ ፡ ተ. ግ. ፡ —አዎን ፡ በእርግጥ ፤ በእውነት ፡ 8—የአሉታ ፡ ተ. ግ. ። —እንኳን ፤ እንቢ ፤ 9—ተጣማሪ ፡ ተ. ግ. ። —ቀስ ፡ በቀስ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፤ ፊት ፡ ለፊት ፤ መሰ ፡ ለመሰ ፡ ግማሽ ፡ በግማሽ ፤ ቀን ፡ በቀን ፡ . . .
ማመዳደሪያ ፡ ደረጃ	1—ተነጻጻሪ ። —(ቀላል ፡ ተ. ግ.) ክፉኛ ፡ ታሟል ። በዝግታ ፡ ይሄዳል ። 2—አብላጭ ። —በጣም ፡ ክፉኛ ፡ ታሟል ። በጣም ፡ በዝግታ ፡ ይሄዳል ። 3—አበላላጭ ። —እጅግ ፡ በጣም ፡ ክፉኛ ፡ ታሟል ። እጅግ ፡ በጣም ፡ በዝግታ ፡ ይሄዳል ። ማስተንበቢያ ፡ አብዛኞቹ ፡ ተውሰከ ፡ ግሦች ፡ የመወዳደር ፡ ደረጃ ፡ ሰይፈልጉ ፡ እንዲያው ፡ በቀላሉ ፡ ይነገራሉ ።
የአገባብ ፡ አጋዥ ፡	1—ተከታይ ፡—ክፉኛ ፡ ታሟል ፤ በእርግጥ ፡ አይቼዋለሁ ፤ ፈርቶ ፡ ሸሸ ። 2—አረጋጋጭ ፡ (በመሆን ፡ ግሥ ፡ የሚያሰር ፡ ነው ።) የምመስክረው ፡ በእውነት ፡ ነው ። የታመመው ፡ ክፉኛ ፡ ነው ።

— 324 —

መስተዋድድ ።

ስሞችና ፡ ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ ከሌላው ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ የሚዘመዱበት ፡ ወይም ፡ የሚዋቀዱበት ፡ ቃል ፡ መስተዋድድ ፡ ይባላል ።

መስተዋድድ ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ ይዘረዘራል ።

ዓይነት ፡	1—የዋህ ፡ መዋ ፡	ህ—መነሻ ፡—ከ ፡ ለ—መገስገሻ ፡—ወደ ፡ እ ፡ ሐ—መድረሻ ፡—እስከ ፡ መ—ማድረጊያ—በ ፡ ሠ—ማንጸሪያ—እንደ ፡ ረ—አቀባይ ፡—ለ ፡
	2—ተደራራቢ ፡	ህ—በመነሻ ፡ የሚገባ ፡—ከወደ ፡ ለ—በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ የሚገቡ ፡ ከ—ጋር ፡ በ—ላይ . .

— 325 —

መስተዋምር ።

ሐረጎች ፡ ወይም ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ የሚያያዙበት ፡ ቃል ፡ መስተዋምር ፡ ይባላል ። መስተዋምር ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ ይዘረዘራል ።

ዓይነት ፡	1—ወደረኛ ፡ መዋ ፡ —«ም ፡ ና ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ወይም ፡ ይሁን ፡ እንጂ» አጅ ፡ እርሱ ፡ ጎበዝ ፡ ነው ፡ ይሁን ፡ ንንጂ ፡ አቅድ ፡ አያውቅም ፡ 2—ጥገኛ ፡ መዋ ፡ «ስለ ፡ እንደ ፡ ከ ፤ ቢ ፤ ሲ ፤ እስከ—ድረስ ፡ » አጅ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ስለተከፈተ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

— 326 —

የአፈታት ፡ ምሳሌ ።

የአፈታት ፡ አኳኋን ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ በሚከተለው ፡ ምሳሌ ፡ እናሳያለን ።

(ሀ) ፡ በድቡሽት ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ ቤት ፡ /ከባድ ፡ ዝናም ፡ ሲዘንም ፡ /ወዲያው ፡ በቶሎ ፡ ይፈርሳል ።

በድቡሽት ፡ ላይ ፡	(1) በ—ላይ ፡ ተደራራቢ ፡ መስተዋድድ ፡ ነው ። ድቡሽት ፡ የሚለውን ፡ ስም ፡ ተገዥ ፡ አደርጎ ፡ በመከከሉ ፡ ይዘ ፡ ገብቶ ፡ «የተሠራ» ከሚለው ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ጋር ፡ አዛምዷል ። (2) ድቡሽት ፡ — የወል ፡ ስም ፡ ነው ። ግዑዝ ፡ ጾታ ፡ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ነው ። ሙያው ፡ ተሳቢ ፡ ነው ። መስተዋድዱ ፡ በ — ላይ ፡ በመነሻውና ፡ በመድረሻው ፡ ገብቶ ፡ ተገዥ ፡ አደርጎታል ። «የተሠራ ፡ » ለሚለውም ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ''አርቴፅ ፡ ተሳቢ ፡ '' ፡ ሆኖአል ።
የተሠራ ፡	ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ነው ። በተባዕት ፡ ጾታ ፤ በነጠላ ፡ ቁጥር ፤ በጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ ተንግሮአል ። «ቤት ፡ » በሚለው ፡ ስም ፡ ላይ ፡ ተከታይ ፡ ውስጠ ፡ የ ፡ ሆኖ ፡ ተቀጽሎአል ። «በድቡሽት ፡ ላይ ፡ » የሚለውም ፡ የመስተዋድድ ፡ ተገዥ ፡ አርቴፅ ፡ ተሳቢ ፡ ሆኖታል ። — በግሥነት ፡ ባሕርዩም ፡ —ተደራጊ ፡ ወምድ ፡ የማይሻገር ፡ ዓይነት ፡ ተገብሮ ፡ ጠባይ ፡ ነው ።
ቤት ፡	የቄሰቀሱስ ፡ ስም ፡ ነው ። በግዑዝ ፡ ጾታ ፤ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ተንግሮአል ። ሙያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ባለቤትነቱም ፡ ለማሰሪያ ፡ አንቀጹ ፡ ለ «ይፈርሳል ፡ » ነው ።
ከባድ ፡	የግብር ፡ ቅጽል ፡ ነው ። በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ተንግሮአል ። ዝናም ፡ በሚለው ፡ ስም ፡ ላይ ፡ ተከታይ ፡ ውስጠ ፡ የ ፡ ሆኖ ፡ ተቀጽሎአል ። ቅጽል ፡ ተቀባዩ ፡ « ዝናም ፡ » በወንድ ፡ አንቀጽ ፡ ከመነጩ ፡ የተነሣ ፡ የቅጽሉ ፡ ጾታ ፡ ተባዕት ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ግናም ፡ የወል ፡ ስም ፡ ነው ። በግዑዝ ፡ ጾታ ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ተነግሮአል ። መ.ያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ባለቤትነቱም ፡ መስተፃምር ፡ ለተጫነው ፡ « ይዘ ንም ፡ » ለሚለው ፡ ለበዙ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

ሲ.ዘንም ፡ (1) ''ሲ'' ፡ (=ስ) ጊዜን ፡ የሚያመለክት ፡ ጥገኛ ፡ መስተፃምር ፡ ነው ። ይዘንም ፡ በሚለው ፡ ትንቢታዊ ፡ ቦዝ ፡ ላይ ፡ ተጭኖ ፡ ገብቶአል ፡ «ገናም ፡ ይዘንም ፡ » የሚለውንና ፡«ቤት ፡ ይፈርሰል ፡ » የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ አያይዘአል ። «ስ» የነበረው ፡ መሠረታዊ ፡ ቃሉ ፡ «ይ» የሚለውን ፡ የአ ርዓታ ፡ መረ ፡ ውጤ ፡ «ሲ» ተብሳ.ል ። ስለዚህም ፡ ስይዘንም ፡ በመባል ፡ ፈንታ ፡ «ሲ.ዘንም ፡ » ተብሳ.ል ።

(2) ''ይዘንም'' ፡ ትንቢታዊ ፡ ቦዝ ፡ ነው ። በተባዕት ፡ ጾታ ፤ በቮኛ ፡ መደብ ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ተነግሮአል ። መስተፃምሩ ፡ «ስ» ወድቆበት ፡ «ሲ.ዘንም ፡ » ተብሎ ፡ ተነግሮአል ።

(1)ወዲያው (2) በቶሎ ፡ ይፈርሰል ፡ የጊዜ ፡ ተውሳክ ፡ ግሥ ፡ ነው ። ተደራርቦ ፡ ተነግሮ ፡ የማሰሪያ ፡ አን ቀጹን ፡ የያፈርሳልን ፡ » ሁኔታ ፡ ገልጾአል ።

ግሥ ፡ ነው ። ተደራጊ ፡ ወምድ ፡ የማይሻገር ፡ ዓይነት ፤ ተገብሮ ፡ ጠባይ ፡ ነው ። በተባዕት ፡ ጾታ ፡ በቮኛ ፡ መደብ ፤ በነጠላ ፡ ቁጥር ፤ በአው ንና ፡ በትንቢት ፡ ጊዜያት ፡ የተነገረ ፡ ወቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። «ቤት ፡ » ለሚ ለው ፡ ለወረፍተ ፡ ነገሩ ፡ ባለቤት ፤ ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ሆኖ ፡ ተነግሮአል ።

(ለ) ያለ ፡ ሀገር ፡ /ሕይወታዊ ፡ ኑሮን ፡ ማግኘትና ፡ /ተጠቃሚ ፡ መሆን ፡ /የማይ ገኝ ፡ መሆኑን ፡ /ስንኳን ፡ እኛ ፡ /ሌላውም ፡ ቢሆን ፡ ሲ.ያውቀው ፡ ይችላልና ፡/ ስለ ፡ ሕይወት ፡ /ሕይወት ፡ ከልተሠዋ ፡ /ሕይወት ፡ አይገኝም ።

ያለ ፡ ሀገር ፡ (1) ''ያለ'' ፡ —የዋሀ ፡ መስተዋድድ ፡ ነው ፤ የአሉታ ፡ ምግባር ፡ ይገ ለጽበታል ። ''ሀገር'' ፡ የሚለውን ፡ ስም ፡ ''የማይገኝ'' ፡ ከሚለው ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ጋር ፡ አዛምዶታል ።

(2) ''ሀገር'' ፡ የወል ፡ ስም ፡ ነው ፤ —ግዑዝ ፡ ጾታ ፤ —ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ነው ፤ መ.ያው ፡ የመስተዋድድ ፡ ተገኘ ፡ ነው ። መስተዋድዱ ፡ ''ያለ'' ፡ በመነሻ ፡ ወድቆበት ፡ ተገዥ ፡ አድርጎታል ። ''የማይገኝ ፡ '' ለሚለውም ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ኢርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ ሆኖ ፡ ገብቶአል ።

ሕይወታዊ ፡ ተክታይ ፡ የግብር ፡ ቅጽል ፡ ነው ። — ተባዕት ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ነው ። ''ኑሮ'' ፡ በሚለው ፡ የነገር ፡ ስም ፡ ላይ ፡ ተቀጽሎአል ።

ኑሮን ፡ (1) ''ኑሮ'' ፡ — የነገር ፡ ስም ፡ ነው ። — ግዑዝ ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ነው ። መ.ያው ፡ ተሳቢ ፡ ነው ። ''ማግኘት'' ፡ ለሚለው ፡ የግሥ ፡ አርእስት ፡ ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ ሆኖ ፡ ገብቷል ። ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ በመባልም ፡ ፈንታ ፡ አን ዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቁጥጥኛ ፡ ተሳቢ ፡ ይባላል ።

(2) ''ን'' ። በቅጽል ፡ ክፍል ፡ ጠቃሽ ፡ አመልካች ፡ ነው ። ''ኑሮ'' በሚለው ፡ የነገር ፡ ስም ፡ መድረሻ ፡ ላይ ፡ ተጨምሮ ፡ ለግሡ ፡ አርእስት ፡ ለ''ማግኘት'' ፡ ርቱዕ ፡ ተሳቢነቱን ፡ የሚያመለክት ፡ ሆኖአል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የነቢር ፡ ምልክት ፡ ይባላል ።

ማግኘትና ፡ (1) ''ማግኘት'' ። የግሥ ፡ አገኘ ፡ አርእስት ፡ ነው ። በግብሩ ፡ የነ ገር ፡ ስም ፡ ይባላል ፡ "ና" ፡ የሚለው ፡ ወደረኛ ፡ መቸተፃምር ፤ 'መሆን' ከሚለው ፡ ከዚኛው ፡ ሐረግ ፡ ጋር ፡ አያይዘታል ። መ.ያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ባለቤትነቱም ፡ ''የማይገኝ'' ፡ ለሚለው ፡ ለግሣዊው ፡ ቅጽል ፡ ነው ። በግሥነት ፡ ባሕርዩም ፡ አድራጊ ፡ ወምድ ፤ ተሻጋሪ ፡ ዓይነት ፤ ገቢር ፡ ጠባይ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ''ሕይወታዊ ፡ ኑሮን'' የሚለውን ፡ ቃል ፡ ቀጥ ተኛ ፡ ወይም ፡ ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ አደርጎታል ።

(2) ''ና'' ወደረኛ ፡ መስተፃምር ፡ ነው ። በግብሩ ፡ አሚፋሪ ፡ ይባ ላል ። ''ማግኘት'' ፡ የሚለውን ፡ የፊተኛውን ፡ ሐረግ ፡ ''መሆን'' የሚለውን ፡ የዚኛውን ፡ ሐረግ ፡ አያይዘአቸዋል ። ይህም ፡ መስተፃምር ፡ በንባብ ፡ አሚፋሪ ፡ ሲመስል ፡ በምሥጢር ፡ አዳጋሚ ፡ ነው ። ትርጓሜውም ፡ ''ወይም'' ፡ ማለት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የቃሉቹ ፡ አንቀጽ ፡ በነጠላ ፡ ስለ ተነገረ ፡ ነው ።

ተጠቃሚ ፡ የግብር ፡ ቅጽል ፡ ነው ። ውስጠ ፡ የ ፤ የወል ፡ ጾታ ፡ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ነው ፤ መ.ያው ፡ ተሳቢ ፡ ነው ። ''መሆን'' ለሚለው ፡ የግሥ ፡ አርእስት ፡ ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ ሆኖ ፡ ገብቶአል ። በቂ ፡ ሆኖ ፡ ተነግሮአል ። ይኸውም ፡ ''ተጠቃሚ ፡ ስውን ፡ መሆን ፡ ለ.ል ፡ በተገባው ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ ነው ። የገ ቢሩ ፡ ምልክት ፡ ''ን'' ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቶአል ። —

(ሰው) ፡ ተጠቃሚ ፡ በሚለው ፡ ውስጠ ፡ የ ፡ ቅጽል ፡ ላይ ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቶአል ።

መሆን ፡ የግሥ ፡ ሆነ ፡ አርእስት ፡ ነው ። ''ና'' በሚለው ፡ ወደረኛ ፡ መስተፃ ምር ፡ ''ማግኘት'' ፡ ከሚለው ፡ ከፍተኛው ፡ ሐረግ ፡ ጋር ፡ ተጫምሮ ፡ ተያ ይዞአል ። መ.ያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ባለቤትነቱም ፡ «የማይገኝ ፡ » ለሚለው ለግሣዊው ፡ ቅጽል ፡ ነው ። — በግሥነት ፡ ባሕርዩም ፡ ተደራጊ ፡ ወምድ ፡ የማይሻገር ፡ ዓይነት ፡ ገቢር ፡ ጠባይ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ''ተጠቃሚ'' የሚለ ውን ፡ በቂ ፡ ቅጽል ፡ ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ አድርጎታል ።

የማይገኝ ፡ ግሣዊ ፡ ቅጽል ፡ ነው ። በአሉታ ፡ ተነግሮአል ። — ግልጾ ፡ የ ፤ ተባ ዕት ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ነው ። መ.ያው ፡ ተሳቢ ፡ ነው ። ''መሆኑን'' ፡ ለሚለው ፡ የግሥ ፡ አርእስት ፡ ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ ሆኖ ፡ ገብቶአል ። በቂ ፡ ሆኖ ፡ ተነግሮአል ። ይኸውም ፡ « የማይገኝ ፡ ነገር ፡ ሊ.ል ፡» በተገባው ፡ ነገር ፡

ማለት ፡ ነው ። የገቢሩ ፡ ምልክት ፡ «ን»ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቶ አል ። — በግሥነት ፡ በሕርዩም ፤ ተደራጊ ፡ ዐምድ ፤ የማይሻገር ፡ ዓይነት ፡ ተገብሮ ፡ ጠባይ ፡ ተባዕት ፡ ጾታ ፤ ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ የአሁንና ፡ የትን ቢት ፡ ጊዜያት ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ «ሕይወታዊ ፡ ኑሮን ፡ ማሟንትና ፡ ተጠ ቃሚ ፡ መሆን ፡ » የተባሉት ፡ በመስተዋምር ፡ የተያያዙት ፡ ፪ቱ ፡ የተሰቢ፡ ሐረጎች ፤ ባለቤቶች ፡ ሆነው ሲታል ። « ያለ ፡ ሀገር ፡ » የሚለውም ፡ የመስ ተዋድድ ፡ ተገኘ ፡ ኢርቱዕ ፡ ተሰቢው ፡ ነው ።

(ነገር ፡) የማይገኝ ፡ በሚለው ፡ ግዛዊ ፡ ቅጽል ፡ ላይ ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቷል ።

መሆኑን ፡ 1 « መሆን ፡ » የግሥ ፡ ሆነ ፡ አርእስት ፡ ነው ። በግብሩም ፡ የነገር ፡ ስም ፡ ነው ። በስም ፡ ደንብ ፡ ስለተዘረዘረ ፡ ሳድስ ፡ የነበረው ፡ የቃሉ ፡ መድ ረሻ ፡ ክፅብ ፡ ሆኖአል ። (.ቁ.180) እይ ። ገቢር ፡ የሚያደርገው ፡ ጠቃሽ ፡ አመልካቹ ፡ «ን» ተጨምሮበታል ። ሙያው ፡ ተሰቢ ፡ ነው ። — « ሲያው ቀው ፤ » ለሚለው ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ ርቱዕ ፡ ተሰቢ ፡ ሆኖ ፡ ገብቶአል ። መስተዋምሩ ፡ « ና » (= ይችላልና) ፡ ለሚያያይዘው ፡ ለዋናው ፡ ሐረግ ፡ ቀጥ ተኛ ፡ ተሰቢው ፡ ይኸው ፡ ቃል ፡ (= መሆኑን ፡) ነው ፡ — የግሥነት ፡ ባሕ ርዩም ፡ ከላይ ፡ እንደተነገረው ፡ ነው ። የግሥ ፡ ወገን ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ «የማይገኝ ፡ » የሚለው ፡ በቂ ፡ ቅጽል ፡ ከነጓዙ ፡ ተሰቢ ፡ ሆኖታል ።

ስንኳን ፡ የምክንያት ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ነው ። ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ የቀረ ውን ፡ የአዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ ሁኔታ ፡ ይገልጻል ። ይኸውም ፡ « ስንኳን ፡ እኛ ፡ ልናጣው ፡ » ያሰኝ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

እኛ ፡ ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ነው ። — የወል ፡ ጾታ ፤ — ፩ደኛ ፡ መደብ ፤ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ ነው ፤ — ሙያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ባለቤትነቱ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ለቀረው ፡ አዋዋይ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ይኸውም፡ «ስንኳን ፡ እኛ ፡ ልናጣው ፡ » ያሰኛል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ልናጣው ፡ ምክንያተኛ ፡ አዋዋይ ፡ ነው ። ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቷል ። ይኸውም ፡ «ሲያውቀው ፡ » በሚለው ፡ በተከታዩ ፡ ቃል ፡ ይታወቃል ።

ሌላውም ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ንግግር ፡ አምስት ፡ ቃሎች ፡ ይገኙበታል ። (ሌላ — ው — ም — (ሰው) ፡ ብ — ይሆን ።)

(ሀ) «ሌላ » ፡ — አመልካች ፡ ቅጽል ፡ ነው ። ብቻውን ፡ ስለተነገረ ፡ በቂ ፡ ሆኖአል ፤ ሙያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ባለቤትነቱ ፡ መስተዋምር ፡ ለተጫነው ፡ ''ይሆን ፡ '' ለሚለው ፡ ለትንቢታዊው ፡ ቦዝ ፡ ነው ።

(ለ) «ው» ፡ — ያልተወሰነ ፡ አመልካች ፡ ነው ። ትርጓሜው ፡ ማንኛ ውም ፡ ማለት ፡ ነው ። በቂ ፡ ሆኖ ፡ በተነገረው ፡ «ሌላ ፡»በሚለው ፡ ቃል፡ ላይ ፡ ተጭኖ ፡ ያልተወሰነ ፡ አመልክች ፡ ሆኖአል ።

(ሐ) «—(ም)፡— አጻጋሚ ፡ መስተዋምር ፡ ነው ። በግዕዝ ፡ ሰዋስው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተለመደው ፡ ስሙ ፡ ዋዊ ፡ ይጠላል ፡ «እኛ» በሚለው ፡ በፈተኛው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ «ሌላ ፡» የሚለው ፡ ቃል ፡ መደገሙን ፡ ያሳያል ።)

(ሰው) ፡ (መ) ''ሰው'' ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቷል ። ይኸውም ፡ «ሰላ ውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ » ያሰኝ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። —

(ሠ) ''ቢ'' (ተ) አጋናኝ ፡ መስተዋምር ፡ ነው ። «ይሆን» በሚለው ፡ በትንቢታዊ ፡ ቦዝ ፡ ላይ ፡ ተጭኖ ፡ ገብቶአል ። «ተ» ያሰኝ ፡ የነበረው ፡ መሠ ረታዊ ፡ ቃሉ ፡ «ይ» የሚለውን ፡ የእርባታ ፡ መሪ ፡ ውጠ፤ ማልሰ ፡ ሆኖ ፡ ''ቢ'' ተብሏል ። ስለዚህም ፡ ብይሆን ፡ በመባል ፡ ፈንታ ፡ «ቢሆን» ፡ ተብሎ ፡ ተነግ ሮአል ። ይህ ፡ መስተዋምር ፡ አጋናኝ ፡ መበሉ ፡ በምሥጢር ፡ «እንኳ ፡» የሚል ፡ ስሚት ፡ ስለሚገኝበት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ''ሌላውም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ'' ፡ ያሰኛል ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ መስተዋምር ፡ «ስንኳን ፡ እኛ ፡ » የሚለውና ፡ ''ሌላውም ፡ ቢሆን ፡'' የሚለው ፡ ሐረግ ፡ ተያይዘበታል ።

(ረ) «ይሆን ፡ » ትንቢታዊ ፡ ቦዝ ፡ ነው ። በተባዕት ፡ ጾታ ፤ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ በቮኛ ፡ መደብ ፡ ተነግሮአል ። የግሥነት ፡ ባሕርዩም ፡ ከላይ ፡ «መሆን ፡ » ከሚለው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ነው ። «ሌላ ፡ » የሚለው ፡ በቂ ፡ ቅጽል ፡ ባለቤት ፡ ሆኖታል ። መስተዋምሩ ፡ «ው» ስለተጫነውም ፡ የእርባታ ፡ መሪው ፡ ተውጦ ፡ «ቢሆን ፡ » ተብሎ ፡ ተነግሮአል ።

ሊያውቀው ፡ ምክንያተኛ ፡ አዋዋይ ፡ ነው ። በተባዕት ፡ ጾታ ፡ በቮኛ ፡ መደብ ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ በትንቢታዊ ፡ ጊዜያት ፡ — ተነግሮአል ። በግሥነት ፡ ባሕር ዩም ፡ አድራጊ ፡ ዐምድ ፡ ተሻጋሪ ፡ ዓይነት ፤ ገቢር ፡ ጠባይ ፡ ነው ። «ሌላ» ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ባለቤት ፡ ሆኖታል ። «የማይገኝ ፡ መሆኑን ፡ » የሚለውንም ፡ ቃል ፤ ርቱዕ ፡ ተሰቢ ፡ አድርጎታል ። የአገባቡ ፡ ሥርዓት ፡ በተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ክፍል ፡ ስለሆነ ፡ ተሰሳቢዎቹን ፡ ጨምሮ ፡ «ይችላል» የሚለውን ፡ የአንቀጽ ፡ ተግባር ፡ ይገልጻል ። «ው» የሚል ፡ የተሰቢ ፡ ዝርዝር ፡ ተጨምሮበታል ። ዝርዝሩ ፡ የሚያሳየው ፡ ተሰቢውን ፡ «የማይገኝ ፡ መሆኑን ፡ » የሚለውን ፡ ቃል ፡ ነው ።

ይችላልና ፡ በዚህ ፡ ንግግር ፡ ፱ ፡ ቃሎች ፡ አሉ ፤ (ይችላል—ና ፡)

(ሀ) ይችላል ። በተባዕት ፡ ጾታ ፡ በቮኛ ፡ መደብ ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ የተነገረ ፡ የአሁንና ፡ የትንቢት ፡ ጊዜያት ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። በአሰማድ ፡ መደ ቡም ፡ አድራጊ ፡ ዐምድ ፤ የማይሻገር ፡ ዓይነት ፤ ገቢር ፡ ጠባይ ፡ ነው ። «ሲያ ውቀው ፡ » የሚለው ፡ ምክንያተኛው ፡ አዋዋይ ፡ በተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ደንብ ፡ ገብቶ ፡ ተግባሩን ፡ ገልጾአታል ። «ና» የሚለውም ፡ መስተዋምር ፡ ስለወደቀ በት ፡ ከግሰሪያነት ፡ ታግዶአል ።

(ለ) «ና» ምክንያት ፡ መስተዋምር ፡ ነው ። ትርጓሜው ፡ «ስለ» ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ይችላልና ፡— ስለሚችል) ይችላል ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ተጭኖ ፡ ማሰሪያነቱን ፡ አስቀርቷል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮቹን ፡ እንዲያያዙ ፡ አድርጎአቸዋል ። ይኸውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። (ሀ) ''ያለ ፡ ሀገር ፡ ሕይወታዊ ፡ ኑሮን ፡ ማግኘትና ፡ ተጠቃሚ ፡ መሆን ፡ የማይገኝ ፡ መሆኑን ፡ ስንኳን ፡ እኛ ፤ ሌሳውም ፡ ቢሆን ፡ ሊያውቀው ፡ ይችላል'' ፤ (ለ) ''ስለሕይወት ፡ ሕይወት ፡ ከልተሠዋ ፡ ሕይወት ፡ አይገኝም'' ፤ ተብሎ ፡ ቢነገር ፡ ኖሮ ፡ ፪ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ መነገራቸው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ መስተዋምሩ ፡ «ና» አያይዘ ፡ አንድ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ አድርጎታል ።

ስለ ፡ ሕይወት ፡

1 «ስለ ፡ » ቀሳል ፡ መስተዋድድ ፡ ነው ። «ሕይወት ፡ » የሚለውን ፡ ቃል ፡ ተገዥ ፡ አድርጎታል ። «ከልተሠዋ» ፡ ከሚለውም ፡ መስተዋምር ፡ ከመ ደቀበት ፡ ግሥ ፡ ጋር ፡ አዛምዶታል ።

2 «ሕይወት» የነገር ፡ ስም ፡ ነው ። ከግሡ ፡ ጋር ፡ በመስማማት ፡ በተባዕት ፡ ጾታ ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፤ በሮኛ ፡ መደብ ፡ ተነግሮአል ። መ·ያው ፡ ተሰቢ ፡ ነው ፤ በመስተዋድድ ፡ «ስለ» ፡ «ተገዝቶ ፡ ከልተሠዋ» ፡ ለሚለው ፡ ተሰቢ ፡ ሆኖአል ።

ሕይወት ፡

የነገር ፡ ስም ፡ ነው ። አዘራዘሩ ፡ እንደ ፡ ላይኛው ፡ ነው ። መ·ያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ፤ ባለቤትነቱ ፡ «ከልተሠዋ» ለሚለው ፡ ነው ።

ከልተሠዋ ፡

በዚህ ፡ ንግግር ፡ ፱ ፡ ቃሎች ፡ አሉ ። (ከ — አል — ተሠዋ ፡ በቀር) ፡

(ሀ) «ከ» ውለታን ፡ የሚያመለክት ፡ ጥገኛ ፡ መስተዋምር ፡ ነው ። «አ» የሚል ፡ ፊደል ፡ በስተፊቱ ፡ ስለገጠመው ፡ «አ» ን ፡ ውጦ ፡ «ከ» ተብሎ ፡ ተነግሮአል ። አል·ተሠዋ ፡ የሚለውንም ፡ የአሉታ ፡ አንቀጽ ፡ ከማሰሪያነት ፡ አግዶታል ። ''በቀር'' ፡ የሚለው ፡ ዓደኛው ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀር ፡ ቷል ። ይኸውም ፡ «ከልተሠዋ ፡ በቀር» ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ መስተዋምር ፡ ለየፈሳቸው ፡ ሊነገሩ ፡ የነበሩትን ፡ ፪ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ አያይዘዋቸዋል ። መስተዋምሩ ፡ በይኖር ፡ ኖሮ ፡ «ስለሕይወት ፡ ሕይወት ፡ አልተሠዋም» ። «ሕይወት ፡ አይገኝም» ፡ በተባለ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

(ለ) «አል» በግሥ ፡ ላይ ፡ የሚጨመር ፡ የአሉታ ፡ ባዕድ ፡ መነሻ ፡ ነው ። ተሠዋ ፡ በሚለው ፡ በአምንታው ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ተጨምሮ ፡ አሉታ ፡ አድርጎታል ።

(ሐ) «ተሠዋ» በተባዕታይ ፡ ጾታ ፡ በሮኛው ፡ መደብ ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር ፡ የተነገረ ፡ ጎላፊ ፡ ጊዜያት ፡ ነው ። በአሰማይ ፡ መደቡም ፡ ተደራጊ ፡ ዐምድ ፡ የማይሸገር ፡ ዓይነት ፡ ተገብሮ ፡ ጠባይ ፡ ነው ።

«አል» የሚል ፡ ባዕድ ፡ መነሻ ፡ ተጨምሮበት ፡ በአሉታ ፡ ተነግሮአል ።

በመስተዋምሩ ፡ ምክንያት ፡ ከአሉታው ፡ ደንብ ፡ የመድረሻው ፡ ቃል «ም» ጎድሎታል ። ይኸውም ፡ «አል·ተሠዋም» ፡ ሳይባል ፡ ቀረ ፡ ማለት ፡ ነው ። «ከ» የሚል ፡ ጥገኛ ፡ መስተዋምር ፡ ስላረፈበት ፡ ከማሰሪያነት ፡ ታግዶአል ። «ሕይወት» የሚለው ፡ በአጠገቡ ፡ የሚገኘው ፡ ቃል ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ባለ ቤት ፡ ነው ። በመስተዋድድ ፡ የተገዛው ፡ «ስለ ፡ ሕይወት» የሚለውም ፡ ቃል ፡ ተሳቢው ፡ ነው ።

(በቀር ፡)

ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቷል ።

ሕይወት ፡

የነገር ፡ ስም ፡ ነው ። አዘራዘሩ ፡ እንደ ፡ ላይኛው ፡ ነው ። መ·ያው ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ባለቤትነቱ ፡ ለማሰሪያው ፡ አንቀጽ ፡ ለ «አይገኝም ፡ » ነው ። በዚህ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ዋናው ፡ በለቤት ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

አይገኝም ፡

ግሥ ፡ በአሉታ ፡ የተነገረ ፡ ወቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። በተባዕት ፡ ጾታ ፡ በቮኛ ፡ መደብ ፤ በነጠላ ፡ ቁጥር ፤ በአሁንና ፡ በትንቢት ፡ ጊዜያት ፡ ተነግሮ አል ። በአዕማድ ፡ መደቡም ፤ ተደራጊ ፡ ዐምድ ፡ የማይሸገር ፡ ዓይነት ፤ ተገ ብር ፡ ጠባይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ዋናው ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባለቤቱ ፡ በአጠገቡ ፡ የሚገኘው ፡ «ሕይወት» ፡ የሚ ለው ፡ ቃል ፡ ነው ።—በመስተዋምር ፡ የሚሰቡት ፡ «ይችላልና» «ከልተሠዋ» ከነተሳሳቢዎቻቸው ፡ ለዚህ ፡ ለማሰሪያ ፡ አንቀጹ ፡ «ለ» አይገኝም ፡ » መስ ተዋምሬውያን ፡ መሙሊያዎች ፡ ሆነውታል ።

— 327 —

የአንቀጽ ፡ ተሳቢ ፡ የሚገባው ፡ ከባለቤት ፡ በኋላ ፡ ነው ። ብለን ፡ ጠቅሳሳውን ፡ ውሳኔ ፡ ተናግረናል ፤ (ቁ.302 ፡ እይ ። ይኸውም ፡ «ዳዊት ፡ ጎልያድን ፡ በወንጭፍ ፡ ድንጋይ ፡ ገደለ ፡ » ይሳል ፡ ማለት ፡ ነው ። ተውሳክ ፡ ግሥም ፤ ከሚገልጸው ፡ ቃል ፡ ሳይርቅ ፡ ይገባል ፡ ብለናል ፡ (ቁ.311 ፡ እይ ።) ይኸውም ፡ «ወንድሜ ፡ ነገ ፡ ይመጣል ፡ » ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የሚጣስበት ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል ። የንግግሩ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ በተሳቢው ፡ ወይም ፡ በተውሳክ ፡ ግሡ ፡ ላይ ፡ እንዲገለጽ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ተሳቢው ፡ ወይም ፡ ተውሳክ ፡ ግሡ ፡ ከባለቤት ፡ አስቀድሞ ፡ እየገባ ፡ ይነገራል ። ይኸውም ፡ እንደሚ ከተለው ፡ ነው ።

(ሀ) ቀጥተኛ ፡ ተሳቢ ፡ የኃይለ ፡ ቃል ፡ መግለጫ ፡ ሲሆን ፡

«ጎልያድን ፡ ዳዊት ፡ በወንጭፍ ፡ ድንጋይ ፡ ገደለ ።»

እነሆ ፤ በዚህ ፡ ንግግር ፡ ሲገለጽ ፡ የተፈሰገው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የጎልያድ ፡ መገደል ፡ ነገር ፡ ነው ።

(ለ) የመስተዋድድ ፡ ተሰቢ ፡ የነጋይለ ፡ ቃል ፡ መግለጫ ፡ ሲሆን ።

«በወንጭፍ ፡ ድንጋይ ፡ ጻዊት ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ ፡»

እነሆ ፡ በዚህ ፡ ንግግር ፡ ሊገለጽ ፡ የተፈለገው ፡ ነጋይለ ፡ ቃል ፡ «በወንጭፍ ፡ ድንጋይ ፡ የመግደል ፡ ነገር ፡» ነው ።

(ሐ) ተውሳከ ፡ ግሥ ፡ የነጋይለ ፡ ቃል ፡ መግለጫ ፡ ሲሆን ።

ነገ ፡ ወንድሜ ፡ ይመጣል ፡»

እነሆ ፡ በዚህ ፡ ንግግር ፡ ሊገለጽ ፡ የተፈለገው ፡ ነጋይለ ፡ ቃል ፡ «ድርጊቱ ፡ ነገ ፡ የመሆኑ ፡ ነገር ፡» ነው ።

ስለዚህም ፡ ተሰቢና ፡ ተውሳከ ፡ ግሥ ፡ ከበለጌት ፡ የሚቀድሙት ፡ የንግግሩ ፡ ነጋይለ ፡ ቃል ፡ በነሱ ፡ እንዲገለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንወስናለን ።

ሰኖ ፡ መልመጃ ።

የቃላት ፡ ዝርዝር ፡ አፈታት ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ከሚከተሉት ፡ ወረፍተ ፡ ነገሮች ፡ አንዳንዶቹን ፡ እየዘረዘርህ ፡ አስረዳ ።

ሀ—ቀላል ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ።

1—እባት ፡ ልጁን ፡ ያስተምራል ።
2—ትጉህ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ በወትር ፡ ይሄዳል ።
3—ጻዊት ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ ።
4—ትናንት ፡ ያየሁት ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ነው ።
5—እርሱ ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጧል ።
6—ከብር ፡ ያለ ፡ ነፃነት ፡ አይገኝም ።
7—በጥቂቱ ፡ የታመነ ፡ በብዙም ፡ ይታመናል ።
8—በትዕግሥት ፡ ሁሉ ፡ ይገኛል ።

ለ—ድርብና ፡ ድርብርብ ፡ ወረፍተ ፡ ነገር ።

1—ክፉ ፡ ነገርን ፡ ሠርቶ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አያገኘኝም ፡ ማለት ፡ ትልቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ በክፉ ፡ ሥራቸው ፡ የጠፉ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ።
2—መከራና ፡ ደስታ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ የተሰጡ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ የመጡ ፡ አይደሉም ።

3—ደስ ፡ መሰኘትና ፡ መከፋት ፡ ሲዘዋወሩ ፡ ስለሚኖሩ ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ እንደሚከፋው ፡ የከፋው ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፡ አያጠረጠርም ።
4—በዕድሜ ፡ መሰንበትና ፡ ፈተናን ፡ ሁሉ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ይሳና ፡ ቀን ፡ መድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መታደልና ፡ መከበር ፡ ነው ።
5—በእናት ፡ ማኅፀን ፡ የተፀነሰ ፡ ፅንስ ፡ ቀኑ ፡ ሲደርስ ፡ በማኅፀን ፡ ታግዶ ፡ እንደማይቀር ፡ ሥራም ፡ በትጋት ፡ ከተጀመረ ፡ የሠራተኛው ፡ አሳብ ፡ ከወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አያልፍም ።
6—ፍልሰትና ፡ አድራሻ ፡ የለውም ፡ ያለ ፡ ዕረፍት ፡ ሲሄድ ፡ የሚኖር ፡ የምርመራ ፡ አሞራ ፡ ከመሆኑም ፡ የተነሣ ፡ ከሁሉ ፡ ይደርሳል ።
7—ግጠቅ ፡ ጠጣም ፡ ወረደ ፡ ለመደነቅ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ስሕተት ፡ የሌለበት ፡ መሉ ፡ ሰውን ፡ ለመሆንም ፡ ነው ፡ እንጂ ።
8—ሥጋ ፡ በመንፈስ ፡ እየተ ንቀሳቀሰ ፡ መንፈስ ፡ በሥጋ ፡ እየተዳበሰ ፡ ግዙፍነት ንና ፡ ረቂቅነትን ፡ ለመግለጽ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ መንፈሳዊነት ፡ ሥጋም ፡ ወደ ፡ ሥጋዊነት ፡ እያዘነበለ ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ አከል ፡ ሁለት ፡ ነጋይል ፡ ሲሠራ ፡ ይኖራሉ ።

ከመልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ (1—8)

9—ፈተናን ፡ ያላለፈና ፡ ወድቆ ፡ ያልተነሣ ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ትግሉ ፡ ተፈጽሞ ፡ ወደ ፡ ትክክለኛ ፡ ኦኗርር ፡ ሲደርስ ፡ ለጉሮው ፡ የበለጠ ፡ ጣዕምን ፡ ያገኝለታል ።
10 ሰው ፡ ሁሉ ፡ ምኞቱ ፡ በፈጸምለት ፡ ምኞቱን ፡ ይተክል ፡ እንጂ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የነበረበትን ፡ አያስተውልም ።
11 ሰው ፡ ከሰው ፡ ይበልጣል ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ከሰው ፡ ያንሳል ፡ ማለት ፡ አይደለም ።
12 ችግር ፡ በሥራ ፡ እንጂ ፡ በምኞት ፡ አይሸነፍም ።
13 አይወደህም ፡ የሚሉህ ፡ አትውደዱ ፡ ሲሉ ፡ ነው ።

ከፀምደ ፡ ሚክኤል ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ (9—13)

14 ሁሉ ፡ የሆነና ፡ የተመላለሰ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ አውንም ፡ ሁሉ ፡ ተመላላሽና ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያልሆነ ፡ ነገርን ፡ የሚያሰይ ፡ ጊዜ ፡ እንሬልታየ ፡ ለአዲስም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለክብርዋ ፡ ማደሻ ፡ ሲሆን ፡ የተጀመረው ፡ ይህ ፡ አዲስ ፡ ዘመን ፡ ከመጀመሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ለክብርዋ ፡ መቀነሻ ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ የነበረው ፡ በ1888ኛ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሚያዝያ ፡ ሸኛ ፡ የሞላው ፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ ለክብርዋ ፡ ማደሻ ፡ ሆኖ ፡ የሞላው ፡ በ1981 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሚያዝያ ፡ ሸኛ ፡ ቀን ፡ መሆኑን ፡ ሁሉም ፡ ያውቀዋልና ፡ ጊዜና ፡ ቀን ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ እንደሚስማማው ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ መሆናቸውን ፡ ሁሉም ፡ በየራሱ ፡ አሳብ ፡ ይመለከተዋል ።

ከሞናርኩ ፡ ንጉሤ ፡

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ባዕድ ፡ መነሻና ፡ ባዕድ ፡ መድረሻ ።

— 328 —

መግለጫ ።

ባዕድ ፡ መነሻ ፡ የሚባለው ፡ በስተ ፡ መጀመሪያ ፡ እየተጨመረ ፡ የሚገባ ፡ ቃል ፡ ነው ። ባዕድ ፡ መድረሻ ፡ የሚባለውም ፡ በስተ ፡ መጨረሻ ፡ የሚገባ ፡ ቃል ፡ ነው ። ባዕድ ፡ መነሻና ፡ ባዕድ ፡ መድረሻ ፡ በነጥብ ፡ ሳይለይ ፡ ከዋናው ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ይጻፋል ።

በዚህ ፡ ክፍል ፡ "ባዕድ ፡ መነሻ ፡ ባዕድ ፡ መድረሻ ፡" የተባለውን ፡ ቃል ፡ ከሌ ቃውንት ፡ ወገን ፡ "ሥረ ፡ ገብ ፡ ሚፈ—ገብ ፡" ብለው ፡ የሚሰይሙ ፡ አሉ ። አንዳን ዶች ፡ ደግሞ ፡ "ቀድሞ ፡ ገብ ፡ ኋላ—ገብ ፡" ብለው ፡ ይሰይሙታል ። የሁሉም ፡ አሳብ ፡ በምሥጠር ፡ የተባበረ ፡ ስለሆነ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ጥቂቶችን ፡ እንጽፋለን ።

— 329 —

(ሀ) ባዕድ ፡ መነሻ ።

ባዕድ ፡ መነሻ ፡	ተግባሩ ፡	ማስረጃ ።
ል—	የአርባታ ፡ መሪ ፡	ልፈልግ ፡ ልሂድ ፡ ልግባ ፡
መ—	የግሥ ፡ አርእስት ፡	መፈለግ ፡ መሄድ ፡ መግባት ፡ ማየት ፡ ማወቅ ፡ (=መለየት ፡ መዐወቅ ፡)
ተ—	የአዕማደ ፡ መነሻ ፡	ተገደለ ፡ ተፈለገ ። ተገዳደለ ፡ ተጋደለ ።
ት—	የአርባታ ፡ መሪ ፡	ትሄድ ፡ ትሄጂ ፡ ትሄዱ ፡ (=ትሄዳለህ ፡ ትሄጃለሽ ።)
አ—ም	አሰራ ፡	አይሄድም ፡ አትሄድም ፡ አልሄድም ፡ አንሄድም ።
አ—	የአዕማደ ፡ መነሻ ፡	አይሄድ ፡ አትሄድ ፡ አትሄጂ ፡ አልሄድ ፡ አንሄድ ።
አ—	»	አረዘመ ፡ አፈሰሰ ፡ አረዛዘም ፡ አገዳደል ።
አስ	»	አስገደለ ፡ አስገባ ፡ አስቀመጠ ።
አስተ—	»	አስተዋወቀ ፡ አስታወቀ ፡ (=አስተዐወቀ ፡)
እ—	የአርባታ ፡ መሪ ፡	እሄድ ፡ እገባ ፡ እፈልግ ፡ (=እሄዳለሁ ፡ እገባለሁ ።)
እን—	»	እንሄድ ፡ እንገባ ፡ እንሂድ ፡ እንግባ ፡
የም—	ቅጽል ፡	የምፈልግ ፡ የምሄድ ፡ (=የምእፈልግ ፡ የምእሄድ ፡) የሚፈልግ ፡ የሚሄድ ፡ (=የምይፈልግ ፡ የምይሄድ ፡) የማይፈልግ ፡ የማይሄድ ፡ (=የምአይፈልግ ፡ የምአይሄድ ።)
ይ—	የአርባታ ፡ መሪ ፡	ይፈልግ ፡ ይፈልጉ ፡

— 330 —

(ለ) ባዕድ ፡ መድረሻ ።

ባዕድ ፡ መድረሻ ፡	ተግባሩ ፡	ማስረጃ ።
—ሁ ፡	የአርባታ ፡ ዝርዝር	መጣሁ ፡ ፈለግሁ ፡ ገባሁ ፡ (=እኔ ፡)
—ህ ፡	»	ፈለግህ ፡ ገደልህ ፡ ወደድህ ፡ መጣህ ፡ (=አንተ ፡) ፈለገህ ፡ ገደለህ ፡ ወደደህ ፡ (=አንተን ፡)
—ህ ፡	አገናዛቢ ፡	ቤትህ ፡ አባትህ ፡ ወንድምህ ፡ =(ያንተ ፡)
—ሚ ፡	ተ ፡ ሚ ፡	ንገረሚ ፡ በለውሚ ፡ ቂይሚ ፡ =(እስቲ ፡)
ማ ፡	ቅጽል ፡	ድንጋያማ ፡ ተራራማ ። ገብስማ ፡ ዛጐልማ ።
—ም ፡	»	ድንጋያም ፡ ከፋታም ፡ እከክም ፡ ሀብታም ።
—ሽ ፡	የአርባታ ፡ ዝርዝር	መጣሽ ፡ ሄድሽ ፡ ፈለግሽ ፡ (=አንቺ ፡) አገኘሽ ፡ ፈለገሽ ፡ ተከተልሽ ፡ (=አንቺን ፡)
—ሽ ፡	አገናዛቢ ፡	ቤትሽ ፡ ልብስሽ ፡ አባትሽ ፡ (=ያንቺ ፡)
—ታ ፡	ስም ፡	ዝግታ ፡ ቀጥታ ፡ ጸጥታ ፡ (=ጸዋ ፡ ማለት ፡)
—ቲ ፡	ቅጽል ፡	ቀያቲ ፡ ነጫቲ ፡
—ት ፡	ስም ፡	ክፋት ፡ ጠላት ፡ ወጣት ፡ መግባት ፡ መብላት ፡ ማየት ፡
—ት ፡	የአርባታ ፡ ዝርዝር	ፈለጉት ፡ ዐወቁት ፡ ተከተሉት ፡ (=አርሱን ፡)
—ች ፡	የአርባታ ፡ ዝርዝር	ፈለጉች ፡ መጣች ፡ ገቧች ፡ (=አርሷ ፡)
—ነት ፡	ስም ፡	ሰውነት ፡ ደግነት ፡ ክፉነት ፡ ትልቅነት ፡ (=መሆን ፡)
—ን ፡	የአርባታ ፡ ዝርዝር	ፈለግን ፡ ገደልን ፡ መጣን ፡ (=እኛ ፡) ፈለገን ፡ ገደለን ፡ ዐወቀን ፡ (=እናን ፡)
—ኖ ፡	ቅጽል ፡	እውነተኖ ፡ ኃጢአተኖ ፡ ወንጀለኖ ፡ ደመኖ ፡
—ኖ ፡	ተ ፡ ግ ፡	ከፉኖ ፡ ሰው ፡—ሰውኖ ፡
—ኝ ፡	የአርባታ ፡ ዝርዝር	ፈለገኝ ፡ ፈለጉኝ ፡ ፈለገችኝ ፡ (=እኔን ፡)
—(አ)ት ፡	»	ፈለጋት ፡ ፈለጓት ፡ (=እርስዋን ፡)
—(አ)ቸው ፡	»	ፈለጋቸው ፡ ፈለግኣቸው ፡ (=እነርሱን ፡)
—(አ)ችሁ ፡	»	ፈለግኣችሁ ፡ መጣችሁ ፡ (=እናንተ ፡)
—(አ)ሞው ፡	አገናዛቢ ፡	ቤታቸው ፡ በቅሎአቸው ፡ (=የእነርሱ ፡)
—(አ)ችሁ ፡	»	ቤታችሁ ፡ በቅሎአችሁ ፡ (=የእናንተ ፡)
—(አ)ችን ፡	»	ቤታችን ፡ በቅሎአችን ፡ (=የእኛ ፡)
—ሞ ፡	»	ቤትዋ ፡ ጌታዋ ፡ በቅሎዋ ፡ (=የእርስዋ ፡)
—ዊ ፡	ቅጽል ፡	ኢትዮጵያዊ ፡ ወንጌላዊ ፡ (ተባ.ጸታ ፡ ነጠላ ፡)
—ዊት ፡	»	ኢትዮጵያዊት ፡ ወንጌላዊት ፡ (አን.ጸታ ፡ ነጠላ ፡)
—ውያን ፡	»	ኢትዮጵያውያን ፡ ወንጌላውያን ፡ (ተባ.ጸታ ፡ የብዙ ፡)

—ውያት ፡	፱	ኢትዮጵያውያት ፡ ወንጌላውያት ፡ (አን . ጸታ ፡ የብዙ)
—ው ፡	የእርባታ ፡ ዝርዝር	ፈለገው ፡ ዐወቀው ፡ ተከተለው ፡ (=እርሱን ፡)
—ው ፡	አገናዛቢ ፡	ጌታው ፡ በቅሎው ፡ (—የእርሱ ፡)
—ዎች ፡	ስም ፡	ገበሬዎች ፡ በሬዎች ፡ (ለማንኛውም ፡ ጸታ ፡ የብዛት ፡ ምልክት ፡)
—ያ ፡	ተ . ግ .	አንድ ፡ ሁለት ፡ አምስት ፡ ነፍስ ፡
—ዉ ፡	አገናዛቢ ፡	ጌታዉ ፡ በቅሎዉ ፡ እማማዉ ፡ አባትዉ ፡ ወንድምዉ ፡ (=የእኔ ፡)
—ዩ ፡	ተ . ግ .	አንደዩ ፡ ሁለተዩ ፡ ሁለዩ ፡ (=ያ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ጊዜ ፡)

ክፍል ፡ ፪ ፡

ከግዕዝ ፡ የተወረሱ ፡ ቃላት ።

መግለጫ ።

አማርኛ ፡ ከግዕዝ ፡ የተወለደ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በብዙዎቹን ፡ የግዕዝ ፡ ቃላት ፡ ወርሶአቸው ፡ ይገኛል ። የአወራረሱም ፡ ዓይነት ፡ በፎ ፡ አከሄድ ፡ ይመደባል ።

፩ኛ ፡ የፊደላቸውን ፡ ዘር ፡ ሳይለውጥ ፡ አማርኛ ፡ በቀጥታ ፡ የወረሳቸው ፡ የግዕዝ ፡ ቃላት ፡ ይገኛሉ ። ይኸውም ፡ «ዓይን ፡ እግር ፡ ምድር ፡ ቀደሰ ፡ ተቀበለ ፡ ተቀየመ ። » እንደማለት ፡ ያለው ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ንባባቸው ፡ በማጥበቅና ፡ በማላሳት ፡ ድምፅ ፡ ልዩነትን ፡ ሲያደርግ ፡ ይገኛል ። እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ «ለጉመ ፡ ባረከ ፡ ፈጠረ ፡ » እኒህን ፡ የመሰሉት ፡ ሁሉ ፡ በግዕዝም ፡ በአማርኛም ፡ የሚነገሩ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ። በማላሳት ፡ ድምፅ ፡ ሲነገሩ ፡ ግዕዝ ፡ ይሆናሉ ። የመከከል ፡ ቀለማቸው ፡ በማጥበቅ ፡ ድምፅ ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ አማርኛ ፡ ይሆናሉ ።

አጅ ፡ ፈጠረ ፡ ዓለመ ፡ (ግዕዝ ።)
ዓለምን ፡ ፈጠረ ፡ (አማርኛ ።)

፪ኛ ፡ የፊደላቸውን ፡ ዘር ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እየለወጠ ፡ አማርኛ ፡ የወረሳቸው ፡ የዕግዝ ፡ ቃላት ፡ ይገኛሉ ። ይኸውም ፡ ፈመሐለ ፡ ያለውን ፡ ግለ ፡ — ጎደረ ፡ ያለውን ፡ አደረ ፡ — እድ ፡ ያለውን ፡ እጅ ፡ » እያለ ፡ ወርሶታል ፡ ግለት ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ በምሳሌ ፡ ለማለየት ፡ ከያይነቱ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ቃል ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ እንጽፋለን ።

— 332 —

ንግግራቸው ፡ ሳይሰወር ፡ አማርኛ ፡ በቀጥታ ፡ የወረሳቸው ፡ ቃላት ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ተጽፈዋል ። (*) ይህ ፡ ምልክት ፡ የሚገኝባቸው ፡ ቃላት ፡ «በፎተኛው ፡ መደብ ፡ በተባዕት ፡ ጾታ ፡ በነጠላ ፡ ቁጥር» ፡ የሚነገሩት ፡ ግሦች ፡ ናቸው ።

(ሀ)	ሕይወት ፡	መንግሥት ፡	ምዕራፍ ፡
ሀገር ፡	ሕግ ፡	መንፈስ ፡	ምድር ፡
ሀብት ፡	ሕግን ፡	መካን ፡	ምግብ ፡
ሁኩት ፡	(መ)	መከ-ንን ፡	ምጽዋት ፡
ሣይማናት ፡	*መሰሰ ፡	መኪንንት ፡	*ሞተ ፡
(ለ)	መልሕቅ ፡	መዐልት ፡	ሞት ፡
*ለመደ ፡	መልአክ ፡	መዓርግ ፡	ሞገስ ፡
*ለቀመ ፡	መምህር ፡	መዝሙር ፡	(ሠ)
*ለበጠ ፡	መሠረት ፡	መዘንጠ ፡	ሠራዊት ፡
*ለከፈ ፡	መሥዋዕት ፡	መድረክ ፡	ሥልጣን ፡
*ለገመ ፡	*መረገ ፡	መድኃኒት ፡	ሥራይ ፡
ሊቅ ፡	መሪር ፡	*መገበ ፡	ሥርጉት ፡
ላህይ ፡	መረት ፡	መጋቢት ፡	ሥቃይ ፡
ሌሊት ፡	*መሰለ ፡	መጠን ፡	ሥዕል ፡
ልማድ ፡	መሰንቆ ፡	መጣብቅ ፡	ሥጋ ፡
ልብ ፡	መስመር ፡	መጽሐፍ ፡	(ረ)
ልብስ ፡	መስቀል ፡	መፀው ፡	ረቂቅ ፡
ልዑል ፡	መስከረም ፡	ሙዳይ ፡	ረበቀ ፡ (ርብ) ፡
ልደት ፡	መስኩት ፡	ሚያዝያ ፡	ረኃብ ፡
ልጓም ፡	መስፍን ፡	ሣጥሌት ፡	*ረገመ ፡
(ሐ)	መሶብ ፡	ሣጥተም ፡	*ረፈደ ፡
ሐሜት ፡	መቃብር ፡	ሣጥበር ፡	ራቁት ፡
ሐምሌ ፡	መቅሠፍት ፡	ሣዕበል ፡	ራእይ ፡
ሐረግ ፡	መቅደም ፡	ሣዕድ ፡	ርስት ፡
ሐተታ ፡	መበለት ፡	ምሕረት ፡	ርኅሙ ፡
ሐዋርያ ፡	መብረቅ ፡	ምሥራቅ ፡	ርግብ ፡
ሐውልት ፡	መናፍቅ ፡	ምሳሌ ፡	ርሣን ፡
ሕልም ፡	መንበር ፡	ምስል ፡	(ሰ) ፡
ሕንፃ ፡	መንገድ ፡	ምቅሐት ፡	*ሰለበ ፡
ሐበብ ፡	መንፈቅ ፡	ምክንያት ፡	ሰላም ፡
		ምዕራብ ፡	ሰማይ ፡
			ሰሚን ፡
			*ሰረቀ ፡
			ሰረገላ ፡

ሰርክ ፡
*ሰበረ ፡
*ሰበከ ፡
ሰኔ ፡
ሰንበት ፡
ስኩና ፡
*ሰወረ ፡
ሰዋስው ፡
ስይፍ ፡
*ሰደደ ፡
*ሰገደ ፡
ሰፍነግ ፡
ሰ.ባይ ፡
ስም ፡
ስሕተት ፡
ስርየት ፡
ስብከት ፡
ስካር ፡
ስደት ፡
ስግደት ፡
ሶራ ፡

(ቀ)

*ቀለመ ፡
ቀለም ፡
*ቀመፈ ፡
*ቀሰመ ፡
ቀሳጠ ፡
ቀብር ፡
ቀኖና ፡
*ቀደመ ፡
ቀጸላ ፡
ቁጠት ፡
ቁም ፡
ቃል ፡
ቀርፅ ፡
ቀብዓት ፡
ቀናት ፡
ቀንዓት ፡
ቀጽር ፡
*ቆመ ፡

(ቁ)

ቁላ ፡
ቁስል ፡
ቁር ፡
ቁርባን ፡

(በ)

በረከት ፡
በቀል ፡
በትር ፡
በከ ፡
*በየነ ፡
በድን ፡
ቡራክ ፡
ቡራኬ ፡
ባሕር ፡
ባሕርይ ፡
*ባረከ ፡
ባዕድ ፡
ቤት ፡
ቤተ ፡ መቀደስ ፡
ቤተ ፡ መንግሥት ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ቤተ ፡ ጸሎት ፡
ቤዛ ፡
ብሉይ ፡
ብርሃን ፡
ብርዕ ፡
ብያኔ ፡
ብፁዕ ፡

(ተ)

*ተለመ ፡
ተምኔት ፡
*ተረጉመ ፡
*ተሳተፈ ፡
ተስፋ ፡
*ተቀበለ ፡
*ተቀየመ ፡
*ተቃወመ ፡
*ተበቀለ ፡
*ተከለ ፡
*ተከዘ ፡
ተክሊል ፡
ተክል ፡
ተኩላ ፡
*ተቀረደ ፡
ተቀርዶ ፡
*ተዘከረ ፡
ተገሠጸ ፡
ተግሣጽ ፡
ተግባር ፡
ታቦት ፡
ታጎሣሥ ፡
ትልም ፡
ትሑት ፡
ትሕትና ፡
ትምክሕት ፡
ትርጓሜ ፡
ትንሣኤ ፡
ትዕቢት ፡
ትዕግሥት ፡
ንዝህላል ፡
ንዴት ፡
ንጉሥ ፡
ንግሥት ፡

(አ)

አለሳ ፡
አሕዛብ ፡
አሜን ፡
አረር ፡
አራዊት ፡
አርእስት ፡
*አስረ ፡
አስማት ፡
አብሳ ፡
አባል ፡
አትርነስ ፡
አንበሳ ፡
አጉት ፡
አካል ፡
አክሊል ፡
አውሎ ፡
አዘቀት ፡
አዜብ ፡
አየር ፡
አጽፍ ፡
አፍ ፡
ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡
አልፍ ፡
እመ ፡ ምኔት ፡
እሳት ፡
እስከ ፡
እብኑ ፡ በረድ ፡
እከይ ፡
እግር ፡
እግዚእብሔር ፡

(ከ)

*ከረመ ፡
ከርሥ ፡
ከበሮ ፡
*ከተረ ፡
ከንፈር ፡
ክሕደት ፡
ክረምት ፡
ክርታስ ፡
ክሳድ ፡
*ከበጠ ፡
ክቡር ፡
ክብር ፡
ክንፍ ፡
ኮክበ ፡

(ኰ)

*ኰነነ ፡
ኮነኔ ፡

(ወ)

*ወለደ ፡
*ወሰደ ፡
ወርቅ ፡
*ወቀረ ፡
*ወገረ ፡
*ወጠነ ፡

(ዐ)

ዐሥራት ፡
ዐሥር ፡
ዐረፍት ፡
ዐቅል ፡
ዐውድ ፡
*ዐጠነ ፡
ዐፀድ ፡
ዓመት ፡
ዓሣ ፡
ዕረፍት ፡
ዕጎሎ ፡
ዕጣን ፡
ዕፃ ፡

(ዘ)

*ዘለፈ ፡
ዘለፋ ፡
*ዘመረ ፡
ዘቢብ ፡
*ዘፈነ ፡
ዛጐል ፡
ዜና ፡
ደመና ፡
ደም ፡
ደረሰ ፡
ደከመ ፡
ደመሰ ፡
ደመል ፡
ደዌ ፡
*ደገመ ፡
*ደፈረ ፡
ዲያቆን ፡
ድምር ፡
ድርስት ፡
ድንጋይ ፡
ድካም ፡
ድጋም ፡

(ገ)

*ገሠጸ ፡
ገባር ፡
ገነት ፡
ገውዝ ፡
*ገደፈ ፡
ገጸም ፡
ገድል ፡
ገጽ ፡
ግብር ፡
ግንቦት ፡
ግዘረት ፡
ግጻዌ ፡
ግጽው ፡

(ጐ)

*ጐለተ ፡
*ጐደሰ ፡
ጐደሎ ፡
ጐጻጐጵ ፡
ጐልት ፡
ጐሐሥት ፡
ጐድፍ ፡

(ጠ)

*ጠረዘ ፡
ጠረጴዛ ፡
*ጠየቀ ፡
ጥምቀት ፡
ጥሬዝ ፡
ጥር ፡
ጥበብ ፡
ጥቅምት ፡
ጥንቃቄ ፡
ጥንት ፡
ጥያቄ ፡

(ጸ)

ጸጸስ ፡
ጸሬቅሊሞስ ፡

(ፀ)

*ፀለየ ፡
ፀሎት ፡
ፀጋ ፡
ፀድቀ ፡
ፀንፍ ፡
ፀድቅ ፡
ፀጋዘ ፡
ፀመ ፡
ፀም ፡

(ፀ)

ፀሐይ ፡
ፀዓዳ ፡
ፀደይ ፡
ፀዳል ፡

(ፈ)

ፈላስፋ ፡
ፈረስ ፡
*ፈረደ ፡
*ፈቀደ ፡
ፈቃድ ፡
*ፈጠነ ፡
*ፈጠረ ፡
ፈጣሬ ፡
ፋቢካ ፡
ፍሥሓ ፡
ፍሬ ፡
ፍርኃት ፡
ፍርድ ፡
ፍትሕ ፡

*ከደነ ፡	ዝማሬ ፡	*ጠፈረ ፡	ፍትሐ ፡ ብሔር ፡
*ከፈነ ፡	ዝናም ፡	ጠፈር ፡	ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡
ከፈን ፡	(ደ)	ጣዕም ፡	ፍዳ ፡
ኪዳን ፡		ጣፋት ፡	ፍጥረት ፡
ካህን ፡	ደመረ ፡		

— 333 —

የየሬይዳላቸው ፡ ዘር ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እየተሰወጠ ፡ አማርኛ ፡ የወረሳቸው ፡ የግዕዝ ፡ ቃላት ፡ በጣም ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ከነርሱም ፡ ጥቂቶቹን ፡ እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ጽፈናል ። በአማርኛ ፡ ውስጥ ፡ ከመቶው ፡ ፭ ፡ ያህል ፡ የሚሆነው ፡ ቃል ፡ ከግዕዝ ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በዘወርዋሬ ፡ መንገድ ፡ የተወረሰ ፡ ነው ፡ ተብሉ ፡ በቅርብ ፡ ግምት ፡ ይገመታል ።

ግዕዝ ፡	አማርኛ ፡	ግዕዝ ፡	አማርኛ ፡
ሀኒት ፡	ኣኒት ፡	ሥርው ፡	ምር ፡
ለብሰ ፡	ለበሰ ፡	ሦከ ፡	እሾህ ፡
ላህም ፡	ላም ፡	ሦዐ ፡	ወሞ ፡
ላህብ ፡	ላብ ፡	ረቀየ ፡	ረቂቅ ፡
ላጸየ ፡	ላጪ ፡	ረድኤ ፡	ረዳ ፡
ሎጥ ፡	ለወሰ ፡	ረጥበ ፡	ረጠበ ፡
ሐለመ ፡	ኣለመ ፡	ርኅበ ፡	ቀራበ ፡
ሐሚየ ፡	እማ ፡	ርእስ ፡	ራስ ፡
ሐረሰ ፡	አረሰ ፡	ሰሐለ ፡	ሳለ ፡
ሐንከበ ፡	አነከሰ ፡	ሰሐቀ ፡	ሳቀ ፡
ሐደሰ ፡	አደሰ ፡	ሰዐመ ፡	ሳመ ፡
ሐገመ ፡	አገመ ፡	ሰሬውር ፡	ሱሪ ፡
ሐፍኝ ፡	አፍኝ ፡	ሰአመ ፡	ሳመ ፡
መሬ ፡	መረረ ፡	ሰገኘ ፡	ሰግን ፡
መርሐ ፡	መራ ፡	ሰ.በት ፡	ሽበት ፡
መኑ ፡	ማን ፡	ስንዳሌ ፡	ስንዴ ፡
መከየድ ፡	መኳኋኔ ፡	ስዝር ፡	ስንዝር ፡
መዋድህ ፡	ዋድያት ፡	ቀለል ፡	ቀሳል ፡
መሳር ፡	ማር ፡	ቀረመ ፡	ቃረመ ፡
መዘግሕ ፡	መዘጊያ ፡	ቀርበ ፡	ቀረበ ፡
መጸዋተ ፡	መጸወት ፡	ቀብዐ ፡	ቀባ ፡
ማእሰር ፡	ማሰሪያ ፡	ቀያሕ ፡	ቀይ ፡
ምቅዳሕ ፡	መቅጃ ፡	ቆቃሕ ፡	ቆቅ ፡
ሠዓለ ፡	ሣለ ፡	ቁስለ ፡	ቁሰለ ፡
ሚመት ፡	ሹመት ፡	በልዐ ፡	በላ ፡
ሜመ ፡	ሾመ ፡	በረቀ ፡	ባረቀ ፡
		በርሀ ፡	በራ ፡

ግዕዝ ፡	አማርኛ ፡	ግዕዝ ፡	አማርኛ ፡
በቅል ፡	በቅሎ ፡	መግዐ ፡	ውጋ ፡
በቈለ ፡	በቀለ ፡	ዋሕስ ፡	ዋስ ፡
በዝኀ ፡	በዛ ፡	ዐብደ ፡	ወሰደ ፡
በጥሐ ፡	በጣ ፡	ዐጠሰ ፡	ወነጠሰ ፡
ቢረሌ ፡	ብርሌ ፡	ዘርዕ ፡	ዘር ፡
ብራር ፡	ብር ፡	ዘግራ ፡	ዝግራ ፡
ተመነየ ፡	ተመኘ ፡	ዘግባ ፡	ዝግባ ፡
ተመዝገነ ፡	ተመሰገነ ፡	ዝእብ ፡	ጅብ ፡
ተንሥአ ፡	ተነሣ ፡	ደምሰሰ ፡	ደመሰሰ ፡
ተወገሠ ፡	ታገሠ ፡	ደክመ ፡	ደከመ ፡
ተያፍን ፡	ወይፈን ፡	ደፍአ ፡	ደፋ ፡
ተግሀ ፡	ተጋ ፡	ድጎነ ፡	ዳነ ፡
ተጠበ ፡	ተጠበበ ፡	ዶርሆ ፡	ዶሮ ፡
ተፍአ ፡	ተፋ ፡	ገፍዐ ፡	ገፋ ፡
ትንንያ ፡	ትንኝ ፡	ጊሚ ፡	ጉም ፡
ትያፕሮን ፡	ትያትር ፡	ጋይሶ ፡	ጋሻ ፡
ነቅሐ ፡	ነቃ ፡	ግፍዕ ፡	ግፍ ፡
ነደ ፡	ነደደ ፡	ጎር ፡	ጎረቤት ፡
ነድአ ፡	ነዳ ፡	ጠቀበ ፡	ጠቀመ ፡
ነግሠ ፡	ነገሠ ፡	ጠብሰ ፡	ጠበሰ ፡
ነጸየ ፡	ነጪ ፡	ጠፍአ ፡	ጠፋ ፡
ነፍሐ ፡	ነፋ ፡	ጢስ ፡	ጭስ ፡
አምነ ፡	አመነ ፡	ጥዒና ፡	ጤና ፡
አብ ፡	አባት ፡	ጸልመ ፡	ጨለመ ፡
እኅዘ ፡	ያዘ ፡	ጸረበ ፡	ጠረበ ፡
አንጠረ ፡	አነጠረ ፡	ጸድቀ ፡	ጸደቀ ፡
ከየደ ፡	ሄደ ፡	ጸጥሮ ፡	ጠጥሮ ፡
ከፍአ ፡	ከፋ ፡	ጽሕም ፡	ጠ.ም ፡
ከር ፡	ከርሥ ፡	ጽርስ ፡	ጥርስ ፡
ኵልያት ፡	ኩላሊት ፡	ጽፍር ፡	ጥፍር ፡
ኵሕል ፡	ኵል ፡	ፈሐቀ ፡	ፋቀ ፡
ወራሲ ፡	ወራሽ ፡	ፈትሐ ፡	ፈታ ፡
ወቅዐ ፡	ወታ ፡	ፋጸየ ፡	አፍዋጨ ፡
ወደቀ ፡	ወደቀ ፡	ፍሕም ፡	ፍም ፡

— 334 —

ከውጭ ፡ ቋንቋ ፡ የተወረሱ ፡ ቃላት ።

መግለጫ ፡

በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ የተወረሱ ፡ ቃላት ፡ በአማርኛ ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ ሲነገሩ ፡ ይሰማሉ ። ወደፊትም ፡ አዲሱ ፡ የሥልጣኔ ፡ ትምህርት ፡ በአገራችን ፡ ሳይ ፡ እየሰፋ ፡ በሄደ ፡ ቁጥር ፡ ከውጭ ፡ ቋንቋ ፡ የሚወረሰው ፡ ቃል ፡ እየበዛ ፡ መሄዱ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ትምህርቱ ፡ የሚያስገኘው ፡ አዲስ ፡ አዲሱ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ በሀገራችን ፡ ያልነበረና ፡ ስም ፡ ያልተሰየመለት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የውጭ ፡ ቋንቋ ፡ ከመበደር ፡ ይልቅ ፡ በቋንቋችን ፡ አዲስ ፡ ስያሜን ፡ ብንፈጥርለት ፡ ብለው ፡ የሚመኙ ፡ አሉ ። ይህ ፡ አሳብ ፡ ለሙራት ፡ ረገድ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ቢሆን ፡ አሁን ፡ ሲጀመው ፡ በትምህርት ፡ እንዳንገፋ ፡ ዳ ፡ ያደርገናል ። ስለዚህም ፡ አዲሱ ፡ ዘመን ፡ የመለዳቸውን ፡ የጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ያለባቸውን ፡ ቃላት ፡ ከውጭም ፡ ብንወርስ ፡ የሚጎዳ ፡ አለመሆኑን ፡ እንመለከታለን ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ አነጋገሩን ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ መወሰን ፡ የተገባ ፡ ነው ። ማለት ፡ ሁሉም ፡ በየፈናው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ቅጥ ፡ አምላኩ ፡ የጠፋ ፡ እንዳይሆን ፡ ነው ። እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ «ዲሬክተር ፡» የተባለው ፡ ቃል ፡ በሀገራችን ፡ ከዛሬ ፡ ሯጫ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ ተለምዶአል ። በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ በሕዝብ ፡ አፍ ፡ «ድልክቴር ፡ ድርክቴርም ፡» ይባል ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ዲሬክተር ፡ በቅ ባል ፡ የታወቀ ፡ ሆኖአል ። እንግዲህ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የተጣረው ፡ "ዳይረክተር" ፡ እቴ ሰው ፡ ቢል ፤ ወይም ፡ ኢጣሊያንና ፡ ዐዋቂው ፡ "ዲሬቶሬ" ፡ እላለሁ ፡ ቢል ፣ ተዘበራረቀ ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ በፎ ፡ ውሳኔ ፡ መጽናት ፡ አለብን ።

ከውጭ ፡ ቋንቋ ፡ ልንበደራቸው ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ቃላት ፡ ሁሉ ፡ "የመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ደራሲው" ፡ በየጊዜው ፡ እየወሰነ ፡ በፈደል ፡ ተራ ፡ ይጽፋቸዋል ። ከየት ፡ መጣውንና ፡ ትርጓሜውንም ፡ በየፊቱ ፡ እየገለጸ ፡ ይጽፈዋል ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ውሳኔውን ፡ ጠብቆ ፡ አለመናገር ፡ ተናጋሪውን ፡ ስሕተታም ፡ ያደርገዋል ።

በአማርኛችን ፡ ተለምዶው ፡ ከቆዩት ፡ ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ቃላት ፡ እነሆ ፡ ጥቂቶቹን ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በፈደል ፡ ተራ ፡ ጽፈን ፡ እናሳያለን ።

ሸሀፒታል ።	ባንክ ፡	ኢንዱስትሪ ፡	ዩኒቤርስቲ ፡
ሆቴል ፡	ቤንዚን ፡	ኤሊስ ፡	ዲሬክተር ፡
ሊትር ፡	ቦርጌስ ፡	ኤሌክትሪክ ፡	ዲፕሎማቲክ ፡
ሳጋር ፡	ቴሌፎን ፡	ኪሎሜትር ፡	ዶክተር ፡
ሌጋሲዮን ፡	ቴሌግራም ፡	ኪሎ ፡ ግራም ፡	ጅዮሜትሪ ፡
ሎተሪ ፡	ትሬንኖሜትሪ ፡	ካሜዮን ፡	ጅዮግራፊ ፡
ሚኒስቴር (ቤቱ)	ትራንስፖርት ፡	ካርታ ፡	ፊዚክ ፡
ሚኒስትር (ሹሙ)	ቶርፔዶ ፡	ካፒቴን ፡	ፋርማሲ ፡
ማጀር ፡	አልጄብራ ፡	ኬሚስትሪ ፡	ፋብሪካ ፡
ሜትር ፡	አምባሳደር ፡	ኮሌጅ ፡	ፍሬንክ ፡
ሞቀር ፡	አናቶሚ ፡	ኮሎኔል ፡	ፓውንድ ፡
ቨሊንግ ፡	አውቶሞቢል ፡	ኮመ-ኒኬሲዮን ፡	ፖሊስ ፡
ቢስክሌት ፡	አይሮፕላን ፡	ኮር ፡ ዲፕሎማቲክ	ፖስታ ፡
	አድሚኒስትሬሲዮን ፡		ፕሬዚዳንት ፡

ክፍል ፡ ፫ ፡ ነጥቦችና ፡ ምልክቶች ።

— 335 —

ነጥቦች ፡ (፡ ፣ ፤ ፥ ።) የቃላችን ፡ መሰን ፡ ድንበር ፡ በመለየት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ናቸው ። ምልክቶችም ፡ የቃላትን ፡ ተግባር ፡ በመግለጽ ፡ ያገለግላሉ ። እነሆ ፡ ሁሉንም ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ፤

ቅርፃቸው ፡	ስማቸው ፡	ሙያቸው ፡
።	ነጥብ ፡	የቃል ፡ መለያ ፡ ነው ።
፣		
፤	ነጠላ ፡ ሠረዝ ፡	በወረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ እንስተኛ ፡ የቃል ፡ መክፈያ ፤ ማሰሪደያ ፡ ነው ።
፥	ድርብ ፡ ሠረዝ ፡	በወረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ የቃል ፡ መክፈያ ፤ ወይም ፡ ማሰሪደያ ፡ ነው ።
።	ሙሉ ፡ ነጥብ ፡	በሙሉ ፡ ቃል ፡ የሚነገር ፡ የወረፍተ ፡ ነገር ፡ መግቻ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ፬ ፡ ነጥብ ፡ ይጠላል ።
	ይዘት ፡	የከፈለ ፡ ቃል ፡ ነጥብ ፡ ነው ። አጅ ፤ -ተ ስ.=ትውላጠ ፡ ስም ። በዚማ ፡ መጽሐፍ ፡ በስተራስጌ ፡ እየዋለ ፡ ልዩ ፡ ሙያ ፡ ይዘ ፡ ይገኛል ። (በፊደላት ፡ ራስጌም ፡ እየዋለ ፡ የማጥበቂያ ፡ ምልክት ፡ እንዲሆን ፡ ሊቁ ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ከሳሌ ፡ ወስነዋል ።)
. . .	ነጠብጣብ ፡	የተጀመረው ፡ ነገር ፡ መቀነሱን ፡ ወይም ፡ በውጥን ፡ መቅረቱን ፡ ያመለክታል ።
?	ትእምርተ ፡ ጥያቄ ፡	የጥያቄ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡
!	ትእምርተ ፡ አንክሮ ፡	የአንክሮ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡
¡	ትእምርተ ፡ ሥላቅ ፡	የነቀፋ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡
" "	ትእምርተ ፡ ጥቅስ ፡	ትን ፡ ወይም ፡ ተናገ ፡ ያለበትን ፡ ቃል ፡ ይገልጣል ።
( ) [ ]	ቅንፍ ፡	የነገርን ፡ ፍች ፡ ያመለክታል ።
___	ቁረት ፡	በቃልና ፡ በቃል ፡ መከከል ፡ ሲገባ ፡ "እስከ" ማለት ፡ ይሆናል ። በሠረገ ፡ ላይ ፡ ተጨምሮ ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡ ተከታይ ፡ ቃል ፡ መኖሩን ፡ ያመለክታል ። በድጓ ፡ ደንብ ፡ ቁረት ፡ የሚባለው ፡ አፖስትሮፍን ፡ የመሰለ ፡ (') በስተራስጌ ፡ የሚጨል ፡ ምልክት ፡ ነው ።
—	ንሎስ ፡ ቁረት ፡	ቃልንና ፡ ቃልን ፡ አጋጥም ፡ በአንድነት ፡ የሚያናግር ፡ ነው ። አጅ ፡ ልብ-ወለድ ፡ ሥራ-ፈት ፡ እ.ማ.አ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነጥቡ ፡ ከተጋጣሚው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ይቀራል ።

? ! ¡ " "	ትእምርተ ፡ ጥያቄ ፡ ትእምርተ ፡ አንክሮ ፡ ትእምርተ ፡ ሥላቅ ፡ ትእምርተ ፡ ጥቅስ ፡	እነዚህ ፡ ምልክቶች ፡ በንግግር ፡ ጊዜ ፡ ነጥብ ፡ ይቀራል ፡

የአገባባቸውን ፡ አኳኋን ፡ በሚከተሉት ፡ ወረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።

ግ ስ ረ ኛ ።

ከትዕቢተኛ ፣ ፈላስፋ ፣ ትጉህ ፣ ገበሬ ፣ ይቸላል ። ማወቅ ፣ ወጣም ፣ ወረደ ፣ ለመደ ነቅ ፣ ብቻ ፣ አይደለም ፤ ስሕተት ፣ የሌለበት ፣ ሙሉ ፣ ሰውን ፣ ለመሆንም ፣ ነው ፣ እንጂ ። መንፈሳዊ ፣ ኃይልን ፣ የሚያደክሙት ፣ ሐሰተኛነት ፣ ዕብለተኛነት ፣ ጨካኝነት ፣ አድላዊነት ፣ ናቸው ። ሰው ፣ ከዕለት ፣ ጥቅም ፣ ይልቅ ፣ ለዘለዓለም ፣ ጥቅም ፣ ቢያስብ ፣ ኖሮ ፣ በተስፋ ፣ የተቀመጠውን ፣ ንዋየ ፣ ቅድሳት ፣ (የተቀደሰ ፣ ዋጋ) ፣ ሊያገኝ ፣ በቻለ ፣ ነበር ። ትጉህ ፣ ገበሬ ፣ ሆይ ! የእዝመራህን ፣ መራት ፣ አትዘንጋ ። ሥራን ፣ የሚዘነጋ ፣ ማነው ? ራሱን ፣ የማይወድ ፣ ሥራ ፣ ፈት ፣ ይሆናላ ! "ጊዜ ፣ አይሥራብን ፣ ጊዜን ፣ ግን ፣ እንሥራበት" እንደተባለው ፣ ጊዜን ፣ የሥራ ፣ መማሪያ ፣ ማድረግ ፣ አለብን ።

ከመልደ ፣ ጊዮርጊስ ፣ መልደ ፣ ጦሐንስ ፣ ተመቀለ ።

ክፍል ፪ ፣ የአማርኛ ፣ መዝሙር ።

— 336 —

መግለጫ ፣

በግዕዙ ፣ የዜማ ፣ ትምህርት ፣ ደንብ ፤ መዝሙር ፣ የሚባለው ፣ ከቅኝቱ ፣ አንሥቶ ፣ እስከ ፣ ጽፋቱ ፣ ድረስ ፣ በአሥሩ ፣ አውታረ ፣ መዝሙር ፣ ምሳሌ ፣ ፲ ፣ ጊዜ ፣ በዜማ ፣ የሚዘለቀው ፣ ምስጋና ፣ ነው ። እርሱም ፣ "መዝሙር ፣ ዘሌሊት ፣ መዝሙር ፣ ዘአርያም ፣" ተብሎ ፣ በሁለት ፣ መደቦች ፣ ይመደባል ።

አሁንም ፣ "የአማርኛ ፣ መዝሙር ፣" የምንለው ፣ የዜማው ፣ ባህል ፣ በመምህራን ፣ ብያኔ ፣ ተቀርጾ ፤ በሕግ ፣ በሥርዓት ፣ ተወሰኖ ፤ በርጋታ ፤ በጸጥታ ፣ የሚነገረው ፣ ምስጋና ፣ ወይም ፣ ጨዋታ ፣ ነው ። አዲሱ ፣ ዘመን ፣ ያስገኘው ፣ ይህ ፣ የሥልጣኔ ፣ አከሂድ ፣ በትምህርት ፣ ሚኒስቴር ፣ ትጋት ፣ እየተሰፋፋ ፣ ሊመራ ፣ ተጀምሮአል ።

ጨዋው ፣ ጀግና ፣ ወኒው ፣ እየቀሰቀሰውና ፣ ሲቃ ፣ እየያዘው ፣ በጉብዝና ፣ መንፈስ ፣ እየቀተራ ፣ በዜማ ፣ የሚገልጸው ፣ ቃል ፣ "ሽለላ ፣" ወይም ፣ "ቀረርቶ ፣" ይባላል ። በትክዜ ፣ ወይም ፣ በደስታ ፣ ቀስ ፣ ቀስ ፣ እያለ ፣ የሚያዜመውም ፣ "እንጉርጉሮ ፣" ይባላል ።

እንዳገር ፣ ልማድ ፤ በእሬልታ ፣ በእስክስታ ፤ በአታሞ ፣ በቻቻታ ፣ የሚዜመው ፣ ነገር ፣ "ዘፈን ፣" ይባላል ። ለእርሱም ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ስልትና ፣ ቤት ፣ አለው ።

ጦልማሶች ፣ በገና ፣ ጨዋታና ፣ በሌላም ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ምክንያት ፣ በዜማ ፣ የሚጫወቱት ፣ ነገር ፣ "ሆታ ፣" ይባላል ። አጫዋቾች ፣ (ወይም ፣ አዝማሪዎች ፣) በመሰንቆ ፤ በበገና ፤ በዋሽንት ፤ በእምቢልታ ፣ የሚገልጹት ፣ ነገር ፣ "ጨዋታ ፣" ወይም ፣ "ምስጋና ፣" ይባላል ።

እነዚህም ፣ ሁሉ ፣ በጠቅላላ ፣ የአማርኛ ፣ መዝሙሮች ፣ ተብለው ፣ ይጠራሉ ። ለያንዳንዱም ፣ በየስልት ፣ በየስልቱ ፣ የግጥም ፣ ቃል ፣ እንደ ፣ ደንቡ ፣ ይገበለታል ።

—337—

መዝሙር ፣ ወይም ፣ ዘፈን ፣ ማለት ፣ የጨዋታው ፣ ጠቅላላ ፣ ስም ፣ ነው ። በየዘፈኑ ፣ ውስጥ ፣ እንደ ፣ ዜቅ ፣ የሚገባውና ፣ ቤት ፣ እየተመታለት ፣ የሚነገረው ፣ ቃል ፣ "ግጥም ፣" ይባላል ። አብዛኛውን ፣ ጊዜ ፣ ግጥም ፣ በጉዶሉ ፣ ቤት ፣ አይነገርም ፤ በ፪ ፣ በ፮ ፣ በ፯ ፣ . . . ቤቶች ፣ ይነገራል ። የቃል ፣ ማለረፊያውና ፣ የዜማ ፣ መግቻው ፣ "ቤት ፣" ይባላል ። በመጀመሪያ ፣ የሚገኘው ፣ የግጥሙ ፣ ቤት ፣ "ቤት ፣ መምቻ ፣" ይባላል ፤ የመጨረሻውም ፣ "መድፊያ ፣" ይባላል ።

በግጥም ፣ ውስጥ ፣ ቃሎች ፣ ተሰካክተው ፣ የሚገለጸበት ፣ ምግባር ፣ "ስንኝ" ይባላል ። ከየቤቱ ፣ በፊት ፣ የሚገኘው ፣ የስንኙ ፣ እኩሌታ ፣ "ሐረግ ፣" ይባላል ፤ ይዝውም ፣ አንስተኛ ፣ የቃል ፣ መግቻ ፣ ነው ።

የዘፈኑ ፣ ቀንቃኝ ፣ "አውራጅ" ይባላል ። "መሪ" ቢሉትም ፣ የተመቸ ፣ ነው ። ዘፈኑን ፣ እንደ ፣ ተሰዋም ፣ የሚቀበሉት ፣ ሰዎች ፣ "ተቀባዮች ፣" ይባላሉ ። አውራጅ ፣ በግዋም ፣ መሻጠሚያ ፣ የሚያዘምተውና ፣ ቃሉን ፣ ሳይለውጥ ፣ የሚመላልሰው ፣ ቃል ፣ 'አገማች" ፣ ይባላል ። ተቀባዮች ፣ በዘጎብረት ፣ የሚሉት ፣ ቃል ፣ "በዘይብል ፣ ወይም ፣ መቀበያ" ፣ ይባላል ። ዘፈኑ ፣ ሲደምቅ ፣ በዘጎብረት ፣ ተደጋግሞ ፤ የሚዜመው ፣ ቃል ፣ "ዮብዮቦ" ፣ ይባላል ፤ የዚህን ፣ ምሳሌ ፣ "አይፈራም ፣ ጋሚ" ፣ በሚለው ፣ ዘፈን ፣ ይመለከታል ።

ስለመዝሙሮች ፣ ሥርዓት ፣ አሁን ፣ የምንጽፈው ፤ ዓይነታቸውን ፣ በጥሩ ፣ ለመግለጽ ፣ ብቻ ፣ ነው ። ዝርዝር ፣ ሙያቸውን ፣ ግን ፣ ለመዝሙር ፣ ደራሲ ፣ ትተነው ፣ እናልፋለን ።

— 338 —

የዜማ ፣ ስልት ፣

በሀገራችን ፣ እንደሚታየው ፣ ትምህርት ፣ የዜማ ፣ ስልቶች ፣ ሰስት ፣ ናቸው ። እነርሱም ፣ (፩) ፣ ግዕዝ ፣ ዜማ ፣ (፪) ፣ አራራይ ፣ ዜማ ፣ (፫) ፣ ዕዝል ፣ ዜማ ፣ ይባላሉ ። ምልክቶቻቸው ፣ ግን ፣ ብዙዎች ፣ ናቸው ።

ከቅዳስ ፣ ያሬድ ፣ የተደረሱት ፣ የዜማ ፣ መጻሕፍት ፣ በነዚህ ፣ በ፫ቱ ፣ የዜማ ፣ ስልቶች ፣ ጣናነው ፣ ተቀምመው ፣ ሲነገሩ ፣ ይኖራሉ ። እነዚህም ፣ ሰስቱ ፣ የዜማ ፣ ስልቶች ፣ በያንዳንድ ፣ መዝሙር ፣ ላይ ፣ በተለይ ፣ ይነገራሉ ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ደግሞ ፣ በ፭ ፣ በዘይብል ፣ ላይ ፣ ተቀላቅለው ፣ ሲነገሩ ፣ ይገኛሉ ።

— 339 —

የአማርኛ ፣ ዘፈን ፣

የአማርኛ ፣ ዘፈን ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ ዜማው ፣ በቅሬምችና ፣ በደንገጥሮች ፣ በአረሆችም ፣ ቅብጠነት ፣ ከመሰን ፣ ቢዘል ፣ ቢቅበዋ ፣ ቢሸቀረቀር ፣ መደቡ ፣ ከሰስቱ ፣

የዜማ ፡ ስልቶች ፡ አይወጣም ። የዜማና ፡ የሙዚቃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ አውን ፡ እያሰናዳ ፡ ያወጣቸው ፡ ዘፈኖች ፡ በጣዕመ ፡ ዜማቸውና ፡ በሥርዓታቸው ፡ ውሳኔ ፡ የተመሰገኑ ፡ ሆነ ዋል ። መደፈትም ፡ እየተሻሻለ ፡ እንዲሠራ ፡ ዲሬክሲዮኑ ፡ አስበበታል ።

— 340 —

የአማርኛ ፡ መዝሙር ።

የአማርኛ ፡ መዝሙሮች ፡ በሰባቱ ፡ የዜማ ፡ ስልቶች ፡ በግዕዝ ፡ በአራራይ ፡ በዕዝል ፡ እየተዜሙ ፡ አዲሱን ፡ የሥልጣኔ ፡ አከሄድ ፡ መከታተል ፡ ጀምረዋል ። የመጀመሪያዎቹ ፡ የአማርኛ ፡ መዝሙሮች ፡ በ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተፈረ ፡ መኩንን ፡ ተማሪ ፡ ቤት፡ በዜማ ፡ የተዘመሩት ፡ ናቸው ። እነርሱንም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ መነሻ ፡ መነሻቸውን ፡ ብቻ ፡ ጠቅሰን ፡ እናሳያለን ።

መዝሙር ፡ ዘሥነ ፡ በዓል ፡ (ሐምሌ ፡ (፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

የኢትዮጵያን ፡ ብርሃን ፡
ዘለዓለም ፡ ያኑርልን ፡ . . .

መዝሙር ፡ ዘርእሰ ፡ ወውደ ፡ ዓመት ፡ (መስከረም ፡ ፭ቀን ፡ ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

ለኢትዮጵያ ፡ እናታችን ፡
ለነፃነት ፡ ትምክሕታችን ፡ . . .

መዝሙር ፡ ዘመስቀል ፡ (መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

መስቀሉ ፡ የጌታችን ፡
መታሰቢያው ፡ ያምላካችን ፡ . . .

መዝሙር ፡ ዘበዓለ ፡ ልደት ፡ (ታኅሣሥ ፡ ፸፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

ከሰባቱ ፡ አክል ፡ አንዱ ፡ አክል ፡
መሬት ፡ ወርዶ ፡ ሰኛ ፡ ሲል ፡ . . .

የሚባሉት ፡ ናቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ትምህርት ፡ ቤትና ፡ በየሴላውም ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መዝሙር ፡ እየወጣ ፡ ይዘመር ፡ ጀመር ። ይልቁንም ፡ ከአቶ ፡ ዮናታሌ ፡ ንጉሣና ፡ ከአቶ ፡ መልእኩ ፡ በጎ ፡ ሰው ፡ የተዘመሩት ፡ መዝሙሮች ፡ በጣም ፡ የታወቁና ፡ የተመሰገኑ ፡ ሆኑ ። በዚያውም ፡ ላይ ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ የዜማና ፡ የሙዚቃ ፡ ትምህርት ፡ እንዲስፋፋ ፡ ስለተጋበት ፡ የመዝሙሮች ፡ ዜማ ፡ በያይነቱ ፡ ይፈለሰፍ ፡ ጀመር ።

የአማርኛ ፡ መዝሙሮች ፡ ከሰባቱ ፡ የዜማ ፡ ስልቶች ፡ በአንዱ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ በሰባቱ ፡ ሁሉ ፡ እየተዜሙ ፡ ይነገራሉ ። በግዕዝ ፡ በአራራይ ፡ በዕዝል ፡ ከተዘሙት፡ መዝሙሮች ፡ እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ አንዱን ፡ ጠቅሰን ፡ የንባቡን ፡ ስልት ፡ እንጽፋለን ። ስለዜማ ውም ፡ ምልክት ፡ የተቀረጸ ፡ ፊደል ፡ ስለሌለ ፡ አውን ፡ ለማሳየት ፡ አልቻልንም ።

የሥነ ፡ በዓል ፡ መዝሙር ። እንደ ፡ መፋቂያ ፡ . . .

ሞት ፡ ቢፈረድበት ፡ / ሔዋን ፡ እንደዋዛ ፡
መጣ ፡ ተወለደ ፡ / የወገኑ ፡ ቤዛ ፡
ሊያደን ፡ ወገኖቹን ፡ / ደሙን ፡ እየነዛ ፡
እናት ፡ ኢትዮጵያ ፡ / ደስታዋ ፡ በዛ/ደስታዋ ፡ በዛ ፡

} በአራራይ ፡ ዜማ ፡

ያገሬ ፡ ጉበዝ ፡ ያ ፡ ከልፍልፉ ፡ ያ ፡ ከልፍልፉ ፡
እንደ ፡ መፋቂያ ፡ / ጦር ፡ ይዚአ ፡ በፉ ፡

} በግዕዝ ፡ ዜማ ፡

ሄሮድስ ፡ ሰማና ፡ / ጌታ ፡ መወለዱን ፡
ከልደቱ ፡ ይልቅ ፡ / ጠላው ፡ መሰደዱን ፡
ሰይፈረድበት ፡ / ተመልክቶ ፡ ፍርዱን ፡
ፈርሶ ፡ ተልቶ ፡ ሞት ፡ እያመመው ፡ ሆዱን ፡ እያ ፡ ሆ ።

} በዕዝል ፡ ዜማ ፡

ከኖፍታሌ ፡ ንጉሤ ፡ ተዘመረ።

— 341 —

የዜማ ፡ ምልክቶች ።

በሀገራችን ፡ የዜማ ፡ ምልክቶች ፡ አሉ ። በዱሮ ፡ ዘመን ፡ ግንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ዜማ ፡ ልዩ ፡ ቅርፅ ፡ ባላቸው ፡ በ፰ ፡ ምልክቶች ፡ ብቻ ፡ እየተቃኘ ፡ ይዜም ፡ እንደነበረ ፡ ይነገራል ። በኋላ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ለጥናት ፡ ማስታወሻ ፡ እንዲሆነው ፡ ከተመሳሳዮቹ ፡ ታላት ፡ አንዱን ፡ ለሌሎቹ ፡ ምልክት ፡ እያደረገ ፡ ስለመደበው ፡ ምልክቶች ፡ እየበዙ ፡ ይሄዱ። ጀመር ። እነዚያም ፡ የጥንቶቹ ፡ ምልክቶች ፡ ተጨማሪ ፡ ሆነው ፡ አውንም ፡ በአንድነት ፡ ሲያገለግሉ ፡ ይኖራሉ ። እነሆ ፡ የስንቱን ፡ ምልክቶች ፡ ስምና ፡ ቅርፅ ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

ቅናት ፡	. . . . .)	ጭረት ፡	. . . . . ⌟
ድፋት ፡	. . . . . ⌒	ቁርፅ ፡	. . . . . ⊢
ደረት ፡	. . . . . ⌣	ርክርክ ፡	. . . . . ⌇
ይዘት ፡	. . . . . ◦	ሂድ ፡ (መንገድ) ፡ . . .	⊔

ምልክቶች ፡ ሁሉ ፡ ከቃል ፡ በስተራስጌ ፡ እየገቡ ፡ ይውላሉ ። (ከሊቃውንት ፡ ወገን ፡ "ድርስ ፡ ፩ ፡ አንብር" ፡ የተባሉትን ፡ ሁለት ፡ ምልክቶች ፡ ጨምረው ፡ የዱሮዎቹ ፡ ምልክቶች ፡ ፀሥር ፡ ነበሩ ፡ ብለው ፡ የሚተርኩ ፡ አሉ ።) እነዚህም ፡ ምልክቶች ፡ በግዕዝም ፡ በአራራይም ፡ በዕዝልም ፡ የሚገቡ ፡ ናቸው ።

ለአማርኛ ፡ መዝሙር ፡ ስለምልክቶች ፡ ነገር ፡ የሚታሰቡ ፡ ሁለት ፡ አሳቦች ፡ አሉ ። (ሀ) የአማርኛ ፡ መዝሙር ፡ የድጓውን ፡ ምልክት ፡ እንዲወርስ ፡ የሚፈቅዱ ፡ አሉ ። ምክን ያቱም ፡ የድጓ ፡ ዜማ ፡ በአጼ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመን ፡ (በ፲፪፴ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያህል ፡) ከያሬድ፡ ተጀምሮ ፡ በሀገራችን ፡ የኖረ ፡ የኮራታችን ፡ ምልክት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያስረዳሉ ። (ለ) ለዘመኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዲስማማ ፡ ነገር ፡ ከአውሮፓውያን ፡ የዜማ ፡ መጽሐፍ ፡ የሚገኘውን ፡ ምልክት ፡ (ኖታ) ፡ እንዲወርስ ፡ የበየኑ ፡ አሉ ።

የሆነ ፥ ሆኖ ፥ ለዘመኑ ፥ አከሄድ ፥ የሚስማማውንና ፥ በአጭር ፥ መንገድ ፥ የሚታወቀውን ፥ ምልክት ፥ (ኖታ) ተቀብሎ ፥ ጣሰመ ። ዜማን ፥ ከድጓ ፥ መጥቀስና ፥ ማስማማት ፥ እንደሚሻል ፥ የተገለጠ ፥ ነገር ፥ ነው ። ይኸውም ፥ አሰብ ፥ በጊር ፥ ሊገለጥ ፥ ተጀምሮአል ።

— 342 —

የግጥም ፥ ዓይነቶች ።

ግጥሞች ፥ ቤት ፥ እየሞቱ ፥ እንደሚነገሩ ፥ ከሁን ፥ በፊት ፥ ተናግረናል ።

(ቁ.337 ፥ እዩ) አሁንም ፥ ዓይነታቸውን ፥ እንገልጻለን ። የግጥሞች ፥ ስንኝ ፥ እንደ ተመደበለት ፥ ዜማ ፥ መጠን ፥ አንዳንዱ ፥ ረጅም ፥ አንዳንዱም ፥ አጭር ፥ ሆኖ ፥ ይገኛል ። በዘር ፥ በነበበቡ ፥ የሚመሳሰሉትን ፥ ሁሉ ፥ ወዳንድ ፥ ወገን ፥ እየጠቀለልን ፥ በሚከተሉት ፥ በስምንት ፥ መደቦች ፥ መድበናቸዋል ።

(ሀ) ፥ የወል ፥ ግጥም ፥ (ተራ ፥ ወይም ፥ ደንበኛ ፥ ግጥም ፥)
(ለ) ፥ ሰንጎ ፥ መገን ፤ ቤት ፤
(ሐ) ፥ ወዳጅ ፥ ዘመዴ ፥ ምነው ፥ ቤት ፤
(መ) ፥ ኢዮሃ ፥ አበባዬ ፥ ቤት ፤
(ሠ) ፥ ሆያሆዬ ፥ ቤት ፤
(ረ) ፥ ቡሄ ፥ በሉ ፥ ቤት ፤
(ሰ) ፥ የበገና ፥ ሰላምታ ፤
(ቀ) ፥ ሕገ ፥ ወጥ ፥ ቤት ፤

እነርሱንም ፥ ለማስረዳት ፥ ከያይነታቸው ፥ ጥቂት ፥ ጥቂት ፥ ምሳሌ ፥ እናመጣለን ።

(ሀ) ፥ የወል ፥ ግጥም ፥ ቤት ፤ የወል ፥ በማለት ፥ ፈንታም ፥ ተራ ፥ ወይም ፥ ደንበኛ ፥ ግጥም ፥ ሊባል ፥ ይቻላል ። ይኸውም ፥ በሁሉ ፥ ዘንድ ፥ የተለመደውና ፥ ስንኙ ፥ ለብዙዎች ፥ ዘፈኖች ፥ ተስማሚ ፥ የሆነው ፥ ግጥም ፥ ነው ።

አጅ ፥ 1—አርበኞች ፥ መሞትን ፥ / ማን ፥ እስተማራቸው ።
ታላቁ ፥ ጴጥሮስ ፥ ነው ፥ / ባርክ ፥ የሰጣቸው ።
ሚካኤል ፥ መንገዱን ፥ / ቀድሞ ፥ ቢመራቸው ።
በጴጥሮስ ፥ ጉዳና ፥ / ብርሃን ፥ ወጣላቸው ።
2— አይዘህ ፥ የኔ ፥ ጌታ ፥ / ነገርሀን ፥ አትርሳ ።
አለስልሰህ ፥ ዝራ ፥ / የስንዲውን ፥ ማሳ ።
የተዘራኸው ፥ ዘር ፥ / ፈርሰና ፥ በስብሳ ።
ታፈራለች ፥ ፍሬ ፥ / ሙታ ፥ ስትነሣ ።
በጊዜው ፥ የዘራ ፥ / መልካም ፥ ዘር ፥ አትርፎ ።
ከገበሮች ፥ ጋራ ፥ / ማታ ፥ ከጥላ ፥ አርፎ ።
በቮርነት ፥ ታጥቆ ፥ / በቀን ፥ ተሰልፎ ።
ዳግም ፥ ዘሩን ፥ ዘራ ፥ / መከር ፥ አሳልፎ ።

(ለ) ፥ ሰንጎ ፥ መገን ፥ ቤት ። ስንኙ ፥ ከወል ፥ ግጥም ፥ ያንሳል ። በዚህ ፥ መደብ ፥ የሚነገረው ፥ ግጥም ፥ ተስማሚ ፥ በሚሆንበት ፥ በሴላም ፥ ከፍል ፥ ሊገባ ፥ ይገኛል ።

አጅ ፥ ገለል ፥ በሉለት ፥ / አንደዜ ፥ ለሱ ።
ግልግል ፥ ያውቃል ፥ / ከነፈረሱ ።
በሽህ ፥ አበዩ ፥ / አባ ፥ ደፋር ።
እያየህ ፥ ውጋ ፥ / እያየህ ፥ ግር ።
ከ ፈ ረ ሰ ኞ ች / አሉ ፥ በልዩ ።
ግኻል ፥ አገዳ / የሚለያዩ ።
ከ ፈ ረ ሰ ኞ ች / የምናውቃቸው ።
በ ሽ ህ ፥ አ በ ዩ ፥ / ኃይሌ ፥ አንዳርጋቸው ።

(ሐ) ፥ ወዳጅ ፥ ዘመዴ ፥ ምነው ፥ ቤት ፥—የመሰንቆ ፥ ዜማ ፥ ነው ። ቤቱ ፥ አጫጭር ፥ ነው ፤ አንዳንድ ፥ ጊዜ ፥ ከጠገና ፥ ግጥም ፥ ይተባበራል ።

አጅ ፥—ሠሪ ፥ ፍጥረቱን ፥ እታሰለ ፥
በኖራ ፥ ሠራሁ ፥ እያለ ፥
አይፈርስም ፥ ነበር ፥ ቤታችን ፥
አውነት ፥ ኖራ ፥ ቢሆን ፥

(መ) ፥ ኢዮሐ ፥ አበባዬ ፥ ቤት ።—ለመስቀል ፥ ድምር ፥ የሚዘረን ፥ የጨዎች ፥ ዘፈን ፥ ነው ። ሐረጉና ፥ ቤቱ ፥ አጫጭር ፥ ነው ። ሐረጉ ፥ ቤት ፥ እየመታ ፥ ይሄዳል ። ስለዚህም ፥ ሐረጉን ፥ ያልቆጠሩት ፥ እንደሆን ፥ በእ ፥ ቤት ፥ የሚነገር ፥ ግጥም ፥ ይበላል ። ሐረጉ ፥ ሲቆጠር ፥ ግን ፥ ፪ ፥ ቤት ፥ ይሆናል ።

አጅ ፥—አትሁራ ፥ ንብሰ / ንመን ፥ በወጣው ፥ ነፍስ ።
አይዞሽ ፥ ነፍሴ / ደረሰልሽ ፥ ፃብሴ ።

(ሠ) ፥ ሆያሆዬ ፥ ቤት ።—ይኸውም ፥ ጉልማሶች ፥ በዘመን ፥ መለወጫ ፥ ሳይ ፥ የሚጫወቱት ፥ ነው ። ግጥሙ ፥ ከሰንጎ ፥ መገን ፥ ጋር ፥ አንዳንድ ፥ ጊዜ ፥ ይገጣጠማል ።

አጅ ፥—ለዝና ፥ ብሎ ፥ / የሰጠኝ ፥ ሙክት ፥
በለጭማ ፥ ነው ፥ / ባለምልክት ፥
መስክረም ፥ ጠባ ፥ / ያንን ፥ ሳነክት ፥

አበባዬ ፥ ሆይ ፥ የተባለው ፥ የሴቶች ፥ ልጆች ፥ ዘፈን ፥ ከዚሁ ፥ መደብ ፥ ነው ።

አጅ ፥—ከአበባ ፥ ጋር ፥ / ስጫወት ፥ ውዬ ፥
የማታ ፥ ማታ ፥ / ንፍሮ ፥ ቀቅዬ ፥
ሳቶ ፥ ባለቤት ፥ / ብላ ፥ ብለው ፥
ጉልቻ ፥ አንስቶ ፥ / ጉኔን ፥ አለው ፥
ባልንጀሮቼ ፥ / ቁሙ ፥ በተራ ፥
እንጨት ፥ ሰብሬ ፥ / ቤት ፥ እስትሠራ ፥
እንኳን ፥ ቤትና ፥ / የለኝም ፥ አዋር ፥
እንዲያው ፥ እድራለሁ ፥ / ከከብ ፥ ስቆጥር ።

(ረ) ፡ ቡሄ ፡ በሉ ፡ ቤት ። ይኸም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ለቡሄ ፡ የሚጫወቱት ፡ ነው ። የግ
ጥሙ ፡ ስንኝ ፡ አጫዋር ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሐረጉም ፡ ቤት ፡ እየመታ ፡ ይነገራል ፡

አድ ። ቡሄ ፡ በሉ ፡ / ልጆች ፡ ሁሉ ።
አንዳን ፡ አምጪው ፡ / አትሰውጪው ።
እዘያ ፡ ማዶ ፡ / ጭስ ፡ ይጨሳል ።
አጋፋሪ ፡ / ይደግማል ።
ያንን ፡ ድግስ ፡ / ውጪ ፡ ውጪ ።
በደንክ ፡ አልጋ / ተገልብጪ ።
ያች ፡ ድንክ ፡ / አመለኛ ።
አላንድ ፡ ሰው ፡ / አታስተኛ ።

(ሰ) ፡ የበገና ፡ ግጥም ።

አድ ። በስመ ፡ አብ ፡ / ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
አሐዱ ፡ አምላክ ፡ / ብቤ ፡ ሰላምታ ፡ ላድርስ ።
ለጊታዬ ፡ / ላንተ ፡ ለላይኛው ፡ ንጉሥ ።
እስክትጠራኝ ፡ / መጥቼ ፡ እስካይህ ፡ ድረስ ።

(ቀ) ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ቤት ። —ይኸውም ፡ አካሂዱ ፡ ግጥም ፡ ሲመስል ፡ ቤት ፡ የሚ
ያፈርስና ፡ የግጥሞችን ፡ ሕግ ፡ የማይጠብቅ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ግጥም ፡ ባዶር ፡
ዘመን ፡ በበላገሮች ፡ ዘንድ ፡ ይነገር ፡ ነበር ። በሁኑ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ መሰቂያ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ለሥራ ፡ አያገለግልም ። ቢሆንም ፡ ለዝክረ ፡ ነገር ፡ ጥቂቶችን ፡ እንጽፋለን ።

አድ ። አትለውሞይ ፡ / ማጅራን ፡ ማጅራን ፡
እንተ ፡ ምንቸገረህ ፡ / እሱን ፡ ታላመመው ።
የማነው ፡ በሬ ፡ / እግዚር ፡ የማረው ።
እቅብቅብ ፡ ጉብቶ ፡ / ይንፈገፋል ።
ከኔውም ፡ እንደሆን ፡ / ተውታቤዬ ።
ስማ ፡ ስይዘው ፡ / ይሸሻብኛል ።
ያውና ፡ እዘያ ፡ ማዶ ፡ / ቃሪያ ፡ በርበሬ ።
ባደረ ፡ እንጀራ ፡ / ቢክሽኩሽት ።
ገናብ ፡ ዘንበ ፡ ዘንበ ፡ / ደጁ ፡ ጭቃ ፡ ነው ።
ያን ፡ እያነሱ ፡ / እግድግዳ ፡ ልጥፍ ።
እንዲህ ፡ ብታየኝ ፡ / መስዬህ ፡ ድኃ ።
ያማቱቹ ፡ ቤት ፡ / ባለጉልላት ።
የጠጣ ፡ ጅራት ፡ / ከወደኋላዋ ።
ሐሰቴም ፡ እንደሁ ፡ / ዘረሀ ፡ እይብኝ ።
አፋፍ ፡ ሳፋፍ ፡ ልጄድ ፡ / ሕፕሁ ፡ ሚዳቋ ።
ጅራቷን ፡ ብይዘት ፡ / ዓይኗ ፡ ፍጥጥ ፡ አለ ።

— 343 —

ሰምና ፡ ወርቅ ። . . .

የአማርኛ ፡ መዝሙር ፡ አንደ ፡ ግዕዙ ፡ ቅኔ ፡ በሰምና ፡ በወርቅ ፡ በሳብርና ፡ በአን
ጸር ፡ . . . ይነገራል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የአማርኛ ፡ ቅኔ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። የየስ
ሞቹን ፡ ትርጓሜ ፡ በሚከተለው ፡ እናሳያለን ።

ሰም ፡ ግለት ፡ ለወርቁ ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ ሆኖ ፡ የሚነገር ፡ ቃል ፡ ነው ።
ወርቅ ፡ ግለታ ፡ ቅኔው ፡ የሚደርስለት ፡ ዋናው ፡ አሳብ ፡ ነው ።
ሰም ፡ ስበስ ፡ ግለት ፡ የቅኔው ፡ ዋና ፡ አሳብ ፡ (ወርቁ ፡) ሳይገለጽ ፡ ምሥጢሩ ፡
በለሙ ፡ ብጅ ፡ የሚታወቀው ፡ ነው ።
ወርቃ-ወርቅ ፡ ግለት ፡ ቅኔው ፡ ያለምንም ፡ ምሳሌ ፡ በግልጽ ፡ የሚነገር ፡ ነው ።
ጎብር ፡ የሚባለው ፡ አንዱ ፡ ቃል ፡ ሰሙንም ፡ ወርቁንም ፡ የሚያስተባብር ፡
ሲሆን ፡ ነው ።
አንጻር ፡ የሚባለው ፡ ለምሥጢሩ ፡ ተንዳዳሪ ፡ የሚሆን ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ የሚጠቀስለ
ትና ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ የሚነገርለት ፡ ነው ።
አፍራሽ ፡ የሚባለው ፡ አስቀድሞ ፡ የተነገረውን ፡ አሳብ ፡ ተክታዩ ፡ የሚለው
ጠው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።
ውስጠ-ወይራ ፡ የሚባለው ፡ ኃይለ ፡ ቃሉ ፡ በሰሙ ፡ ተሰውሮ ፡ ለሕሊና ፡ የሚ
ሰማ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

የቅኔ ፡ መንገድ ፡ ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልቶች ፡ አሉት ። ጸሩ ፡ ግን ፡ ውሳ
ኔን ፡ ግብዛት ፡ ተማሪን ፡ ማታከት ፡ ይሆናልና ፡ እነዚሁ ፡ ይበቃሉ ፡ ብለን ፡ እናቆማለን ።
እነርሱም ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እየተዘመዱ ፡ ሲገቡ ፡ ይገኛሉ ። ይልቁንም ፡ ሳብርና ፡
ውስጠ-ወይራ ፡ ከሁሉ ፡ ይገኛሉ ።

እነሆ ፡ ሁሉንም ፡ በሚከተሉት ፡ ማስረጃዎች ፡ እናሳያለን ።

1— ሰምና ፡ ወርቅ ፡ የአማርኛ ፡ ቅኔ ።

(ሀ) ወላድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ / ለልጆቿ ፡ ብላ ፡
እጅግ ፡ ሳይጥሩባት ፡ / ሳይዘሩዋት ፡ አብቅላ ፡
ስንዴውን ፡ ጠብቃ ፡ / እንክርዳዱን ፡ ነቅላ ፡
ስትመግበን ፡ እየን ፡ / በፀሐይ ፡ አብስላ ።
ምሳሌ ፡ ዘር ፡ ሀገራችን ፡
ንጹሕ ፡ ዝናም ፡ መንግሥታችን ፡ } አዝማች ፡)

የናኮሌ ፡ ንጉሤ ።

(ለ) ልጅነት ፡ የያዘው ፡ / ምላሳችን ፡ መንካ ፡
ከቋንቋችን ፡ በፊት ፡ / ሌላ ፡ ቋንቋ ፡ አይንክ ፡
ግእዝ ፡ ከማርኛ ፡ / አስተባብሮ ፡ ሲያውቅ ፡
ከውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ / ያንጊዜ ፡ ይንጠቅ ።

እ ፡ ኪሳኑ ፡ መልድ ፡ ከፍሌ ።

2—ሰም ፡ ለበስ ፡ የአማርኛ ፡ ቅኔ ፡

(ሀ) ሰፈድና ፡ ወንፈት ፡ / እያለ ፡ በጃችን ፡
ያልተነፋ ፡ ዳቂት ፡ / ምነው ፡ ማዙክታችን ።

ኣ ፡ ኪሳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ።

(ለ) ያ ፡ ማዶ ፡ ተራራ ፡ / ረጅም ፡ ነው ፡ በጣም ፡
በከብት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ / በአግር ፡ አያስወጣም ፡
ያ ፡ ልጅ ፡ ተራራውን ፡ / ሊወጣ ፡ ያስባል ፡
ሀሞቂ ፡ ሲያቅተው ፡ / ድኾ ፡ እንዴት ፡ ይዘልቃል ።

ግዛተመ ፡ ወርቅ ፡ እሸቴ ።

3—ሰም ፡ ለበስ ፡ ውስጠ — ወይራ ፡ የአማርኛ ፡ ቅኔ ።

(ሀ) ተሰቦ ፡ ገብቷል / ከቤታችን ፡
መቹ ፡ ይወጣል ፡ / በሽታችን ።

የፍታሔ ፡ ንጉሤ ፡ (ጀደጀር ፡ ኅ ፡ ም ።)

(ለ) እምቢልታ ፡ መለከት ፡ / የሚሰማው ፡ የት ፡ ነው ፡
አንዱም ፡ በስርቆሽ ፡ በር ፡ / አንዱም ፡ በግቢ ፡ ነው ።

ግዛተመ ፡ ወርቅ ፡ እሸቴ ፡ (ጀደጀጀ ፡ ኅ ፡ ም ።)

(ሐ) ሰንበቴያችን ፡ ደርሶ ፡ / ድግስ ፡ አለብን ፡ } (ጥያቄ 1)
እንድትረጂን ፡ ይሁን ፡ / እሀል ፡ ቅመሙን ፡ }
እሺ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡ / ያለኝ ፡ ጉልበቱን ፡ }
ለምለም ፡ ወጥቤታችን ፡ / ታውቃለች ፡ ምጥን ፡ } (ምላሽ ፤)
እኛ ፡ ነጭ ፡ አዝሙዱን ፡ / እንችላለን ፡ }
አንተ ፡ ጥቁር ፡ ቅመም ፡ / አበሱዳን ፡ ሁን ።

የፍታሔ ፡ ንጉሤ ፡ (ጀደጀሸ ፡ ኅ ፡ ም ።)

4—ወርቃ—ወርቅ ፡ የአማርኛ ፡ ቅኔ ።

(ሀ) አጥንቱን ፡ ልልቀመው ፡ / መቃብር ፡ ቆፍሬ ፡
ጎበናን ፡ ከሸዋ ፡ / አሉላን ፡ ኮትግሬ ፡
ስመኝ ፡ አድሬአለሁ ፡ / ትናንትና ፡ ዛሬ ፤
አሉላን ፡ ለጥይት ፡ / ጎበናን ፡ ለጭሬ ፡
ተሰበሰቡና ፡ / ተማማሉ ፡ ማላ ፡
አሉላ ፡ ተትግሬ ፡ / ጎበና ፡ ተጋላ ።
ጎበና ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ / ሊያስተምር ፡ ፈረስ ፡
አሉላ ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ / ጥይት ፡ ሊያስተኩስ ።
አገሬ ፡ ተባብሬ ፡ / ከልረገጠች ፡ እርከብ ፡
ንገረኝ ፡ ሁሉ ፡ / የእንባይ ፡ ከብ ፡ የእንቢይ ፡ ካብ ።

ትምህርት ፡ እንዲሰፋ ፡ / ጉልበት ፡ እንዲጠና ፡
አራቱ ፡ ጉበኤ ፡ / ይነሡልንና ፡
መኰንን ፡ ደረሰ ፡ / አሉላ ፡ ጎበና ፡
አገራችን ፡ ትማር ፡ / አሁን ፡ እንደገና ፡
ጎበና ፡ ከፈረስህ ፡ ጋራ ፡ ተንሥ ፡ እንደገና ፡ (አገማች ፡ ፡)

ኮኖታሔ ፡ ንጉሤ ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ኅ ፡ ም ።

የመገጸ ፡ ጉበዝ ፡ በመር ፡ ተማሬ ፡ ቤቱ ፡ በአደጸጸይ ፡ ጎራረት ፡ የሚገጥመው ፡ ወርቅ ፡ ወርቅ ፡ ግጥም ።

(ለ) ውረድ ፡ እንውረድ ፡ / ተብሰሉና ፡
አስደበደብት ፡ / አፋፍ ፡ ቆሙና ፡
የዋኛ ፡ ሣሩ ፡ / መምሬ ፡ ማምሽ ፡
ወዲህ ፡ በዳዊት / ወዲህ ፡ በጋሽ ፡
ፈሬ ፡ ፊሬና ፡ / አጉድባ ፡ ቢኖ ፡
ጀሮውን ፡ በላው ፡ / ያይጥ ፡ ቀበኛ ፡
ቂጡን ፡ ደግመው ፡ / የአበጥ ፡ ሽረኛ ፡

(ሐ) በስም ፡ ብቻ ፡ መክበር ፡ / ሥራውን ፡ ሰይሠሩ ፡
የግብጦች ፡ ዱለት ፡ ነው ፡ / መቼ ፡ የማኅበሩ ።
በሀገራችንም ፡ / ጉበሬድና ፡ እጨጌ ፡
የጳጳሳት ፡ ስም ፡ ነው / መቼ ፡ የበለጌ ፡
ነፃነት ፡ ከሌላት / ከሀነት ፡ በሀገሯ ፡
ፍጹም ፡ አይበልም ፡ የነፃነት ፡ ክብሯ ።
ንጉሥ ፡ ሳይኖራቸው ፡ / ሸርያና ፡ አርመን ፡
መርጠው ፡ ይሾማሉ ፡ / በትረከና ፡ አቡን ፡
ከወጉ ፡ መርጠ ፡ / ጳጳስ ፡ የማይሾም ፡
ከሀቢያችን ፡ በቀር ፡ / ሴላ ፡ ሕዝብ ፡ የለም ፡

ኣ ፡ ኪሳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ።

5—ጎብር ፡ የአማርኛ ፡ ቅኔ ፡

(ሀ) አሁን ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፡ / ሱሰኛ ፡ መሆን ፡
ብዙ ፡ ቤት ፡ ፈረሰ ፡ / ትናንት ፡ በዚያ ፡ ቡን ፡

ግዛተመ ፡ ወርቅ ፡ እሸቴ ፡ (ጀደጀጀ ፡ ኅ ፡ ም ።)

(ለ) ቍርሰችን ፡ እንጦጦ ፡ / ምሰችን ፡ ወሰይ ፡
ሽይ ፡ ግብዣችን ፡ ዳሞት ፡ / ቡሬ ፡ አደባባይ ፡
ራታችን ፡ ጎንደር ፡ / አጣጣሚ ፡ ላይ ፡
አቶሞቢላችን ፡ / ላንቾይደለሞይ ፡

የፍታሔ ፡ ንጉሤ ፡ (ጀደጀሸ ፡ ኅ ፡ ም ።)

(ሐ) እግረኛ ፡ እንዳይሆን ፡ / ይሽ ፡ ሙ ፡ ጋዲን ፡
ጊዜው ፡ ሳያልፍበት ፡ / በደጉ ፡ ዘመን ፡
ዘሕግ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ / ምነው ፡ ቢወሰን ፡

ደራሲው ፡ መ ፡ ነ ፡ መ ፡ ቂ ፡ (፲፱፻፷፱ ፡ ኅ ፡ ም ፡)

6—አንጸር ፡ የአግርኛ ፡ ቅኔ ፡

(ሀ) ወላጅ ፡ ማለት ፡ አብሮ ፡ / ሲባክን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
እንደ ፡ ዓይን ፡ እንደ ፡ ጆሮ ፡ / እንደ ፡ እግር ፡ እንደ ፡ እጅ ።

(ለ) የኔንም ፡ ጎጆ ፡ ቆጠሩሽ ።
እንደ ፡ ሰው ፡ አላራሽ ።

7— እፍራሽ ፡ የአግርኛ ፡ ቅኔ ፡

(ሀ) ማለዳጣ ፡ ታውቃለህ ።
አትሰቀም ፡ እንጂ ፡ ከጠላህ ።

ግጥሙ ፡ ወርቅ ፡ እሸቱ ።

(ለ) እምዬ ፡ ምኒልክ ፡ / በቅሎ ፡ ስጠኝ ፡ ብዬ ፡ / እኔ ፡ አልለምንህም ።
ክባ ፡ ስጠኝ ፡ ብዬ ፡ / እኔ ፡ አልለምንህም ።
ብርም ፡ ስጠኝ ፡ ብዬ ፡ / እኔ ፡ አልለምንህም ።
እምና ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ / ዘንድሮ ፡ የለህም ።

ይህ ፡ ግጥም ፡ የተገጠመው ፡ የአጼ ፡ ምኒልክ ፡ መሞት ፡ ተደብቆ ፡ ሳለ ፡ ፲፱፻፲፮ ፡ ኅ ፡ ም ፡ ነው ።

8—ሙስጠ-ወይራ ፡ የአግርኛ ፡ ቅኔ ፡

(ሀ) ግሽላና ፡ ስንዴ ፡ / ባንድ ፡ አብረን ፡ ስንቆላ ፡
እያረረ ፡ ሳቀ ፡ / የባሕር ፡ ግሽላ ።
ከሰል ፡ የሚሆኑ ፡ ብዙ ፡ እንጨቶች ፡ ሰሉ ።
ዝግባ ፡ ለምን ፡ ይሆን ፡ ይቂረጥ ፡ የሚሉ ።

ዮፍታሔ ፡ ንጉሤ ፡ (፲፱፻፸፱ ፡ ኅ ፡ ም ፡)

(ለ) አብርሃም ፡ ቢጣላ ፡ / ከሣራ ፡ ከሚስቱ ።
ባሪያውን ፡ አጋርን ፡ / አስወጣት ፡ ከቤቱ ።
በዚህም ፡ ተጣልተው ፡ / ወጡ ፡ እደብይ ።
ሳኖውም ፡ ፈረደ ፡ / በሁለቱም ፡ ላይ ።
እንተም ፡ ሠርተህ ፡ ብላ ፡ / እንቺም ፡ ሠርተሽ ፡ ብዪ ።
አላጋር ፡ እንጀራ ፡ / አይበላም ፡ ወይ ።

ወልደ ፡ ጽጥ ፡ ጋሽ ፡ (፲፱፻፷ ፡ ኅ ፡ ም ፡)

— 344 —

የአግርኛ ፡ ቅኔ ።

የአግርኛ ፡ ግጥም ፡ ወይም ፡ መገሙር ፡ «የአግርኛ ፡ ቅኔ ፡» እንደሚባል ፡ ባለፈው ፡ አስታውቀናል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ከጎበዜ ፡ ቃና ፡ እስከ ፡ መወድስ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዕጣን ፡ ሞገር ፡ ባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ሁሉ ፡ እየገባ ፡ ሲነገር ፡ የአግርኛ ፡ ቅኔ ፡ ይባላል ። እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግዕዙን ፡ ጣልቃ ፡ እያስገባ ፡ በመተባበርና ፡ በመተሳሰር ፡ ሲነገር ፡ ይታያል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ከጋልኛና ፡ ከሴላም ፡ ቋንቋ ፡ ጋር ፡ እየተሰባጠረ ፡ ይነገራል ። እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ ጥቂቶቹን ፡ እናሳያለን ።

የአግርኛ ፡ ጉባኤ ፡ ቃና ። (ምሥጢሩ ፡ አፐፈ ፡ ሳስ ፡ ያሳወፈ ፡ አይጉላ ፡ ማስት ፡ ነው ።)

ልጆች ፡ ተማሩ ፡ / የፍርድን ፡ ሥራ ፡ ቀጥታ ፡
አይጥ ፡ በበላ ፡ ስንዴን ፡ / አምጣኑ ፡ ዳዋ ፡ ተመታ ።

የአግርኛ ፡ ዋዜማ ። (ምሥጢሩ ፡ መወጥ ፡ ማብዛትን ፡ ጸለ ፡ መንቀፍ ፡ ነው ።)

(ሀ) ቆመ ፡ የለኳር ፡ ጠጅ ፡ /
ሙስተ ፡ ይብረ ፡ ማሕው ፡ ልብነ ፡ / ሀገረ ፡ ሥቃይ ፡ ወተድላ ፤
ወወይይነ ፡ በበተራሆሙ ፡ አረቄ ፡ መጠላ ፡
ወበውስተ ፡ ቤርሜል ፡ ልብነ ፡ / ምስትግቡአ ፡ በቀል ፡ አተላ ፤
እሳተ ፡ አራዳ ፡ ኰኽነ ፡ / አሲው ፡ ተቃጥላ ፤
አውዐየቃ ፡ ሰባቢሶን ፡ ገላ ።

ዮፍታሔ ፡ ንጉሤ ፡ (፲፱፻፸፩ ፡ ኅ ፡ ም ።

(ለ) ጭንየበር ፡ ደብተራ ፡ ስንጉሥ ፡ ግሀለ ፡ ሥላሴ ፡ የተቀኘው ፡ (በ፲፰፻፫ ፡ ኅ ፡ ም ፡ ያህል ።)

ግሩም ፡ እምግሩማን ፡ /
ግሀለ ፡ ሥላሴ ፡ ያዕቆብ ፡ / እንተ ፡ ጸኅከ ፡ ልዕልና ፤
ወዙኀረየከ ፡ መለከት ፡ ፍና ፤
እስመ ፡ አበ ፡ ዲና ፡ ለሊከ ፡ / ወፈረሰ ፡ ዘአከ ፡ ዲና ፤
በዲና ፡ ተጎጉሉ ፡ / ዘይቤሉ ፡ ዲና ፤
ወኢተርፈ ፡ አሐዱ ፡ ለዘና ።

የአግርኛ ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ።

(ሀ) የሥንኡስ ፡ ደብተራ ፡ ብርሌ ፡ ለጸሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ንዘረ ፡ ሥላሴ ፡ የሰጡት ፡ ቅኔ ።

ዐምደ ፡ ቤት ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ / ቅንቅን ፡ ሲበላህ ፡ የምትኖረው ፡
አሰናብተኝና ፡ ልውረድ ፡ ጌታዬ ፡ / አድናለሁና ፡ ብሔር ፤
ደግሞ ፡ ቆቅ ፡ (ቆቃ) አለ ፡ አሉ ፡ / የሚያዝ ፡ ሲበር ፤

አንድም ፡ ነት ፡ አጥቺ ፡ ክንተ ፡ ቤት ፡ / እንዲት ፡ ወድቂ ፡ ልቅር ፤
ከባዶ ፡ መሬት ፡ ስቆረቆር ፤
ወእር ፡ ኢታገብዕ ፡ ሲተ ፡ / ለምድረ ፡ ጎንደር ፤
ማጎፀንተ ፡ ልቡናከ ፡ ምድር ።

(ለ) የአንየበር ፡ ደብተራ ፡ ለወሀኒ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ በጋልኛ ፡ የተቀኘው ፡ (ዘሙት ፡ ፲፱፻፲፭ ፡ ኅ ፡ ም ፡ ፡ ያህል ፡ ይመስላል ።)

ናገርሲሲ ፡ ከራ ፡ ሐዘሎ ፡ / ሚኝ ፡ ምኒልክ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
አኒ ፡ ቤኬ ፡ ኢንጅሩ ፡ ጎፍታከ ፡ / ከራ ፡ ሐዘሎ ፡ ሁንዱማ ፤
ጹቢን ፡ ኬቲ ፡ ጻጺ ፡ / አፋን ፡ ኬቲ ፡ ደማ ፤
ሴንጂ ፡ ጎፍታከ ፡ / አርከ ፡ ምኒልክ ፡ ይልማ ፤
ወረሞ ፡ አበ·ልቲ ፡ ምስለ ፡ ሲጻማ ፤
ዒኝ ፡ ጎፍታ ፡ ኬኖ ፡ ሁኖቲ ፡ / ቢፍቱ ፡ ዲረማ ፤
አፅይንተ ፡ ይሰብር ፡ በግርማ ።

የአማርኛ ፡ መዝገስ ፡

(መ) ተንሰኤ ፡ በው ፡ የተቀኘው ።

እግዚአብሔር ፡ አንተን ፡ በመበይል ፡ ጊዜ ፡ /
የሚያህለኝ ፡ የለም ፡ እኔን ፡ / ከፈጠርኸው ፡ ሁሉ ፡ ፍጡር ፤
እመስላለሁና ፡ መቼም ፡ / ይሁዳን ፡ ወንድሜን ፡ በግብር ፡
ምንም ፡ ብበልጠው ፡ በዋበብ ፡ በኩር ፡
ከባቲ ፡ ከነዊ ፡ ጋር ፡
የተከከልሁ ፡ ነኝ ፡ እኔም ፡ / ወርቅና ፡ ብርን ፡ በማፍቀር ፡
እንብላ ፡ እንብላ ፡ ሲሉ ፡ ሰዎች ፡ / ሥጋ ፡ መልከኛው ፡ ቢቀር ፡
ቆርጠው ፡ የሄዱ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ / እኔን ፡ ጨልሞኝ ፡ ስድበረበር ፡
ከነጋም ፡ ወዲያ ፡ እንዳልሄድ ፡ / እኒያ ፡ በሄዱበት ፡ አገር ፡
ይጠብቀኛል ፡ በኋሰዬ ፡ / የሁሉ ፡ ጠላት ፡ መቃብር ።

(ለ) አቶ ። ሮፍታሉ ፡ ንኑሜ ፡ በ፲፱፻፴፩ ፡ ኅ ፡ ም ፡ በካርቱም ፡ ሳሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ በጂኔቦ ፡ ላይ ፡ ቀርቦ ፡ ንገ ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ እየተባለ ፡ በመዘገየቱ ፡ እያዘኑ ፡ የዘረፉት ፡ መወድዘ ። ምሥጢሩ ፡ እጪ ፡ ነገ ፡ ወደ ፡ ጀኔቫ ፡ ሂዳ ፡ አራይትንና ፡ ቱሞርን ፡ አፍተር ፡ ቱሞርን» ፡ ወለደች ፡ ማለት ፡ ነው ። (አራይት ፡=እሺ ፡ ቱሞር ፡=ነገ ፡ አፍተር ፡ ቱሞር ፡=ተነገ ፡ ወዲያ ።)

ምንተ ፡ ንግበር ፡ የዐመፅ ፡ ልጆች ፡ /
ለእመ ፡ ዐረፍት ፡ ይእቲ ፡ / ቃለ ፡ አፉነ ፡ ወስላታ ፡
ወተድባበ ፡ ብሩር ፡ ልብነ ፡ / ስታ·ሣው·ተን ፡ ጨዋታ ፡
ንግበር ፡ ማለያሃ ፡ / ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ ወቃለ ፡ ሐሰት ፡ ወአከ ፡ ባሕቲታ ፡
ወዳያና ፡ ወዳህም ፡ ሰትንገላታ ፡
በየበራችን ፡ ለትቁም ፡ / የዝግበ ፡ ማንታ ፡ ይሉንታ ፡
በጀኔቭሂ ፡ አመ ፡ ተፀንሰ ፡ / ዘኢትዮጵያ ፡ አለኝታ ፡
የቱሞር ፡ እናት ፡ እሺ ፡ ነገ ፡ / ለብሂለ ፡ አራይት ፡ ወለደታ ፡
ወእሺ ፡ ነገ ፡ እኅትነ ፡ / እምድኅረ ፡ ወለደት ፡ መንታ ፡
ሕማማ ፡ ኢትዘክር ፡ / ወእፍተር ፡ ቱሞር ፡ ተቀበለታ ፡

— 345 —

ምሳሌ ፡ (ተረት ፡)

በአማርኛ ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ ከአበው ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ ብዙ ፡ የምሳሌ ፡ ንግግር ፡ አለ ። ሽማግሌዎቻችን ፡ "እከሥት ፡ በምሳሌ ፡ አፉዋ" ያለውን ፡ ሲገልጡ ፡ ነገር ፡ በምሳሌ ፡ ጠጅ ፡ በብርሌ ፡ ብለው ፡ ይተርታሉ ። በግብሩ ፡ ምሳሌ ፡ ይበላል ፤ በጥንታዊነቱም ፡ ተረት ፡ ይበላል ። በእርሱም ፡ ሕግና ፡ ምክር ፡ ሴላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት፡ ትምህርት ፡ ይገኝበታል ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በዳሮ ፡ ዘመን ፡ ጨዋው ፡ ሲተችና ፡ ሲፈርድ ፡ ለነገሩ ፡ የሚስማማውን ፡ አንዳንድ ፡ ምሳሌ ፡ እየጨመረ ፡ ይናገር ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ አንቀጽ ፡ ጠቅሶ ፡ እንደ ፡ መፍረድ ፡ መሆኑ ፡ ይመስላል ።

ለፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሲጠቀሱ ፡ ከነበሩት ፡ ምሳሌዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ ከፍርድ ፡ መጻሕፍት ፡ ጋር ፡ በም/ ር ፡ የተዛመዱና ፡ የተስማሙ ፡ ናቸው ። እነሆ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ከሚጠቀሱት ፡ ምሳሌዎች ፡ ጥቂቶቹን ፡ በሚከተለው ፡ ጽፈን ፡ እናሳያለን ።

ምሳሌ ፡ (ተረት)	ጥቅስ ፤
፩ — ሺ ፡ በመከር ፡ አንድ ፡ በወረመር ፤	
፪ — ከያያዝ ፡ ይቀደዳል ፤ ከነጋገር ፡ ይፈረዳል ፤	
፫ — ባንድ ፡ ራስ ፡ ሁለት ፡ መላስ፤	
፬ — በፍ ፡ ይጠፉ ፡ በለፈለፉ ፤	
፭ — ሳይገድሉ ፡ ጎለሬ ፡ ሳያስረግጡ ፡ ወሬ ፤	
፮ — ዓሣ ፡ ግርጎሪ ፡ ዘንዶ ፡ ያወጣል ፤ የሰው ፡ ፈላጊ ፡ የራሱን ፡ ያጣል ፤	
፯ — ለወሬ ፤ የለሙ ፡ ፍሬ ፤ ላበባ ፡ የለው ፡ ገለባ ፤	
፰ — ደባ ፡ ፊሱን ፤ ስለት ፡ ድጉሱን ፤	
፱— ተልጅ ፡ እትጫወት ፤ ይወጋሃል ፡ በንጨት ፤	
፲ — ተዋጊ ፡ በሬሀን ፡ ተናከሽ ፡ ውሳሀን ፡ (ያዝ)	
፲፩— አንድ ፡ እያነድ ፡ አንድ ፡ አይፈርድ ፤	
፲፪— በፈሳ ፡ ይታፈሳል ፡ በነበር ፡ ይመለሳል ፤	
፲፫— የለበት ፡ ዕዳ ፡ ለልጅ ፡ የአፍንጫ ፡ እድፍ ፡ ለእጅ ፡ (ቢወርስ ፡ ነው ፡)	
፲፬— ከኑግ ፡ የተገኘህ ፡ ሰሊጥ ፡ አብረሀ ፡ ተወቀጥ ፤	
፲፭— የሌባ ፡ ዋሽ ፤ የቀማኛ ፡ መሸሻ ፤	

፲፯ — የሰው ፡ በልቶ ፡ አያጅፍም ፡ ተኝቶ ፡
፲፰ — እንደ ፡ ልጅ ፡ በቀለበት ፡ እንደ ፡ ድመት ፡ በወተት ፡
፲፱ — እከስ ፡ ያለ ፡ ታግሦ ፡ አጸድቅ ፡ ያለ ፡ መንኩሰ ፡
፳ — ዳኛ ፡ ይመረምራል ፤ ጣዝማ ፡ ያሠረጽራል ፡
፳፩ — ተመመርመር ፡ ይገኛል ፡ ነገር ፡
፳፪ — ብአፍ ፡ ከወጣ ፡ አፋፍ ፡
፳፫ — ውሻ ፡ በበላበት ፡ ይጮኻል ፡
፳፬ — ዋቢ ፡ ያለው ፡ ያመልጣል ፤ ዋቢ ፡ የሌለው ፡ ይሰምጣል ፡
፳፭ — የግፍ ፡ ግፍ ፡ በፅንቅርት ፡ ላይ ፡ ጀር ፡ ደግፍ ፡
፳፮ — ሥራ ፡ ለሠረው ፡ እጅህ ፡ ላጣረው ፡
፳፯ — ከተዘጋ ፡ ቤቱ ፡ ከተዳለን ፡ እሳቱ ፡
፳፰ — ለንጉሥ ፡ ያልረዳ ፡ ከቤሕር ፡ ያልቀዳ ፡
፳፱ — አያገባው ፡ ገብቶ ፡ አያወጣው ፡ ተቀብቶ ፡
፴ — አልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይ ፡
፴፩ — የሞተ ፡ አይከሰስ ፡ የፈሰሰ ፡ አይታፈስ ፡
፴፪ — የበላ ፡ ዳኛ ፡ የወጋ ፡ መጋኛ ፡
፴፫ — ያልጠረጠረ ፡ ተመነጠረ ፡
፴፫ — አለውድ ፡ በግድ ፡
፴፬ — ንጉሥ ፡ አይከሰስ ፡ ሰግይ ፡ አይታረስ ፡

—346—

ስለ ፡ ጽሕፈት ፡

ቃል ፡ በብራና ፡ ወይም ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ በተለም ፡ ተቀርጸ ፡ ትምህርት ፡ የሚ ተሳለፍበት ፡ እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ከሩቅ ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ በሩቅ ፡ ሆኖ ፡ አሳብን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻልበት ፡ ብልሃት ፡ "ጽሕፈት" ይባላል ። ስለዚህም ፡ "በታል ፡ ያለ ፡ ይረሳል ፡ በመጽ ሐፍ ፡ ያለ ፡ ይወረሰል ፡" ተብሎ ፡ ይተረታል ።

ለጽሕፈት ፡ መልክትና ፡ ሥርዓቶች ፡ አሉት ። እንድ ፡ ዓይነት ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ ሕሳብ ፡ በጽሕፈት ፡ ተሰናድቶ ፡ ሲመጣ ፡ "መጽሐፍ" ይባላል ። ለሰላምታ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ጉዳይ ፡ የሚጻፈው ፡ የመልእክት ፡ ቃል ፡ "ደብዳቤ" ይባላል ። መጽሐፍ ፡ በጥራዝ ፡ ይከፈ ላል ። ጥራዝ ፡ በቅጠሎች ፡ ይመደባል ። የቅጠሎች ፡ ብዛት ፡ በጸሐፈው ፡ ፈቃድ ፡ ይወ ሰናል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሽ ፡ ጥራዝ ፡ አምስት ፡ ቅጠሎች ፡ ይገኙበታል ። አንድ ፡ ብራና ፡ ወይም ፡ ወረቀት ፡ ለተፈለገው ፡ ጉዳይ ፡ በልክ ፡ በመጠን ፡ ሆኖ ፡ ሲቀጸ ፡ "ቅጽ" ወይም ፡ "ቅጠል" ይባላል ። ወረቀት ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ "ሉህ" የሚባል ፡ የትውስት ፡ ስም ፡ ተገኝቶለታል ። አንዱ ፡ ቅጠል ፡ ወይም ፡ ቅጽ ፡ ታጥፎ ፡ ሲጠረዝ ፡ በጥራዝ ፡ የተከፈለውን ፡ እኩሌታ

ውን ፡ "ነጠላ ፡ ቅጠል ፡" ማለት ፡ በተገባ ፡ ነበር ፡ ጻፉ ፡ ግን ፡ መታጠፉ ፡ ከቅጽ ፡ ተቆጥሮ በት ፡ እርሱም ፡ እንደዚያው ፡ "ቅጠል ፡" ይባላል ።

የቅጠል ፡ አንደኛው ፡ ፊቱ ፡ "ገጽ ፡" ይባላል ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ቅጠል ፡ በጥራዝ ፡ ደንብ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ሁለት ፡ ገጾች ፡ አሉት ። በቅጽ ፡ ደንብ ፡ ሲታሰብም ፡ አራት ፡ ገጾች ፡ ይኖሩለታል ።

ቀለም ፡ የሚወድቅበት ፡ ሚዳው ፡ (መለሱ ፡) ከጽሕፈት ፡ በፊት ፡ ተዳምሞ ፡ ተፅ ምሮ ፡ ሲሰናዳ ፡ ሰሌዳ ፡ ይባላል ።

ቀለም ፡ ከሚያርፍበት ፡ ከሰሌዳው ፡ በስተራቂኔና ፡ በስተግርጌ ፡ በጉንና ፡ በጉን ፡ የሚገኘው ፡ ባዶው ፡ ስፍራ ፡ በጠቅላላ ፡ "ጎዳኅ ፡" ይባላል ። ትርጓሜው ፡ የጽሑፍ ፡ ግለት ፡ ነው ። በዝርዝር ፡ ሲነገርም ፡ የላይኛው ፡ "እርእስት ፡ ጎዳኅ ፡" የታችኛው ፡ "ግልየት ፡ ጎዳኅ ፡" ወይም ፡ "ጎዳኅ ፡" ብቻ ፡ በመገልበጫው ፡ በኩል ፡ የሚገኘው ፡ "ገጽ ፡ ጎዳኅ" ፡ በመጠረጊው ፡ በኩል ፡ የሚገኘው ፡ "ምስጣክ ፡ ጎዳኅ" ይባላል ።

በመቅድመ ፡ መንጌል ፡ የሚነገርው ፡ ውጣኔ ፡ ከጸሀይ ፡ ዝናት ፡ ውሳኔ ፡ ተፍጥ ፡ የተሰየ ፡ ነው ። ጎግልየት ፡ ጎ ዳኅ ። ለውለም ፡ እየተጸመ ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ ይሰየራል ፤ ታችኛው ፡ ጎግልየት ፡ ጎዳኅ ፤ ላይኛው ፡ ገጽ ፡ እርእስት ፡ ግል የት ፡ ጎዳኅ ፤ ጸርና ፡ ላሩ ፡ ምስጣክ ፡ ጎልየት ፡ ጎዳኅ ፡ ተባሏል ።

ቀለም ፡ የሚውልበት ፡ ስፍራ ፡ ዐምድ ፡ ይባላል ። መጽሐፍ ፡ ወይም ፡ ጋዜጣ ፡ በሽ ፡ ዐምድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ዐምዶች ፡ እየተጻፈ ፡ ይወጣል ። በዐምድና ፡ በዐምድ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ድምበር ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ ስፍራ ፡ "ሐሙልት" ፡ ይባላል ።

ለጽሕፈት ፡ መግቻ ፡ ወይም ፡ መወሰኛ ፡ የሚደረገው ፡ የመስመር ፡ ምልክት ፡ "ሲራክ" ፡ ይባላል ። ቃሉ ፡ በቀለም ፡ ተቀርጸ ፡ የሚያርፍበት ፡ "መስመር" ፡ ይባላል ። በፊደልና ፡ በፊ ደል ፡ መከከል ፡ የሚገኘው ፡ ስፍራ ፡ "ኖኅት" ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ "ኖኅት" ፡ በእሁኑ ፡ ዘመን ፡ አስፓስ ፡ እየተባለ ፡ በማተሚያ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ዘንድ ፡ በተውሶ ፡ ስም ፡ የሚ ጠራው ፡ ነው ። በያንዳንዱ ፡ ፊደል ፡ መከከል ፡ የሚገኘው ፡ ስፍራ ፡ "ሕፅን" ፡ ይባላል ። ለምሳሌ ፡ "ሐጠበ" ፡ በተባሉት ፡ ፊደሎች ፡ መከከል ፡ የሚታዩት ፡ ክፍቶቹ ፡ ስፍራዎች ፡ ሕፅኖች ፡ ናቸው ። በያንዳንዱ ፡ ፊደል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ስፍራ ፡ (በቅርጽ ፡ የተከበበ ፡ ሲሆን ፡) "ማሕፀን" ይባላል ። ለምሳሌ ፡ "መ ቀ ፀ" ፡ በተባሉት ፡ ፊደሎች ፡ ውስጥ ፡ የሚ ታዩት ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ የመሰሰሉት ፡ ኮሮጮች ፡ ስፍራዎች ፡ ማሕፀኖች ፡ ናቸው ።

መጽሐፍ ፡ "በአንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ በክፍል ፡ በቁጥር" ይከፈላል ። አንቀጽ ፡ ከፍተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ መከከለኛ ፡ ክፍል ፡ አነስተኛ ፡ መከፈያ ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ መክፈያዎች ፡ ንኡስ ፡ ምዕራፍ ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ እየተባሉ ፡ እንደኛና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አካሄድ ፡ ይደነገጋሉ ። ቁጥር ፡ ከእንቀጽ ፡ ወይም ፡ ከምዕራፍ ፡ ወይም ፡ ከክፍል ፡ እየ ተነሣ ፡ ዝርዝር ፡ ከፋይ ፡ ይሆናል ። በእንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ይልቁንም ፡ በፍርድ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ላፍ ፡ የሚዘረው ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ "አንቀጽ" ይባላል ። በመቅድመ ፡ መንጌል ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ ንኡስ ፡ ምዕራፍ ፡ አርእስተ ፡ ንባር ፡ ተብሏል ።

ሰዋስው ፡ ተፈጸመ ።